« ገጠር አልሽ ልጄ ፤ የገጠሩ ባለቤት ቢፈቅድልሽ አይደል ፣ ለጉልበቱማ ሠርቶ መብላቱን የሚጠላ ማን አለ ? »

ድንገት ከፊት ለፊታቸው ፣ ሩቅ ከማይባል ስፍራ የሆነ ነገር ዓይናቸውን ሰረቀው ። ከሲታው ሰውነታቸው መዝለፍለፍ የጀመረ እጃቸውን መሸከም አቃተው ። ግርግር ይታያል ፤ ሰዎች ይተራመሳሉ ።

« ነይ እስቲ እንሂድ ። ዛሬ ደግሞ ምን ተፈጠረ ? ወደፖሊስ ጣቢያ እንዳይሆን የሚሄዱት . . . » አሉና ፍጥነት ጨመሩ ። ጎስቋላ ቤቶችን አልፈው ዙርያውን በግንብ የታጠረ ፣ መሀሉ ላይ ሰንደቅ ዓላማ የሚውለበለብበት ግቢ ሲደርሱ ካዩት ትርምስ ጋር ተገጣጠሙ ። አንድ ሰውነቱ ሁሉ ደም የለበሰ ሰው ፖሊሶች ወደ ጣቢያ ያዳፉታል ። ልጅቷ « ምን ሊያደርጉት ነው ? . . . » ስትል ጠየቀች ድንጋጤና ፍርሃት እየናጣት ።

« እኔ ምን አውቃለሁ ብለሽ ነው » ሲሉ እራሳቸውን በመነቅነቅ መለሱላት ። ቢሆንም ሁኔታው ከቁጥጥራቸው ውጭ ነበር። ካጠገባቸው የሚገኙትን ሰዎች እየገፋፉ ሰርስረው ወደፊት አለፉ ።

« መጥኔ ለሚስቱና ለልጆቹ ። ምን ይሉ ይሆን ? እዚህ መሀል እኮ ይኖሩ ይሆናል ? » ከነፋሱ ጋር የሚታገለውን ነጠላቸውን ወደ አፋቸው እያስጠጉ ። ሳያስቡት እንባቸው ከዓይኖቻቸው እርግፍ እርግፍ አለ ። ወዲያው በነጠላቸው ጫፍ እንባቸውን እየጠራረጉ « በይ ነይ እንሂድ ይህ ዓይነቱ ቦታ ላንቺ ለእምቡጧ ጥሩ አይደለም፣ እኛ የሰራነው ግፍ ለልጆቻችን ተረፈ ። » አሉና የሕሊናን እጅ በመጎተት ከተሰበሰበው ሰው መሀል ለመውጣት ሞከሩ ። ልጅቷ ለመውጣት ፍላጎት አልነበራትም ።

« ለምን መጥፎ ነገር ማየት አባቴም እርስዎም ትከለክሉኛላችሁ ? ማየት ለመማር ይጠቅም የለ ? » ስትል ጠየቀች ።

« አዬ ልጄ ! መጥፎን ነገር ማወቁ ለማንም ቢሆን ጥሩም አይደል ። ሁሉንም ለማወቅ እንደምትፈልጊ ይገባኛል ። የልጅነት ነገር ሆኖብሽ ነው እንጂ » አሉና ድምፃቸውን ውጠው « ክፉና ደጉን ለይቶ ማወቅ አይከፋም ነበር ፣ ከበስተኋላው ተንኮል የማያስተምር ቢሆን ኖሮ ። » ሲሉ በውስጣቸው አጉተመተሙ ።

« አባቴ ሁልጊዜ እንደሱ ጎበዝና ደፋር ፣ እውነት ፈላጊ እንድሆን ይመክረኛል ። ነገር ግን እንደ አባቴ ጎበዝ ፣ ደፋርና ሀቀኛ ይገኝ ይሆን ? እቴቴ በላይነሽ ። »

« እንደ አባትሽ ደፋር ፣ ጎበዝና ሀቀኛ አይገኝም » እያልዋት ጥቂት ርቀት ከሄዱ በኋላ ፊት ለፊታቸው የሚታየውን ትልቅ መስኮት እየጠቆሙ ይኸው « የመጣንበት መድኃኒት ቤት ፣ እኔ ገብቼ ለአባትሽ የሚሆን መድኃኒት ልጠይቅ ። አንቺ ደግሞ ከዚያ ሱቅ ሂጂና ቡናና ስኳር ገዝተሽ ነይ ። ያዥ ይሄን » ብለው ሃምሳ ሳንቲም ሰጧት ። ልጅቷ ወ/ሮ በላይነሽን በፍቅር ዓይን እያስተዋለች « እቴቴ በላይነሽ በጣም ተቸገሩ አይደል ? » ለጥያቄዋ መልስ አልጠበቀችም ፤ ወደተባለው ሱቅ በሩጫ በረረች ። ብዙም ሳትቆይ በወረቀት ሁለት ትንንሽ ጥቅሎችን ይዛ ተመለሰች ።

ወ/ሮ በላይነሽ ሀዘን በተሞላው ድምፅ « አገኘሽ ልጄ » ፀጉሯን እየደባበሱ ጠየቋት ። እሷም ማግኘቷን ጭንቅላቷን በማወዛወዝ ገለፀችላቸው ።

« በይ እንግዲህ ወደማረፊያችን ተመልሰን ቡናችንን አፍልተን ከአባትሽ ጋር እንጠጣለን ፣ አባትሽ ቡና በጣም ይወዳል ። ቡና ሲጠጣ ከበሽታው ትንሽ የተፈወሰ ይመስለዋል . . . » ብለው የጀመሩትን ሳይጨርሱ ልጅቷ ከአፋቸው ነጠቀቻቸው ።

« አባቴ ቡና ከጠጣ ሦስተኛ ቀኑ ነው ። ቡና ሳፍላ ብዬ ስጠይቀው ፊቱ ይከሳተራል ለምን እንደሆነ አልገባኝም » እንባዋ

ታገላት ፣ ሳግ ተናነቃት ። ወ/ሮ በላይነሽ ፊት የነሷት መሰሉ ። ዝም ተባብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

« ሕሊና » አሉዋት ቤታቸው አካባቢ ሲደርሱ ፤ « ጥሩ ልጅ ነሽ ። አሁን ወደ ጉልት ሄደን የሚበላ ነገር ገዝተን ወደ ቤታችን እንገባለን ። »

« እኔም ጉልት መሄድ እፈልግ ነበር ። እዛ ሁሉም ነገር ይገኛል ። ስኳር ድንች . . . አይገኝም እቴቴ በላይነሽ ? »

« ገንዘብ ላለው ሰማይ ቅርቡ ነው ሲሉ አልሰማሽም ። ገንዘብ ካለ እንኳንስ ስኳር ድንች የሰው ነፍስም ይገኛል ። . . . ስኳር ድንች ፈለግሽ እንዴ ? »

መፈለጓን ቅር ባሰ ስሜት በመግለጽ ቀና ብላ ወ/ሮ በላይነሽን አስተዋለች ። ገንዘብ ሳይኖራት የምትፈልገውን በመናገሯ አሳፈራት።

« ምን አለበት እቴቴ በላይነሽ እንደ እናቴ ማለት ናቸው » ብላ ራሷን ለማፅናናት ሞከረች ። እሳቸው የፈለገችውን ነገር ሁሉ ያደርጉላታል ። « ገንዘብ ከየት ያመጣሉ ? ሊጠየቅ የማይገባውን ነገር ነው ያነሳሁት » በእጇ ጥብቅ አርጋ ለያዘችው ዕቃ የምታወራ ትመስላለች ።

« ዛሬ አባቴ አምሽቼ እንድሰራ የሚፈቅድልኝ ይመስልዎታል? እቴቴ በላይነሽ ፣ አባቴም ሥራ ካቆመ ቆየ ፣ እስከ መቼ ድረስስ በርስዎ ትከሻ ይኖራል ? ደግሞ ሥራውም ጠፋ ። ከእንግዲህ አባዬም ቶሎ የሚሻለው አልመሰለኝም » አለች ሕሊና ።

« በይ አርፈሽ ተቀመጭ ! አባትሽ እንዲያውም ያንቺን በቤት ሠራተኛነት ላይ መሰማራት በጣም ነው የሚጠላው ። የሰው እጅ እንዳታዩ የሚያደርገው ጥረት ይህ ነው አይባልም ። ደግሞ የኔ ነገር ምን አደረኩላችሁ ! ምነው በቻልኩና አቀማጥዬ በያዝኳችሁ » እንደድንገት የሆነ ብርሃን ታያቸው « ለማንኛውም የነገውን ቀን

እንዴት እንደምናደርግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ተጨምሮበት በነገው ዕለት እናያለን » አሏት ::

* * *

ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ አንድ ገርበብ ብሎ የተዘጋ የቆርቆሮ በር ገፋ አድርገው ገቡ :: ወ/ሮ በላይነሽ ራሳቸው ላይ ጣል ያደረጉትን ነጠላ አውርደው « እንደምን ዋላችሁ » ሲሉ ከቤት ውስጥ ሲያንጎዳጉድ የቆየ ውሻ ሲወጣ በድንጋጤ ጮኹ ::

« ችሩ እኮ ነው እቴቴ በላይነሽ ፤ ፈሩት እንዴ ? » ሕሊና ፈገግ ብላ ፣ ሳቋን አፍና ልታረጋጋቸው ሞከረች :: ወ/ሮ በላይነሽ ቤት ውስጥ መሬት ላይ ቡቱቶ ለብሶ የተኛውን ሰው መልከት አድርገው ፣ በእጃቸው የያዙትን ወረቀት ገለጡና « እንካ ቀና በል እስቲ ይሄን ዋጥ :: ትንሽ ቢያሽልህ » ብለው ሁለቱን ኪኒን እጃቸው ላይ አደረጉላቸው :: « ውኃ አምጭለት እስቲ » አሏት ሕሊናን ::

ከወለሉ ላይ የተዘረጉት ፣ በዒም የተወረሩ፣ ህመም ያጉሳቆላቸው አቶ የፊላ ከአንገታቸው ቀና ብለው ፤ የተሰጣቸውን ኪኒን ከወ/ሮ በላይነሽ እጅ ተቀብለው ወደ አፋቸው ወርወር አድርገው ከሕሊና በጣሳ የተቀበሉትን ውኃ እየተናነቃቸው ተጎነጩ ::

ወ/ሮ በላይነሽ የተረፈውን መድኃኒት ለሕሊና ሰጥተው ከቤት እንደወጡ ፤ ሕሊና መድሃኒቱን ለአባቷ እያሳየች « ይህን ሁሉ መድኃኒት ውጠህ ስትጨርስ ከበሽታህ ትፈወሳለህ አይደል አባብዬ ?» አለች ::

አቶ የፊላም የልጃቸውን ምኞት በደስታ የተቀበሉ ይመስል ፈገግ ሲሉ ፣ ልጃቸውም አፀፋውን በደስታ ስሜት መለሰችላቸው :: አጥንት ብቻ የቀረውን እጃቸውን ወጣ አድርገው በተከማተሩ ጣቶቻቸው መድኃኒቱን ተቀብለው እንደ ትራስ በሚጠቀሙት የግንድ

እንጨት ሥር ወርወር አድርገው ቀስ ብለው ተመልሰው በግንዱ ላይ ራሳቸውን አሳረፉ ::

ሕሊና አባቷ ከተኙበት ወለል ፊት ለፊት ተቀምጣ ፊቷን በእጆቿ መሀል አስደግፋ ሀዘን በተሞላበት ስሜት አባቷን ከላይ እስከታች ቃኘች :: አቶ የፊላ በደከመና በለለ ድምፃቸው « ሕሊና በዚህ ንፁህ አስተሳሰብሽ ላይ የተማርሽ ብትሆኚ ምንኛ የረካሁ በሆንኩ :: በድህነታችን ምክንያት በዘራችን የተማረ የለም :: አንቺን ለምኜም ፣ ለፍቼም ለማስተማር የነበረኝ ምኞት የላቀ ነበር ::

ግና ምን ያደርጋል ፣ አቅሙ ጠፋ ! የአቅም ማነስ . . . አቅም . . .» ሕሊና ልታስጨርሳቸው አልቻለችም :: እንባዋ እየተናነቃት እጃቸውን በእጆቿ እየዳሰሰች » አባዬ አንድ ቀን እግዚአብሔር ሲፈቅድ እማር ይሆናል :: እየለመንኩም ቢሆን እማራለሁ :: ነገር ግን ካንተ ተለይቼ ለመኖርም ለመማርም ምንም ሀሳብ የለኝም :: ለትምህርት ብዬ ከአንተ ተለይቼ ለመኖር ፈጽሞ አልፈልግም :: በዚህ ህመምህ ስለኔ መማር ያለመማር መጨነቅ የለብህም :: ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው :: » አባቷ የሕሊናን የልጅነት አንደበት በማለሳለልና እየበለለች መምጣቷን በማድነቅ ፣

« መማር ልጄ ማንንም አልጎዳም :: እኔ ላንቺ መከራ እንጂ ደስታን የማመጣ ሰው አልሆንኩም ፣ ሆኖም እንድትማሪ እፈልግ ነበር :: »

« አባዬ ከእንግዲህ እኔ ልጅ አይደለሁም :: የምትለው ሁሉ ይገባኛል :: . . . ምኞትህ ከሆነ ትምህርቴን ጊዜና ቦታ ሲያጋጥመኝ እማራለሁ » ስትል አባቷን ለማፅናናት ያህል ተናገረች ::

« ሕሊና ! ለመሆኑ አንድ አክስት እንዳለችሽ ታውቂያለሽ ?» የሆነ ተስፋ የሚያስቆርጥ ስሜት እየወረራቸው ፣ ለውነታቸው እየከዳቸው የሄደ መሰላቸው ::

« አዎ አንድ ቀን ነግረኸኝ ነበር » አለቻቸው ::

ቀስ ብለው ራሳቸውን በጃቸው ደገፍ አድርገው ክንዳቸውን መሬት ላይ በማሳረፍ « ሕሊና ! ሌላዋ አክስትሽ ደግሞ እዚህ ትልቅ ከተማ አለች » አሏት ::

« እዚህ ሀገር ? » አለች በመገረም :: እራሳቸውን በማነቃነቅ የአዎንታ ምልክት አሳይዋት ::

« ይህችኛዋ አክስትሽ ደግሞ የእናትሽ እህት ነች » አሏት ::

« የኔ እናት እህት የእውነት እዚህ ከተማ አሉ ነው የምትለኝ? » አለቻቸው ::

« እዚህ በአቅራቢያችን ሳይሆን ትንሽ እራቅ ወዳለ ሠፍራ ነው » አሏት ::

« ግን እኛ ልናገኛቸው እንችላለን ? » ስትል በጉጉት ጠየቀቻቸው ::

« እኔ እንኳን . . ላያት አልችልም እኔን አትወደኝም :: ግን አንቺ ሄደሽ አግኚያት »

ሀዘን በተሞላበት አነጋገር « አንተን የሚጠሉ ከሆነ እኔም አልወዳቸውም . . . » የአባቷ አለመወደድ አክስቷን ለማወቅ የነበራትን ጉጉት አጨለመው :: አባቷ እጇን እየዳሰሱ ለስለስ ባለ አነጋገር « እኔን በመጥላቷ አትፍረጅባት :: ለጥላቻዋ ተመጣጣኝ ምክንያት አላት :: እናትሽን ወርቂቱን ጠልፌ እንድታገባኝ ያስገደድኳት እዚች አክስትሽ ጋር ትኖር በነበረበት ጊዜ ነው :: በዚህ ምክንያት አክስትሽ እናትሽንም ሆነ እኔን ሁለተኛ ዞር ብላ ለማየት አትሻም ነበር :: » ሲሉ ሊያስረዷት ሞከሩ ::

« እንግዲያውስ እኔንም ለማየት አይፈልጉም :: »

አባቷ የልጃቸው የወደፊት ሁኔታ እየታያቸው ለማግባባት ቢሞክሩም እሷ ባደረባት የጥላቻ ስሜት ላለመቀበል ጣረች ::

« አይ አንችንማ ብታይሽ አትጠላሽም »

« እኔ ደግሞ ከአንተ ተለይቼ እሳቸውን ለማየት አልፈልግም:: በዚህ ላይ ከሰሞኑ አንተ ታመህ በመተኛትህ ለእቴቴ በላይነሽ ለቤት ኪራይ የምንከፍለውና ለምግብ የሚሆነን ገንዘብ የለንም :: እንደምንም ብዬ የሚሰራ ሥራ ፈልጌ ገንዘብ ማግኘት አለብኝ :: እቴቴ በላይነሽ ይረዱኛል :: »

« ስማሽ ሕሊና ! በየሰው ቤት እየተንከራተትሽ እንድትሰሪ አልፈልግም ፤ ከእንግዲህ በቃ ! በቃ ነው የምልሽ ! » ዓይናቸውን ከድነው እራሳቸውን እየነቀነቁ ቁጣ ባዘለ ስሜት « የኔና ያንቺ እህል ውኃ በዚህ ያበቃል » አሏት ::

« ለምን ? ምን አደረኩ አባባ ? » አለች ሕሊና በድንጋጤ ::

« . . . የኔ ሕሊና ከግርድና ሥራ የተሻለ ነገር ነው ላንቺ የምመኘው :: »

ቁጣቸው እየበረደ መጣ :: እንደ ትራስ በሚጠቀሙበት ግንድ ላይ እራሳቸውን አሳረፉ :: « እንዲህ ቁርጠኛ ከሆንክ ያኔ ወደ ነገርከኝ ያንተ እህት ወደ ሆነችው አክስቴ ብሄድስ ? » አለች ሕሊና ፍርሃት በተሞላው ቃል ::

እንደማጉረምረም ያለሳቅ በማሰማት ዓይናቸውን ጥቅርሻ ወደወረሰው ጣሪያ እየተመለከቱ « የእኔም ምኞት ነበር :: ምኞት ብቻ ሆነ እንጂ ! እሱማ ቢሆን . . . ነገር ግን . . . አይሆንም :: የኔ እህት ያለችበት ቦታ በጣም ሩቅ ነው . . . በዚህ ላይ እህቴ እኔ እንደምፈልገው ልታሳድግሽ ዕድሜዋ የሚፈቅድላት አይመስለኝም ፤ በአሁኑ ወቅት የኔ እህት ዕድሜዋ ወደሰባው እየተጠጋ ነው » አሉ ሀዘንና ሀሳብ በተቀላቀለው ስሜት ::

« . . . አዎ ዓይኖችሽ የደጓን እህቴን ዓይኖች ይመስላሉ :: ስሜትሽም እንደ እሷው ነው :: ያቺን ደጓን የገጠር እህቴን መስለሽ ተፈጥረሻል :: አዎ የአባዋጅ ዘሮች በደማቸው ያስታውቃሉ . . . እናትሽ የስሜት ተገዥ አልነበረችም :: እናትሽ መልከ መልካም

ነበረች ። አንቺም እንደ እናትሽ መልከ መልካም ነሽ ። ፀጉርሽ የእናትሽን ይመስላል ። ፀጉርሽ ተባይ እንዳይፈጥር ተንከባከቢው ፤ ታጠቢው ።

እናትሽ ፀጉሯን መታጠብ ትወድ ነበር ። . . . እናትሽ በጣም ደግ ሴት ነበረች ። በጣም ! በጣም ! . . . ! » ሀሳባቸው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየችው ባለቤታቸው ጋር ሄደ ። ብዙ በመናገራቸው ፣ ቶሎ ቶሎ መተንፈስ ጀምረዋል ።

ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ ድምፃቸው እየራቀ መጣ ። ለመመን ይሏቸው ወደ ጣር ዱካ አስጠጋቸው ። ሒሊና በጉልበቷ ተንበርክካ አባቷን በድንጋጤ ተመለከተች ። ጭንቀታቸው ሠላም ነሳት ። በወረቀት የተጠቀለለውን ኪኒን ከትራስጌያቸው አንስታ « አባዬ ፣ አባዬ ፣ እንካ ይሄን ዋጥ ያሽልሃል ። አባብዬ . . . ። » ልጅቷ የያዘችውን ነጫጭ ኪኒኖች ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ተመለከቱ ። መድኃኒቱን ሳይሆን ወ/ሮ በላይነሽን እንድትጠራ ተማፀኗት ።

« እቴቴ በላይነሽ እቴቴ በላይነሽ ! » በማለት ደጋግማ ተጣራች በተደናገጠ ስሜት ።

ወ/ሮ በላይነሽ በአካባቢው ባለው የወዳደቀ አጥር አጠገብ ለከሰል ማቀጣጠያ የሚሆን የረገፈ የባህር ዛፍ ቅጠል ይለቃቅሙ ነበር። ድንገት የሒሊና የድረሱልኝ ድምፅ ተሰማቸው ።

ወ/ሮ በላይነሽ እየተጣደፉ ቤት ሲደርሱ አቶ የፊላ ከሞት ጋር ግብግብ ገጥመው ነበር ። ወ/ሮ በላይነሽን እንዳዩ ቀርበው እንዲሰሟቸው ምልክት አሳይዋቸው « ወ/ሮ በላይነሽ . . . እህ . . . እህ . . . እህ . . . የሒሊና . . . እህ . . . እናት . . . እህ . . . እህ እናት እህት . . . አቃቂ በለቃ . . . እህ . . . እህ . . . የቡና . . . ቤት ባለቤት . . . ባለቤት . . . ለሷ . . . ስጡልኝ . . . ሒሊና ትምህርት . . . ትምህርት አባይነሽ . . . ሒሊና መማር . . . መማር . . . መማር . . . » እያቃሰቱ የቻሉትን ያህል ለማስረዳት ሞከሩ ።

ሒሊና እየተቆራረጠ የሚወጣውን የአባቷን ቃል ከወ/ሮ በላይነሽ ጎን ቀረብ ብላ ተንበርክካ ለመስማት ሞከረች ።

* * *

ሒሊና ከአባቷ ሞት በሁዋላ በነበሩት ተከታታይ ቀናት ስለተፈጸሙት ሁኔታዎች እጅግም አታስታውስም ። ጎኑዋ ላይ ከሚሰማት ህመምና እንደብኸርታ ከሚታያት የአባቷ መቃብር ውስጥ ሳትወድቅ እንዳልቀረች ትገምታለች ። ከዚህ በቀር እንደዋዛ አባቷ ከጎንዋ የሉም ። አላፊ አግዳሚው ከንፈሩን የሚመጥላት ምስኪን ሆናለች ። ስለምንም ነገር ማሰብ አልቻለችም ። ተስፋ ቆርጣ ሀሳቧን ሁሉ ለወ/ሮ በላይነሽ ትታ ይሆን ? ያሰኛል ። በእርግጥ ወ/ሮ በላይነሽ አሳቢዋ ፣ ለወደፊት ህይወቷ ተጨናቂ ነበሩ ።

አንድ ቀን ወ/ሮ በላይነሽ ከአንድ ሠፈርተኛ መነኩሴ ጋር ሆነው ሒሊናን ወደ አክስቷ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት መሄድ እንዳለባት ገለጹላት ። ሒሊና ግራ ተጋብታ ዓይኖችዋን ከወዲያ ወዲህ እያንከባለለች ሁለቱን ሴቶች ተመለከተች ።

« እውነቷን ነው ። ይህ እንዲሆን አደራ ያለው አባትሽ ነው። ያ ባይሆን የዚህ ሰፈር ሰዎች ተጋግዘን አንቺን እንደገዛ ልጃችን ለማሳደግ ባልሰነፍንም ነበር ። የሆነ ሆኖ የአባትሽ ፣ የሙት ቃል በምድርም በሠማይም ያስጠይቃል መከበር አለበት » አሏት መነኩሴዋ የወ/ሮ በላይነሽን ሀሳብ በመደገፍ ።

« አባትሽ ከመሞቱ በፊት ወ/ሮ አባይነሽ ዘንድ ሽማግሌ በመላክ እንዲታረቁት መማፀኑን ነግሮኛል ። በዚህ ላይ ወ/ሮ አባይነሽ የተነገረላቸው ሀብታም ነጋዴ መሆናቸውን ሰዎች ሁሉ ያወራሉ ። ላንቺም ከሳቸው ጋር መሆኑ ሳይሻልሽ አይቀርም ። ትምህርትሽንም መማር ትችያለሽ » ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽም ሀሳቡን አጠናከሩ ።

መቀነታቸው ላይ የነበረውን ቋጠሮ ፈትተው አራት ቀያይ የብር ኖት አነሱና « ያዥው ፤ ለዕዝንሽ ሠፈርተኛው ያዋጣልሽ ብር ነው :: ትንሽም ቢሆን ይጠቅምሻል » አሏት :: ሒሊና የእዝን የሚሰውን ቃል ገና እንደሰማች የሆነ ነገር ውስጧን ሲቆርጠው ተሰማት :: የአባቷን ሞት ዕዝን መቀበል በጣሙን ቀፈፋት ፤ ዘገነናት :: ወ/ሮ በላይነሽ እጅ እንዲቀር ተመኘች :: ሴትዮዋ ግን ላለመቀበል አንገራገሩ ::

« እዚህ አብረን ስንኖር የቤት ኪራይና የምግብ እንዳልከፈልንዎት ያውቃሉ :: አባዬ ቢኖር ከዚህ የበለጠ ይከፍልዎት ነበር :: በአባቴ አፅም ይዤዎታለሁ ! ይተውኝ » አለቻቸው ::

በአባቷ ትዝታ ህመሟ የሚያገረሽባት ስለመሰላቸው ሁኔታዋን ለማረጋጋት ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ ከብዙ ማመንታት በኋላ ከሒሊና ብሩን ተቀብለው « በአባትሽ አፅም ከያዝሽኝ ምን አደርጋለሁ :: ባይሆን ለአባትሽ የተዝካር ማውጫ ይሆናል » አሉና ብሩን በመቀነታቸው መልሰው ቋጠሩ :: ሒሊና አቅሟ በፈቀደላት መጠን አባቷን ከዕዳ ነፃ በማድረጓ ደስታ ተሰማት :: ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ የአባቷን ልብስና መጥረቢያውን ከራሷ ዕቃ ጋር በማዳበሪያ መሳይ ከረጢት ቋጥራ ለማይቀረው ጉዞ ተዘጋጀች ::

ወ/ሮ በላይነሽም በገቡት ቃል መሠረት አክስቷ ዘንድ ሊያደርሷት ተነሱ :: ከበሩ ወጣ እንዳሉ ፤ የሠፈሩ ሰዎች ከንፈራቸውን በሀዘኔታ እየመጠጡ ፤ ጉንጯን አገላብጠው እየሳሙና እየመረቁ ተሰናበቷት :: በእጇ ያንጠለጠለችውን ከረጢት ታዳጊዎች ተሸክመው መኪና ተራ ድረስ ተከተሏት ::

የአቃቂ አውቶቢስ ጥቂት ካስጠበቃቸው በኋላ በቦታው ቆሟል:: ሒሊና አብሮ አደግ ጓደኞችዋ እጠገቧ ቆመው ዓይን ዓይኗን ሲያዩ እንባዋ እቀረረ :: የልጅነት ስሜቷ ያለችበትን ሁኔታ አስረሳት:: ዓይኖችዋን ከልጆቹ ላይ ሳትነቅል በደመነፍስ ወደ አውቶብስ ስትገባና

አውቶብሱ ሲንቀሳቀስ አንድ ሆነ :: በዚሁ መሀል እግሯ ተንሸራቶ በመውደቅ ላይ ሳለች በሩ አጠገብ ቆሞ የነበረ ወጣት እጇን ይዞ አዳናት :: በወቅቱ የምትተነፍሰው ቃል አልነበራትም :: አንገቷን አቅንታ እንዳትወድቅ ለታደጋት ወጣት ምስጋናዋን ገለፀችለት :: ወ/ሮ በላይነሽ በመካከል ፤ ሒሊና ከቀኛቸው ከመውደቅ የጠበቃት ልጅ ከግራቸው በኩል እንደተቀመጡ አውቶቢሱ ወደ አቃቂ ከተማ መጣደፉን ቀጠለ ::

ሁኔታው ለወ/ሮ በላይነሽም ሆነ ለሒሊና ሁለት ገፅታ ነበረው:: ሁለቱም መለያየቱ ጨንቋቸዋል :; ግን ደግሞ መለያየት አለባቸው :: ከወሬ እንደታወቀው የሒሊና አክስት ሀብት ያላቸው በመሆናቸው የሒሊና ህይወት ይለወጣል :: በዚህ ደግሞ ወ/ሮ በላይነሽም ይጠቀማሉ ፤ ሒሊና አትረሳቸውም :: በእንዲህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ሆነው ብዙ ተጓዙ :: አቃቂ ከተማ በመቃረብ ላይ እንዳሉ ሒሊና የሆነ ጥያቄ ለወ/ሮ በላይነሽ ሰነዘረች ::

« እቴቴ በላይነሽ ፤በቃ የምኖረው አቃቂ ነው ማለት ነው?» አለቻቸው :: ቤቱ ከተገኘ የመለያየታቸው ነገር አሳሰባት :: ወ/ሮ በላይነሽ ስሜቷ የሳቸውም ስለነበር ጥያቄዋ ውስጣቸውን ይበልጥ አሸበረው :: ፊቷን ላለማየት እየጣሩ ፤

« ምን አለበት አቃቂ ሩቅ አይደል :: እኛም እየመጣን እንጠይቅሻለን :: አንቺም ትመጫለሽ :: በእርግጥ የአባትሽ የአደራ ቃል ባይሆን ከኔ ጋር አብረን ብንኖር እንዴት ደስ ባለኝ :: ቢሆንም የአባትሽ ቃል ይበልጣል :: አባትሽ የሆነ ነገር ባያስብ ይኸን አያደርግም ነበር » አሏት እሷንም ራሷቸውንም ለማሳመን ::

« እኔኮ አክስቴን አላውቃቸውም :: አባዬም ስለሳቸው ካለዚያ ቀን በስተቀር ሲናገር ሰምቼ አላውቅም » ስትል ዓይኖችዋ የእንባ ደመና እየጋረዳቸው ፤ ሳግ ንግግሯን እያሻከረው ውስጣዊ ፍርሃቷን ተነፈሰች ::

ወ/ሮ በላይነሽ ሰውነታቸውን ወደ ሕሊና አስጠግተው ፣ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከቱ ፤ በእጃቸው የሕሊናን እራስ እየደባበሱ « አይዞሽ መቼም ከዛ ከድህነት ኑሮ የማይሻል ነገር የለም። እንደሰማሁት አክስትሽ የታወቁ ሀብታም ናቸው ። ምንም ቢሆን ስጋቸው ነሽ አይዞሽ ጥለው አይጥሉሽም » አሏት ። ለማፅናናትና ለማረሳሳት ያህል ። ሕሊና አንገቷን አቀረቀረች ። « ምን መሆንሽ ነው ሕሊና ? መንገድ ሲሄዱ እየሳቁ እንጂ አይለቀስም ። ደግም አይደል ! » አሏት ። ወደደረታቸው ለማስጠጋት እየሞከሩ ።

« ድንገት ምን ሆና ነው ? » አላቸው ከጎናቸው የነበረው ወጣት ። ወጣቱ ሁኔታቸውን ይከታተል ስለነበር ስሜቱ ሳይነካ አልቀረም ።

« ምን ትሆናለች ብለህ ነው ፤ እንደው ዝም ብላ ነው » ሲሉ መለሱለት ባጭሩ ። ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈለጉም ። ወጣቱ የተሰጠው መልስና የሚያየው ሁኔታ ሊጣጣሙለት አልቻሉም ። ውስጡን የሆነ የሀዘን ስሜት ጨምድዶታል ። የሕሊና ለቅሶ የእህቱን ያህል የሆነበት መሰለው ። የሴትየዋን ፊት ለማየት ጓጓ ።

« አመማት እንዴ ? » ሲል ጠየቃቸው ።

ወ/ሮ በላይነሽ ወጣቱን ልጅ ለአንድ አፍታ መልከት አደረጉ። ፊቱ ላይ መጥፎ ስሜት አይታይም ። « ልጂ ሀዘን ደርሶባት ነው » ሲሉ መልሳቸውን አሳጠሩ ።

ለወጣቱ ከመልሳቸው ይልቅ ገፅታቸውን ማየት መቻሉ እጅግ በጣም አስደነገጠው ። እራሱን እስኪጠራጠር ሁኔታው ተምታታበት።

« እማማ ከዚህ በፊት የማውቅዎት መሰለኝ . . . » አላቸው። ራሱን ለማረጋጋት ፣ ሁኔታውን ለማጥናት ጊዜ ለማግኘት በማሰብ ።

ወ/ሮ በላይነሽ ወደ ወጣቱ ፊታቸውን መልሰው « ኧረ . . . ልጂ ምን ይታወቃል . . . በየቦታው ተቀጥሬ ስለሠራ ተገናኝተን

ይሆን? ለመሆኑ የት ነው ኑሮህ ? » በማለት ፈገግ ብለው ጠየቁት። አጋጣሚው ድንገተኛ ቢሆንም እራሱን አረጋጋ ። ወላጅ እናቱ በልጅነቱ ስለሞቶታቸው እርግጠኛ መሆኑን ቢያውቅም የሴትየዋ ሁኔታ በብዙ መልኩ ከእናቱ ጋር መመሳሰል አስገረመው ። እናቱ አለመሆናቸውን ቢረዳም ሊለያቸው አልወደደም ። አብሯቸው ቆይቶ ቢያጫውታቸው ፣ ቢረዳቸው ተመኘ ።

« ኑሮዬ እንኳ ወደ አፍንጮ በር ነው ። እማማ . . . ደፈረኝ ባይሉኝ ፊትዎን ላይ እናቴን አስታወሱኝ ፣ ቁርጥ እናቴን ይመስላሉ . . . ድንገት ዝምድና ይኖራችሁ ይሆን ? »

ሕሊና የወጣቱ ንግግር የነበራትን ስሜት ነጠቃት ። አውቶቡስ ውስጥ ስትሳፈር ከመውደቅ የታደጋት ፣ አብሯቸው መቀመጡ ፣ . . . ሁሉ የሆነ ነገር ሳይኖረው እንደማይቀር አስላሰለች።

« የእኔ ዘመዶች ወሎየዎች ናቸው ። የሞቱት ሞተው የተረፉትም አሉ ። እኔ እንኳን ከሀገሬ ከወጣሁ ቆይቻለሁ ። የኖርኩት ግን መርካቶ መሀል ነው » አሉት ።

« እንግዲህ ሊሆን ይችላል » አለና በሀፍረት ስሜት ዝም አለ።

« ለመሆኑ ! እናትህ በህይወት አሉ ? » ሲሉ ጠየቁት ወይዘሮ በላይነሽ ።

ለወጣቱ መጥፎ ጥያቄ ነበር ። በቋፍ የነበረ የሀዘን ስሜቱ ተቀሰቀሰ ፣ እንደበቱ በሳግ ተወጥሮ እንባ ተናነቀው ። መንፈሱ ተረበሸ ። አንገቱን በቅሬታ ደፋ አድርጎ « ከሞተች ቆይታለች » አላቸው ።

« ተው እንጂ ልጄ ፣ ወንድ ልጅ እኮ አይሳሳም ። በዚያ ላይ እኔም እናት እሆንሃለሁ » አሉት ለማፅናናት ያህል ።

አውቶቡሱ አቃቂ ደርሶ የታፈነ በሩ እንደተከፈተ ተሳፋሪዎቹ እርስ በእርሳቸው እየተጋፉ ወረዱ ። ወ/ሮ በላይነሽን ከጎናቸው ተቀምጦ ሲያጫውታቸው የነበረው ወጣት በቦታው አልነበረም ። እንደድንገት ጥሏቸው መውጣቱ ፣ አካባቢ ያመላክተኛል የሚል ተስፋ ስለነበራቸው ተደናገጡ ። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆነው ፣ የሕሊናን ከረጢት ከሥር ጎትተው ፣ ሕሊናን አስከትለው ከመውረዳቸው ወጣቱ ይጠብቃቸው እንደነበረ አወቁ ።

« እኔስ ጥለኸን የሄድክ መስሎኝ ነበር ። እግዜአብሄር ይባርክህ ልጄ፣ እንዲያው ከዚህ ሀገር ሰው ብጠይቅህ ታውቃለህ ? » ሲሉ ጠየቁት ።

« እኔ እንኳን ለቦታው አዲስ ነኝ ። ለመሆኑ ማን ይባላሉ ?» አላቸው ።

« እዚህ ሀገር የታወቀ ቡና ቤት ያላቸው ሴት ናቸው ። ወ/ሮ አባይነሽ ይባላሉ » አሉት ። አላወቃቸውም ። የአካባቢውን ሰው መጠየቅ ነበረበት ። አንድ በእሱ ዕድሜ ያለ ልጅ አስቆመ ።

« የኔ ወንድም ! እባክህ ወ/ሮ . . . ማን ነበር ያሉኝ ? » አላቸው ወይዘሮ በላይነሽን ሥሙ ጠፍቶበት ።

« አባይነሽ ቡና ቤት » የት አካባቢ ነው የሚገኘው ? » ሲሉ የጀመረውን በመጨረስ ጠየቁ ።

« እንዲህ የሚባል ቡናቤት አላውቅም ። ለማንኛውም ቡና ቤት እዚህ አካባቢ የለም ። ትንሽ ወረድ ብላችሁ ብትጠይቁ ይሻላል» አለና መንገዱን ቀጠለ ። ወጣቱ ዕቃቸውን ተሸክሞ ፊት ፊት ወ/ሮ በላይነሽን እና ሕሊናን እየመራ ከአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ወጣ ብሎ ከሚገኘው ጋራ መሳይ ጉብታ ተነስተው ወደ ከተማው ወሰዳቸው ። በዝምታ እየተጓዙ ሳለ ፣

« እንዲህ ያለ የተባረከ ልጅ በአሁኑ ጊዜ ! . . . ልጄ ሥምህ ማን ይባላል ? » አሉት ዝምታውን በማባረር ።

« ሥሜ ያሬድ ይባላል . . . ያሬድ እንደሻው ። . . . የመባረኩን ነገር ግን ይርሱት » አላቸው ።

« ምነዋ ? . . . በዚህ ዕድሜህ ? እንዲህማ መሆን የለብህም። እይዞህ ሁሉም ያልፋል ። በዚህ ደግነትህ ለአንተ እንጀራ ያልወጣ ለማን ይወጣል ? ለመሆኑ ስንተኛ ደርሰሃል ? »

« መማር ምን ፋይዳ ይፈጥራል ብለው ነው እማማ ። ስነገሩ የሁለተኛ ዓመት ኮሌጅ ጨርሻለሁ ። አሁን ግን ትምህርቴን አቋርጬ ሥራ እየፈለኩ ነው ። ረዳት በማጣቴ ትምህርቴን ለመቀጠል አልቻልኩም ። » ወጣቱ ያሬድም ወ/ሮ በላይነሽን ፣

« ምን ሞቶባችሁ ነው ? እኔ እኮ መጀመሪያ ሳያችሁ እናትና ልጅ መሰላችሁኝ ነበር ። ለመሆኑ ምንዎ ናት ? » ሲል ጠየቃቸው።

ወ/ሮ በላይነሽ ችግራቸው የሚቃለልላቸው ይመስል አጋጣሚው ሲያመች ለጠየቃቸው ሁሉ ማስረዳት ይወዳሉ ። በዚያ ላይ ከልጁ ጋር የነበራቸው መቀራረብ ምን ይሉኝ የሚያሰኝ አልነበረም ። የራሳቸውን የኑሮ ሁኔታ ባጭሩ በመግለጽ ስለ ሕሊና የደረሰባትን ሀዘንና አሁን የት እንደሚሄዱ ታሪኩን አወጉት ። በመጨረሻም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ « የባሰ አታምጣ » ማለት ነው አሉና ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

ከዚህ በኋላ አንዳችም ቃል ሳይለዋወጡ አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ደረሱ ። ያሬድ ወደ ፋብሪካው በር እየተመለከተ « እማማ ፣ እዚህ መሥሪያ ቤት ስራ ለመቀጠር ዛሬ የፈተና ቀጠሮ አለኝ ። እንደው ቢቀናኝ ፣ እማማ እባክዎ በዚህ ንጹህ የድሃ አንደበትዎ ይጸልዩልኝ » በማለት ሠፍኖ የነበረውን ዝምታ ለመስወጥ ሞከረ ።

ወ/ሮ በላይነሽም ፀሎቱን ውለታ የመመለስ ያህል አድርገው ነበር የቆጠሩት ። እጃቸውን ወደ ሠማይ ዘርግተው « ልጄ ፣ ወዳጄ ቀንና ለሊት እፀልይልሃለሁ ፤ እግዚአብሄር ይርዳህ » ሲሉ ክልባቸው

ፀሎት አደረሱለት ። ቀጥለውም ተሸክሞላቸው የነበረውን ዕቃ ለመቀበል እጃቸውን ዘረጉ ።

« ጊዜው ገና ስለሆነ እስከ ከተማው እሸኛችኋለሁ » አለ ።

« አይ ግድየለ ! ግድየለ ተጋግዘን እናደርሰዋለን » አሉ ይሉኝታ ተሰምቷቸው ። ያ ባይሆን እንዲለያቸው አልፈለጉም ነበር። ለነሱ ከዚህ በኋላ ያለው የአድራሻ ፍለጋ የበለጠ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ተገንዝበውታል ። ያሬድም ከእናቱ አምሳያና ከምስኪኗ ሕሊና ተለይቶ መቅረቱን አልፈለገም ነበር ። የቀጠሮውን ሰዓት አለመድረሱን ምክንያት አድርጎ አብሯቸው መሄዱን ፈልጓል ። ዕቃውን እንደያዘላቸው አብረው ወደ ከተማው መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ፋብሪካዎች እንደብዛታቸው የአየር መበከልን አልፈጠሩም ፤ የዛፎችና የዕፅዋት መኖር የአቃቂን ከተማ ሰብአዊ ህይወት እስትንፋስ ሲጋት ላይ የሚጥለው አይመስልም ። ከጋሪ ፈረሶች የሚወጣው እዳሪ ብናኝ ግን አየሩን ብቻ ሳይሆን ሰውንም ጤና ነስቶታል ። ጥርጊያ መንገዶቹ ከዋናው መንገድ አንፃር ሲታዩ የእንግዳን ዓይን ይስባሉ ። የፋብሪካዎቹ መናኸሪያ የሆነችው ከተማ ከዋናው መንገዷ ዳርና ዳር ጥቅጥቅ ብለው ከተሰሩት ቤቶች የሽቀጣሽቀጥ ሱቆች ፤ የሕዝብ መዝናኛ ቡና ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ይገኛሉ ።

ለአቃቂ ከተማ ትልቁ መዝናኛ በመሆን የሚታወቀው የሾፌሮች ቡና ቤት በዚህ ዋና መንገድ ላይ ይገኛል ። በጉዞ ላይ እንዳሉ ወ/ሮ በላይነሽ ለብቻ ገንጠል ብለው ወደ አንድ ቤንዚን ማደያ ታጠፉ ። የማደያው ሠራተኛ ሁኔታቸው የልመና ስለመሰለው በጥላቻ ገላምጦአቸው ስራውን ቀጠለ ።

« ምን ትፈልጊያለሽ ? ናፍታ አሁን አይሸጥም ! ከዚህ ዞር በይ! » ሲል ጮኸባቸው ፤ የማደያው ሰራተኛ በተሰላቸ ስሜት ።

« እባክህ የኔ ወንድም ናፍታ ለመግዛት አይደለም የመጣሁት። የሰው ቤት ለመጠየቅ ነው » አሉት የሰሙትን ያልሰሙ ያህል ሆነው።

ቤንዚን አዳዩ የሆኑ ደረሰኞችን በትክክሉ ወደአንጠለጠለው ቦርሳ እየከተተ በለሰለሰና በችኮላ ቃል « ምን ዓይነት ሰው ነው ? እኔን ሕዝብ ግንኙነት ነው አለሽ ? በይ ተናገሪ . . .ማን ይባላል ? » እለ ወደማደያው ቢሮ እየገባ ። ከኋላ ኋላው እየተከተሉ « የወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤት ። . . . እዚህ ሀገር የታወቀ ነው ። የቱ ጋ ይሆን?» አሉ በተደነባበረ አጠያየቅ ።

ቤንዚን አዳዩ አንገቱን ቀና አድርጎ ወ/ሮ በላይነሽን ከእግር እስከራሳቸው እየገላመጠ « ቡና ቤት » ሲል እራሱን ጠየቀ « አይ ሄ-ሄ-ሄ ! አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል አቃቂ እስከአሁን አልተወለደም። ይልቁንም ሥራ ባትፈቺ ይሻልሻል ። ኋላ መኪና እንዳይገጭሽ ከዚህ ዞር በይ ! » ሲል በንቀትና በማሾፍ ገላመጣቸው ።

በሁኔታው ግራ የተጋቡት ወ/ሮ በላይነሽ በሰውየው ንግግር ሳይሆን የተባለውን ቤት የሚያውቅ በማጣታቸው ግራ ተጋቡ ። አንገታቸውን በሀዘን አቀርቅረው አጋጣሚውን አማረሩ ። « ምነው ! እቶ የፊላ ሲዋሽኝ ነው እንዴ ? ተረት ይሆን እንዴ? ወ/ሮ አባነይሽ ቡና ቤት የሚባል አቃቂ የለም አለኝ ። ለምን ይሆን ? ወይስ ጆሮዬ ነው ? አንገታቸውን ደፍተው ወደ ያሬድና ሕሊና አመሩ ።

ያሬድ ከፊታቸው ላይ የነበረውን ሁኔታ እስተውሎ ቀድሞ « ምነው አልቀናዎትም እንዴ ? » ሲል ጠየቃቸው ።

ጥቂት ካመነቱ በኋላ « አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል አቃቂ የለም አለኝ፤ ባያውቀው ይሆናል » አሉ ።

መሀል ከተማ ደረሱ ። መንገድ ዳር ካለ ከአንድ ቤት ግድግዳ ሥር ወንበራቸውን ደርድረው ደንበኞቻቸውን የሚያስተናግዱ ጫማ ጠራጊዎችን ጠየቁ ። ሁሉም እየተቀባበሉ አለማወቃቸውን ገለጹ ።

ያሬድ አንደኛውን ጫማ ጠራጊ « እስቲ ና ! » ሲል ተጣራ፡፡ ጥሪውን ያዳመጠ ጫማ ጠራጊ ሮጦ የሊስትሮ ዕቃውን መሬት ላይ አስቀመጠ ፡፡ ያሬድ አንገቱን ቀና አድርጎ አስተዋለው ፡፡

« ስማ አባይነሽ ቡና ቤት የሚባለውን ታውቃለህ ? » ሲል ጠየቀው ፡፡

ለመጥረግ የነበረው ጉጉት እየከሰመ ከተቀመጠበት ቦታ ቀስ ብሎ ብድግ አለና በሀሳቡ እያወጣና እያወረደ ትንሽ ካመነታ በኋላ አንገቱን በአሉታ እየነቀነቀ « አባይነሽ ቡና ቤት ? የሚባል የለም » ሲል ተነፈሰ ፡፡ ቀጥሎም አጠገቡ ሜዳ ላይ የተቀመጡትን ጓደኞቹን በቋንቋው ጠርቶ አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል ያውቁ እንደሆነ ጠየቃቸው ፡፡ ሁሉም እርስ በርሳቸው በሹክሹክታ ተነጋግረው የደረሱበት መልስ ዝምታ ብቻ ሆነ ፡፡

ጫማ ጠራጊው ያሰበው ግቡን ስላልመታ በስጨት ብሎ መሬት ላይ ያስቀመጠውን መሳሪያውን አንስቶ ወደ ጓደኞቹ ተቀላቀለ፡፡

ያሬድ ግራ በመጋባትና ድንገት ተሳስተው እንደሆነ በማለት በመጠራጠር « ቡና ቤቱ እዚህ አቃቂ በሰቃ ስመሆኑ እርግጠኞች ናችሁ » ሲል ጠየቃቸው ፡፡ « እንግዲህ አቃቂ መባሉን ደጋግሜ ሰምቻለሁ » ስትል ሕሊና ተስፋ በመቁረጥ ተናገረች ፡፡

« ድንገት ለቀው ወደ ሌላ ሀገር ሄደው ይሆን ? እንግዲህ በከተማው አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል ከሌለ ! . . . » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ አፋቸው ላይ እንደመጣ ፡፡

« አሁን ያ ደሀ ሰው ቡና ቤት ያላት ዘመድ ብትኖረው ኖሮ ለምን ተጠግቶ አይኖርም ነበር? እኔም ሞኝ ነኝ ፡፡ በጣር ራሱን የሳተ ሰው ብዙ ያልማል . . . ህልሙን እውነት አድርጌ ይህችን ከርታታ በአጉል ተስፋ ማባዘኔ » ሲሉ በሃሳባቸው አብሰለሰሉ ፡፡

እስቲ ደግሞ እዚህ ቡና ቤት ልግባና ልጠይቅ ፡፡ በይበልጥ የቡና ቤት ሠራተኞች ሊያውቁ ይችላሉ » ብሎ የያዘውን ዕቃ ለሕሊና ሰጥቶ ፈጠን ባለ እርምጃ ወደ ቡና ቤቱ አመራ ፡፡ ቡና ቤት እንደገባ ከፊት ለፊት አንድ ብቸኛ ወንበር ላይ የተቀመጠች ረዘም ያለች መልከመልካም ሴት ልጅ ጋ ጠጋ አለ ፡፡

« ይቅርታ እህት ሰው ለመጠየቅ ነበር ፡፡ . . . ወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል ታውቂ እንደሆነ ብትረጂኝ ? » ሲል ጠየቃት ፡፡

አስተናጋጅዋ ትኩር ብላ ተመለከተችው « አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል የለም ፡፡ ነገር ግን ወ/ሮ አባይነሽ የሚባሉ ቡና ቤት ያላቸው አውቃለሁ » አለችው ፡፡ ያሬድ በደስታ ተሞላ ፡፡ ልቡ ውስጡ ዘለለች፡፡ የሆነ ሲቃ ያዘው ፡፡ « ሊሆን ይችላል ፡፡ ለነገሩ የምፈልገው ፅሁፉን ሳይሆን የቡና ቤቷን ባለቤት ነው ፡፡ የምታውቂ ከሆነ ባለውለታዬ ትሆኚያለሽ » አላት በጉጉት ውጪ ውጪውን እያየ ፡፡ ለሕሊና ለመናገር ተጣድፏል ፡፡

ልጅቱ አትኩራ ያሬድን እየተመለከተች « ለመሆኑ ለምን ትፈልጋቸዋለህ ? » የጥርጣሬ ሁኔታ ከፊቷ ይነበባል ፡፡

ያሬድ አንገቱን ወደ ጎን ደፋ አድርጎ ፤ ገና መውጣት የጀመረ ፂሙን እየዳሰሰ በፈገግታ ልጅቷን እየተመለከተ « ከገጠር የመጡ ዘመዶቻቸው ስለሚፈልጓቸው ነው » አላት ፡፡

« የትኞቹ ናቸው ? » አለች ፡፡ ያሬድ ጥያቄዋን ለመመለስ ወደ በሩ ሲሄድ ከኋላ ተከተለችው ፡፡ በሩ ላይ ቆም ብሎ ራቅ ብለው የቆሙትን ወ/ሮ በላይነሽንና ሕሊናን አመለከታት ፡፡ ልጅቷ ያየችውን እንዳመነች ሁሉ ፈገግ ብላ ያሬድን ከላይ እስከታች እየተመለከተች « እኔ እንደነገርኩህ እንዳትነግራቸው ዋ ! » አመልካች ጣቷን በማስጠንቀቂያ መልክ ካሳየችው በኋላ « ቡና ቤቱ ሾፌሮች ነው የሚባለው ያውልህ ! ከዛ ከግንብ ቤት አጠገብ ያለው ቢጫ ቀለም የተቀባው ነው » አለችው ፡፡

ያሬድ ክልቡ አመስግኖ ወደ እነ ሕሊና ሮጠ ። « አገኘሁት ! ተከተሉኝ እንሂድ » አላቸው ። ወ/ሮ በላይነሽ ጆሮአቸውን አላመኑም። « አገኘሁ - - ት ? የት ነው ? እዚሁ አቃቂ ? » ቁና ተነፈሱ ።

« አዎን እዚሁ ነው ። የተሳሳትነው የቡና ቤቱን ሥም ነበር። በእውነትም አባይነሽ ቡና ቤት የሚባል በአካባቢውም የለም ። ስሙ አባይነሽ ሳይሆን « ሾፌሮች ቡና ቤት » ነው የሚባለው » አላቸው ።

« አይ አለማወቅ ! ድሮውንም ያልተማረ ሰው ምን ያውቃል . . . የተማረ ይግደለኝ » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ ።

ሕሊና በሀሳቧ የዚህን ቅን ልጅ አንደበትና ደግነት እያደነቀች በሌላ በኩል የራሱን ሥራ ትቶ ከነሱ ጋር ለምን እንደሚንከራተት እያሰላሰለች « ምነው ወንድሜ በሆነ ። እሱን የመሰለ አንድ ወንድም ቢኖረኝ እንዲህ ግራ ባልተጋባሁ ነበር ። በውስጤ የታመቀውን ጥያቄ ሁሉ አውጥቼው መልስ ባገኘሁለት ነበር ። ምን ያደርጋል አልታደልኩም» አለች ሕሊና ለራሷ የያሬድ መልካም ሥራ ከአቅሟ በላይ ሆኖባት ። የተባለው ቡና ቤት እንደደረሱ « ይህ ነው ቤቱ ፤ ግቡና ጠይቁ ፤ እንግዲህ እኔ የቀጠሮ ሰዓቴ እየደረሰ ስለሆነ ልመለስ» አላቸው ያሬድ ።

ወ/ሮ በላይነሽ እጃቸውን ፊት ለፊታቸው ወደ ሠማይ ዘርግተው « በል እንግዲህ ልጄ ብድርህን እንዱ አምላክ ይክፈልህ ፤ ይቅናህ ፤ ከክፉ ቀን ይሰውርህ » በማለት ደጋግመው መረቁት ። ሕሊና ያሬድ ያሬድ ሁለቱንም ተሰናብቷቸው ወደመጣበት ተመለሰ ። ሕሊና ያሬድ እርቆ እስኪሄድ በዓይኗ ተከተለችው ። ዓይኖቿን ከሄዱበት የመለሱት ወ/ሮ በላይነሽ ነበሩ ።

« በይ እንግዲህ ሕሊና አንቺ እዚህ ሆነሽ ጠብቂኝ ። እኔ ልግባና ላረጋግጥ » አሏት ። ሕሊና እሽታዋን በጭንቅላቷ ንቅናቄ ገልፃ ዓይኗን ወደ ያሬድ መለሰች ።

* * *

ሕሊና ፣ ያሬድ ከዓይኗ ርቆ እንደጠፋ በልቧ « ደህና ሁን ! ይቅናህ » አለችው ። ከዚያም በሁለት እግሮቿ መሀል ከረጢቷን አጥብቃ ይዛ ከቡና ቤቱ ወጣ ገባ የሚሉትን ሰዎች ቀና እያለች ማስተዋል ጀመረች ። ጥቂት እንደቆየች ወ/ሮ በላይነሽ ከአንድ መሀከለኛ ወፍራም ሴት ጋር ሆነው ከቡና ቤቱ በር ሲወጡ አየች ።

« ተዋወቂያት ሕሊና የአክስትሽ ሠራተኛ ናት ። አክስትሽ እቤት የሉም አሉ ። እስከሚመጡ ከሷ ጋር ትቆያለሽ » አሏት አጠገቧ እንደደረሱ ። ወፍራሟ ሴትም ሕሊናን ትከሻዋ ላይ ዳበስ አድርጋ ፤ ወደራሷ ፊቷን አዙራ ፤ ከንፈሯን እየመጠጠች ለስለስ ባለ አነጋገር ፤

« ማን አሉሽ ስምሽን ማሚት ? » ስትል ጠየቀቻት ። ሕሊና መሬት መሬቱን በሀፍረት አየች ።

« ሕሊና » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ የሕሊናን ፍርሃት አስተውለው። ወፍራሟ ሴትም ፤

« አዎ እናትሽን ወ/ሮ ወርቂቱን አውቃቸዋለሁ ። ቁርጥ በአካል እሳቸውን እኮ ነው የምትመስለው በአባቴ አምላክ ! አዎ ባለፈው ሁለት ወር ነው መሰለኝ አባትሽ ሽማግሌዎች ልከው ነበር ። እትዬ . . . » ትንሽ በሀዘኔታ አሰብ አድርጋ « አዎ እትዬን አነጋግረዋቸዋል ። መልሱን እንኳ አላውቀውም ። » ከንፈሯን ደጋግማ መጠጠች « ምን መንገድ ላይ አቆመን ኑ እንግባ » አለችና ከሕሊና ስር የተቀመጠውን ዕቃ አንስታ መራቻቸው ። ሁሉም

ተያይዘው አልቤርጎውን በትይዩ ታከው በመኖሪያ ቤቱ ጠርዝ በኩል በጓሮ በር ወደ ውስጥ ገቡ ::

« እዚህ ተቀመጡ » በማለት ወፍራሟ ሴት በዕቃና በጠርሙስ የተጨናነቀ ክፍል ውስጥ መቀመጫ ወደ አለበት እያመለከተች አረፍ እንዲሉ ጋበዘቻቸው :: ሕሊና በጣም ተጸከማለች:: ካፊያው በላያቸው ላይ ነበር ያለቀው :: በቤቱ ውስጥ የተዳፈነው የእልከል ሽታ ሕሊናን አልተስማማትም ::

ሴትዬዋ « ምን ይምጣላችሁ ? ቡና ወይስ ሻይ ? » ስትል ወ/ሮ በላይነሽንና ሕሊናን ጠየቀች :: ሕሊና ሻይ ፣ ወ/ሮ በላይነሽ ደግሞ ቡና እንደሚሻላቸው ተናገሩ :: በሩ ላይ ቆሞ ሲያዳምጥ ለነበረው ዘበኛ « ፈሩቅ ሁለት ቡናና አንድ ሻይ ይዘህልን ና ለማርታ አስካበች ናት ያለችው በላት :: » ትዕዛዝ ሰጥታ የሕሊናን ዓይን ዓይን መመልከት ጀመረች ::

ሁሉም በዝምታ ተፋጠው የቀረበውን ሻይና ቡና ጠጥተው እንደጨረሱ በመካከል ከውጭ የመኪና ጡሩምባ ድምጽ ተሰማ :: አስካበች ከመቀመጫዋ ብድግ ብላ « እትዬ መጡ ፤ በሉ እንግዲህ . . . » በማለት የጀመሩትን ሳይጨርሱ በፍጥነት ከክፍሉ ወጣች ::

ወ/ሮ በላይነሽና ሕሊና ፊታቸው ላይ የመሸበርና የፍርሃት መልክ ቢታይባቸውም « አይዞሽ እንግዲህ ደርሰሻል :: የምታይው ሀብት ሁሉ እንኳን ለአንቺ ቀርቶ ለባዕድም ይተርፋል » ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ ሕሊናን አፅናኗት :: ሕሊና ግን ፣ የምታየውና የምትገምተው ሀብት ሁሉ አላማራትም :: ያው የነበረችበት የድህነት ኑሮዋ ይሞቃት እንደነበር ተሰማት :: ሆድ ባሳት :: ዓይኖችዋ እንባ አዘነቡ ::

ወ/ሮ በላይነሽ « ምነው ነውርም አይደል ! በእንግድነት መጥቶ በደስታ ቤት ሀዘን ማምጣት ? በይ ዝም በይ ልጄ ! » ሲሉ ሊያበረታትዋት ሞከሩ :: በዚህ መካከል አንድ በጣም ወፍራም የሀበሻ

ቀሚስ የለበሰ ዘመናዊ ሴት በሩን ሞልተው እንደቆሙ ወደ ክፍሉ ውስጥ አማተሩ :: « ትንሽ ቆይተዋል ፤ ቤቱ ጠፍቷቸው በፍለጋ ነው ያገኙት » በማለት ሰትፈራ ስትቸር አስካበች ከኋላቸው ሆና ተናገረች ::

ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ለሠላምታ ከተቀመጡበት ተነሱ :: ወ/ሮ አባይነሽ ሕሊናን ከእግር እስከ እራሷ አትኩረው እየቃኟት ወ/ሮ በላይነሽን « በግዜር ይቀመጡ ይቀመጡ » አሉና ፈሩቅ ወንበር እንዲያመጣላቸው አዘዙት :: ያዘዙት መቀመጫ እንደመጣ ከወ/ሮ በላይነሽ አጠገብ ተቀመጡ :: ያቺ ክፍል የዝምታ ጫና ወረደባት ::

አስካበች ዝምታው ሰላልጣማት ፣ ሕሊናን እየተመለከተች « እትዬ ወርቂቱን አትመስልም ? አብሶ የፀጉሯ ነገር በጣም ይገርማል » አለች ::

« ወደ ሥራሽ ሂጂ ! ሥራ ፈት » አሏት ወ/ሮ አባይነሽ በቁጣ :: አስካበች ሹልክ ብላ ወጣች :: ሕሊና ውስጧ ተረበሸ ፤ ሰውነቷ ሲሸማቀቅ ታወቃት :: አክስቷ ኃይለኛና ቁጡ እንደሆኑ ፣ ለእሷ እንደማይመቹ ገመተች :: አባቷን አሰበች ::

« እንግዲህ ከመጣሽ ደህና :: ግን አባትሽ ጨከኖ እንዴት ላከሽ ? » ሲሉ ወ/ሮ አባይነሽ የሕሊናን ከረጢት እየተመለከቱ ያልታሰበ ጥያቄ አቀረቡ :: « አይ-ይ ነገሩስ ወዲህ ነው ! » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ የሕሊናን ፊት የጎድን እያዩ ወዲያው እንባቸው ዓይናቸው ላይ አቀረረ :: ቀጥለውም ሲፈሩ ሲቸሩ የአባቷን ሞት በማሳዘን ለወ/ሮ አባይነሽ አረዷቸው ::

« ድሮውንም ብዬ ነበር :: ያቺ ከላባ እናቷ ከማይሆን ሰው ጋር ፍቅር ፍቅር ብላ እንደከበት ከደህና ቤቷ ስትኮበልል ፣ እስኪ ምን አሰኛት ? የምትበላው ፣ የምትጠጣው ሳታጣ » :: ሕሊና የአክስቷን ክፋት ቀደም ብላ ከአባቷ አነጋገር ስለተረዳች አልገረማትም:: አክስቷ በእባቷ ላይ ስለነበራቸው ጥላቻ አባቷ

« አትፍረጂባት » ብለው የነገሯት ትዝ አላት ። ግን ምንስ ቢሆን ከሥጋቸው ወልዷል ። ወ/ሮ አባይነሽ መርዶውን ሰምተው እንባ ያለማፍሰሳቸው ቢገድም ለይስሙላ አለማዘናቸው ለሕሊና እንቆቅልሽ ሆነባት ። ይህን የተገነዘቡት ወ/ሮ በላይነሽ ሁኔታውን ለማረጋጋት የአባቷን ኑሮ ፣ የሞተበትን ሁኔታ ከንፈር እየመጠጡ አስተዛዝነው ቢነግሩም ያሰቡት ሊሳካላቸው አልቻለም ።

« እንግዲህ እሷም ልጃችን ናት ፣ እየመጣን እንጠይቃለን ፣ እሷም እየመጣች ትጠይቀን ፣ እኔም ይመሽብኛል ወደቤቴ ልግባ » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ ።

« በሉ እንግዲህ አባቷ ካሉት ሀብቶቹ እሷን ካወረሰኝ ስልጡን አርጌ አሳድጋታለሁ ፣ እሷም እንደእናቷ እስከምትከበልል ። ግን ከእንግዲህ ዘመድ አለኝ ብላ ወዲያ ወዲህ መሽከርከር የለባትም ። እናንተስ ምን በወጣችሁ በሰው ዲቃላ እዚህ ድረስ የምትለፉት ። እሷስ ከእንግዲህ ምን ይከፋታል ብለው ነው ? » በማሾፍ እየተናገሩ ከመቀመጫቸው ተነስተው ፈሩቅን ተጣሩ ። ፈሩቅ አፍታም አልቆየ። ትዕዛዝ ለመቀበል ከወ/ሮ አባይነሽ ፊት ከመቆሙ ፣

« በል እንግዲህ እሳቸው እ - ወ/ሮ . . . »

« በላይነሽ » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ እራሳቸውን በማስተዋወቅ ዓይነት ።

« እዎ ወ/ሮ በላይነሽን ሸኛቸው ፤ በዛውም አስካበችን ጥራልኝ » አሉት ።

ወ/ሮ በላይነሽ በሀዘንና በማጽናናት ዓይን ሕሊናን እየተመለከቱ ከመቀመጫቸው ተነስተው ወደ በሩ ሲወጡ ሲጠጉ ሳያስቡት ከኋላቸው ሕሊና እንገታቸው ላይ ተጠምጥማ እየተንሰቀሰቀች አለቀሰች ። የእንባዋ እፈሳሰስ እስከወዲያኛው ይመስል ነበር ። ወ/ሮ በላይነሽ ዞር ብለው ሕሊናን በጉያቸው አቅፈው አይዞሽ ! አይዞሽ እያሉ ለማጽናናት ሲሞክሩ ከቁጥጥራቸው

ውጭ በሆነ ሁኔታ እንባቸው እርግፍ እርግፍ ሲል ለስለስ ያለ ድምፃቸውን አሰሙ ።

« ምነዋ እቴ ! በቤቴ ጉሪ ፈቻ ባትሉብኝ ፣ አታልቅሱብኝ ! ምነው እርሶ ደግሞ ትልቅ ሰው አይደሉም እንዴ ? » ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ ላይ ጮኹባቸው ።

« እመይቴ ! እመይቴ ! በህይወቴ እንደዚህች ልጅ የምወደውን ማህፀኔ ለማፍራት አልታደለም ። ልጂ እኮ ነች ልጂ ! ልጂ ! በማልቀሳችን አይፍረዱብን » ሲሉ ተማፀኗቸው ።

* * *

ቀጠሮው ቦታ ቀድሞ የደረሰው ሀሰን ነበር ። ከቤቱ ሲወጣ የሆነ ነገር እየተጫጫነው ፣ እየቀፈፈው ቢሆንም የጓደኛው ማርፈድ ደግሞ ብሽቀቱን ጨመረበት ።

« አይሞላልህ ! ዛሬ ደግሞ ምን አጋጠመኝ ልትል ይሆን ይህን ያህል ያረፈድከው ? » ሲል ፀጋው ላይ በቁጣ ጮኸበት ።

« አንተ የደላህ ነህ ወንድሜ ፣ . . . ይልቅስ ሰዓት እንዳያልፍብን እንፍጠን » አለና ወደፊት ተራመደ ፀጋው ። ቃል ሳይለዋወጡ የሚፈልጉበት የአውቶቡስ ፌርማታ ደረሱ ።

« እመቤት ዘጠኝ ቁጥር አውቶቡስ አልፋለች ? » ሲል ፀጋው ከፌርማታው የነበረች መልከመልካም ወጣት ጠየቀ ።

« ከመጣሁ አላየኋትም » ስትል ባጭሩ መለሰችለት ።

ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም ። ፌርማታው ውስጥ የሆነ ጥግ ቦታ ፈልገው ተቀመጡ ። « እንዲያው ለነገሩ እንኖው ብለን ካልሆነ እስከአሁን ዘመድ ሳይከቱበት ቀረ ብለህ ነው ? » አለ ሀሰን ።

« አንተ ደግሞ አንድ ነገር ሳትጀምር ለመጨረስ ትሮጣለህ !» አለው በቁጣ ።

« በእስከዛሬው ድካማችን . . . » ዝም አለ ሀሰን ::

በመካከል ይጠብቁት የነበረው አውቶብስ መጣና እየተጣደፉ ተሳፈሩ :: ከተሳፋሪው ጋር ተቀላቅለው ጉዞአቸውን ቀጠሉ :: አውቶቡሱ በየፌርማታው እያቆመ ገቢና ወጪውን ሲያስተናግድ ከቆየ በኋላ እንደ ድንገት ያልጠበቁት ጩኸት ተሰማ :: አውቶብሱም እንደሰካራም ወዲያና ወዲህ ተንገጫግጮ የሚዘገንን ድምፅ በማሰማት ቀጥ አለ :: ተሳፋሪው እርስ በእርሱ እየተያየ አጉረመረመ :: ኡኡታ ተሰማ :: ሁሉም ኡኡታው ወደመጣበት አቅጣጫ አስተዋለ :: እነ ፀጋው በአሉበት አካባቢ አንድ በመሀከለኛ ዕድሜ የሚገኝ ጋቢ የለበሰ አጠር ያለ ሰውና የለበሰውን ኮት ግማሽ ድረስ በማውለቅ ደረቱን ገልብጦ የሚቀልድ ከሚመስል ሰው ጋር ይጨቃጨቃሉ :: ጋቢ የለበሰው ጀንበሬ ደርብ ይባላል ::

የደብረታቦሩ ልጅ ይገፍሃለሁ ! መልሳት ! አለቅህም ዛሬ ደምህ ከደሜ ! » እያለ ጀንበሬ ይጮሀል :: ኮት የለበሰው የተሳፋሪውን ዓይን ለመሳብ እየሞከረ « ምን አድርግ ነው የሚለኝ ፣ እባካችሁ አላቁኝ :: እብድ ነው እንዴ ? » አለ ስቆ ለማሳቀም ፈገግ ብሎ :: ሁኔታቸው ገብቶት የነበረው ሹፌር ዞሮ መጥቶ እጁን ወደኮት ለባሹ እየጠቆመ « መልሳት ! መልሳት ነው የምልህ » አለው ::

« ያልወሰድኩትን ከየት አመጣለሁ » ሲል በሹፌሩ ላይ ተሳለቀ:: ሾፌሩም በእልህና በንዴት ኮት የለበሰውን አንድ በአንድ ኪሱን ይፈትሸው ጀመር :: ምንም ነገር ሊያገኝ አልቻለም ፤ ከአንድ አንድ ብጣሽ ወረቀትና የተለያዩ ጨርቃ ጨርቆች በስተቀር :: ሾፌሩ ፍተሻውን እንደጨረሰ ጋቢ ለባሹን መለስ ብሎ እያየ « ቀደም ብለው ጥለውት ይሆናል :: እንደአየሁት ይህ ሰው ገንዘብምን አልወሰደም » አለና በአካባቢው ያሉትን ሰዎች ተመለከተ :: በዚያው ሁኔታ ጋቢ ለባሹ የሹፌሩን ዓይኖች ተከትሎ ዙሪያውን በአጠሩት ሰዎች ላይ

ዓይኖቹ ተንቀሳቀሱ :: ድንገት ዓይኖቹ ሀሰን እና ፀጋው ላይ ሲደርሱ እይታቸው ተገታ ::

« ብሬን ! ሰዎች ጉድ ሆንኩ እኮ ! ተዘረፍኩ :: » ብሎ ሀሰንን እና ፀጋውን ልብሳቸውን ጨምድዶ ያዛቸው :: « ብሬን ሞልሱልኝ » በማለት እሪታውን አቀለጠው :: »

* * *

ጠረጴዛ ላይ ተቀመጠ ፊት ለፊቱ የነበሩትን ሁለት ሰዎች በማነጋገር ላይ ያለ የደንብ ልብስ የለበሰ ፖሊስ ካለበት ክፍል ጋቢ ለባሹ ፣ ፀጋውና ሀሰን በፖሊስ ታጅበው ገቡ :: አጃቢው ፖሊስ ወታደራዊ ሠላምታ ከሰጠ በኋላ « እነኚህ ሁለት ወጣቶች ከዚህኛው ሰው ሁለት መቶ ብር ሰርቀዋል ስለተባለ አምጥቻቸዋለሁ» ሲል ወደዝርዝሩ ሳይገባ በአጭሩ ተናገረ :: ከዚያም እስረኩቦ ወጣ :: እሰቃው ቀደም ሲል አብረውት የነበሩትን ሁለት ባለጉዳዮች « በኋላ እንቀጥላለን » ብሎ ውጭ እንዲቆዩ አሰናብቶ ፊቱን ወደ እንግዶቹ መለሰ ::

« እንዴት ነበር ዘረፋው » አለው ባለ ጋቢውን ::

ፀጋው ቀደም ብሎ ሁኔታውን ለማስረዳት ሲሞክር ፖሊሱ « አንተን የጠየቀህ የለም ፣ ዝም በል » ሲል ገሰፀው :: « ጌታዬ ቢፈተሹ አሁንም የዘረፉት ሁለት መቶ ብሬ በእጃቸው ይገኛል » ሲል ጋቢ የለበሰው ወደ ሀሰን እጁን በመጠቆም እንዲፈተሹለት ተማፀነ ::

« ታዲያ ለምን አትመልሱም ? ሲነቃባችሁም አታውቁም ?» አላቸው ፖሊሱ ጎርነን ባለ ድምፅ እነ ፀጋውን ከአንዱ ወደ ሌላው እየተመለከተ ::

ፀጋው ለመናገር በጉጉት ዕድል ሲጠብቅ ነበረና አጋጣሚውን ተጠቀመበት :: « ጋሼ እኛ አልሰረቅንም :: ሰውየው ከኛ በፊት ሌላ

ሰው ሰርቆብኛል ብሎ አውቶቡሱ ውስጥ ሲጮህ ነበር ። እኛ ስንወርድ ምን እንዳሰበ አናውቅም እኛን ሰርቃችሁኛል ብሎ አስያዘን ? » በማለት በማሳዘን ስሜት ለማስረዳት ጣረ ።

« ለመሆኑ ስራችሁ ምንድነው ? » ሲል ጠየቃቸው ፖሊሱ።

« ለጊዜው ሥራ የለንም ። በዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ነበርን ። ዛሬ ሥራ ለመቀጠር የፈተና ቀጠሮ ስለነበረን ወደ አቃቂ ለመሄድ ስንል ነው ይህ ጉድ የገጠመን » ሲል ሀሰን መለሰለት ።

« የተሰረቀብህ ዝርዝር ብር ነው ጥቅል ? » ሲል ፖሊሱ ባለጋቢውን ጠየቀው ።

« ሚስቴን ሆስፒታል አስገብቼ ለድንገተኛ ከሀገሬ ከደብረታቦር ያመጣሁት አራት ባለ ሃምሳ ጥቅል ብር ነበር » አለ ።

ፖሊሱም ሀሰንን « ና ወደዚህ ቅረብ ። ኪስህ ውስጥ ያለውን ዕቃ እዚህ ላይ አስቀምጥ » ወደ ጠረጴዛው ጫፍ በጁ እያመለከተ አዘዘው ።

ሀሰን ከላይኛው ከኮት ኪሱ ጀምሮ ያሉትን ሁሉ እየፈተሸ በውስጣቸው የሸከፉትን ዕቃ እያወጣ አስቀመጠ ። ከኪሱ ሁለት ዝርዝር ብርና ሳንቲሞችን አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ ሲያስቀምጥ አንድ ስሙኒ ከእጁ አምላጦ ወለሉ ላይ ወደቀ ። ለማንሳት ጎንበስ ሲል ፖሊሱ « ግድ የለም ተወው » አለውና ወደ ባለጋቢው ዞሮ ፣

« ለመሆኑ ሥምህ ማን ይባላል ? » ሲል ጠየቀው ።

« ጀንበሬ ይባላል ጌታዬ ፤ጀንበሬ ደርብ » ሲል በማስተዛዘን ደጋግሞ መለሰለት ።

« በል አቶ ጀንበሬ የወደቀውን ሳንቲም አንስተህ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጥ » አለውና ፍተሻውን ቀጠለ ። በመጨረሻም « በል ሱሪህን ፍታ» ሲል ሀሰንን አዘዘው ። ሀሰን የታዘዘውን ፈጸመ ። ፖሊሱ ፀጋውንም ፈተሸ ። የተሰረቀው ገንዘብ ሲገኝ አልቻለም ።

ፀጋው ኪስ ውስጥ የተገኘው አንድ ባለ አምስት ብር ኖትና ሃያ ሳንቲም ብቻ ነበር ።

ፖሊሱ ጣቱን አፍንጫው ላይ አስሞርክዞ ትንሽ ከተከዘ በኋላ « ለመሆኑ ቀደም ሲል ሰረቀ የተባለው ሰው ምን ዓይነት ነው » ሲል ጠየቃቸው ።

« አጠር ያለ ፣ ጠይም ፣ አለባበሱ ዘመናዊ ፣ ቂም ያለውና ፊቱ ላይ ከግንባሩ ገደማ ጠባሳ ያለው ነው » ሲል ሀሰን ለመግለጽ ሞከረ ።

« የሰውየው አለባበስ ምን ይመስላል ? » ሲል በድጋሚ ጠየቀ ።

« በጣም ደህና ነው ። ከላይ እስከታች ሱፍ ነው የለበሰው ። ሠዓትና ትልቅ የወርቅ የጣት ቀለበት ያደረገም ይመስለኛል » በማለት ፀጋው መልስ ሰጠ ።

ፖሊሱ ሥዕላዊ መግለጫውን በአምንታ መልክ ራሱን እየነቀነቀ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ እነ ፀጋውን ዕቃቸውን እንዲወስዱ አዘዘ ።

ቀጥሎም « አቶ ጀንበሬ ሌባውን ለቀውታል ። ይህ የተባለው ሰው በዘጠኝ ቁጥር መስመር የታወቀ ሌባ ነው ። በሉ እናንተ ሥማችሁንና አድራሻችሁን ስጡና ወደ የስራችሁ ሂዱ » ሲል አሰናበታቸው ።

« በምንም ዓይነት ! ዘራፊዎቹን መልቀቅዎ ትክክል አይደለም ! ተዘርፌ ልቀር !» እያለ እጆቹን ራሱ ላይ አድርጎ « ጉድ ነው ! ጉድ ነው ! » ሲል ባለጋቢው ጀንበሬ ጮኸ ።

« አዳምጥ አቶ ጀንበሬ ! » አለው ፖሊሱ « እኛ ሰዎችን ከሜዳ ላይ ለብሰበን ሌቦች ብለን አናስርም ። ሌቦች ያልካቸው ሰዎች ለሌብነታቸው ማስረጃ የሚሆን ምንም ተጨባጭ ነገር ስለአልተገኘ ባቸው ወንጀላቸው ግልጽ አይደለም ። ከፈለክ ሰርቀውኛል ስትል

ፋይል ከፍተህ ከለህ አስመስክር » ሲል የመጨረሻውን ትዕዛዝ አዘል ቃል ገለፀለት ። እነ ፀጋው ዕቃቸውን ሰብስበው ፖሊሱን አመስግነው ቢሮውን ለቀው ወጡ ።

ፖሊስ ጣቢያውን አለፍ እንዳሉ ፀጋው « እንደርሳለን ብለህ ነው ? » ሲል ጥያቄ አቀረበ ። « ትራንስፖርት በቶሎ ካገኘን እንደርሳለን ። የቃል ጥያቄ ስለሆነ ሌሎቹ እስከሚፈተኑ ይቆያል » አለው ሀሰን ።

« ጠዋት ስንነሳ ባትለክፈኝ ኖሮ ይህ ጉድ አያጋጥመንም ነበር። » ሲል ፀጋው እየቀለደበት መንገዳቸውን ተያያዙት ። አቃቂ አውቶቡስ ማቆሚያ እንደደረሱ የሞላ መኪና አጋጠማቸው ። የተሳፈሩበት መኪና አቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ፊት ለፊት እስኪደርስላቸው በገጠማቸው ሁኔታ ውስጥ ነበሩ ። ከመኪና ወርደው ልብሳቸውንና ፀጉራቸውን እያስተካከሉ ፋብሪካው ዋና በር እንደደረሉ የደንብ ልብስ ያጠለቁ ሰው ከበሩ ኋላ ቆመው « ወዴት ነው ? » ሲሉ ድምፃቸውን ጎተት አድርገው ጠየቋቸው ።

« የፈተና ቀጠሮ ነበረን ፣ ወደ አስተዳደር ቢሮ ነው የምንሄደው » ሲል ፀጋው መለሰላቸው ።

« ጠብቁ » ብለው ከበሩ አጠገብ ወደ አለው አንድ ትንሽ ቤት ሄደው ትንሽ ቆይተው እንደተመለሱ ትንሿን በር ከፍተው ሁለቱንም በደንብ ፈትሸው « በዚህ በኩል ሂዱ » ብለው አቅጣጫውን በያዙት አጭር ዱላ አመለከቷቸው ።

ለመግባት በመቻላቸው እየፈነደቁ መንገዱን በፍጥነት ተያያዙት ። የልባቸው ምት ጨምሮ ነበር ። አስተዳደሩ ቢሮ ሲደርሱ ከበሩ አጠገብ ግድግዳ ተደግፈው የቆሙ ሦስት በነሱ ዕድሜ የሚገኙ ወጣቶችን አስተዋሉ ።

ሀሰን ከሦስቱ ወደ አንዱ ወጣት ትኩር ብሎ ተመልክቶ « ያሬድ ደግሞ መቼ መጣ ? » ሲል ፀጋውን ጠየቀው ። ፀጋውም

ሀሰን ወደሚመለከተው ሰው አንገቱን ቀና አድርጎ ተመለከተ ። ሁለቱ ተያይዘው ወደ ያሬድ አመሩ ።

ያሬድ የትምህርት ቤት ጓደኞቹን በማግኘቱ ደስ አለው ። እጆቹን በሰፊው ዘርግቶ « ከየት ተገኛችሁ እነ አጅሬዎች » በማለት የእንኳን ደህና መጣችሁ ፈገግታውን በፊቱ ላይ ስሎ ተቀበላቸው ።

« እንዴት ነው ? የቃል ጥያቄውን ጨረሳችሁ ? » ሲል ሀሰን ያሬድን ጠየቀው ።

« ማለቅስ አልቋል ። የሚቀበሉኝ አልመሰለኝም እንጂ እዚሁ ቆይ ተብዬ ነው የምጠባበቀው » አለ ። ቀጥሎም « እንደምታውቀው አብሮን የመጣ ዜድ ሳይኖር አይቀርም »

« አይ እናንተ ምነው መጨረሻውን ለማየት ያብቃን ብትሉ፣ ለመሆኑ ስንት ሰው ነው የሚፈልጉት » አለ ፀጋው በሁለቱ ንግግር መሀል ጣልቃ ገብቶ ።

« የሚፈለገው ሁለት ሰው ነው ። ለቀለም ክፍል አንድ ሰው ለዲዛይን ክፍል አንድ ሰው » ሲል መለሰለት ያሬድ ።

« በዚህ ዓይነት ኬሚስትሪ የወሰደና የኢንጅነሪንግ ተማሪ ነዋ የሚፈልጉት » ሲል ሀሰን በውስጡ ተስፋ ይዞ ተናገረ ።

« በል እንግዲህ እንጂነየር ሀሰን ሥራ ተገኘልህ » አለው ፀጋው በፌዝ አነጋገር እጁን ለመጨበጥ እየዘረጋ ።

« እባክህ አታሹፍ ሥራ አተዋል እኔን ሲቀጥሩ . . . ለመሆኑ እናንተ ብቻ ናችሁ እስከአሁን ቃለ-መጠይቁን የወሰዳችሁት ? » ሲል ሀሰን ያሬድን ጠየቀው ።

« ጠዋት እዚህ የቀረቡ ብዙ ሰዎች ነበሩ ። ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ ሥማችን ተጠርቶ ለቃለ መጠየቁ የቀረብነው አስር ብቻ ነን ። [illegible]ብ አላልናችሁም እንጂ የናንተም ሥም ተጠርቶ ነበር » ከማለቱ ከቆመበት በር አጠገብ አንድ ረዘም ያለ ባለቢም አፍሮ ወጣት ብቅ ሲል አንዲት መልከ መልካም ወጣት ግማሽ ሰውነቷን ከበሩ ወጣ

አድርጋ « ፀጋው ወልደ አማኑኤል አንተ ነህ ? » ስትል ከበሩ አጠገብ ቆሞ ይመለከታት የነበረውን ሰው ጠየቀችው ። ፀጋውም ከነበረበት ፈንጠር ብሎ « አቤት እኔ ነኝ » ሲል ተናገረና ወደ ውስጥ ገባ ።

ሀሰን ከፀጋው ጋር በጠዋት ስለአጋጠማቸው ዱብእዳ በሥዕላዊ መልኩ በመግለጽ ለያሬድ ሲያጫውተው ሩብ ሰዓት ያህል ካለፈ በኋላ ያስተዳደሩ ቢሮ ተከፈተ ። ፀጋው ከውስጥ ወጥቶ ራሱን በሀዘኔታ መልክ እየነቀነቀ ከጓደኞቹ ጋር ተቀላቀለ ።

የቅድሟ ወጣት በእጇ የያዘችውን ወረቀት መልከት አድርጋ « ሀሰን መሀመድ » ብላ ተጣራች ። ምላሽ አጣች ። ለሁለተኛ ጊዜ ተጣራች ። አቤት ባይ አልነበረም ።

« ሀሰን ስቁር እንዳይሆን ? » አለ ሀሰን ። ወጣቷም ሀሰንን በንቀት ዓይን ገላምጣ ለሦስተኛ ጊዜ « ሀሰን መሀመድ » አለች ። ማንም መልስ እንዳልሰጠ ካረጋገጠች በኋላ « አበራ ወ/ማሪያም » ስትል ሦስት ጊዜ ደጋግማ ተጣራች ። አሁንም መልስ የለም ። ሶስተኛው ተጠራ ፣ ገብረየሱስ አለማው ነበር ። ሥሙ እንደተጠራ መኖሩን አሳውቆ ከወጣቷ ጋር ወደ ውስጥ ገብተው በሩ ተዘጋ ።

ፀጋው ፣ ያሬድና ሀሰን ስለቃለ-መጠይቁ መነጋገር ጀመሩ ። ፀጋው « ለምሳሌ እርጥብ ጨርቅ ቀለም ለመቀባት ምን እንደሚያስፈልግ ቢጠይቀኝ » ብሎ ሳይጨርስ ሀሰን መመለስ ጀመረ። ሀሰን በሰጠው መልስ ያሬድ እንደማይስማማ በመግለጽ ተከራከሩ ።

« ምን አስቸገራችሁ ! ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም » ብሎ ፀጋው ክርክሩን ለመግታት ሞከረ ።

« ተሳስተሃል ። ክረምት አንድ ብቻ አይደለም ። በማያልቁት ዓመታት ሁሉ ተደጋጋሚ ነው ። ካንተ ቀጥሎ ያለው ክረምት ሀሰን ነው መሰለኝ ። ቤት ያስፈልገዋል » በማለት ያሬድ ቀለደበት ። ወሬያቸው ሞቅ ብሎ ከአንዱ ወደ ሌላው እየተቀባበሉ ለአስር ደቂቃ

ያህል እንደቆዩ ያ ልማደኛ በር ወገግ ብሎ ተከፈተ ። መልከመልካሟ ወጣት ከወረቀቷ ጋር አልነበረችም ። ጠየም ያሉ ፣ መነፅራቸው ከአፍንጫቸው ላይ ደስስ ብሎ ሊወልቅ የደረሰ ፣ ጥቁር ሱፍና ከረባት ያደረጉ ፣ ፂማቸውን ሙልጭ አርገው የተላጩና ከሆዳቸው ገፋ ያሉ ሰው ነበሩ ።

« ጌታቸው ልሳን » ብለው ተጣሩ ፣ ፊታቸውን ዘቅዘቅ አድርገው በመነፅራቸው ጫፍ ወደ ፀጋው እያስተዋሉ ። መልስ የለም ደጋግመው ተጣሩ ። ቀጥለውም « ሀሰን ስቁርስ የለም ? » አሉ ።

« አቤት ! አለሁ ፣ እኔ ነኝ ። » አለ ሀሰን እየተቻኮለ ። ሰውየው ይዘውት ገቡ ። ፀጋው « ለምን ይሆን ? እኔም እንዳንተው ቆይ ተባልኩ እኮ » ሲል ያሬድን ጠየቀው ። እሱም ያለማወቁን ለማስረዳት ትከሻውን ከፍዝቅ በማድረግ መለሰለትና ከአዲስ አበባ ወደ እቃቂ ሲመጣ ስለገጠመው ሁኔታ ፣ ስለሕሊናና ፣ ስለ ወ/ሮ በላይነሽ፣ በስሜት ሆኖ ተረከለት ። ልቤን የነካኝ የኛ ደሀ ሴት ሁኔታ ነው ። እሳቸውን ስመለከት ያቺ ደሀ እናቴ ትዝ አለችኝ ። እስከ አሁን ምስላቸው ከሕሊናዬ ሊፋቅ አልቻለም » እያለ ሲያወራለት ልማደኛው በር ሀሰንን ወለደ ። ሀሰን ጓደኞቹን አዲስ እንደተገናኙ ሁሉ ሳይታወቀው ጠበቅ አድርጎ ጨበጣቸው ። ፀጋው ግራ በመጋባት « ምነው ማለፍህን ነገሩህ እንዴ ? » ሲል ጠየቀው ።

« ምን ማለፌን ይነግሩኛል ! በተቃራኒው አለማለፌን ገለፁልኝ እንጂ ! የሚቆረቁረኝ ለትራንስፖርት የከፈልኩት . . . አላልኩህም ! ጠዋት ወደዚህ ከመነሳታችን በፊት ነግሬህ ነበር እኮ !»

« እባክህ በመጥፎ ዕድል ቀለም አትቀባን ። ማን ያውቃል ከሁለት ዜድ ጋር አጣምረው አንድ ማወናበጃ ቢወስዱ » አለ ያሬድ እራሱን ለማፅናናት ያህል ።

ባለመነፅሩ አዛውንት ወረቀታቸውን እየተመለከቱ « ያሬድ እንዳሻው . . . ሀሰን ሰቂር . . . ፀጋዬ ተረፈ. . . . » ብለው ከጠሩ በኋላ የመጀመሪያውን ወረቀት ገልብጠው « ፀጋው ወልደአማኑኤል፣ እናንተ በሚቀጥለው ሰኞ እዚህ ቢሮ እንድትመጡ ። ሌሎቻችሁ ወደ ቤታችሁ መሄድ ትችላላችሁ » አሏቸው ።

ሀሰን ደስታ በተላበሰ አነጋገር « እኛ አልፈናል ማለት ነው ?» በፈገግታ ጠየቀ ለማረጋገጥ ጓጉቶ ። ባለመነፅሩ አዛውንት ምንም መልስ ሳይሰጡ ወደ መጡበት ተመለሱ ።

*　　*　　*

ወ/ሮ አባይነሽ ክፍሉ ውስጥ ሆነው ሕሊናን እየተመለከቱ ሲያስቡ « እትዬ ጠርተውኝ ነበር ? » ስትል አስካበች ገባች ።

« በይ ይህችን ልጅ ውሰጅና ልብሷን ለውጪላት ። ፀጉሯን ትታጠብ ፣ የሚበላም ስጧት ፣ የማደሪያ ቤቷን ደግሞ ካንቺ ጋር አሰናጅላት ። » ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ ። አስካበች « ነይ እንሂድ » በማለት እጅዋን ዘረጋችላት ።

ሕሊና ወለሉ ላይ የነበረውን ከረጢቷን ይዛ ፣ አስካበችን ተከተለች። አስካበች ለመስማት በማይቻል ድምፅ ታጉረመርማለች ። የሚከራየውን የመኝታ ክፍል አልፈው ከአንድ በቆርቆሮ ግድግዳና ጣሪያ የተሠራ ቤት ጋ ሲደርሱ አስካበች ከያዘችው ቁልፍ በአንደኛው የተዘጋውን በር ከፈተችው ።

የአስካበች ክፍል በጣም አጭርና ጠባብ ነበር ። ከክፍሉ በአንዱ ግድግዳ ትንሽ መስኮት በቆርቆሮ ተለጥፏል ። አስካበች መስኮቱን ከፈተችው ። ሕሊና ወደ ክፍሉ ገብታ ግራ ተጋብታ መሀል ላይ ቆመች ። ከክፍሉ በስተመጨረሻ በኩል አንድ ድንክዬ አልጋ አለ ። አንድ ወንበር ከአልጋው አጠገብ ቆሟል ። ግድግዳው

በተለያዩ የጋዜጣ ዕትሞች ተለብዷል ። በላዩ ላይ የተለያዩ ፎቶግራፎች ተለጥፈውበታል ።

« አባትሽ ክፉ ሰው ባይሆኑ ወደዚህ ሊልኩሽ አይገባም ነበር ። » አሰች አስካበች በመቆርቆር ስሜት ።

« አባቴ በህይወት የለም ። የሞቱ ሰዎች ደግሞ የሰሩትን መልሰው ማረም አይችሉም » አለቻት እንደድንገት ስለ አባቷ መነሳቱ መጥፎ ስሜት ጥሎባት ።

« እሱማ አውቃለሁ ! ወደዚህ እንድትመጪ መደረጉን ማለቴ እንጂ ! ። እየሽ እክስትሽ እዚህ በመምጣትሽ በጣም ተከፍተዋል ። እናትሽ ከዚህ ኮብልለው ሲሄዱ አንጀታቸው ቆርጦላቸው ነበር ። እናትሽ አባትሽን ባያገቡ ኑሮ ከእትዬ የማያንስ ሀብት በኖራቸው ነበር። ከመኮብለላቸው በፊት እቶ ካብትይመር አጭተዋቸው ነበር ። ግን ምን ያደርጋል እናትሽም ኮበለሉ ፣ እቶ ካብትይመርም ምን የመሰለ እመቤት አግብተው ተዋልደው ይኖራሉ » አለቻት ።

እስከዛሬ ድረስ ሕሊና የአባትና የእናቷን ጋብቻ በዚህ መልኩ አታውቀውም ነበር ። ከአስካበች አነጋገርም አባቷን እንደሚጠሉት ተገንዝባ ዕንባ ተናነቃት ።

« እንደኔማ ቢሆን ወደዚህ ለመምጣት ምኞት አልነበረኝም » አለችና ዝም አለች ።

« ሕሊና ከእንግዲህ አንድ ጊዜ መጥተሻል ። የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም ። ባይሆን እዚህ እስከኖርሽ ማወቅ የሚገባሽ ጉዳይ አለ። እዚህ ቤት የነፃ እንጀራ የለም ። ደም እየተፋሽ ቀንና ለሊት መስራት አለብሽ ። አክስትሽ ለዚህ ነው ንጹህ ልብስ እንዲሰወጥልሽ የፈለጉት» አለቻት ። « ታዲያ ምን አሰበት ፣ ሥራ ጥሩ ነው ። እኔም ለመስራት ዝግጁ ነኝ » ስትል መለሰች ።

« መስራት እችላለሁ ነው የምትይው ? እዚህ አካባቢ የሚሰራው ሥራ ምን ዓይነት እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ለአንቺ መናገሩም ይዘገንናል ። » አለቻት አስካበች በመራር ስሜት ።

« ከእንጨት መሸከም ፣ ከቤት ቤት እየዞሩ በግርድና ከመስራት የበለጠ ከባድ ሥራ የለም ። በጉልበቴ ሠርቼ ማደር ከአባቴ የወረስኩት መልካም ምግባር ነው ። » አለቻት ሒሊና በየዋህነት ። አስካበች እንድታወቅ የፈለገችው ነገር እንዳልገባት ተገነበበች ።

« በይ እንግዲህ ለማንኛውም ከረጢቱን ፍችና ዕቃሽን በመልክ በመልኩ አስቀምጭ ፣ ዐጉርሽንም ተጣጥበሽ የሚመጣውን ጠብቂ » አለቻት ።

ሒሊና የታዘዘችውን ለመፈፀም ከረጢቷን ፈትታ ከውስጥ ያለውን ዕቃ ማውጣት ጀመረች ። በመጀመሪያ ያረጁ የአባቷን ልብሶች አወጣች መጥረቢያ ተከተለ ። ሒሊና በልዩ ስሜት « የአባቴ መጥረቢያ » ብላ አፍንጫዋን እጀታው ላይ አሳረፈች ። አስካበች በሒሊና ባህሪ በመገረም እንደጉድ ታያት ጀመር ። ሒሊና የመጥረቢያውን እጀታ መሀሉ ላይ በሁለት እጆቿ ጥርቅም አድርጋ ደረቷ ላይ ለጥፋ እንባዋን ለቀቀችው ።

« የማናት ሞኝ እባካችሁ ። በይ አሁን መጥረቢያውን አልጋ ስር አስቀምጪውና ተንቀሳቀሽ » አለቻት አስካበች ፊት ላለመስጠት ያህል ለመቆጣት እየሞከረች ።

« የሞኝነት አይደለም ። አባቴ ያወረሰኝ ቢኖር ይህን መጥረቢያ ነው ። ይህ መጥረቢያ ሁልጊዜ አባቴን ከነደግነቱ፣ ከነሥራ ወዳድነቱ ያስታውሰኛል ። ብርታትም የሚሰጠኝ ይመስለኛል ። » ስትል ሒሊና ተናገረች ።

እንደድንገት የአስካበች ስሜት ተለዋወጠ ። በሒሊና ውስጥ የሒሊናን አባት ለማየት ሞከረች ። አባቷን ደግሞ ከሒሊና አባት ጋር አነፃፀረች ።

« የኔ አባት ብዙ ከብቶች ነበሩት ። ለመጀመሪያ ባሌ አስገድዶ ከዳረኝ በኋላ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ዞር ብሎ አይቶኝም አያውቅም ። ገና ሳላገባም አባቴ ወንድሞቼን እንጂ እኔን ከመጤፍ አይቆጥረኝም ነበር ። በዚህ የተነሳ አባቴን በፍቅር ተመልክቼው አላውቅም ። ሲሞትም መቃብሩ ላይ አልቆምኩም ። አባቴ ከመሞቱ በፊት ከተማ ይወድ ነበር ። ታዲያ ከእትዬ ጋር ወዳጅነት ተያይዘው ሳሉ ያለውን ሀብት ሙጥጥ አርጎ ሸጦ እሳቸው ቤት ገባ ። እኔም ኑሮው አልሆንልኝ ይልና ከባሌ ጋር ተጣልቼ ወደ ወላጆቼ ጋ ስሄድ አባቴ ዓይንሽን ላፈር ብሎ ወደዚህ አመጣኝ ። ታዲያ ይሄውልሽ ውሉ ባልታወቀ ወይ በቅጥር ወይ በዝምድና ልፈታው በማልችለው ሁኔታ እዚሁ ታስሬ ቀረሁ ። አሁንማ ምን ይደረጋል መሄጃውም ጠፋ ። » ሀሳቧን ገታ አድርጋ ፤ « ከዚህ ቤት ጋር ያቆራኘኝ አንዳች ነገር አለ ። መሄድ እየፈለኩ አልቻልኩም» ስትል ቀጠለች ። ከሒሊና አስተያየት ማግኘት አልቻለችም ።

« ሒሊና አሁን ያጫወትኩሽ ምስጢር ነው . . . እርቦሻል መሰል » ብላ መልስ ሳትጠብቅ ከበሩ ሥር ቁምሳጥን መሳይ ሳጠራ ላይ በጨርቅ ተከድኖ የተቀመጠውን ዝርግ ሳህን አቀረበችላት ። አልፎ አልፎ ሽሮ መሳይ ወጥ የነካካው እንጀራ ነበር ።

« በይ እንግዲህ ብይ ! የሚመጣው ነገር አይታወቅም » ።

በሚቀጥሉት ቀናት ሒሊና የቤቱን ነዋሪዎችና የስራውን ሂደት ተመለከተች ። በአክብሮትና በተራ ሥም የሚጠሩትን ለይታ አጠናች። ወ/ሮ አባይነሽን « እቴቴ » ስትላቸው ባይቀበሉትም ደፍረው « አትበይኝ » ማለት አልቻሉም ። አስካበችንም « እትዬ » ስትላት ሌሎችን እንደየዕድሜ ድርሻቸው ወንዶችና ሴቶችን በመለየት

በስማቸው ላይ « ጋሼና እትዬ » ብላ መጥራቱን ተላመደችው ። በቤት ውስጥ በእሷ ዕድሜ አስናቀና ሰለሞን ብቻ በመሆናቸው ሰለሞንን በትሁትነቱ ይበልጥ ማቅረብ ጀመረች ። ሌሎቹን እንደየጸባያቸውና እንደአቀራረባቸው መያዝ ወደደች ።

በደረሰች በማግስቱ የምትሠራው ሥራ በአስካበች በኩል ተነግሯት ስለነበር በዋናው ቤት ውስጥ የሚገኘው የመጠጥ መጋዘንና የሚከራይ መኝታ ቤት ቁልፍ ያዥ ሆና ቁልፎቹን እንድትረከብ ተደረገ ። በተጨማሪም በአራት ብር የሚከራየውን የመኝታ ቤት ወለል ማፅዳትና በዋናው ቤት ለወ/ሮ አባይነሽ መላላክ ፣ ቡና ማፍላት የፅለት ተግባሯ ሆኗል ። አስካበች ግን የሥራ መመሪያውን በምትሰጥበት ወቅት ለስለስ ባለ አነጋገር ነበር ።

ሒሊና በአስካበች እርዳታ ሥራውን በአጭር ጊዜ ተላመደችው ። ከጠዋቱ አስራ አንድ ሰዓት ከእንቅልፏ ተነስታ እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት በመራወጥ ሥራዋን ታካሂዳለች ። ለእንግዶች የመኝታ ክፍል ታከራያለች ፤ ጠዋት ተነስታ መኝታ ክፍሉን አይታ ትረከባለች ። አንሶላውን ለአጣቢ ሰጥታ ፤ ቤቱን አፅድታ ፣ አልጋ ታነጥፋለች ። መሸት ሲል ደግሞ ከትልቁ ቤት መጠጥ እንዲያወጡ አድርጋ ለወ/ሮ አባይነሽ ቡና ታፈላለች ። አልፎ አልፎም የወ/ሮ አባይነሽን የግል እንግዳ እግር በማጠብና በመላላክም ታገለግላለች ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ምስጋና የላትም ። ወ/ሮ አባይነሽ ሥራው ምንም ያህል በጥራት ቢከናወንም እንከን በመፈለግ በጥቃቅኑ በሠራተኞች ላይ የመጮህ ልማዳቸው አባዜ እሷንም አላለፋትም ።

ሒሊና ከወ/ሮ አባይነሽ የወንድ ደንበኞች ሁሉ አዘውትረው የሚጎበኟቸውን አብዩ ጋሻዬን በጣም ትፈራቸዋለች ። እሷን በቀጡ አስተውለው እስከአሁን ባያዩዋትም የቤቱ ሠራተኞች ምን ያህል እንደሚሸቆጠቆጡ በማየቷ አንዳች አስፈሪ ገጽታ እንዳላቸው

ትገምታለች ። አንዳንድ ጊዜም የሆነ ፍርሃት ሲወራት ወደ አባቷ መጥረቢያ ትርባለች ።

*   *   *

ሒሊና በአዲሱ ቤቷ ሁለት ወሯን ያዘች ። ክረምቱ እያለፈ ፣ ዝናቡ እየቀረ ፣ የፀሀይ ብርሃን በቅጡ መታየት ጀምሯል ። ለአቃቂ ስቅዝቃዜው ይልቅ ሙቀቱ በማየሉ ወበቁ ጀምሯል ። ሒሊናም ከቤቱ ሰዎች ትውውቅ አልፋ የውጪ ደንበኞችም በስም እየጠሩ የሚፈልጉትን በመጠየቅ ተግባብተዋታል ። የመስከረም ወር ለሒሊና እንደ ጠዋት ጮራ በልቧ ውስጥ የተስፋ ብርሃን የሚፈካበት ወቅት ነው ። በአካባቢው ያሉት ሰዎች ለልጆቻቸው ደብተርና እርሳስ ገዝተው ሲሄዱ ፣ የቤት ውስጥ ጓደኞቿ አስናቀና ሰለሞን የትምህርት መሳሪያቸውን ይዘው ሲመጡ ስትመለከት የበለጠ የተስፋ ብርሃን በውስጧ እየጎላ ታያት ። የአባቷን ቃል በህይወት እያለች ልትረሳው አትችልም ። በአንድ ወቅት ከአባቷ ጋር በቁምነገር ሲጫወቱ ደጋግሞ « በዚህ ጥሩና ንፁህ እንደበትሽ የተማርሽ ብትሆኝ ምንኛ በረካሁ ! በድህነታችን በዘራችን የተማረ የለም ። » ብለው የነገሯት ትዝ አላት ። ቃላቸውን አመነችው ፤ ፍላጎታቸውን ልታሟላላቸው ፣ በዘራቸው እሷ የተማረች ሰው ለመሆን ለራሷ ቃል ገባች ።

በሩ ተበርግዶ ወ/ሮ አባይነሽ እሳት ጎርሰው ወደ ውስጥ እስኪዘልቁ ድረስ ሒሊና ሀሳብ ውስጥ ነበረች ።

« አንቺ የዘላን ልጅ ! እየሰማሽ ነው ዝም የምትይኝ ? » ሲሉ የቀኝ ክንዷን በወፍራም እጃቸው ጨብጠው ፈርጠም ባለው ሌላኛው እጃቸው እራሷን ገጩት ። ሒሊና መልስ አልነበራትም ። ተሸማቅቃ ዝም አለች ። ሁኔታውን ትከታተል የነበረችው አስካበች

ወደ ውስጥ ስትዘልቅ ሕሊና በመጠኑም ቢሆን ለመረጋጋት ሞከረች::

ወ/ሮ አባይነሽ በቁጣ እንደተንጨረጨሩ የእንጨት ዘር ለማግኘት ሲማትሩ ዓይናቸው ግድግዳውን ታከ የተጋደመ መጥረቢያ ላይ አረፈ ::

« ይሄ ደግሞ ምናችሁ ነው ? » ሲሉ በመገረም ጠየቁ ::

« የልጅቱ ትራስ ነው » አለች አስካበች የሕሊናን ስሜት በመረዳቷ ::

ወ/ሮ አባይነሽ ወደ ሕሊና እየተመለከቱ « ገፊ ! ዘመዶችሽን ሁሉ አስናብተሽ እኔን ደግሞ ልትገፊ ነው የመጥረቢያ ትራስ የምታደርጊው ! በይ ባስቸኳይ አንሽው » ብለው ዞር ሲሉ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን በቅርቡ የተነሱትን ፎቶግራፍ ተመለከቱ :: በየቀኑ ከሚመለከቷቸው የቀድሞ ፎቶግራፎች ጋር አወዳደሩ :: በአስካበች ክፍል የተሰቀለውን ፎቶግራፍ ግን አልወደዱትም :: የቀድሞ ውበታቸውን አደብዝዞ እርጅናቸውን አጉልቶ ተስፋቸውን አመነመነው :: አላስቻላቸውም ::

« አስካበች እባክሽን ምን አደረኩሽ ? ይሄን ፎቶግራፍ ከፊቴ ብታነሽው ? ስንት ቀን ልንገርሽ ? » ብለው በፍጥነት እርምጃ ከክፍሉ ወጡ ::

አስካበች የወ/ሮ አባይነሽን ፎቶግራፍ አንስታ ከድንኩ አልጋ ሥር ካለ የእንጨት ሳጥን ውስጥ በልብሶቿ መሀል አስቀመጠችው :: ቀጥላ ትርጉሙን ለመለየት በማይቻል ድምፅ እያጉረመረመች ወደመጥረቢያው ተመለከተች :: ፊቷን ከመጥረቢያው ስታነሳ ከሕሊና ጋር ዓይን ለዓይን ተገናኙ ::

« ሕሊና እኚህ እርጉም ሴትዬ አይለቁሽም ልውሰድና ኩሽና ላስቀምጠው » አለቻት :: ሕሊና ውስጧ ተላወሰ :: የማታውቀው መጥፎ ስሜት ወረራት ::

« እትዬ በህይወቴ ያለኝ ቅሪትና ተስፋ እሱ ብቻ ነው :: » አለች ቀይ ፊቷን በእጆቿ ሸፍና ጣራ ጣራውን እያየች ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ::

« እትዬ መጥረቢያውን ስጪኝና ከዚህ ቤት እጠፋለሁ » ስትል እጆቿን ወደ አስካበች ዘረጋች ::

አስካበች በልመናና በቅሬታ ዓይነት ፣ አንድም በማዘን ሌላም በፍርሃት ፣ « ሕሊና የእትዬን ፀባይ ያወቅሽው ይመስለኛል :: መጥረቢያው ከእሳቸው ህይወት ጋር የተገናኘ ስለመሰላቸው ፣ በመጥፎ ስሜት አይተውታል :: የትም ብትሄጂ አይለቁሽም :: ይልቅስ ኩሽና ወስጄ ላስቀምጠው » አለቻት ::

« ለእኔኮ የእባቴ ሽታ ነው » አለች ሕሊና ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች :: አስካበች ሆድዋ ሊጨክን አልቻለም :: ሕሊና አንጀቷን በላችው ::

« በቃ ተይው :: ባይሆን ልብስሽ ውስጥ ደብቂው :: የሚሆነውን እናያለን » አለችና « በይ ዕንባሽን ጥረጊ ፤ እትዬ እንደሆኑ በላቸው ቤት ከፍቶት የሚያለቅስ ሁሉ ሟርተኛ ነው :: » ስትል ምክሯን ለገለቻት ::

ወ/ሮ አባይነሽ ፊታቸውን ኮሶ አስመስለው ፣ ጋቢያቸውን ደርበው መኝታ ክፍል ውስጥ ከተረኛው የወንድ እንግዳቸው ጋር ሲጠጡ አምሽተው እንኳ የቀኑ ንዴታቸውን በውስጣቸው አምቀዋት ነበር ::

« ሕሊና » ሲሉ ተጣሩ :: ሕሊና ድጋሚ አልተጠራችም ::

« አቤት » ብላ የመኝታ ቤቱን በር ከፍታ ገባች ::

« የእግር ውኃ አሙቀሻል ? » ሲሉ ጠየቋት :: መልሱን ሳይጠብቁ « ወንበር አምጪና የአብዬ ጋሻዬን ልብስ ተቀበይ » ሲሉ አዘዟት :: ከመብል ጠረጴዛ አጠገብ ከተደረደረው ወንበር አንዱን ብድግ አርጋ ወደ መኝታ ቤት ወሰደች :: አብዬ ጋሻዬ ልብሳቸውን

በማውለቅ ላይ ነበሩ ። ከግዙፍ ወፍራም ሰውነታቸው ላይ ልብሳቸውን በጭንቅ እስኪያወልቁ ጠብቃ ፤ እንዳወለቁ ተቀብላ ባዘጋጀችው ወንበር ላይ አስቀመጠች ። አብዬ ጋሻዬ ሕሊና ወደ ክፍሉ ከገባች ጀምሮ መንፈሳቸው ተረብሾ ነበር ። እሷን እየሰረቁ ለማየት ሲሉ ጊዜ ለመግደል ልብሳቸውን ላለማውጣት ሲታሹ ከቆዩ በኋላ ትታቸው ከመውጣቷ በፊት የመለሳቸውን አማራጭ ወሰዱ ።

« ስምሽ ማን ይባላል ማሚት ? » ሲሉ ጠየቋት ።

« ሕሊና » ብላ መለሰች ፤ በፍርሃት ፣ እጆችዋን ወደኋዋላ አድርጋ ወደ መሬት አቀርቅራ በለስላሳ ድምፅ ። « ሕሊና ! ሕሊና!» ሲሉ ሁለት ጊዜ ለራሳቸው ተናግረው « ቆንጆ ስም ነው ፣ ለመልክሽም ይስማማል » አሏት ።

« አባይነሽ ይህችን ቆንጆ ከየት መዘዝሻት ? » ሲሉ ጠየቋቸው ወደ ውስጥ ሲገቡ አይተው ።

« ኡኡቴ ቆንጆዎቹ አለቁብህ እንዴ ? ምነዋ ልጅት ! ይህች ምንቸት ደግሞ ከቅላቷ በስተቀር ምኗ ነው ቆንጆ ? » አሉና እየተውረገረጉ ወደ ቁምሳጥኑ አመሩ ። ቁምሳጥኑን ከፈት አድርገው የሆነ ነገር ከወሰዱ በኋላ ወደመጡበት እንደገና ተመለሱ ።

አብዬ ጋሻዬ ከረባታቸውን ከአንገታቸው እውልቀው በእጃቸው እንደያዙት ሕሊና ለመቀበል ሁለት እጆችዋን ዘረጋች ። « ግድ የለም ተይው » አሏትና እጆችዋን ይዘው አጠገባቸው የነበረውን ፎቴ ወንበር እያመለከቱ « ተቀመጭ » አሉ ። ሕሊና ለመውጣት ፈለገች። ሰውነቷ ላብ አመነጨ ። የለውየውን ዓይን ለመሸሽ ስትዞር ከወ/ሮ አባይነሽ የደፈረሰ ዓይን ጋር ተገጣጠሙ ።

« አይዞሽ አትፍሪ ተቀመጭ ፣ እኔ ነኝ ያዘዝኩት » አሏት ሰውየው በድጋሜ ።

« በላ ጋሻዬ ጥሩ ትምህርት ነው የምታስተምርልኝ ! ነገ ደግሞ እራስሽ ላይ ልቀመጥ ትበላ » አሉ ወ/ሮ አባይነሽ በንዴትና ሰቆጣ ።

« ግን ልጅቱ በጣም ቆንጆዬ ልጅ ናት ! » አሉ ሰውዬው ሕሊና ከወጣች በኋላ ።

« ቢሆንም እፊቷ እንደዚያ አይባልም ። እንኳን እንዲህ ተብላ እንደውም ዘረ ኮብላይ ናት ታስኮበልልብኛለህ ! »

* * *

ጠዋት በ2:30 ገደማ ሁሉም ወደሥራ ለመግባት ይጣደፋል ። ጋሪዎች ይርመሰመሳሉ ፣ ፀሐይዋ ለስለስ ብላ ትሞቃለች ። ሦስቱ ጓደኛሞች መሀል ከተማ ከሚገኘው የአውቶቡስ መናኸሪያ ተነስተው ቀጠን ባለ እርምጃ አስፓልቱን አቋርጠው ፣ . . . እቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ዋናው በር ደረሱ ። ከመካከላቸው ፣ ያሬድ ፋብሪካው በር ላይ የደንብ ልብስ ለብሰው የቆሙትን ዘበኛ ፣

« ቀጠሮ ነበረን » አላቸው ፤ ለመግባት ፈቃድ በመጠየቅ ዓይነት መልክ ። ዘበኛውም « ማን ጋ ነበር ? » ሲሉ ጠየቁት ።

« አስተዳደር ቢሮ »

« እዚሁ ቆዩ » አሉና ዘበኛው አጠገባቸው ወደሚገኘው ትንሽ ቤት ገባ ብለው ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንደገና ተመለሱ ።

« ሥማችሁን እዚህ ላይ አስፍሩ » አሏቸው ። ያሬድ የተሰጠውን ወረቀት ተቀብሎ የሦስቱንም ሥም ከነአባታቸው ፅፎ ሰጣቸው ። ዘበኛው ወደ ትንሿ ቤት ገቡና አሁንም እፍታ ቆይተው ተመልሰው ትንሿን በር ከፍተው ሦስቱን አንድ በአንድ ሰውነታቸውን ዳሰው አስገቧቸው ።

« ተቀብለውን ይሆን እንዴ ? እኔ መቼም አላምንም » አለ ሀሰን ::

« ምን አስቸኮለህ መጥተን የለ ! ለማንኛውም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተቀብለናል ወይም አልተቀበልንም ይሉናል » አለ ፀጋው እርምጃውን በማፋጠን ::

አስተዳደሩ ቢሮ አካባቢ ሌሎች በርካታ የፋብሪካ ሠራተኞች አስተዳደሩ ቢሮ ለመግባት ተራቸውን ይጠብቁ ነበር :: ወረፋ ጠብቆ የመግባቱ ነገር አስቸጋሪ መስሎ ታያቸው :: ሀሰን እነሱ የመጡበት ጉዳይ የተለየ መሆኑን በመግለጽ የተላላኪውን ትብብር መፈለጉ እንደሚሻል ሀሳብ አቀረበ :: ሁሉም ለውጤቱ ጓጉተው ስለነበር በሀሳቡ ተስማሙ :: የቆሙትን ባለተራዎች እያለፉ ወደ ተላላኪው ቀረቡ ::

« ይስሙ ጋሼ ባለፈው ሣምንት ለቅጥር ፈተና ወስደን ፣ ዛሬ እንድንመጣ ተነግሮን ነበር ፣ ምን ይሻለናል ? » አለ ያሬድ ሁሉንም በመወከል ::

« ሰው ገብቷል ፣ በዚህ ላይ ይህ ሁሉ እዚህ የተሰለፈው እሳቸውን ለማነጋገር ስለሆነ ተራ ያዙና ጠብቁ » አሏቸው ተላላኪው::

« እኛ እኮ ሠራተኞች አይደለንም :: » አለ ያሬድ :: ዘበኛው ፊቱን አዞረና ተቀመጠ :: ፀጋው የሚከተለውን መጠበቅ አልፈለገም እየጎተተ ወደሰልፉ ወሰዳቸው :: ተራ ሳይደርሳቸው ወደ ግማሽ ሰዓት ያህል ጠበቁ :: አራት ሰዓት እየተቃረበ ነበር :: በመሰልቸት ላይ እንደነበሩ ቀደም ብለው የሚያውቋቸው ጥቁር ሱፍ ለባሽ ከቢሮ ወጡ :: ሲጠባበቁ የነበሩት የፋብሪካው ሠራተኞች ሰውየውን ከበቡዋቸውና የጥያቄ መአት አጎረፉባቸው :: ሰውዬው ግን ወደፊት እየተራመዱ ፣

« ሰሁሉም እመለሳለሁ » የሚል ቃል ብቻ ነበር የሚወጣቸው :: ሀሰንም እንደምንም ብሎ ሲታያቸው ሞከረ :: አልረሷቸውም ::

« መጣችሁ ? እመለሳለሁ ፣ ጠብቁ » አሉት :: ሌላ አማራጭ አልነበረም :: መጠበቅ ነበረባቸው ::

« ለምን ይሆን ጠብቁ የሚሉን ? ጊዜያችንን ባይገሉብን አይሻልም ? » አለ ሀሰን ::

« አይ ችኩል ! አሁን ሲመለሱ ጠብቅና ፣ አሁኑኑ ሥራ ካልጀመርኩ በላቸው » አለ ፀጋው በማፌዝ ::

« ለመግባት የቸኮለ ለመውጣትም እንደዚያው ነው ፣ ደግሞ አንድ ወር ሰርተህ አሰናብቱኝ እንዳትል » ሲል ያሬድም ተናገረ ::

« ያስገቡኝ እንጂ መሰናበቱን ደግሞ አስብበታለሁ :: የተሻለ ከተገኘ በጨረታው አንገደድም » ሲል ሀሰን ለመቀለድ ሞከረ ::

« ለመሆኑ አሁን ብንቀጠር ተመላልሰን ለመስራት ነው ? ወይስ እዚሁ ለመኖር ? » ሲል ፀጋው አዲስ ሀሳብ አቀረበ ::

« እኔ እንኳን ኑሮዬና እንጀራዬ የተጣመሩ ናቸው :: እዚህ ሥራ ከያዝኩ እንጀራዬም ኑሮዬም እዚሁ ይሆናል :: አባት የለኝ እናት የለኝ ፣ ምኔ ቀረና አዲስ አበባ እመላለሳለሁ ? » አለ ያሬድ ::

« እኔስ ከቤተሰቦቼ ተለይቼ መኖር አልፈልግም ፣ በጠዋት ተነስቼ ወደ ሥራዬ ማታ እሮይ ብዬ ወደቤቴ » አለ ሀሰን ::

« እኔም ቤተሰቦቼ ቢስማሙ እዚህ መኖሩን እመርጣለሁ :: ምን ጠዋትና ማታ አንከራተተኝ ? . . . አለ ፀጋው ::

« እናንተ ሁለታችሁ እዚህ ብትከራዩ ሳይሻል አይቀርም :: እኔም ሲመሽብኝ እዚሁ አድራለሁ » አለ ሀሰን በማሾፍ ::

« እኔ እንኳን አይመስለኝም :: ቤተሰቦቼ አይፈቅዱልኝም :: ተመላልሰህ ሥራ ነው የሚሉኝ » ፀጋው የራሱን ሀሳብ በማሻሻል ተናገረ ::

« እናንተ የታደላችሁ ናችሁ ። የቤት ኪራይ ፣ የምግብ ሳታስቡ ከዚህ እንደሄዳችሁ የሞቀ ቤት ይጠብቃችኋል ፣ እኔ እናንተን ብሆን ቤትም አልከራይ ፣ ቀድሞውንም ትምህርቴን ሳልጨርስ ስራም ለመያዝ አልሞክርም ነበር ? » ሲል ያሬድ በሚያሳዝን ሁኔታ ተናገረ።

« ቤተሰብ ውስጥ መኖር ማለትክ ሁሉም ነገር የተሟላ ነው ማለት አይደለም ። ብዙ የሚጎሉ ነገሮች አሉ » አለ ሀሰን ። በመካከሉም የሚጠበቀው ሰው ሲመጣ አየና ጨዋታቸውን አቁመው በባለጉዳይ መልክ ጠበቁ ። ሰውየው አጠገባቸው እንደደረሱ ቆም አሉና ፣ « ኑ እናንተ » ብለው ሶስቱንም ወደ ቢሮአቸው ይዘዋቸው ገቡ ። አንድ ቢጫ ፋይል አወጡ ። « አንደኛው ጓደኛችሁ ጠዋት መጥቶ የቅጥር መዘርዘር እንዲያሟላ ሰደነዋል » አሉና ፋይሉን ገለጥ ገለጥ አድርገው « ያሬድ እንዳሻው » ሲሉ ተጣሩና ቀና አሉ ። ያሬድ ከሌሎች ወደፊት ቀድሞ ቆመ ። « እኔ ነኝ » በሚል ዓይነት።

« አንተ ነህ ? » አሉና እንደገና ወደ ወረቀቱ አስተውለው ፣

« ሀሰን ሰቂር » ብለው ቀና አሉ ። ሀሰንን ተመለከቱ ።

« እንግዲህ ፀጋው አንተ የተያዝከው በተጠባባቂነት ነው ። እየመጣህ መጠየቅ ትችላለህ ። እናንተ ሁለታችሁ ግን » አሉና ፊት ለፊታቸው ባለ ማስታወሻ ደብተር ላይ የሆነ ማስታወሻ ፅፈው « ቁጥር 10 ቢሮ ሄዳችሁ አቶ ታዬ ለሚባሉ ይህን ወረቀት ስጡት ፣ የቅጥር መዘርዝሩን እሱጋ ታገኛላችሁ ፣ እንግዲህ መልካም ዕድል » ሲሉ አሰናበቷቸው ። ጓደኛሞቹ እጅ ነስተው ክቢሮ ሲወጡ በፀጋው አለመቀጠር ቅር ተሰኝተው ነበር ።

« እንግዲህ እኔ ልሂድ » አለ ፀጋው በብቸኝነት ስሜት ።

« ምነው አብረን እንሄዳለን ፣ ጠብቀን » አለ ሀሰን በጓደኝነት ስሜት ።

« እኔ እንግዲህ ብቸኛ ሥራ ፈላጊ ነኝ ፣ ወደሚቀጥለው የዕድል ቀጠሮዬ ብሰማራ ይሻላል » አላቸው ። ከዚህ በላይ ፊቱን ማየት ፈሩ ። አስገድደው ከነሱ ጋር ለማቆየት ከበዳቸው ። በሀዘን ስሜት ተሰናበቱት ።

*　　*　　*

በቢሮው ውስጥ ሁለት ሴቶችና ፣ ሦስት ወንዶች ተቀምጠዋል ። ክፍሉ ሰፋ ያለ ነው ። ከሁለቱ አንደኛዋ ሴት ታይፒስት መሆንዋን ፊት ለፊቷ የተቀመጠው ታይፕ ይናገራል ። ሁለቱ አቀርቅረው ጋዜጣ ያነባሉ ። አንደኛው ግን አንድ ቀጠን ካለ ቀይ መልከ መልካም ሰው ፊት ለፊት ተቀምጦ በወረቀት ላይ እንገቱን ደፍቶ ይፅፋል ። እነ ያሬድ ወደ ክፍሉ እንደገቡ አንደኛዋ ሴት ቀና ብላ ፣ « ምን ነበር ? » ስትል ጠየቀቻቸው ።

ሀሰን ቀረብ ብሎ የያዘውን ወረቀት እያሳየ ፣ « አቶ ታዬን ነበር የምንፈልገው » አላት ። የተባለውን ሰው በእጇ ምልክት ጠቆመችው ። ሀሰን ወደ አመለከተችው ወንበር ሄዶ የያዘውን ወረቀት ለአቶ ታዬ ሰጠው ። የተፃፈውን ከተመለከተ በኋላ ፊት ለፊት የተቀመጠውን ወጣት እያሳየ ፣ « በሉ እሱ ክጨረሰ በኋላ ትመጣለችሁ ፣ እስከዚያ ውጪ ወጥታችሁ እየተዝናናችሁ ቆዩ » አላቸው ። እንደታዘዙት አደረጉ ። ውጪ ወጥተው የክሪደሩን ግድግዳ ተደግፈው ስለ አዲሱ ስራቸው አነሱ ።

« እንግዲህ እኔን የቀጠሩኝ እንደሚመስለኝ ለዲዛይን ክፍል ነው ፣ ማን ይለቀዋል እንይዘዋለን ፣ ትንሽ ጠርቀምቀም አድርጌ ወደ ት/ቤት እመለሳለሁ ፣ የሥራ ልምዱ ግን ጠቃሚ ነው » ሲል ደስ እንዳለው ሀሰን ለያሬድ ገለጸለት ።

« እኔ እንኳን አጠራቅሜ ልማር ብልም የሚከፈለኝ ገንዘብ ከእለት ጉርሴ የማያልፍ ነው ። ክቻልኩ ግን ኤክስቴንሽን ተምሬ

እጨርሳለሁ እንጂ ከአሁን በኋላ ሥራ ፈትቼ እራሴን ችግር ላይ ለመጣል አልፈልግም ፣ አንተ እንኳ ቤተሰቦችህ ስላሉ ምንም ወጪ አይበዛብህም ። ግፋ ቢል የምግብና የትራንስፖርት ብታወጣ ነው ።» ሲል ያሬድ የ10 ቁጥር ቢሮ በር ተከፈተ ።

« ያሬድ እንደሻው »

ተጠራና ገባ ። አቶ ታዬ ፊት ለፊት ሲደርስ « ተቀመጥ » አሉት ። ከመሳቢያ ውስጥ አንድ ጥራዝ አውጥተው ፣ « ይህ የእኛ የሠራተኛ መተዳደሪያ ህጋችን ነው ፣ አንብበህ ከተረዳህ በኋላ የስምምነት ውል ትፈርማለህ » አሉት ።

ያሬድ በትዕዛዝ መልክ የተሰጠውን ጥራዝ እያገላበጠ « አሁን እዚህ ውስጥ የእኔን ህልውና የሚፃረር ቢፃፍ አልፈልግም ይላል ብለው ነው ? ይቀልዳሉ ልበል ! የፈለገውን ቢሆን በስንት ፈተናና ውጣ ውረድ ያገኘሁትን ሥራ አልፈልግም ይላል ብለው ማሰባቸው አይገርምም » እያለ ለራሱ ሲያወራ ቆይቶ አስተካክሎ ጥራዙን አስቀመጠ ። አቶ ታዬ ወደ ያሬድ እየተመለከቱ ፣ « አንብበህ ጨረስክ ? » ሲሉ ጠየቁት ። ጥራዙን አንስተው አምስት ገፅ የያዘ ወረቀት ሰጡትና ፣ « ይህን ደግሞ ሙላ » አሉት ። የተሰጠውን የፎርም ወረቀት ተቀብሎ ሞልቶ አስረከበ ። አቶ ታዬም የተሞላውን ተመልክተው እያስቀመጡ ፣

« ሥራህን ከነገ ጀምሮ መተዋወቅ ትችላለህ ፣ ከሰሞኑ ግን እስከ አንድ ሳምንት ድረስ አራት ጉርድ ፎቶግራፎች እንድታመጣ ፣ ይህን ወረቀት ውሰድና ነገ ስትመጣ ለአቶ አድማሱ ማጂቦ ስጠው ። እሱ ተቀብሎ ሥራውን ያሳይሃል ። የተቀጠርከው ለቀለማቀለም ክፍል ነው » ሲሉ አሰናበቱት ። ሊወጣ ሲል « ሀሰን ለቂርን ጥራው» ብለው ጨመሩ ። ሀሰንም እንደ ያሬድ የተጠየቀውን ፎርም አሟልቶ ጨርሶ ተያይዘው ወደ አውቶቡስ መጠበቂያው አመሩ ። ጥቂት እንደተጓዙ አንድ ቢጫ ቀለም የተቀባ ቤት አጠገብ ሲደርሱ

ያሬድ አተኩሮ ተመለከተ ጨክኖ ሊያልፈው አልቻለም ። ምነው ምን ሆንክ ? » ሲል ሀሰን ግራ ተጋብቶ ጠየቀው ። ያሬድ ዝም አለው ።

« ምነው የምታውቀው ሰው አለ እንዴ ? » አለ ሀሰን በድጋሚ ።

« አይ ምንም አይደል » አለ ያሬድ በቀዘቀዘ ስሜት ።

ያሬድና ሀሰን አዲሱን ሥራቸውን ከጀመሩ ሦስት ሣምንታት አልፏቸዋል ። አዲሱ ሥራቸው ብዙም አላስቸገራቸውም ። በተለይ ሀሰን ከሥራውም ከሰውም ጋር ብዙ እንደቆየ ሰው ተላምዶታል ። ያሬድ ግን ከሰው ጋር ለመቀላቀል ዳተኛ ነው ። ቶሎ መልመድ ቶሎ መሰላቸትን ያመጣል የሚል ፈሊጥ ስላለው ዝግታን ይመርጣል ።

ያሬድ ሥራ በጀመረ በሣምንቱ እዚያው አቃቂ እነ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት አቅራቢያ አነስተኛ ቤት ተከራየ ። በትርፍ ጊዜው ከተማዋን ከነጉራንጉሯ በመተዋወቅ ኑሮውን መምራት ጀምሯል ። ወደ ሥራ ሲሄድ ሌላ ቅያስ መንገድ ቢኖርም ምርጫው አልነበረም ። ከዛ ይልቅ ቢጫ ቀለም ያለውን ግንብ ቤት ጎማው እንደተበላሸ አውሮፕላን አዘውትሮ ይዞረዋል ። ቤቱን ባለበ ቁጥር ፣ በሩን ባየ ቁጥር ሕሊና ፣ ወ/ሮ በላይነሽ ይላል ውስጡ ። ግን እርግጠኛ አልነበረም ። ሕሊናም ሆነች ወ/ሮ በላይነሽ እረስተውት፣ ዘንግተውት ሊሆን ይችላል ። ማን ያውቃል ? እርሱ አዲስ አበባን መርሳት ይዞ የለ ። እራሱን መታዘብ ሲጀምር « የት አውቃቸውና ነው ይህን ያህል የማስበው ? » ሀሳቡን ከራሱ ለማስወገድ ይጥራል ። በዚህ ወቅት አእምሮው ዳግም ምስላቸውን ያቀርብለታል ፤ እኒያን ጎስቋላ አሮጊት ሴት ። ምርቃታቸው ፣ የዋህነታቸውን አይረሳውም ። ሥራውን ከሳቸው ፀሎት ጋር ያስተሳስረውና በባለውለተኛነት ስሜት ያሰባቸዋል ።

ያሬድ ብዙውን ጊዜ ብቸኛም ቢሆን ጓደኛም አፍርቷል ። በጣም የተቀራረበው ግን ከተሾመ ገ/እየሱስ ጋር ነው ። ተሾመ

ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ፣ መዝናናት የሚወድ ፣ በሥራው የማይቦዝንና በፋብሪካው ሠራተኞች ዘንድ መልካም ግንኙነት ያለው ሠራተኛ ነው ::

« ያሬድ ምነው ፈዘዝክሳ ፣ ተጫወት እንጂ ! ደግሞ ጠጣ ፣ መፍዘዝ ሰበግም አልበጀው » አለው :: ተሾመና ያሬድ ከአንድ ቡና ቤት ተቀምጠው በመጠጣት ላይ እንዳሉ የያሬድ ሁኔታ ግራ አጋብቶት :: « እየተጫወትኩ እኮ ነው ፤ ምነው የፈዘዝኩ መሰልኩ እንዴ ? አንዳንድ ግዜ አለ አይደል - ሀሳቤ ወደ አዲስ አበባ ይዘምትብኛል » አለው ስሜቱን ለመቀየር እየሞከረ ::

« አዲስ አበባ ሩቅ መሆኑ ነው እንዴ ? ከፈለክ ሰምን አሁን ተነስተን እንሄድም ነገ በጠዋት ከተፍ ነው » አለው ነገሩን በማቃለል::

« በሳምንቱ መጨረሻ አይሻልም ? በሥራ ቀን ይደክመናል :: ለነገው ሥራችን ዛሬ ማረፍ ይገባናል :: »

« አይ ፍሬሽ ! ሠርተህ ሞተሃል :: እኛ ሥራ እንደጀመርን ሥራ እየሰራን እንቅልፍ እንቅልፍ ይለን ነበር :: » አጠገቡ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን ብርጭቆ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጎ ባንኮኒው አጠገብ የቆመችውን አስተናጋጅ በእጁ እየጠራ

« ሂሳብ ስንት ነበር የእኔ እህት ? » ሲል ጠየቀ ::

« አንተ ጋ ሦስት ቢራ እርሱ ጋ አንድ ቢራ በጠቅላላው አራት ቢራ ፤ አስራ ሁለት ብር ነው » ስትል መለሰችለት ::
ሂሳቡን ከፍሎ ወደ ያሬድ ዞር ብሎ « በል ደመ ቀዝቃዛው ሌላ ቤት እንለውጥ ፣ ትንሽ ሞቅ ቢልህ :: »

* * *

ያሬድ አቃቂ ፋብሪካ ተቀጥሮ መሥራት ከጀመረ ስድስተኛ ወሩን ያዘ :: በዚህ ጊዜ ውስጥ ለጉብኝት ወደ ባሕር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካና ወደ ድሬዳዋ በመሥሪያ ቤቱ ተልኮ ነበር :: በሥራው ተወዳጅነትን ፣ ከቅርብ አለቆቹና አብረው ከሚሰሩት ጓደኞቹ ዝናን አተረፈ :: ቀስበቀስ ሥራውንም ፣ ሰውንም ፣ አካባቢውንም ተዋወቀ :: አቃቂን በሚገባ አወቃት :: መዝናኛና መጠጥ ቤቶችን ባያዘወትርም ፤ መዝናናት ከፈለገ « የወንድማማቾች ቡና ቤት » ይቀሰዋል :: ቡና ቤቱ በንጽህናው ፣ በግቢው ስፋት ፣ በሙዚቃ አቅርቦቱ . . . . ብቻ ግልፅ ባልሆነለት ምክንያት ለያሬድ ተመችቶታል :: እየቆየ ሲሄድ ደግሞ በዚሁ ቡና ቤት ስለወ/ሮ አባይነሽ የቤት ውስጥ ሁኔታና ስለሕሊና ወሬ ለመስማት ቻለ :: ከዚያ ወዲህ ደግሞ « የወንድማማቾች ቡና ቤት » የራሱ ቤት እስኪመስለው ድረስ አዘውታሪ ሆነ ::

« ጠጣ እንጂ » አለው ተሾመ አስተናጋጅዋ ላይ የተከለውን ዓይኑን እያየ ::

« ምክንያቱን ባላውቅም የዝች ልጅ ነገር ይገርመኛል » አለ ያሬድ ::

« የየቷ ፣ የትርሲት? » ሲል ጠየቀ ተሾመ ::

« አዎን »

« እውነትከን ነው ፤ ታሳዝናለች :: በትምህርቷ አስረኛ ክፍል ደርሳ ነበር ፤ ምን ያደርጋል ከቤተሰቦቿ ተለይታ ትኖራለች » አለና የትርሲትን የህይወት ታሪክ መተረክ ጀመረ ::

« ነፍሱን ይማረውና አንድ ተስፋዬ የሚባል ፍቅረኛ ነበራት:: ተስፋዬ የኛ የልጅነት ጓደኛችን ነበር :: በሰፈራችን የታወቀ

የእግር ኳስ ተጫዋች ነበር ። ታዲያ ይህቺ ልጅ ከቤተሰቦቿ ጋር እያለች በጣም ይዋደዱ ነበር ። የልጅቷ አባት ቀኛአዝማች ወልደሰማያት ይባላሉ ። በጣም ክፉ ሰው ናቸው ። አሁንም በህይወት አሉ ። ልጆቻቸውን በፍርሃት የገዙ ለማንም ግድ የሌላቸው ሰው ናቸው ። ታዲያ ይሄውልህ ይቺ ልጅ ቤተሰቦቿ ቤት እያለች ከተስፋዬ ትፀንስና ከቤቷ ወጥታ ትኮበልላለች ። ትንሽ ቀናት አዲስ አበባ ቆይታ ወደ አቃቂ መጣች ። ብዙ ችግር ደርሶባት ልጁ ይወሰዳል ። ህፃኑም ጤነኛ አልነበረም ፤ ሁለት ቀን እንደቆየ ሞተ ። እሷም ወደ ቤተሰቦቿ አልተመለሰችም ። ይኸውልህ ከዚያን ጊዜ እንስታ ከቡና ቤት ቡና ቤት እየቀያየረች ትኖራለች ። እዚህ ወንድማማቾች ቡና ቤት ከመምጣቷ በፊት ሾፌሮች ቡና ቤት ትሰራ ነበር ። እዚያ እያለች የማታ ትምህርት ስመማር ሞክራ የሥራው ፀባይ አላመቻትም ። የቡና ቤቱ ባለቤት በጣም የወጣላቸው አረመኔ ናቸው . . . » ሲል ተረከለት ።

ያሬድ የሾፌሮች ቡና ቤት ሲወራ ወደ ትርሲት እያየ ፣ « ሾፌሮች ቡና ቤት ትሰራ ነበር ነው ያልከኝ ? » ሲል እንደገና ለማረጋገጥ ጠየቀው ። ተሾመ ፈገግ እያለ « ምነው ታውቃት ነበር መሰለኝ » በማለት ያሬድን ተመለከተው ።

« ማወቅስ . . . አላውቃትም ። ሆኖም እዚያ ቤት የማውቃት አንዲት ልጅ አለች ። የሴትዬዋ ዘመድ ናት » አለ ስለ ሒሲና በማሰብ አንገቱን እየነቀነቀ ።

ተሾመ እጆቹን አጠላልፎ በመገረም ስሜት ያሬድን እየተመለከተው « የትኛዋን ዘመዳቸውን ነው ? እዛ ቤት እንደሆነ መላው ሠራተኛ ቤተሰብ ነው ሲባል ነው የምሰማው » አለው ። ያሬድ ወደ ኋላ መመለስ አልሆነለትም ። ተሾመ ጥሩ ጓደኛው ሲሆን እንደሚችል አሰበ ።

« ተሾመ አንድ ምስጢር ባማክርህ ፈቃደኛ ትሆናለህ ? » ሲል ጠየቀው ።

« እጅግ የሚያስቅ ከሆነ ንገረኝ ፤ ምክንያቱም የሚያስቁ ነገሮችን ከጓደኞቼ ጋር ካላወጋሁ በእንቅልፍ ልቤ ያባንኑኛል ። . . . አይዞህ ተናገር ስቀልድ ነው » ሲል ምስጢረኛው ሲሆን እንደሚችል በሚገልፅ ስሜት አበረታታው ። « . . . ይኸውልህ እዚህ መ/ቤት ስመቀጠር ስመጣ አንድ በዕድሜያቸው ጠና ያሉ ሴትና አንዲት ዕድሜዋ በአሥራ ሦስትና በአሥራ አራት ዓመት መሀከል የሆነች ውብ ልጅ ይህንን ሾፌሮች ቡና ቤት የሚባለውን በመፈለግ ሲንከራተቱ ሳሉ ሁኔታቸው አሳዝኖኝ አፈላለኳቸው ። ቤቱን ካገኘሁ በኋላ ወደ ሥራዬ ሄድኩ ። ከዛን ቀን ጀምሮ እኛን ሴት ሁልጊዜ በህልሜ አያቸዋለሁ ። እኚያ ባልቴት ሲያነጋግሩኝ የሞተችው እናቴ በህይወት እንደገና እንዳነጋገረችኝ ነበር የቆጠርኩት ። ከዛም ይኸውልህ ያለብዙ መንከራተት ወደዚህ ሥራ ገባሁ ። ሳስበው እኛን ባልቴት ዳግመኛ መጠየቅ ነበረብኝ ። ልጅቱም ቢሆን ሲጠይቋት የሚገባ ምስኪን እና ቆንጆ ነበረች » አለ እፉ እንዳመጣለት ።

« ምንድን ነው የምትለው ፤ አሮጊቷን ነው ልጅቷን ለማየት የምትፈልገው » አለው ተሾመ ፍርጥም ብሎ ።

ያሬድ በጥሞና ወደ ተሾመ እያየ « እየነገርኩህ » በማለት ከፊት ለፊቱ የቀረበውን ጠርሙስ ብድግ አድርጎ ተጎነጨና መልሶ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ፣ ጠርሙሱን በእጁ እያሽከረከረ ፣

« አንተ ደግሞ ቁም ነገር ሲነግሩህ ወደ ፌዝ ትሰውጠዋለህ። አሮጊቷ እዚህ እንደማይኖሩ ቀድሞውንም ነግረውኛል ። ስለእርሳቸው ማወቅ ብፈልግም መጀመሪያ ማነጋገር ያለብኝ ልጅቷን ነው » አለው።

ተሾመ ከት ብሎ ሳቀና «ታዲያ ተረት ከማብዛት ልጅቷን. . . ለማየት . . . አፈልጋለሁ አትልም ? ለመሆኑ ልጅቷ ፣ ልጅቷ

ከማለት ስሟ ማን ይባላል ? ይሄም ምስጢር ካልሆነ ? » በማለት ጠየቀው ::

ያሬድም ከንፈሩን ወደፊት ዥርገግ አረገና « ምንም ምስጢርነት የለውም :: የልጅቱ ሥም ሕሊና ይባላል » አለው :: ተሾመ ጮክ ብሎ « ካልጠፋ ሴት ያችን ልጋጋም ልጅ ምን አስወደደህ » አለው በማፌዝ ::

« ድሮውንስ ካንተ ጋር ማውራት የኩሽና ወሬ ነው እንጂ የዚህ ዓይነት ቁም ነገር የት ይሆንሃል ? » አለው ያሬድ በንዴት ::

የቢራውን ጠርሙስ ብድግ አደረገ :: ተሾመ የያሬድን ሁኔታ ሲያይ አቀራረቡን ወደ ቁምነገር ቀየረው :: « ምስጢርህ የጨዋታ ነበር የመሰለኝ :: እንዲህ የምር ከሆነ ከእኔ ይልቅ ዝርዝሩን የሚነግርህ ሰው አለ » በማለት ወደ ባንኮኒው መለስ ብሎ የጥሪ ጭብጨባውን አሰማ ::

« አንቺ ማነሽ . . . ንግስት » አለ ::

ባንኮኒውን ተደግፋ ተክዛ የቆመች ጠይም አፍሮ መልከመልካም አስተናጋጅ ራሷን ወደ ፊት ወርወር አድርጋ ፣

« እኔን ነው ተሼ ? » በማለት እነ ያሬድ ወደ ተቀመጡበት ባንኮኒ ተጠጋች ::

« ምን ልታዘዝ ተሼ ! » ስትል ፈገግታዋን አስቀደመች:: እጁን ሸንቀጥ ባለው ወገቧ ላይ አሳርፎ ፣ « እስቲ እባክሽን ትርሲትን ቶሎ ጥሪልኝ :: እንግዳ ይፈልጋታል » በማለት ከበስተጀርባዋ ገፋ አደረጋት :: ትርሲት አጠገባቸው ቁጭ ከማለቷ ያሬድን እያስተዋለች፣

« ዛሬ ደግሞ ለማን ልትድረኝ ይሆን ? » ስትል አንገቷን ነቅነቅ አደረገች ::

« ለሁሉም ትደርሻለሽ :: ጨዋታው ረጅም በመሆኑ እኛን ምሰይ » ሲል ተሾመ አዘዛት :: ግብዣውን ተቀብላ ተመቻችታ ተቀመጠች :: ያሬድ ወሬውን ለመጀመር ፈራ፣ ውስጡ ታፈነ ::

« ስሚ ትርሲት » ሲል ጀመረ ተሾመ ፤ የያሬድ ችግር ገብቶት ::

« ዛሬ ደግሞ የመጣው እንግዳ ያስኘው የሾፌሮች ቡና ቤት ወሬ ነው :: በይ እንግዲህ የምታውቂውን ያለምንም ቅመም ንገሪው» አላት ::

« ምን የሚወራ ነገር አለ :: ለአራት ወራት እዛ ስሰራ ቆይቼ ስለአልተስማማኝ ወጣሁ » ስትል ከንፈሯን መጠጠች ::

« እዛ እያለሽ ከሕሊና ጋር ትገናኙ ነበር ? » ሲል ያሬድ ጠየቃት ::

« ከዛች ገገማ ጋር ምን አገናኘኝ ? እዎ አውቃታለሁ :: የቡና ቤቱ ቁልፍ ያዥ ነበረች » ስትል ባጭሩ መለሰችለት ::

« እሺ ታዲያ በኑሮዋ ደስተኛ ነች ወይስ እንደሚባለው ወ/ሮ አባይነሽ እሷንም ያገኟታል ? » ብሎ ጠየቃት ::

« እኔን ማን አፈቀላጤ አደረገኝ ? ሄደህ አትጠይቃትም ? » በማለት ቁጣዋ ገንፍሎ ብድግ ስትል ያሬድ እጇን ይዞ « ተቀመጭ ፤ ገና አውርተን መቼ ጨረስን » አላት ቁጣዋን በማብረድ ዓይነት ::

« ምን ማውራት ያስፈልጋል ? አንተ የምድሩን ሲሉህ የቆጡን ትጠይቃለህ :: ታዲያ ለዚህ ዓይነቱ ጨዋታ ጊዜው የመሸ አልመሰለህም ? » ብላው ዳግመኛ ከተቀመጠችበት ተነሳች :: የተጋበዘችው ለሌላ ነገር መስሏት ነበር ::

« ምነው እባክህ የሠፈራችሁ ልጅ የዋዛም አይደለች ፤ ተልድም አታውቅ እንዴ ? ለማንኛውም እንኳን ምስጢሩን አወቅን » አለ ያሬድ ::

« ይህን ያህል የሚጠቅምህ ከሆነ ለምን እግረ መንገዳችንን ገባ ብለን አንወጣም » ሲል ተሾመ ሀሳብ አቀረበ ::

« ተሼ ዛሬ ይቅርብን መሽቷል :: በዚህ ላይ መጠጥ ወሳስደናል :: ሌላ ጊዜ እናድርገው :: » አለ ያሬድ በፍርሃት ውስጥ ሆኖ :: እንደ ድንገት ከሕሊና ጋር መገናኘቱ ከአቅሙ በላይ ሆነበት :: ራሱን ለማረጋጋት ጊዜ ፈለገ ::

« ካልፈለክ የራስህ ጉዳይ ፤ ግን ሁለተኛ ሕሊና ፣ ሕሊና ብለህ ስሟን እንዳትጠራብኝ » አለው ተሾመ በቁጣ ፤ ሂሳብ ለመክፈል ኪሱን እየደባበሰ ::

* * *

ዶሮ ሲጮህ የተነሳችው ሕሊና ፀሐይዋ ጎህ ስትቀድ አንሶላ በመሰብሰብ ሥራዋን ጀምራለች :: ከትራስጌዋ ሥር ለደበቀችው መጥረቢያ ማምሻውን ያጋጠማትን ነገር በማይሰማ ድምፅ ነግራዋለች:: መጥረቢያውን ባሰበች ፣ ባየች ቁጥር ደግሞ የአባቷ ጥሩ ፀባይ ይታወሳታል :: መከራና ችግርን በትዕግስት ማሳለፍ ከአባቴ ያገኘሁት ሀብት ነው ብላ እራሷን አፅናንታ ነበር ከመኝታዋ የተለየችው :: የመኝታ ክፍሉን ለማፅዳት ውሃ በባልዲ ቀድታ ስትሄድ « ሕሊና ነይ ቁርስ እንብላ » ስትል አስካበች ከክፍሏ በር ላይ ቆማ ጠራቻት :: ሕሊና አልተግደረደረችም :: ባልዲውን አስቀምጣ ለቁርስ ቀረበች ::

ሁለቱ የሚገናኙት በእንደዚህ ዓይነት የዕረፍት ወቅት ነው :: በእንደዚህ ዓይነቱ አጋጣሚ ሁለቱ እንደ እኩያ ጓደኞች ቅሬታቸውንም ሆነ ደስታቸውን ፤ የሆዳቸውን አውጥተው ይነጋገራሉ :: ሕሊና ትናንትና ስለአጋጠማት ሁኔታ ለአስካበች በጥቂቱ ልታወራላት ፈለገች :: ሁሉንም አፍረጥርጣ ለመንገር የዚህ ዓይነቱን ጉዳይ ጀምራው ስለማታውቅ ሀፍረቷ ቀደማት ::

« ዛሬ ደግሞ ምነው ምን ሆነሻል ? ብይ እንጂ ! በእህል ላይ ማለም ጀመርሽ ? ኧረ ይሄስ አያድርስ ነው » ስትል አስካበች ከጠዋት ህልሟ አባነነቻት ::

« ትናንትና ማታ አንድ ሰውዬ አስደንግጠውኝ እስከ አሁን አለቀቀኝም » ስትል ባላወቀችው ኃይል ልትደብቅ የነበረውን ጉዳይ ጀመረች ::

« የትኛው ሰውዬ ነው ? ምን አደረገ ? » አለች አስካበች በድንጋጤ ::

« ምንም አላረጉኝም እኮ ብቻ . . . ብቻ » ልትጎርሰው ያዘጋጀችውን እንጀራ በሳህኑ ላይ መልሳ አንገቷን በሀፍረት አቀረቀረች ::

« ማነው እሱ ለመሆኑ ? » ርህራሄ ባዘለ ቁጣ ::

« የእቴቴ . . ማነው ሥማቸው ? » አለች ሁኔታውን ለማቃለል በመፈለግ ዓይነት ::

«አብዬ ጋሽዬ ? እህስ ምን አደረጉሽ . . .ተቆጡሽ እንዴ. . .»

« አይ መቆጣትስ አልተቆጡኝም :: የተቆጡት እቴቴን ነው:: ፎቴው ላይ ተቀመጭ ብለው ሳልፈልግ በግድ አስቀመጡኝ . . . » አለችና ዝም አለች :: ዓይን ዓይኗን አየች :: ቀሪውን መተረክ አላስፈለጋትም :: ተግባቡ ::

« በይ ተይው ገባኝ . . . ገባኝ . . . እሳቸው ሲለክፉ ልማዳቸው ነው » አለች አስካበች በማረጋጋት ሁኔታ :: ሕሊና ከዚህ በላይ ደፍራ በጉዳዩ ላይ ለመወያየት አልቻለችም :: ከአስካበች ዘንድ ለመራቅ የበሉበትን ሰሀን አንስታ ከክፍሉ ወጣች :: በመጠኑም ቢሆን ሁኔታውን ለአስካበች በመንገሯ የሆነ ነገር ቀሏታል :: ውሎ ቢያድርም ወ/ሮ አባይነሽ የአደባባይ ምስጢር ማድረጋቸው እንደማይቀር ታውቃለች ::

የመኝታ ቤቱን ፅዳት ጨርሳ የሚቀጥለውን ለመጀመር ስታስብ በክፊል የተሰናበተው ጭንቀቷ እንደገና በውስጧ አንሠራራ ። ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ፊት ለፊት መገናኘት ይቀራታል ። ስለውስጧ ንፅህና ቢታውቅም ይኼ ብቻውን ለወ/ሮ አባይነሽ መልስ አይሆንም ። መሸሽ ብትችል ደግ ነበር ፤ ግን አትችልም ። በግዷ ወ/ሮ አባይነሽ ፊት ቀርባ የሚጠብቃትን መቀበል አለባት ። የመግቢያውን በር ቁልፍ በፍርሃት ተሸንፎ በሚንቀጠቀጠው እጇ ለመክፈት ሙከራ አደረገች ። የህልም ትግል ያህል በዳሰሳ ከፍታ ወደ ውስጥ ገባች ። በሳሎኑ ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎችን በፊርጅ በፊርጃቸው ለማስቀመጥ ወንበሮችን ከቦታ ቦታ ስታንቀሳቅስ ከመኝታ ክፍሉ « ማነሽ አንቺ ?» የሚል ድምፅ ሰማች ። የቆመችበት መሬት ተከፍቶ ቢውጣት በወደደች ነበር ። ወደ መኝታ ቤቱ በር ጠጋ ብላ « እኔ ነኝ እቴቴ » ስትል በስጋት ተናገረች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ቀስ ብለው በለሰለሰ አነጋገር ፣ « አንቺ ነሽ ሕሊና » አሉና መተኛታቸውን ቀጠሉ ። ሕሊና የሚቀጥለውን ንግግር ለመስማት ጆሮዋን ወደ በሩ ጠጋ አድርጋ ቆመች ። ምንም ድምፅ የለም ። ጠበቀች ። እንቅስቃሴም ፣ የተለየ ድምፅም የለም ። እንቅልፍ አሸንፏቸው ሊሆን ይችላል ብላ ገመተች ። አባይነሽ እንደገና ተወልደው አዲስ ሰው ሊሆኑ አይችሉም አለች ለራሷ ። ይልቅስ ስቃይዋ በመራዘሙ አዘነች ። ላይቀር ነገር ቢወጣላት ፣ የሚጠብቃትን ቁርጡን ብታውቀው ይሻል ነበር ። ለማንኛውም ሥራ ሀሳቧን ይቀንሳልና ወደስራዋ ተመለሰች ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ የማይገባት ነገር ተፈጠረ ። ወ/ሮ አባይነሽ የሳሎኑን በር ከፍተው ወደሌላኛው ክፍል ዘለቁ ። ሰውነቷ መራድ ጀመረ ። ወ/ሮ አባይነሽ የገቡበትን በር እንደገና ከፍተው ወደሳሎኑ ተመለሱ ። ሕሊና እንደልማዷ እጅ ነሳቻቸው ። ክፍሉ ውስጥ ሕሊና መኖርዋን የረሱ መሰሉ ። እንቅልፍ የተጫጫነውን

ፊታቸውን እያባበሱ ከቡፌ ውስጥ ብርጭቆ አውጥተው ከሕሊና አጠገብ ከቆመ ማቀዝቀዣ ጠርሙስ ውሃ ወሰዱ ። ለሕሊና ህልም ሆነባት ። ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ስለመሆንዋ ተጠራጠረች ። ህልም ላይ መሆን አለባቸው ። እሳቸው ቢሆኑ ኖሮ ውሀ ለምን ቀጠነ ትዕዛዝ ያዥጎደጉዱ ፣ እኔንም ያተራምሱ ፣ ግራ ያጋቡኝ ነበር ። እውነትም ህልም መሆን አለበት አለች ። ምናልባት በዝምታ ስቃይዋን እያራዘሙት ቢሆንስ ? እንደሳቸው ባህሪ ከዚህም በላይ ሊያደርጉ ይችላሉ ። ሕሊና ለጊዜውም ቢሆን ከሳቸው ፊት ራቂ ራቂ አላት ። ትንፋሽዋን ብትመልስ ይሻላት ይሆናል ። ከፋቱ ፍላጎቷ ምኞት ነው ። ማነው « ደሀ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ንጣት ይገድለው ነበር » ያለው ። ከፊት ለፊታቸው ቡና ማፍላት አለባት ።

የሰውነቷ ትኩሳት ጨመረ ። ለወ/ሮ አባይነሽ ቡና ላለማፍላት የምትችልበት መንገድ ቢኖር በማለት ማሰብ ጀመረች ። ሆኖም ተደርጎ አያውቅም ። የሥራ መመሪያ ከደረሳት ቀን ጀምሮ ሌላ ሰው ለወ/ሮ አባይነሽ ቡና አፍልቶ አያውቅም ። የእውር ድንበሯን ሳሎን ቤቱን ጽድታ ወደ መኝታ ክፍሏ ስትሄድ ሰለሞንን አገኘችው ።

« እራሴን ከፋኛ አምኛል እትዬን ጥራልኝ » በማለት ፊት ለፊት ካለው በረንዳ በሁለት እጆችዋ እራስዋን አስደግፋ ተቀመጠች ። እስካበች መልዕክቱ እንደደረሳት አፍታ ሳትቆይ ደረሰች ።

« ምነው ሕሊና ? እኔን ፣ እኔን ፣ አመመሽ እንዴ ? » ብላ አጠገቧ ተቀመጠች ።

« ነይ ከፀሐይ ላይ ተነሽ » ስትል ደግፋ አንስታ ወደ ክፍሏ ወሰደቻት ።

በሕሊና መታመም በጣም ካዘኑት ሰለሞን አንዱ ነበር ። ወደ ቤታቸው ለመግባት ምክንያት ለማግኘት በበሩ አካባቢ ሊያንዣብብ እስካበች እንደ ድንገት ጠራችው ።

« ሰሰሞን ሂድና ከዋናው ቤት ከሰልና ምድጃ ይዘህ ና ፣ ጎሽ ቶሎ በል » ስትል ግማሽ ትዕዛዝ ግማሽ ልመና በሆነ ቃል ተናገረች። እሱም ለሕሊና ይህን እገዛ በማድረጉ እየተደሰተ በፈገግታ ትዕዛዙን ተቀብሎ በፍጥነት ወደ ዋናው ቤት ሄደ ። ምድጃውን በከሰል ሞልቶ እሳት ከኩሽና ወስዶ ከአቀጣጠለ በኋላ ወደ አስካበች ክፍል ይዞ ተመለሰ ። ወለሉ ላይ የሕሊና የሳር ፍራሽ ተዘርግቷል ። ከላዩ ላይ የአልጋ ልብስ መሳይ ጣል ተደርጎበታል ። አስካበች ሰለሞንን ቡና እና የቡናውን አጃቢዎች እንዲገዛ በድጋሚ ላከችው ። ሰለሞን ትዕዛዙን በደስታ ሲቀበል ሕሊናን አክሞ የሚያድን ያህል ነበር የተሰማው ። በመካከል ላይ ሕሊና ዓይኗን ገልጣ ጣሪያ ጣሪያውን እየቃኘች ስትቃብዝ አስካበች ጠጋ ብላ « ሕሊና ተሻለሽ ? » ስትል በጉጉት ዓይን እየቻት ። እራስዋን በማንቀሳቀስ የአዎንታ መልስ እየሰጠች ከወገብዋ ብድግ ብላ ለመነሳት ሞከረች ።

« የት ልትሄጂ ነው ? » ስትል ጠየቀቻት « ወደ ሥራ ፤ እዚህ ተኝቼ ምን አደርጋለሁ ? ተነስቼ አልጋ ላከራይ » አለች ።

« በይ አሁን ተኚ ! ሥራው እየተሰራ ነው ። አንቺ የሚፈልግ ሥራ የለም ፣ ለመሆኑ መነሳት ትችያለሽ ? » በማለት የሰውነቷን ትኩሳት ለመለካት እጅዋን በግንባሯ ላይ አሳረፈች ።

« ገና ነሽ ፤ እራስሽ እንደ እሳት ያቃጥላል » አለቻት ። ትዕዛዝ ለማክበር ያህል ፍቅር የተሞላበት ፈገግታ አሳይታት መል በትራሱ ላይ አረፈች ።

ሰለሞን የያዘውን ዘንቢል አስቀድሞ ወደክፍሉ ውስጥ ሲገባ ሕሊና ነቅታ በማየቱ ፈገግ ብሎ « እንደምን ዋልሽ ሕሊና ተሻለሽ?» ሲል ጠየቃት ።

« ተሽሎኛል ፤ ሰለሞን ምን ይዘህ መጣህ ? » ብ ጠየቀችው እሷም በፈገግታ ።

« ጉዝጓዝ ፣ ቡና ፣ ነጭ ማሽላ . . . » ሕሊናን ለማንጓት ይችላል ብለው ባሰቡት አነጋገር ሕፃን ልጅን ለመሸንገል እንደሚያደርጉት ሁሉ አስካበች ተናዘዘች ።

« እትዬ ይህ ሁሉ ለምንድነው ? እኔ እንደሆንኩ ድኛለሁ፤ ለምን ትቸገሪያለሽ ? » አለቻት ።

« ለቤቱ ነው ፤ ማነው ላንቺ ነው ያለሽ ? ይልቁንስ ተኚ እንደገና እንዳያምሽ ። የራስ ህመም እረፍት ያስፈልገዋል ። » ከተቀመጠችበት እየተነሳች ተናገረች ። ሳሩ ተጎዝጉዞ ፣ ሲኒዎች ተደርድረው ፣ ወገግ ባለው ፍም ላይ ጀበናው ተጥዶ ፣ ቤቱ በከርቤ ዕጣንና በሰንደል ጭስ ታፍኗል ። አስካበች ነጠላዋን ተከናንባ ፍራሹ ላይ ተቀምጣለች ። ሕሊናም ክንዷን በትራሱ ላይ ተክላ እራስዋን ድጋፍ ሰጥታ አጠገብዋ ወንበር ላይ ከተቀመጠው ከሰለሞን ጋር ታወራለች ። ስንተኛ ክፍል እንደሆነ ፣ ትምህርት ቤት ከገባ ስንት ዓመት እንደሆነውና በአጠቃላይ ስለ ትምህርት ትጠይቀዋለች። በመጨረሻም ፣

« ሰለሞን አንድ ነገር ልጠይቅህ ? » አለችው ።

« ጠይቂኝ ከቻልኩ እመልሳለሁ » አላት ።

« ሰለሞን እስኪ ፊደል አስተምረኝ ? »

« ከፈለግሽ ዛሬውኑ እንጀምር »

አስካበች ንግግራቸውን በጥሞና ስታዳምጥ ቆየችና ፣ « ዛሬማ አይሆንም ፣ በሌላ ቀን ፣ እትዬ ሳያዩ ይሻላችኋል » አለቻቸው። ሕሊና አክስቷ ወ/ሮ አባይነሽ መማር ስለመቻልዋ ስለሚኖራቸው ግምት እስከዛሬ አስባበት አታውቅም ነበር ።

« እቴቴ ቢያዩ ምን ይላሉ ? » አለች ።

« አይ ልጄ አክስትሽ የሚማር ሰው አይወዱም ። እነ ሰለሞንም በስንት መከራ ፣ በእናታቸው ጉብዝናና ባአማላጅ ብዛት

ነው የተፈቀደላቸው ። ያም ቢሆን ሁልጊዜ አይደለም ። ጥፋት ባጠፉ ቁጥር ከት/ቤት በማስቀረት ነው የሚቀጡት ። » አለቻት ።

የአስካበች ንግግር ለሕሊና ጥሩ መሠረት ሰጣት ። ባላቸው ትርፍ ጊዜ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ትምህርቱን ለመጀመር ከሰለሞን ጋር ተስማሙ ። አስካበችም ሃሳባቸውን በመደገፍ በትርፍ ጊዜዋ የሕሊናን ሥራ ለመሸፈን በራሷ ፈቃድ ቃል ገባችላቸው ። ምሽቱ በመግፋቱ ሰሰሞን የደህና እደሩ ሠላምታውን አቅርቦ ተሰናብቷቸው ወጣ ።

« በይ እንግዲህ ሕሊና ዛሬ አንቺ በሽተኛ ስለሆንሽ አልጋ ላይ ተኚ » አለች አስካበች መሬት ላይ ያለውን የሕሊናን ፍራሽ እያስተካከለች ።

« አላደርገውም ። እኔ መሬት ላይ ነው መተኛት ደስ የሚለኝ። አልጋ ላይ መተኛት አለመድኩም » ከአልጋ ወርዳ ፤ አስካበች የምታስተካክለውን ፍራሽ ተቀብላ ከረጢቷን ትራስጌዋ አድርጋ ቁጭ አለች ። አስካበች ተጨማሪ ክርክር ማድረግ ዋጋ የሌለው መሆኑን ተገነዘበች ። ወደ አልጋዋ ሄዳ ለመተኛት ስትመቻች የሕሊናን ሥራ አስተዋለች ።

« ይህች ልጅ ምን ደግ ቢሰሩላት ሆዷ አይገኝም ። አሁን እኮ ከዚያ ከመጥረቢያ ላለመለየት ነው ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ ፤ የአህያ ሥጋ ከአልጋ ሲሉት አመድ አሉ ፤ ለምን እራስዋን ትበድላለች ? » አለች ለራሷ ።

* * *

ወ/ሮ አባይነሽ በአብዬ ጋሻዬና በሕሊና መካከል የተፈጠረው ሁኔታ በጣም ስላሳሰባቸው የመሰላቸውን እርምጃ ወሰዱ ። ከግል ደንበኞቻቸው ጋር የሚያቀራርብ ሥራ በወንዶች እንዲከናወን በማድረግ ሕሊናን ጨምሮ ሴቶቹን አራቁ ።

የቤቱን ፅዳት በቀን ከማከናወንና ቡና ከማፍላት በስተቀር ሕሊና በምሽት ወደትልቁ ቤት መሄዷ ቀረላት ። ይህም ለሕሊና ጥሩ አጋጣሚ ሆና ከሰለሞን ጋር ለጀመረችው ምስጢር አመቺ ሁኔታ ፈጠረላት ። ሕሊና የቅጥያ ምልክቶች ቢያስቸግሯትም የራሷን ስም በግዕዝ ደረጃ « ሀለነ » እያለች መፃፍ ጀምራለች ። በአጭር ግዜ የአባቷን ተስፋ ፤ የራሷን ምኞት እንደምትጨብጥ እየታያት ክፉና ደጉን በጸጋ ተቀብላ መኖር ጀምራለች ።

አንድ ቀን ምሳዋን በልታ ጥናት ላይ ሆና ሰለሞንን ስትጠብቀው ዘግይቶ በመምጣት የረባ ሠላምታ ሳይለዋወጡ ያልጠበቀችውን መርዶ አረዳት ።

« አሁን የመጣሁት ዛሬ ማታ መምጣት እንደማልችል ልነግርሽ ነው » አላት ።

« ምነው ምን አጋጠመህ ? » ስትል ጠየቀችው በድንጋጤ ።

« ሕሊና አትቀየሚኝ የእኔንና የአንቺን በተደጋጋሚ አንድ ላይ መሆን ወ/ሮ አባይነሽ በመስማታቸው እናቴን ጠርተው ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋታል ። ስለዚህ ነገሩ እስኪረሳ ለተወሰነ ጊዜ መራራቅ ይኖርብናል » ሲል በማሳዘን ነገራት ።

« ምን አድርጊ ነው የሚሉኝ ? እኔ ብማር አሁን ምን ይጎዳቸዋል ፤ የተሰጠኝን ሥራ እንደሆን ምንም ሳላጓድል እየሠራሁ ነው ። ለምን ሰው እንዳይማር ይፈልጋሉ ? » በማለት እንባ የሞላውን ዓይኗን በሰለሞን ላይ አሳረፈች ።

« ግድ የለም ሰለሞን እስከአሁን ላደረክልኝ ዕርዳታ ከልብ አመሰግናለሁ ። ለወደፊቱ የሚቸግረኝን አልፎ አልፎ እጠይቅሃለሁ ። አሁን አጀማመሩን ካወኩት እኔው ራሴ ፊደል ቆጠራውን ለመጨረስ እሞክራለሁ ። በኔ ምክንያት በእናትህና በአንተ ላይ ችግር ማምጣት አልፈልግም » አለችው እያለቀሰች ። ሕሊና ያሰበችው አልቀረም ። ከሰለሞን ጋር የነበራት ግንኙነት ቢቋረጥም በጥረቷ በአጭር ጊዜ ውስጥ በእጇ የገባውን ጽሑፍ ለማንበብ ቻለች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ባይፈልጉትም ፣ ሊቆጣጠሩ ቢሞክሩም ሕሊና ማንበብና መፃፍ መቻሏን ተረዱ ። ለዚህ ሁሉ ለማይፈልጉት ነገር ሆና መገኘት ዋናዋ ጠላታቸው አስካበች እንደሆነች ራሳቸውን አሳመኑ ። በዚህ ዓይነት ሌላም ነገር ሊፈጠር እንደሚችል መጥፎ ሽታ አጠናቸው ። የሚጎዳቸው ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት መፍጠን አለባቸው ። አስካበች እራሷ ቂም ልታረግዝባቸው እንደምትችል ልባቸው ያውቀዋል ።

አንድ ቀን ሕሊና ወደ ቅልቁ ቤት ተጠርታ ትሄዳለች ። ወ/ሮ አባይነሽ ትልቁ ቤት ሳሎን ፎቴ ወንበር ላይ ጉብ ብለው ይጠብቋት ነበር ። በርጩማ አምጥታ ፊት ለፊታቸው እንድትቀመጥ ያዟታል። ሕሊና ክበሩ አጠገብ ወደ ግድግዳው ጠጋ ብላ ከወ/ሮ አባይነሽ ትይዩ ተቀምጣ ሁለት እጆቿን እንደሚታጠብ ሰው እርስ በርሱ እያፋተገች መሬት መሬቱን ትመለከታለች ። ለጥሩ ነገር ሊጠሯት እንደማይችሉ በመገመት ክፉውን ነገር በትዕግስት ለመቀበል ራሷን ተዘጋጅ ትለዋለች ።

« ሕሊና ትምህርትሽ እንዴት ነው ? » አሏት ወ/ሮ አባይነሽ። ለጥያቄአቸው መልስ ሳይጠብቁ « ቸኮልሽ እንጂ እኔማ ቄስ ትምህርት ቤት እንድትገቢ እያሰብኩ ነበር ። ሆኖም የዕድሜሽ ነገር እኮ ነው ችግር የሆነብኝ ። አሁን በዚህ ዕደሜሽ ከነዚያ ህጻናት ጋር አንድ ላይ መዋሉ ላንቺም ደስ አይል ፤ እኔም አላደርገው ።

የአባይነሽ ዘመድ በዚህ ዕድሜዋ እማራለሁ እያለች ትጨማለቃለች መባል ከሞት ይቆጠራል » አሏት ለስለስ አድርገው ። ሕሊና የወ/ሮ አባይነሽ ንግግር መርዘኛ እንደሆነ ወዲያው ነበረ የገባት ። ሰው ሲጎዱ ፣ የመጣን ተረኛ ወንድ ሁሉ የግላቸው ሲያደርጉ ፣ የሉ ብቻ እንደሆኑ ሲያሳምኑ በእንዲህ ዓይነት የማሳዘን መንፈስ ነው ።

ወ/ሮ አባይነሽ የጀመሩትን ቀጠሉ ። « አሁን እንግዲህ ማን አለኝ ብለሽ ነው ? አንቺ ብቻ እኮ ነሽ ቀሪ ዘመዴ ። ሁሉም ባዕድ . . . ነገ ቀን ቢጎድልብኝ ጥሎኝ እንደሚሄድ አልጠራጠርም ።

« ሥጋ ከዘመዱ አህያ ካመዱ » አይደል ! እኔ እስከአሁን መጣፍና ማንበብ የሚችል ተቆርቋሪ ሰው በማጣቴ ይኸው የምግብና የመጠጥ ሂሳቡን እነዚያ ጋለሞታዎች እያጭበረበሩኝ ነው . . . » በማለት ከንፈራቸውን እየነከሱ ቀና ብለው ግድግዳ ግድግዳውን ተመለከቱ ።

« አሁንማ አንቺ አለሽኝ ፤ እንደ ድሮው መፈንጠዝና የፈለጉትን አስቀርተው የቀረውን ከመስጠት እንዲቆጠቡ ታደርጊልኛለሽ ። አይደለም ሕሊና ? » አሉዋት ። ሕሊና ዕውቀቷን በመጠራጠር ፣ በተለይም ማንን ጋለሞታ ብለው እንደሰደቡ ስለምታውቅ ዝም አለቻቸው ።

« ሕሊና ከእንግዲህ ወዲያ አንቺ ልጅ አይደለሽም ። እስካሁንም ችላ ያልኩ የመሰልኩት ሁሉን ነገር እንድታውቂው ብዬ ነው ። ከአሁን በኋላ የምትሰሪው ሥራ በጽዳትና በመሳለለው መሆን የለበትም ። አየሽ የኛ ዘሮች ወራዳና ቆሻሻ ሥራ አይሠሩም » አሏት። ሕሊና መልስ አልነበራትም ። በተሰላቸ ስሜት የተመረጠላትን ሥራ እስክትነገር በዝምታዋ ገፋችበት ።

« ሰማሽ ? ሕሊና ከነገ ጀምሮ ሥራሽ ይህ ይሆናል » አሉና ከተቀመጡበት ተነሱ ። ሕሊናም አብራ ተነሳች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ፈገግ አሉና ወደ ሕሊና ጠጋ ብለው ለመጀመሪያ ጊዜ ትከሻዋን በአንድ እጃቸው ያዝ አድርገው በሌላው ነፃ እጃቸው ፀጉሯን ነካ ነካ እያደረጉ « ጎሽ የእኔ ይሉ ምን ጊዜም ሥጋ ሥጋ ነው ። አሁን ሁለት ቆንጆ አዳዲስ ልብስ አስቀድድልሻለሁ » ሲሉ ገለጹላት ። የአክስቷ መለወጥ ገዘፈባት ። ምን ታይቷቸው ይሆን ? ስትል ለውጡን በመልካም መንፈስ ለማየት ሞከረች ። የማይለወጥ ነገር የለም ። አክስቷም ተለውጠው ሊሆን ይችላል ።

« ምን አለበት ለዘለዓለም በሁለንተናቸው እንዲህ ለስላሳና ደግ ቢሆኑ » እያለች ከራሷ ጋር እያወራች ወጥታ አስካበች ዘንድ አመራች ። አስካበች አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብላ ምሳ አቅርባ ስትጠብቃት ደረሰች ።

« እትዬ ቆየሁ እንዴ ? » ስትል እጠገቧ ሄዳ ቁጭ አለች ።

« ለመሆኑ ምን አድርጊ ነው የሚሉሽ » አለቻት አስካበች ።

ሕሊና ፊቷ ከቀረበው ማዕድ ወደ አፏ እየላከች ፣ « ዛሬስ ተይኝ እባክሽ . . . ዝምድናችንን ስናረጋግጥና ዘራችንን ስንቋጠር ውዬ መጣሁ » አለቻት ። «ምነው በስጋነትሽ ተጠራጠሩሽ ደግሞ ?» ስትል ጠየቀቻት ። « ምን መጠርጠር ይባላል የበለጠ ማረጋገጥ ነው እንጂ » አለች ቅሬታ ባዘለ ስሜት ። ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ ሕሊና ቀጠለች፤ « እትዬ እኔ እንጃ ፍርሃት ፍርሃት አለኝ ። ይህ ሁሉ ደግነት ለጤናም አልመሰለኝም » ብላ ፊቷን በማኮሳተር ልትጎርስ የነበረውን እንጀራ ሳህኑ ላይ ተወት አድርጋ አስካበች ትከሻ ላይ ጋደም አለች ።

« ምነው ? ክፉ ነገር ተናገሩሽ እንዴ ? » አለቻት ። « ክፉማ ቢሆን ጥሩ ነበር ። ደግነታቸው ያለቅጥ በዛብኝ ፣ ልብስ አስፋልሻለሁ፤ አንቺ ወራዳ ሥራ መሥራት የለብሽም ፤ ሥጋዬ ነሽ እኮ ይሉኛል » ።

« ታዲያ ምን ቸገረሽ የምትሠሪው ሥራ የልፋትሽና የላብሽ ዋጋ ነው ። ከተስፋልሽ ሥራም አትስሪ ካሉሽ ተቀምጠሽ መጽሐፍሽን ማንበብ ነው ፤ ምኑ አስጨነቀሽ ? » ሕሊናን ብዙ ነገር እንደሚያስጨንቃት ለአስካበች ማን በነገራት ! « ጋለሞታ » የተባለችው አስካበች እንደሆነች ፤ ሴራው ከሷ ጋር ለማቆራረጥ እንደሆነ ማን በነገራት ! ሕሊና ሁሉ ነገር ፍች የሌለው ቅዠት እንዲሆን ተመኘች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ያሰቡትን ፈጸሙ ። የመኝታ ቤቱን ሥራ ለፈሩቅ ሰጡ ። የሕሊና ሥራ በዋናው መጠጥ ቤት ሂሳብ ያዧን መከታተልና ከዚህ ቀደም አስካበች ትለራው የነበረውን አጠቃላይ ቁጥጥር ያጠቃልላል ። ይህን የሕሊናን አዲስ ኃላፊነት ወ/ሮ አባይነሽ ራሳቸው ለሠራተኞቹ በግንባር ቀርበው አውጀዋል ። ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ድርጊታቸው የፈለጉትንም ያህል ባይሆን በመጠኑ ሳይሰራላቸው አልቀረም ። ድርጊቱ ለሕሊና ባይገባትም አስካበች ግን ከእርሷ ጋር የነበራትን ግንኙነት እያራቀች እየቀዘቀዘች መጣች ። እንዲያም ሆኖ ሕሊና አስካበችን ተክታ መሥራት ከጀመረች ሦስተኛ ሣምንቷን አሳለፈች ። አንድ ባለ ሦስት ብር የመኝታ ቤት ተለይቶ ተለጥፏት ከረጢቷን ተሸክማ ገብታለች ። አብዛኛውን ጊዜ ምግቧን የምትበላው በዚያው በምትሰራበት ቦታ ሆነ ።

ሕሊና በመልኳም ሆነ በአለባበሷ የደረሰች ልጅ ስለመሰለች ሰው ዓይን ገባች ። ፀጉሯን ለሁለት ከፍላ ጉንጉን ተሠርታለች ። ከደረቷ ገና ወጣ ወጣ ያሉት ጡቶቿ የለበሰችውን ልብስ ብድግ ብድግ አድርገውታል ። ከሁሉም የበለጠ ሰውን የመሳብ ኃይል ያለው በመላ ፊቷ የተሳለው ውበትዋ ነው ። በመጠጥ ቤቱ የሚገባ ደንበኛ አዲሷን ለጋ ወጣት ዓይኑን ጥሎባት ነው የሚያልፈው ። በሆነው ባልሆነው ጠጋ ብሎ ለማነጋገር የሚፈልጋትን በቀዘቀዘ ስሜት መሸኘቱን ችላበታለች ። ቀደም ሲል ከነበራት ህይወት ብዙ መጥፎ

ፀባዮችን የተላመደች ስለሆነ ምንም ግራ የሚያጋባት አልነበረም ። ቢሆንም አዲሱ ሥራዋ በጣሙን አማሯታል ። አልፎ አልፎ ማንበብ ብትፈልግ ጊዜ የላትም ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የአስካበችን ሥራ መቀማት ስበቡም ሆነ ቀሚዋ ራሷ መሆንዋን ስታሰላስለው በተፈጠረው አጋጣሚ ውስጧ ያሰቅሳል ። ነገር ግን በሰው ቤት ይህን እሰራለሁ ፣ ይህን አልሰራም ብሎ መምረጥ አይቻልም ። የታዘዘችውን ስርታ የዕለት ጉርሷን ማግኘት አለባት ።

አስካበች ህይወቷ ባዶ መሆኑን የተረዳችው ውሎ ሲያድር ነበር። ሒሊና ከከዳቻት ወዲህ ብቸኛ መሆኗ በጣም እየተሰማት መጣ። በቤት ውስጥ ካሉት ሰዎች ጋር ሁሉ መነታረክና ተራ ስድቦችን መለዋወጥ ከጀመረች ሰነበተች ። አልፎ አልፎ ከአቅሟ በላይ በመጠጣት መስከር ፣ የማታ ማታም ካገኘችው ሰው ጋር በአንዱ መኝታ ቤት ተዳብላ ማደር ጀመረች ። ነገር ግን ብሶቷን ለማንም አታወራም ። ወ/ሮ አባይነሽም ባገኙዋት ቁጥር አንጀት የሚበጥስ ንግግር ይናገሯታል ። ግን ከሳቸው ቤት ለቆ መውጣቱን ስለምትፈራ ስድቡን ፣ ክፉ ንግግሩን ሁሉ በመጠጥ ልታጥበው ትሞክራለች ።

አንድ ቀን እኩለ ለሊት ወደ ማሰፉ ግድም ነበር ። ሒሊና መኝታ ቤቷ ገብታ የአባቷን ማስታወሻ መጥረቢያ አልጋዋ ላይ አስቀምጣ በአባቷ ትዝታ ውስጥ ሰጥማ ሳለች ድንገት የመኝታ ክፍሏ በር በኃይል ይመታል ። የተሳሳተ ሰው ይሆናል ብላ ዝም አለች ። በድጋሚ በሩ በኃይል ተደበደበ ። ሒሊና በመደናገጥ ብርድ ልብሷን አንስታ መጥረቢያውን ሸፈን በማድረግ ፣ « ማነው ? » ስትል ጠየቀች በፍርሃት ።

« ክፈች ፣ ክፈች ነው የምልሽ ! » የሚል የሰካራም ድምፅ ተሰማት ። አስካበች ነበረች ። ሒሊና አላመነታችም ። በድንጋጤ መንፈስ ውስጥ እንዳለች በሩን ለመክፈት መቀርቀሪያውን በማላላት

ላይ እንዳለች አስካበች በሩን በርግዳው ገባች ። ለቅጽበት ፊት ለፊት ተያዩ ።

« ትሞቻለሽ ! አንቺ መጥፎ ሰው ትሞቻለሽ ! » አለች አስካበች ሰውነቷን መቆጣጠር አቅቷት እየተወላገደች ። ሒሊና በሰማችው ንግግር ሳትደናገጥ አስካበችን አልጋዋ ላይ አሳረፈቻት ። አስካበች ፊቷን አልጋው ውስጥ ቀብራ ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች። ሒሊና የአስካበች ስሜት ተጋብቶባት አልቅሽ አልቅሽ ቢላትም ጊዜው አመቺ ባለመሆኑ ራሷን ተቆጣጥራ አስካበችን ማረጋጋቱን መረጠች ።

« እትዬ እረባክሽን ሰው እንዳይሰማ ዝም በይ » አለች ። ሒሊና የፈራችው ግን አልቀረም ። የመኝታ ቤቶች ኃላፊ ፣ ፈሩቅ የሒሊናን ክፍል በር ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ ።

« ምንድነው ብጥብጡ ? የተኛ ሰው ለምን ትረብሻላችሁ ? » በማለት ሒሊና ላይ ጮኸ ። ሒሊና ለጥያቄው ማስተባበያ ለመስጠት ጊዜ አላገኘችም ። አስካበች ድንገት በብርድ ልብስ ተሸፍኖ የነበረውን መጥረቢያ አንስታ ወደፈሩቅና ሒሊና ፈጠነች ። ሒሊና እንደ ብራቅ ጮኻ ወደ ውጪ ወጣችና ፣

« ተጋደሉ ! የለው ያለህ ! » ስትል እኡኡታዋን አቀለጠችው ። ከመኝታቸው ተነስተው ልብሳቸውን ለመልበስ ጊዜ ያጡ ደንበኞች በእንሶላና በግማሽ ልብሳቸው ሆነው ጩኸት ወደተፈጠረበት አካባቢ በሩጫ ተሰባሰቡ ። ግማሹም ባለበት ሆኖ ምንድነው ? ምንድነው ? እያለ ሲጠይቅ የአካባቢው ሠላም እየደፈረሰ ለመሆኑ በትርምሱ ያስታውቅ ነበር ።

ፈሩቅ ደሙን እየበራ ፣ መጥረቢያውን በአንድ እጁ ይዞ ብርሃን ወደአለበት ወደ በረንዳው መብራት አካባቢ ተጠጋ ። « ምን አደረካት ? » ስትል ጮኸች ሒሊና አፏ ላይ እንደመጣላት ፣ በሁለት እጆችዋ እራሷን ይዛ ።

« ምን አደርጋታለሁ ? ይህች ሰካራም » ብሏት ጋቢ ለብሰው ገና በመድረስ ላይ ወደ አሉት ወ/ሮ አባይነሽ አመራ ። ሕሊና በማታውቀው ኃይል ተገፍትራ ወደ ክፍሏ ገባች ። ያየችውን ማመን አልቻለችም ። ክፍሏን ዘጋች ።

« እንዴት አድርጎ መጥረቢያውን ሊቀማት ቻለ ? » ወለሉ ላይ ተዘርግታ ፊቷ ወደ ምድር የተደፋውን አስካበችን በእጇ ነካ ነካ አደረገቻት ። ሁለቱም ክፍሉ ውስጥ እንዳሉ በሩ ተበርግዶ ተከፈተ ። የወ/ሮ አባይነሽ ግዙፍ ሰውነት ከዳር እስከ ዳር በሩን ሞላው ። ግንባራቸውን ቋጠር ፈታ እያደረጉ አስካበችን አተኩረው ሲመለከቱ ቆይተው ፣ ንዴት በርትቶባቸው ለመናገር ብዙ ጊዜ ከወሰዱ በኋላ ፣

« ጥጋብሽ ብሎ ብሎ ለዚህ አበቃሽ ፤ አንቺ ምን ታደርጊ ። እኔ ነኝ ጥፋተኛዋ ! « መጀመሪያ እንቁላል ስሰርቅ . . . » አለ ሰውየው ! እንቡላሽን እየተጋትሽ መጥተሽ ቤቱን ስትረብሺ በትዕግስት ሳልፍሽ ነው ነገሩ የጠፋው ! እኔ ደግሞ አብረን ኖረናል ፤ ክፉና ደጉን አይተናል በማለት ሁሉን ነገር ብተው ውለታዬ ይሄ ይሁን ? ለመሆኑ ልጁ ምንሽ ላይ ደረሰ ? ለምን ለአባይነሽ ተቆረቆርክ ነው ? » ሰውነታቸውን እያውረገረጉ እጃቸውን ወገባቸው ላይ አድርገው እንደአስክስታ ወራጅ አንገታቸውን እየሰበቁ ፣

« እኮ ንገሪኝ ! ይህ ልጅ ምን አደረገኝ ነው የምትይው ? ሌት እንቅልፍ የለው ፤ ቀን እንቅልፍ የለው ። ለምን የአባይነሽ ቤት አልተዘረፈም ነው ? እንደፈለግነው እንጫወትበት ነው ? ይንጋልኝ ብቻ የአቃቂው . . . አይለመነኝ እሰራልሻለሁ » ብለው ንዴታቸውን ተወጥተው ፣ ፊታቸውን መለስ ከማድረጋቸው አስካበች ከነበረችበት እመር ብላ ተነሳች ።

« መጣሽ አንቺ ደም መጣጭ አረመኔ ! የአባቴን ሀብት ሙጥጥ አድርገሽ በልተሽ ጨረሽና እኔንም እንደሎሚ መጠሽ ፣ መጠሽ ሲበቃሽ እንደአሮጌ ቁና ልትጥይኝ ትፈልጊያለሽ ። ገብስማ

ዶሮ ፣ ጥቁር በግ ጠምዝዘሽ እየጣልሽ ሰውን ማፍዘዝ ሁልጊዜ የሚሳካልሽ እንዳይመስልሽ . . . ይሄ ደግሞ ደንደሳም የወንድ አልጫ አለሁ ይበል ! ትናንት ቅማሉን አራግፎ ዛሬ ከሰው እኩል ሆነና እኩል መናገር ጀመረ ። ወይኔ አስካበች ! ድራሽ ቢስ ደሃ ምንጊዜም ውሉን አይስትም ስሚ ! » አለች አመልካች ጣትዋን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቀስራ ።

« ካለእኔ የሚያውቅ የለም ። ጉድሽን ነገ ለአደባባይ አበቃዋለሁ » ስትል ዛቻ አከለችበት ።

ወ/ሮ አባይነሽ የሚሰሙት ጉድ ከአስካበች የወጣ አልመሰላቸውም ። ጆራቸውን በመጠራጠር ወደ ግራ ወደ ቀኝ እየተመለከቱ ማረጋገጫ ፈለጉ ። . . . ከፈዘዙበት ሲነቁ ሌላ ነገር ከመስማታቸው በፊት እራሳቸውን ማግለል እንደሚኖርባቸው ወሰኑ። የፈሩቅን የቆሰለ እጅ ይዘው ወደ ቤታቸው አመሩ ።

« ይቺ እርጉም ሀሳቧስ ሌላ ነበር ። እግዜር አተረፈህ ልጄ፣ የአንተ ሲገርመኝ እኔንም ወረደችብኝ እኮ ፣ ሠይጣን የተፈናጠጣት ፣ አሁን ምን ነካት ይባላል ? . . . ሁሏም አንድ በአንድ ልቅም ብላ ትወጣታለች እንጂ በአንተስ ቀልድ የለም ። የማላውቅ መሰላቸው እንዴ ለምን እንደጠመዱህ ? ለእኔ በመቆርቆርህም አይደል እንዲህ የተነሱብህ ፣ ሌላ ምናቸውን ነካህባቸው ? » አሉ ዓይናቸውን ከእጁ ላይ ነቅለው ፊት ፊቱን እየተመለከቱ ።

« እኔ ያደረኳቸው አንድም ነገር የለም ። በተለይ አስካበች ሥራዋን ከለቀቀች ወዲህ ልታናግረኝ እንኳን አትፈልግም ። ተሰብስበው እንኳን ሲያወሩ እኔ ከደረስኩ በየአቅጣጫው ይበታተናሉ። ይህች ሕሊናም ብትሆን ፊት ለፊት አትናገርም እንጂ ውስጥ ውስጡን ተንኮለኛ ሳትሆን አትቀርም ! እንደው ስራዋ ሁሉ እንደ ምስጥ ነው ። » ወ/ሮ አባይነሽ የሕሊና ሥም ሲነሳ ንዴታቸው ነፍስ ዘራ ፣

« ይቺ እከካም ፣ ዘረ ኮብላይ ፣ የዘላን ልጅ እንደው እግዚአብሔር ተቃጠይ ሲለኝ አይደለም እሺ ብዬ የተቀበልኳት ! ቆይ ለእሷም ቢሆን መድኃኒት አለኝ ። ቆይ ኧረ ቆይ እያንዳንዳቸውን የማደርገውን አውቃለሁ ፣ ነገ እዚች ቤት ጉድ ይፈላል » በማለት የነገውን ቀን በዓይነ ህሊናቸው ቅርፅ ሰጥተው አሰላሰሉ ። እስካበችን በለመዱት አቀራረብ ይቅርታ እንድትጠይቃቸው ሲያደርጉ ፣ ሕሊናም የአስካበችን ፈለግ እንድትከተል ልክ ልኳን ሲነግሯት እየታያቸው ፊታቸው ፈገግ ሲል ይሰተዋል ነበር ።

« በል ነገ ክሊኒክ ትሄዳለህ ። ለአዳርህ ህመሙ ብዙ አይሰማህም ። እንደው ግድ ሆኖ ነው እንጂ ለብርዱ እዚሁ ሳሎን አንጥፈህ ብትተኛ እወድ ነበር ። »

« ኧረ ምንም አይደለም እሜቴ ። ጨርቅ ከጠቀለልኩበት ምንም አይለኝም » በማለት ብድግ ብሎ እጅ ነስቶ ወደ ሰሊት ስራው ሲያመራ ወ/ሮ አባይነሽ የፈሩቅን ቁመና ግዙፍነትና የተከሻውን ስፋት በዓይናቸው ይቃኙ ጀመር ።

እንዲህ ጥቃት በተሰማቸው ጊዜ ፤ እንዲህ ንዴት ባጋጠማቸው ቁጥር ተዳፍኖ የቆየው የወንድ አምሮት ስሜታቸው ነፍስ ዘርቶ ቅርፅ ይዞ ይታያቸዋል ። እንደአንዳች አቅበጠበጣቸው ። በደም ስራቸው እየተመላለሰ የሚበላቸውን አንዳች ስሜት የሚያሳርፍላቸውን ጠንካራ የወንድ ክንድ መንተራስ ተመኙ ። ፈሩቅን . . . ። ዘወትር ለእርድ የሚመጡትን ሰንጋዎችን እንደቀላል ነገር ጠምዝዞ ድባቅ የሚያገባ ፈርጣማ ጡንቻዎቹን ለአንድ አፍታ ቃኙ ። በዘጠኝ ዓመቱ ቆይታው በፊቱ ገጽታ ላይ የታየውን ለውጥ አጡት . . . የመልኩን ማማር አንድ በአንድ ሰለው .ማለፍያ ነው ብለው ወሰኑ። ለሌላው ደግሞ . . . ቀን ቀጠሮ ቆረጡ ።

« ወይ ጉድ ! አባይነሽ ሆ. . . ሆ ቁጭ ብዬ ላድር ነው ? » ብለው ዘርፋፋ ሰውነታቸውን እያንከባለሉ ወደ መኝታ ቤታቸው አመሩ ።

ሕሊና ሳታስበው የተቀሰቀሰው ፀብ እንዳበቃ የአባቷን ማስታወሻ መጥረቢያዋን አንስታ ወደ መኝታ ቤትዋ ብትገባም ፣ ይህን የአባቷ ምስል አድርጋ የምትቆጥረውን መጥረቢያ ለዚህ አንባጓሮ ምክንያት መሆኑ ዕረፍት ነስቷት ከተኛችበት ዞታ ሆና ትገላበጣለች ። በተለይ በመጥረቢያው ጫፍ ላይ ያየችው ደም ሕሊናዋን አሰጨነቃት ። ትኩስ ዕንባ በእራቱም መአዘን ፊቷን እየሞቀ ትራስዋን ሲያርሰው ከለመመን ነቃች ።

« ግድ የለም ለሊቱ ይንጋ እንጂ ነገውኑ ለወ/ሮ አባይነሽ አዲሱ ሥራዬ እንደአልተስማማኝ ተናግሬ እስካበች ወደ ቀድሞ ሥራዋ እንድትመለስ አደርጋለሁ » እያለች ስታወጣና ስታወርድ እጇን ወደ ትራስጌዋ ሰዳ የመጥረቢያውን እጀታ እያሻሸች የአባቷ መንፈስ ለኅላማዋ ዕናት እንዲረዳት ስትማጠን ድንገት ከውጪ የሰው ኮቴ የለማች ሰለመሰላት አቅጣጫውን ለማጣራት ጆሮዋን ቀሰራ ስታዳምጥ ኮቴው እየቀረባት ሲምጣ ተሰማት ። ሕሊና የልቧ ትርታ ጨመረ ። እጆቿን ደረቷ ላይ አስቀምጣ ድምጿን አጥፍታ የሚሆነውን በመጠባበቅ ላይ እንዳለች ያው ኮቴ በሯ ላይ ሲደርስ ባለበት ረጋ ። በሯ ሁለት ሦስት ጊዜ ቢንኳኳም ሕሊና ደፍራ በሩን ለመክፈት ወኔው አልነበራትም ። ከጥቂት ሰዓት በፊት ያየችው ዘግናኝ ሁኔታ የሚደገም መሰሎ ታያት ። ድብደባው እንደማይቆም ስትረዳ ፣

« ማ – ማነው ? » ስትል ተነፈሰች ።

« እኔ ፈሩቅ ነኝ ። መጥረቢያውን አስገብተሻል ? አጣሁት » አላት ።

« አላስገባሁትም ። ቀድሞ ነገር እኔ የት አየሁት ? » ብላ መጥረቢያውን ወደ ሰውነቷ አጥብቃ ይዛ የሚከተለውን ስትጠባበቅ የፈሩት ኩቴ እየራቀ ሲሄድ ሰማች ። ጆሮዋን በየአቅጣጫው ቀስራ መሄዱን ካረጋገጠች በኋላ መጥረቢያውን እንደታቀፈች ተጋደመች ። ፈሩት በጠዋት ተነስቶ አስካበች የተማታችበትን መጥረቢያ ፍለጋ ይንጎዳጎዳል ። ትላንት ከአስካበች ታግሎ ካስለቀቃት በኋላ የት እንዳደረሰው አሰላሰለ ። የመጥረቢያውን አድራሻ ለማወቅ አልቻለም።

« ኸረ ምንድን ነው የምትፈልገው ? ለመሆኑ እጅህ እንዴት ሲያደርግህ አደረ » አሉት ወ/ሮ አባይነሽ ። አትኩሮቱን ሁሉ በመጥረቢያ ፍለጋ ላይ አድርጎ ስለነበር የመኝታ ቤታቸውን መስኮት ከፍተው ሲያስተውሉት ልብ አላለም ነበር ።

« ተሽሎኛል እሜቴ ፣ ትላንት የተመታሁበትን መጥረቢያ እዚህ ማስደገፌ ትዝ ይለኛል ፣ ሕሊናን ብጠይቃት አላየሁም ብትለኝ ልፈልገው ብዬ ነው » በዓይኑ ወዲያና ወዲህ አማተረ ።

« የቱን መጥረቢያ ነው የምትፈልገው ? ይህች መርዘኛ የአባቴ ውርስ ነው የምትለውን ነው ? » አሉ ።

« አዎ እሱ ነው መሰለኝ ከእሷው ፤ መኝታ ቤት አውጥታ አይደል የቀለጠመችኝ ! » አለ የተመታውን ቦታ በአንድ እጁ እያሻሸ።

« የሷ መዘዝ ነው ለካ ! ይህን መጥረቢያ አውጥተሽ ማድቤት አስቀምጪው ብያት አልነበረም ? » ቢጣል ኖሮ ይህ ሁሉ እንደማይደረስ በመገመት የፈሩትን ፊት እየተመለከቱና ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ « ግድ የለም ጠፍቶ ከሆነ አያለሁ ፤ ካለም እኔው እራሴ ነኝ ከእሳት የምማግደው » ብለው ፈሩት በቆመበት ጥለውት ወደ መኝታ ቤታቸው ገቡ ።

* * *

ያለወትሮአቸው ወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤቱ ውስጥ በጠዋት ገብተው በገንዘብ መቀበያው ባንኮኒ ተቀምጠዋል ። ንዴታቸው ከፊታቸው ላይ ይነበባል ። ሆኖም ሕሊናን አላመናጨቁም ። የተደረገውንም አንስተው አልጠየቁም ። ብቻ ዝም ብለው ተቀምጠዋል ። በሆዳቸው ነገር እያብሰለሰሉ ነበር ። ሥራ ቦታዋ ያልተገኘችው አስካበች ነበረች ። በሯ እንደ ድሮው ተዘግቷል አስካበች ግን ከነጋ ብቅ ሳትል ሠዓታት ነጎዱ ። እንደ ሕሊና ምኞት የወይዘሮ አባይነሽ ንዴት ተግ እስኪል አስካበች በአካባቢው ባትታይ ፈቃድዋ ነበር ። ዛሬ ባለመምጣቷ በጣም ደስ ብሏታል ። ጊዜው እያለፈ ፣ የምሳ ሰዓት ሲደርስ የአስካበች ድምፅ በርቀትም ቢሆን ሊሰማ አልቻለም ። ወ/ሮ አባይነሽ መቁነጥነጥ ጀምረዋል ። ከነበሩበት ቦታ ተነስተው አንድ ጊዜ ወደ በሩ ፣ ሌላ ጊዜ ወደ ባንኮኒው እየገቡ የተቀመጠውን ዕቃ ወዲያና ወዲህ እያስባጠሩ ፣

« ሰምን እዚህ ተቀመጠ ?ይህ ደግሞ እዚህ ምን ይሰራል ?» እያሉ ወዲያ ወዲህ የቤቱን ሠራተኞች ሲያራውጡ ቆዩ ። ወደ ሕሊና ተጠግተው ፣ « ሂጂ እባክሽ ያቺን ሰካራም ቀስቅሺት » ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ ።

ሕሊና አስካበችን የመጀመሪያዋ ሆና ለማነጋገር ባትፈቅድም የወ/ሮ አባይነሽን ቃል መፈጸም አለባት ። አስካበች የተኛችበትን ክፍል ሄዳ በሩን ቀስ ብላ ደጋግማ አንኳኳች ። መልስ ስታጣ ጊዜ « እትዬ ! እትዬ ! » እያለች ትጣራ ጀመር ። ምንም መልስ የለም።

« እኔ ሕሊና ነኝ ! እቴቴ ይፈልጉሻል ክፈቺ ብትልም ፣ በሩ ሊከፈትላት አልቻለም ። ወ/ሮ አባይነሽ በሕሊና መቆየት ተናደው አጠገቧ እንደደረሱ « የለችም እንዴ ? ለምንድነው የማትከፍተው? » ሲሉ በጥርጣሬና በድንጋጤ ዓይነት ጠየቋት ።

« መኖር አለች ። በሩ ከውስጥ ነው የተቀረቀረው ። መልስ ግን የለም » አለቻቸው ።

« ፈሩቅን ጥሪልኝ » አሉና ወደ አስካበች በር ተጠግተው ባላቸው ኃይል ደጋግመው ደበደቡት ። መልስ የለም ። ከሕሊናና ከፈሩቅ ሌላ ሌሎችም የቤቱ ሠራተኞች በበሩ አካባቢ ራቅ ብለው ቆመው ሁኔታውን መመልከት ጀመሩ ። ሁሉም በሩ ተከፍቶ ሁለቱ ሴቶች ፊት ለፊት ሲገናኙ ማየት ይፈልግ ነበር ። የቻሉትን ያህል ቢሞክሩም በሩን የሚከፍት ጠፋ ። ቀስ በቀስ ግቢው በሰዎች ተወረረ። ሀሳብ ሰጪ በዛ ። ግማሹ በሩ ይሰበር ፣ ለጤና አይደለም ሲል ፣ ሌላው መስኮቱ ይሰበር ይላል ። በመጨረሻ ወ/ሮ አባይነሽ ፈሩቅን ፣ « ስበረው » ብለው ትዕዛዝ ሰጡት ። ፈሩቅ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ከብዙ ልፋትና ትግል በኋላ በሩን በረገደው ። ክፍሉ ወለል ብሎ የያዘውን አሳየ ። መሬት ሳይነካ በሥሩ የተንጠባጠቡት ቀያይ ፈሳሽ ምልክቶች ያልተጠበቁ ነበሩ ። ይህን ጉድ ከማየቱ ፈሩቅ ጩኸቱን ለቀቀው ። ግቢው በጩኸት ተዋጠ ። ሕሊና የተንጠለጠለውን የአስካበችን አስከሬን እንዳየች ተዝለፍልፋ ወደቀች ።

« ምነው ይቅርታ በጠየኳት »

* * *

በሚያዘወትሩበት የመዝናኛ ቤት ናቸው ያሬድና ተሾመ ። አጠገባቸው ትርሲት ነበረች ። ተሾመ ዓይኑ እንባ እያቀረረ ፣ « ለመሆኑ ዘመድ የላትም እንዴ ? ከወ/ሮ አባይነሽ ሌላ ? » ሲል ጠየቀ ። ትርሲት ከንፈሯን መጠጠችና « ምን ዘመድ ይኖራታል ! ከልጅነቷ ጀምሮ ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ነበር የምትኖረው ። ጉልበቷን መጠጡና ሕሊና ስትመጣ ዓይንሽን ለአፈር አሏት እንጂ » አለች ። በሕሊና ላይ መፍረዷ ነበር ። ያሬድ የሕሊናን ሁኔታ ቀደም ብሎ ከትርሲት ተረድቷል ። አስካበችን ተክታ ዕድሜዋን ሙሉ የወ/ሮ አባይነሽ ሠራተኛ ትሆን ዘንድ እንደተፈረደባት ገባው ። ይህን በመናገር ለሕሊና ሊከራከር አልፈቀደም ።

« ይቺ አስካበች የተባለችው ሴት ለመሆኑ ምኝ ናት እንዴ ? ጥሎ መሄድ እያለ እራሷን እንዴት ትሰቅላለች ? » አላት ትርሲትን።

« ሰውማ ወ/ሮ አባይነሽ ናቸው ያስገደሏት እያለ ያማል » ያሬድ እራሱን በአሉታ እየነቀነቀ ፣ « በምን ምክንያት ሊያስገድሏት ይችላሉ ? መቼም የሆነ ምክንያት መኖር አለበት » አለ ።

ትርሲት እጇን ወደ ላይ አንስታ « የሚነግዱትም ሆነ ለቤታቸው የሚያውሉት እህል ከአስካበች አባት መሬት ነው እሉ የሚመጣው ። አስካበች በአደራ የተሰጠቻቸው ልጃቸው ነበረች ። በኋላ ግን አባቷ ሲሞቱ መሬቱን በስማቸው አዛውረው በሴትየዋ ነፍስ መጫወት ጀመሩ » አለች በማያሳዝን ቅላፄ ።

« ህግ ባለበት ሀገር ምንድን ነው ችግሩ ? ለምን አይከሷቸውም ? » ሲል ያሬድ ጠየቃት ። « አንተ አታውቃትም ! አባይነሽ እኮ በዚህ ሀገር ንጉስ ነች ፣ ማን እሷን ይከሳል ? » አለ ተሾመ ከትርሲት ቀድሞ ።

*   *   *

በዋናው ቤት የከተማው ሰው ተሰብስቦ ወንበርና መሬት ላይ በተነጠፈው ፍራሽ ላይ ተቀምጦ በሹክሹክታ ያወራል ። ከስሩ ፍራሽ፣ መካከል ላይ ብርድ ልብስና ከላይ አልጋልብስ በተነጠፈበት ስፍራ በርከት ያሉ ሴቶች ከመካከላቸው አንዲት ወፍራም ሴት ከበው ያስተዛዝናሉ ። የተወሰኑ ራሳቸውን ገለል አድርገው የግል ጨዋታቸውን የያዙም ይታያሉ ። አስተናጋጆች አስር ጊዜ እየተነሱ ለአዳዲስ ለቀስተኞች ኮካኮላ ፣ ቡና ፣ ንፍሮ በእንቅብ ለማቅረብ ይጣደፋሉ ። የቸኮለ ወይም መሄድ የፈለገ ወደ ትልቋ ሴት ቀረብ ብሎ ማዘኑን በመግለጽ እጅ ነስቶ ይወጣል ።

ተሾመና ያሬድ እንደሌሎቹ ሁሉ እጅ ነስተው ተያይዘው ከትልቋ ሴት ትይዩ ካለው መቀመጫ ላይ አረፍ አሉ ። አንድ መልከ መልካም ረዘም ያለች ሴት ልጅ እነያሬድ ከተቀመጡበት አካባቢ ፈገግ ብላ እንቅብ መሳይ መሶብ አቀረበች ። ተሾመ ያሬድን አትኩሮ እያየ ከንፍሮው ዘገነ ።

ያሬድ መላው ሰውነቱ ደንዝዞ በደመነፍስ ወደአቀረበችው ንፍሮ እጆቹን ዘረጋቸው ። ዓይኖቹ ግን ከልጅቷ ፊት ላይ ተንከራተቱ « ሕ - ሊና አወቅሽኝ ? » አላት ለሷ ብቻ በሚሰማ የሹክሹክታ ድምጽ ። ሕሊና ለአፍታ ዓይኖቿን አጥብባ ከተመለከተችው በኋላ ከመቅጽበት የፊቷ ገጽታ ተለዋወጠ ። ግራና ቀኙን ተገላምጠች ። በተለይ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ አቅጣጫ በመሳቀቅ ቀስ ብላ ተመለከተች ። ወ/ሮ አባይነሽ ሊያስተዛዝኑዋቸው ከመጡ የሰፈሩ ሴቶች ጋር ጨዋታ ይዘዋል ።

ፊቷን ወደያሬድ መለስ አርጋ እያየችው « አውቄሃለሁ ። » ግን እንዴ . . ት ልትመጣ . . . » አላስጨረሳትም ። « ገባኝ ገባኝ ስላንቺ የነሮ ሁኔታ ሁሉንም ባላውቅም የተወሰኑ ነገሮችን ግን

እሰማለሁ ። በስራዬ ምክንያት እዚሁ አቃቂ እናንተው አካባቢ ቤት ተከራይቻለሁ ። » አላት እሱም እንደሷ ለጋት ይዞት ።

ሁኔታዎች አመቺ ባለመሆናቸው ብዙ ሊያነጋግራት አልቻለም። የወ/ሮ አባይነሽ ጐረቤቶች እግዜር ያጥናችሁ በማለት አንድ በአንድ መውጣት ጀምረዋል ። ያሬድ ከዚህ በኋላ መቆየቱ ፋይዳ እንደሌለው ስለተገነዘበ ሕሊናን በርቺ በማለት እጆቹን ለስንብት በመዘርጋት አጥብቆ ጨበጣት ። ሕሊና እነያሬድ ተርታ ላሉ ሰዎች ከንፍሮው ካስዘገነች በኋላ እንገቷን ደፍታ ወደመጣችበት ተመለሰች።

ያሬድና ተሾመ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቀረብ ብለው አንገታቸውን ዝቅ በማድረግ እግዜር ያጥናችሁ በማለት ተሰናብተው ወጡ ። ጥቂት እንደተራመዱ « የማይታመን ሰውጥ ነው ። ይህን ያህል ሰውጥ ይኖራታል ብዬ መገመቱ ይከብደኛል ። እንኳን አንድ ቀን ያያት አብሯት ያደገ ይለያታል ብዬ ለመገመት ይቸግረኛል ። » አለ ያሬድ እራሱን በመገረም እየነቀነቀ ።

« እሱን ተወውና ከእንግዲህ ምን ቀረህ ? መነጋገራችሁ መልካም ነው ። አለመርሳቷም ይገርማል ጥሩ የማስታወስ ችሎታ አላት » አለው ተሾመ ያሬድን የጎሪጥ እያየው ።

« እባክህ ተሼ አታፊዝብኝ እኔ ልጅቷን ሳይሆን . . . በማን ልማልልህ – የእናቴን ሥጋ ነው የምልህ ፤ እኛን ባልቴት . . . »

* * *

የአስካበች ድንገተኛ ሞት የወይዘሮ አባይነሽን ቤት ሀዘንና የፖሊስ ምርመራ አናጋው ። ንግዱ ቀዝቀዝ አለ ። ወ/ሮ አባይነሽ ሀዘኑን በትልቁ ቤታቸው ተቀምጠው ሰባቱንም ቀን ሳይነሱ አሳለፉ ። ነገር ግን የፖሊስ ምርመራው አስክሬኑ ከተገኘበት መኝታ ቤት አንስቶ በቤት ውስጥ ከአስካበች ጋር ግንኙነት አላቸው የሚባሉትን ሰዎች ሳይቀር ቃላቸውን እንዲሰጡ ተደርጎም አልቆመም ። ወ/ሮ አባይነሽ ፖሊስ ጣቢያ ደርሰው የሚመጡትን የቤት ሠራተኞቹን ሁሉ እያስጠሩ ጥያቄ ያቀርቡላቸዋል ። እራስዋን መግደሏ ሳይሆን ያስጨነቃቸው ራስዋን ለመግደል ያበቃትን መንስዔ ነበር ። ለአስካበች ህይወት ማለፍ ምክንያት የወ/ሮ አባይነሽ ድርጊት መሆኑን ራሳቸው ሳይጠረጥሩ አልቀሩም ። አስካበች ከመሰቀሏ ቀደም ብሎ በተፈጠረው ሁኔታ የተናገሩት ነገር ተደብቆ የኖረን ምስጢር በጥቂቱም ቢሆን ይፋ ሳያደርግ አልቀረም ። በዚህ ምክንያት የቤት ሠራተኞቹ ነገር አሳሰባቸዋል ። ሠራተኛ የሰማው ነገር ክንፍ አውጥቶ ይበራል ይባላል ።

ወ/ሮ አባይነሽ ሰው ሸሹ ። ሰው በተሰበሰበበት መታየቱን ጠሉ ። የግድ ሆኖባቸው እንጂ ሀዘኑን ባጭሩ በመቅጨት ብቸኛ ለመሆን ፈልገው ነበር ። ሰው በገባና ሀዘኑን በገለፀ ቁጥር የራሳቸው ሁኔታ እያሳዘናቸው ያለቅሳሉ ። ፖሊስ ጣቢያ ተጠርተው ቃላቸውን የሰጡ ቀን ምንም ሳይናገሩ ወደ መኝታ ክፍላቸው ገብተው ሰው ሳያዩ ቀኑንሙሉ ውለው ነበር ።

ሒሊና በአስካበች ሞት ከልቧ አዝናለች ። ይህን ትፈጽማለች ብላ አልጠበቀችም። ግፉ ቢል በስካሯ ትቀጥላለች የሚል ግምት ነበራት ። የእሷን ስራ መልሶ መስጠትና ወደ ቀድሞ ሥራዋ

መመለስ መፍትሄ ነው ብላ አስባ ነበር ። ሳይታሰብ አስካበች እራሷን አጠፋች ። ባሰበቻት ቁጥር አልቅሽ አልቅሽ ይላታል ።

« ለምን ታለቅሻለሽ ? » የሚላት ግን የለም ። ወ/ሮ አባይነሽ ብቻ የሒሊና ያን ያህል መሆን እየከነከናቸው ፣ መኝታ እየነሳቸው መጣ ። የማያውቁት ነገር ወሰወሳቸው ። ሒሊና ከመምጣቷ በፊት ከአስካበች ጋር ሠላም ነበሩ ። እሷ ከመጣች በኋላ ግን በመጀመሪያ ሆድ ለሆድ ተራራቁ ፣ ቀጥሎ ተጣሉ ፣ በመጨረሻም እራሷን አጠፋች ። ቤታቸው ተበጠበጠ ። መጪውን ማሰብ አልፈለጉም ። ይኸ ሁሉ የሆነው ግን ሒሊና ከመጣች በኋላ ነው ።

« ይህች ገሬ ዘመዶችዋን ሁሉ ጨርሳ እኔንም ልትጀምረኝ ነው ? » አሉና ካለችበት አስጠሯት ። አጠገባቸው እንደቀረበች ስለመጥረቢያው ነበር ያነሱባት ። መጥረቢያው ከአባቷ የወረሰችው ማስታወሻ እንደሆነ በመግለጽ አሁንም ከእሷ ጋር መኖሩን ነገረቻቸው።

« አባትሽ ይህን መጥረቢያ ከየት ነው ያመጣው ? » ሲሉ አፋጠጧት።

« ከገበያ ገዝቶ ነዋ ! » ስትል በፍርሃትና በጥርጣሬ መለሰች።

« እሱስ አይደለም . . . የደብተራና የቃልቻ ሥራ መሆኑን መቼ አጣሁት » አሉና በውስጣቸው ፤ « አሁን ታዲያ መጥረቢያው ምን ያደርግልሻል ልጄ ? » በማለት ጠየቋት ። ሒሊና ይህንን ነበር የፈራችው ዓይኗን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ አፍጥጣ « በቃ የአባቴ ማስታወሻ ነው ። » አለቻቸው ።

« ጅል ነሽ ልበል ። ከመቼ ወዲህ ነው መጥረቢያ የአባት ማስታወሻ ሆኖ የሚያውቀው ፤ ፎቶ አይደል . . . በይ አምጪውና፣ ማድቤት ይቀመጥ ፤ ቦታው እዚያ ነው » አሏት ።

« እቴቴ ምንም ቢሆን የአባቴ ቅርስ ስለሆነ ይተውልኝ ። ምናልባት ቀስ እያልኩ እረሳው ይሆናል ። እስከዚያው ግን

ይተውልኝ ፤ እርሶን መቼም አይጎዳዎትም » ስትል ተሰማመጠቻቸው ። አፈጠጡባት ። አፌ ሡፌ አውሬ መስሰው ታይዋት አፈገፈገች ።

*   *   *

ሕሲና ከቤት ስትወጣ በአንድ አሮጌ ጨርቅ የጠቀለለችውን አስር ብር ይዛ ነበር የተነሳችው ። የወ/ሮ አባይነሽን ዋናውን በር ወጣ እንዳለች ሁሉም ነገር ቀልሎ ተሰማት ። . . . ሞት . . . ፍርሀት . . . ጭንቀት . . . ከዚያ ችግር ካሳለፈችበት ቤት ስትወጣ የነፃነት ትርጉሙ እየገባት ነበር ። ግን ደግሞ ወደዬት እንደምትሄድ አታውቅም ። ከወ/ሮ አባይነሽ እጅ ማምለጡ በቂ እንዳልሆነ መረዳት ስትጀምር ፍርሀት ሽው አለባት ። ቢሆንም ወደኋላ መመለስ የለም ። ራሷን ማጠናከር ይሻላታል ። ምሽቱን ራሷን አረጋግታ ለማሳለፍ ወሰነች ።

ከከተማው ወጣ እንዳለች ማደሪያ ስትቃኝ « ወንድማማቾች ቡና ቤት » የሚል ፅሁፍ ጠራት ። በጓሮ በር በኩል ቀስ ብላ ገባች።

« መኝታ አለ ? » በሩን የከፈተላትን ዘበኛ ጠየቀች ። እሱም ሕሲናን መልከት አድርጎ በእጇ ያንጠለጠለችውን ከረጢት በጥርጣሬ ዓይን እየተመለከተ « ባለስንት ? » ሲል ጠየቃት ።

« ባለሁለት ወይም ባለ ብር ከሃምሳ » አለችው ።

ወደ መኝታ ክፍል ኃላፊዋ ወሰዳት ። የመኝታ አከራይዋ በቦታው አልነበረችም ። አለበት ቆሞ ጮክ ብሎ « ትርሲት . . . ትርሲት ! አንቺ ትርሲት » እያለ ተጣራ ። በዚህ ጊዜ ጨለማ የመሰለው ፊቷ ወገግ እያለ ፣ እየፈካ መጣ ። አንዲት መልኳ የማያስከፋ አጠር ያለች ጠይም ሴት ወደቆሙበት እየመጣች ፣

« አለቀባችሁ እንዴ ? ዛሬስ ገቢያችን እንዴት ደርቷል ? » ብላ « ባለስንቱን ነው የምትፈልጊው ? » አለቻት ልብ ብላ ሳታያት።

« እንደምን ውሰሻል ትርሲት ? ባለአምስቱን አስቲ ልየው » አለች ሕሲና ዕቃዋን ብድግ እያደረገች ። ትርሲት ሥሟ ሲጠራ ቀና ብላ ለማየት ሞከረች ። ዓይኖችዋን ተጠራጠረች ። ግራ ተጋባች ። « ለ . . ለ . . ለ . . ራስሽ ነው ወይስ ሰሰው ነው የምትፈልጊው ? ውጪ ማደር ጀመርሽ እንዴ ? ጎሽ ልጄ እንዴት አማረብሽ » በወቀሳ ዓይነት ከሕሲና እጅ ከረጢቱን ተቀብላ ወደ መኝታ ክፍል እያመሩ ።

« ይሄ ደግሞ ምንሽ ነው ? » አለቻት የከበዳትን ከረጢት መሬት ላይ አሳርፋ ። ዓይን ዓይኗን እየተመለከተች መልስ ስታጣ « አባረሩሽ እንዴ ? » አለቻት ። ሕሲና እንባ ያቀረረውን ዓይኗን ትርሲት ላይ ተክላ ፣ « እኔው እራሴ ወጣሁ » ስትል መለሰችላት ። በሁኔታዋ እጅግ ያዘነችው ትርሲት እነሱ ከሚተኙበት አልፎ ያለውን ክፍል አከራይታት መጣሁ ብላት ወጣች ።

የትርሲትና የሕሲና ትውውቅ የጀመረው በወ/ሮ አባይነሽ ቤት ነበር ። ድሮ እንዲህ አልጋ ፈላጊ ሳትሆን የመጠጥ ቤት ኃላፊ ሆና ትርሲት አስተናጋጅ ነበረች ። ከአስካበች ጋር በፈጠረችው አምባጓሮ ከቀን ወደቀን ፀቡ እየከረረ ስለመጣና ስለተማረረች ቤቱን ለቃ ወደሌላ መሸጋገሩን መረጠች ። ይህ ለትርሲት ቀላል ነበር ። መደበኛ ሥራዋ ስለሆነ አልከፋትም ።

ሕሲና ትርሲትን በማግኘቷ በአንድ በኩል ደስ ሲላት በሌላ በኩል ምስጢር ይባክናል በማለት መፍራቷ አልቀረም ። ብዙ ላለማውራት ወሰነች ። የትርሲት እንደ ድንገት መውጣት ደግሞ አላሰባት ። ሮጣ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ለመናገር የሄደች መሰላት ። በጣም ተሸበረች ።

« አንቱ ! አንቱ ጋሼ ! » ብላ ተጣራች ። ከቡና ቤቱ ጓሮ በር አጠገብ የቆመውን ብርድልብስ የለበሰ ዘበኛ ። « እባክዎት ትርሲትን ይጥሩልኝ » አለች በልመና ዓይነት ። አብሮት ካለው ካኪ ለባሽ ጋር በከባድ ወሬ የተጠመደ የሚመስለው ዘበኛም ፣

« ከሰው ጋር ነኝ አሁን አልችልም » አላት ቆጣ ብሎ ::

« መቼስ ምን ይደረጋል ፣ ለሁሉም ትዕግስት ያስፈልጋል » አለችና ለራሷ ተመልሳ ወደተከራየችው ክፍል ገብታ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች :: መጥፎ ነገር እንዳይገጥማት የራሷን ፀሎት እያደረገች ትርሲትን በመጠበቅ ቆየች ::

« እንደምን ዋልሽ » የሚል ድምፅ ከብቸኝነቱ ሲያባንናት ነቃች :: ሦስት ሴቶች ክፍሏ ውስጥ ነበሩ ::

« ይኸውላችሁ ወጣችውና አረፈች » አለች ትርሲት መደንገጥዋን አውቃ በማረጋጋት ስሜት ::

« አይ ትርሲት ያስገርማል ብለሽ ነው ? » አለችና ሌሎቹ በጥርጣሬ ተመለከተቻቸው :: ከዚህ ቀደም አይታቸው ስለማታውቅ ግራ ገባት :: አንደኛዋ ፀጉሯን አፍሮ ያበጠረች ጠይም ቆንጆ ናት :: ሌላኛዋ ደግሞ ቀይ መልከ መልካም ስትሆን ሱሪ ሰብሳለች ::

« አሁን የት ለመሄድ ነው ? ወደቤተሰቦችሽ ? » ስትል ጠየቀቻት ሱሪ ለባሽዋ ::

« ዘመድ የታላት ብለሽ ነው ? ዘመድዋማ ወ/ሮ አባይነሽ ነበሩ :: አባረሯት እንጂ :: ውይ ! ውይ ! እንዴት ያሉ ጨካኝ አረመኔ መሰሏችሁ :: በቀደም ሠራተኛቸውን ደብድበው ገድለው እራስዋን ሰቀለች አሉኝ » አለች ትርሲት :: እንዲህ በማለቷ ሕሊና አልጠላቻትም :: የወ/ሮ አባይነሽን ሥራ እሷም ታውቀዋለች እሷንም ጥላ እንድትጠፋ አድርጓታል ::

« እመልስሻለሁ ቢሉ እምቢ በያቸው . . . መብት የላቸውም . . . አልፈልግም ካልሽ አስገድደው እንዳይወስዱሽ ዕድል እንዳትሰጪያቸው » አለቻት ሱሪ የለበሰችው በምክር ዓይነት :: ሕሊና ስሜቷ መረጋጋት ፣ ጥርጣሬዋ መወገድ ሲጀምር ተሰማት ::

« ለጊዜው ነው እንጂ አይዞሽ ፣ በዚህ መልክሽ አንዱ ቡና ቤት ትቀጠሪያለሽ » አለቻት አፍሮዋ በአድናቆት ::

« እህህህ ልጅቱ . . . ቡና ቤት እንኳ የምትፈልግ አይመስለኝም ፤ ባይገርማችሁ ልጃገረድ ሳትሆን አትቀርም » አለችና ትርሲት ከትከት ብላ ሳቀች ::

« አትይኝም እስከአሁን ? ምን ትጠብቂያለሽ ? ለምትወጅው በይውና ተገላገይ እንጂ ፤ አሰበለዚያ እንዳትንከራተች » አለቻት ባለሱሪዋ ሕሊናን እያስተዋለች ::

« ሠይጣኖች ! ምን አድርጊ ነው የምትሏት ? ከዚህ ኑሮ ይልቅስ ሰው ቤት ተቀጥራ ትምህርቷን እንድትማር መምከሩ አይሻልም » ስትል አፍሮዋ በማዘን ዓይነት አየቻት ::

ሦስቱም ሥራ ስለነበረባቸው ከሕሊና ጋር መቆየት አልፈለጉም :: ሕሊናን ተሰናብተው ወጡ :: ሕሊና በብዙ ነገሮች ተጨንቃ ከመኝታዋ ውስጥ ስትገለባበጥ ለጥቂት ጊዜ ቆየች :: እንቅልፍ እንቢ ብሏት ነበር :: ስትቆይ ግን እንቅልፏ አሸነፋት ፤ ሸለብ አደረጋት :: በማግስቱ የሚያስቸኩላት ጉዳይ ባለመኖሩ አረፋፍዳ ነበር የተነሳችው :: ፊቷን አጠገቧ በተቀመጠው ጠርሙስ ውሀ ተጣጥባ ወጣችና አካባቢውን ቃኘች :: ምንም የሚያሰጋ ሁኔታ አላየችም :: ወደ መኝታ ክፍሏ ገብታ በከረጢቱ ውስጥ ያስቀመጠችውን የአባቷን ማስታወሻ መጥረቢያ አውጥታ አልጋው ላይ አስቀመጠችው :: አባቷ በናፈቋት ወይም በታሰቧት ቁጥር መጥረቢያውን ስታይ ቀለል ያላት ይመስላታል :: ከመጥረቢያው ጋር እንደተፋጠጠች ፣ በመጥረቢያው ውስጥ የአባቷን ምስል ያየች መሰላት በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለች በሩ ተንኳኳ :: በሚርበተበተው እጇ የያዘችውን መጥረቢያ ወደነበረበት ቀስ ብላ መልሳ ጆሮዋን አነቃች :: ድጋሚ ተንኳኳ :: ምርጫ እንደሌላት ስታውቅ በሩን ከፍታ አንገቷን ወጣ ከማድረጓ « ትፈለጊያለሽ » አላት ዘበኛው ::

« ማነው የሚፈልገኝ ? » ስትል አፏ ላይ እንደመጣ ዘበኛ ውን ጠየቀችው :: አጠገቧ አልነበረም :: ወዲያው የሆኑ ሰዎች

ተግተልትለው ወደክፍሉ ዘለቁ ። ወ/ሮ አባይነሽን አየቻቸው ። መዓቱን ያወርዱታል ። ሁሉም ነገር ግልፅ ሆነላት ።

« ና ጠፍርልኝ እባክህ » አሉ በትእዛዝ መልክ ። ሕሊና ሁሉንም ነገር በንቀት ነበር የተመለከተችው ። ፖሊሶቹ አንደኛው ሕሊናን ሌላኛው የሕሊናን ከረጢት ያዙና ወ/ሮ አባይነሽን አስከትለው እየተንደረደሩ ከቡና ቤቱ ወጡ ። ፖሊስ ጣቢያ እንደደረሱ ከረጢቱን የያዘው ፖሊስ ሕሊናን እንደያዛት ገንጠል ብላ ወደምትገኘው አነስተኛ ወደሆነች ቤት አመሩ ። ፖሊሱና ሕሊና ተከታትለው ወደ ውስጥ ዘለቁ ። ሕሊና ከረጢቷን አስመዝግባ ስትጨርስ « ተከተይኝ » አላት ፖሊሱ ። ጥቂት እርምጃዎች እንደተራመዱ በፊት ከገቡበት ቤት ሠፋ የሚል ክፍል ውስጥ ይዟት ገባ ።

ሕሊና የክፍሉን ዙሪያ በዓይኖቿ አማተረች ። ክፍሉ የዝምታ ድባብ ተጭኖታል ። ሁሉም ነገር በስርአቱ ተቀምጧል ። መዝረክረክ አይታይበትም ከግድግዳው በስተቀኝ በኩል አስር አለቃ አለነ ከደረቱ ለጠጥ ብሎ ተቀምጧል ። በቀኝ እጁ በብእሩ ጫፍ ጠረጴዛውን ያንኳኳል በክፍሉ ውስጥ የሚሰማው ብቸኛ ድምጽ የብእሩ ኳኳታ ነበር ። አንገቷን አቅንታ ወደመርማሪው ፖሊስ ስትመለከት በድፍርስ ዓይኖቹ በፌዝ ያያታል ።

እጆቹን ጠረጴዛው ላይ በማስደገፍ ፊቱን ወደ ሕሊና ለገግ አድርጎ « አንቺ ነሽ እህ . . ገንዘብ ተቀባይ ? » ከእግር እስከራስዋ አስተዋላት ፤ መርማሪው ።

ወ/ሮ አባይነሽ በሩን ሞልተው ከውጭ ሲገቡ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ከመቀመጫቸው ተነስተው ተቀበሏቸው ።

« ይቺ እኮ ነች » አሉና በጥላቸው ጫፍ ወደ ሕሊና እያመለከቱ ፤ « ሞሽላቃ ሌባ » በማለት የስድብ ናዳቸውን አወረዱባት ።

የ፲ አለቃ አለነም በተለመደ ዘዴው ማስፈራሪያዎችንና ዛቻዎችን አወረደባት ። « መች አጣኋት ፤ አውቃት የለም እትዬ » ሲል ወገናዊነቱን አሳየ ። ከሌሎች እስረኞች ጋር እንዲቀላቀሏት ተደርጎ ወ/ሮ አባይነሽና የ፲ አለቃ ለብቻቸው ምርመራ ክፍል ውስጥ ምክክር ጀመሩ ። ለሁለት ሰዓታት ከሌሎች ሴት እስረኞች ጋር ከቆየች በኋላ እንደገና ተጠርታ የ፲ አለቃ ወደሚገኝበት ክፍል ገባች ። በሚያስፈራ ዓይኑ አፍጥጦ እየገላመጣት ፤

« አሁን የምልሽ አጭር ነገር ነው ። ወደቤትሽ ትመለሻለሽ ወይስ እዚሁ ለመበስበስ ትፈልጊያለሽ ? » አላት በኃይለ ቃል ። የመናገር ዕድል የተሰጣት መሆኑን ከ፲ አለቃው ዝምታ በመረዳት ፤

« እኔ የምመለስበት ቤት የለኝም ። የግል ሀብቴ የሆነውም በእጃችሁ ይገኛል ንብረትነቱ የራሴ ነው ። አመጥታችሁ ማየት ትችላላችሁ ። » አለች ወደ መርማሪው አስር አለቃ አለነ እያየች ። መርማሪው ትንሽ አሰብ አድርጎ ፊቱን ወደፖሊሱ መለስ በማድረግ ንብረቴ የምትለውን እንዲያመጣ አዘዘው ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፖሊሱ አንዲት አነስተኛ ከረጢት ይዞ ገባ ። ጌታዬ ቢፈቅዱልኝና እኔው በሳይዎት ስትለው መፍቀዱን አንገቱን በማወዛወዝ ገለጸላት ። ሕሊና ወደመርማሪው ቀረብ ብላ እኔ ከወ/ሮ አባይነሽ ቤት የነካሁት ነገር የለም ብላ ውስጡ ያለውን ዕቃ ወለሉ ላይ ጣለችው ።

በአድራጎቷ የተደናገጠው የ፲ አለቃ አንዳች ነገር ሳይተነፍስ ዓይኖቹን ዕቃው ላይ ተክሎ ቆየ ።

« ይህ ደግሞ ምንሽ ነው ? » ብሎ ዕቃውን በእግሩ ገፋ አደረገው።።

« የአባቴ መጥረቢያ ነው ! » ስትል በአጭሩ መለሰችለት ። አጭር መልስ ስትመልስለት በራስዋ የመተማመን ስሜት ሰፍኖ ታያት ።

« እኔ ወደዚያ ቤት ከዚህ በኋላ ተመልሼ አልሄድም ። ከዚህ በፊት እዚያ ቤት ተቀምጬ እራሴን ያሰጨነቅሁት ይበቃኛል » አለች ቁርጥ ባለ አነጋገር ።

* * *

« ምን ልታዘዝ » ስትል ተቅለሰለሰች ፣ ፈገግታዋን አስቀድማ ።

« ፈቃድሽ ከሆነ እኔ የምፈልገው ዳንስ ነው » አላት ሀሰን እሱም በፈገግታው አፀፋውን እየመለሰላት ።

« ግድ የለም ለሌላ ጊዜ ይሁን » አለችና « እርስዎስ ? » ስትል ጣቱን እየነከሰ ወደሚተክዘው ተጠግታ ጠየቀች ፣ ያሬድ ነበር።

« አሁን የምንጠብቀው ሰው አለ ፣ ከምናመላልስሽ ቢመጣ አይሻልም እመቤት ? » ሲል አክብሮት በተሞላው ዓይነት ከላይ እስከታች ወጣቷን ዳሰሳት ።

« ያንተው ይሻላል » ስትል እንደሕፃን ልጅ መሬቱን ዳስ ዳስ እያደረገች ወደ ባንኮኒዋ ተራመደች ። ትዕግስታቸው በማለቅ ላይ ነበር ተሾመ ሲመጣ ። ከኋላው ትርሲትን አስከትሏል ። ተሾመ ፊት ላይ የመደናገጥ ስሜት ይነበብ ነበር ።

« ያሬድ ና ጉድህን ስማ » አለውና እጁን ጎትቶ አስቀመጠው።

« ምንድን ነው ጉዱ ? »

« አሳሰሯት እኮ » ስትል ወሬውን ትርሲት ጀመረች ።

« ወ/ሮ አባይነሽ መቼ ነው . . . እቴ ? . . እም ከሦስት ቀን በፊት ሕሊና ትታቸው ስትወጣ ጊዜ ሀብቴን ዘርፋለች በማለት ከሁለት ፖሊሶች ጋር እዚህ መጥተው ይዘዋት ሄዱ ። » የያሬድ ፊት በድንጋጤ ተለወጠ ። « ቆይ እንደዚህ አይደለም ፣ እኛም

እንቀመጥ፣ ሀሰንም ይስማው » አላቸው ። ሀሰን ወደተቀመጠበት ወንበር ተያይዘው ሄዱ ። ትርሲት ከሦስት ቀን በፊት ስለተፈጠረው ድርጊት ፣ ስለሕሊና መታሰር ዘርዝራ አስረዳቻቸው ። በመጨረሻም « ይኸውላችሁ አሁን መሄጃ ጠፍቷት ፖሊስ ጣቢያ በቆይታ ትገኛ ለች » አለች ።

ያሬድ የተሰማውን ስሜት መደበቅ አልቻለም ። ባይነ ሀሊናው ወገን አልባ ፣ ምስኪንና ጥገኛ ሕሊናን ፣ እና ጎሰቋላዋን ባልቴት አሰበ ። በአውቶቢስ ተሳፍረው ወደ አቃቂ አብረው የመጡበትን ሁኔታ አስታወሰ ። በተለይ በተለይ ለቅሶ ቤት የተለዋወጡት ጥቂት ቃላቶች ትህትናዋ ፣ ፍርሃቷ ፣ ታወሰው ። እንዳች ኃይል ገፋው በፍጥነት እርምጃ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አመራ ።

በያሬድ ሁኔታ የተደናገጡት ሀሰንና ተሾመ ተከትለውት ሄዱ። ያሬድ የፖሊስ ጣቢያውን ሥነ ሥርአት ተከትሎ ሕሊና ላደረሰችው ጥፋትና በደል በኃላፊነት ሊጠየቅ ዋስትናውን አረጋግጦ ሕሊና በቆይታ ወዳለችበት ክፍል በፖሊስ አጃቢነት አመራ ። ሀሳቡ ተበተነ ራሱን ለሕሊና እንዴት እንደሚያቀርብ አብሰለሰለ ። ከጥቂት የሀሳብ ውጣ ውረድ በኋላ በመጀመሪያ ደረጃ ከአሥር ማስፈታት ብሎም ቀጣዩን እንደአመጣጡ ለመመለስ ወሰነ ። ስሜቱ አይሉ ድርጊቱን የተሻማው ፊቱ የቆመችውን ሕሊናን ሲያይ ነበር ። በሁኔታው ግራ የተጋባችው ሕሊና እጇን አጣጥፋ በእርሷና በያሬድ መሃከል ያለውን ፖሊስ በዝምታ ተመለከተች ።

ያሬድና ሕሊና ለአፍታ ትኩረታቸው አንድ ሆነ ። ስሜታቸውን ለመግለጽ ቋንቋ አላስፈለጋቸውም ። አንዱ በሌላው ፊት ላይ የተሳለውን ተናበው በመረዳት ባሉበት ቆመው ቀሩ ።

« ሕሊና ያጋጠመሽን ሰማሁ አይዞሽ » ያለው ያሬድ ቅስሙ እንደተሰበረ በሁኔታዋ እንዳዘነ ተመስጦ ነበር ። ዕንባ ያቀረዘዙት የሕሊና ዓይኖች የደረሰባትን በደልና ብቸኝነት ቢያመላክቱም ፣ ዝግ

የሆነው አንደበቷ እስከወዲያኛው ለማንም ምንም ላለመናገር የወሰነ ይመስል ነበር ። ያሬድ ጊዜ አላጠፋም የእስር ቤት ጣጣውን ጨርሶ ዕቃዋን በእጁ አንጠልጥሎ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር አጅቦ ወደ ቤቱ ወሰዳት እርሷም ያለአንዳች ጥርጣሬና ቅሬታ ያሬድ ቤት ገብታ ለመኖር ወሰነች ።

« ለመሆኑ እንዴት ሰምተህ መጣህ ? »

« ስለነገሩ የአቃቂ ሰው ሁሉ ሰምቷል ። እኔ ግን አሁን ነው ከተሾመ የሰማሁት » አላት ጣቱን ወደ ተሾመ እየጠቆመ ።

ያሬድ ቤቱ እንደደረሰ ጓደኞቹን አሰናብቶ የቤቱን የውስጥ ሁኔታ ለሕሊና ለማስተዋወቅ ቸኮለ ። የእንግዳው ጠረጴዛ በአማረ ልብስ ተሸፍኖ መሀል ሳሎን ጉብ ብሏል ። በማያብረቀርቅ ማስቀመጫ ትኩስ የዕኄረዳ አበባ ይታያል ። የመጽሐፍት መደርደሪያው በመጽሐፍት ተሞልቶ እልፍ ብሎ ቦታውን ይዟል ። በአራቱ ግድግዳ ጥግ ሀረግ የሚያበቅሉ ምንቸቶች ሀረጉ ለምልሞባቸው እስከጣሪያው እራሳቸውን ዘርግተው ይገኛሉ ። ግድግዳው በተለያዩ ያማሩ ሥዕሎች አሸብርቋል ።

« ታዲያስ ሕሊና እንግዲህ ቤቴ ይህን ይመስላል » አላት በጠረጴዛው ዙሪያ ከተቀመጡ በኋላ ። እንዴት ቆንጆ ነው ? » ከረጅም ማቀርቀርና ዝምታ በኋላ ተናገረች ።

« እንግዲህ ቀስ በቀስ ትለምጃለሽ » አላት ያሬድ ።

« መቼም የወንደላጤ ግብገር ከሻይ ይጀምራል » ብሎ ከሳሎን በስተግራ ያለውን መጋረጃ ጠቅሎ ወደ ውስጥ ገባ አለ ። ሕሊና ካለችበት ሆና የምድጃውን ድምጽ ስትሰማ ያሬድ እሳት ለማያያዝ ማሰቡን አውቃ ወደ እሱ ዘለቀች ። ያሬድ ከኩሻ ውስጥ ከሰል እያነሳ ማንደጃው ላይ ሲጨምር አገኘችው ።

« ቆይ እኔ ላያየ' ፤ በኔ ያምራል አለችው » እጇን ወደ ከሰሉ ኩሻ እየ..

« አንቺ ዛሬ እንግዳዬ ነሽ ፤ ትንሽ አረፍ ብትይ ጥሩ ነው » አላት ።

« ግድ የለም » የሴት እንግዳ የለውም » አለችና ሥራውን ተቀበለችው ። እንቢ እንዳለችው ሲረዳ ዕቃዎቹን የምታገኝበትን ቦታ አሳይቶ ወደ ሳሎን ተመለሰ ።

ምዕራፍ ሁለት

ወ/ሮ አባይነሽ ፀባያቸው ከድሮ እጅግ በጣም ተለወጠ ። የእውሬነት መልክ እየያዘ ሄደ ። ያገኙትን ሰው ሁሉ መቆጣት አበዙ። ሁሉም ትዕግስቱን ጨረሰ ። እንደድሮ ቁጣቸውን ዝም ብሎ የሚቀበል ጠፋ ፤ ደንበኛ ራቃቸው ። ምግብ ቤት የሚሰራው ሁሉ ማንም ሳይበላው እያደረ መደፋት ጀመረ ። ማታ ማታ በደንበኛ ጥበት ሲፈነዳ የሚደርሰው ቤታቸው በየጠረጴዛው ዝንቦች ያንዣብቡበት ጀመር ። የማይከራየው የአልጋ ብዛት ቁጥር እየጨመረ መጣ ። ወ/ሮ አባይነሽ ለዚህ ሁሉ የገበያ መቀዝቀዝ ምስጢሩ ገብቷቸዋል ። ሕሊና . . . መጥረቢያዋ . . . በቀል . . ሟርት . . መተት . . . ይሄ ነው በቃ ።

« ይህች ሟርተኛ ፣ የዚያ የሟዋርተኛ ዘር ቂሙን ሲበቀል ነው ወደእኔ የሰደዳት » ብለው ደምድመዋል ። መፍትሄው ደግሞ ግልፅ ነው ። ድግምቱን ማስፈታት አለባቸው ። ለዚህ ደግሞ መጥረቢያው መገኘት ፣ እጃቸው መግባት ነበረበት ። እሁን እሁን ሲያስቡት ይቆጫቸዋል ። መጥረቢያው እርቋል ። ሰዶ ማሳደድ ሆኖባቸዋል ። ግን ደግሞ መገኘት አለበት ። የህይወት ጉዳይ ነው ። ለዚህ ጉዳይ ፈሩቅ አለ ። ፈሩቅ ታማኛቸው ከመሆኑ ጋር ጥሩ የመረጃ ስራም ያውቅበታል ። ሕሊና የምትኖርበትን ቦታ ሲያገኝ ቀናት አልፈጀበትም ። መጥረቢያውን በእጁ ለማስገባት ብዙ ለፋ ። ጎረቤቶቿን ለመደለል ሞከረ ። ከሕሊና እጅ ግን የፈለገውን መጥረቢያ ማግኘት አልቻለም ። ተስፋ መቁረጥ ጀመረ ።

አንድ ቀን ወ/ሮ አባይነሽ ፈሩቅን ወደ ክፍላቸው አስጠርተውት በምስጢር ዓይነት በልመና ዓይን እየተመለከቱት ፣ « ፈሩቅ የእኔ ጌታ እባክህን መላ እታጣም አንድ መላ ፍጠር »

በማለት ተማፀኑት ግራ ቢገባቸው ። ፈሩቅም የተጣመሩ እጆቹን እያፋተገ ፣

« እትዬ እኔ ልሙት ! መላው ጠፋብኝ እኮ ! እትዬ ያልሞከርኩት ነገር የለም » አላቸው ።

« ለእኔ እኮ ህይወቴ ነው ይገባሃል ፈሩቅ ! የፈለገው ወጪ ይውጣ እንጂ እሱን ማግኘት አለብኝ » አሉት በእልህ ።

« ለመሆኑ እትዬ አዋቂ ቤት ሄደዋል ? እዚያው እንዳለ እኮ ማርከስ የሚችል አዋቂ አይጠፋም ። እስኪ ያጠያይቁ » ሲል ቀስ ብሎ ነገራቸው ። ከጭንቀት የተገላገለ ያህል ነበር የቆጠረው ። ወ/ሮ አባይነሽ ለፈሩቅ በሚሰማ በሹክሹክታ ድምፅ ፣ « የአዋቂውን ነገርማ ተወው ። ያች እርጉም ከሞተች ጀምሮ እስከአሁን በሸዋና በሐረርጌ አሉ የተባሉ አዋቂዎች የሚሉት በዘርሽ ተቆጥሮ በገዛ ሥጋሽ ተጠምጥሞብሻል ፤ ግማሹ ይሄን አረጂ ይሄን አድርጊ ይለኛል ። ሆኖም እውነተኛውን ያገኘሁት እዚሁ አቃቂ ነው ። የየማነብርሃን ውቃቢ ነው እውነቱን የነገረኝ ። ስሟን ከነአባትዋ ፣ የተበተበችበት ቦታ ሳይቀር ነው ቁልጭ አድርጎ የተናገረው ። ጠምጣሚው አባቷ ነው ።

« መተቱን ለማርከስ ግን መጥረቢያው ካልመጣ ከሥረ መሠረቱ መንቀል አልችልም ብለውኛል » አሉት ሁለት እጃቸውን ወደጣሪያው ከፍ አድርው « የእሳቸውን አውሊያ የታረቀች የዚህች ግቢ አድባር እንዳለች ይህን መጥረቢያ እጄ ታስገባልኝ ፤ ጥቁር በሬ እርጄ ነው የምክሰው » እያሉ ተለማመኑ ። ለማልቀስም ዳዳቸው ። ፈሩቅ የወ/ሮ አባይነሽ ጭንቀት እጅጉን ያሳሰበው መሰለ ። እምጦ እምጦ አንድ ሀሳብ መጣለት ።

« እ - እ እትዬ ! እትዬ » ሲል ተጣራና ፀጥ አለ ። በሀሳብ እንደሚዋዥቅ ፣ ጥቂት ዘግየት አለ ። « ይስሙ እትዬ ፤ መቼም በነብሴ ፈርጄ ነው የምገባው ። እርስዎ እንዲህ ሲሰቃዩ ማየት

አልችልም ። የእኔስ መኖር እርስዎ ኖረው በቤቱ ውስጥ የተሰራው ሲሸጥና ገበያው ሲኖር አይደል ? እንግዲህ እንዲህ እናድርግ ፣ መቼም በግዥ ከእጇ መውሰድ የማይታሰም ነገር ነው ። ሆኖም በስርቆት ለማውጣት ይሞከራል ። ግን ግን ጉልበት ሲያስፈልግ ስለሚችል በጉዳዩ ላይ ከጓደኞቼ ጋር መመካከር ይገባል ። ይህ እንግዲህ የሞትና የሽረት ሙከራ ይሆናል » አላቸው ፣ ዕቅዱ ሲሳካ እንደሚችል እራሱን ለማሳመን እየሞከረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ፊታቸው በፈገግታ ተውጦ « ታዲያ ምን ወሬ ታበዛለህ ? » አሉና ጮኸቡት ፤ መልሰው « ቆይ ! ቆይ ! » እያሉ ወደ መኝታ ቤታቸው ሮጠው በእጃቸው ቀያይ ብር ይዘው ተመለሱ ።

እራሱን እያሻሸ በፍንደቃ ይጠብቃቸው የነበረው ፈሩቅ ሁለት እጆቹን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዘርግቶ ፣ « ገና እኮ ነው አሁን ምን ያደርግልኛል ብለው ነው ? » ሲል በማቅማማት ዓይነት ተናገረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ለማንኛውም ይገዳል በሚል ዓይነት ብሩን ጠቅልለው ሲሰጡት ፣ « ይልቅስ መጠጥና ደግነት የማይደልለው ወንድ የሰም፤ ጋብዛቸው » ብለው እስከ ጓሮ በር ተከትለው ሸኙት ።

ፈሩቅ ከወ/ሮ አባይነሽ ዓይን እስኪሰወር ቀስ እያለ አዘገመ ። ከእይታቸው ከራቀ በኋላ ግን ከኋላው በጦር እንዳባረሩት እሩጫውን ተያያዘው ። ሠፈሩን እልፎ አሳቻ ቦታ ሲደርስ ኪሱ ውስጥ ተጠቅሎ የተቀመጠውን ቀያይ ብር ወጣ አድርጎ በፍጥነት ቆጠረው ። ስድሳ ብር ነበረ ። እልተከፋም ። ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ተስፋ በመፈንጠቁ ከሰሞኑ ያልታየባቸውን ፈገግታና ደግነት ለሠራተኞቹ ፣ ገብቶ ለሚወጣውም ደንበኛ በአዲስ መልክ በመቅረብ ያሰወትሮአቸው ቀልድና ፌዝ በማውራት መሳቅ አበቡ ። አዲስ የገቡት ሠራተኞች ይህን የተደበቀ ደግነት ሲመሰከቱ እውነትም የዘላለም ደግ ሰው አድርገው ቆጠሯቸው ። ነባሮቹም ሠላም በመውረዱ እየተገረሙ

እርስ በርሳቸው ይጠቃቀሳሉ ። ቀኑ ሲመሽ የመጠጥ ቤቱ ገበያም ከወትሮው እየደራ መጣ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ከአሁን አሁን ፈሩቅ የመጣ እየመሰላቸው በጓሮ በር ብቅ እያሉ ከዚያ አካባቢ የሚታዩትን የማዕድ ቤት ሠራተኞቹን ፣ « ፈሩቅ መጣ ? » ሲሉ ይጠይቃሉ ። ፈሩቅ ግን ድምፁም በአካባቢው አልተሰማም ። አዝማሚያው አልጥማቸው እያለ መሄድ ጀመረ ። መነጫነጭ ጀመሩ ።

ፈሩቅ በአለባበሳቸው እስከዚህም ደስ ከማይሉ ሰዎች ጋር በፊት ለፊት በር ሲገባ አዩት ። ደስታቸው ልኩን አጣ ። የሚያደርጉትን አሳጣቸው ። ፈሩቅና አብረውት ያሉት ሰዎች የፈለጉትን መጠጥ የፈለጉትን ያህል እንዲጠጡ ለሠራተኞቻቸው ቀጭን ትእዛዝ አስተላለፉ ።

« አበዱ እንዴ ሴትየዋ ? ዛሬ ደግሞ ማን ይሆን ተረኛ ? » አለች ቆየት ካሰችው ሠራተኞች መካከል አንዷ ። የወ/ሮ አባይነሽ ድርጊት ሳይገርማቸው አልቀረም ። ለሁሉም የዛሬ ደግነት ምስጢር ሊከሰትላቸው አልቻለም ። አንዳንድ ጊዜ የታደሰ ሰው የሚሞትበትን ቀን ቀደም ብሎ ስለሚያውቅ የቁም ተዝካሩን ያወጣል እሉ ።

ወ/ሮ አባይነሽ እስከዛሬ የናፈቃቸውን የጤና ዕንቅልፍ በዛሬው ቀን መልሰው እንደሚያገኙት ፍንድቅድቅ ያለው ፊታቸው ይናገራል። የመኝታ ሰዓቱን የሚወስነው ግን የፈሩቅ ተልዕኮ ነው ። መላ ህይወታቸውን በፈሩቅ እጅ ጥሰውታል ።

« ፈሩቅ እንግዲህ አደራ ፤ መጥረቢያው እጄ እንደገባ ወዲያውኑ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር ቆጥሬ አስረክባለሁ » አሉት። ፈሩቅ ቃል ሳይተነፍስ ከሦስቱ ሰዎች ጋር ተልዕኮውን ለመፈፀም ወጣ ። የመንደር ውሾች ጩኸት አልፎ አልፎ እየተሰማ ጨለማውን እየሰነጠቁ ወደ ተልዕኮዋቸው በጥንቃቄ ተጓዙ ።

* * *

ያሬድና ሕሊና ኑሮአቸውን በመተጋገዝ መምራት ጀምረዋል:: ሕሊና ተደብቆ የነበረ ባልትናዋን በተግባር መተርጎም ጀመረች :: የቤት አያያዙን ፣ የምግብ ሥራውን፣ ቤት ውስጥ መሰራት የሚገባውን ሁሉ አጠቃላ በራስዋ ቁጥጥር ሥር አደረገች :: ያሬድ ፣ ሕሊና እቤት ውስጥ ከገባች ዕለት ጀምሮ ቤት ውስጥ መመገብ ጀመረ:: እንደ ወንድምና እህት በመግባባት ሁለተኛ ወራቸውን ጨርሰው ሦስተኛውን አገባደዋል :: መጀመሪያ ያሬድ ሕሊና ቄስ ትምህርት ቤት ገብታ መስከረም እስከሚደርስ እንድትማር ፈልጎ ነበር:: ነገር ግን ሕሊና ከቄስ ትምህርት በላይ ችሎታ እንዳላት በተጨባጭ አሳየችው :: ያሬድ ባሰው ትርፍ ጊዜ ሕሊናን ለማስተማር ቆርጦ ተነሳ :: እሷም ትምህርቷን ሳታሰልስ በመከታተል ትጉህ ተማሪ መሆንዋን አስመሰከረች :: ያሬድ መደበኛ ፕሮግራም በማውጣት ጊዜውን በየትምህርቱ ዓይነት በመከፋፈል ማስተማር ጀመረ :: አልፎ አልፎም ጠዋት ጠዋት ስፖርት በማሰራት ያስተምራታል :: እሷም ሳቅ እያፈናት በደስታ እየፈነደቀች ነበር የምትሰራው ::

ከትምህርት ውጪ ሥራ ስትፈታ ያሬድ በመደበኛ ሥራው ላይ ስለሚያጋጥመው ችግርና ስላሉት ሠራተኞች ክፉውንም ደጉንም ያወራላታል :: አምኖ ግን ብቻዋን ከቤት ውጭ እንድትወጣ አያደርግም :: ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ያጫወተችው ፣ እሱም የደረሰባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ሕሊናን ብቻዋን ወደ ውጪ እንድትወጣ የሚያደፋፍሯት አልነበሩም :: የምትፈልገው ቦታ ለማድረስም አይሰለችም ነበር ::

አንድ ቀን ያሬድ እራሱን አሞት በሥራ ሰዓት ወደ ቤት ይመጣል :: በቀጥታ ወደ ሕሊና መኝታ ቤት ሲያመራ ሕሊና አልጋዋ ላይ ተቀምጣ በእጅዋ መጥረቢያ ታቅፋ የሆነ ነገር ስታደርግ ይደርሳል :: ሳያንኳኳ በመግባቱ ይቅርታ ጠየቃት :: የፈፀመችው ግን አዲስ ነገር ስለሆነበት ግር አለው :: በሳሎኑ መሀል የቆመውን ጠረጴዛ በሁለት እጁ ተደግፎ ፊቱን ወደ እሷ መልሶ አትኩሮ አያት:: በድንጋጤ የተቀመጠችው ሕሊና ያቀፈችውን መጥረቢያ እንደያዘች ቀና ብላ አስተዋለችው :: ሁለቱም ከመናገር ተቆጠቡ :: በዝምታ ተያዩ :: መጥረቢያውን አልጋዋ ላይ አሳረፈች ::

« ምነው እንደዚህ ታየኛለህ ? » ስትል የምንተዕፍረቷን ጠየቀችው ::

« ለምን አላይሽ ፤ ይህ ደግሞ ምን ዓይነት ስፖርት ነው ? » በማለት ጠየቃት ::

« ስፖርት አይደለም አለች ቆዘም ብላ :: ብቻ አንድ ቀን ስለዚህ መጥረቢያ ታሪክ አጫውትሃለሁ :: » ብላ ወደኩሽናዋ አመራች ::

ወደ አልጋው ሄዶ መጥረቢያውን አንስቶ እጀታውን ይዞ ወዲያና ወዲህ እያገላበጠ አስተዋለው :: ሕሊናን በሀዘን እየቃኘ ፣ ግራ ቢገባው መጥረቢያውን እያወዛወዘ የሳሎኑን በር አልፎ ሕሊና ወዳለችበት ኩሽና በመሄድ ከበሩ እንደደረሰ ፤ ሕሊና « ውይ ! » ብላ ጮኸች ::

« የመጥረቢያውን ታሪክ እነግርሃለሁ ብለሽኛል ፣ አሁኑኑ ንገሪኝ ! ከዚህ በፊት የምሰራው ሥራ የለም አላት ፍርጥም ብሎ »::

« መጥረቢያውን የነበረበት ቦታ አስቀምጥና እነግርሃለሁ :: » በማለት ወደ በሩ ስታመራ ያሬድ « ግድ የለም እዚሁ ንገሪኝ » ፊት ለፊት መንገዷን ዘግቶ ቆመ :: እሷም ያላሰበችው ነገር ስለተፈጠረባት እና በቀላሉ እንደማይለቃት ስታውቅ ፣

« በል መጥረቢያውን ስጠኝና ልንገርህ » ስትል ሁለት እጆችዋን ዘረጋች ፤ ሰጣት ።

« ስለአባቴ ሞት ነግሬሃለሁ ። አባቴ ሲሞት ትቶልኝ የሄደው ይሄንንና አንድ የራሱን ሱሪና ኮት ብቻ ነው ። አባቴ ከእንጨት ፈለጣ ሥራው ሲመለስ ይህን መጥረቢያ አጠገቡ አስቀምጦ የአባትነት ሙቀቱንና ምክሩን ይለግሰኝ ነበር ። ይህ መጥረቢያ እኔን ለማሳደግ ከአባቴ ጋራ አብሮ ተንከራቷል ። አባቴና ቤተሰቦቼ በስደት ከሀገራቸው ሲወጡ አለኝታቸው ሆኖ ከእነሱ ጋር አብሮ የተሰደደው ይህ መጥረቢያ ነበር ። ከአክስቴም ጋር እንድጣላ ያደረገኝ ይህን መጥረቢያ ለመውሰድ በመሞከራቸው ነበር ። አሁንም በዚህ መጥረቢያ ላይ የአባቴ ወዝ ይገኝበታል ። ሲከፋኝ ይህ መጠረቢያ ነው የሚያጽናናኝ ። ስለዚህ ማንም እንዲነካው ፣ ካጠገቤም እንዲርቅ አልፈልግም » በማለት በፍቅር ዓይን አየችው ።

« አሁንስ ተረዳህ ታሪኩን ? በል እንግዲህ ፍቀድልኝና ልሂድ» አለችው ።

በራሱ ንቅናቄ መፍቀዱን ገለፀላት ። ሁኔታዋ ስሜቱን ተጭኖት ነበር ። ወደ መኝታ ክፍሏ እንደገባች ከረጢቱ ውስጥ የቀረውን የአባቷን ቁምጣ ሱሪና ካኪ ኮት አስቀምጣ አልጋዋ ላይ አረፍ አለች ። እፍታም አልቆየች ። ብድግ ብላ ወደበሩ ተጠጋታ ፤

« ጋሼ ያሬድ » ስትል ተጣራች ።

« ምነው ጠራሽኝ ? » ሲል ጠየቃት ። ምንም ሳትናገር አንገቷን ቀና አድርጋ ወደ አልጋዋ ጠቆመችው ። ከመጥረቢያው ሌላ ሱሪና ኮት አስተዋለ ።

« ለመሆኑ አባትሽ ዕድሜያቸው ስንት ነበር ? » ሲል ጠየቃት ።

« የት አውቀዋለሁ » አለችው ፣ ከሀዘንዋ ሳትወጣ ።

ያሬድ ሕሲናን ብዙ ጥያቄ ለመጠየቅ ፍላጎት ቢኖረውም እነኝህ ጥያቄዎች ሀዘኗን የሚቀሰቅስባት ፣ ክፉ ነገሮችን የሚያስታውሳት ስለመሰለው ከመጠየቅ ተገታ ።

ይህን መጥረቢያ እንደአባቷ ማስታወሻ አድርጋ ማየቷ አይከፋም ። ግን እንደ አምልኮት ማመን እንዳትጀምርና የሰብእናዋን ጥያቄ እንዳይፈታተናት ፈራ ። በተለይም የእምነት ህይወቷን እንዳያበላሽባት የተለየ ትምህርት እንደሚያስፈልጋት አሰበ ።

« ሕሲና ፣ አባትሽ ከመሞታቸው ቀደም ብሎ የተነሱት ፎቶግራፍ የለም ? » ሲል ያላሰበችውን ጥያቄ ጠየቃት ።

« እይ ጋሼ ያሬድ አባቴ እንኳን ስለፎቶግራፍ ሊያስብ ቀርቶ የዕለት ጉሮሮአችንን በመከራ ነበር ። አሸንፈን የምንኖረው ። በነገርህ ላይ ስለአባቴ እንድታስብ አልፈልግም ። ከኔ አልፎ አንተን ማስጨነቅ አልፈልግም » አለችው ፣ ከራሷ ይበልጥ የያሬድ ሁኔታ አሳሰባት::

« ስለሞተ ሰው ማሰብ በህይወት ያሉትን አለመዘንጋት መሆኑን ተገንዘቢ ። እኛ በሙታን ህውልት የምንኖር ሰዎች ነን ። የእኛ አባቶች ለፍተው ግረው ጥረው ይህን ህይወት ባያቆዩን ኖሮ እኛ ከመጀመሪያ ሀ . . ሁ . . ብለን ይህችን ዓለም መገንባት በተገደድንም ነበር ። ሆኖም እነሰም በዛ ኑሮአችን በአባቶቻችን መሠረት ላይ የተጣለ ነው ። የእንቺም አባት እንቺን ተከተው ሲያልፉ ከእሳቸው የተሻለ ኑሮ ፣ ዕውቀትና ዝንባሌ እንዲኖርሽ መመኘታቸው አይቀርም:: መቼም ሰው ሆኖ ከወለደ ለልጁ ጥሩውን ብቻ ነውና የሚመኘው » ሲል ምክሩን ለገሳት ።

« ጋሼ ያሬድ አባቴም ሁልጊዜ እንዲህ ይል ነበር ። አብረን በኖርንበት ወቅት እኔ በምሰራው ሥራ ደስተኛ አልነበረም ። በመጨረሻ የህይወቱ ሰዓትም የተመኘልኝ ተምሬ እራሴን እንድችል ነበር ። ይህ ቃሉ እስከመጨረሻው ህይወቴ ድረስ አብሮኝ ተቆራኝቶ የሚኖር ቀሪ ሀብቴ ነው ። » አለችው ሳግ እየተናነቃት ።

« ከመ/ቤት ያስሰዓቱ የመጣሁት እራሴን ስላመመኝ ነበር ። ሀመሙንም አስረሳሽኝ » ሲል ወደመኝታ ክፍሉ አመራ ። ሁኔታውን መቀየር ነበረበት ።

« ምሳህን በልተህ እንደኛህን ብትተኛ አይሻልም ? » አለችው።

አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብሎ የጫማውን ክር እያላላ ፣ « ትንሽ ልረፍና ትቀሰቅሽኛለሽ » እያለ ወደላይ ወጣ ። እንዳሰበው ግን ሊያሸልብ አልቻለም ። « ሕሊና . . . ሕሊና በጣም አዋቂ ልጅ ናት ። በመጥረቢያ ማመንን አሁን ምን አመጣው ? የአባቷ ፎቶግራፍ አብሮአት ቢኖር ኖሮ ትተወው ነበር ። ማን ያውቃል ? ስለመጥረቢያው ስትናገር ከአባቷ እኩል ለፍቶ ግሮ ጥሮ ማሳደጉን ታወሳለች ፤ ይህን ሥራ ታዲያ ሌሎች መጥረቢያዎች ሊፈፅሙት አይችሉም ነበር ? . . . »

ሕሊና ሥራዋን ጨርሳ የያሬድን መነሳት ስትጠባበቅ ፀሐይዋ አሽቆለቆለች ። እንዲተኛ ስለፈለገች ልትቀሰቅሰው አልሞከረችም ። ያሬድ በራሱ ጊዜ ሲነቃ በጣም መሽቷል ። እራት ቀርቦ እየተጫወቱ በልተው ወደየመኝታቸው ሄዱ ። ያሬድ ግን እንቅልፉን ጨርሶ ነበር። ዝናቡ መጣል ሲጀምር ፣ « በሩ በደንብ ተዘጋ ? » ስትል ጠየቀችው ።

* * *

ከሌሊቱ ዘጠኝ ሠዓት ሆኗል ። ጭለማው ድቅድቅ ያለ ነበር። ዝናቡ በመጠኑ ያካፋል ፤ አልፎ አልፎ የሠማይ ብልጭታ ይፈነጥቃል ። ፈሩቅ ያልተዘጋውን የግቢ በር ቀስ ብሎ ከፈተ ። ወደ ወ/ሮ አባይነሽ መዝጊያ አመራ ። መኝታ ቤታቸው ከሳሎኑ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ወደዚሁ መግባት የሚቻለው ሳሎኑን አልፎ በኮሪደሩ በኩል ነው ። ከውጪ ከበረንዳው በስተቀኝ በኩል የሚገኘው የመኝታ ቤት መስኮት ለፈሩቅ ማንም ሳያየው ለማንኳኳት አመቺ ነበር ። የግቢው መብራት በአጠቃላይ ጠፍቷል ። ፈሩቅ የመኝታ ቤቱን መስኮት ቀስ ብሎ አንኳኳ ።ወ/ሮ አባይነሽ እንቅልፍ ስላልወሰዳቸው፣

« ማነው ? » አሉ ፤ ዝግ ባለ ድምፅ ።

« እኔ ነኝ » ሲል ደጋግሞ አንኳኳ ።

ወ/ሮ አባይነሽ መስኮቱን ለመክፈት እጀታውን ከያዙ በኋላ አመንትተው ፣ « በጓሮ ዙርና ና » ሲሉ አዘዙት ። ፈሩቅም በመጣደፍ በጓሮ በኩል ዞሮ የውጭውን በር ቀስ ብሎ በመክፈት በዳበሳ ሁለተኛውን በር አልፎ ወደሳሎን በር ገብቶ ግራ ቀኙን ሲቃኝ የወ/ሮ አባይነሽ ምልክት ስላልታየው በኮሪደሩ በኩል ወደመኝታ ቤት በር ሲጠጋ እሳቸውም የመኝታ ቤት በራቸውን ገርበብ አድርገው ከፍተው አንገታቸውን ብቅ አደረጉ ።

« ቀናችሁ ? » ሲሉ ጠየቁት ለመልሱ ጓጉተው ። ልብሱ ርሶ ውሃ ውስጥ ገብታ የወጣች አይጥ የሚመስለው ፈሩቅ በጨለማው ውስጥ ፈገግ አለና በእጁ የያዘውን መጥረቢያ ለወ/ሮ አባይነሽ እያሳየ ፣ « የሰይድ ኑርዬ አምላክ ቀናን እትዬ ፤ እንኳን ደስ ያለዎት » ሲል ፣ ወ/ሮ አባይነሽ የመኝታ ቤቱን በር ወገግ አድርገው ከፈቱለት ።

« የኔ ፈሩቅ ዝናቡ አበስብሶህል ና ግባ አሁን እሞቅሃለሁ » አሉት ፤ በደስታ ተውጠው ::

ፈሩቅ ወደ መኝታ ቤቱ ገብቶ እንደቆመ ወ/ሮ አባይነሽ ወደቁምሳጥናቸው ሮጠው ነጣ ያለ ጨርቅ አምጥተው ሰጡት ::

« አውልቅ ይህን ልብስህን እና ቢጃማውን ልበስ » አሉት :: ፈሩቅ በማመንታት ልብሱን ከላዩ ላይ ወደእሳቸው በሀፍረት እየተመለከተ አወለቀ :: ከአልጋቸው ላይ ተንጠልጥሎ የነበረውን ፎጣ እየወረወሩ ፣

« ሰውነትህን አድርቅ » አሉት :: ያሉትን አደረገ :: አጠገባቸው ጋደም ብሎ መጥረቢያውን እንዴት አድርገው ከሕሲና ኩሽና ሰብረው እንደሰረቁ እንዲያወራላቸው ጠየቁት ::

« ማንም ሰው ነቅቶ ስመከራከር አልሞከረም ? » አሉት ::

« ሰዎቹኮ እኛ ነን :: መጀመሪያውኑ ማን ቢሰማ » አላቸው:: ጥንካሬውንና ወንድነቱን በኩራት እያሳየ ::

« ቱፍ ! ቱፍ ! . . . ቱፍ ! ምኖቹ ናቸው የሞቱ . . ሆ . ሆ አይጣል ነው ወይ ፈርተው ይሆናል ? » አሉ የፈለጉትን በማግኘ ታቸው እየተደሰቱ ::

« ከጓደኞችህ ጋር ስመቼ ነው የተቃጠራችሁት ? »

« ነገ በጠዋት ሰው ሳይነሳ :: ድንገት ያያቸው ሰው እንኳን ቢኖር ከዚህ አካባቢ መሰወር አለባቸው » እያመነታ መለሰላቸው ::

« ታዲያ አሁን እውነት በአንድ ጊዜ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር ሊወስዱ ነው ? » ብለው ፈሩቅን ክንዳቸውን እያንተራሱ ጠየቁት :: ገንዘባቸው እያሳዘናቸው ነበር የተናገሩት ::

« እንዳታስገድሉኝ ፤ እነሱ እንደሆነ በደም የታጠቡ የሰው ነፍስ ምንም የማይመስላቸው ነፍስ ገዳዬች ናቸው :: እኔን ለማጥፋት ደግሞ ቀደም ሲል ከገደሏቸው ሰዎች ጋር ሲያወዳድሩት ምናቸውም አይደል:: ቃሌን መጠበቅ አለብኝ ! :: » አላቸው በማስተዛዘን ::

« አታዝንልኝም ? እኔ ላንተ የፈለከውን አደርጋለሁ :: ከስሞኑ እንደምታየው ምንም ገበያ የለኝም :: ይህን ያህል ገንዘብ ደግሞ ከየት ታመጣለች ብለህ ነው ? እባክህ ለምናቸው » አሉት እንደማባበል ጠጋ እያደረጉ ::

« አሆሆ ! የምን ልመና ነው ያስገድሉኛል ነው የምልዎት :: ይልቁንስ ስነፍሰችን እንፍራ ፤ እነሱ በእኔ አያቆሙም ይቀጥላሉ :: ጉዳዩን ከእርስዎ እንደበት ሰምተውታል :: ባያይዎት እንኳን ደህና ነበር :: »

« የዚያን ቀን ለምን አመጣሃቸው ? » እኔ እኮ ሲመጡ አልወደድኩም እህ . . ድንገት ቢያዙ እንኳን . . . « ይምጡ ልያቸው» አላሉኝም ፤ ምን ላድርግ ? »

« አሁን ይልቁንም አንድ ሺህ አምስት መቶውን አሁኑኑ እሰጣቸዋለሁ :: ትንሽ ቆየት ብዬ ደግሞ አንዱን ሺህ ብር እጨምራለሁ :: አሰበለዚያ ገንዘብ ከዬት አመጣለሁ ? በዚህ ቢስማሙ ተስማሙ ካልሆነም መጥረቢያውን ወስዶ ፖሊስ ጣቢያ ማስመዝገብ ነው ብለህ ንገራቸው :: እንዲህ ስትል አንተንም ይፈሩሃል ወንድ አይደለህም እንዴ ? » ሲሉ በክርናቸው ፈሩቅን ጎሸም አደረጉት ::

ወ/ሮ አባይነሽ ክንዳቸውን አንተርሰውት በሌላው ነፃ እጃቸው ሰውነቱ ላይ እንዳሻቸው ተራወጡ ፣ ደባበሱት . . . . ፈሩቅ የወንድነት ፈተና በአንድ ላይ ተደራርቦበት መደራደር አልቻለም :: እቅሉን ሳተ፣ አእምሮውን ተው ሊለው ሊያዘው ቢሞክርም አሻፈረኝ አለው :: ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ ከእጃቸው ለመውጣት በወጥመድ እንደተያዘች አይጥ ተፍጨረጨረ :: ሆኖም ሁሉም ነገር ሀሳብ ሆኖ ቀረ :: ሻካራ እጆቹን ትርፍስፍስ ሰውነታቸው ላይ ላካቸው ፣ መጋለብ ጀመሩ :: እሳቸውም እጃቸውን ላላ አድርገው የሰጡት ህክምና ምን ያህል

እንደሰራ ፈሩቅን ሰረቅ አድርገው አዩት ። እውነትም ሠርቷል ። ከንፈሩ ከንፈራቸውን ዳሰሰ ።

« ወንድማ ወንድ ነኝ ። ነገ ሄጄ እንደነገሩኝ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብሩን ወርውሬላቸው አይ የሚሉ ከሆነ አፋቸውን ለማስያዝ እሞክራለሁ » አለ ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ማለት ጀመረ።

ወ/ሮ አባይነሽ በመስጠትና ባለመስጠት በሀሳብ ባሀር ሲወጡና ሲወርዱ ቆዩ ። « ይህን ሁሉ ለፍተው አልሰጥም ብል በቀላሉ አይለቁኝም ነገሩ ከተባባሰ መቼም ውርደት ነው ። እንኳን መጥረቢያው መጣልኝ እንጂ ከእንግዲህ ገበያውም እንደሚያንሰራራ ተስፋ አለኝ ። ሺህ አምስት መቶ ብር ምን አለው ? የሁለት ቀን ሥራ ነው ። ስጦቹ ከሁሉም ጭንቀት ብገላገል ይሻላል ። እኔማ እንዳሰብኩት አምስት ሽህ ብር አምጪ ማለትስ ይችሉ አልነበር ? ታዲያ በቀላሉ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ሰጥቶ መገላገሉ በጣም ቀላል ነው ። ሆኖም ምስጢሩን ሁሉ ፈሩቅ ወደውጪ ያወጣው ይሆን ? ከነገሮች ሁሉ ከባዱ እሱ ነው ። ከአሁን በኋላ በጥንቃቄ መያዝ አለብኝ ። . . . አጠገቤ አርጌ ብቆጣጠረው ማን ይጠይቀኛል። ባይሆን . . . ልብሱን መለወጥ አለበት ። ሥራውም በዚያ አካባቢ ሲሆን አይችልም ሲቀየር ይገባዋል ፣ » የወፎች ጩኸት ተሰማ ። ንጋት ሆነ ።

ወ/ሮ አባይነሽ በድንጋጤ ተነስተው « ፈሩቅ . . . ፈሩቅ . . . ፈሩ . . ተነስ ነግቷል » ሲሉ ቀሰቀሱት ። ፈሩቅ የቀኝ እጁን አንገቱ ላይ ጠምጥሞ በዕንቅልፍ ልቡ ፣

« ምነው ቦጌ . . . ገና . . . ገናኮ ነው » ሲል አጉረመረመ ። ወ/ሮ አባይነሽ ክትክት ብለው ከልባቸው ሳቁና « ተበላሽቻለሁ እኔ አባይነሽ » ሲሉ ስሜታቸውን ወደንዴት ለወጡት ።

« ወራዳ ! ደሞ የማነች ቦጌ ? ቦጌ አባክ ይጥፋና ! በል አሁን ልብስህን ለብሰህ . . . የጀመርነውን ሌላ ጊዜ እናወራለን ።

ወደተላከበት ሂድ ፣ » አሉ ስሜታቸውን ለመግታት እየተጣጣሩ ። ነገር ላለማበላሸት ጥንቃቄ እያደርጉ አጠገባቸው ከነበረ ኮመዲኖ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር ቆጥረው ሰጡት ።

ከመኝታ ቤት ሲወጣ ሲል አስቁመው « አትፍራ ፣ ቀሪውን በቅርብ ቀን እሰጣለሁ ። ይህቺ ቦጌ ያልካት ደግሞ ዋ ነግሬሃለሁ ። እንግዲህ ይቅናህ . . . » አሉና ሸኙት ። እንደወጣ የመኝታ ቤቱን በር ዘግተው ትራስጌያቸው ሥር ያስቀመጡትን መጥረቢያ አውጥተው ከእጀታው እስከብረቱ አጠኑት ። የሚፈልጉት መጥረቢያ ላይ አንዳች የተለየ ፅሁፍ ወይም ምልክት ይኖራል ብለው ገምተው ነበር ። ግን እጀታውም ሆነ ጫፉ እንደማንኛውም ተራ መጥረቢያ ሲሆንባቸው ፣ « ታዲያ ምኑ ይሆን ድግምቱ ? » ሲሉ አሰቡና ፣

« ምን አስጨነቀኝ ? የሚቀጥለው ዓርብ አዋቂው ራሱ ይፈታው የለ ? » ሲሉ ሀሳባቸውን ደመደሙ ። የእሳቸው ግዴታ ዕቃውን ጠብቆ እስከ ዓርብ ማቆየትና ማቅረብ ነው ። ከመቀመጫቸው ተነስተው ከቁምሳጥናቸው አዲስ ነጠላ አውጥተው መጥረቢያውን ጠቀለሉት ። ቀስ ብለው ልብሳቸው መሀል አስቀምጠው ቁምሳጥኑን መልሰው ቆለፉት ። ከዚያም እጃቸውን ጨብጠው ሽቅብ ወደሠማይ እያነሱ « የትአባቷ በዚህ ያከትምላታል» እያሉ ወደ መኝታቸው ተመለሱ ።

ሕሊና በጥዋት ተነስታ ፀጉሯን አበጣጥራ ፣ አልጋዋን አንጥፋ ፣ ቁርስ አዘጋጅታ እንደጨረሰች ያሬድን ለመቀስቀስ የመኝታ ክፍሉን በር አንኳኳች ።

« ተነስ ሰዓት ደርሷል » አለችውና የፊት ለፊቱን መግቢያ በር ከፍታ ወደ ኩሽና ተመለሰች ። ኩሽናው አጠገብ ስትደርስ ክው ብላ ቀረች ። እራስዋን በእጆችዋ ይዛ ለመጮህ ቃጣት ። ዓይኖቿን ከኩሽናው በር ሳትነቅል የዋናውን ቤት የጓሮ በር እያንኳኳች ፣

« ጋሼ ያሬድ ! ጋሼ ያሬድ ! » እያለች እንደገና ተጣራች ።

ያሬድ በሩን እየከፈተ ፣ « ምን ሆነሻል ? ምን ሆነሻል ? » አላት በተቻኮለ አነጋገር ፤ በሩን ከፍቶ ከመኝታ ክፍሉ እየወጣ ::

« ሠረቁን . . . ተዘርፈናል ! ትናንትና በቁልፍ ዘግቼው ነበር:: » ስትል በመማፀን ስሜት ነገረችው የኩሽናውን በር እያመለከተች ያሬድ የበሩ ጓንቻር ተፈልቅቆ መሬት ላይ መጣሉን አስተዋለ ::

« እውነትም ሰብረውታል » አለ ያሬድ የተፈለቀቀውን ጓንቸር ከመሬት አንስቶ አገላብጦ እያየ ::

ሒሊና ያሬድን ካየች በሁዋላ እየተጣደፈች ወደክፍሉ ዘልቃ ገብታ ነበር :: በምትችለው ፍጥነት ዕቃውን ሁሉ ለማየት ሞከረች :: ቁምሣጥኑም ፣ ብሀቃውም በቦታቸው አሉ ::

« ምንም አልወሰዱም ፣ ለምን ታዲያ ሰበሩት ? » አለች ያሬድ ወደ ኩሽናው ክፍል ሲገባ አይታው ::

« እነኚህ ፈሪ ሌቦች ሳይሆኑ አይቀሩም :: ሰው ሲገላበጥ ሰምተው ወይም መብራት ሲበራ አይተው ፈርጥጠዋል ማለት ነው:: ግን እኔን ምን ነካኝ ? ቁልፍን ያህል ነገር ሲሰብሩ መስማት ነበረብኝ» አለ በሁኔታው በመገረም ::

« ለዛሬ ተርፈናል ይመስገነው ፤ ለወደፊቱ ግን ጥሩ ማስጠንቀቂያ ይሆናል :: ነቅተን እንጠብቃለን :: . . . በል አሁን ሰዓት ደርሶብሀል ፊትሀን ታጠብ ፤ እኔም ቁርስሀን ላቅርብልህ » አለችው :: ያሬድ የታዘዘውን ፈፅሞ ቁርስ ስታቀርብለት ፣

« እስኪ አምጪ እንብላው የሌቦቹን ትራፊ » አላት ሠረቅ አድርጎ እየተመለከታት ::

« መቼ ተነካና ነው ትራፊ የምትለው ? » አለች በቅሬታ ዓይነት ::

« ሁሉም ነገር በቦታው አለ አልሽ እንጂ ይጨምር ይቀነስ በምን ታውቂያለሽ ? »

« እኔ ዕቃ ስከድን ምልክት የማድረግ ልምድ አለኝ » አለችው የጠፋ ዕቃ አለመኖሩን እንዲያምንላት ::

« በነገራችን ላይ ዛሬ ሀሰን ይመጣ ይሆናል ፤ ጥሩ ምሳ አዘጋጅተሽ ጠብቂን ሲል የጀመሩትን ርዕስ አስቀየራት ::

« ለመምጣት ያብቃችሁ እንጂ ምሳውስ አይቸግርም » አለችው ::

* * *

ጭጋጋማው የክረምት ወራት አለቀ :: ደመናው ሸሽቶ ለንፁህ ሠማይ ቦታውን ሰጠ ፣ አደይ አበባዎች ፈነዱ :: « ዕንቁጣጣሽ በየዓመቱ ያምጣሽ » እያሉ ህፃናት ቦረቁ :: « እዮሃ አበባዬ » በማለት አዲሱን ዓመት በደስታ አበሰሩ :: የተዘጉ ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ ::

የአቃቂ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ግቢ በልጆች ተወረሰች :: ሁሉም ለዘመን መለወጫ የተገዛላቸውን ልብስ ለብሰው አበባ ይመስላሉ :: ወንዶቹ በጨርቅ ኳስ የእግር ኳስ ይጫወታሉ ፤ ሴቶቹ ሰኞ ማክሰኞ ይዘላሉ :: የተወሰኑት ሁለት በሁለት ተጓድነው አረንጓዴ ምንጣፍ በሚመስለው ለምለም ሣር ላይ ተቀምጠው የጠጠር ቅልልቦሽ ይጫወታሉ ፤ ሌሎች ደግሞ « ከም . . . አሞ . . . ሴላ . . . ሪካ . . . » እያሉ የገመድ ዝላይ ይጫወታሉ ::

ቀደም ሲል ት/ቤት ከመከፈቱ በፊት ዳይሬክተሩ ለያሬድ በገቡለት ቃል መሠረት ሒሊና የሦስተኛ ክፍል ፈተና እንድትወስድ ተደርጋ መልካም ውጤት ብታመጣም ለማንኛውም ተብሎ ከሁለተኛ ክፍል እንድትጀምር ተደረገ :: 2ኛ ሀ እንደተመደበች ከበራፉ ላይ ከሌሎች ተማሪዎች ስም ዝርዝር ጋር አብሮ ስሟ ተፅፎ ወጥቷል :: ሒሊና የትምህርት ቤቱ ሁኔታ እንደጓጓችለት አልሆነላትም ::

ከት/ቤቱ ተማሪዎች መካከል አኩ·ያዋን ማየት ባለመቻሉዋ ወይም የልጆቹ የልጅነት ድርጊት አደናግሯት ወይም በሁሉም ምክንያት ግቢው አልመቻት አለ ። እራሷን እንደምንም ስትቆጣጠር፣ ግቢውን ስታጠና ውላ ሲመሽ ወደቤቷ እስክትመለስ ድረስ የሆነ ነገር ሆድዋን ይጎረብጠው ነበር ።

ያሬድ ቤት የገባው አምሽቶ ነበር ። በጥድፍያ ልብሱን አውልቆ ፒጃማውን ለብሶ ሕሊና ጎን ሲቀመጥ በጉጉት ነበር ።

« ውሎሽ እንዴት ነበር ? » ሲል ጠየቃት ።

« ጥሩ ነበር . . . ግን ምንም ትምህርት አልተማርንም ። ዝም ብለን ሜዳ ላይ ስንጫወት ውለን መጣን »

« ታዲያ ትምህርት ቤት መዋሉ ጥሩ አይደለም ? »

« አይ እሱማ ጥሩ ነበር ። ነገር ግን እነኛ ውጪጮች ሲበጠብጡ በጣም ያስጠላሉ . . . . አቤት . . . ጨኸታቸውስ አያድርስ ነው ። የሁሉም በየፊናው መጯጯህ ይሰለቻል ። »

« አይዞሽ አትፍሪ እየቆየሽ ትለምጂዋለሽ ። የት/ቤት ህይወት እውስጡ ካልገቡ በስተቀር ከጅምሩ መረዳት አይቻልም » ሲል ሲያበረታታት ሞከረ ።

በማግስቱ ሕሊና ወደ ትምህርት ቤት አመራች ። ከግቢው ስትደርስ ከሠንደቅ ዓላማው በስተኋላ ተማሪዎች ሲተራመሱ ተመለከተች ። ተማሪዎቹ በየክፍል በየክፍላቸው በመሠለፍ ሠንደቅ ዓላማ ለመስቀል እየተጣደፉ ነበር ። ሕሊና የክፍሏን ልጆች እንደምልክት ተጠቅማ ወደክፍሏ መስመር ገባች ። ለትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ የሠልፍ ቀን ስለነበር ሥነ-ሥርዓቱ የጠበቀ አይደለም ። ሠልፍ መስለፋቸውን መምህራኑ አረጋግጠው አስፈላጊውን የሠንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት ከፈፀሙ በኋላ አንድ ወፈር ያለ ጠይም ደልዳላ ሰው ከተማሪዎቹ ፊት ለፊት ቆመው የሥነ ሥርዓት ሁኔታውን ለተማሪዎች ካስረዱ በኋላ ተማሪዎቹ

ወደየክፍሎቻቸው አመሩ ። ሕሲናም ከ2ኛ ሀ ተማሪዎች ጋር ተቀላቅላ ወደ ክፍሏ ሄደች ።

በክፍሉ ውስጥ 57 ተማሪዎች ይገኛሉ ። አብዛኛዎቹ ከስምንት ዓመት በታች ናቸው ። በቁመትም ቢሆን ከሕሊና ጋር ሲመጣጠኑ በጣም ትልቅ ልዩነት እንዳለ ይታይ ነበር ። ተማሪዎቹ ክፍላቸው ከገቡ በኋላ የሚፈልጉትን ቦታ ለመያዝ ከፍተኛ ትርምስ ተቀሰቀሰ ። ግማሹ ያለበትን ወንበር ላለመልቀቅ ፣ ሌላው ለማስለቀቅ ሲጋፉ ፣ ሌሎች ደግሞ ላልመጡት ጓደኞቻቸው ቦታ በመያዝ ጭቅጭቅ ሲፈጥሩ ሕሊና ግራ ተጋብታ መሀል ሜዳ ላይ ቆማ በመገረም ስታይ ቆይታ ባገኘችው ባዶ ቦታ ላይ ሄዳ ተቀመጠች ። በመካከል የሥም ጠሪው መምህር ፋይላቸውን ይዘው ወደ ክፍሉ ገቡ። መምህሩ ፂማቸውን ያሳደጉ ፣ ቲትሮን ኮትና ሱሪ የለበሱ ፣ ከቁመታቸው አጠር ብለው መሀከለኛ ውፍረት ያላቸው ፣ በሉጫ ፀጉራቸውና ፂማቸው ላይ አልፎ አልፎ ሽበት ወጋ ወጋ ያደረጋቸው ሲሆኑ ገና ወደ ክፍል ሲገቡ ተማሪዎቹ በአንድ ድምጽ ፣

« ውይ ! » በማለት ከተቀመጡበት ተነሱ ። እዚያው እንደቆሙ ግማሾቹ እጃቸውን በአፋቸው ጋርደው አጠገባቸው ለቆመው ጓደኛቸው በሹክሹክታ ማውራት ጀመሩ ። መምህሩ በጠረጴዛው ላይ ፋይላቸውን ወርውረው ወደ ተማሪዎቹ ፊታቸውን መልሰው ፣

« እንደምን አደራችሁ ተማሪዎች ? እንኳን ለአዲሱ ዓመት የትምህርት ዘመን አደረሳችሁ» ሲሉ ሠላምታ አቀረቡ ። ተማሪዎቹ አፀፋውን እንደመለሱላቸው ሕሊና ወደ ተቀመጠችበት ቦታ እየተራመዱ « ተነሽ ! » ሲሉ ቆጣ ብለው አዘዟት ። ሕሊና ከመቀመጫዋ ለመነሳት ብትሞክርም አነስተኛ የሆነው የመቀመጫው ድጋፍና በውስጥ ያለው ተደራቢ የደብተር ማስቀመጫ አንድ ላይ ተባብረው ጉልበቷን አጣብቀው ስለያዟት መነሳት አልቻለችም ።

ከአጣብቂኙ በግድ ተላቃ ወደ ዳር በመውጣት ቆመች ። የስም ጠሪው ትዕዛዙን ሰጥተው ወደ መደበኛ ቦታቸው በመመለስ ፣ « ተማሪዎች ተቀመጡ» ሲሉ አዘዙ ። ሕሊና ግን ሳትቀመጥ እንደቆመች ቀረች ። በክፍሉ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በሙሉ ፊታቸውን ወደ ሕሊና መልሰው ተመለከቷት ። ሳቅ አፍኗቸው ነበር ። የክፍል ኃላፊው ተማሪዎቹን እያዩ ፣ « ትምህርት ቤት እንደ ቡና ቤት ሁሉንም ሰው ቁጭ ብሎ መቀበል አይቻልም ፤ አይደለም እንዴ ተማሪዎች ? » ሲሉ በሽሙጥ ጠየቁ ። « አይቻልም » በማለት በህብረት ጮሁ ተማሪዎቹ ።

« ስመሆኑ እንዴት ትምህርት ቤት ገባሽ ? » ወደ ሕሊና እየተጠጉ ጠየቋት ።

ሕሊና ለዚህ ላልጠበቀችው ስድብና ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት አልቻለችም ። መምህሩን እያየች ዕንባ ተናነቃት ። በልመና መልክ ዓይኖችዋ ከብለል ከብለል ይሉ ጀመር ። ግን ሊገባቸው አልቻለም። እንዲያውም የመምህሩ ድርጊት የተንኮልና ሰው የላከው ዓይነት መስሎ ታያት ። በዚህ ላይ በት/ቤት ውስጥ የዚህ ዓይነቱ ዘለፋ ቀመስ ፌዝ እንደሚካሄድና ሁሉም ተማሪዎች በየተራ እንደሚደርስባቸው አላወቀችም ።

በወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤት በፈገግታ የሚቀበሏት እቶ ጌታቸው አድማሱ ፣ የአሁኑ መምህሯ በእነኚህ ትንንሽ ልጆች ፊት እሷን ማዋረዳቸው ሊዋጥላት አልቻለም ። ገፍትራቸው ልትወጣ አሰበችና የያሬድ ጭንቀት እየታያት ከድርጊቷ ተገታች ። መምህሩም ፣

« ሁለተኛ እንዳይሰምድሽ እሺ ወይዘሪት . . . ወይስ ወ/ሮ » ሲሉ መምህሩ በማፌዝ ጠየቋት ። ታፍኖ የነበረ የተማሪዎች ሳቅ ፈነዳ ። ሕሊና ድርጊቱን መቋቋም አልቻለችም ። በማታውቀው ኃይል ተገፋፍታ ከመምህሩ ፈቃድ ሳትጠይቅ እያለቀሰች ወጥታ በረረች ። መምህሩ በሕሊና ድርጊት ተደናግጠው ተከተሏት ።

« ሕሊና ! ሕሊና » ሲሉ ጠሯት ። ሆኖም ምንም መልስ አላገኙም ። መልሰው ወደ ክፍላቸው ገብተው ተማሪዎችን በመቆጣት በችኮላ ከክፍል ወጥተው እየተምዘገዘጉ ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ አመሩ ። ተማሪዎቹ በድንጋጤ ፀጥ ብለው ቀሩ ።

ሕሊና እንባዋን እያዘራች ወደቤትዋ ነበር የሄደችው ። ቤት እንደደረሰች ከረጢቷን አውጥታ አልጋዋ ላይ ተጋደመች ።

« እንግዲህ አባቴ አትቀየመኝ ። ትምህርት ለመጀመር የመጨረሻ ሙከራዬን በዛሬው ቀን አድርጌ ነበር ። ነገር ግን የተፈታተኑኝን ሁኔታዎች ሁሉ ለመቋቋም ባለመቻሌ መተው ግዴታ ሆኖብኛል ። ቀደም ብዬ ቃል በገባሁልህ መሠረት እንተን በመርሳት ወይንም በፍላጎቴ ሳይሆን በመገደዴ ብቻ ነው » አለችና መጥረቢያው ላይ ዓይኖችዋን ተከለች ። እንደድንገተኛ ውሃ ሙላት ፍርሃት ዋጣት። መንፈስዋ ባዶ ሆነ ። በዓይኗ የሆነ ምስል የሚታያት መሰላት ። ማመን አልቻለችም ።

« አባዬ ! አባዬ! » እያለች ቤቱ ውስጥ ስትጮህ ለእርሷ አልታወቃትም ነበር ። ከብዙ ቆይታ በኋዋላ ጎረቤቷ የሆኑት የኩቻ እናት ተደናግጠው ወደነያሬድ ቤት ገቡ ። ሕሊና በትምህርት ቤት ውሎዋ የገጠማትን ዝርዝር ሆኔታ ስትነግራቸው በጣም አዘኑ ። በማጽናናት መልክ እራስዋን እየደባበሱ ሊያስተኟት ሞከሩ ።

ያሬድ ከሥራ ሲመለስ ቤቱ በጎረቤት ሰዎች ተሞልቶ አገኘው ። ክፉኛ ተደናገጠ ። «ምን ሆናችኋል ? ሕሊና ምን ሆነች?» ሲል ዓይኑን አፍጥጦ ጠየቀ ። የኩቻ እናት « ዝም በል » በሚል ምልክት ተማፀኑት ። ያሬድ ግራ ተጋባ ።

« አውቄዋለሁ ! ይህን መጥረቢያ አውጥቶ መጣል ነው ! እሱ ካልጠፋ ምንም ጤና አታገኝም ። ግን በምን ዓይነት ሁኔታ ማስረዳት ይቻላል ? እሷ በጆ አትል ! » እያለ በንዴት እየጮኸ ወደ

ቤት ገባ ። ተቀምጠው ስነበሩት ሴቶች የረሳውን ሠላምታ ሰጥቶ ወደ ሕሊና በመቅረብ ፣

« ሕሊና ደህና ነሽ ? ተሻለሽ ? » ሲል እራ ኗዋን አሻሻት ። እራስዋን በማንቀሳቀስ የእምንታ ምልክት ፈገግ ብላ አሳየችው ። ሠዓቱ እየቆየ ሲሄድ ሊጠይቋት የመጡ ሰዎች « እግዜር ይማርሽ » እያልዋት ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

ያሬድና ሕሊና ስለሁኔታው ለመወያየት ጊዜ ያገኙ መሰሉ ። ሕሊና ክንዷን ተንተርሳ የያሬድን ዓይን እየተመለከተች ፣

« ጋሼ ያሬድ አትቆጣኝ ከአሁን በኋላ ትምህርት ቤት አልሄድም ። . . . አውቃለሁ ። አሁን ልክ አይደለሽም ብለህ ልትመክረኝ ትሞክር ይሆናል ። የዛሬው ቀን የትምህርት ገበታዬ እንዳሰብኩት ሊሆን አልቻለም ። በዚህ ምክንያት ነው እራሴን ያመመኝ » አለችው ትንፋሿን በረጅሙ ለቃ ። በቀን ውሎዋ ያጋጠማትን የአስተማሪዋን ዘለፋ ፣ ስለልጆቹ ሳቅ አንድም ሳታስቀር ነገረችው ። እና አለች ለስለስ ባለ የድምጽ ቃና በዚህ ሁኔታዬ የአባቴን ምኞት ለማሳካት እንደማልችል ስለተረዳሁ ነው አለችው በሰጨት ብላ ።

« መጀመሪያ ህመምሽ ይሻልሽና ለስ ትምህርቱ በኋላ እንነጋገራለን » አላትና ሌላ መልስ ላለመስማት ወደሳሎን ሲመለስ ከእልጋው ሥር ግማሽ እካሉ የወጣውን መጥረቢያ እስተዋለ ።

* * *

ወ/ሮ አባይነሽ መጥረቢያውን በፈሩቅ አስይዘው ከምሽቱ 1 : 30 ሲሆን ከአቃቂ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው ገጠር መሳይ አካባቢ ሄዱ ። ጊዜው ጨረቃ በመሆኑና ዝናብም ባለመኖሩ ለጉዞው አመቺ ሁኔታን ፈጥሮላቸው ነበር ። እኩል ለዓት ያህል ከተጓዙ በኋላ እጅብ ያሉ የጎጆ ቤቶች ወደሚገኙበት አካባቢ ሲደርሱ ለፈሩቅ ስለሚሄዱበት ቤት ሥነ ሥርዓት ነገሩት ። እሱም የሚነገረውን ሁሉ እራሉን በማነቃነቅ በእሺታ አዳመጠ ። « ፈሩቅ ስትገባ ጫማህን አውልቀህ መግባት እንደአለብህ እንዳትረሳ » አሉት ወ/ሮ አባይነሽ ።

« ኧረ የጫት ቃሚ ዘር እኮ ነኝ ቀን ጎሎብኝ የሰው ጓሮ ጠባቂ ሆንኩ እንጂ ። ግድየለም የሚያስፈራ ነገር የለም » ሲል እንደድሮው ሳይሽቆጠቆጥ መለሰላቸው ።

« አይ ፈሩቅ አንተ ደግሞ ደግ ደጉን ሲነግሩህ ግራ ነው የምትመልሰው »

« እሱን እንኳ ግራ ተናጋሪው ማን እንደሆነ እሱ ነው የሚያውቀው ። ግን ሰውን ትንሽ እድርጎ ሁልጊዜ መገመት ተገቢ አይደለም » አላቸው ። ቤቱ አካባቢ ሲደርሱ ፣ « ለማንኛውም ያ ትልቁ እልፍኝ ነው ። ብዙ አታውራ ። ቀስ ብለን ነው የምንገባው ። እዚያ የተሰበሰበው ሁሉ የከተማው መኳንንትና ወይዛዝርት ናቸው ። የእኔ ተራ ሲደርስ አንተ ልብ ብለህ አዳምጥ » አሉት ።

አንድ የሣር ክዳን ያለው ክብ የጭቃ ቤት አጥር በር አጠገብ ደርሰው እንደቆሙ መልኩን ለመለየት ያዳገተው ጋቢ የሰበሰ ሰው ከቤቱ ወጥቶ « ወ/ሮ አባይነሽ ደግ ዋላችሁ ፤ በር ላይ አትቁሙ »

በማለት ወደ ቤት አስገባቸው ። ጫማቸውን አውልቀው ወደ አልፍኙ ገቡ ።

የሚበራው ሻማ ከማሾ ጋር ተደባልቆ ቤቱን የብርሃን ፀዳል ሞልቶታል ። የፊት ለፊት እግራቸውን አጠላልፈው የተቀመጡ ወፋፍራም ሰዎች ነፋስ እንደሚያወዛውዘው ዛፍ አንገታቸውን እየነቀነቁ እጃቸውን ወደ ፊት ለፊታቸው ዘርግተው እራሳቸውን ወደ ለማይ አንጋጠው « አሜን . . . አሜን » ይላሉ ። ከፊት ለፊታቸው በመጋረጃ ውስጥ የማይታይ ሰው ቅኝት ባለው ዜማ እየዘመረ « ሰለላ . . ያ መሀመዴ . . ና ታረቀን ቤትህ ነው አንተ አዳልሞቴ ደፋሩ ግባ በበሩ . . . » በማለት ያዜማል ።

በቤቱ ውስጥ የተሰበሰበው ሴትና ወንድ ከንፈሩን በመምጠጥ፣ « አይ ጌታዬ ባንተው መጀን . . » በማለት እየተቀበለ አመኔታውን ይገልፃል ። ወ/ሮ አባይነሽ ከመጋረጃው ፊት ለፊት እንዲቀመጡ ካዳሚው እያጋፈራቸው በተሰጣቸው ቦታ ላይ ተቀመጡ፡፡ ፈሩቅም ከኋላ ከነበሩት ሰዎች ጋር ተደባለቀ ።

ከወ/ሮ አባይነሽ አጠገብ የተቀመጡት አብዬ ጋሻዬ ቢሆኑም አልተያዩም ። አብዬ ጋሻዬ ነጠላቸውን እስከ አፍንጫቸው ድረስ ተከናንበው ሕዝቡ የሚያደርገውን ሁሉ ይፈፅማሉ ። ከፊት ለፊት የቆመው ካዳሚ በመጋረጃው ውስጥ እጁን ሰዶ በእጁ ሙሉ እቃራ ጫት ከማይታየው ሰው በሁለት እጁ ጎንበስ ብሎ ይቀበልና እጅ ነስቶ መለስ ብሎ ከወገቡ ቀና ሳይል ለወ/ሮ አባይነሽ ሲሰጣቸው ከካዳሚው ተቀብለው ስመው በቀሚሳቸው ላይ በማስቀመጥ አንዱን ዘለላ አንስተው እየቀነጠሉ ወደ አፋቸው መክተት ጀመሩ ። አብዬ ጋሻዬ ወ/ሮ አባይነሽን ቀረብ ብለው ከተመለከቱ በኋላ ፣

« ምን እግር ጣለሽ ወ/ሮ አባይነሽ » ሲሉ በሹክሹክታ ጠየቋቸው ። እሳቸውም የተሰጣቸውን የጫት ቅጠል እያመነዠጉ ፣

« አንተን ያመጣህ እኔንም ጎተተኝ » በማለት ፈገግ አሉ ።

« መቼም ሰው ወዶ አይደለም ከሠይጣን የሚዛመደው ፣ የሚያደርገው ሲጠፋው ነው እንጂ » አሉና አብዬ ጋሻዬ በመቀጠል « አውሊያው አልገባም ብሎ ሰው ሁሉ እየቃመ ነውኮ » አሏቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽም « አውሊያው የሚገባው እኮ ሀጢአት የሰራው ሁሉ ለውቃቢው ሲሳል ነው ድንገት መናፍስት ገብተው ከሆነ ያረክስብናል » እያሉ ሲወያዩ ከመጋረጃው ውስጥ የማይታየው ሰው በተለየ ድምጽ ምርቃቱንና እርግማኑን ጀመረ ።

« ጫት ሺዲድ ፣ ሽቶ ሺዲድ ፣ አውዛ ሺዲድ ፣ የሚጠላን ሁሉ ይወገድ ፣ ድንበራችንን ጥሶ የመጣ ፣ እኛን በሰው ፊት ያሳጣ፣ ጠዋራውን ያላነጣ ፣ ሽንኩርትና ቁጦ አላምጦ ውጦ የመጣ ፣ ከንፈሩን መጦ በሰው አሻጥር ለመስራት የሚጠራጠር ፣ ወጊድ በለው እባክህ ፤ እንፈራፍሮ እንዳይረግጠው . . . አዳልሞቴ ፍርዱ የማያወላዳ መጥቻለሁ እንደ እሳት የሚፈጀው ፊቴ ኤሎሂ ! ኤሎሂ ! . . . » በማለት አጓራ ። በአካባቢው የተኮለኮሉ ሰዎችም አንገታቸውን ደፍተው « እግዚዮ ማረን ጌታዬ ይቅር በለን » በማለት እራሳቸውን መሬት ላይ ደፍተው እጃቸውን ወደ መጋረጃው ዘርግተው ይማፀናሉ ። ከባለጉዳዮቹ መካከል አንድ በመሀከለኛ ዕድሜ የሚገኝ ሰው ብድግ ፣ ብሎ

« ጌታዬ በደል ደርሶብኝ ነው የመጣሁት ። ፍርድህን ስጠኝ፣ ስለትህን እገባልሃለሁ » በማለት ሰገደና ቀና ብሎ ተንበረከከ ።

« እሀ. . . ሀ. . . ሀ. . . ሀ የመጣኸው ከሩቅ ሀገር ነው ። ቤትህንና ትዳርህን ለማፍረስ ጎረቤቶችህ አድመውብሃል . . . . እሀ. . . ሀ. . . ሀ. . . ሀ ከዚህ ቀደም መጥተህ ፈርደንልህ ነበር ። አንተ ችላ አልከው እንጂ አሁን ጊዜም የለኝ እየመሸብኝ ነው » ሲል ከመጋረጃ ውስጥ ያለው ድምፅ አስተጋባ ። የተንበረከከው ሰው ሰገደና ፣

« ኧረ ጌታዬ ያሰብኝን እፈጽማለሁ አትጨክንብኝ » ሲል ተማፀነ ::

« በቤትህ በራፍ ጥቁር በግ አረድና በጣትህ ደሙን ነክተህ በእራስህ ዙሪያ ሶስት ጊዜ አዙር :: የበጉን ጭንቅላት ጓሮ ወስደህ ቅበረው :: የተረፈውን ላሞራ ስጥ ፤ ጠላትህ እንደ አሞራ ይብረር ፤ ሃጃህ ሲሞላ እኛን እንዳትረሳን ፤ ሰማህ ወይ ? » አለው የመጋረጃው ሰው ድምፅ ::

« ሰምቻለሁ ጌታዬ :: ስለቴን ጉዳዬ በተፈፀመ በማግስቱ አስገባለሁ » አለና እጅ ነስቶ ተቀመጠ :: ባለተራው አብዬ ጋሻዬ ነጠላቸውን አጣፍተው ሲቆሙ ፤

« አትምጣብኝ ብዬ አልነበረም አንተ ወላዋይ ? » አለ የማይታየው የመጋረጃ ድምጽ ::

« ጌታዬ ማረኝ በጥፋቴ ልትቀጣኝ ይገባሃል አትጨክንብኝ » በማለት መሬት ላይ ተደፋ ::

« የልጆችህን እናት ለምን አስቀየምካት ? የህብትህ መሠረት እሷም አይደለች? »

« ጌታዬ ሀቅ ነው አስቀይሜአታለሁ :: ሆኖም የወለደቻቸው ሴቶች ብቻ በመሆናቸው ወንድ ልጅ እንድትሰጠኝ ተማልጄህ ነበር :: አሁንም አልተፈፀመልኝም » በማላዘን ተንበርክከው ተናገሩ ::

« ወንድ ልጅ ወንድ ልጅ እህ . . . ህ . . . ህ » በማለት አዜመና « አምናም ወንድ ልጅ ዘንድሮም ወንድ ልጅ ፤ እንደእሳት የሚፈጅ ፤ ለእውሊያችን የሚሆን አጎብዳጅ ፤ እሱማ እውነትህን ነው:: ታዲያ የልጆችህ እናት ማህፀንዋ ወንድ ልጅ አይሸከምም ፤ ከሴላ ሞክር ብዬህ አልነበረም ወይ ? » ሲል የማይታየው ሰው ፀጥ አለ ::

« ጌታዬ ሞክሬ ነበር ፤ አልሆነልኝም እንጂ » አሉ ወ/ሮ አባይነሽን የጎድን እያዩ ::

« የነጠፈች ከብት ምንም ብትጠቃ ለፍሬም አይላት እህ . . . ህ . . . ህ . . . ጊደር መሳይ ፈልግ ፤ ስታይህ የምትለውን ፈገግ እህ . . . ህ . . . ህ ሰማህ ወይ ? » አለ :: አብዬ ጋሻዬ ፈጠን አሉና፤ « አዎ ሰምቻለሁ ጌታዬ አመጣጤም ለዚሁ ነው ጌታዬ፤

ከአንድ አልባሌ ቦታ ፤
ስሟን የማልጠራው የሆነች ከርታታ ፤
ስሜቴን የነካችው በጥርሷ ፈገግታ ፤
አለች አንዲት ውብ ልጅ ያየኋት ላንዳፍታ ፤
መርቅልኝና ልድፈራት አቤት የኔ ጌታ :: » በማለት

ዓይናቸው ከወ/ሮ አባይነሽ ወደ መጋረጃው በደስተኛነት ስሜት አስተዋለ ::

« እህ . . . ህ . . . ህ . ህህ
እሷን ለመድፈር ከሆነ ፈቃድህ ፤
ለማግኘት ወንድ ልጅ እንደምንም ብለህ ፤
አውልያው ይከተልህ አቦ እንደልማድህ ::
እህ . . . ህ . . . ህ የምድሩ ባለቤት የሰማዩ ጌታ ፤
እንግዲህ ይስማልህ ይህን አቤቱታ » በማለት

የማይታየው ሰው ድምፅ ፍርዱን ሰጠ :: አብዬ ጋሻዬ እየፈነደቁ አጠገባቸው የነበሩትን ወ/ሮ አባይነሽን እንኳን ሳይቀር « አሜን . . . አፎቱሱላሂ » በማለት ስመው ዞየሩ :: በዚህ ዓይነት የብዙ ሰዎች ጥያቄ ፍርድ ከተሰማ በኋላ የወ/ሮ አባይነሽ ተራ ደረሰና ተነስተው ተንበረከኩ ::

« አቤት ! አቤት ! የኔ ጌታ ! » በማለት መማፀን ጀመሩ ::

« ሠላም የለሽ በቤትሽ ፤
የእህትሽ ባል በመጥረቢያ ያስደገመብሽ ፤
ወ/ሮ ፤ የተባልሽውን አገኘሽ ? » ሲል ጠየቃቸው ::

« አግኝቻለሁ ። ጌታዬ እም አግኝቻለሁ ካንተ ምን ይሰወራል፣ ስለትህን ይኸው ለማስገባት እምጥቻለሁ » ሲሉ ከተንበረከኩበት ሆነው በእጃቸው የጨበጡትን ለካዳሚው ሰጡ ። ካዳሚውም ተቀብሎ በመጋረጃው አሳልፎ ለማይታየው ሰው አቀበለ።

« እህ . . . ሀ . . . ሀ . . መጥፎ ያለበውን በላ ይውረድበት፣ አሁን ምን አደረገችህ ይህች የዋህ ሴት ፣ ለፍታ ስለበላች ! በሠራችው ቤት ፣ . . . ለንፋስ ይዳርገው ፣ እርጉም አጋንንት ፣ እናረክሰዋለን ለጥተን ትሩፋት » በማለት መጥረቢያውን ከሆነ ነገር ጋር ሲያጋጨው የብረት ጩኸት ተሰማ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ሳቅና ለቅሶ በአንድ ላይ በማደባለቅ አጠገባቸው የተቀመጡትን ሰዎች አንድ በአንድ እጃቸውን ስመው ቦታቸው ተመልሰው ተቀመጡ ። ከዚያም ወደ አብዬ ጋሻዬ እቅጣጫ እየተመለከቱ ከቢጤዎቻቸው ጋር የባለወረፋውን አቤቱታ እየሰሙና ከንፈራቸውን እየመጠጡ ፣ « አሜን . . . አሜን . . . » በማለት የፈራጁን ድምፅ ተቀበሉ ። በዚህ ዓይነት ሌሊቱ በጭፈራና በዜማ አሰፈና ዶሮ አንድ ጊዜ ሲጮህ በመጅሊስ ላይ የነበሩት ሰዎች ሁሉ እየወጡ መበታተን ጀመሩ ።

ወ/ሮ አባይነሽና ፈሩቅ ተከታትለው ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ እንዳሉ ፣ « አየኸው ያ ወራዳ ሽማግሌ ፣ ቀላል ! ደግሞ ብሎ ብሎ ወንድ ልጅ አጥቻለሁ በማለት . . . ያቺን ወሰላታ ገፊ እኮ ነው አግኝቻለሁ የሚለው » ሲሉ ወሬ ጀመሩ ።

« እሷ ደግሞ ማነች ? » ሲል ጠየቀ ፈሩቅ ።

« ያቺን መተተኛ ሕሊና ናታ ! በዚያ በመተቷ ዳበስ ዳበስ ሳታደርገው አልቀረችም ። አንድ ቀን እኔ ጋ መጥቶ ይህች ውብ ቆንጆ እያለ ጆሮዬን ሲያደነቁረኝ ነበር ። »

« እይ . . . ሄ እሱን እንኳ ይተውት ። መተተኛነቷ ከፋ እንጂ ሰውበቷስ ምንም እንከን አይወጣላትም » አላቸው ። ወ/ሮ አባይነሽ ቆም ብለው ፈሩቅን ዓይን ዓይኑን በቁጣ ከገረመሙ በኋላ ፣

« እኔስ ምን ይሻለኛል የዘንድሮ ወንዶች ፣ አንተንም አስነክታህ እንዳይሆን ፣ ዳሩ ምን ያደርጋል መጥረቢያውን በእጅህ ጨብጠህ የለ ምን ቀረህ ? » አሉ በቅናት ።

የፈሩቅ መዳፈር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መጣ ። ወ/ሮ አባይነሽ ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ እየሆነባቸው ሄደ ። ከብዙ ማሰላሰል በኋላ ፈሩቅን ከአጠገባቸው ማራቅ እንዳለባቸው እራሳቸውን አሳመኑ ። ቢሆንም ፈሩቅን ከአጠገባቸው ማራቅ ቀላል አይደለም ። ጠቅላላ ምስጢራቸውን ያውቃል ። ተንኮላቸውን አጥንቶታል ። ከሁሉም በላይ ጭናቸውና ሀብታቸው ጥሞታል ። ሀብታቸውን እሱ በመሰለው መንገድ መቆጣጠርና የእልጋ ደንበኞቻቸውን ማባረር ያዘ። እያደር የእሳቸው ባል ፣ የንብረታቸው ባለቤት እየሆነ ፣ ለውም እየፈራው መጣ ።

በዚህ ዓይነት ከተራ ሠራተኛነት ወደ ባለሟልነት ከዚያም እያለ ወደ ባልነት በመጨረሻም የሀብቱ ፈላጭ ቆራጭ አባወራነት እየተሸጋገረ መጣና ወ/ሮ አባይነሽን ማዘዝ ጀመረ ። የሀብታቸው ሁሉ የበላይ ሆነ ።

አንድ ጊዜ ወ/ሮ አባይነሽ በጠና ይታመማሉ ። ፈሩቅ ወደ ህኪም ቤት እንዳይሄዱ በመፈለግ ቤቱ ቂጤማ አስጎዝጉዞ ፣ ቡና አስፈልቶ ፣ ዕጣን አስጭሶ ጠያቂ በመጣ ቁጥር ፣ « ውቃቢ ነው ያልፍላቸዋል » በማለት ከሳሉን እያስቀረ ይሸኛል ። ወደ ወ/ሮ አባይነሽ መኝታ ቤት እንድታልፍ የተፈቀደላት የወጥ ቤት ሠራተኛዋ ካብትሽ ብቻ ነበረች ። ወ/ሮ አባይነሽ ጣር ባዘለ ድምጽ ፣ ካብትሽ የነብስ አባታቸውን እንድትጠራላቸው ተማጸኗት ። ወ/ሮ አባይነሽ

ሲፈሩ ሲቸሩ የነፍስ አባታቸውን ጠበል እንዲረጩ ነው በሚል ሰበብ ወደ መኝታ ቤት አስገቧቸው ::

« ምነው ልጄ ? ምን ነካሽ ? » በማለት ጠጋ ብለው የነፍስ አባታቸው ጠየቋቸው :: ከአንገታቸው ነቃ አሉና በሴባ ጣታቸው የነፍስ አባታቸው ዝም እንዲሉ አፋቸውን እየጠበጠቡ አሳዩና ፣

« ካብትሽ » ሲሉ ተጣሩ :: ካብትሽ ከተፍ አለች ::

« ፈሩቅ ሳሎን እንዳለ አይልኝ » ሲሉ አዘዟት ::

« ማንም ሰው የለም » ብላ ካብትሽ ወጣች ::

« አባቴ ይቅር ይበሉኝ :: ሀጢአቴ ከራሴ ፀጉር የበዛ ነው » በማለት መናዘዝ ጀመሩ ወ/ሮ አባይነሽ ::

« ምን ሀጢአት ሰርተሽ ነው ይቅር የምልሽ ፣ ፀበል ፀዲቁን በጊዜው እየለገስሽ ፣ የነፍስ አባትሽን በየዓመቱ በዓሉ እያስታወስሽ ፣ ፀሎትና ቤተክርስቲያን መሳም ሳይለይሽ ፣ ከይህ የበለጠ በሥጋሽ የኖርሽ ለምኑ ነው ንስሃው ? » ብለው የነፍስ አባታቸው ከያዙት መፅሀፍ አንዱን አውጥተው ማንበብ ሲጀምሩ ሲሉ ፣

« ለሱ ጊዜ የለኝም ፤ በጥሞና ያዳምጡኝ :: ይህ ሰውዬ ተጫወተብኝ :: ለእኔ የሚቆም ዘመድ አዝማድ የለኝም :: ሀብቴን ሙጥጥ አድርጎ እራቁቴን ሊያስቀረኝ ነው :: ምን ላድርግ ብዬ ላማክርዎት ነው ያስጠራሁዎት » በማለት ዕንባቸውን በአንሶላቸው ጫፍ እየጠራረጉ ወደ ነፍስ አባታቸው አስተዋሉ ::

« ይህማ ምን ንስሀ አለው :: እግዚአብሄር በመገላገያው ይገላግልሽ እንጂ :: ምን አድርግ ትይኛለሽ ? በማያገባኝ ነገር ገብቼ ነፍሴን ልሸጥ ? » በማለት ወደ መፅሀፋቸው እንደገና በማትኮር ትንሽ አመነቱ ::

« የእህትሽ ልጅ እዚህ አለች ማለትን እለማለሁ :: እሷን ጠርተሽ ለምን አታማክሪያትም ? » አሉና መልሰው መጽሐፋቸውን

ማንበብ ጀመሩ :: ወ/ሮ አባይነሽ መኝታቸው ላይ በጭንቀት እየተገላበጡ ያስባሉ ::

« ከዚህ ሰው ነፍሴን ሳያጠፋ የሚያላቅቀኝ ቢገኝ የዘላለም ቤቱን የሠራ ነው :: ቀደም ብሎ በሞኝነቴ ያራቅኳቸው ዘመዶቼ አጠገቤ ቢኖሩ ኖሮ አሁን ለዚህ ሁሉ ውርደት ባልተዳረግኩም ነበር :: ምንም ያህል ሕሊና ብትሆን በላይዋ ላይ የፈፀምኩት በደል ኃያል ስለሆነ ይቅር የምትለኝ አትሆንም :: አፌን ከማበላሸት እራሴ ያመጣሁትን መከራ እራሴ ብወጣው ይሻለኛል » በማለት በዝምታ አሰላሰሉ :: በጭንቅ ቀን የዘመድ አስፈላጊነት ከቁሉ ምክር ጋር ልባቸው ውስጥ ገባ :: « ምህረቱን ያውርድልሽ ! » አሉ የነፍስ አባታቸው ከተቀመጡበት እየተነሱ ::

*   *   *

ያሬድ ከሕሊና ጋር ወደ ት/ቤት በመሄድ በመጀመሪያ የትምህርት ቀን ስለተፈጠረው ሁኔታ ለት/ቤቱ ዳይሬክተር አስረድቶ፣ የሕሊና ቡና ቤት መሥራት በሥራ እጦትና ከዕለት ጉርስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልጾ ፣ አሁንም እንደማንኛውም የት/ቤቱ ተማሪዎች ሥነ ሥርዓትን አክብራ እንደምትገኝ ቃል ገባና እርምት እንዲካሄድ አድርገው ወደ ክፍሏ እንደገና ተመልሳ እንድትገባ አደረገ:: ይህን ከማድረጉ በፊት ግን ሕሊናን በት/ቤቱ ውስጥ በዕለቱ የተፈጸመው ድርጊት ለእርሷ ብቻ እንደተፈጠረ ሳይሆን አጥፊና ሥነ ሥርዓትን የማይከተሉ ተማሪዎች ሁሉ የዚህ ዓይነቱ ቅጣት እንደሚፈፀምባቸው በማስረዳት እንደገና ተመልሳ ት/ቤት እንድትገባ አሳመናት ::

ሕሊና ከሣምንት በኋላ ተመልሳ ወደጠላችው ክፍል ስትገባ እየቀፈፋት ነበር :: ሆኖም ቀደም ሲል ሕሊናን ከክፍሉ እንድትወጣ ምክኒያት የነበሩት መምህር በፈፀሙት ስህተት ተፀፅተው እና

ተለውጠው ስታገኛቸው በፊት የነበራት መጥፎ ስሜት ተለወጠ ። እኚህ መምህር ይባስ ብለው የክፍል አለቃ ሆና እንድትመረጥ አደረጉ። በመጀመሪያ ምን እንድትሆን ወይም እንድትሰራ መመረጧ አልገባትም ነበረ ። ከቀን ብዛት ግን ነገሮችን ቶሎ የመቀበል ችሎታዋን አዳበረች ። በጋራም ሆነ በግል የሚሰጣትን ኃላፊነት ለመወጣት ቻለች ።

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በፌዝም ሆነ በቀልድ ከእሷ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አርመው አክብረው አሜን ብለው ተቀበሉ። የቤትና የክፍል ሥራ በመስራት ከክፍሏ ልቃ ተገኘች ።

ለዚህ ሁሉ ያበቃት ወደ ቤት በምትመለስበት ወቅት በቀኑ ሥራዋ ስላጋጠማት ችግር ሁሉ ከያሬድ ጋር በመወያየት የምታገኘው ምክር ነበር ። ሕሊና ከመጀመሪያ ጊዜ አንስቶ ከያሬድ ጋር ዓይን ለዓይን ሲተያዩ የምትመኘው የዚህ ዓይነቱን ግንኙነት ነበር። ከትምህርቷ መልስ የቤቱ ውስጥ ሥራውን ችላ ባትለውም አጋዥ እንዲሆኗት አንድ ጠና ያሉ የቤት ሠራተኛ በቀን ሥራ ደረጃ ተቀጥረውላታል ። ኑሮዋ በተማሪ ደረጃ የተደላደለ ቢሆንም አልፎ አልፎ ከትምህርት ዓለም ለማለናከል የሚመጡ ሀሳቦች አልጠፉም ። የሦስተኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቃ ወደ አራተኛ ክፍል ስትዛወር ስሜቷን ከሚጎዳ ፣ ባህሪዋን ከሚያሻክር ሁኔታ ጋር ነበር ።

አንድ ቀን ሕሊና ከት/ቤት ወደ ቤቷ ስትመለስ አንድ ነጭ 304 ፔጆ መኪና በምትሄድበት አቅጣጫ በዝግታ ይከታተላት ኖሮ አጠገቧ እንደደረሰ ጥሩንባ ያሰማል ። እንዲህ ዓይነት መኪና ያለው ሰው ከዚህ ቀደም አነጋግሯት ስለማያውቅ ፊቷን ሳታዞር መንገዷን ቀጠለች ። የመኪናው ጥሩምባ ያለማቋረጥ ከኋላዋ ጮኸባት ። ሕሊና ግን በዝምታ አሳለፈችው ። ከመኪናው ውስጥ በስተግራ በኩል አንድ ፊቱን በውል ለመለየት ያልቻለችው ሰው በመስኮት በኩል እጁን ወጣ አድርጎ የጥሪ ምልክት አሳያት ።

ባለችበት ቆም ብላ ለጥቂት ጊዜያት አሰተዋለች ። መልስ ሳትሰጥ መንገድዋን ቀጠለች ።

ነጯ መኪና ከቆመችበት ቦታ ተንቀሳቅሳ ወዲያው ተከተለቻት። አሁንም ጥሩምባ ተሰማ ። መኪናው በድጋሚ አጠገቧ እንደደረሰ በመኪናው ውስጥ የተቀመጠው ሰው « ሕሊና አንችን እኮ ነው ! » በማለት በጎርናና ድምፅ ጠራት ። ስሟን ስትሰማ ዞር አለች። ለአንድ አፍታ የጠራትን ሰው ፊት በተከፈተው የመኪና መስኮት አስተዋለችው ። የሰውዬውን ማንነት ለመለየት አልቻለችም። ፊቷን መልሳ ወደ ፊትለፊቷ ፈረጠጠች ። ከሚከተላት ሰው መራቋንና እሱም መመለሱን እንዳወቀች ሩጫዋን አብርዳ ልቧን በቀኝ እጇ ይዛ ስለሰውየው ለማስታወስ ሞከረች ። መልኩ አዲስ አለመሆኑ ገብቷታል ። ግን ልታውቀው አልቻለችም ። ቤቷ እስክትደርስ የዚህን ሰው ማንነት ለማወቅ አዕምሮዋን በማስጨነቅ ብዙ አሰበች ። ወደቤት ስትገባ ያሬድ ከሥራ ተመልሶ ምሳ በመብላት ላይ ነበር ። ቀና አለና ፣

« ደህና ዋልሽ ? » በማለት በፈገግታ ተቀበላት ። አፀፋውን መልሳ ደብተሯን አስቀመጠች ። ያሬድ ፊት ያለውን ወንበር ስባ አረፍ አለች ። ፊቷን በሁለት እጆችዋ መሀል በማድረግ ፣ « እፎይ!» ስትል በረጅሙ ተነፈሰች ።

« ምነው ዛሬ ደግሞ ስፖርት በመጨረሻ ፔሬድ ያሰሯችሁ ጀመር እንዴ ? » ሲል ጠየቃት ። « ስላላበኝ ነው ። ዛሬ ደግሞ የሆንኩትን ብነግርህ ትገረማለህ » ስትል ጀመረች ። አዲስ ነገር ለመስማት በመጓጓት ያሬድ ባለበት ተቁነጠነጠ ።

« ደግሞ ምን ተፈጠረ » ሲል ጠየቃት ።

« ነጭ መኪና ያለው ጓደኛ አለህ እንዴ ? ማለቴ እዚህ ከተማ ነጭ መኪና ያለው ሰው ታውቃለህ ? » በማለት አትኩራ ተመለከተችው ። በዝምታ አንገቱን በአሉታ ነቀነቀ ።

« አሁን ከት/ቤት ስመለስ መንገድ ላይ መኪናውን አቁሞ ወርዶ ወደ እኔ ሲመጣ እሮጬ አመለጥኩኝ »

« ስመሆኑ ምን ዓይነት ሰው ነው ? »

« ወፍራም ፣ ቀላ ያለ ፣ ነጭ ኮፍያ ያደረገ ። እኔ እንኳን መኪና ውስጥ እንዳለ ነው ያየሁት ። ወርዶ በሩን ሲዘጋ እኔም ዞር ሳልል ሩጫዬን ተያያዝኩት ። »

« ለምን አታነጋግሪውም ነበር ? ለክፉ አይሆን ይሆናል ። »

« ከእኔ ጋር ምን አገናኘው ? ባለፈው ጊዜ ብዙ የከተማው ሊስትሮዎች ሥም ሳይጠቅሱ እዚህ ቦታ በዚህ ሰዓት ሰው ይፈልግሻል እያሉ ሲያስቸግሩኝ ነበር ። አሁን ደግሞ ባለመኪና መጣልኛ » በማለት ፈገግ ብላ ያሬድን አስተዋለችው ። « ሌላ ጊዜ ይህ ሰው ቢጠራሽ የሚፈልገውን ነገር እስከሚነግርሽ እንዳትሸሽ ። መቼም ቀን በቀን በሀገር አማን አይሰርቅሽ » አላት ያሬድ የሰውየውን ማንነት ለማወቅ በሚፈልግ አስተያየት እያስተዋላት ። ከት ብላ ሳቀችና ፣

« እኔን ሰርቆ ምን ያደርግለታል ? » በማለት የዋህ አነጋገሯን ጣል አደረገች ።

« በይ አሁን ልብስሽን እውልቂና መክሰስ በልተሽ ወደ ጥናትሽ » አለና ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ ። አልጋው ላይ ተጋድሞ ቴፕ ከፍቶ በስሜት ተዋጠ ።

ሕሊና « እኔን ሰርቆ ምን ያደርግለታል » ነበር ያለችው ። ቃሉን እየደጋገመ አኘከው ። ሀሳቡን እያወጣ እያወረደ አብሰለሰለው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሕሊናን በማዘን ፣ በማገዝና በመርዳት ልቡና እንጂ በሌላ መልኩ አይቷት አያውቅም ነበር ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የሕሊናን እንድ ገጽታ ባየ ቁጥር ልዩ ጭንቀት ሰውነቱን እየወረረው መምጣት ጀምሯል ። ሕሊናን በሌላ መልክ ላለማሰብ

ራሱን ደጋግሞ ለማሳመን ቢሞክርም ደመነፍሱን እስከመጨረሻ ማሳመን አልቻለም ።

« ግን ሰውየውን ለምን አነጋግሪው አልኳት ? » ሲል እራሱን ጠየቀ ።

* * *

ሕሊና ከት/ቤት ስትወጣ ከመንገድ ላይ ቆሞ የሚጠብቃትን ነጭ ፔጆ መኪና ከሩቅ አስተዋለች ። መንገዷን አሳብራ በሌላ በኩል ለመሄድ አሰበችና ያሬድ የተናገራት ትዝ አላት ። መለስ ብላ መንገዷን አቅንታ ወደ መኪናው ተጠጋች ።

« ነይ ግቢ » ብሎ ቢያስገድደኝ « አልገባም ፣ በመኪና መሄድ አስመደብኝም እለዋለሁ ። የሚጠይቀኝ ጥያቄ ካለ እንደዚሁ ያለመኪና ቢጠይቀኝ እንደሚሻል እነግረዋለሁ ። እንቢ ብሎ ሰማስገደድ ቢያስብ በድንጋይ መኪናውን አመድ አደርግለታለሁ » እያለች ከራስዋ ጋር እየተማከረች መኪናው አጠገብ ደረሰች ። የተለመደው የመኪናው ጥሩምባ ፓም . . . ፓም . . . የሚል ድምፅ እንዳሰማ ሕሊና ዘወር ብላ ተመለከተች ። ያየችው ባለኮፍያውን ሳይሆን ኮፍያ የሌለው ከራሱ ገባ ያለ ሰው ነበር ። ሕሊና መልኩን ስታይ ወዲያውኑ አስታወሰችው ።

የመኪናው ባለቤት እጁን በመስኮት ወጣ አድርጎ ሕሊናን በምልክት ሲጠራት ካለችበት አልተነቀሳቀሰችም ። ከመኪና ወጥቶ ወደ እሷ ቀስ እያለ ተጠጋት ።

« እረሳሽኝ እንዴ ሕሊና ? እንተዋወቃለን እኮ » አላት በፈገግታ እያስተዋላት ።

« መርሳት አልረሳሁም ፤ ሆኖም ለምን ነበር የሚፈልጉኝ ? እቸኩላለሁ » ብላ መንገዷን መቀጠል ጀመረች ።

« አብዬ ጋሻዬ እኮ ነኝ አባይነሽ ቤት አታስታውሺኝም ? » አሏት ከኋላዋ እየተከተሏት ::

« ገብቶኛል ፤ ሆኖም ለምን ይፈልጉኛል ? » በማለት በፍርሀት ዓይነት ከላይ እስከታች ሰውየውን በዓይኗ ፈተሸቻቸው ::

« ልጋብዝሽ ነው የምፈልግሽ ? » በማለት በጥያቄ አመለካከት ዓይን ዓይኗን አስተዋሏት ::

« ግብዣ » የሚለው ቃል የቡና ቤት ትዝታዋ አንደኛው ገፅታ ነው :: ቃሉ እየዘገነናት እርምጃዋን ቀጠለች :: አብዬ ጋሻዬ በግዙፍ ሰውነታቸው መንገዱን ዘግተው ያዙባት :: ሕሊና ቀጥላ ምን ማድረግ እንዳለባት ስታሰላስል ከማታውቀው አቅጣጫ የሆነ ጎይሰቃል ተወረወረ ::

« ልቀቃት ትሂድ ! እኩያህ አይደለችም ! ቀላል ! . . . » የሚል ንግግር ተሰማት :: ቀና ስትል ያሬድና አብዬ ጋሻዬ ፊትለፊት ተፋጠዋል :: አብዬ ጋሻዬ የዘጉትን መንገድ ለቀቅ አደረጉ ::

« ለመሆኑ አንተ ማነህ ? » በማለት ያሬድን ጠየቁት ::

« መንገደኛ ነኝ ፤ ከዚህ በላይ ስለእኔ ባታውቅ ይሻልሃል :: ለማንኛውም ከዛሬ ጀምሮ ይህችን ልጅ አነጋግራለሁ ወይም መንገድ ላይ እከተላለሁ ብትል ኋላ በሰው እንዳታዝን :: ይኼ የመጨረሻ ቃሌ ነው :: በተረፈ የሠላም መንገድ ያድርግልህ » አላቸውና ባሉበት ትቶአቸው ፣ ሕሊናን አስከትሎ ወደፊት ገሰገሰ :: ቤት እንደገቡ « ሕሊና ተቀመጭ የምንነጋገረው ነገር አለ » አላት :: በፍርሃት ተውጣ አጠገቡ ተቀመጠች ::

« ይህን ሰው የት ነው የምታውቂው ? »

« የማውቃቸው . . . የማውቃቸው ቀደም ሲል እቴቴ ጋ እያለሁ ነው » አለችው ::

« አነጋግሮሽ ያውቃል ? ማለቴ ከዚህ ቀደም . . . »

« የእቴቴ ወዳጅ ነበሩ :: አንድ ቀን ብቻ ነው ያየኋቸው ::»

« ታዲያ ምን ይልሽ ነበር ያኔ ? »

« ምንም » አለች ::

« ታዲያ እንደዚሁ ከምድር ተነስቶ ይከተልሻል እንዴ ? ለመሆኑ ዛሬ ምን ነበር ያለሽ ? » ሲል ጠየቃት በቅናት ዓይነት ::

« ልጋብዝሽ ነው ያሉኝ »

« ልጋብዝሽ ? እንዲሁ ዝም ብሉ ? ይህ የማይመስል ወሬ ነው » አላት :: ሕሊና የተናገረችው ውሸቷን መሰለው :: አላመናትም :: ጥርጣሬና ቅናት በአንደበቱ ውስጥ ተድበሰበሰ :: ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደመኝታ ቤቱ ገባ :: ያለልማዱ ልብሱን አወላልቆ ተጠቅልሎ ተኛ :: በአእምሮው ቁርጡ ያለየለት ፣ እንደ ደመና እየተነኑ የሚያስጨንቁ የተለያዩ ሀሳቦች ተፈጠሩ ::

የተፈጠረው ሁኔታ ሕሊናንም አስጨንቋት ቆየ :: በተለይ ፈልጋው ባይሆንም በሷ ምክንያት ያሬድ እንዲከፋ አትፈልግም ነበር:: ብዙ ነገር ስታወጣ ስታወርድ ከቆየች በኋላ ቢያንስ ያሬድን እራት ማብላት እንዳለባት ወሰነችና የመኝታ በሩን አንኳኳች ::

« ጋሼ ያሬድ ራት እንብላ » ስትል በፍርሀት ድምጿን አሰማች ::

« አሞኛል አልበላም አንቺ ብይ » አላት ፤ በብርድልብሱ ውስጥ እንደተጠቀለለ :: ከዚህ በላይ ልትረብሸው አልፈለገችም :: ደስተኛም አልነበረችም :: እሷም እራቷን ሳትበላ በሯን ዘግታ ልብስዋን አወላልቃ ተኛች ::

ዕንቅልፍ አልነበራትም :: የያሬድ ማኩረፍና በእሷ ላይ ያለው ጥርጣሬ ምስጢር ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረች ::

ያሬድ ለሕሊና ያለው እምነት እየመነመነ መጣ :: ፊቷን ለማየት ያለው ፍላጎት ከድሮው እየቀነሰና ውጪ ማምሸት እያዘወተረ ሄደ :: በቤቱ ውስጥ ቀደም ሲል የነበረው የትብብር መንፈስ ተሰወጠ:: ቁጣና ትዕዛዝ ለያሬድ አዲስ ፀባይ ሆነ :: የዚህ ዓይነቱ

የመኮራረፍ ግማሽ ኑሮ በመካከላቸው ለአንድ ሳምንት ያህል ሰፍኖ ቆየ ። ሆኖም ያሬድ በዚህ ሁኔታ መቀጠሉ የትም እንደማያደርሰው ተገነዘበ ። ራሱን ለመለወጥ ፤ አቀራረቡን ለማሻሻል ወሰነ ።

አንድ ቀን ከስራ መልስ በጊዜ ወደቤቱ ገባ ። ሕሊና እራሷን በሁለት እጆችዋ መሀከል አድርጋ የምታጠና መስላ ጠረጴዛ ላይ ተደፍታ ነበር ። ያሬድ ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ተነስታ ወደጓዳ አመራች።

« ሕሊና ተቀመጪ እንጂ ፤ ሰው ሲመጣ ወዴት ሽሽት ነው። ደግሞ ዛሬ ካንቺ ጋር መጫወት እፈልጋለሁ » አላት በፈገግታ።

« ከሥራ አይደለም የምትመጣው ? » ስትል ወደ ኩሽና ሄደች ። የያሬድ መለወጥ ልትገልፀው የማትችለው ልዩ ተዓምር ነበር የሆነባት ። ያሬድ ወደ መኝታ ክፍሉ ገብቶ ፣ የለበሰውን ልብስ አወላልቆ ፣ የቤት ውስጥ የስፖርት ቱታውን ለብሶ ሕሊና የምታዘጋጀውን ጨርሳ ወደ ሳሎን ስትገባ እሱም አብሮ ገባ ።

« ትምህርቱ እንዴት ይዞሻል ? ለፈተና ተዘጋጀሽ ? » አላት የሻዩን ማንኪያ እያወዛወዘ ።

« ደህና ነው ። ለፈተና የቀረን ሁለት ሳምንት ስለሆነ ለዝግጅቱ እደርሳለሁ »

« ትምህርቱን እንኳን እተማመናለሁ በደንብ እንደምታጠኚ ብቻ . . . ብሎ ያሰበውን ሳይጨርስ አቆመ ።

« ለምን ብቻ ብለህ ታቆማለህ ጋሼ ያሬድ ተናገር እንጂ ! ምንድነው ውስጥህ ያለው ነገር ? » ስትል ጭንቅላቷን በቅሬታ አወዛወዘች ።

« ተይው ሕሊና . . . ምን ያደርጋል . . . የኔው ሞኝነት ነው . . . በቃ ፣ በቃ ስለአለፈው አናውራ . . . » አላት ።

« ለምን ጀምረህ ትተወዋለህ ? ስሞኙን የሆንኩትን እኔና አንድ አምላክ ብቻ ነን የምናውቀው ። . . . » አለችው በመለማመጥ መንፈስ ። ዓይኖችዋ እንባ አግተዋል ። ፊቷ መቅላት ጀምሯል ።

ያሬድ ድንገት ጥንካሬው ከላዩ ላይ እንደጥላ ሲሸሸው ተሰማው ። ከሕሊና ጋር ፍቅር አስቦ የነበረው ስሜቱ ያሳበቀበት መሰለው ። እርግጠኛ ስለመሆኑ ራሱን ተጠራጠረ ።

የቤቱን ጣሪያ በዓይኖቹ እየዳሰሰ « ሕሊና ለሁሉም ነገር መነሻ አለው ። ለእኔም መነሻ አለኝ ። ከዚያ ሰው ጋር ያደረጋችሁት ንግግር ሆዴን አሻክሮታል ።

ሕሊና እኔ ላንቺ የምመኘው ጥሩ ህይወት ነው ። ተምረሽ እራስሽን እንድትችይ ፣ ያለአንዳች ተፅእኖ ሁሉንም ነገር በራስሽ ፈቃድ መስራት እንዳይሳንሽ እፈልጋለሁ ። ለዚህ ደግሞ ባለኝ አቅም የምችለውን ሁሉ አደርግልሻለሁ የሚል እምነት ነበረኝ ። ሆኖም ከሰውዬው ጋር የነበረሽ ግንኙነት ተስፋዬን ሁሉ አጨለመው ። መጥፎ ስሜት አሳደረብኝ ። እየሽ ሕሊና . . . ቡና ቤት ያውቃት ይሆናል ብዬ መጠራጠር ጀመርኩ ። ቢሆንም አትፍረጂብኝ . . . » አለና ዝም አለ ።

ሕሊና ያሬድ ተናግሮ ሳይጨርስ ከት ብላ ከልቧ ሳቀች ። እሱም ግራ በመጋባትና ሀፍረት በተቀላቀለበት ስሜት ወደ ሕሊና እያስተዋለ « ምነው ! ምን ያስቅሻል ? . . . እውነቱን እኮ ነው ፣ ያስቃል እንዴ ? » አለና ፊትለፊቱ ቀዝቅዞ ያበቃለትን ሻይ አነሳ ።

*　*　*

ወ/ሮ አባይነሽ በሥማቸው አንድ አርጌ ቶዮታ ፒክአፕ መኪና በደላላ አስገዝተው በሾፌር እንድትነዳና በፈሩቅ ትዕዛዝ ሥር እንድትውል አደረጉ ። እቅዳቸው ለጥቂት ጊዜያት አይስራ እንጂ ውሎ አድሮ በድርጊት መፈጸሙ አልቀረም ። ፈሩቅ ባጭር ጊዜ የመንጃ ፈቃድ አወጣ ። የመጀመሪያ ዕቅድ መኪናው፣ ራሱ መያዝ ነበር ።

ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር በውሃ ቀጠነ ንትርክ አበዛ ። ቆይቶ መኪናውን እራሱ መያዝ እንዳለበት አፍ አውጥቶ ተናገረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ጥያቄ ሊቀርብላቸው እንደሚችል ያውቁ ነበር ፤ ይፈልጉም ነበር ። መኪናው እንዲገዛ ሲያደርጉም ለዚሁ ብለው ነበር። የፈሩቅን ባህሪ በውል አውቀውታል ። ከስራቸው ለማራቅ ባሰቡ ቁጥር መኪና መግዛት ነበረ የታያቸው ። ግን ያሰቡት ቢሳካም፣ ሊያስጠረጥሩ አልፈለጉም ። ተቃወሙት ። ፈሩቅም ማሸነፉን ያውቅበታል ። ከመኪናውና ከምስጢራቸው የሚበጃቸውን እንዲመርጡ ቀጭን ቃል ተነፈሰላቸው ። ቀስ እያሉ መኪናውን ለቀቁለት ። ፈሩቅ ጊዜ አልፈጀም ። ህይወትን መኖር ጀመረ ። ህይወት ከከተማ ከተማ ጠራችው ። በመኪና ሄደላት ። ልዩልዩ ሰበቦች እየፈጠረ ፤ ወ/ሮ አባይነሽም ያመኑት እየመሰሉ ውጭ ውሉ ማደሩ ተለመደ ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ለወ/ሮ አባይነሽ የሚጠብቁትን መልካም አጋጣሚ ፈጠረላቸው ። እንደልብ ቡና ቤታቸውን ለመቆጣጠር ፣ የቆዩ ወዳጆቻቸውን ለማግኘት ፣ በሰላይነት ይጠቀሙባቸው የነበሩ ተላላኪዎቻቸውን ለማለማራት ዕድል ሰጣቸው ። እንደልብ ከቤት

ወጥተው ለመመለስ ፣ ቤተክርስቲያን ለመሳለም አመቻቸው ። አንድ ቀን ወ/ሮ አባይነሽ እንደልማዳቸው ቤተክርስቲያን ደርሰው ሲመለሱ እንደድንገት ከያሬድና ሕሊና ጋር በመንገድ ላይ ተላለፉ ። ወ/ሮ አባይነሽ ባዩት ነገር እርግጠኛ አልነበሩም ። ያሬድና ሕሊና ከዓይናቸው እስኪሰወሩ ባሉበት ቆመው ሸኙዋቸው ።

« እሷ ነች አይደለችም ? » አሉ በሀሳብ ከሄዱበት ሲመለሱ። አልተሳሳትኩም እሷው ነች ። » በማለት ለራሳቸው አረጋገጡ ። ቤታቸው እንደገቡ ሰለሞንን ትልቁ ቤት አስጠሩት ። ካለበት ተፈልጎ በጓሮ በር ወደ ሳሎን እንደገባ ፤

« ሰለሞን ስንተኛ ክፍል ደረስክ ? » ሲሉ ጠየቁት ።

ፈገግ ብሎ « አሁን የአስረኛ ክፍል ፈተና ወስጃለሁ ። ለከርሞ ፈተናውን ካለፍኩ አስራአንደኛ ክፍል እገባለሁ » አለ አንገቱን አቀርቅሮ ።

« ጎሽ ! ጎሽ ! ልጄ ጎበዝ » በማለት ጥቂት ከአሰላሰሉ በኋላ « ለመሆኑ ሕሊናን አይተሃት ታውቃለህ ? » አሉት ።

እያቅማማ « እ . . . እ . . . እ . . ሕሊናን ካየኋት . . ብዙ ጊዜ ሆኖኛል » መቼ እንዳያት እያሰላሰለ መለሰ ።

« ዛሬ መንገድ ላይ ያየሁዋት መሰለኝ ። አንድ ወንድ አብሮአት አለ » አሉ ።

« ምን ዓይነት ወንድ ነው ? » አላቸው በጥርጣሬ ዓይነት ።

« መልከ መልካም ወጣት ነው ፤ እረዘም ያለ ፣ ምነው የምታውቀው ነገር አለ እንዴ ? » በማለት ወደ ሰለሞን ተመለከቱ ።

« አዎ አሁን የሚሉት ጋሼ ያሬድን ነው ። ከእሱ ጋር ነው የምትኖረው » አላቸው እንደተራ ነገር ። « እህህ . . . ህ . . ም . . ም . . » በማለት እየተገረሙ ፣ « ሰው እንደዚህ ይለወጣል ? » በማለት እራሳቸውን ጠየቁ ።

« በትምህርት ቤቱ የታወቀች ተማሪ ሆናለች ። ባለፈው ጊዜ ለወላጆች ቀን ከጎበዝ ተማሪዎች አንዷ በመሆን ሽልማት ተቀብላለች። አሁንማ ሒሊና የአምስተኛ ክፍል ተማሪ እኮ ነች ። » ሲል ሰለሞን የጀመረውን ንግግር ቀጠለ ።

« ሰለሞን አሁን የጠራኸው ማን አልከው ስሙን ? . . . አዎ ያሬድ . . . ነገ በምሳ ሰዓት ይዘኸው እንድትመጣ » አሉት ትዕዛዝ በመሰለ አቀራረብ ።

« እዬ . . . እህ . . . ሀ . . ሀ . . ጋሼ ያሬድ እንኳን እሺ የሚል አይመስለኝም ። እሱ እኛ ቡና ቤት ገብቶ አያውቃም ። እኔ እንጃ ብቻ እስኪ እነግረዋለሁ » አለ እርግጠኛ ባለመሆን ።

« ምን ማለትህ ነው ? ለምን አይመጣም ? ለማንኛውም አንተ የተባልከውን ፈፅም ። ይምጣ አይምጣ የአንተ ችግር አይደለም» አሉት ተቆጥተው ።

« እሺ እስኪ እንግዲህ መልዕክቱን አደርሳለሁ » አላቸው ።

« ታዲያ መልሱን መቼ ይዘህ ትመጣለህ ? »

« ዛሬ ማታ እሄዳለሁ ። » አለና እጅ ነስቶ ወጣ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ያሬድ እቤታቸው መጣ ማለት ከሒሊና ጋር የመታረቅ ዕድላቸው በእጃቸው የጨበጡትን ያህል ሆኖ ተሰማቸው ። ጨለማ ለብሶ የነበረው ተስፋቸው እንደገና እያንሰራራ መጣ ። የያሬድን መልስ በጉጉት ነበር የሚጠብቁት ። ከሒሊና ጋር ታረቁ ማለት በፊሩቅ የተገፈፉትን ነፃነታቸውን በቀላሉ ማስመለስ እንደሚችሉ እርግጠኛ ነበሩ ። እስከዚያው ሁሉም ነገር በምስጢር መከናውን አሰበት ። ለእቅዳቸው መሳካት ያመች ዘንድ ካብትሽን ጠሯት ። ሦስት አራት ጊዜ እጅ በመንሳት ወደ ሳሎን የገባችው ካብትሽ ታማኝነቷን በህይወት ዘመናቸው ብተደጋጋሚ ያዩት ስለሆነ አልጠረጠሯትም ።

« ካብትሽ ሂጂና አባን ጥሪልኝ ። በጣም እፈልግዎታለሁ ። ሌላም ሥራ ቢኖርዎት ለአንድ አፍታ ብቅ ይበሉ በይልኝ » በማለት አዘዟት ።

« እሺ እሜትዬ » በማለት ካብትሽ እጅ ነስታ ወደተላከችበት ሄደች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ወደ ጓዳ ገብተው የቤት ልብሳቸውን ቀይረው ወደ ሳሎን ተመለሱ ። ፊሩቅ ከቤት ከወጣ አራተኛ ቀኑን ይዟል ። ሲወጣ ብርቱካን ለማምጣት ወደ ዲላ እንደሚሄድ ቢነግራቸውም ከወሰደው የገንዘብ መጠን አኳያ በቅርቡ እንደማይመለስ ገምተዋል ። ሳሎን ተቀምጠው ቡና እያስፈሉ ቁርሳቸውን እየበሉ እንዳሉ የነፍስ አባታቸው በጓሮ በር ገቡ ። ያልታጠቡትን እጃቸውን ወደኋላቸው እንደመደበቅ አደረጉና ከመቀመጫቸው ተነስተው « ይግቡ አባ » ከማለታቸው ፤ አባ ከጋቢያቸው ውስጥ በኪሳቸው የያዙትን መስቀል በቀኝ እጃቸው ወጣ አድርገው በሹክሹክታ የማይሰማ አባባላቸውን አነበነቡና አሳልመው « እግዚአብሔር ይፍታ » አሉ ።

« የእጅ ውሃ አምጡ ፤ አባ ወዲህ ይቅረቡ ቁርስ እናድርግ ። ገና አሁን መግባቴ ነው » አሉአቸው ።

አባ ወደገበታው ጠጋ ብለው በተጋበዙበት ወንበር ላይ ተቀምጠው « በስመአብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ » በማለት እጃቸውን ታጥበው መብላት ጀመሩ ። ፊት ለፊታቸው የተቀመጡት ወ/ሮ አባይነሽ « ቡናውን ቶሎ ቶሎ በሉ » በማለት ትዕዛዝ ሰጥተው መመገቡን ተያያዙት ። ወደ ዋናው ውይይት ሳይገቡ በአጠቃላይ ሁኔታ ላይ ሲጨዋወቱ ቆይተው ማዕድ ሊነሳ ሲል የነፍስ አባታቸው ተነሱና የገበታ ማሳረጊያ ፀሎታቸውን አሰሙ ። በክፍሉ ውስጥ የሦስተኛ ሰው መኖርን ያልፈለጉት ወ/ሮ አባይነሽ ቡና ተፈልቶ እስካለቀ ድረስ ዋናውን ቁም ነገር አልጀመሩም ነበር ።

« በይ እንግዲህ አንቺ ሂጅና ማዕድቤት ሥራ አግዥ » አሉና አሰናበቷት ምስጢር እንዳይባክን በመስጋት ። ነፃ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ፣ « አባ አሁን የጠራሁዎት ከዚህ ቀደም ስላነሳነው ጉዳይ እንደገና ላማክርዎት ነው » አሉ ።

አባም ዓይናቸውን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ በማተኮር ግራ እንደተጋቡ ሁሉ « የትኛው ጉዳይ ? . . . በይ እንጂ » አሉ ፊታቸውን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ አስጠግተው ።

ወ/ሮ አባይነሽ የነጠላቸውን ጫፍ በእጃቸው ያዝ አድርገው እንደመቋጨት እያፍተለተሉ « አባ መቼም ሰው ሆኖ ኖሮ ኖሮ መሞቱ አይቀርም ። ሞት ቀጠሮ አይሰጥም ። ሰው እኖራለሁ ይላል፤ ሆኖም እግዚአብሄር ሲጠራ አስቀድሞ መልዕክተኛ አይልክም። የእኔ ህይወት እንደምታውቁት መና ሆኖ ቀርቷል ። ይህን የለፋሁበትን ሀብቴን ለማንም በትኜ ብሞት እስከፊ ሞት ሞተች ይባላል ። ከፋም ለማም ያለችኝ የሥጋ ዘመዴ የእህቴ ልጅ ብቻ ነበረች ። ምንም ቢሆን ብሞት ተዝካሬን እንኳ በሚገባ ልታወጣ ትችል ነበር ። ይኸው አብሮኝ ያለውም ሰው የእኔን ሞት ከዛሬ ነገ እየጠበቀ ነው ። ስለዚህ ይቅር ብለውኝ ከእህቴ ልጅ ጋራ እንዲያስታርቁኝ ነው የምፈልገው » አሏቸው ።

« ይኸውልሽ ልጄ ፤ ከሥጋ ኖረው ሞት አይቀርም ። እንዳልሽው የማይሞተው ነፍስ ብቻ ነው ። ይሄን ካሰብሽ መልካም ነው ። እግዚአብሔር መንገዱን መርቶሻል ። ታዲያ እርቁን እውነተኛ እርቅ ለማድረግ ሊያሸንፉ የሚችሉ ሽማግሌዎች ልሰብሰብና አብረን ሄደን እንማፀናታለን » ሲሉ የነፍስ አባታቸው የሌላ ሰው መኖር አስፈላጊ መሆኑን ተናገሩ ።

« የለም . . . የለም . . . ሽማግሌማ አያስፈልግም ። ሰው ሳይሰማ ተቀራርበን ሁለታችን ይቅር ለእግዜር መባባሉ ነው

የሚሻለው ። ለዚህ ደግሞ የእርስዎ ሽምግልና ይበቃል ። ወሬ ማባዛት ምን ያደርጋል ? » አሉ እጃቸውን እያወናጨፉ ።

« ይህማ ደንብም አይደል ። ሰው መኖሩ ደግ ነው ። ድንገት አሻፈረኝ ብትል እንኳ ከብዙዎቹ አንድ የሚያሸንፉት ይገኛል ፤ የሰው ብዛት አይከፋም » አሏቸው ።

« አባ ይህማ እንደው አጉል ይሆናል ። ይልቁንስ ነገ ለምሳ አብሮአት ያለውን ሰው እዚህ ድረስ ቀጥሬዋለሁ ። እርስዎም ተገኝተው ከእሱ ጋራ ብንነጋገር የእርቁን ነገር ማዘጋጀት ይቻላል » አሉ ።

« እንግዲህ በይ እንዳልሽ . . . መስሎኝ ነው » አሉ አባ ።

*   *   *

ሒሊና ማዕድቤት ገብታ እራት ስታዘጋጅ እጠገብዋ ዕቃ እየነካካ የሚያስቸግራት ኩቻን « አንተ መቼም ያለማጥፋት ሥራ የለህ ። አታስቀምጥም አሁን ! መጣሁብህ ! » እያለች ስትናገር ሮጦ ከማዕድቤት ወጥቶ ሜዳ ላይ ቆመ ። ኩቻን ተከትላ በር ላይ ቆማ ፣

« አታመጣም አሁን » ብላ በግሳፄ ዓይን ተመለከተችው ። እሱም እሷን እያየ « አልሰብረውም እኮ » አላት ።

« ምን ልታደርግበት ነው ? እጅህን ትቆርጣለህ ፣ አምጣ ነው የምልህ ! » በማለት ወደ ኩቻ ራመድ ስትል ኩቻ ተፈተለከ ። ሒሊናም እልህ ያዛትና ተከትላው ሮጠች ። መሀል መንገድ ላይ ስትደርስ የሆነ ነገር ባለችበት ገትሮ አስቀራት የምታውቀው የሚመስላት አፍሮ ጠይም ልጅ ተመለከተች ። በእርግጥም ታውቀው ኖሯል ። « ሰለሞን ከየት መጣህ ? » አለችውና ይዛው ወደ ቤት ገባች ።

« ጋሼ ያሬድ የለም እንዴ ? » ሲል ተናገረ ሰለሞን ። ያሬድ ጆሮውን ተክሎ ያዳምጥ ስለነበረ ከመኝታ ቤት « ማነው ? ሕሊና » ሲል ተጣራ ።

« እኔ ሰለሞን ነኝ ጋሼ ያሬድ » ሲል መለሰለት ።

« ሰለሞን ነህ ?ደህና ነህ ? ምነው በምሽት ምን አጋጠመህ?» በማለት በበሩ በኩል ብቅ አለ ።

« ፈልጌህ ነበር ጋሼ ያሬድ » አለ ሰለሞን ። ሕሊና ነፃነት ልትሰጣቸው ስለፈለገች በጓዳ በር በኩል ወጣች ።

« ምን አስቸኳይ ጉዳይ አጋጠመህ ? ደህናም አይደለህ ? » ሲል ያሬድ ሰለሞንን ጠየቀው ።

« ደህናስ ደህና ነኝ . . . እንዲያው » እያለ ነገሩን ለመናገር በማመንታት ትንሽ አቅማማ ። « እማማ አባይነሽ ወደ አንተ ጋ ልከውኝ ነው የመጣሁት » አለ ። ያሬድ የሰማውን ባለማመን ፤

« አባይነሽ ? አባይነሽ የሕሊና አክስት ? » ሲል በማረጋገጥ ዓይነት ጠየቀው ።

« አዎ የሕሊና አክስት ። መቼም አዲስ ነገር ነው ። ይኸውልህ ዛሬ አስጠርተው ነገ ለምሳ እንዲመጣ ንገረው አሉኝ ። እኔ እንኳን ዝም ብዬ አልመጣም አለኝ ልላቸው ነበር ። በኋላ በሌላ ሰው አስጠይቀው ደግሞ ቢታወቅ ብዬ ነው የመጣሁት » አለ ሰለሞን።

« ምን ፍጠር ነው የሚሉኝ ደግሞ ? » ሲል ግራ በተጋባ ሁኔታ ጠየቀው ።

« እኔ እንጃ ግን በጣም ነው የሚፈልጉህ »

« ለሠላም ነው ለፀብ ? እንዲህ አጣዳፊ የሆነ ጥሪ ። በእርግጥ ያሬድ ብለው ነው የነገሩህ ? » በጥርጣሬ ዓይነት ጠየቀ ።

አዎ ያሬድ ብለው ነው ። ጠዋት ከሕሊና ጋራ ስትሄዱ አይተዋችሁ ነበር ። ከቤተክርስቲያን መልስ እንደመጡ አስጠርተው

ሕሊናን አይቻት አውቅ እንደሆን ጠየቁኝ ። እኔም እንደልማዳቸው አስናቀን ስደባት ብለው እንደሚልኩት ሁሉ እኔንም ሊልኩኝ ነው ብዬ አውቄ ብዙ ጊዜዬ ነው ካየኋት አልኳቸው ። በኋላማ ዕንባ እየተናነቃቸው አንተን እንድጠራህ የመለመን ያህል ነበር የነገሩኝ » አለ ሰለሞን ።

« ለመሆኑ ጥሪው በስንት ሰዓት ነው ? » ሲል ጠየቀው ።

« የተወሰነ ጊዜ እንኳን አልተናገሩም ። ሆኖም በምሳ ሰዓት ማለታቸውን አውቃለሁ ። » በማለት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ « እየመሸ ነው ፤ ጋሼ ያሬድ ልሂድ » አለ ። ያሬድም እተቀመጠበት ቦታ ሆኖ « ሕሊና . . . ሕሊና . . . » ሲል ተጣራና መልስ ሲያገኝ « ሰለሞን ደህና እደሪ ይልሻል » አላት ። ሕሊና ከማዕድቤት ተጣድፋ ወጣችና « ምነው ሰለሞን አትጫወትም ? ሥራ ይገፔ ነው እኮ ያላጫወትኩህ » አለችው ።

« የለም መሽቷል ፤ ሌላ ጊዜ መጥቼ እጫወታለሁ » ብሎ ያሬድን ጨብጦ ወደ በሩ አመራ ።

« በል እናትህን ሠላም በልልኝ ፤ ሌሎቹንም በሙሉ » ስትል ተሰናበተችው ።

« በል እንግዲህ እንዳትረሳ ! እሞክራለሁ ነው ያልኩህ ድንገት ሥራ ሊያጋጥመኝ ይችላል » አለው ያሬድም ።

እራት ቀርቧል ። ሕሊና የመጨረሻ ፈተናዋ ስለነበረው ስለ እጅሥራ ትምህርት ከባድነት ለያሬድ በማስረዳት ላይ ነበረች ። ያሬድም ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ጥሪ በማሰላሰል ላይ ስለነበር ምን እንዳለችው በቅጡ አላዳመጣትም ሕሊና ቀና ብላ ያሬድን ስታየው ሀሳብ ውስጥ መግባቱን ተመልክታ ብቻዋን የምታወራ እብድ የሆነች መሰላትና ደነገጠች ።

« ምነው ያሬድ አትበላም እንዴ ? » አለችው ሳይደነግጥ ከሄደበት እንዲመለስ አስባ ።

« እንደዛሬም ጠግቤ አላውቅ » አላት ፈገግ ብሎ « ባይገርምሽ ሀሳብ ውስጥ ገብቼ ብዙ ሳልበላ አልቀረሁም » ሲል አከለ ::

« ምን እያሰብክ ነው የምትበላው ? ወጡ አልጣፈጠህም እንዴ ? » ብላ ምላስዋን በማጣጣም ዓይነት ድምፅ እያሰማች የወጡን መጣፈጥ ሞከረችው ::

« ያንቺ እጅ የነካው ምን ይወጣለታል :: ወጡስ ይጣፍጣል:: ሀሳቡ ግን ወዲህ ነው » አላት :: « በል ነገሩን ብቻህን አትበላው ባይሆን አካፍለኝ » አለችው ::

« ሕሊና . . . አክስትሽ እኮ ለነገ ምሳ ጋበዙኝ :: » አላት እንደድንገት ::

« አልገባኝም ፤ የምን ምሳ ? ለምን ? » ብላ ጠየቀችው በድንጋጤ ::

« አይዞሽ አትደንግጪ. ሕሊና ለክፉ አሳልፌ አልሰጥሽም :: ለሰሞን የመጣው ይህንኑ ተልኮ ሊነግረኝ ነበር :: ነገር ግን የምሳውን ዓይነትና ለምን ? የሚለውን ጥያቄ ስሄድ አውቀዋለሁ :: » በማለት ፈገግ አለና መለሰላት :: « መሄድስ አትሄድም :: እሳቸው እንደሆኑ ለማንም አይመለሱም ድንገት . . . » በማለት የጀመረችውን ሳትጨርስ ሳግ አነቃት :: እንደምንም እንባዋን ተቆጣጥራ « እባክህ አልሄድም በለኝ ! ጋሼ ያሬድ አልሄድም በለኝ » ስትል የግድ ተነፈሰች ::

« ሕሊና ሕፃን አትሁኚ :: የሚሉትን ማወቁ አይከፋም :: ለማድረግ ያሰቡት ነገር ካለ መቼም ቢሆን ሊሆንላቸው አይችልም :: በዚህ ላይ ብቻዬን አልሄድም :: ከተሾመ ጋር ነው የምሄደው » በማለት የሕሊናን ዓይን በአንክሮ አስተዋለ ::

« እኔ ፈርቻለሁ አትሂድ ነው የምልህ ::አልሄድም በለኝ :: »

« ምን እሆናለሁ ብለሽ ነው ? እንዲያው ቀን በቀን ጠርተው

እያስደበድቡኝ :: ቢሆንም ደግሞ ተሾመ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች እያንዳንዳቸውን ያውቃቸዋል :: » በማለት ለማሳመን ሞከረ ::

« መርዝ ያበሉሃል :: እሳቸው ግድ የላቸውም ፤ ለሰው ነፍስ አይሳሱም :: በሆነ ነገር ነው ለግድያ የሚዘጋጁት » በማለት በዕንባ በታጀበ ቃል እንዳይሄድ ተማፀነችው :: ያሬድ ዱብ ዱብ እያለ የሚወርደው እንባዋ የመንፈስ ጭንቀት ፈጠረበት :: ተነስቶ ፀጉሯን እያሻሸ « አይዞሽ በቃ አልሄድም :: ለምን ታለቅሻለሽ ? አልሄድም አልኩኮ » ሲል ማባበል ጀመረ :: ለያሬድ የሕሊናን ፀጉር መነካካት ከበረዶ የወጣን እጅ የሞቀ ውሃ ውስጥ እንደመክተት ያህል ነበር የተሰማው ::

« እውነትህን ነው » አለች ሕሊና ቀና ብላ እያየችው :: በፈገግታ ደምቃ ታየችው :: ውስጡ ተረበሸ ::

* * *

ትዕግሥታቸው አልቋል :: ሰለሞን የቁራ መላክተኛ ሆኖ ቀርቷል :: የማይፈልጉትን ሁኔታ ላለመቀበል ብቻ « ትዕግስት » ይላሉ ለራሳቸው :: እንዲያም ሆኖ ዓይናቸው ደጋግሞ ወደጓሮ በር ይወረወራል :: ቢያንስ በሰለሞን ላይ ተስፋ አልቆረጠም :: በተዘበራረቀ ስሜት ውስጥ እንዳሉ ከሰለሞን ጋር ተገናኙ ::

« ነገርከው ? » አሉት በጉጉት ::

« አዎን ነግሬዋለሁ :: እሞክራለሁ ግን ከመጣሁ ከሰው ጋር ነው ብሏል » አላቸው ::

« የምን ሰው ነው ደግሞ ? » በማለት ፊታቸውን በማኮማተር ጠየቁት ::

« ለእኔ አልነገረኝም ፤ ብቻ ይህንኑ ንገራቸው ነው ያለኝ :: »

« ሕሊና ነበረች ? » ሊሉ ጠየቁት ::

« መኖሩን ነበረች ። ነገር ግን እሷ አልሰማችም ። ሁለታችን ብቻ ስንሆን ነው የነገርኩት » በማለት አስረዳቸው ። ሆኖም የመልዕክቱን ውጤት በጥርጣሬ ነበር የተቀበሉት ። ያሬድ « እሞክራለሁ » ብሎ መመለሱ አልመጣም ማለቱ እንደሆነ አድርገው ገመቱት ። ቢሆንም ተስፋ ለመቁረጥ አልደፈሩም ። በመኝታቸው ላይ ሆነው እንደሚሳካ ወስደው ከራሳቸው ጋር መከሩበት ። አጋጣሚው ለህይወታቸው ወሳኝ ነው ። ከሕሊና ጋር መታረቅ ከፈሩቅ የተንኮል ወጥመድ ነፃ መሆን እንደሆነ ካመኑ ቆይተዋል ። ስለዚህ ማንኛውንም መስዋዕትነት በመክፈል የሕሊናን ይቅር ባይነት ለማግኘት መሞከር ምርጫ የሌለው ጉዳይ ነው ። አንድ ጊዜ እርቁ ይስመር እንጂ የዘመድን ጥቅም አውቀው ስለመቀበላቸው ከእንግዲህ ያውቁበታል ።

ነገን በተስፋ ተሞልተው እያሰላሰሉ ጠዋት ማልደው ተነሱ ። የትልቁን ቤት ዝግጅታቸውን ገና በማለዳው ጀመሩት ። ተሠርቶ የማያውቅ ዓይነት ወጥ በልዩ ትዕዛዝ በእሳቸው በራሳቸው ተመልካችነት ተሰራ ። ሳሎን ቤትም ተነጥፈው የማያውቁ ምንጣፎች ፤ የከት ጌጣጌጦች በየጠረጴዛውና በየወለሉ ላይ ተቀመጡ። እሳቸው ራሳቸው ምርጥ የአበሻ ቀሚሳቸውን ፤ በአንገታቸው ላይ ትልቁን የወርቅ ሀብል አጥልቀው ፤ በጣታቸው ልክ ቀለበት አድርገው ላያቸው በሰውነታቸው ሀብታቸውን ለማሳየት የተዘጋጁ ይመስላሉ ። የቤቱንና የራሳቸውን ዝግጅት ከጨረሱ በኋላ የዋናውን ቤት ፊት ለፊት በር ከፍተው ሳሎን ባለው የፎቴ ወንበር ላይ ተቀምጠው እንግዳቸውን መጠባበቅ ጀመሩ ።

« እንደምንዋላችሁ ? » ሲሉ የነፍስ አባታቸው በዋናው በር ሲገቡ ብድግ ብለው የተለመደውን ሥነ-ሥርዓት በመፈፀም ተቀበሏቸው ።

« የምሳ ሠዓት አልፏል ። ግን የሚጠበቀው እንግዳ እስካሁን ብቅ አላለም ። » አሉ በጥርጣሬ መንፈስ ። የነፍስ አባታቸው መምጣታቸው ትንሽ ፋታ ሰጥቷቸዋል ። ሰለሞን ከግቢ ውጪ በበሩ አካባቢ እየተንጎራደደ መንገድ መንገዱን በመቃኘት እንግዳውን ጠበቀ:: ወ/ሮ አባይነሽ አልፎ አልፎ ወደ ትልቁ በር ብቅ እያሉ « አልመጣም ? » ሲሉ እየጠየቁ ይገባሉ ።

ያሬድና ተሾመ ከሩቅ ሲመጡ ታዩ ። ሰለሞን በሮ ሄዶ « እማማ አባይነሽ እየመጡ ነው ! » አለ ።

« በል ፍጠን ሰለሞን ፤ ቶሎ አስገባቸው » አሉ እየተጣደፉ። ያሬድና ተሾመ ወደ ሳሎን ገብተው ፎቴ ወንበር ላይ ተቀመጡ ።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ « ምሳ ይቅረብ ወይንስ ማባያ የሚሆን ምን መጠጥ ይምጣላችሁ ? » አሉ ወ/ሮ አባይነሽ ደስታ እየተሰማቸው ።

ያሬድ ከነሱ ራቅ ወዳሉት ቄስ ዓይኑን ተክሎ « እኔ እንኳን ምሳ ሌላ ሰው ጋብዞኝ አሁን በልቼ ነው የመጣሁት » አለና ወደ ተሾመ ተመለከተ ።

« ምሳማ እስከአሁን ማን ይጠብቃል ? ባይሆን እንኳን ወንድ ልጅና አትክልት ከወደ ውሀው ነው ይባላል » አለ ተሾመ ። ሁሉም ሳቁ ። ቄሱም « ልክ ነው » በሚል ዓይነት ራሳቸውን ነቀነቁ ። ወ/ሮ አባይነሽ ዝግጅታቸው መና እንዳይቀር ምግብ ለማቅረብ ብዙ ታገሉ ። ማንንም ማሳመን አልቻሉም ። ወደ መጠጡ ተመለሱ ። የተሾመንና የያሬድን ምርጫ ጠየቁ ።

« እኔ ቢራ ይሻለኛል » አለ ያሬድ ። ተሾመም ቢራ መረጠ። ወ/ሮ አባይነሽ ቢራ ከፍሪጅ አውጥተው ከንፁህ ብርጭቆ ጋር አቀረቡላቸው ። ተሾመ ቢራውን አጋባ ። ያሬድ ግን የጠርሙሱን አፍ በግራ እጁ ጠረግ ጠረግ አድርጎ አስቀመጠው ።

« መቼም ለቄስ ቢራ አይታዘዝለትም ፤ በይ ለእኔ ከዚያ ከነጩ ነገር እምጪልኝ» አሉ ቄሱ ። ወ/ሮ አባይነሽ ለነፍስ አባታቸው መጠጥ እያቀረቡ ፣

« ምነው ከሰሞኑ የት ሄደህ ነበር ጠፋህሳ ? » ሲሉ ተሾመን ጠየቁ ።

« አይ እትዬ ሁልጊዜ ይደላል ብለው ነው ? ከሰሞኑ እንኳን በሥራ ብዛት ነው ለመምጣት ያልቻልኩት » በማለት እየተቁነጠነጠ መለሰላቸው ። ያሬድ የቤቱን ሁኔታ ከወ/ሮ አባይነሽ የለውነት ይዘት ጋር በማነፃፀር በሀሳብ ተጠምዶ ነበር ።

« ይህ ሁሉ ሀብት በስንቱ ላብ የተገነባ ነው ። በከተማ በንግዱ በኩል ወሳን የሌለው ትርፍ በማግበስበስ በሌላ በኩል ደግሞ ከገጠር አርሶ አደሩን የላቡን ውጤት ምርት በመንጠቅ የግል ኑሮአቸውን እንደዚህ አሳምረው ይኖራሉ ። ግን ምን ያህል ስግብግብ ናቸው የአንድ እህታቸውን የሥጋ ቁራጭ የሆነችውን ልጃቸውን አስተምረው ለቁም ነገር ለማድረስ ያልፈለጉት ? ሲሞቱ እኚህ ግዙፍ ሴት የሚኖራቸው ሀብት አንድ የእንጨት ሳጥንና ግፋ ቢል ሁለት ሜትር ስፋት ያለው ጉድጓድ ነው ። ምን አለበት የወደፊቱን ኑሮአቸውን ሲያስቡ ሞትም በመንገዳቸው እንዳለ ቢገነዘቡ ? አይ ስግብግብነት ! ስግብግብነት መሀፀኑ ሰፊ ነው ። ቢቃኝን አያውቅም » እያለ ከራሱ ጋር ይጫዋወት ነበር ።

ወ/ሮ አባይነሽ እየተቁነጠነጡ እጃቸውን ግራና ቀኝ ባለው ፎቴ ወንበር ላይ አሳርፈው ፤ « በሉ እንግዲህ አባ ወደ ቁም ነገሩ ብንግባ አይሻልም ? » በማለት የነፍስ አባታቸውን ለውይይቱ ጋበዟቸው ። አባም ከመቀመጫቸው ብድግ ሲሉ ሌሎቹም አብረው ተነሱ ። አባ ቃለ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ፣

« እግዚአብሄር ይፍታህ » አሉና ተቀመጡ ። በፊታቸው ላይ ዝርር ያለውን ሂማቸውን በእጃቸው እየጠመለሉ ዓይኖቻቸውን

ከወ/ሮ አባይነሽ ወደ ሁለቱ ወንዶች እየወረወሩ ፤ « እንግዲህ ሰው ሆኖ የማይጣላ የለም ፤ ከለው ስህተት ከብረት ዝገት እንዳለ ሁሉ ወ/ሮ አባይነሽ ከልጇ ከሕሊና ጋር በስህተት በመጣላትዋ ከቤቷ ወጥታ እንድትኮበልል ሆናለች ። ታዲያ እናትና ልጅ እስከመቼ ተለያይተው ይኖራሉ ? ይህን እግዚአብሔርም አይወደውም። ስለዚህ ዛሬ እነኚህ ሁለት ሰዎች እንዲታረቁ ነው እዚህ እንድንገናኝ የተደረገው ። » አሉና ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ፊታቸውን መልሰው « አይደለ እንዴ ? » ብለው ጠየቁ ።

ስለጉዳዩ ለመናገር የተርበተበቱት ወ/ሮ አባይነሽም ወደ ያሬድ እያዩ « ለአባት ለእናታችን እኔና ወርቂቱ የሕሊና እናት ብቻ ነበርን። የሕሊና እናት ታናሽ ነች ። እናትና አባታችን በተከታታይ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የሕሊናን እናት ከሀገር ቤት ያስወጣኋት እኔ ነኝ። እዚሁ ቤት ከሕሊና አባት ጋር ይተያዩና ይሰራረቃሉ ። ይህችው ሕሊና ሆድዋ ትቀራለች ። እናቷ ለኔ ምንም ሳትነግረኝ ከሕሊና አባት ጋር ኮብልላ ጠፋችብኝ ። እህቴን ይዞ ከሀገር ከጠፋ በኋላ በሽማግሌ ሊታረቁ መፈለጋቸውን ብዙ ጊዜ ገልጸውልኝ ነበር ። ሆኖም በጊዜው በጣም በመናደዴ ሽማግሌዎችንም መቀበል አልቻልኩም ። ከዚያም ትንሽ ቆየት እንዳልኩ ሕሊና ተወለደች አሉ። ሁለት ዓመት እንደሞላትም እናትዋ ሞተችባት ። መርዶዬን ተረዳሁት ። ሕሊናን የት እንዳለች ባፈላልግ አባትየው ያለበት ቦታ በመሰወሩ ለማግኘት አልቻልኩም ። ከዚያ እንግዲህ አባትዋ ሲሞት ሕሊና እሱ በነገራት አድራሻ ወደዚህ መጣች ። እናትዋን ሳልድራት ከቤት ኮብልላ ቀረች ። አሁን ደግሞ ልጅቱ . . . » በማለት ወደ ያሬድ ዓይናቸውን በመትከል ፤ « እንደ እናትዋ ከቤት ወጥታ ቀረች ልጂ » ብለው እጃቸውን ወደ ደረታቸው ጨብጠው አስቀሩ ።

« እኔ መሀን ነኝ የእህቴን ልጅ በሠርግ ደግሼ ለመዳር የነበረኝን ፍላጎት መቼም ለእናንተ አላወራውም ። ግን ምን ያደርጋል

እሁንም የልጅነት ፀባይ ይዟት እኔን ለማየት አትፈልግ ይሆናል ፡፡ ለዚህ ነው እናንተን በአማላጅነት እንድታስታርቁኝ ዛሬ እዚህ የጠራኋችሁ » ብለው ለተሰበሰቡት ሰዎች ሳይሆን ለራሳቸው ዕንባቸው ዓይናቸው ላይ እያቀረረ « ምነው ከዚህ ሁሉ የራሴ ነው የምለው አንድ ልጅ ቢኖረኝ አይ አንተ አምላክ ፍረደዋ ! » በማለት እጃቸውን ወደ ሠማይ በመዘርጋት ወደ ላይ አንጋጠው ጣሪያውን ተመለከቱ ፡፡ የነፍስ አባታቸው « መቼም ኖረው ኖረው ከመሬት፤ ዞረው ዞረው ከቤት እንደሚባለው ሁሉ » ሲሉ ቀኝ እጃቸውን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዘርግተው « ከእንግዲህ ይህች ሰው ቆርባ መኖሪያዋ ነው ፡፡ የለፋችበት ሀብት ሜዳ ላይ ተበትኖ እዳይቀር ይህችን ልጅ በምክንያት እግዚአብሄር በደግነቱ ሰጥቷታል ፡፡ ታዲያ የእነሱ መጣላት ለምኑ ነው ፡፡ ግድ የሰም ይሁን ልጅቱ በገዛ ፈቃድዋ ቤቷን መርጣለች . . . ማለፊያ ነው ፡፡ መቼም ዘመኑ ያመጣው ስለሆነ ይቅር ብሰን መቀበል አሰብን ፡፡ ይሁንና ለልጅቱም ቢሆን ኑሮዋ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለውና ደስተኛ እንድትሆን የእናትዋ ምርቃት አስፈላጊ ነው ፡፡ ታዲያ በወግ በማዕረጉ በሠርግ ከቤትዋ ብትወጣ ምን ይከፋል ?» በማለት ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ ያሬድን ለሕሊና እንደ ባል በመቁጠር ነበር ፡፡

ያሬድ ሁለቱ የሚናገሩትን አዳመጠ ፡፡ ብዙ ግልፅ ያልሆኑለት ጉዳዮች ስለነበሩ ለመቸኮል አልፈለገም ፡፡ ጆሮዎቹን ቀስሮ ለማዳመጥ ቅድሚያ ሰጠ ፡፡ ተሾመም በጉዳዩ ላይ ከያሬድ በላይ አልነበረም ፡፡

ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ግንኙነት በወደፊት ህይወታቸው ላይ ያለውን ወሳኝነት በመገመት እነያሬድ እንዲያዝኑላቸው ገለፃቸውን በለቅሶ ቀጠሉ ፡፡

« ሕሊና ገና እዚህ ቤት ስትመጣ የእህቴ የወርቂቱ ምስል በመሆንዋ እራስዋ ወርቂቱ በህይወት ተመልሳ የመጣች ነበር የመሰለኝ ፡፡ ግን ምን ያደርጋል ከአባትዋ ጋር ስትኖር የወረሰችው

ፀባይ ልግመኛ አድርጓታል ፡፡ የምለውን አትሰማም ፣ እንደመጣች እዚህ አብራኝ የምትኖር አንድ ሴት ነበረች ፡፡ ከእሷ ጋር ገጠሙ ፡፡ ከዚያ በኋላ ነው እኔን ዓይንሽን ላፈር ብላ የጠላችኝ ፡፡ ያው ያቺም የነገር ቋት የማትለው የላትም በመጨረሻ በስካር እራስዋን ስታ ተሰቅላ ሞታ ተገኘች ፡፡ አይ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ ! » በማለት ወደ ኮርኒስ በዓይናቸው እየተመለከቱ ፡፡

« እሷም የዘመድ ልጅ ነበረች ፤ አይ አስካበች . . . » ብለው ዕንባቸውን ማንባት ሲጀምሩ የነፍስ አባታቸው ተቆጡ ፡፡

« የሙት ስም አታንሺ ! እግዚአብሄር ይቅር ይበልሽ ! ኧረ ነውርም አይደል ፡፡ ካለፈ በኋላ ነፍሷን ይማር ይባላል እንጂ » በማለት ወደነያሬድ እየተመለከቱ « በሉ ልጆቼ አይከፋችሁም መቼም ልጆቼ ብላችሁ ይሄን መሳይ ጉድ ነው ይህች ሴት ተሸክማ ያለችው፡፡ እግዚአብሄር ይቅር ይበላችሁ ይቅር በሏትና የጠየቀችውን ፈጽሙላት» በማለት ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው እጃቸውን ወደ እነያሬድ ዘረጉ ፤ በልመና ዓይነት ፡፡

ያሬድም ቄሱ በአዛውንትነታቸው መከበር እንዳለባቸው ስላመነ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ « ኧረባክዎ አባባ ተቀመጡና እንነጋገር » አላቸው ፤ ቶሎ ይቅርታ ለማድረግ ባልፈለገ አቀራረብ ፡፡

« ይቅርታ ሳላገኝ እንዴት ልቀመጥ ? ይቅርታህን ስጠኝና ልቀመጥ » በማለት እንደቆሙ ቀሩ ፡፡

« ነገሩ ወዲህ ነው ፡፡ ይቅርታ ለማድረግም ላለማድረግም እርሶ ይቀመጡ » በማለት ወደ አባ ቀረብ ብሎ በእጁ እጃቸውን ይዞ እንዲቀመጡ አደረገና እርሱም ተመልሶ ተቀመጠ ፡፡

ያሬድ ወ/ሮ አባይነሽንና የነፍስ አባታቸውን ከአንዱ ወደሌላው በማቀያየር እያየ « ይቅርታ ለማድረግ እኔ ብቻ ብቁ አይደለሁም ፡፡ ጉዳዩ እንዲያውም እኔን አይመለከተኝም ፡፡ ተበደልኩ ባይ እኔ ባለመሆኔ የእኔ ይቅር ባይነት ያለቦታው ይሆናል፡፡ እኔም

ከእርሶ ጋር ትውውቅም ቂምም የለኝም ። ግን በእናንተ አስተሳሰብ የተሳሳተ አባባል አለ ።

ሕሊና ለእኔ ሚስቴ አይደለችም ። በቅድሚያ ይህን ልታውቁልኝ ይገባል ። በመካከላችን ምንም ዓይነት ግንኙነት አልፈጠርንም ። ስለመመለስና ስለ ሠርጉ ጉዳይ እንግዲህ ወሳኟዋ እራሷ ባለቤቷ ነች። የእርስዎም የእማማም አባባል ከልብ ገብቶኛል።

ሆኖም በእኔ በኩል ልፈፅመው የምችለው ነገር ቢኖር ይህንኑ መልዕክት ለእሷ ማድረስ ነው ። አይመስላችሁም ? » በማለት ለወ/ሮ አባይነሽና ለአባ ጥያቄ አቀረበ ።

« ጎሽ እግዚአብሔር ይባርክህ፣ የአዋቂ አነጋገር ነው የተናገርከው ። መቼም ስለሁሉም ነገር እናንተ ታውቃላችሁ ። ለው ግን የሚያወራው አግብታ እየተማረች ነው እያለ ነው ፣ ካልሆነም ማለፊያ . . . » አሉና ወ/ሮ አባይነሽን ተመለከቱ ።

« መቼም መጋባቱ በመንገዱ ቢሆን ነውርም የለው ። እኔም አባ እንዳሉት ሰው መቼም ወሬኛ ነው ያሳየውን በይሆናል ያወራል ። ግን ካልሆነም በሀሳብ የተዛመዱ ሰዎች ኖረው ኖረው በሥጋ መዋሃዳቸው አይቀርም » በማለት ያሬድን በፈገግታ አስተዋሉት ።

ተሾመ ጣልቃ ገባ ። « እንዲያው በማታውቀው ነገር ገባህ ባትሉኝ በዚህ ንግግር የሚጎለን ሁለቱን ተበዳይ ነን ባይዎች አቀራርቦ ማነጋገርና የበደሉን መጠን አመዛዝኖ በዳይ ተበዳይን እንዲክስ አድርጎ ማስታረቅ ነው ። ታዲያ ይህም የመጀመሪያ ግንኙነት ስለሆነ አይከፋም ። ለዋናው መነሻ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ የሚቀጥለው ግኑኝነታችሁን የምታደርጉበት ቀን ቀጠሮ ወስኑና ያሬድም ሕሊናን ያነጋግር ፣ እናንተም እንግዲህ ወ/ሮ አባይነሽ ዝርዝር ሁኔታውን አስበውበት መዘጋጀት ይሻላል » በማለት ሀሳብ አቀረበ ።

« ይባርክህ ማለፊያ ፣ ሀሳብ ነው ያቀረብከው ። እንግዲህ ወ/ሮ አባይነሽም የሚመችሽን ቀን እናንተም የሚመቻችሁን ቀን ወስኑልኝና በዚሁ እንለያይ » አሉ የነፍስ አባታቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ በራሳቸው መንገድ ቀጠሮውን ሊያደርጉ ብዙ ቢታገሉም ያሬድ ከሳምንት እሁድ ውጪ አይመችኝም ስላለ በዚሁ ተስማሙ ። ቀጠሮው ከተያዘ በኋላ ያሬድ ወደ ቤቱ ለመመለስ ከተቀመጠበት ተነሳ ። ወ/ሮ አባይነሽ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሲለምኑት ተቀመጠ ። አንድ ሌላ ቢራ እንዲደግም አስገደዱት ፣ እና ተቀበለ ። ባልታወቀ ሁኔታ ከመጠጡ ጋር ጨዋታ ተጀመረ ። አልኮልዋ የስራች መሰለች ። ወ/ሮ አባይነሽና ያሬድ አፍ ለአፍ ገጥመው መጫዋወት ጀመሩ ። በዚህ መሀል ወ/ሮ አባይነሽ ተቆርቋሪነታቸውንና ስለ ሕሊና በቅርብ መከታተላቸውን ለማረጋገጥ እንደ የሚያውቋትን የግዛ ምስጢራቸውን ለያሬድ ተነፈሱ ።

« ባለፈው ጊዜ ማን ነበር እሱ ? ሕሊና አዲስ እንደመጣች ቤታችሁ ተሰብሮ ነበር ብሎ ነገረኝ ። መቼም በጣም ነበር የደነገጥኩት ። እንዲያው እዚህ ሀገር እኮ የዚህ የፋብሪካ የቀን ሠራተኞች ሥራ ሲፈቱ ማታ ማታ የሚያድርጋቸውን ነው የሚያሳጣቸው » በማለት እንደተቆረቆረ ሁሉ ጉዳዩን ለመስማት በመጓጓት ያሬድን ተጠጉት ። « አይ እሱማ ያለ ነው ። ግን እኮ የሚገርመው ምንም ነገር ሳይወስዱ በሩን ሰብረው ትተው ነው የሄዱት ። ለእነሱ የሚጠቅም ሳህን ፣ ማንኪያ ፣ ሹካ እያለ አንዱንም ነገር ሳያነሱ መውጣታቸው በጣሙን ነው የገረመኝ » ሲል ተናገረ በጥርጣሬ ዓይን እየተመለከታቸው ። የወ/ሮ አባይነሽ የፊት ቀለም ሲቀያየር አስተዋለ ፣ የታችኛው ከንፈራቸው የሚናገሩትን ሳይሆን የደበቁትን ለመናገር ትግል አደረገ ። ሆኖም እንደምንም ብለው አንደበታቸውን ገቱት ።

« ልክስክስ ሌባ ነው ። እንዲያው አንድም ነገር ሳያነሳ ሄደ በሞቴ ? » አሉ ። « ምንም የተነሳ የለም ። በቤቱ ውስጥ የተቀመጠው ዕቃ እንኳን ቦታውን አለወጠም ። እንዳለ አገኘነው » አላቸው ።

ለወ/ሮ አባይነሽ ይህ በቂ ነበር ። ቀደም ብሎም ስርቆቱ ምንም ኮሽታና ጩኸት ወይም ጋጋታ ሳይሰማ መፈጸሙ የድርጊቱን ምንነት ምልክት አጠራጣሪ አድርጎባቸው ነበር ። አንድ ነገር የጎደለ መሆኑን ሰውነታቸው ነግሮአቸው ነበር ። ግን ማንን ይጠይቁ ? ምስጢሩ ምስጢር ሆኖባቸው እንዲሁ እንደቀፈፋቸው ነበሩ ። አጋጣሚውን ተጠቀሙበት ። ጥርጣሬአቸው ልክ ነበር ። ግን ጭንቅላታቸው ሊቀበለው የሚፈልገው እውነት አልነበረም ። ሠማይ ምድሩ ዞረባቸው ። ሰውነታቸው የሚፋጅ ላብ መትፋት ጀመረ ። ውስጣቸው ተቃጠለ ። ትንፋሻቸው ፍጥነቱን ጨመረ ። ያሬድ ፊት ለፊት እያያቸው ከተቀመጡበት ሽርተት ብለው ፎቴው ላይ ተዘረጉ። ያሬድ የሚያየው ሁሉ ህልም መሰለው ። የማያውቀው ድንገተኛ ድንጋጤ ወረረው ።

« ምነው እመመዎት እንዴ ? » አለ ።

« ውኃ ፣ እባካችሁ ውኃ አምጡ » ሲሉ ጮኹ የነፍስ አባታቸው ።

* * *

ያሬድና ተሾመ በገጠማቸው ሁኔታ ተደናግጠው ከግቢው አጥር በር እንደወጡ ያመሩት ወደ ወንድማማቾች ቡና ቤት ነበር ። ያሬድ የወ/ሮ አባይነሽ ሁኔታ በጣም አሳዝኖታል ። ሲያስመስሉ እንዳልሆነ ከሁኔታቸው ተረድቷል ። ያ ሁሉ ላብ ያለአንዳች ምክንያት ሲመነጭ እንዳልቻለ ተገንዝቧል ። ያነቡት ዕንባ የዋዛ አልነበረም ። « ሴትየዋን ምን ነካቸው ? በጤና ሲያነጋግሩን ቆይተው ከመቅስፈት የተለዋወጡት ? » ሲል ተሾመን ጠየቀው ።

ተሾመም ከያሬድ የተለየ ህሳብ አልነበረውም ። ለወ/ሮ አባይነሽ ከልብ አዝኖላቸው ነበር ። « በሠሩት ኃጢያት ተፀፅተው ይሆናል ። በሰው ላይ ክፉ ነገር መሥራት መጥፎ ነው ። የመንፈስ ጭንቀት ተገዥ ያደርጋል » ሲል መለሰለት ።

« በህይወት ይኖራሉ ብለህ ነው ? የዚህ ዓይነት በሽታ ያለበት ሰው ዕድሜው አጭር ነው » አለ በምሬት ።

« ምን ይሆናሉ ብለህ ነው ? ለእኛ አዲስ ነገር ሆነ እንጂ የተዋሃዳቸው በሽታ ይመስለኛል » እየተባባሉ ወንድማማቾች ቡና ቤት በራፍ ደረሱ ። ከመግባታቸው በፊት ውጪ ትንሽ ቆም አሉና ተከታትለው ወደ ውስጥ ገቡ ። ጥግ ይዘው ቢራ አዘዙ ። ሳያስቡት ጀምረውት ወደነበረው ውይይት ተመለሱ ።

« ምን ነበር የሚዘላብዱት ? ጋብቻ ፣ ሠርግ ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው ? » ሲል ያሬድ ጠየቀ ።

« ያው ነው ! ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ ። እንግዲህ አንተንና ሕሊናን ሲያጋቧችሁ ይሆናላ » በማለት ፈገግ አለ ።

« ይቀልዳሉ ! አሁን ደርሰው ስለ ጋብቻ ምን አሳሰባቸው ? »

« ምን ግራ ይገባሃል ? አንተን የመሰለ ጥሩ አማች እንዳያመልጣቸው ብለው ነው:: ያሬድ አትቀየመኝና አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ :: አሁን ሕሊና ትምህርቷን ስትጨርስ ሌላ ሰው እንዲያገባት ቢጠይቅህ ትፈቅዳለህ ? » ሲል ያሳሰበውን ጥያቄ አቀረበለት :: ያሬድ እራሱን በአሉታ እየነቀነቀ ፣

« ምን ማለትህ ነው ? ጥያቄህ አልገባኝም » ሲል በጥሞና ተሾመን አስተዋለው ::

« ስማኝ ጥሩ ምክር ልምክርህ :: ያልከውን ብትል አንተ ሕሊናን አግብተህ አብራችሁ እንደምትኖሩ አትጠራጠር :: ግን ወ/ሮ አባይነሽ ይህ የደከመ ህይወታቸው አንድ ቀን ሲሰናበት ያየኸው ሀብት ሁሉ የሕሊና ይሆናል :: ሌላ ወራሽ የላቸውም :: አሁን የተቸገሩት የመሞቻ ጊዜያቸው የተቃረበ እየመሰላቸው በህይወት ዘመናቸው ያፈሩትን ሀብት ለማንም አባክነው አሳልፈው እንዳይሰጡ ነው:: አብሮአቸው ያለውም ሰው ሞታቸውን ነው የሚጠባበቅላቸው:: ነገር ግን ሀብታቸው በዚህ ሰው እጅ እንዲወድቅ አይፈልጉም :: ገባህ? የዕርቁ መሠረት ይህ ነው :: የቀረውን እንግዲህ አንተ እወቅበት » አለው በተቆርቋሪነት ዓይነት ::

ያሬድ በሀሳብ ማዕበል በመዋጥ በውስጡ እየተጨነቀ ተሾመን ተመለከተውና « ሰለ ጋብቻው ያልከው እንግዲህ ጊዜ ነው የሚወስነው :: ግን ሕሊና ትምህርቷን እስከምትጨርስ የዚህ ዓይነቱ ሀሳብ በእኔም በእሷም እንዲፀነስ ፍላጎቴ አይደለም :: ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ሀብት ወሳኟዋ ሕሊና ነች :: ለመታረቅ ብትፈልግ መልካም፤ ካልፈለገች ግን ይህን አድርጊ ብዬ እኔ አልገፋፋትም » በማለት የቀረበውን ጠርሙስ ቢራ ብድግ አድርጎ ጉሮሮውን እራሰ ::

« ያሬድ ይህን ብታደርግ ሞኝ ነህ :: ሰው በእግር በፈረስ የሚፈልገውን ዕድል በርህን እንኳኩቶ ሲመጣ አልፈልግህም ብለህ ብትሸኘው ይህን የዋህነት እለዋለሁ እንጂ ሀቀኝነት አይደለም ::

ሕሊና ምን ይወጣላታል :: በዚህ ላይ ተቀጥላ ሀብት ይዛ የምትመጣ ከሆነ ለማን ብለህ ነው አሳልፈህ ለሌላ የምትሰጣት ? እኔ አንተን ብሆን ኖሮ አሜን አማምዬ ብዬ ሕሊናን በእጅ በእግሯ ገብቼ ነበር እርቁን እንድትቀበል የማደርገው :: ብቻ . . . ተወው አንዱ ጭልፊት ይቀድምህና ሕሊናን አግብቶ በተደላደለ ኑሮ ሲዝናና ወይኔ እኔ ነበርኩ እኮ የዚህ ዕድል ባለቤት አያልክ በንዴት የሚደርቀውን ከንፈርህን ስትመጥ እንዳላይህና እንዳልስቅ » አለው :: ያሬድ ለመነሳት እየተዘጋጀ « የምትለውን ጨረስክ ? » ሲል ተሾመን ጠየቀው ::

ያሬድ ወደ ቤት ሲገባ ጊዜው አልመሸም ነበር :: ሆኖም በሀሳብ እየዋለለ ወደ መኝታው አመራ :: አልጋው ላይ ልብሱን ሳያወልቅ ጋደም ብሎ ቀን ሲፈጽም የዋለውን እያንዳንዱን ቃላት በመመርመር በሀሳብ ተጓዘ ::

« እውነታው ተሾመ እንዳሰቀመጠው ነው :: ሕሊና ከሀብት ጋር ብትሆንም ፣ ያለሀብት ብትቀርም ለሌላ ሰው አሳልፌ ለመስጠት አልቃጣም » አለ በሀሳቡ :: « ግን እኮ ጋብቻም ቢሆን በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ለእኔም ሆነ ለሕሊና ያለምንም መሰናዶ መፈፀም አይቻልም :: ለሕሊና ይህን ሀሳብ ማቅረቡ ከአስተሳሰብዋ ማለትም የአባትዋ ቅሪት ከሆነው እምነቷ ጋር መቃረን መሆኑን እረዳለሁ :: እነዚህን ውስብስብ ጥያቄዎች ለመፍታት በመጀመሪያ ደረጃ መፈፀም ያለበት ሕሊና ከአክስቷ ጋር እርቅ እንድታደርግ መገፋፋት ነው :: ብቻ መታረቅ እንኳን ቀርቶ የአክስቷ ስም ሲነሳ እንደሚያንገፈግፋት አውቃለሁ :: ታዲያ በምን ዓይነት ዘዴ ነው ሕሊናን ማሳመን ቀርቶ ማነጋገርስ የሚቻለው ? » ሲል አሰበ ::

ባለፈው ጊዜ በውስጣዊ ስሜቱ ተገፋፍቶ ሕሊና ወ/ሮ አባይነሽ ጋር እንዳይሄድ ስትጠይቀው እሺ አልሄድም ብሎ መስማማቱ ታሰበው :: ለዚህም « ሄጃለሁ » ማለቱ ብቻ ለሕሊና

መቀየም መሠረት ሊሆን እንደሚችል ተገነዘበ ። መቀየሟ ከሕሊና ጋር ሳይነጋገር ውሎ ማደርን እንደሚያመጣበት ገመተ ። ድንገት « አልችልም ! » ሲል ጮኸና ከአልጋው ላይ ተስፈንጥሮ ተነሳ ።

*　　*　　*

አብዬ ጋሻዬ የሕሊናን አድራሻ አጠያይቀው ሲደርሱበት እንደገመቱት ሕሊናን በእጃቸው ለማድረግ አልተሳካላቸውም ። መንገድ ላይ ጠብቀዋትም ሆነ ከትምህርት ቤት አስጠርተው ሊያነጋግሩዋት ሞክረው አልሆነላቸውም ። ፊት ለፊት ሲያገኟትም ቢሞክሩ ያሬድ ህልማቸውን እውን እንዲሆን አላደረገም ። ይህን ጉዳይ ከቅርብ ጓደኛቸው ከቀኛአዝማች አዲሱ ጋር ለመነጋገር የወሰኑት ብቻቸውን ሊወጡት የማይችሉት መሆኑን ከተገነዘቡት በኋላ ነበር ። ቀኛአዝማች አዲሱ እንደወትሮአቸው በአብዬ ጋሻዬ የእህል መጋዘን በረንዳ ጊዜያቸውን በሚያሳልፉበት ወቅት ነበር ሁኔታውን ከሥር ጀምረው ያወሩላቸው ።

« ጉድ ሆነሃላ ! ምነው ታዲያ እስከአሁን ደበቅከኝ ? » አሉ ቀኛአዝማች አዲሱ ፣ አብዬ ጋሻዬ የገጠማቸው ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን በሚያሳይ ፊት ። ጭንቀትና ችግራቸውን እንዴት ሊወጡት እንደሚገባቸው ሲያውጠነጥኑ ከቆዩ በኋላ አንድ ሀሳብ ድንገት ብልጭ እንዳለላቸው ወደ በረንዳው ዳር እያመሩ ፣ « መንገዱን ሁሉ አጥረህብኝ ምን ዓይነት መፍትሄ እንደማመጣ እኮ ቸገረኝ ። ብቻ አንድ ነገር ማድረግ የሚቻል ይመስለኛል » ብለው አካባቢያቸውን ግራና ቀኙን ከቃኙ በኋላ በአብዬ ጋሻዬ ጆሮ አንድ ነገር ሹክ አሏቸው።

« ይሆናል ብለህ ቀኛአዝማች ? እንዲህ ያለውን ምክር ታዲያ አደራህን በምስጢር መያዝ ይገባሃል »

« ምነውጃል ! ለእኔ ነው የምትነግረኝ ? ወንድምህን አጣኸው? በሦስት ቀን ውስጥ ውጤቱን አሳይሃለሁ » ለእኔ ተወው በሚል አመለካከት ነበር የተናገሩት ። አብዬ ጋሻዬና ቀኛአዝማች የተለመደውን የግል ወሬያቸውን ጨርሰው ተለያዩ ።

ቀኛአዝማች እንደተለዩ ያመሩት ቀጥታ የያሬድ የቅርብ ጓደኛ ተሾመ ዘወትር ወደሚገኝበት ወደ ወንድማማቾች ቡና ቤት ነበር ። ተሾመን ለመቅረብ ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም ። እንደአጋጣሚ ቢራ አዞ ይጠጣ ስለነበር የሦስቱን ቢራ ሂሳብ ከፍለው እንዲጋበዝ አደረጉት ። ሂሳቡን የከፈሉት ቀኛአዝማች መሆናቸውን እንዳወቀ በደንብ ተዋወቃቸውና ስለ ግብዣው አመስግኖ ተለያዩ ።

ማክሰኞ ዕለት ሌላ ቦታ ቆይቶ ቡና ቤቱ የደረሰው ዘግይቶ ነበር ። ቀኛአዝማች ሲጠብቁት ቆይተው ትዕግስታቸው ሊያልቅ ሲል ነበር የደረሰው ። ገና ሲገባ ብድግ ብለው ሞቅ ባለ ሰላምታ ተቀበሉት። አጠገባቸው ያለውን ወንበር ሳብ አድርገው እንዲቀመጥ ጋበዙት ።

« ልጅ ተሾመ እንዲያው ከሩቅ ሆኜ ሁኔታህን ስመለከት እንዲያ ሰውን ሁሉ በሳቅ ስትጨርሰው እኔም የጨዋታህን ለዛ መካፈል ፈለግኩ ። እስኪ ቀርቤው እንጫወት ብዬ ነው ። »

« ምናለ ታዲያ ደግ ነው ። እኔ እንኳን ጨዋታ አላውቅም ማለትም እጅግም ነኝ የጎረምሳ ጨዋታ ደግሞ . . . » ብሎ ሽምግልናቸውን ቢጠራ ስሜታቸውን ይነካል ብሎ ፈራና የፈለገውን ሳይናገር በእንጥልጥል ተወው ።

« እይ የእናንተ ነገር ፣ ማነው ሽማግሌ ያለፈ የጉርምስና ታሪኩን እንዳይለማ የከለከለው እኮ የትኛው ህግ ነው ? ይልቁንስ እኛ ከናንተ እናንተ ከእኛ የምንማማረው ብዙ ነገር አይኖርም ብለህ ነው ልጅ ተሾመ ? ይህ እንኳን የማይመስል ነገር ነው » አሉ ቀኛአዝማች አዝማሚያው ከዓላማቸው ጋር እንዳይጋጭ በመፍራት።

« እንደሱ እንኳን ማለቴ አይደለም » አለ ተሾመ ከእሳቸው ጋር በዚህ ጉዳይ መከራከሩ የትም እንደማያደርሰው በመገመት ::

ቀኘአዝማችና ተሾመ ከረጅም የመግባቢያ ንግግር በኋላ ስለ ጓደኛው ያሬድና አብራው ስለምትኖረው ስለ ሕሊና ዳር ዳር ሲሉ ቆይተው ዋናውን ጉዳይ አለስልሰው ነገሩት :: ተሾመ በቀኛአዝማች ትረካ መካከል የአብዬ ጋሻዬን ስም ሲሰማ ከዚህ በፊት በወ/ሮ አባይነሽ ቤት በተደጋጋሚ ለሕሊና ያላቸውን አመለካከት ከአሁኑ ሁኔታ ጋር ሲያገናዝብ የሰማው ነገር ይህን ያህል ባያስደንቀውም ስሜቱ ረግብ ሲልለት አብዬ ጋሻዬ የሕሊናን እጅ እንዲሰጧቸው ጥያቄ አቅርበዋል ብሎ ለያሬድ እንዲነግር የተመረጠበትን ምክንያት በጉዳዩ ጣልቃ እንዴት ሊያስገቡት እንደቻሉ የጠየቃቸው ኮስተር ብሎና በቁጣ ነበር ::

« አይ ልጅ ተሾመ ፤ እንስማማ እንደሆነ በዚህ እንድንጨርሰው ብዬ እንጂ የማንግባባ ከሆነ እኮ ጉዳዩ ቀላል ነው :: አሁን ማ ይሙት . . ጋሻዬ እንቢ የሚባል ፣ ለዚህ የማይበቃ ሰው ሆኖ ነው ? እንኳን ይህችን መጤ ቀርቶ የፈለገውን መርጦ ማግባት ቻትተዋል ? እንዲያው ጥሎብት እንጂ » አሉ :: ቀኛዝማች እኔ የያዝኩት ነገር እንዴት ተናቀ በሚል የቁጭት አመለካከት ::

« ታግባባው እንደሆ አግባባው :: ጓደኛዬ ነው ብለህ የለ ? የጓደኛህን ጥቃት የማትወድ ከሆነ ልጅቷን ጠልፈን ከምንወስዳትና የማታገኝት ቦታ ከማስቀመጣችን በፊት እኔም ሆንኩ አንተ በደንብ ብናስብበት ይሻላል :: እስከአሁን ከእኛ ምክር የወጣ በአቃቂ አለመኖሩንም ጠይቀህ ተረዳ » አሉ ኮስተር ብለው ::

ተሾመ ከረጅም ዝምታና ሀሳብ በኋላ « እንዴ ! እኔ እኮ እሺም እምቢም ለማለት ስልጣን የለኝም :: ያሉትን መልዕክት ለመናገሩ ከሆነ ነገውኑ እነግረዋለሁ :: »

« ጎሽ ተባረክ ! ገና ወጣት ነህ :: በሥራህም ማደግ ትፈልጋለህ :: ከእኛ ትዕዛዝና ምክር መውጣቱ ደግም አይሆን » አሉት ቀኘአዝማች ዓላማቸው እንደተሳካላቸው ሲያረጋግጡ ::

« በል እንግዲህ እኔን ታገኘኛለህ በማንኛውም ነገር ስትፈልገኝ ከዚህ አልጠፋም እንዲያው የሆነውን ብቅ ብለህ አጫውተኝ » ብለው ሂሳቡን ከፍለው ከቡና ቤቱ ወጥተው ሄዱ ::

ተሾመ ቀኛአዝማች መራቃቸውን ሲያረጋግጥ የቀድሞውን የደህና እደሩ ሠላምታ ለቡና ቤቱ ሠራተኞች ሳያቀርብ ወጥቶ ሄደ :: እግሩ በተለምዶ ይራመዳል እንጂ ወዴት እንደሚሄድ እንኳን አያውቅም :: ከራሱ ሀሳብ ጋር ይሟገታል :: « አሁን በምን እግሬ እዚህ ቤት መጣሁና ይህን ውስብስብ ጉዳይ ለማሁት ? አሁን ያሬድ ማ ይሙት ያቺን እንደ ጣኦት የሚያመልክባትን ፣ የሚወዳትንና ከሰው ጋር የተጣመደባትን ልጅ ለአብዬ ጋሻዬ . . . ያውም ለአብዬ ጋሻዬ አሳልፈህ ስጥ ብዬ ልነግረው ? ወይ ጉድ ! ይህን እንኳ አላደርገውም የማልችለውን :: » ብሎ ወደ ውሳኔ ሲቃረብ ቀኛአዝማች በመጨረሻ ስለ ሥራው የተናገሩት ጉዳይ ደግሞ ሀሳቡን እንደገና እንዲመረምረው ፣ እንዲያጤነው ወተወተው ::

« ማን ከነሱ ጋር ይቃቃራል ? እንኳን ሥራዬን እኔነቴን ሊያሳጡኝ ይችላሉ :: ምን ፈተና ፣ ምን ዕዳ ዳረገብኝ ? » እያለ የሚሆነውንና የማይሆነውን እያሰላሰለ እቤቱ ደረሰ :: ተሾመ ሲያሰጨንቀው ያደረውን ጉዳይ ለያሬድ ለመንገር በቀጥታ እንደተጣደፈ ወደ ቢሮ አመራ :: ያሬድ ግን ያለ ወትሮው ቢሮው አልነበረም :: ሲንቆራጠጥ ቆይቶ ከሥራ ለመውጣት ሩብ ሰዓት እንደቀራቸው አገኘው ::

« ምነው በደህና ? ዛሬስ ዘገየህ :: ጠዋት ቢሮህ ብመጣ አልገባህም ነበር »

« ድሮ ከምገባበት ሠዓት ትንሽ አሳለፍኩ እንጂ ማርፈዴስ ይህን ያህል አይደለም ። ይልቅ ምነው የደከመህ ትመስላለህ ። ዓይንህም ከብዶታል ። »

« ማታ አምሽቼ ነበር የተኛሁት ። እዚህም ስመጣ ማሽን ተበላሽቶ እሱን ፊክስ ለማድረግ ስጨናበስ ዋልኩኝ ። ዕረፍትም አላገኘሁም » አለው ።

ያሬድ እና ሀሰን ሳያስቡት ነበር ወንድማማቾች ቡና ቤት የደረሱት ። በረንዳ ላይ ቁጭ እንዳሉ ተሾመ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ የተሸከመውን ጉዳይ እንዴት እንደሚተነፍሰው ሲያመነታ « አንድ የምነግርህ ጉዳይ ነበር ። ጠዋትም የፈለግኩህ በምክንያት ነው ። ያውም ያንተ ጉዳይ » አለ ተሾመ በረጅሙ ተንፍሶ ።

« ያውም የእኔ ? ደግሞ ምን ተፈጠረ ? የትርሲት የዘወትር አርቲቡርቲ ወሬ ከሆነ ልሰማው አልፈልግም ፤ እንዳታወራልኝ »

« አንተ ደግሞ ጉዳይህን የያዝኩት እኔ ፤ የምትጨሰው አንተ! ሰው ሁልጊዜ አይቀልድም » አለ ተሾመ በሥስልቾትና በማማረር አኳኋን ።

ተሾመ ቀኝአዝማችን ከተዋወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ትናንት ድረስ ያለውን ታሪክ ሁሉ ለያሬድ ሲነግረው የያሬድ ፊት ቀስ በቀስ እየተለወጠ ፤ በቁጭትና በንዴት እየተመረዘ ይሄድ ጀመር ። ተሾመ ተርኮ እንደጨረሰ እፎይታ ተሰምቶት አጥፎ የነበረውን እግሩን ዘርግቶ ተዝናንቶ ተቀመጠ ። ያሬድ ለሰማው ነገር ቀንድና ጭራውን ለይቶ ለማወቅ እረጅም ሰዓት ወሰደበት ።

« ይልቅ ለምን ሆነ ብለን ከምንከራከርና ጉዳዩ ስውየው እንዳሉት ወደ መጥፎ አዝማሚያ ከመድረሱ በፊት ማድረግ የሚገባንን በወቅቱ መፈጸሙ ላይ ብናተኩር የተሻለ ይመስለኛል ። ቀኝአዝማችም ጉዳዩን በቀላሉ ያዩት አይመስለኝም » አለ ተሾመ የመጠቡት አቅጣጫ በሩቁ እየቀፈፈው ።

ያሬድና ተሾመ ለረጅም ሰዓት ቡና ቤት ውስጥ ቆይተው ማምሻውን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ተነጋግረው ተለያዩ ። ያሬድ ወደ ቤቱ አቅጣጫ ሲያመራ ተሾመ ወደ ከተማ አቀና ። ያሬድ እንደተለመደው ሳሎን አልተቀመጠም ። ለሕሊና እራሱን እንዳመመውና ሻይ እንድታፈላለት ነግሯት ወደ መኝታ ቤቱ ገብቶ የበኩሉን ሀሳብ እያውጠነጠነ « ይህ ሽማግሌ አልተው አለ አይደል ? አሁን ምን ልሁን ብሎ ነው በዚህ ዕድሜው እንዲህ የሚቀለው ? የሞቀ ትዳሩን ትቶ ልጁን ለማግባት የሚጥረው ? ከእሷ የማይተናነሱ ልጆች አድርሷል ። ምን በሀብት ላይ ሀብት ቢኖረው ፣ የተከበረም ቢሆን ለዚህች ለቀረችው አጭር ዕድሜ ሥሙን ባያጠፋና የልጅቷንም ዕድል ባያበላሽ ምን አለበት ። » እያለ ያሬድ የሰው ልጅ ክፋትና ስግብግብነት እያሳዘነው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕሊና ወ/ሮ አባይነሽ ቤት በነበረችበት ወቅት ምናልባት ከኔ የደበቀችው ከሽማግሌው ጋር የሆነ ግንኙነት ይኖራት ይሆን ? ሲል እየተጠራጠረ ሳለ ሕሊና ሻይውን በማቅረቢያ አምጥታ ከመዷና ላይ አስቀመጠችለት ።

« ምነው አልተሻለህም ? ጋሼ ያሬድ ካፌኖል ለምን አትውጥም ? » አለችው ።

« ይሻለኛል ፤ ግድ የለም ሻይው ያሽለኛል » ብላት ያሬድ ቶሎ እንድትወጣለት በአጭሩ በመመለስ ።

« የለም ሕሊና ይህን አታደርግም ። በፍጹም በዚህ አትጠረጠርም ። የምትደብቀኝ ነገር የለም » ሲል ወደ ጀመረው ሀሳብ ተመለሰ ።

ከሁለት ቀን በኋላ ያሬድና ተሾመ ከሥራ መልስ በረንዳ ላይ ወንበር አስመጥተው ቁጭ ብለዋል ። ተሾመ በቀደም ከያሬድ ተለይቶ እንደሄደ አንድ የትምህርት ቤት ጓደኛውን አግኝቶ ከቀኝአዝማች ጋር እንደተገናኙና ጉዳዩ ምን ደረጃ እንደደረሰ

ተነጋግረው ለእርብ በ12 ሠዓት ያሬድ ቤት መጥተው ፊት ለፊት በጉዳዩ ላይ ውይይት ለማድረግ እንደሚሹ አስረዳው ። ጉዳዩም በሰላም እንደሚያልቅ መምሩ ገዝሙ የሚባል እዚያው የነበረ የተሾመ ጓደኛና ሌሎች ሁለት ሽማግሌዎች አብረውት እንደሚመጡ በዝርዝር አጫወተው ።

« ወይ ጉድ እኔ ምን መሆኔ ነው ወደ እኔ የሚመጡት አክስቷ እሉ አይደለም ? እሳቸው ዘንድ አይሄዱም እንዴ ? እኔ እኮ የትናንት ሰው ነኝ ። እንደምታውቀው ከእኔ ጋር እንድትኖር ያደረግሁት . . . . » ብሎ የታወቀ ነገር መድገሙ እንደማያስፈልግ በመገንዘብ በእንጥልጥል ተወው ።

« ያሬድ አሁን እንደ አዲስ አትሁን ። በቀደም ስለ ሰዎቹ ማንነትና በከተማው ስላላቸው ተሰሚነት ተነጋገረንበት አልፈናል ። በውድ ካልሆነ በግድ ብለዋል ። እሱ ደግሞ መሆን እንደሌለበት ሁለታችንም ተስማምተናል ። ስለዚህ ውይይቱ አንድ መፍትሄ ሳይሰጠን አይቀርም ። ምናልባትም ማን ያውቃል ነገሩን ይተውት ይሆናል » አለ ተሾመ ያሬድን ለማግባባት በእጁም በጭንቅላቱም ንቅናቄ እያሳየ ።

« እንዳልከው የማይጋፉትን ባለጋራ መጋፋቱ አያዋጣም ። ግን . . . » ብሎ እቀመ ያሬድ ፤ ሊናገር ያሰበው እንደጠፋበት አፉን ከፍቶ ቀረ ። « የሽማግሌዎቹ መገኘት ነው ያልገባኝ እነሱ ደግሞ ምን ሊፈጥሩ ነው ? »

« ሽማግሌዎቹማ » አለ ተሾመ ቀለል በማድረግና በፈገግታ « አንተ ዘንድ ነው የሚመጡት ፤ ሊያግባቡህ ። ሰዎቹን እንኳን እኔ እንድመርጥ ዕድል ተሰጥቶኛል ። ድንገት የአንተና የሒሊና ምክንያት አይሎ ዕርዳታ ቢያስፈልጋችሁ ብዬ የሚያስማሙን ሰዎች እንዲመረጡ አድርጌአለሁ ። » ያሬድ የአገሩ ሰው ባለመሆኑ ለጥቃት እንደተዳረገ በመገመት በጣም አዘነ ። ዓይኑ እያየ ሒሊናን

ሊያስነጥቅ፣ ይህችን ውብና ለግላጋ አስተዋይና እሩህሩህ ልጅ ለማይገባ ሽማግሌ አሳልፎ ሊሰጥ ነው ። አማራጭ አልነበረውም ። የነገው ውይይት የመጨረሻ ዕድሉን የሚሞከርበት ይሆናል ። የሒሊና የወደፊት ዕድል የሚወሰንበት እንደሚሆን በመቁጠር ተሾመ የራሱን ሀሳብ አውጠነጠነ ። ተሾመ ከቀኝአዝማች ጋር የተስማማበትን ቀጠሮ በእሽታ ነበር የተቀበለው ። እርብ በ12 ሰዓት ያሬድ ቤት ተባብለው ነገሩን ጨርሰዋል ።

ለሞኑን ያለማቋረጥ የአቃቂን ከተማ ሲያዳርስ የነበረው ዝናብ ጭው ባለ ፀሐይ ተተክቷል ። ጭቃው ደርቆ መንገዱም እንደልብ ያስኬዳል ። የያሬድ ቤት መግቢያ ያለ ችግር ያራምዳል ። ያሬድ ቀደም ብሎ ከሥራው ተመልሶ እቤት ነበር ። ከጎረቤት ሁለት ወንበሮች አስመጥቶ በእንግዶቹ ልክ መቀመጫ አዘጋጅቷል ። ሳሎኑ በሰንደል ሽታ እንዲታወድ ተደርጓል ። ሒሊና ቤቱን ስትጠራርግና ስታስማምር ዋለች ።

« ጋሼ ያሬድ እንግዳው የሚመጣው ከአዲስ አበባ ነው ወይስ ከዚሁ ? » አለችው ።

« ከአዲስ አበባ እንኳን አይደለም ሌሎች እንግዶች ናቸው ከመ/ቤት የሚመጡት » አላት በደፈናው ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እንግዶቹ ቤቱን ሞሉት ። ተሾመ ያሬድን ከቀኝአዝማችና ከሌሎችም ሽማግሌዎች ጋር አስተዋወቀው ። እብዬ ጋሻዬ ከእንግዶች ጋር እኩል አልገቡም ነበር ። ከያሬድ ቤት ትንሽ ራቅ ብሎ ከሚገኘው ቡና ቤት አረፍ ብለው ሽማግሌዎቹን መጠበቁን መርጡ ። ከሽማግሌዎቹ አንዱ አብዬ ጋሻዬ መምጣት እንደሚገባቸው ሲናገሩ ሰው ተልኮባቸው ካሉበት ተጠርተው ከሽማግሌዎቹ ጋር ተቀላቀሉ ። ነገሩ ግራ የገባቸው ሽማግሌዎች በዝምታ እርስ በእርሳቸው መተያየት ጀመሩ ። ቀኝአዝማች ረዥም ቁመናቸውን አግዝፈው ተነስተው ድምፃቸውን ለንግግር ሳሉና ፤

« እንግዲህ ወንድሞቼም ልበላችሁ እህቶቼ የተሰበሰብንበትን ዝርዝር ምክንያት በመግለጽ ጊዜ ላጠፋ አልፈልግም ። ሁላችሁም ነገሩን በጭምጭምታ የሰማችሁት መሰለኝ ። አባቶቻችን የመከረ ጊደር ምክር ያጣ ወይፈን ገዛ ይላሉ ። መምከር ማስመስከር አግባብ ነው ። ውጤቱም ጥሩ ነው ብለን ነው ዛሬ መገናኘታችን ። እንደምታውቁት . . . » ቀኝአዝማች ዞር ብለው በአገጫቸው አብዬ ጋሻዬን እያመላከቱ « እዚህ አቃቂ ሰረጅም ጊዜ ነዋሪ የሆነና በርስቱ፣ በፀባዩና በዘሩ የተከበረ የሰው ልጅ መካሪና አስታራቂ በመሆንም በቀደምትነት የሚጠራ ሰው ነው ። ታዲያ ይህ ሁሉ ሞልቶ ተርፎለት ዘሩን የሚቀጥሉለት ሴት ልጆች ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ሞልተውት ሳለ እንዲያው ቤቱን የሚያከብርለትና ወራሽም ሆኖ ታሪኩን የሚያስጠራ ወንድ ልጅ ሞክሮ ሞክሮ አልተሳካለትም » በማለት የተሰበሰቡበትን ምክንያት ሲተርኩ ከውጭ « የአቶ ያሬድ ቤት ነው ? » የሚል የሴት ድምጽ ተሰማ ።

ቀኝአዝማች የሰሙት ድምጽ የማን መሆኑን ለማረጋገጥ ወደ በሩ አንገታቸውን አቅንተው ሲመለከቱ ወደ ቤት በመግባት ላይ የሚገኙትን የአብዬ ጋሻዬን ባለቤት ወ/ሮ ይትባረክን አዩ ። ተከትላም አንጋፋዋ የአብዬ ጋሻዬ ልጅ ትዕግሥት ገባች ።

የቀኛዝማች ዓይን ፈጦ የሚመለከቱት እውነት ነው ወይስ ህልም ነው የሚል ይመስላል ። ረጅም ሰውነታቸው ወደ አንድ ጎን አዘንብሎ ሲወድቅ ተዳርሷል ። ብዓይናቸው የአብዬን ዓይን ፈለጉ ። አብዬ ጋሻዬ ዓይኖቻቸው ፈጠው ፣ ላባቸው በግንባራቸው ቸፍ ብሎ፣ ከንፈራቸው ደርቆ ፣ የተከሰተውን ትርዒት ይመለከታሉ ።

« ቀጥል እንጂ ቀኝአዝማች ! ወይስ ያበቀልከው የእንጨት ሽበት ነው ። መች አጣሁት ? ከ25 ዓመት ባለቤቴ ጋር ልታስያየኝ ከዚህ በፊትም ስትዶልት ነበር ። ያ ባይሳካልህ አሁን ደግሞ አሥር ልጆች እቤት ውስጥ አፍስሶ ሌላ የልጆቹን እኩያ እንዲያገባ ላይ

እታች ስትል ትንሽ አታፍርም በማለት ቀኝአዝማች ላይ አፈጠጡባቸው » ።

ወ/ሮ ይትባረክ የአብዬ ጋሻዬን የአሰፈ ታሪክ በየቦታው መወሸማቸውንና በዚህ ዕድሜያቸው የሚያደርጉትን ዝሙት ለተሰበሰበው ሲናገሩ አንድም ሰው ለመመለስ አልሞከረም ። ወ/ሮ ይትባረክ የዛሬውን ሁኔታ እንዴት እንደተጠነሰሰና ማን እደጠነሰሰው መናገር ሲጀምሩ ዕንባቸውን ሲያግዱት አልቻሉም ። ሳግ ወረሳቸው። ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ። ትዕግስትም ከነበረችበት ተንደርድራ አባትዋ ጉልበት ላይ ተንበርክካ መሪር ለቅሶ አሰማች ።

ያሬድ የመኝታ ቤቱን በር ተደግፎ ትርዒቱን ሲመለከት ከቆየ በኋላ በመጨረሻ የሰዎቹን ሁኔታ በውስጡ ለመሸከም ትዕግሥቱን ጨረሰ ። ብሶቱ ገነፈለበት ።

« አባቶች ከእናንተ የበለጠ ባላውቅም ከነገሩ ፊር ማጣት ከጓደኛዬ ከተሾመ ጋር ስንከራከርበት ነበር የከረምነው ። ይህችን ገና እንቡጥ የሆነች ልጅ ያህይወት ታሪክ በከተማው እንደሰማችሁት ወይም እናንተ እንደምታውቁት አይደለም ።

ሕሊና . . . » ብሎ ስለ ሕሊና ትውልድ ዕድገት ፣ ስለ ቤተሰቦችዋ ሁኔታ የሚያውቀውን ሁሉ በዝርዝር አስረዳ ። አብዬ ጋሻዬን ሊደግፉ የመጡት ሽማግሌዎች አንገታቸውን በመነቅነቅና በሀዘኔታ ነበር ያዳመጡት ።

« እና ይህች ልጅ ለእሷም ሆነ ለወገኗ የምትጠቅመው እኩያዋ ያልሆኑ ሰው ፣ ያስዕድሜዋ አግብታ ሳይሆን ከራስዋ አንደበት ለመስማት እንደምትችሉት ተምራና እራስዋን ችላ ፣ ፍቅር ምን ማለት እንደሆን በውስጧ ስትረዳ ብቻ ነው ። የአባቷን አደራ ለመወጣት የቆረጠች ወጣት ናት ። ስለዚህ አባቶች ድፍረት አይሁንብኝና የእናንተን ልመና አልፈልግም ። ከዚህ አሳዛኝ ታሪክ

አንፃር እንድትፈርዱልኝ ወይም እንድትፈርዱብኝ ነው ልመናዬ » አለ ያሬድ ግንባሩ ላይ የወጣውን ላብ በመሀረቡ እየጠረገ ።

« ይህን አሳዛኝ የህይወት ታሪክ ሰምተው ምንስ ተጨማሪ ማብራሪያ ፣ ምንስ ጥያቄ ይኖረዋል ? እንዲህ ባለ ቅሌት ውስጥ እራሴን አግብቼ አላውቅም ነበር ። ዛሬ ግን ተሳሳትኩ » ብለው ማንንም ሳይመለከቱ በመጀመሪያ የወጡት ለተሾመ ቤት ያከራዩት አቶ ድንበሩ ነበሩ ። ሌሎቹም እንገታቸውን እንደደፉ ተከታትለው ወጡ ። ትዕግስትና ወ/ሮ ይትባረክ በስተመጨረሻ ያሬድን ተሰናብተው ሄዱ ።

ያሬድ በዚያን ቀን የተቀዳጀው ድል በሰፈሩ ተነዛ ። አብዬ ጋሻዬ ግን ከዕለቱ ጀምሮ የሞተው ልባቸው አላገገመላቸውም። በከተማውም አዘውትረው ከመታየት ታቀቡ ።

ምዕራፍ ሦስት

ወ/ሮ አባይነሽ ስለ መጥረቢያው ምስጢር በተዘዋዋሪ ከያሬድ አነጋገር ከተረዱ ወዲህ አንድም እሳቸውን ያህል ሰው በአንድ አልባሌ ዘበኛ መታለሉ ፣ ይበጀኛል ብለው የሰሩት ደባ በሥሩ እንዲተዳደሩ ስለአደረጋቸው በጣም ፀፀታቸው ። አዋቂ ነኝ ባዩ ጠንቋይ የማነብርሃን አረክሳለሁ፣ አወግዛለሁ በማለት የወሰደው ገንዘብ እንደ እግርእሳት አቃጠላቸው ። ምስጢሩ ይፋ ከሆነላቸው በኋላ ደግሞ ለፀፀትም ለመቃጠልም ቦታ አጡ ። መበቀል አሰባቸው ። ሁሉም የእጃን ማግኘት አለበት ። እቅድ አወጡ ። በመጀመሪያ ፈሩቅ የገዛቸውን ጓደኞቹን ማሸነፍና በቁጥጥር ሥር ማዋል ። ከዚያ በኋዋላ እሳቸው ያውቁበታል ። ፈሩቅን ማጅራቱን መቶ መጣል ነው በቃ-ግልግል ! እስከዚያ ፈሩቅን ማባረር እንደሌለባቸው አምነዋል። ለዚያውም ቢሆን ጠባቂ ያስፈልጋቸዋል ። ፈሩቅን የሚያሸንፍ ሰው አሰቡ ። ግን ማን ይታመናል ? ከፈሩቅ ወዲህ ሰውን ማመን አይቻልም ። ሌላ አማራጭ አገኙ ። ሽጉጥ ገዝተው ተለማምደው ራሳቸውን ለመጠበቅ ወሰኑ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ለዝግጅታቸው ጊዜ አላባከኑም ። በደላሎች አማካኝነት አንድ ኮልት ሽጉጥ በሺህ ሁለት መቶ ብር ገዙ ። አንድ ጡረተኛ ወታደር በምስጢር ቀጠሩና ልምምዱን ጀመሩ ። ቃታ አሳሳቡን ፣ የሽጉጥ ጥይት አጎራረሱንና ፣ ማነጣጠሩን ሲያጠኑ ቆይተው ፣ በመጨረሻም በድብቅ ከከተማ ወጥተው የተግባር ልምምድ አደረጉ ። ቀጥለው ከፈሩቅ ጋር የሚያያይዟቸውን ገመዶች መበጣጠስ ያዙ ። አዲስ አበባ ሄደው ለድስት አስተናጋጆች ይዘው ተመለሱ ። የቡና ቤቱን በር ዘጉ ። ከቀድሞዎቹ የቡና ቤት

አስተናጋጆች መካከል ከሁለት ሰዎች በስተቀር ሌሎቹ ሂሳባቸውን እንዲያስረክቡ አደረጉ ። ሰራተኞቹም እየተደረገ ባለው ሁኔታ እየተደናገጡ ያለባቸውን ሂሳብ አስረከቡ ። « በሉ በጣም ነው የማመሰግናችሁ ። በጉልበታችሁ ረድታችሁኛል ። ከዛሬ ጀምሮ ግን እንድትሰሩልኝ አልፈልግም ። አሰናብቻችኋለሁ » ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ።

« መሄድስ እንሄዳለን ሸፌሮች ብቻ አይደለም ቡና ቤት ዕድሜ ሰጉልበታችን ወጣቶች ነን ደሞዛችንን ይስጡን ። » በማለት አንዷ አስተናጋጅ አፈጠጠችባቸው ።

« ቦኔ የናንተን ደመወዝ የማስቀር ሰው አይደለሁም ። ነገ ኑና ውሰዱ ። አልጠፋም ቤት ንብረት ያለኝ ሰው ነኝ ። » ብለው እያጣደፉ ሸኟቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ በዚህ ስልታቸው የፈሩቅ ቅምጦች ናቸው ብለው የጠረጠሯቸውን ሴቶች ከቡና ቤት አሰናበቱ ። ፈሩቅ በቤት ውስጥ የሚደረገውን ድርጊት በቅርቡ እንዳይከታተል የሩቅ መነጽሩን እንደቀሙት አድርገው ቆጠሩ ። አዲስ ቀጥረው ያመጧቸውን ሴቶች በተባረሩት ምትክ አሰማሩ ።

« ከእኔ በስተቀር ለዚህ ቡና ቤት ኃላፊ የለም ። የሚያስፈልገውን ነገር እኔን መጠየቅ ትችላላችሁ ። ማንም ሰው መጥቶ እኔ ነኝ ኃላፊ ብሎ ቢያጭበረብራችሁ በኃላፊነት ትጠየቃላችሁ » በማለት ግልጽ ትዕዛዝ አስተላለፉ ። አስተናጋጆቹም ለአዲሱ ሥራቸው ያመቻል ያሉትን ጌጣ ጌጥና ልብስ ለብሰው ወደ ሥራ ገበታቸው ተሰማሩ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ሳሎን ሄደው ጥቂት ቆይታ አድርገው ፣ አንድ በጨርቅ የተጠቀለለ ነገር ይዘው ቡና ቤታቸው ገቡና በገንዘብ ተቀባይ ባንኮኒ ተሰየሙ ። ቡና ቤቱ በአዲሶቹ ሠራተኞች ተወሯል ። አመሻሹ ላይ አዲሶቹ አስተናጋጆች በወ/ሮ አባይነሽ ፊት ምን ያህል ተወዳጅ እንደሆኑና ቅልጥፍናቸውን ለማሳየት በቤቱ ውስጥ

እንደዕንዝርት በመሽከርከር ደንበኞቻቸውን ማስተናገዱን ተያያዙት ። በወረት አዲስ ፊት ለማየት የተኮለኮለው ደንበኛም የቡና ቤቱን ገበያ አደራው ።

ወ/ሮ አባይነሽ ከቀድሞው በበለጠ ፈገግታ ደምቀው ገቢውን በመቀበል ወጪውን በመሰናበት ቤቱን ከዳር እስከዳር ይቃኛሉ ። ለአንድ አፍታም ቢሆን ከተቀመጡበት ወንበር አልተነሱም ። ሳይሰለቹ በዚሁ ሁኔታ ቡና ቤታቸውን ሲመሩ አመሹ ። ጊዜው መሽቶ ደንበኞች በሙሉ ከወጡና ቤቱ ባዶ ከሆነ በኋላ ወደመኝታ ክፍላቸው ሲያመሩ በጨርቅ የጠቀለሉትን ነገር ጠበቅ አድርገው ይዘው ነበር ።

* * *

ለያሬድ ይህ ሳምንት የፈተና ጊዜው ሆኖበታል ። ከአብዬ ጋሻዬ ጋር ቁርጥ ያለ ውይይት አድርጓል ። በዚህ ጉዳይ ከሕሊና ጋር ተግባብተዋል ። የቀረው ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ስለሚያደርገው ድርድር ከሕሊና ጋር ለመወያየት መቻል ነበር ። ያሬድ ለሕሊና ደፍሮ ለመንገር አልቻለም ። ቢሆንም አንድ ምሽት ደፈረ ። ጊዜው መሽቶ ሕሊና ኩሽና ውስጥ ለእራት የሚሆን ምግብ በማበሳሰል ላይ ነበረች ። ወደ ቤት ስትገባ ያሬድ ከከረጢቷ ውስጥ የአባቷን መጥረቢያ አውጥቶ ፣ አልጋዋ ላይ አስቀምጦ ፣ ወንበሩን ወደ አልጋዋ አዙሮ ፣ ዓይኖቹን መጥረቢያው ላይ ተክሎ ሲመለከት አገኘችው ። በሁኔታው በመደናገጥ መለስ ሰውነቷን ወደ ሳሎን ሳታስገባ በሩ ላይ ቆማ አስተዋለችው ። ያሬድ ፊቱን ሳያዞር ወደ መጥረቢያው እየተመለከተ « ሕሊና ግቢና ተቀመጭ » አላት ። ምንም ድምጽ ሳታሰማ ወንበር ስባ ከያሬድ በስተጀርባ ተቀመጠች ።

« ሕሊና አባትሽን በጣም ትወጃቸው ነበር ? » ሲል ጠየቃት።

« እንዴት ማለት ትወጂያቸው ነበር ስትል ? አሁንም እወደዋለሁ » አለችው አጠያየቁ ግራ ገብቷት ::

ያሬድ ፊቱን ወደ ሕሊና መልሶ ፣ « አይዞሽ አትፍሪ » በማለት ፈገግ አለና ፣ « አባትሽ በጣም ጥሩ ሰው ነበሩ :: የዚያ የሰይጣን ሀሳብ ባይረብሽን ኖሮ ዛሬ ላነጋግርሽ ያሰብኩት ስለ አንድ ጉዳይ ነበር :: ሆኖም አሁንም ዝም አልልሽም :: ልንወያይ እንችላለን » በማለት አልጋው ላይ የተቀመጠውን መጥረቢያ አነሳና ለሕሊና ሰጣት ::

መጥረቢያውን እንደ ቀድሞዋ በደስታ ወዲያውኑ አልተቀበለችውም :: ፍርሃት በተሞላበት አመለካከት እያየች ሁለት እጆችዋን ቀስ ብላ ዘረጋችና የመጥረቢያውን እጀታ በዓይኖችዋ ከላይ እስከታች ዳሰሰች :: ያሬድ የሕሊናን ድርጊት በማስተዋል ከመጥረቢያው ላይ ዓይኑን ሳያነሳ ፣ « ሕሊና በጠረጴዛው ላይ አስቀምጪው » አላት :: በጥንቃቄ የተባለችውን አደረገች ::

« ጋሼ ያሬድ ያለፈው አለፈ :: ጉዳዩን ሁሉ ሳትረዳ አልቀረህም :: አሁን ደግሞ ምን አደረግሽ ልትለኝ ነው ? » ዓይኖችዋን በልመና መልክ ዕንባ ሞልታ በያሬድ ዓይኖች ላይ አሳረፈች ::

ያሬድ በሀሳቡ « አይ ሕሊና እነኚህ ውብ ዓይኖችሽ ሲያለቅሱ የኔ ልብ ይደማል እባክሽ አታልቅሺ :: ፈገግታሽ ለሰውነቴ ሙቀት ለማንኛውም በሽታዬ መድኃኒት ነው :: እባክሽ ሕሊና ካንቺ ዓይን ጠብ ጠብ የሚሉት ዘለላ እንባዎች ከኔ ልብ እንደሚፈስ ደም ነው የምቆጥረው :: » በማለት ሳያስበው ብድግ ብሎ ወደ ሕሊና ጀርባ ዞረ:: ከበስተጀርባዋ ሆኖ በእጆቹ የሕሊናን አንገት ዳሰስ አድርጎ አቀፋት እሷም እጆቹን ከእጆችዋ ጋር በማጣመር ወደ ደረቷ አስጠግታ ያዘቻቸው :: ለሕሊና የመንፈስ ጭንቀት የያሬድ አጠገቧ መኖር ወሳኝ ነበር :: ዓይኗ ላይ ያቀረረው እንባ ተመልሶ ተዋጠ ::

ፍም መስሎ ደም ሊተፋ የደረሰው ጉንጭዋ እየፈካ መጣ :: አንገቷን ወደኋላ መለስ አድርጋ ከላይዋ ላይ የቆመውን ያሬድን ፈገግ በማለት አስተዋለች ::

« ምንድነው ተናገር እንጂ ለምን ዝም ትላለህ ? » በማለት እጆቹን በእጆችዋ ዳሰሰቻቸው ::

« ሕሊና አትቀየሚኝ ዋሽቼሻለሁ :: ዛሬ ከአዲስ አበባ የሚመጡ እንግዶች ብዬ የነገርኩሽ እነማን እንደነበሩ አይተሻል :: ይህ አንደኛው ውሸት ነው » ብሎ እንደገና አንገቱን ዝቅ አድርጎ የሕሊናን ዓይን በመፈለግ ዓይነት ተመለከተ ::

« አልቀየምህም ተናገር :: ለዚህ ነው አባቴን ያስታወስከው?» ስትል ፈገግ አለች:: ያሬድ እጆቹን ከሕሊና እጆች ላይ የግዱን አላቆ ፊት ለፊቷ ያለው ወንበር ላይ ተቀመጠ ::

« ሁለተኛው ውሸት ደግሞ ሕሊና በቀደም እሁድ አትሂድ ያልሽኝ ቦታ ሄጃለሁ :: » በማለት ቀና ብሎ ተመለከታት ፣ እራሱን በቀኝ እጁ እያሻሸ ::

« እህ . . . እናስ ? » ስትል በድንጋጤ ጠየቀችው :: ፊቱ ከመቅጽበት ጨለመ ::

« ሕሊና ጉዳዩ ፈፅሞ አንቺ እንዳሰብሽው አይደለም :: አክስትሽ የጋበዙኝ ምሳ ለመብላት ሳይሆን ከአንቺ ጋር እርቅ ለመደራደር ነው » አላት ፍርጥም ብሎ ::

« እርቅ ? ይህ ዘዴ ደግሞ መቼ ተከሰተላቸው ? መቼም ከዚህ ሀሳባቸው በኋላ ሌላ ዕቅድ ይኖራቸዋል :: ታዲያ አንተ ምን ብለህ መለስክላቸው ? » ስትል ጠየቀችው ::

« መቼም ያልደረደሩት ምክንያት አልነበረም :: የለቅሶውን ነገር ተይው :: በመጨረሻም እራሳቸውን ስተው ታመሙና ለሌላ ጊዜ ተቃጥረን ተለያየን » ሲል አስረዳት :: የሰማችውን በጥሞና

የምታዳምጥ መስላ ዓይኗን ፊት ለፊት የተጋደመው መጥረቢያ ላይ ተክላ ተመለከተች ::

« እ . . እ . . . ምን አልከኝ ? ጋሼ ያሬድ » በማለት አስተዋለችው :: የሕሊና ሀሳብ በምን ላይ እንዳተኮረ ለማወቅ አላዳገተውም :: መጥረቢያው ! ሕሊና እንኳን በግልፅ ፊት ለፊቷ ተቀምጦ ቀርቶ በከረጢትም ውስጥ ሆኖ ጫፉ ከታየ ሀሳቧ ከሱ ጋር እንደሚሆን ካወቀው ቆይቷል ::

« ወ/ሮ አባይነሽ በእውነትም ባደረጉት ጥፋት ተፀፅተው ከልባቸው ይቅርታ የሚጠይቁ ከሆነ ከአባትሽ የወረስሽው ደግነት እንዲታሰብሽ ስል ነው መጥረቢያውን ያወጣሁት :: ሕሊና ፣ ከይቅርታ በስተቀር ወ/ሮ አባይነሽ ከእንቺ የሚፈልጉት ነገር አይኖርም :: ሕሊና ወ/ሮ አባይነሽ በበሽታ የታጠሩ ይመስለኛል :: ምናለ በጥፋታቸው ይቅር ብትያቸው ? » አላት በልመና ዓይነት ከአንገቱ ጋደል ብሎ አትኩሮ እያስተዋላት ::

« ጋሼ ያሬድ ከዕለታት አንድ ቀን አባቴ ፣ ደግነት ፣ ሀቀኝነት ሁሉም በቦታቸው ሲደረጉ ብቻ ነው ትርጉም የሚኖራቸው፤ ያለቦታቸው ከተጠቀምንባቸው ትርጉማቸው ሞኝነት ይሆናል ብሎ ነግሮኝ ነበር :: » አለችና ከተቀመጠችበት ተነስታ መጥረቢያውን በእጇ እየዳሰሰች « የእኔ አክስት ላደረሱብኝ ጥፋት ከእኔ ይቅርታ ቢያገኙም የሞቱትን ግን ይቅርታ ሊጠይቋቸው አይችሉም :: የእኔ ይቅርታ ብቻውን ሠላም ሊሰጣቸው መቻሉን እጠራጠራለሁ :: ከእኔ በበለጠ ግፍ የተዋለባቸው እሱ :: በእርግጥ እሁን በህይወት የሉም :: ለዚህም ነው የሞቱትን ይቅርታ ለመጠየቅ ባለመቻላቸው ቋሚውን በራሳቸው ጭንቀት ግፍ ሊውሉባቸው እንዳች ነገር የሚያስገድዳቸው:: ጋሼ ያሬድ ባንተ ስም ስለመጡብኝ እኔ እራሴ ብቻ ይቅርታ ላደርግላቸው ዝግጁ ነኝ :: ሆኖም የእኔና የእሳቸው ግንኙነት እንደ ቀድሞው ሊሆን አይችልም :: የቀድሞውን ከሞቱት

ሰዎች ጋር አንድ ላይ ቀብረውታል » በማለት እራስዋን ቀና አድርጋ እጆችዋን ከመጥረቢያው ሳትለይ ያሬድን እያየች ፈገግ ብላ ቀረች ::

ያሬድ የሕሊናን አነጋገር በተመስጦ ነበር ያዳመጠው :: በሰጠችው ቃል ፍላጎቱ በመርካቱ ፊቱ ፈካ :: « ሕሊና በጣም ደግ ሰው ነሽ :: ለእኔ ብለሽ ለወ/ሮ አባይነሽ ይቅርታ ማድረግሽ በእኔ ዘንድ እንደ ትልቅ ውለታ ነው የምቆጥረው :: አመሰግናለሁ ! » ብሏት ከመቀመጫው ብድግ ሲል ፣

« ጋሼ ያሬድ » በማለት ጠራችው :: ዓይን ዓይኑን እያየች « እንግዲህ ሁሉንም ባንተ በኩል ፈፅመው :: እኔ ከእሳቸው ጋር ዓይን ለዓይን መተያየት አልፈልግም :: » አለችው ::

እራሱን ቀስ ብሎ በመነቅነቅ መልስ ሰጣት :: ሕሊና ተመልሳ የአባቷን መጥረቢያ በፍቅር ተመለከተች :: ዓይኗ እንባ አቀረረ :: በማይሰማ ድምፅ ከንፈሯን አንቀሳቀሰች :: ከከባድ ሥራ እንደተመለሰ ሰው « እፎይ » ብላ በረጅሙ ተነፈሰች :: ያሬድ የቀን ሸክሙን ካራገፈ በኋላ ቀለል ስለአለው ወደ መኝታው ገብቶ አልጋው ላይ ጋደም አለ :: ፊቱ እንደፈካ እንቅልፍ ሸለብ አደረገው ::

ሕሊና ሥራዋን እንደጨረሰች ከነልብሷ መኝታዋ ላይ ጋደም ብላ ክንዷን ተንተርሳ ሳለ የያሬድን ንግግር ማሰላሰል ጀመረች :: ወሰን የለሽ ደግነቱን በማድነቅ በአባቷ ምትክ ይሁን ሰው በማግኘቷ በጣም ደስ ተሰኘች :: ያሬድ ተቀምጦበት የነበረውን ወንበር ፈገግ ብላ መልከት አደረገችና ቀስ ብላ ልብሷን አወላልቃ የእንቅልፍ ጉዞዋን ጀመረች ::

* * *

ወ/ሮ አባይነሽ ያሰቡትን ቅድመ ዝግጅት ያጠናቀቁ ቢሆንም የፈሩቅ ሽታ በአካባቢው ሲገኝ አልቻሉም ። ፈሩቅን ለማየት የነበራቸው ጉጉት በጣም ከፍተኛ ነበር ። ሆኖም ይህ ጉጉት ቀደም ሲል በፍቅር ዘመናቸው የነበረው ዓይነት ባለመሆኑ ለዓመታት ሲያስፈራራቸው የነበረውን ሰው ለመገላገል መሻት ነበር ጉጉታቸው፡፡ በቤታቸው ውስጥ የፈሩቅ ሽርክና ያላቸውን ወንዶችና ሴቶች ሠራተኞች አባረዋል ። ቀደም ሲል ፈሩቅን በመፍራት ሽሽተዋቸው የነበሩ ወዳጆቻቸውን እራሳቸው ፈልገው ግንኙነቱን እንዲቀጥል አድርገዋል ። ከውጫዊ ለውጥ ሌላ በራሳቸው ላይም ውስጣዊ ለውጥ ተቀዳጅተዋል ። የድሮው ልክ የሌለው ፍርሀት ወሰን በሌለው ድፍረት ተለውጧል ።

ሲጠብቁት የነበረው ቀጠሮአቸው ጊዜው ደርሷል ። መሰናዶዋቸውን ለማሰናዳት እጅግ ማልደው ነበር የተነሱት ። ያሬድና ተሾመ በቀጠሮው ሰዓት ሳሎን ተቀምጠዋል ። ወ/ሮ አባይነሽ በቤት ውስጥ ወዲያና ወዲህ ሽር ጉድ እያሉ የሚበላና የሚጠጣ ለእንግዶቹ ከማቅረብ ያለፈ ነገር ብቻቸውን ለማድረግ አልደፈሩም ። የነፍስ አባታቸው ያስፈልጓቸዋል ። ከቀጠሮ ሰዓት አንድ ሰዓት ያህል አሳልፈዋል ። ጭንቀት ቁጭ ብድግ አደረጋቸው ።

« ሂጂና አባን ምነው ሰዓቱ አልፏል ይምጡ እንጂ ብለሽ ጥሪያቸው ። ጎሽ ! እየጠበቅናቸው ነው » ሲሉ ካብትሽን ላኳት ። አባ ጊዜ ያጠፉ አይመስሉም ። ካብትሽን አስከትለው ከተፍ አሉ ። ወዲያው ሲደርሱ ሳሎን እንደገቡ ፤ « ትልቅ ይቅርታ ፤ ከቤተክርስትያን እንደገባሁ አንድ ዘመዴ የሆነች ሴት ቤት ውስጥ ስለቆየችኝ እሷን ለማነጋገር ብዬ ነበር የዘገየሁት ። » ሲሉ ይቅርታ

ጠይቀው የተለመደ ሐይማኖታዊ ሠላምታቸውን አድርሰው ተቀመጡ፡፡ ወ/ሮ አባይነሽ ለነፍስ አባታቸው የሚጠጣ አምጥተው ፤

« አባ ቁርስ አድርገዋል ? » ሲሉ ጠየቋቸው ፤ በማቅማማት፡፡

« እናንተ በላችሁ እንጂ ? » አሉና ፤ « መቼም ቁርስና ዶሮ በጠጣ ቁጥር መብላት ይወዳል ። በይ እስኪ አምጪው ለውሃው አይከፋም » በማለት ጋቢያቸውን ማስተካከል ጀመሩ ። በመጀመሪያ እነ ያሬድ መብላት አልፈለጉም ነበር ። ወ/ሮ አባይነሽ በማሪያም በመማፀን አስገደዷቸው ። ከዚያ በኋላ የሚግደረደር አልነበረም ። በተሰይ ወ/ሮ አባይነሽ አዲሶቹን እንግዶች የታቦት ስም እየጠሩ በጉርሻ እያስጨነቁ ጋበዟቸው ። ከቁርስ በኋላ አባ ወደ ዋናው ጉዳያቸው ተመለሱ ።

« ቀጠሮአችን መቼም ደጉን እንጂ ክፉን የሚያርቅ ይሁንና ፤ ልጅቷ ተጠይቃ መልስ ሰጠች ? » አሉት ያሬድን እያስተዋሉት ።

ያሬድ በእጁ የያዘውን ብርጭቆ በእጁ አሸት አሸት በማድረግ « ሕሊና በነገሩ ተስማምታለች ። ሁሉንም ነገር ነግሬአት ከጥቂት ማመንታት በኋላ በእርቁ የተስማማች መሆንዋን ገልፃልኛለች ። ይህንም ለእናንተ እንዳደርስ ፈቅዳለች » በማለት አበሰራቸው ።

« እሰየው ! እሰየው ! መልካም መልካሙን ያሰማን . . . » ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዘወር ብለው ፤ « እንኳን ደስ ያለሽ » አሏቸው ። ወ/ሮ አባይነሽም ፤ ከመቀመጫቸው ለአመል ያህል ብድግ ብለው አንገታቸውን ደፋ በማድረግ « በአምላክም » በማለት ተቀበሉ ።

« እንግዲህ ዋናው ነገር ካለቀ ዘንዳ እናትና ልጅቱን አገናኝቶ ማነጋገሩ አይከፋም ። ለዚህ እንግዲህ ሽማግሌም አያስፈልግም ። አንተው ትጨርሰዋለህ » በማለት ወደ ያሬድ አስተዋሉ ።

ያሬድ በነገሩ እያቅማማ « ዋናው መታረቁ ይመስለኛል ። መገናኘቱ ቀስ በቀስ ይሆናል ። » በማለት ወ/ሮ አባይነሽን ተመለከተ።

ወ/ሮ አባይነሽ አንገታቸውን እንደ ደፉ « አዬ . . . ኧረ. . . ለእሱ ግድ የለም ። ምን ይከናል ብለው ነው ? እሩቅም አይደል እዚሁ እያለን ከእንግዲህ እንጠያየቃለን » በማለት ሁኔታውን ማስማማት ጀመሩ ።

ያሬድ ሁሉንም ነገር ገልጾ ለመናገር አልፈለገም ። እንደ ሕሊና አባባል እርቁ ፍጹም እንዳልሆነ አድርጋ ነበር የተናገረችው ። በእሷ በኩል ይቅርታ ታድርግ እንጂ በወላጆችዋና በአስካበች ላይ የተዋለውን ግፍ የማትረሳ መሆንዋን ገልፃለች ። ያሬድ ይህን መናገር እንደመነሻ መልካም ነው ብሎ ያመነበትን ግንኙነት ማፍረስ እንደሚሆንበት ገመተ ። በመቆየት ቂም ስለሚፋቅ ቀሪውን ለጊዜ መስጠት እንደሚሻል አመነ ። ወ/ሮ አባይነሽ ያሰቡት ስለተሟላ በጣም በመደሰታቸው የመጠጡ ዓይነት ከቢራ ወደ ውስኪ እንዲቀየር ሀሳብ ሲያቀርቡ ያልተስማማው ያሬድ ብቻ ነበር ። አባ ብርጭቆአቸውን እየተመለከቱ « ይሻል ብለሽ ነው » በሚል ዓይነት ያስቀዱትን ጭልጥ አደረጉ ።

ያሬድ ብቻውን በቢራ ሲያዘግም ለሌሎቹ ጠርሙስ ውስኪ ቀረበና መኮምኮሙን ተያያዙት ። ጨዋታው እየደራ ቀደም ሲል የነበረውን የሥነ-ስረዓት ልውውጥ በቤተሰባዊ ሁኔታ ተለውጦ ሆድ ያባውን . . . እንዲሉ የዘወትር ፀባያቸውን ቀየረና የተደበቀውን ወጣ ማድረግ ጀመረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ፣ « የጋብቻ ዝምድና አለኝ » ብለው ከሚያምኑት ከያሬድ ጋር የሆዳቸውን ጨዋታ ከፈቱ ። እሱም የሚናገሩትን ሁሉ « እህ . . እህ . . » እያለ ማዳመጡን ተያያዘው ። በመካከል አንገታቸውን ወደ ያሬድ ለገግ አድርገው ምስጢር ለማውራት እንደሚጥር ሰው ፣ « አንተዬ አንድ ነገር እጠይቅሃለሁ

ብዬ አሁንም ሕሊና በዚያ መጥረቢያ ታመልካለች ? » ሲሉ የሚከነክናቸውን ጥያቄ ጠየቁት ። ያሬድም ይህን ጥያቄ ከወ/ሮ አባይነሽ እንደጠበቀው ሁሉ ከት ብሎ ሳቀና ፣

« አይ እማማ አምልኮት እኮ አይደለም » አለ ።

ወ/ሮ አባይነሽ « አምልኮ አይደለም ? » አሉት ። እራሳቸውን ወደ ጎን መለስ አድርገው በጉጉት እያስተዋሉት ፣

« ታሪኩ እንዲህ ነው ። በቀላሉ ፣ ሕሊና አባቷ ሲሞቱ ፎቶግራፍ አላገኘችም ። በእሱ ምትክ ያገኘችው መጥረቢያቸውን ነበር ። ይህ መጥረቢያ ከአባቷ ጋር ብዙ ጊዜ የቆየ በመሆኑ ስታየው የአባቷን ምስል ያስታውሳታል ፣ ይህ ጥንቆላ ወይንም አምልኮት አይደለም ። ማስታወሻ ማለት ነው ። እንደማንኛውም ወርቅ ፣ ልብስ ፣ ፎቶግራፍ ሊሆን ይችላል ። » በማለት አትኩረው የሚመለከቱትን ወ/ሮ አባይነሽን አስተዋላቸው ፤ የተናገረው ገብቶአቸው እንደሆነ ለማረጋገጥ በመፈለግ ዓይነት ።

ወ/ሮ አባይነሽ አፋቸውን ወደ ጎን በማጣመም እንደማሽሟጠጥ አድርገው « እሱስ አይደለም ፤ ቢቻል ማስጣል ነው። አምልኮት ባይሆን ኖሮ ይህን ያህል ከመጥረቢያ ጋር አጣብቆ የሚያንከራትታት ምን አለ ? » በማለት ጉዳዩን በቾልታ ለመጨረስ አሳጠሩት ። ንግግራቸው ለያሬድ አልተዋጠለትም ነበር ።

« ሕሊና አባቷን በጣም ነው የምትወደው ። በአባቷ የሚመጣባትን ሁሉ ትጠላለች ። ስለዚህም ነው መስለኝ ከእርሶ ጋር በአንዳንድ ጉዳዮች መግባባት ያልቻላችሁት » በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ የሚመስለውን ሀሳብ ገለጸላቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ ትንሽ አሰብ አደረጉና « ማን ዘመዱን የማይወድ አለ ? ሆኖም እኔ ምን ላድርግ ? አንድ እህቴን ከጉያዬ ፈልቅቆ የወሰደብኝ ስለሆነ አባትዋን መውደድ አልቻልኩም » ከማለታቸው ዓይናቸው እንባ አቀረረ ።

« በሕሊና ፊት ስለ አባትዋ ከተቻለዎት መጥፎ ነገር አለማንሳቱ ይመረጣል :: መጥረቢያውም ከዚህ የተለየ አይደለም » አላቸው ባለፈው እሁድ ያየው እንዳይደገም እየሰጋ ::

ወ/ሮ አባይነሽ በረጅሙ ተንፍሰው « መቼስ ምን ይደረጋል » ብለው ከመጠጡ ተጎነጩ :: አባና ተሾመ ስለሐይማኖት እንስተው በክርክር መልክ ያወራሉ :: አባ የታቦት ሥም እየጠሩ « ኧረ ይቅር ይበልህ » እያሉ ተሾመን ለማላመን ሲሞክሩ ተሾመም

« ሰውን እኩል አድርጎ ከፈጠረ ታዲያ ለምን ያበላልጣል ? » በማለት አባ ለሚሉት ሁሉ በተቃውሞ ይመልስላቸዋል ::

ጨዋታው ደርቶ ፣ መጠጡም እየተቀዳ ፣ ጊዜው እየመሸ መምጣቱን ያስተዋለ አልነበረም :: የመኪና ጡሩንባ ድምፅ የፈሩቅን መምጣት አበሰረ :: ወ/ሮ አባይነሽ የመሸበር ሁኔታ ሲታይባቸው በጉዳዩ ትንሽም ያልተደናገጡት ተሾመና ያሬድ ነበሩ :: የቀረበላቸውን መጠጥ በአንድ ትንፋሽ ጅው አድርገው ጨለጡና ብድግ ብለው ተሰናብተው ከቤቱ ወጡ :: ያሬድና ተሾመ ለመሄድ እንደተነሱ ወ/ሮ አባይነሽ « እባካችሁ ቆዩልኝ ይሄን ሰው ብቻዬን እንዳገኘው አልፈልግም » በማለት ተማፀኑዋቸው :: በሁኔታው ግራ የተጋባው ያሬድ ብቻ ነበር :: ተሾመ ጉዳዩን በጥቂቱም ቢሆን ከውጭ ሳይሰማ አልቀረም ::

« የትኛው ሰው ነው ? » በማለት ያሬድ እንደቆመ ወ/ሮ አባይነሽ ያልሰሙ መስለው ወደመኝታ ቤታቸው አመሩ :: ስለ ፈሩቅና ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ግንኙነት በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ ተሾመ ያሬድን ሊያስረዳው ሞከረ :: ያሬድ የሚሰማው ነገር እጅግም ሊገባው አልቻለም :: በኋላ ተሾመን « ተነስ እንውጣ :: ታዲያ እኛ ምን ቤት ነን ? » አለው :: በዚሁ መካከል ወ/ሮ አባይነሽ ከመኝታ ቤታቸው በትንሽ ነገር የተጠቀለለ አንዳች ነገር ይዘው ተመለሱ :: ያሬድ በሀፍረት ወደ መቀመጫው ተመልሶ ወ/ሮ አባይነሽ በእጃቸው

የያዙትን ጥቅል ነገር ተመለከተ :: ወ/ሮ አባይነሽ ወንበራቸው ላይ ሆነው አስር ጊዜ የሳሎናቸውን በር ይከታተላሉ :: ጭንቀታቸውና የሽብር ሁኔታቸው ለያሬድ ሠላም አልሰጠውም ::

« ምነው ተጣልታችኋል እንዴ ? » ሲል ለስለስ ባለ አነጋገር ጠየቃቸው ::

ወ/ሮ አባይነሽ የያዙትን የተጠቀለለ ነገር ጨበጥ ጨበጥ እያደረጉና ከንፈራቸውን እየጠራረጉ « መጣላትስ አይደለም :: ሆኖም ከእሱ ጋር እናንተ ባላችሁበት የምንነጋገረው ነገር ስላለ ነው » አሉና ዓይናቸውን ወደ በሩ ወረወሩ ::

ፈሩቅ መኪናውን አቁሞ ወደ ቤት ወዲያውኑ አልገባም :: በመኪናው ላይ የተጫነውን ዕቃ እንዲያወርዱ አጠገቡ ለቆሙት የወጥቤት ሠራተኞች ከተናገረ በኋላ በቀጥታ ወደ ቡና ቤት ነበር ያመራው :: በቡና ቤቱ ውስጥ ለውጥ መኖሩን ወዲያው ተረዳ :: ግራ በመጋባት የሚያውቃትን ባሬስታ ጠጋ ብሎ « ምን ተፈጠረ እባክሽ ? » በማለት ጠየቃት :: ሴትዮዋ ከፈሩቅ ጋር እጅግም ቅርበት አልነበራትም :: እንገቷን ከምትሰራው ሥራ ለአፍታ ቀና አድርጋ « ምን ተፈጠረ ? » በማለት ፈገግ አለችና « ለምቱን ነው ? ሄዱኮ ጋሼ ፈሩቅ » አለችው ::

ፈሩቅ በሁኔታው መደናገጥ ብቻ ሳይሆን በጣም ተናደደ :: በማይሰማ ድምፅ እያጉረመረመ በጓሮ በር እየተንደረደረ ወጣ :: ወደ ሳሎን ሲገባ ተሾመና ያሬድ ተነስተው ተቀበሉት :: ፈሩቅ ቀጥ ብሎ እንደገባ ከተሾመ ጋር የእጅ ሰላምታ ተለዋወጡ :: ፊቱን ወደያሬድ መለስ አድርጎ ከላይ እስከታች እየገላመጠው ያሬድን አስተዋለው :: እጁን ዘረጋለት :: ያሬድ በአድራጎቱ ሲበቀለው ቢፈልግም በግድ ስሜቱን ተቆጣጥሮ ጨበጠው :: ፈሩቅ ቀጥሎ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዞር አለና « ምነው ዛሬ ደግሞ ተክዛችኋል ? ውስኪ ተንተርሶ ትክዛ

በቤታችን ያልተለመደ ነገር ነው:: ምን ሆናችሁ ? » ብሎ ፊት ለፊት ባለው ፎቴ ወንበር ላይ ዘርፈጥ ብሎ ተቀመጠ ::

« እፎይ » ብሎ በረጅሙ ተንፍሶ በእጁ ከፀጉሩ እስከ ፂሙ ፊቱን ዳበሰ :: ወ/ሮ አባይነሽ በቀኝ እጃቸው ምስጢራዊ ዕቃቸውን እንደጨበጡ ፣ ፈሩቅ ላይ አፍጥጠው ባልተረጋጋ ስሜት « እሺ ሲወጣም ወጣሁ አይባልም :: ከየት ነው ደግሞ ብቅ ያልከው ? » በማለት የመግቢያ ንግግራቸውን ጀመሩ ::

ፈሩቅ የተፈጠረው ሁኔታ አዲስ ስለሆነበት ፣ ከዚያም በላይ እሰው ፊት ለመነጋገር ስላልፈለገ ፣ ለቀረበበት ጥያቄ ችላ ብሎ « ብርጭቆ የለም እንዴ ? » በማለት የውስኪውን ጠርሙስ ወደራሱ ጎተት አደረገው :: ወ/ሮ እባይነሽ የቀኝ እጃቸው የያዘውን ጥቅል ወደ ጉልበታቸው እያስጠጉ

« በመጀመሪያ የተጠየቅከውን መልስ ፣ለመጠጡ ትደርሳለህ» አሉት ::

« ደህናም አይደለሽ እንዴ ? ምን ተፈጠረ ደግሞ ? » አለና ወደ ያሬድ እየተመለከተ ፣

« ለጥያቄና መልሱ በኋላ እንደርሳለን ፤ አሁን እንግዶቻችንን እንሸኝ » ብሎ ብድግ አለ ::

« ተቀመጥ ! ባለህበት እንዳትንቀሳቀስ » ሲሉ ለረጅም ጊዜ እነ ያሬድ በጉጉት ሲጠብቁት የነበረውን ጨርቅ ከመቅስፈት ከላዩ ላይ እንደመግለጥ አደረጉት :: በእጃቸው የያዙት ጠቆር ያለ ሽጉጥ ነበር :: ያሬድና ተሾመ በድንጋጤ ከመቀመጫቸው ተነሱ :: ወ/ሮ አባይነሽ እነያሬድን በቁጣ መልክ « ተቀመጡ » ብለዋቸው የሽጉጡን አፈሙዝ ወደ ፈሩቅ አዞሩት « እንዳትንቀሳቀስ ! አለበለዚያ ደምህ ደመከልብ ነው የሚሆነው :: እኔ በዕድሜዬ ብዙ ደስታን ያየሁ ሰው ነኝ ፣ ባልፍም አይከፋኝም :: እምቢ የምትል ከሆነ አንድ ለእኔ አንድ ለአንተ :: » አሉት ፈሩቅን እየተመለከቱ :: ፈሩቅ ሲገልፀው

በማይችለው ስሜት ውስጥ እንዳለ ዓይኖቹን ወ/ሮ አባይነሽ ላይ ተከለ::

« ውሸት እንዳይመስልህ :: ይልቁንስ ያለምንም ደም መፍሰስ ሥራችንን ብንጨርስ ይሻላል » አሉት :: ሽጉጣቸውን በእጃቸው ጠበቅ እያደረጉ :: የነተሾመን ጭንቀት የተረዱ ይመስል « እናንተ ቁጭ ብላችሁ አዳምጡ :: ይህ ታሪክ እናንተንም ይመለከታል :: አትንቀሳቀስ ብየሃለሁ አንተ ወራዳ » ሲሉ ፈሩቅን በኃይለ ቃል አስጠነቀቁት :: ፈሩቅ በተቀመጠበት እየኮሰሰና የድሮ ቁመቱ እያጠረ፣

« የምን ቲያትር ነው ? አበድሽ እንዴ ? በመሣሪያ ጨዋታ የለም :: ይልቁንስ ባርቆብሽ እንዳታበላሽኝ » ሲል ተናገረ ::

« መባረቁን ተወው :: ስለዚህ የት ታውቃለህ ? እንከፍ ሳይባርቅ አዳፍንብሃለሁ :: ወስላታ ቀጣፊ ያ ምላስህ ከአንተ ተለይቶ አይሞትም » በማለት በርቀት ደረቱ ላይ ደገኑበት :: ፈሩቅ ተነስቶ እራሱን ለመከላከል ሙከራ አደረገ :: የወ/ሮ አባይነሽ ትዕዛዝ ከመሣሪያው የበለጠ ተሰሚነት ነበረው ::

« ተቀመጥ ! ተቀመጥ ነው ያልኩህ ወራዳ » በማለት እንደ ብራቅ ጮሁበት :: ለፈሩቅ ይህ አዲስ ፀባይ የእብደት ቢመስለውም ድርጊቱ ሁሉ ከመቼውም በበለጠ ወ/ሮ አባይነሽ ቆርጠው መነሳታቸውን አስገንዝቦታል :: በሁለት እጁ ራሱን ይዞ « ወይኔ ፈሩቅ ወንዱ መጫወቻ ሆንኩኝ » አለና ወደ እነ ያሬድ እጁን ዘርግቶ፣ « ምነው ሰዎች ዝም ብላችሁ ታያላችሁ ? ኧረ ገላግሉኝ » በማለት ተማፀነ ::

« አይዞህ እስከ መጨረሻው ትገላገለዋለህ :: በል አሁን በመጀመሪያ ስለ ሰረከው መጥረቢያ እስኪ ንገረን » አሉት :: ዝም አለ :: አፉ ተዘግቶ ምላሱ ተሳሰረበት ::

እራሱን ወደ መሬት አቀርቅሮ እጁን ደረቱ ላይ እንዳነባበረ አጎንብሶ ቀረ :: ወ/ሮ አባይነሽ የፈሩቅን ሁኔታ የተረዱ ይመስል

ጥያቄውን ቸል ብለው « ቤታችሁን የሰረሰረው ሌባ ይሄ ነው ። እኔንና ሕሊናን ለማጣላት ከመሠረቱ በነገር ሲያዋጋን የነበረው ይሄ ሾካካ ነው » አሉ ። ቀጥለውም ፈሩቅን በንቀት ዓይን እያዩ ።

« በል የመኪናውን ቁልፍ እዚያ ላይ ቁጭ አድርግ » ሲሉ አዘዙት ፤ በግራ እጃቸው ጠረጴዛውን እያሳዩት ።

« የየትኛውን መኪና ? መኪና ላይ ነው ያለው ። » አለ በግድ የተሳሰረ ምላሱን ታግሎ ። ወ/ሮ አባይነሽ ያሬድን ተነስቶ እንዲፈትሸው አዘዙት ። ፈሩቅ ባላወቀው ምክንያት ፊቱን ዞር አደረገ። ባልጠበቀው ቅፅበት በተሰነዘረ ጥፊ ፊቱ ነደደ ።

ያለምንም ማንገራገር ኪሶቹን አስፈተሸ ። የመኪና ቁልፍ ግን አልተገኘም ። ወ/ሮ አባይነሽ ውስጣቸው በእልህ ተሞላ ። በድጋሚ የመጨረሻ ኃይላቸውን አሳረፉበት ። በዚህ ወቅት ፈሩቅ ጭካኔያቸውን በሚገባ ተረዳ ። ለትዕዛዙ ከመቅስፈት መልስ ሰጠ ። ራሱን ፈተሸ ። ከሱሪ ኪሱ ውስጥ በትንሽ የቆዳ ቦርሳ የታሰሩ ቁልፎችን አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ ። ወ/ሮ አባይነሽ የሚፈልጉትን ያገኙ መሰሉ ።

« በል አሁን ትንፍሽ ሳትል ሰተት ብለህ ውጣ !አንተ ባለጌ !» ሲሉ ፈሩቅን አዘዙት ። ፈሩቅ ቃል አልተነፈሰም ፤ አላቅማማም ። እንደታዘዘው ትንፋሹን ውጦ ወደ ውጭ ገሰገሰ ። ከበስተጀርባው ሽጉጣቸውን እንደደገኑ እስከዋናው በር ድረስ ከሸኙት በኃላ ዘበኛ ቸውን ጠርተው « ሁለተኛ እዚህ ግቢ እንዳይገባ » ሲሉ የከረረ ትዕዛዝ አስተላለፉ ።

ይህ ከሆነ ብዙም አልቆየ ። በግቢው በር ላይ የድንጋይ ጋጋታ ዘነበ ። የቆርቆሮው ጩኸት ከጥይት ድምፅ ያስመስለግን ነበር።

ወ/ሮ አባይነሽ ከውስጥ ሆነው ሽጉጥ የያዘ የቀኝ እጃቸውን ከፍ አድርገው ሁለት ጊዜ ተኮሱ ። ወዲያው የድንጋዩ ጋጋታ ቀጥ አለ በመቀጠል የኡኡታ ድምፅ ተሰማ ።

* * *

ሕሊና በሯን ዘጋግታ ፣ ምግብ አዘገጃጅታ ፣ የያሬድን መምጣት ከአልጋ ላይ ጋደም ብላ ትጠባበቃለች ። ሆኖም ያሬድ ከሄደበት ሳይመለስ ጊዜው እየመሸ ሲሄድ ሀሳብ ውስጥ ገባች ። ዛሬ ቀን ላይ ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ቀጠሮ እንደነበረው ታውቃለች ። ቀጠሮው በያሬድ ላይ የከፋ ነገር ያስከትላል የሚል ግምት አልነበራትም ። ቀኑ ወደ ምሽት ፣ ምሽቱ እየዘገየ ወደ ሌሊት እየተሸጋገረ ሲመጣ የሕሊናም አእምሮ መረበሽ ጀመረ ። በዚሁ ስሜት ውስጥ እንዳለች ራቅ ካለ ስፍራ ጩኸት ስትሰማ ልቧ ለሁለት ትርክክ አለ ። ጆሮዋን ቀና አድርጋ የጩኸቱን አቅጣጫ ለመለየት ሞከረች ። ለጊዜው መነፈሷ በመጠኑ ረጋ አለ ።

ብዙም ሳይቆይ የተኩስ ድምፅ ተሰማት ። ከነበረችበት ተስፈንጥራ ተነስታ በሩን በርግዳ ወጣች ። ኃይለኛ ጩኸት ተቀበላት። ጊዜ አላጠፋችም ወደ ጎረቤት በረረች ።

« የኩቻ እናት ! አንቱ የኩቻ እናት ! » ስትል በሩን እያንኳኳች ተጣራች ።

« ማነው ? ምንድነው ? » አሉ የኩቻ አባት መብራት እያበሩ ። « እኔ ነኝ . . . እኔ ሕሊና ነኝ . . . ጋሼ » አለች እየተንቀጠቀጠች። የኩቻ አባት በሩን ከፍተው« ግቢ ምን ሆናችሁ? » አሉና ሕሊና ስትገባ በሩን ዘጉት ። የኩቻ እናት በውስጥ ልብሳቸው ላይ ጋቢ እንደደረቡ በድንጋጤ መናገር ያቃታት ሕሊናን እየተመለከቱ « ተጣላችሁ እንዴ » ሲሉ ጠየቋት ።

« አልሰማችሁም ! የተኩስ ድምፅ ! » አለችና ምላሷ ስለተሳሰረ ዝም አለች ።

« ማነው እሱ ? » በማለት ጎርነን ባለ ድምፅ ሕሊናን በድንጋጤ ዓይን እየተመለከቱ ጠየቋት የኩቻ አባት ።

ሕሊና ዓይኖቿ እንባ እያቀረሩ « እኔ እንጃ ጋሼ ያሬድ እስከአሁን አልገባም ። እንደዚህ አምሽቶ አያውቅም ። ቀን እንደወጣ ነው » እንዳለች ፤ እራሷን በሁለት እጆችዋ ይዛ « ወይኔ መከራዬ ! ወይኔ ወይኔ ! » ስትል ለቅሶዋን ለቀቀችው ።

የኩቻ አባት « ኧረ ዝም በይ ምን ይሆናል ብለሽ ነው ? ቆይ እኔ ሄጄ የት እንዳለ ፈልጌ ይገኘው እመጣለሁ » አሉና ወደ ጓዳ ገባ አሉ ።

« የት ነበር የሄደው ? አዲስ አበባ ከጓደኞቹ ጋር ሄዶ እንዳይሆን ? አይዞሽ ምን ይሆናል ብለሽ ነው ? » በማለት የኩቻ እናት ፊቷን ቀና አድርገው እየተመለከቱ አባበሏት ።

« ከዛች አረመኔ ጋር ቀጠሮ አለኝ ብሎ ነው የሄደው ፤ ምን ይታወቃል » አለች ሕሊና ። የኩቻ አባት ከጓዳ በር ልብሳቸውን ለብሰው ሽጉጣቸውን አቀባበሉና ወጣ አሉ ።

« ሕሊና ፤ ሕሊና » እያለ በጩኸት አንድ ድምፅ ተጣራ ። የኩቻ እናት « እስኪ ዝም በሉ» በማለት የሁሉንም ጆሮ ወደ ጥሪው እንዲያቀና አደረጉ ። ያሬድ ነበር ።

ሦስቱም ተያይዘው ወደነያሬድ ቤት ሲሄዱ በሩ ተከፍቶ የበረንዳ መብራት እየበራ ነበር ። ሁለቱ ጎረቤቶቹ ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ሕሊና ያሬድን አልፋ ወደ መኝታዋ ሄዳ አልጋዋ ጫፍ ላይ ተቀምጣ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። የኩቻ አባት ወንበር ሳብ አድርገው ተቀመጡና « ምነው እባክህ ሰው ይሰጋል አትልም ? » በማለት የግሳጼ ዓይናቸውን በያሬድ ላይ ጣል አደረጉ ። የኩቻ እናት የባላቸውን ቁጣ በመቀበል ዓይነት ራሳቸውን አወዛወዙ ።

ያሬድ እራሱን በሀዘኔታ እየነቀነቀ « እንዳስቸገርኳችሁ ይገባኛል የኩቻ አባት ! በጣም በጣም ይቅርታ . . . ሆኖም ያመሸሁት ከቁጥጥሬ ውጪ የሆነ ጉዳይ ስላጋጠመኝ ነው ። የኩቻ እናት ተቀመጡ » አለና ብድግ ብሎ ወደ ወንበሩ አመለከተ ። አይ አልቀመጥም ፤ እንኳን በደህና መጣህ ! ቤቱ ክፍት ነው እንሄዳለን » አሉና ዓይኖቻቸውን ወደባለቤታቸው መለሱ ።

« እውነቷን ነው . . . በል ወቀሳው ለነገ ይደር ። ደግሞ መሽቷል ። እናንተም ተኙ » እያሉ ከተቀመጡበት ተነስተው ከባለቤታቸው ጋር ተያይዘው ወጡ ።

ያሬድ ክንዱን በጠረጴዛው ላይ ተክሎ በሁለት እጆቹ መሀል ፊቱን ቀብሮ ጥቂት ከተከዘ በኋላ ወደ ሕሊና ዞር ብሎ « በቃ አለፈ። ምን የሆንኩ መሰለሽ ? » በማለት ፈገግ አለ ። ሕሊና ቃል ሳትተነፍስ ከተቀመጠችበት ተነስታ እራት አቀረበች ።

« ሕሊና እራት አልፈልግም ፤ ጠግቤያለሁ ፤ ነይ ተቀመጭ» በማለት ጎኑ ያለውን ወንበር ሳብ አድርጎ ከጠረጴዛው ራቅ ብሎ ተቀመጠ ። አነጋገሩ የኩርፊያ ወይም የመቀየም መሰላት ። ልታሳዝነው አልፈለገችም ።

« የተቆጣሁ መስሎህ ነው ? አልተቆጣሁም ። እኔ ሲተከስ . . . » አለችና የጀመረችውን ሳትጨርስ አቋረጠች ።

ያሬድ « እሮይ . . . » አለና ተነፈሰ ። « ተከፍቶ ነው ያስደነገጠሽ ? እሱስ እኔንም አስደንግጦኛል ። » አላት ዝርዝር ሁኔታውን ለሕሊና ሳለመናገር ። ቀጠለናም « ባይሆን አንቺ እራትሽን ብዪ ። እኔ ደክሞኛል ሄጄ ልረፍ » ብሎ ከመቀመጫው ብድግ አለ ።

« አንተ ካልበላህ ብቻዬን አልበላም » አለችው ንግግሯን ጫን አድርጋ ።

« እሺ አብረን እንብላ » አለና ተመልሶ ተቀመጠ ። እራት ስታዘጋጅ ወጡ ቀዝቅዞ ነበር ። ሕሊና « ቆይ ወጡን ላሙቅ » ብላ ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

« ማሞቅ አያስፈልግም ። ገና አሳት አንድደሽ ? አይሆንም » አለና ያሬድ አስቀራት ። ሁለቱም እራታቸውን መብላት አያበለው አበላል ተያያዙት ። ያሬድ በተረፈው ወኔ በመጠኑ ሲያዘግም

ሕሊናም የተረበሸ ሰውነቷን በማስገደድ ጥቂት ጎራረሰች ። አራት ተበልቶ እንዳለቀ እጃቸውን ታጥበው ፣ ሕሊና ዕቃውን በወግ በወግ አድርጋ እንደጨረሰች ያሬድ « የበላነው እስከሚንሸራሸር ትንሽ እንቀመጥ » የሚል ሀሳብ አቀረበ ። ሕሊና በሀሳቡ ተስማምታ አጠገቡ ተቀመጠች ። ሕሊና ከጎኑ ተቀምጣ ያሬድን በፈገግታ እያየችው « እኔኮ ሞኝ ነኝ ። የኩቻን እናትና አባት በጠበጥኳቸው ። አሁን ምን ይባላል ? » ብላ ፊቷን በቀኝ እጇ ሸፈነች ።

ያሬድ የሕሊናን ንግግር ቸል ብሎ « ሕሊና እስኪ ንገሪኝ ? አክስትሽ መጥረቢያሽን ለመውሰድ ሞክረው ነበር ? » አላት ።

« ደግሞ ምን ነግረውህ ይሆን ? ቀደም ሲል ከእኔ ጋር የመጨረሻ ጥል የተነሳው በመጥረቢያው ነው ። » በማለት እንዴት በመጥረቢያው እንደተጣሉ ዘርዝራ አጫውታው ስታበቃ « ግን ምን አሉህ ? » ስትል ጠየቀችው ።

« አይ እንደዚሁ የአንቺና የአክስትሽን የጥል መነሻ ለማወቅ ያህል ነው ። » በማለት ጥያቄዋን ቀጭቶ ብድግ አለ። « የተረፈውን ሌላ ጊዜ እንጫወታለን ። ለዛሬ በዚሁ ይብቃን እንተኛ » አለና ወደ መኝታ ክፍሉ አመራ ። ልብሱን አወላልቆ ብርድልብሱ ውስጥ ገብቶ ስለ ምሽቱ ድርጊት አሰላሰለ ።

« መቼም ሴትዮዋ በጣም የሚገርሙ ናቸው ። ልክ እንደ ወንድ ያንን ግዙፍ ሰው አዝረጠረጡት ። ግን ለምን ነበር መጥረቢያውን ከሕሊና እንዲሰርቅ የፈለጉት ? ምስጢሩን ለመናገር ያልፈለጉበት የራሳቸው ምክንያት ይኖራቸዋል ። ግን ፈሩቅ ጉድ አድርጓቸዋል ። አሁንም ቢሆን መጥረቢያውን ሳያገኝ የሚተው አይነት አይደለም ። ፈሩቅም ትዕዛዛቸውን ቢፈጽም ኖሮ ይህ ሁሉ መከራ አይደርስበትም ነበር ። አይ ምስኪን ፣ መቼም እኔ ነኝ ያጋለጥኩት ። » የሚገርም ነው « የመጥረቢያውን ታሪክ ከሕሊና ጋር በማያያዝ ታመልከበታለች አሉኮ ። አምልኮትና ማስታወስ

የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። የእኔ ሕሊና በመጥረቢያ አታመልክም ። ኡፋ ሕሊና . . . ሕሊና . . . ሕሊና መቼ ይሆን እውነተኛውን ጨዋታ የምንጫወተው ? እስከመቼ እንደዋሸሁሽ እኖራለሁ ። እስከመቼ . . . እስከመቼ . . . የዛሬ ሁለት ፣ ሶስት፣ አራት አመት ! አይሆንም አሁኑኑ ሄጄ ከጎኗ ተኝቼ ክንዷን ተንተርሼ . . . » ሌሊቱ እየተገባደደ ነበር ።

* * *

ያሬድ ከሕሊና የሚጠብቃቸው ብዙ ነገሮች የሉትም ። ከሕሊና አንድ ነገር ብቻ ነው የሚፈልገው ። እሱንም በራሷ ጊዜ እንድትረዳለት ይሻል ። ከዚህ አልፎ ሁኔታውን ገልጾ መናገር ግን ወኔው አልፈቀደለትም ። እሷን አዘውትሮ ማየትና ውበቷን በማድነቅ ከማምለክ የተሻለ አማራጭ አላገኘም ። በእርግጥ ሕሊና እንደምትወደው ያውቃል ። ይህ መውደድ ግን ከየትኛው ወገን እንደመነጨ አምኖ ለመቀበል አልሆነለትም ። ሕሊና በኑሮዋ ደስተ፣ በባህሪዋ አርቆ አሳቢ ከመሆኑዋ ጋር በትምህርቷ የከፍተኛ ውጤት ባለቤት ለመሆን በቅታለች ።

አንድ ቀን ያሬድ ከሥራ በጊዜ ወጥቶ ቤቱ እንደገባ ሕሊና ከትምህርት ቤት ስትመለስ መክሰሱን አቅርቦ ሲበላ ደረሰች ። ከዘወትር የሠላምታ ልውውጥ በኋላ ልብሷን ለውጣ እንደተመለሰች ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ተውጦ ውበቷን ካስተዋለ በኋላ ፣

« ሕሊና ! » አላት ።

« አቤት » አለችው ጥያቄያዊ በሆነ አቀራረብ ።

« አክስትሽ በጠና ታመዋል ። ምናለበት ሄደን ብንጠይቃቸው? » አለ ።

« መታመማቸውን ከሰማሁ ቆይቻለሁ ። ሆኖም ዓይናቸውን ለማየት አልፈልግም ። ጋሼ ያሬድ እኔን አትቀየመኝ ። አንተ

ልትጠይቃቸው ትችላለህ ። እኔ ሄጄ ለእሳቸው የማደርገው አንዳች ነገር አይኖርም ። እባክህ ጋሼ ያሬድ » ብላ ዓይን ዓይኑን እየተመለከተች ፣

« እንድጨነቅ አታድርገኝ ። እኔ ያንተን ጥያቄ እንቢ ማለት አልችልም ። ግን እሳቸውን ባላያቸው ደስ ይለኛል ። » ስትል ተለማመጠችው ። ኮስተር ብሎ ሕሊናን እያየ « ሕሊና ስሚ አባትሽንና ወ/ሮ አባይነሽን ያቀያየማቸው ጉዳይ ሥረ-መሰረቱ ከሀገራችን በሚገባ ተወግዷል ። ዛሬ ሁሉም ነገር መልኩን ቀይሯል፣ ለእናትሽ ሞት ፣ ለአንቺ ችግር ውስጥ መውደቅ ፣ እንዲሁም ለመላው ህብረተሰብ መጨቆንና መረገጥ መንስዔ የሆነው መሬት ከእንግዲህ ወዲያ ለግለሰቦች የሀብት መደለቢያ መሆኑ ቀርቶ መሬት ላራሹ ተብሎ ጭቁኑ ሕዝብ ሠርቶ የሚበላበት ፣ የወዙን የላቡን የሚያገኝበት ጊዜ መጥቷል ። ወ/ሮ አባይነሽም ሆኑ መሰሎቻቸው ከእንግዲህ ወዲያ ለግሌ የሚሉት ሀብት የላቸውም ሁሉም ሰው በእኩልነት የሚኖርበት መልካም ጊዜ ከፊታችን ተደቅኗል ። አብዮት ፈንድቷል ፣ በመሆኑም እያንዳንዳችን ልንደሰት ይገባናል ። አንቺንም የሚያሰጋ አንዳች ነገር የለም ። ዛሬ ወ/ሮ አባይነሽ ሁሉንም ነገር አጥተው የአልጋ ቁራኛ ሆነዋል ። ምግብ በወጉ የሚያቀርብላቸው ሰው እንኳ የላቸውም ። ሳደረጉት ጥፋት መቼም ከሰው ሁሉ በላይ ኖረው ከሰው በታች ሆነው መዋላቸው ሳይሞቱ በህይወታቸው እንዲሁሁ ሳይረዳቸው አይቀርም። እየከፈሉት ያለው የሚበቃቸው ይመስለኛል ። አንቺ ልጅ ነሽ ፤ ይቅር ልትያቸው ይገባል » ሲል ለመናት ። ሕሊና የጭንቀት ሁኔታ እየተሰማት ወደ ያሬድ ተመለከተች ።

« ጋሼ ያሬድ አጥብቀህ ስለለመንከኝ ለመሄድ አስገደድከኝ ። ግን እዚያ ቤት ብዙ አልቆይም ። የእሳቸውን ዓይን ሳየው የሞቱትን ያስታውሰኛል። የሞቱትን ደግሞ በስቃያቸው ማስታወስ

አልፈልግም። ሠላም የነሳኟቸው ይመስለኛል » ስትል ዓይኖችዋን እንባ እየሸፈናቸው ተናገረች ።

ያሬድ ከዚህ በላይ መስማት አልቻለም ። የሕሊና መራር ንግግር ለራሱም የሬት ያህል ሆኖበት ነበር ። ከነበረበት ተነስቶ መኝታ ክፍሉ ገብቶ ተኛ ። አልጋው ላይ ተጋደሞ ስለወ/ሮ አባይነሽ ማሰብ ጀመረ ። ፈሩቅን ከቤታቸው ሲያባርሩት የነበራቸውን ቆራጥነት አስታወሰ ። በተለያዩ ቀናት ተጠርቶ ሄዶ ስለ ብዙ ነገሮች ሲያማክሩት የጤንነታቸውን መባባስ አስተዋለ ። በተለይ አንድ ቀን በጠና ታመው ሕሊናን ለማየት የፈለጉበት ቀን ትዝ አለው ። እሱና ሕሊና ከሳቸው ጋር አብረው እንዲኖሩ የለመኑት ሁሉ ትዝ አለው ። በወቅቱ አሳዝነውት ነበር ። ለምን ለሕሊና እንዳልነገራት ለማስታወስ ሞከረ ። « ሕሊና እሺ አትለኝም እንጂ እጠገብዎ ብትሆን እኔ በበኩሌ ደስ ባለኝ ነበር » ሲል ቃል ገብቶላቸው ነበር ። ሆኖም አለመንገሩ ልክ ነበር ። ሕሊና ለዚህ ፈቃደኛ የምትሆን አልነበረችም።

*   *   *

ሕሲና ውሀ ሰማያዊ ቀሚስ ለብሳ ፤ ቢጫ ሹራብ አላይዋ ላይ ደረብ አድርጋ ፤ ቡኒ ጫማ ተጫምታ ፤ ፀጉሯን ተጎንጉና ያሬድ ከመኝታ ቤት እስከሚወጣ ጠበቀችው ። እጅግ በጣም አምርባት ነበር። ያሬድ ከመኝታ ቤት እንደወጣ ሕሊናን ያለወትሮው አፍጥጦ አስተዋላት ። እንደማፈር አንገቷን ወደ መሬት ሰብራ ከመቀመጫዋ ብድግ አለች ።

« ምን ታፍሪያለሽ ፤ ቀና በይ እንጂ » አላት ። በሀፍረት ፈገግታ ተይዛ ቀና ብላ አየችው ። የውበት አምድ ሆና ታየችው ። ውስጡ ተቀጣጠለ ። ሰውነቱ ስሜት ብቻ ሆነ ። ጠጋ አለና ግንባሯዋ ላይ ሳማት ። ሕሲና የያሬድ ከንፈር ሳይሆን የኤሌክትሪክ ኃይል ግንባሯ ላይ የወደቀ ነበር የመሰላት ። ከእግር ጥፍሯ እስከ እራስ ፀጉሯ ነዘራት ። እየቆየች ስትሄድ ያሬድ ግንባሯን በመሳሙ የተለየ ትርጉም ያየችበት መሰላት ። ግንባርዋን ወደኋላ ሳብ አድርጋ አንገቷን መለሰች ።

« በል ና እንሂድ » በማለት የምንተእፍረቷን ተነፈሰች ።

« በጣም ውብ ሆነሻል » አለና ተከተላት ። ተያይዘው ክበሩ ሲወጡ ሕሊና ሀሳብ ላይ ነበረች ። በመንገድ ላይ ምንም ሳይነጋገሩ ሲጓዙ ቆይተው ፤ የተዘጋውን የሾፌሮች ቡና ቤት በር አልፈው የቆርቆሮ መዝጊያውን ከፍተው ገቡ ። ሕሊና የቡና ቤቱ የመኝታ ቤት አጠገብ ስትደርስ ሥራ የጀመረች ጊዜ የነበረው ሁኔታ ታወሳት። ዋናው ቤት ፊት ለፊት በር ሲደርሱ ያሬድ ቀደም ብሎ በሩን ከፈተና ገቡ ።

ዋናው ቤት ሕሊና ታውቀው እንደነበረው አይደለም ። ውጭውም ውስጡም ቀድሞ የነበረው ንፅህናና ውበቱ ጠፍቷል ።

ዕቃው በየሜዳው ተጥሎ ፤ ውስጥ ያለው ዕቃ በየቦታው ተዝረክርኮ፤ አቧራና ሸረሪት አድርቶበት ስታይ ልቧን ሀዘን ተሰማው ። መኝታ ቤቱ ፊት ለፊት ካብትሽን ስታገኛት አላወቀቻትም ነበር ። ማንነቷን ስትነግራት እንደ ትልቅ ሰው ጎንበስ ብላ እጅ ከነሳች በኋላ አቅፋ ጉንጯን እያገላበጠች በመውደድ ስሜት ሳመቻት ። የወ/ሮ አባይነሽ የመኝታ ክፍል የድሮ ዕቃውን በውስጡ እንደያዘ ቢሆንም የሚከብድ ዓይነት ነበር ። ወለሉ ላይ የተነጠፈው ምንጣፍ አቧራ ለብሶ ወደ አፈራማነት ተቀይሯል ። ሕሊና ይህ ሁሉ ሰውጥ አልገረማትም ። በጣም የዘገነናት ግን በዚያ ሠፊ አልጋ ላይ ሞልተው የሚተኙት ወ/ሮ አባይነሽ ዛሬ በአልጋው አንድ ጠርዝ በብርድ ልብስ ተሸፍነው የት እንዳሉ እንኳን ለመለየት በማይቻልበት ሁኔታ ላይ መገኘታቸው ነበር ።

« ሥጋ ባዳ ነው እንዲሉ » ወፍራም እክስቷ ሚሽሽው ለማለት ጥቂት ቀናት የቀራቸው መሰላት ። እነ ሕሊና መኝታ ክፍላቸው መግባታቸውን እንዳወቁ አንገታቸውን ቀና አድርገው ለመቀበል ሞከሩ ። አልሆነላቸውም ። እራሳቸውን ወደ መኝታቸው መለሱና ፀጥ አሉ ። ዓይናቸውን በማንከራተት በልመና አስተዋሉአት። ይህን የተመለከተው ያሬድ ችግራቸውን ተረድቶ ስለነበር ከሥር በትራስና በጨርቃጨርቅ አስደግፎ ቀና ብለው እንዲተኙ አገዛቸው ። ሕሊና እክስቷን የማጥናት ያህል አየቻቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ ከለበሱት ብርድ ልብስ ውስጥ እጃቸውን ወጣ አደረጉና ሕሊናን እያዩ አልጋው ጫፍ ላይ እንድትቀመጥ አመለከቷት ። ሕሊና ሀሳቧ እንደተረበሸ እንዳዘዟት አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች ። ወ/ሮ አባይነሽ ሕሊናን « ደህና ነሽ ? » አሉና ከአንገታቸው ቀስቀስ አሉ ።

« ይኸውልሽ እንደዚህ ሆኜ ቀረሁ » አሏትና እንባ ያቀረረው ዓይናቸውን ጨፈን አድርገው እራሳቸውን ወደ ትከሻቸው መልሰው

ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ። « አያልቅስ እማማ . . . ማልቀስ ለእርስዎ ጥሩ አይሆንም » አለና ያሬድ የለበሱትን ጋቢ አስተካከለላቸው ።

ሒሊና ምንም እንኳ ቂሟ በውስጧ ስርጾ የተቀመጠ ቢሆንም ካየችው ሁኔታ አንፃር ልቧ በጣም አዘነ ። በደላቸው ሁሉ ተረሳት ። ወ/ሮ አባይነሽም መረጋጋት ጀመሩ ። እንባ በሀዘኔታ የሚያፈስላቸው አንድ ሰው አጠገባቸው በማግኘታቸው ከበሽታቸው ተጽናኑ ። ከእንግዲህ ብቸኛ አይደሉም ። ሒሊና ከጎናቸው አለች ። ወደ አጠገባቸው እንድትቀርብ በእጃቸው ምልክት እያሳዩዋት « ነይ እስኪ ደህና አድርጌ ልይሽ ? » አሉ ። እሷም የወረደውን እንባዋን በያዘችው ነጭ መሀረብ ጠራርጋ ተጠጋቻቸው ። በእጃቸው ፀጉሯን ዳሰስ ዳሰስ እያደረጉ እንደገና ለቅሶአቸውን ሲጀምሩ « እቴቴ እባክዎት አያልቅሱ » በማለት ኮስተር ብላ ተመለከተቻቸው ።

« ፀጉርሽ የወርቂቱን ነው የሚመስለው ። እያደግሽ ስትሄጂ የበለጠ ወረቂቱን እየመሰልሽ መጣሽ » አሉ ቀስ ብለው በሚንቀጠቀጥ ድምፃቸው ። በሀፍረት ዓይን አንገታቸውን ዞር ሲያደርጉ ያሬድ አጠገባቸው ቆሟል ። « ምነው አትቀመጥም ? ያሬድ ደህና ነኝ » አሉት ። ፎቴ ወንበሩ ላይ ሄዶ ተቀመጠ ።

የሁለት ዘመዳሞች ከብዙ ቂምና ጥል በኋላ መገናኘት አስደሰተው ። ብቻቸውን ሆነው እንዲጫወቱ ፈለገ ።

« የምደርስበት ቦታ አለ ። ሒሊና እስክምመጣ እየተጫወታችሁ ቆዩኝ » አለና አስተያየት ሳይጠብቅ የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ወጣ ። ወ/ሮ አባይነሽ ወደ ሒሊና ትኩር ብለው እየተመለከቱ « ሒሊና መቼም ያለፈው አለፈ ። ቂም እንደማትይዥብኝ አምናለሁ ። እኔን ያሳሳተኝ ያ መናጢ ነው ። ነገር በማመላለስ የራሱን ቦታ ለማመቻቸት ሲል እኔና አንቺን አቆራረጠን። መቼም አንዱ አምላክ ብድሩን ይከፈለው እንጂ » አሏት ።

ሒሊና በእጇ የያዘችውን መሀረብ እያገላበጠች በሀዘኔታ ታዳምጣቸው ነበር ። በወ/ሮ አባይነሽ አነጋገር ተገርማ « ሰው በመሞቻው ደግ ደጉን ነው የሚያሳስበው » ስትል አሰላሰለች ።

« ፀጉርሽ የእናትሽን ይመስላል » የሚለውን አነጋገር ከአባቷ የመጨረሻ ቀን አባባል ጋር በማመሳሰል የወ/ሮ አባይነሽ ቀን መቃረቡ ታሰባት ።

« ሰው ሲባል በአጠቃላይ ሲኖር እንጂ ሲሞት ማየት አልፈልግም » በማለት በህይወቷ የሁለት የሞቱ ሰዎችን በድን በአእምሮዋ ሳለች ። አንደኛው የአባትዋ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአስካበች ነበር ። ሒሊና ቀና ብላ አክስቷን ለአንድ አፍታ ተመለከተች ። ለሁለቱም ሞት የአክስቷ ድርሻ እንደነበረበት ታውቃለች ።

« ሒሊና » ሲሉ አክስቷ ከሀሳቧ አባነኗት ። « እመት » አለቻቸው ።

« እንዴት ነው ኑሮሽ ፤ አይከፋሽም ? » ሲሉ ጠየቋት ።

« በጣም ደህና ነኝ ። ምንም አይከፋኝም ፤ ተደስቼ ነው የምኖረው » በማለት መለሰችላቸው ።

« አዎ ፣ ሰውነትሽ ያስታውቃል ። ምን ይከፋሻል አንቺ ውብ ወጣት ነሽ ለኔ ይብላኝ እንጂ ፈላጊ የሌለኝ » በማለት ፊታቸውን ዞር አድርገው በማይሰማ ድምፅ ለብቻቸው አጉረምርመው «ሒሊና የእኔ ልጅ ምናለበት እዚህ ብትኖሪና እስከዕለተ ሞቴ አንገቴን ቀና ብታደርጊው ? ለምድሩ ሳይሆን በሠማይ ቤት ይቀበልሻል ። ይኸው ቡና ቤቱንም ዘወር ብሎ የሚያየው ሰው በመጥፋቱ ተዘጋ ። እባክሽ ሒሊና ምንም ቢሆን የሥጋዬ ቁራጭ ነሽ። ቤቱ በቁሜ እንደ መቃብር አይዘጋብኝ ። ከሞትኩም ሁሉም ያንችው ነው ። ተማጠኚኝ » በማለት እንደ ህፃን ልጅ እየተንፈቀፈቁ በማልቀስ ለመኗት ።

እሷ ግን ለለቅሶው ምንም ሀዘኔታ አልተሰማትም ። በውስጧ የሚፈላውን ቂም አውጥታ ልትዘረዝረው አልፈለገችም ። ትዕግስት እንደሚያሻት ተገነዘበች ።

« እባክዎትን አያልቅሱ እቴቴ ጥሩም አይደል » ስትል ተነፈሰች ።

« እባክሽ ፣ እባክሽ በፈጠረሽ እሺ በይኝ » ሲሉ በድጋሚ ተማፀኗት ።

« እቴቴ የእኔ መምጣት ምንም ነገር አይሰውጠውም ። ተማሪ ነኝ ። ቀን ቀን ትምህርት ቤት ነው የምውለው ። ብመጣም ለንብረቱም ሆነ ለእርስዎ ማድረግ የምችለው ነገር የለም » ብላ ፊቷን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ መለሰች ። « በዚህ ላይ . . .በዚህ ላይ. . . ከጋሽ ያሬድ ተለይቼ መኖር አልፈልግም ። የክፉ ቀን ባለውለታዬ ስለሆነ ልለየው አልችልም » አለቻቸው ።

ፊታቸውን በጋቢያቸው እየጠራረጉ ቀና ብለው አዩዋት ። « እኔ አሁን መቼ ተለያዩ አልኩ ። አብራችሁ መጥታችሁ እዚሁ እንድትኖሩ ነው ፍላጎቴ ። ቤቱ እንደሆነ ሠፊ ነው ። ቤትሽም ነው። ምን አለበት ባትጨክኚብኝ ? » አሏት ።

አዘነችላቸው ። ሀዘኔታዋ ግን ከልክ ያለፈ አልነበረም ። የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም ይባላል ። ዓይኖችዋን ጣለችባቸው ። ተያዩ ። የመኝታ ቤቱ በር ተንኳኩቶ ተከፈተ ። ያሬድ እራሱን ጎንበስ አድርጎ ወደ ውስጥ ገባ ። የያሬድ መምጣት ከነበረባት ጭንቀት ገላገላት ። ያሬድ ፊት አብራቸው እንድትኖር እንደማይጠይቋት እርግጠኛ ነበረች ። ወ/ሮ አባይነሽ ግን ያሬድ ተስተካክሎ እስኪቀመጥ ጊዜ አልሰጡትም ።

« ያሬድ እባክህ ልጄ አንተን እሺ ትልሃለች ። ለምንልኝ ። እኔን እንቢ አለችኝ ። እንደዚህ ሆኜ እያያችሁ ምንም ቢሆን ሥጋዋ ነኝ ስሞት ማልቀሷ አይቀርም ። እባክህ ለምናት » ሲሉ ተማፀኑት።

መልሱን የሰጠው ያሬድ አልነበረም ። ሕሊና ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

« አክስቴ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልንገርዎት ። እኔ እዚህ ቤት ለመኖር አልፈልግም ። ወደፊት እየመጣሁ ልጠይቅዎት ፈልጌ ነበር ። ግን የዚህ ዓይነት የማይሆን ጥያቄ በማቅረብ የሚያለቅሱ ከሆነ ለወደፊቱም አልመጣም ። » አለችና ወደ ያሬድ ዞራ « ወደ ቤታችን እንሂድ እየመሸ ነው » አለችው ። ወ/ሮ አባይነሽ የሕሊና ንግግር ሆዳቸውን አባባው ። እንደ ልጅ እየነፈረቁ ለቅሶአቸውን ቀጠሉ ። ያሬድ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ጠጋ ብሎ « ለበሽታዎ ጥሩ አይደልም አያልቅሱ ። » እያለ ሲያባብላቸው ሕሊና የመኝታ ቤቱን በር ከፍታ ወጣች ።

* * *

ሕሊና በወ/ሮ አባይነሽ እና በእርሷ መካከል ለብዙ ጊዜ የቆየውን ጥል በተፈጠረው እርቅ እንኳ ልትረሳ አልቻለችም ። ያሬድም ሕሊናን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት እንድትሄድ ማድረግ አልቻለም ። ማድረግ የቻለው ነገር ቢኖር በራሷ ጊዜ እንድትጠይቃቸው መተው ነበር ። ያም ቢሆን እንደማንኛውም የማይግባቡት የጎረቤት በሽተኛ ደርሳ ከመመለስ የረዘመ ጊዜ አትቆይም ። እንደዘመድ አታማክራቸውም ፣ አታፅናናቸውም ። አንድ ቀን ያሬድ ከሥራ ተመልሶ ወደ ቤት ሲገባ ሕሊና መጽሐፍ ስታገላብጥ አገኛት ።

ከተቀመጠችበት ቀና ብላ « እንደምን ዋልክ ጋሼ ያሬድ ? » ስትል ሠላምታዋን አቀረበች ።አፀፋውን መልሶ ፊት ለፊቷ በሚገኘው ወንበር ላይ አረፍ አለ ። በመካከላቸው የነበረው ታጠናበት የነበረው ጠረጴዛ ብቻ ነበር ። ሕሊና ያሬድ ፊት ላይ የጭንቀት ዳመና ጥሎበት አስተዋለች ። የሆነ ችግር እንዳለ ጠረጠረች ።

« ምን ሆነሃል ጋሼ ያሬድ ? » ስትል ጠየቀችው ::

« ሕሊና አሁን እኔ ወደ ሌላ ቦታ ብዘዋወር ምን ታደርጊያለሽ? » በማለት ጠየቃት ፣ ሲያምጥ ሲያምጥ ቆይቶ :: ፊቷን መለስ ቀለስ አድርጋ አካባቢዋን ቃኘችና « ምን ዓይነት ጥያቄ ነው ? ከአንተ ጋር እሄዳለሁዋ ! » ስትል ግራ በተጋባ ሁኔታ አየችው ::

ያሬድ እራሱን በአሉታ ነቀነቀ :: « ሕሊና . . እሱን አይደልም የምልሽ ፤ እንደ ድንገት እኔ የምሄድበት ቦታ ብቻዬን ከሆነ ማለቴ ነው » አለ ::

ሕሊና በድንጋጤ ያሬድን አፍጥጣ አየችው :: « እኔ አብሬህ እንድኖር አትፈልግም ማለት ነው ? በቃህ ? » በማለት የታችኛውን ከንፈሯን ጣል አደረገች :: « ታዲያ የት እሄዳለሁ ? » በሚል ዓይነት አስተዋለችው :: እሱ ግን እንዲህ የምትደነግጥ አልመሰለውም :: ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ ሕሊና ዞሮ አንገቷን በሁለት እጆቹ አቀፋቸው :: « ሕሊና እንደእሱ ማለቴ አይደለም :: እኔ አንቺን በህይወቴ ለደቂቃ እንኳን እንድትለይኝ አልፈልግም » አለ እንባ ያቀረሩ ዓይኖችዋን በዓይኖቹ እያባበለ ::

« ሕሊና እኔ አንቺን በጣም . . . እናፍቅሻለሁ :: ሆኖም ሕሊና » ብሎ በአንድ እጁ አንገቷን አቅፎ እራሷን ወደ ራሱ አስጠጋ:: « ወደ ውጪ ለትምህርት መሄዴ ነው » አላት ሲፈራ ሲቸር ::

ሕሊና ይህን አልጠበቀችም ነበር :: ከዚህ ውጭ ሁሉም ነገር ቢሆን አያስገርማትም :: ግን እንደ ወንድም የምትወደውና ለችግሯ ሁሉ የምታማክረው ከማንም በላይ የራሷ የቅርብ ተጠሪ የሆነው ያሬድ ከአጠገቧ ይለያል ብላ አልማም አስባም አታውቅም :: ጉዳዩ ዱብ ዕዳ ነው የሆነባት :: የያሬድን እራስ እንደተደገፈች ዓይኖችዋ

የቋጠሩትን እንባ በዝምታ አነባች :: ለዚህ አስደንጋጭ ዜና አስተያየት ለመስጠት አልተዘጋጀችም ነበር ::

ያሬድ የሕሊናን ለቅሶ ሲመለከት የሚያደርገው ቅጡ ጠፋው:: ከኪሱ መሀረብ አውጥቶ በጉንጮችዋ ላይ የፈሰሰውን እንባ እያደረቀ « ገና እኮ ነው :: ነገ አይደለም የምሄደው :: ይልቁንስ እንደ ልጅ ከማልቀስ ዝም በይና እንዴት አድርገን ኑሮአችንን እንደምንመራ እንነጋገር » አለና ቀና አደረጋት ::

ለመጀመሪያ ጊዜ አባቷ ከተለያት ወዲህ በህይወቷ በእጆችዋ የወንድ አንገት አቀፈች :: እጆችዋን በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥማ ፣ ፊቷን ጉያው ውስጥ ቀብራ « አትለየኝ ጋሼ ያሬድ ! አትለየኝ እባክህ! እኔ በህይወቴ የምወዳቸው ሁሉ ተለይተውኛል :: ከአንተ ሌላ ማን አለኝ? ጥለኸኝ አትሄድ » በማለት መወትወት ጀመረች ::

ያሬድ የሕሊናን ፀጉር በሁለት እጆቹ እያሻሸ ፊቷን ወደ አንገቱ ጠጋ አደረገና « አልሞትኩም እኮ እንዲህ የሚለቀሰው ለሞተ ሰው ነው :: » በማለት ሕሊናን አባበላት :: ብዙ ከነፈረቀች በኋላ አፍንጫዋንና ዓይኖችዋን እየጠራረገች ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች :: ያሬድ በዚያች ደቂቃ ውስጥ የተፈጠረው ሁኔታ እስከወዲያኛው እንዲቀጥል ምኞት ነበረው :: የሕሊናን ለቅሶ ግን ሊቋቋመው አልቻለም :: ሳሎን ውስጥ ጥሏት መኝታ ክፍሉ ገብቶ ልብሱን ማወላለቅ ያዘ :: ሕሊና ግን ብቻዋን ሳሎን ውስጥ መቆየቱ አስፈራት:: ያሬድ አሁኑኑ ከአጠገቧ የሚሰወር መሰላት :: መለየቷን ስታስበው ደግሞ ፈለገችው :: በሩን በርግዳ መኝታ ክፍሉ ገባች :: ያሬድ ደንግጦ አልጋው ላይ ዘፍ አለ :: እርቃኑ ስጋውን ነበር ::

« ሕሊና ምን ነካሽ ? ልብሴን ሳለብስ ? » አላት በቁጣ መልክ ::

« ልበስ አላይህም » አለችው ፊቷን አዙራ ። ያሬድ የስፖርት ቱታውን ሱሪ የሩጫ ያህል ካጠለቀ በኋላ ዘና ባለ አነጋገር « አሁን ማየት ትችያለሽ » አላት ፈገግ ብሎ ።

« ጋሼ ያሬድ ስላስደነገጥኩህ ይቅርታ አድርግልኝ ። ካንተ ጋራ ለመሆን ስለፈለግኩ ነው » አለች እሷም ፈገግ ብላ ። ፈገግታዋ ብቻ ሳይሆን ውበት በውበት ሆና ታየችው ። ውስጡ ታገለው ።

ሕሊና በሩን በርግዳ ወደ ያሬድ ክፍል ስትገባ ምንም ዕቅድ አልነበራትም ። ያሬድ ስለመለየት ካነሳበት ጊዜ አንስቶ የውስጥ ስሜቷን ለመግታት ያላትን ጊዜ ከእሱ ጋር ለማሳለፍ በመፈለጓ ነበር። ክፍሉ ውስጥ አልጋው ጫፍ ላይ አረፍ አለች ። ያሬድ ፤ ልቡ ውስጡ አታሞዋን እየደለቀች ፤ ሠውነቱ ሙቀት እያመነጨ ከጎንዋ ተቀመጠ ። ከወገቡ በላይ ዕርቃኑን ነበር። አያት፤ አየችው ፤ አፈረ ፤ ተያዩ ፤ የተፋፈሩ መሰሉ ። ያሬድ ካለበት ሁኔታ ማምለጥ ፈለገ ።

*　　*　　*

ያሬድ የሚጠጣውን ሻይ ተወት አድርጎ ሕሊና የምታደርገውን ይመለከታል ። ከረጢቷን ፈታ ፈታ አድርጋ ውስጡ የነበረውን መጥረቢያ ቀስ ብላ አወጣች ። ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ ፊቷን ወደ ያሬድ አዞረች ።

« እንግዲህ እኔና አንተ ልንለያይ ነው ። ሆኖም እንዳሰብከው የምንለያየው ለጥቂት ጊዜ ይሆናል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምን እንደምንሆን አናውቅም ። ስለዚህ . . . » ስትል እጆችዋን በመጥረቢያው እጀታ ላይ አሳርፋ « ለእኔ የዋልከው ውለታ በህይወቴ ከማንም ያልጠበቅሁትና የማላገኘው ነው ። ይህን ውለታህን በገንዘብም በምንም የምመልሰው አይደለም ። አሁን ይህን መጥረቢያ ያወጣሁት የአንተን ውለታና የአባቴን ምክር ለማስታወስ ያህል ነው።

አባቴ እኔ እንድማር በህይወቱ የነበረው ምኞት ከፍተኛ ነበር። ሆኖም በአቅም ማነስ ምክንያት ምኞቱን ሳያሟላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ። ይህ ምኞቱ ግን ዛሬ በአንተ ተሟልቷል ። እኔ ለእናት ለአባቴ ብቸኛ ልጃቸው ነኝ ። ወንድም አልነበረኝም ። የምወድህ ወንድሜ አንተ ነህ ። ምንም እንኳን አባቴ በህይወት ባይኖርም ምኞቱን እንዳሟላህለት ሁሉ የአንተም ምኞት እንዲሟላልህ በአባቴ ሥም ምኞቴን እገልጽልሃለሁ » ብላ ፈገግ አለችና ያሬድን ተመለከተችው ።

ያሬድ ይህን አነጋገር የጠበቀው ቢሆንም ከሕሊና አንደበት መስማት አልወደደም ። « ወንድሜ አንተ ነህ » የሚለው አባባል ስሜቱን ነው የጎዳው ። ለሱ ሕሊና እህቱ ልትሆን አትችልም ። እስከ ህይወቱ መጨረሻ በአንድ ጣሪያ ስር አብረው ኖረው እንከን የማይወጣለትን ፀባይዋንና ውበቷን ለራሱ ብቻ ለማድረግ ነበር የሚፈልገው ። ስሜቱን መግለፅ ባለመቻሉ እራሱን እየረገመ ፤

« ሕሊና ለለምኞትሽ በጣም ነው የማመሰግንሽ ፤ ተቀመጭ» አለና ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠችውን ሻይ የያዘውን ብርጭቆ ዞር ዞር እያደረገ አለተዋለው። ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላም ቀጠለ ፤

« ሕሊና እኔ ላንቺ ያደረግሁት ምንም የተለየ ነገር የለም ። ማንኛውም እውነተኛ ሰብአዊ ፍጡር ሊያደርገው የሚችል ነገር ነው። ሆኖም የአባትሽ ምኞት በእኔ ስለተፈፀመ በጣም ዕድለኛ ነኝ ። ፊትሽ ላይ ማድነቅ አይሁንብኝና የአባትሽን ምኞት ያሳካሽው በፅኑ እምነትሽ እና በጠንካራ ሞራልሽ ነው ። ለወደፊቱም በዚህ ዓላማሽ እንደምትቀጥይ ተስፋ አደርጋለሁ ። እኔ ከአጠገብሽ ስለይ ምንም እንኳን ብቻሽን ብትሆኚ ለሚያጋጥሙሽ ችግሮች ሁሉ ቀደም

ብለሽ የሰማሻቸውን የአባትሽን ምክር አስታውሺ » ብሎ ወደ መጥረቢያው ተመሰከተ ::

« ሒሲና መማር የሚሰው የእባትሽ አባባል በአጭሩ የሚያልቅ አይደለም :: በህይወታችን በምንኖርበት ጊዜ በዕድሜያችን ሁሉ ተፈፃሚነት ሲኖረው የሚገባ አባባል ነው :: ትምህርት አያልቅም :: በመሆኑም ምን ጊዜም የማያወላዳ ሀሳብ ሲገጥምሽ አባትሽን አስታውሺ » አላት :: ሒሲና የያሬድን ንግግር እንጼ ወደመጥረቢያው እንጼ ወደ ያሬድ እፈራርቃ እያየች በጥሞና አዳመጠችው ::

« እኔ በህይወቴ የምመኘው በድህነት እራሳቸውን ለማስተማር ያልበቁትን ወገኖቼን ተምሬ ሰማስተማር ነው :: በዚህም የአባቴና የአንተ ምክር እስከአሁን እንደረዳኝ ሁሉ ለወደፊትም እንደሚረዳኝ እርግጠኛ ነኝ :: » ብላ መጥረቢያውን በሁለት እጆችዋ ከጠረጴዛው ላይ አንስታ በጥልቅ ስሜት አይታ መልሳ ወደ ከረጢቱ አስገባችው::

* * *

ወ/ሮ አባይነሽ ከህመማቸው አገገሙ :: የያሬድን ወደ ውጪ ሀገር መሄድ በእልልታ ነበር የተቀበሉት :: በለሙ ማግስት ሒሲናና ያሬድ በዚያው ሣምንት ምሳ እንዲጋበዙላቸው ጠሩአቸው :: ጥሪውን ሒሲና ለመጀመሪያ ጊዜ ለመቀበል አልፈሰገችም ነበር :: ሆኖም በቅርቡ ከአጠገብዋ ለሚሰየው ያሬድ ስትል ተቀበሰች :: በቀጠሮው ቀን የክት ልብሳቸውን እንደለበሱ ወ/ሮ አባይነሽ ሳሎን ተቀምጠዋል፣ የነፍስ አባታቸውም ተገኝተዋል :: እነ ሒሲና ገና ወደ ሳሎን ሲገቡ ወ/ሮ አባይነሽ ትልቁ ፎቴ ወንበር ላይ ተቀምጠው የያሬድን ጉንጭ እንቀው እየሳሙ « እንኳን ደስ ያሰህ !» ሲሉ ተቀበሏቸው ::

ምንም ቢደኸዩ ወ/ሮ አባይነሽ ለዚህ ጊዜ የሚሆን ማስተናገጃ መጠጥና ምግብ አላጡም :: እንደቀድሞው ለእሳቸው ተብሎ በአዋቂ የደለበ ሙክት በግ አይታረድ እንጂ ትንሽ ጠቦትም ብትሆን ደም መፍሰሱ አልቀረም :: ጠርሙስ ውስኪም ባይሆን አንድ ኡዞ አረቂና የተወሰነ ቢራ አልጠፋም :: ሆኖም ያሬድን ያስገረመው የመጀመሪያውን የእርቅ ድርድር የመሩት የወ/ሮ አባይነሽ የነፍስ አባት እንደ ወ/ሮ አበይነሽ ሁሉ ስጋቸው እርቆአቸው ፣ ግርማ ሞገሳቸው ተገፎ ፣እንደ ወተት ነጭ የነበረው ጋቢያቸው አድፎ . . . ማየቱ ነበር ::

ወ/ሮ አባይነሽ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ ጓዳ ሲገቡ ያሬድ በክፍሉ ውስጥ የነበረውን ዝምታ ለመስበር ፊት ለፊቱ በራሳቸው ሀሳብ ግንባራቸውን እጨማትረው ሽበት የወረረውን ፂማቸውን የሚያፍተለትሉትን « አባ ታዲያስ ኑሮ እንዴት ይዝዎታል ? » በማለት ለንግግር መንደርደሪያ የሚሆን ጥያቄ ጣል አደረገ :: እሳቸውም ከሀሳባቸው ጋር እያጉረመረሙ ትንሽ ዘግየት ካሉ በኋላ ፣

« የእኛ ኑሮ ምን ብሰኸው ፣ ኑሮ ጌታውን ይመስላል » አሉት ። ቀጥለውም « ምን ኑሮ ነው ? ልጅ በአባቱ ፣ ወንድም በወንድሙ ፣ እናት በልጅዋ ላይ ሲነሱ ። ይህን ምን ትለዋለህ ? የምፅአት ቀኑ እየተቃረበ ነው እንጂ እህ . . . ህም. . . ህም . . . እግዚዮ መሀረነ ክርስቶስ » ብለው ሁለት እጃቸውን ወደ ሠማይ ዘርግተው እራሳቸውን ወደ ኮርኒሱ አንጋጠጡ በልመና ዓይነት ።

ሁኔታቸውን በጥሞና ስትከታተል የነበረችው ሒሊና የሽማግሌው ንግግር ፈገግ አድርጓት ያሬድን አየችው ። እሱም ፈገግ ብሎ ነበር ። አንድ መሀከለኛ ዕድሜ ያለው ልጅ የእጅ ማስታጠቢያና ፎጣ ይዞ ከወ/ሮ አባይነሽ ኋላ እየተከተላቸው ወደ እነ ያሬድ ቀርቦ አስታጠባቸው ። ሁሉም ታጥበው ሲጨርሱ ካብትሽ በዝርግ ሰሀን ምግብ አቀረበች ። ወ/ሮ አባይነሽ « ብሱ እንግዲህ ቤት ያፈራውን መካፈል ነው » በማለት መጋበዝ ጀመሩ ።

« ታዲያ መቼ ነው መንገድህ ? » አሉ ወ/ሮ አባይነሽ ምግብ ተበልቶ አልቆ መጠጡ ከተጀመረ በኋላ ።

« እንግዲህ ገና ነው ። ብቻ በሚቀጥለው ሁለት ሣምንት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም » አላቸው ።

« ምኑን ገና ሆነ ሁለት ሣምንትማ ነገም አይደል ? » አሉና ቀጠል አድርገው « ስንት ጊዜ ነው የምትቆየው ? » ሲሉ ጠየቁት። እሱም በፈገግታ « ብዙም አይደል ፣ አንድ አምስት ዓመት ያህል ነው የምቆየው » አላቸው በማቃለል ።

« አ . . . ! . . አ ! . . . አ . . . ! » አሉ ወ/ሮ አባይነሽ በማጋነን እራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው ።

« ይሄማ ዕድሜ ይፍታህ ነው ። ለመሆኑ ሀገሩ ሩቅ ነው ?» አሉት ።

« ሀገሩስ . . . አዎ ትንሽ ራቅ ይላል ፣ ምስራቅ ጀርመን ይባላል ። » አላቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ ትካዜ እንደገባው ሰው ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ቆዩና ወደ ሒሊና እያዩ « ታዲያ ሒሊና እስከዚያ የት ትቆያለች ? » ሲሉ ወደሚፈልጉት ነጥብ አመሩ ። ሒሊና ፊቷን ኮስተር አድርጋ ወደ ያሬድ እየተመለከተች በተቀመጠችበት መቁነጥነጥ ጀመረች ።

« ሒሊናማ እንደ ድሮዋ ተቀምጣ ትማራለች » አለ አጠር አድርጎ ።

« ገንዘቡስ አይቸግርም ? ገንዘቡስ ቢገኝ ሴት ልጅ ብቻዋን እንዴት አድርጋ ትወጣዋለች ? » አሉ ።

« ለዚህ ሁሉ ተነጋግረንበታል ። እኔ ውጭ በምቆይበት ጊዜ ደመወዜን እየተቀበለ ለሒሊና የሚያመጣላት ሀሰን የሚባለው ጓደኛዬ ተወክሏል » አለና እንደማሰብ ብሎ « ሒሊና ብቻዋን አትኖርም ። አንዲት ዘመድ የሆኑ ባልቴት አብረዋት እንዲኖሩ ተስማምተናል ። ከሚቀጥለው ሣምንት ጀምሮ ይመጣሉ » አላቸው ። ወ/ሮ አባይነሽ ያሬድ መርዶ ያረዳቸው ነበር የመሰላቸው ።

« ምነው በሞትኩት ! ካልጠፋ ዘመድ ባዕድ ለምን አስፈለገ ? የቤት ኪራይስ ካልጠፋ ቤት ለምን በነፃ ትገፈግፋላችሁ ? ይልቁንስ የሚሆነውን እናውራ ። እሷም ከሌላ ከማታውቀው ሰው ጋር አትኖርም ። ያም ቤት ምንም አያደርግላት ። እዚህ ትምጣና ከኔው ጋር ብትኖር ይሻላታል ። » አሉና « አይደለም ? » በሚል ዓይነት የነፍስ አባታቸውን አስተዋሉ ።

« እንዲያው እኮ ይገርማል ። . . . ለመቼ ነው እንግዲህ ዝምድናው ። ከአባይነሽ ወዲህ ለሷ የሚቀርብ ማነውና እንዲህ ወዲያ ወዲህ የምታደርጉት ነገሩን ። ኸረ ነውር ነው ፣ ሰውስ ምን ይላል ? » ሲሉ አባ የነፍስ ልጃቸውን ሀሳብ በመደገፍ ተናገሩ ። ሒሊና ትዕግስቷን ጨርሳ ነበር ።

« ስለነሮዬ የራሴ ምርጫ ነው ፡፡ እኔ ከአሁን በኋላ ቤት አለኝ ፡፡ ከማንም ጋር ተዳብዬ መኖር አልፈልግም ፡፡ በላይነሽን እቴቴም ያውቋቸዋል ፡፡ ለኔ ባዕድ አይደሉም ፡፡ ከማንም ዘመድ የበለጠ የሚሳሱልኝ እናቴ ናቸው ፡፡ » በማለት ቀስ ብላ በለሰለሰ አንደበት ተናገረች ፡፡

ወ/ሮ አባይነሽ ቀደም ሲል የዚህ ዓይነቱ ንግግር ምን እንደሚያስከትል ስለአወቁ ሁኔታውን ለማረጋጋት « እንግዲህ እንደምርጫሽ ፤ ያበጀሁ መስሎኝ ነው » በማለት ግራና ቀኝ የተቀመጡትን ያሬድንና የነፍስ አባታቸውን ከቃኙ በኋላ ቀጠል አድርገው ፤

« ምን ትሆናለች ፤ ከእንግዲህ እንጠያየቃለን ፡፡ » ብለው ቀደም ብሎ የነደደውን እሳት ለማቀዝቀዝ ፈለጉ ፡፡ ሕሊና እንደልማዷ ጥላ የምትሄድ መሰላቸው ፡፡ ዝምታው ለጥቂት ጊዜያት ሠፈነ ፡፡ ሁሉም የተግባቡ ይመስል ያሬድና ሕሊና ተሰናብተው ወጡ ፡፡

ምዕራፍ አራት

ያሬድ ከኢትዮጵያ ከለቀቀ ስድስተኛ ወሩን ያዘ ፡፡ ሕሊና በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራቶች በያሬድ ናፍቆት ክብደቷ ቀንሶ ነበር፡፡ ሆኖም አጠገቧ እንደ እናት በሚንከባከቧት በወ/ሮ በላይነሽ ፍቅር የስምንተኛ ክፍል ፈተናዋን በደህና ውጤት አልፋ ዘጠነኛ ክፍል ገብታለች ፡፡ በት/ቤት ውስጥ ባሉት የትርፍ ጊዜ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በመሳተፍ ጉልበቷንና ዕውቀቷን ሳትቆጥብ ትሠራለች ፡፡ በመሠረተ ትምህርት በተማሪ አስተማሪነት ያለማቋረጥ በከፍተኛ ፍላጎት በመሳተፍ መሀይምነትን ለማስወገድ ግንባር ቀደም ሆናለች ፡፡

ሕሊና በየጊዜው ከሚደርሳት የያሬድ ደብዳቤ ፤ ስለጤንነቱና ስለሚማረው የትምህርት ዓይነት እንደዚሁም ስለምስራቅ ጀርመን ዕድገትና ብልፅግና ተረዳች ከያሬድ የሚደርሷትን ደብዳቤዎች ሁሉ አከማቸች ፡፡ አልፎ አልፎም ደብዳቤው ሲዘገይባት ከቀድሞ ደብዳቤዎችዋ የተወሰኑትን በመምረጥ ደጋግማ ታነባቸዋለች ፡፡

ከደብዳቤዎቹ ጋር የሚልክላትን ፎቶግራፎች በቀድሞው መኝታ ቤቱ ፤ አሁን ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር በሚተኙበት ክፍል ግድግዳ ላይ በሚያማምሩ ፍሬሞች ሰቅላቸዋለች ፡፡ ከያሬድ ደመወዝ የሚጠቀሙት አንድ መቶ ሃምሳ ብሩን ብቻ ነበር ፡፡ ሴላውን ቀሪ ሦስት መቶ ሰባ ብር ወደ ባንክ በመውሰድ ታስቀምጣለች ፡፡

አንድ ቀን ሀሰን እንደተለመደው የያሬድን ደመወዝ ይዞ ወደ ቤት ሲመጣ ሕሊና ትምህርት ቤት በመሆንዋ ተቀምጦ መጠበቅ ግድ ሆነበት ፡፡ ጥቂት እንደጠበቀ ከት/ቤት ተመለሰች ፡፡ ገንዘቡን ቆጥሮ ካስረከባት በኋላ ስለያሬድ ወሬ አነሱ ፡፡ ሕሊና በቅርብ የላከላትን ፎቶግራፍ « እንዴት ወፍሯል መሰለህ ? » በማለት ለሀሰን

ሰጠችው ። ጉርድ ፎቶግራፉን ከሕሊና ተቀብሎ ጠጋ አድርጎ ተመለከተው ።

« በጣም አምሮበታል » በማለት መለሰላት ። ሕሊና የተቀበለችውን ፎቶግራፍ እየተ አድርጋ በከንፈሮቿ እየሳመች በደረቷዋ ላይ ጥብቅ አድርጋ ለጥቂት ለኮንዶች ያህል ያዘችው ። ሀሰን በዚህ አድራጎቷ በጣም ተገረመ ። የሕሊናንና የያሬድ ግንኙነት ምን እንደሆነ እራሱን እንዲጠይቅ አደረገው ።

ከያሬድ ጋር ለረጅም ጊዜ በነበረው ጓደኝነት ከሕሊና ጋር ስላለው ግንኙነት አጫውቶት አያውቅም ። የተለየ ጥርጣሬም አልነበረውም ። ይህ ድርጊቷ ግን አስቦት ወደማያውቀውና እንግዳ ወደሆነበት የጥርጣሬ ስሜት ከተተው ። በቀጥታ ሕሊናን ለማነጋገር ውስጡ ገፋፋው ። ሆኖም ወቅቱና ሁኔታው ስለማይፈቅድለት በዝምታ አለፈው ።

« በይ እንግዲህ ትምህርትሽን በርትተሽ አጥኚ ። ያሬድ ሲመጣ ደስ እንዲለው ከድሮው የክፍል ደረጃሽ ዝቅ ማለት የለብሽም» አለና ከተቀመጠበት ተነሳ ። ቀጥሎም « ሕሊና የሚቸግራችሁ ነገር አለ ? » ሲል ጠየቃት ።

« ሰጋሼ ያሬድ ስትጽፍለት ምንም ችግር እንደሌለብንና በሠላምና በደስታ የእሱን መምጣት እንደምንጠብቅ ፃፍለት ። » ስትል ችግር እንደሌለባቸው በተዘዋዋሪ ነገረችው። እየሳቀ ወጣ ። ወዲያው ማዕድቤት ሥራ ላይ ያሉትን ወ/ሮ በላይነሽን ጠርታ « እቴቴ በላይነሽ ይኸው የወር ወጪ » በማለት አንድ መቶ ሠላሳ ብር ቆጥራ ሰጠቻቸው ።

ወ/ሮ በላይነሽ ዕድሜ ቢጫጫናቸውም ከቀድሞው ሁኔታቸው ሻል ብለዋል ። በቤቱ ውስጥ የሚሠራውን ሥራ ብቻ ሳይሆን ለቤት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ በርካሽ ዋጋ ከሚገኝበት ገበያ ሄደው ይገዛሉ ። ሕሊና የማዕድቤት ውስጥ ሥራ እንድትነካ

አይፈቅዱላትም። እምቢ ብትል እንኳን ለይምሰል ያህል ሰሀንና ብርጭቆ ማጠብ እንጂ ከጥላሸት ጋር ንኪኪነት ያለውን ሥራ ሁሉ የሚሰሩት ወ/ሮ በላይነሽ ነበሩ ። እራት በልተው ከጨረሱ በኋላ ወ/ሮ በላይነሽ ቡና አፍልተው የኩቻን እናት ጠርተው ከዚያም ከዚህም ያገኙትንና የመሰላቸውን ወሬ ተወራውረው መለያየት ልማዳቸው ነበር ።

ሕሊና ደግሞ ከእራት በኋላ ትምህርቷንና ጥናትዋን ትቀጥላለች ። የሕሊና በዕድሜ መብሰል ፣ በትምህርት መግፋት ለወ/ሮ በላይነሽ ደስታን ቢያጎናጽፉቸውም አዕምሮአቸውን የሚከነክናቸው ጥያቄ ግን አልጠፋም ።

አንድ ቀን ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ምሽት ወ/ሮ በላይነሽ ቡና አፍልተው ፣ የኩቻ እናት ደግሞ ዘመድ ለመጠየቅ በመሄዳቸው ብቻቸውን ቡና እንዳይጠጡ ሲሉ ሕሊናን አስቸገሯት ። ሕሊናም ፍላጎታቸውን ለማሟላት ስትል ለይምሰል ያህል አንድ ሲኒ ቡና ተቀብላ ፊቷ አስቀምጣ ወሬ ጀመሩ ። ሣር ቢጤ እያገላበጡ በእናትነት ዓይን እያስተዋሉአት « ሕሊና . . . ልጄ ለምንድን ነው እስከአሁን ያልወለድሽው ? » በማለት ጠየቂት ። ሕሊና በጥያቄው ግራ በመጋባት « እቴቴ በላይነሽ ምነው ምን አደረኩዎት ? የምን መውለድ ነው ? » ስትል በድንጋጤ መለሰችላቸው ።

« አይ የልጅ ነገር ባል አግብቶ ዝም ብሎ መቀመጥ አለ ? ይህን የመሰለ ትዳር ለጥቶሽ በጊዜ ዱብ ዱብ አድርጎ ወንድምና እህት ማድረስ ነው » አሉ በቁምነገር ። ሕሊና ብብቷን የኮረኮሯዋትን ያህል ከት ብላ ሳቀች ።

« እቴቴ በላይነሽ ማነው እሱ ባሉ ? ከየት አመጡት ? » እንደገና ከልቧ ከት ብላ ሳቀች ።

« ምነው ሕሊና ! እኔን ነው የምትደብቂኝ ? » አሉና ጀበናውን ከምድጃው ላይ አነሱ ። ቅር ተሰኝተው ነበር ።

« አይ እቴቴ በላይነሽ ፣ አያውቁም ለካ . . . ያሬድን ነው የሚሉት ? እሱኮ ወንድሜ ነው » ብላ አፍጥጣ አየቻቸው ::

« ወንድምማ ከወንድም ይበልጣል :: ወንድም በሥጋ ? ማን ቢወልድ ማንን » አሉ ሽሙጥና መቀየም በተቀላቀለበት አነጋገር :: ሕሊና ከተቀመጠችበት ተንቀሳቀሰች :: የወ/ሮ በላይነሽን ጉልበት በሁለት እጆችዋ ተደግፋ « እቴቴ በላይነሽ መቼም ያውቃሉ :: በአባቴ ከማልኩ - የአባቴን ሥጋ ነው :: ጋሽ ያሬድ ለእኔ ንጹህ ወንድሜ ነው :: በእሱና በእኔ መሀከል የሴትና የወንድ ግንኙነት ቀርቶ አዝማሚያውም አልተፈጠረብን » ስትል ዓይን ዓይናቸውን አየች ::

« ታዲያ እሱስ ይሁንና እጮኛም የለሽ ? እንዲያው ለነገሩ » በማለት በመገረም እያዩ ጠየቋት ::

ሕሊና ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ « ምን ያደርግልኛል ? እኔ ከጋሼ ያሬድ ተለይቼ መኖር አልፈልግም :: ባል ፣ እጮኛ ለምን ብዬ ነው ? »

« የአንቺስ አፈጣጠር ሰብቻው ነው :: ታዲያ ለምን ያሬድ ሲመለስ አታገቢውም ? ለምን ሌላ ሰው ትፈልጊያለሽ ? እንደወንድምም እንደባልም ይሆንሻል :: ከእሱ የበለጠ ቁም ነገረኛ ሰው ከየትም አይገኝ » አሏት ::

« እቴቴ በላይነሽ ጋሼ ያሬድ ለእኔ እንደ እናቴ ልጅ ነው :: እንደባል ወይም እንደ ሌላ ባዕድ ወንድ ላየው አልፈልግም :: ባልና ሚስት ይጣላሉ :: አልፎ አልፎም ይደባደባሉ :: እኔ ለጋሼ ያሬድ ያለኝ መወደድ ልክ የአባቴን ያህል ነው :: ፊቱን ሳየው እንደ አንድ የእናት የአባቴ ልጅ ነው የምንሰፈሰፈው :: ስለዚህ ለእሱ ያለኝን መውደድ ባል ብዬ ለማገባው ሰው አይኖረኝም :: » አለችና አንገቷን አቀረቀረች ::

« እኛ በልጅነታችን ስንዳር ባሎቻችንን ወንድሞቻችሁ ናቸው እየተባልን ለብዙ ጊዜ ምንም ሳናውቅ አብረን ተቀምጠን ነው በኋላ

ባል መሆኑን የምናውቀው :: ብታገቢው ፍቅራችሁ የበለጠ ይጨምራል እንጂ ምን ይቀንሰዋል ? በወንድም ፍቅር ላይ የባልነት ፍቅር ሲጨመርበት የበለጠ መውደድ ያመጣል :: ይልቅስ ሞኝ አትሁኚ » አሉዋት ::

ሕሊና ሁሉንም ካዳመጠች በኋላ አጠገብዋ ያለውን ወንበር ሳብ አድርጋ ተቀመጠችና « ለርስዎ መሰለዎት እንጂ እኔ የሥጋ ወንድሜን የማገባ ያህል ነው የምቆጥረው ፣ ጋሼ ያሬድን ማግባት :: ደሞስ ጋሼ ያሬድ እኔን እንደ እህቱ ሲቆጥረኝና ሲሳሳልኝ ሚስት ካልሆንኩ ብዬ የምረክሰው በእኔ ላይ ያለውን እምነት ዝቅ ማድረግ አይሆንም ? » በማለት እየዘገነናት « እቴቴ በላይነሽ እንዳልቀየምዎት ሁለተኛ የዚህ ዓይነቱን ሀሳብ እንዳይደግሙብኝ » ስትል በልመና ዓይነት አስጠነቀቀቻቸው ::

* * *

ሕሊና ሳሎን ተቀምጣ አዲስ የደረሳትን ደብዳቤ እንባዋን ከዓይኖችዋ በመሀረብ እየጠራረገች አንብባ እንደጨረሰች ፊት ለፊቷ የተሰቀለውን የያሬድን ፎቶግራፍ ትክ ብላ አስተዋለች :: ዓይኖችዋን ከያሬድ ፎቶግራፍ ላይ ሳትነቅል በደብዳቤው ውስጥ ስላሰፈረው ፅሁፍ አለመች :: የጤንነቱን ሁኔታ በአጭሩ ካሰፈረ በኋላ ያሬድ ሲመለስ ቤት ኖሮት ትዳር እንደሚመሰርትና ልጆቹን ለመንከባከብ ያለውን ፍላጎት ነበር በደብዳቤው የገለጸላት :: በሀሳብ ደብዳቤውን ደግማ አነበበችው ::

ባለፈው ሳምንት የፈረንጅ ጓደኛዬ የሆነው ቶማስ ቤት ነበር ቅዳሜና እሁድን ያሳለፍኩት :: ባለትዳር እና የሁለት ልጆች አባት ሲሆን እሱና ቤተሰቦቹ በኑሮአቸው በጣም ደስተኞች ናቸው ::

አባትና እናቱ ጡረተኞች ሲሆኑ ባለቤቱ የምትኖረው በዚሁ ቤተሰቦቹ በሚኖሩበት ግቢ ቶማስ በሰራው ትልቅ ቤት ውስጥ ነው ። የቶማስና የባለቤቱ ፍቅር እና መተሳሰብ እንዲሁም ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር ፍፁማዊ ነው ብል አልተሳሳትኩም። ታዲያ እነዚህን ደስተኛ ቤተሰቦች ሳይ ነው የእኔ የትዳር ወኔዬ የበለጠ በውስጤ ያንሰራራው ። ሕሊና ወደ ሀገሬ እንደተመለስኩ ሌላ ምንም ምኞት የለኝም ። ትዳር መስርቼ እንደቶማስ ያለውን ቤተሰብ ከማፍራት በስተቀር ። ወደ ሀገሬ ለመመለስ በጣም ነው የቸኮልኩት ። የተማርኩትን በሥራ ተርጉሜ ሀገሬ ካለችበት የድህነት አዘቅት ለማውጣትና የራሴን ህይወት ለመምራት ነው ። ሕሊና በዚያች የደሀ ጠረጴዛችን ፊት ለፊት ሆነን ብቻ ተቀምጠን አሁን ስለምልሽ ነገር ብናወራ ምንኛ በረካሁ ። ዳሩ ምን ያደርጋል ለማውራት የምፈልገውን በዓለም ላይ ያሉትን ወረቀቶችና ብዕሮች ባስተባብር ዓይን ለዓይን ተያይተን ከምናወራው የሚሰማኝን ስሜት ያህል አያረኩኝም ።

ለማንኛውም በርትተሽ ተማሪ ። ለሁሉም እንደርሳለን ። ወደ ሀገሬ ስመለስ ስለሁሉም ነገር አጫውትሻለሁ እንቺን ካልለለቸሽ ። ለእማማ በላይነሽ የከበረ ሰላምታዬን አቅርቢልኝ ።

ያንቺው ያሬድ ።

ሕሊና ደብዳቤውን አንብባ እንደጨረሰች ብዙም ሳትቆይ ወ/ሮ በላይነሽ ሳታስበው ከማዕድቤት የጓዳውን በር ከፍተው ገቡ ። ሕሊና የነበረችበትን ሁኔታ ከወ/ሮ በላይነሽ መሸሸግ አልቻለችም ። በርበሬ የመሰለው ዓይኗን ደም የለበሰው ጉንጯ ማልቀሷን በግልፅ ያሳዩ ነበር። ወ/ሮ በላይነሽ ምንም እንዳላዩ ሆነው የፊት ለፊቱን በር ገርበብ አድርገው ዘጉና ሕሊና አጠገብ ወንበር ጎተት አድርገው ተቀመጡ ። ፊቷን በሁለት እጃቸው ቀና አድርገው በእናትነት ዓይን ከላይ እስከታች እየተመለከቷት ፣

« ምን ነካሽ ሕሊና ? ምነው ተከፋሽ ? » በማለት ለስለስ ባለ ድምጻቸው ጠየቋት ።

ሕሊና ለወ/ሮ በላይነሽ ጥያቄ መልስ መስጠት አልቻለችም ። አንገቷን ወደመሬት አቀርቅራ ዝም አለች ። ሁኔታው ሠላም የነሳቸው ወ/ሮ በላይነሽም አጠገባቸው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ደብዳቤ በእጃቸው አገላብጠው አዩት ፣ ትርጉም ሊሰጣቸው አልቻለም። እንደገና ወደ ሕሊና ፊታቸውን መልሰው « ለመናገር አልፈለግሽም ? » በማለት ስሜቷን ላለመጉዳት ብድግ አሉ ።

« እቴቴ በላይነሽ ይቀመጡ ፣ ልንገርዎት ። » አለቻቸው እንዳያመልጧት እጃቸውን ይዛ ፣ ቀና ብላ እያየቻቸው ተቀመጡ አለቻቸው ።

ሕሊና የወ/ሮ በላይነሽን ፊት ለማየት አልደፈረችም ። ጀርባዋን ሰጠቻቸውና « እቴቴ በላይነሽ አይታዘቡኝ ። በጣም ከሚወዱት ሰው አብረው ለመኖር እየፈለጉ ሊለይዎት ምን ይሰማዎታል ? » ስትል ጠየቀቻቸው ። እሳቸውም የገባቸው ይመስል ሁኔታውን እንደቀላል በመውሰድ « ምን ታደርጊያለሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ከባድ ነው ። ውሎ አድሮ ግን እየተረሳ ያልፋል ። እንኳን በህይወት ያለውን ቀርቶ የሞቱትስ ይረሱ የለ ? » በማለት ጥያቄዋን ቀለል አድርገው መለሱላት ።

ሰው ከሞተ ሞተ ነው ። ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቃብር ሲገባ ይሰናበቱታል ። ሆኖም እየኖረ የሚለዩት ፣ የሚወዱት ሰው በየጊዜው ባዩት ቁጥር ምኞትዎ እየታደሰ ይሄዳል ። ይህ የቁም ስቃይ አይደለም ? » አለቻቸው ።

« እሱስ እንግዲህ እንደባለቤቱ ነው ። ሆኖም የሰው ዕድሜ የማይፍቀው ክፉ ነገር አይገኝም ። ለጊዜው ይመስላል እንጂ መውደድስ ባታውቂው ነው እንጂ ከዕድሜ ጋር እየከሰመ ይመጣ የለ» አሏት ።

« እንዴት አድርጌ ልንገርዎት ? እም . . . ም . . . » ብላ ጥቂት ካመነታች በኋላ « ጋሼ ያሬድ ደብዳቤ ፅፎ ነበር ። በደብዳቤው ላይ ወደዚህ እንደተመለሰ እንደሚያገባ ነገረኝ ። ይሄ ማለት ደግሞ እሱ ካገባ እኔ አብሬው ለመኖር አልችልም ከእርሱ ጋር አብሬው ለመኖር ደግሞ በጣም እፈልጋለሁ » በማለት ጮክ ብላ ድምጿን በማሰማት ተንሰቅስቃ ማልቀስ ጀመረች ።

ወ/ሮ በላይነሽ የሕሊናን ፊት ቀስ ብለው ወደራሳቸው አዙረው እቅፋቸው ውስጥ አስገብተው ጀርባዋን እንደ ሕፃን ልጅ መታ መታ እያደረጉ « አልቅሽ ፣ በማልቀስ ክፉ ነገር ይወጣል ይባላል » ሲሉ አባበሏት ። ሕሊና ለቅሶዋን ከጨረሰች በኋላ እንደ ትንሽ ልጅ እየተነፋነፈች « ምን አለበት ሳላውቀው ብቀር ኖሮ ። ባልማርስ ቢቀር ። ወይ ክፉ ነገር ሰርቶብኝ እንድጠላው ቢያደርገኝ » በማለት እንባዋን ከፊቷ ጠራረገች ።

« ክፉ ለመሥራት መጀመሪያውኑ ክፋትን መልመድ ያስፈልጋል ሕሊና ። ክፋትን ያለመደ ክፉ ነገር ልስራ ቢል ዩግነት ነው የሚሆንበት ። » አሉና « ሕሊና ለመሆኑ ሲፅፍ ማንን እንደሚያገባ ጠቅሷል ? » በማለት በጥርጣሬ ዓይን ተመለከቷት ። ትንሽ አስብ አድርጋ « እሱን አልጠቀሰም ። ገና በሀሳቡ ብቻ ነው ለማግባት እንደሚፈልግ የገለፀልኝ » አለቻቸው ።

« ታዲያ አንችንስ ላግባ ቢል ምን ይታወቃል ? » ሲሉ ዓይናቸውን ከፈቱ ። ከአንገቷ ቀና ብላ ወ/ሮ በላይነሽን በክፉ ዓይኖቿ ቃኘቻቸው ። ለዚህ ጥያቄ መልስ አልሰጠችም ። ወ/ሮ በላይነሽ ከዚህ ቀደም የተባባሉት ትዝ አላቸውና ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው « እንግዲህ ጊዜ ይፈታዋል » አሉና ሕሊናን ሸሽት ተነስተው ወደ ማዕድቤት ሄዱ ። ሕሊና ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠችውን ደብዳቤ አነሳች ።

* * *

ወ/ሮ አባይነሽ መጠጥና መኝታ ቤቱን በኮንትራት ለሌላ ሰው አሳልፈው በመስጠት በየወሩ የተወሰነ ኪራይ ማግኘት ጀምረዋል። ይህም እንደቀድሞው የተትረፈረፈ የቅንጦት ኑሮ እንዲኖሩ ባያደርጋቸውም በቂ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል ። ሕሊና ለያሬድ ስትል አልፎ አልፎ ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር በመሆን ትጠይቃቸዋለች ።

እሷም ወ/ሮ አባይነሽ የሚጠይቋትን ሁሉ ማሟላት እንደማትፈልግ ብትነግራቸውም ወደ ቤታቸው በሄደች ቁጥር አዳዲስ ሀሳቦችን ማፍለቃቸውን አልተውም ። በተለይ አንድ ቀን ልትጠይቃቸው ወደቤታቸው የሄደች ዕለት ከአንድ ሰው ጋር እንድትተዋወቅ ሲለምኗት በግዴለሽነት እራሷን አስተዋወቀች ። ሆኖም ትውውቁ ይህን ያህል ወ/ሮ አባይነሽን እንዲያስቡበት ያደረጋቸው ምክንያት አልገባትም ። ቀደም ባሉት ቀናት ስለ እድገቷ እንዳሰቡ ሁሉ « እንግዲህ በሰለሻል ማለት ነው ። ምንም ቢሆን ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ ። እኛ በልጅነታችን ትዳር አንፈልግም ብለን ሀብት ንብረት ስንጋፍፍ ሜዳ ላይ ቆመን ቀረን ። » እያሉ የራሳቸውን ሁኔታ ከሕሊና ጋር ለማዛመድ ይሞክሩ ነበር ። በዚህ

አድራጎታቸው ሁለተኛ ቤታቸው አካባቢ ላለመድረስ ወስና ነበር ። ነገር ግን ያሬድ በደብዳቤው አደራ ስለሚያበዛባት አደራውን በቸልተኝነት ማለፍ እንደማትችል ተገነዘበች ። ከተጋደመችበት አልጋ ብድግ አለችና « እቴቴ በላይነሽ » ብላ ተጣራች ። ወ/ሮ በላይነሽ ኩሽና ውስጥ እንጀራ እየጋገሩ ስለነበር ለአንድ አፍታ ወደ ዋናው ቤት ብቅ አሉና ፣

« ጠራሽኝ ሒሊና ? » ሲሉ ጠየቋት ።

« እቴቴ በላይነሽ አልጨረሱም ? አንድ ነገር ልነገርዎት ነበር» አለቻቸው ።

« አንድ ጊዜ ፤ የመጨረሻ እንጀራ ነው ያሰፋሁት ተመልሼ መጣሁ ። » ብለዋት የስራ ቀሚሳቸውን ከወገባቸው አካባቢ እያስተካከሉ ወደ ማዕድቤት ተመለሱ ።

ወ/ሮ በላይነሽ ሥራቸውን ጨርሰው ከተጣጠቡ በኋላ ሒሊና ወዳለችበት ክፍል ገብተው « አሁንም ትንሽ ቆይኝ » ብለው የሥራ ልብሳቸውን አወላልቀው ነጣ ያለ የአበሻ ቀሚስ መልበስ ሲጀምሩ ሒሊና ቀና ብላ ፣

« እቴቴ በላይነሽ አዲሱን ልብስዎትን ይልበሱ » አለቻቸው በሁለት እጆችዋ አቅፋቸው እንደመላፋት እያለች ። የአበሻ ልብሳቸውን በእጃቸው አንጠልጥለው « አሞሻል ? ምን ነካሽ ? » በማለት ፈገግ አሉ ።

« እቴቴ በላይነሽ ያሬድኮ ደብዳቤ ፃፈ ። » ብላ እየሳቀች ዓይን ዓይናቸውን አስተዋለች ። እሳቸው ቀደም ሲል ሊለብሱት የሞከሩትን ቀሚስ እንደገና እያጠለቁ « ለዚህ ነው አዲስ ልብስ ለበሺ የምትይኝ ? » አሏት ቀሚሳቸውን እያጠለቁ ።

« ጋሼ ያሬድ እቴቴን እንድንጠይቃቸው ስለፃፈልኝ አንድ አፍታ ደረስ ብለን እንድንመለስ ነው » አለች ።

« ምን አለ አንቺ ብቻሽን ብትሄጂ ? እዚያ ቤት መሄድ በጣም ነው የምጠላው » አሉ ።

« አይ እቴቴ በላይነሽ እኔን ደግሞ ከእርሶ ይበልጥ ነው የሚያስጠላኝ ። እንደዚሁ ቃሉን ለመሙላት ያህል ደረስ ብለን እንምጣ ብዬ ነው እንጂ » አለቻቸው ። ሒሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ተያይዘው በራቸውን ዘጉና ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት አመሩ ።

የሾፌሮች ቡና ቤት የቀድሞ መልኩን መልሶ ተጎናጽፏል ። በአካባቢው ብዛት ያለው ሰው ውር ውር ይላል ። በውስጡም ብዛት ያላቸው ሠራተኞች ከወዲያ ወዲህ እያሉ ደንበኞቻቸውን ያስተናግዳሉ። ሒሊናና ወ/ሮ በላይነሽ በግቢው በር በኩል ገብተው ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲያመሩ ሒሊና ግራና ቀኝ ተመለከተች ።

መኝታ ቤቱ ታድሷል ። ወደ ቤት ሲገቡ ወ/ሮ አባይነሽ ብቻቸውን አልነበሩም ። አብረዋቸው በእሳቸው ዕድሜ የሚገኙ አንዲት አዛውንት ሴት ነበሩ ። ወ/ሮ አባይነሽ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው እነ ሒሊናን በመሳም ከተቀበሉአቸው በኋላ ሒሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ፎቴ ወንበር ላይ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀመጡ ።

« አያውቋትም እንዴ ? ይህች ነች እኮ የእህቴ ልጅ » በማለት ወደ ሒሊና እየተመለከቱ አዲሷን አዛውንት ሴት ከሒሊና ጋር በማስተዋወቅ « ሒሊና ነይ ሳሚያቸው ። የክፉ ቀን ጓደኛዬ ናቸው » አሉ ። ሒሊና ከመቀመጫዋ ተነስታ አዛውንቷን ሳመቻቸው። አዛውንቷም « ቆንጆ ልጅ አለዎት ። » በማለት የሒሊናን ውበት በማድነቅ ተናገሩ ።

« ምን ያደርጋል ። ታዲያ ይኸው አላገባም ብላ አሸንፋለች » በማለት ፈገግ ብለው ሒሊናን አስተዋሉአት ።

« ምነው ! ወ/ሮ አባይነሽ እስከአሁን ምን ነካዎት ? » አሉ አዛውንቷ ።

« ይሄ መከረኛ ትምህርት የሚባል ዘመን አመጣሽ አለ :: እማራሰሁ ብላ እምቢ አለች :: » ሕሲና በሀፍረትና በንዴት ውስጧ ተቃጠለ :: ነገር ለመሸሽ ስትል ራሷን ለመቆጣጠር ታገለች ::

ወ/ሮ አባይነሽ ከጥቂት ዝምታ በኋላ ንግግራቸውን ቀጠሉ ፤ « በከተማው ያሉ የጨዋ ሰው ልጆች ፣ ሀብታም ነጋዴዎች እየመጡ ያስቸግሩኛል :: ይኸው ባለፈው ሰሞን የአቶ ጌታሁን ልጅ ማነው ስሙ . . . አዎ ! አለፈ ካላስተዋወቅሽኝ ብሎ ቁም ስቃዬን ሲያሳየኝ፣ እንግዲህ በሀገሩ ደንብ በሽማግሌ ይሁን ብለን ተስማምተን እንዲያው ዳር ዳሩን ስንነግራት ጊዜ እመቤቲቷ ከነጭራሹ አኩርፋ እኔን ለመጠየቅ እኳን አሻፈረኝ ብላ ቀረች » አሉ ::

ሕሲና ከዚህ በላይ ስሜቷን መቋቋም አልቻለችም :: « ለነገሩ የማገባውን ለመምረጥ ህግ የሚፈቅድልኝ ይመስለኛል :: ሆኖም አክስቴ ያልገባዎት ነገር አለ :: ከሁሉም በፊት እራስን ማወቁ ይቀድማል :: እኔ ትምህርቴን ሳልጨርስ ለግርድና ባል አላገባም :: ባገባም ቢጤዬን እንጂ ለገንዘብ ብዬ ባርነት አልገባም :: አክስቴ እውነት ትመራለች :: ነገር ግን ሀቅ መናገሩ ከሺ ውሸት የበለጠ ያረካኛል :: የእርስዎ ሀብት ከራስዎ ተርፎ ሰው ያስተዳድር ነበር :: ያ ሀብት ሲታመሙና ዕርዳታ ሲፈልጉ እየመነመነ መጣ :: በመጨረሻም አሁን ካለንበት ደረጃ አደረሰዎት :: አክስቴ ሁሉም ሀብት ያለው ከዚህ የተለየ አይደለም :: የማይሰረቅ ፣ የማይዘረፍ ፣ የማይመነምንና የማይነጥፍ ዘለዓለማዊ ሀብት ትምህርት ነው :: ትምህርት የራስን የዕውቀት አድማስ እያሰፋ ሀገርን ያበለጽጋል :: ወገንን ከድህነት ያወጣል :: ትምህርት እራሱ የብልጽግና ምንጭ እንደመሆኑ መጠን ሀብትን ያፈራል :: ስለዚህ አይሳሳቱ :: . . . ደግሞ እኔ እራሴ ነኝ ለራሴ ህይወት ወሳኝ :: በመሆኑም ከዛሬ ጀምሮ በእኔ ሥም ማንንም ቢሆን ሰባልነት ወይም ለመተዋወቅ እንዲነጋገሩ አልፈቅድልዎትም :: አሁንም ለመምጣት አልፈለኩም

ነበር :: ለጋሼ ያሬድ ስል ነበር አመጣጡ :: ነገር ግን ከእንግዲህ ወዲህ ሌላ እርቅ አይኖርም :: እኔ የእርስዎ የእህት ልጅ አይደለሁም :: እርስዎም ለእኔ አክስቴ አይደሉም :: ከዛሬ ጀምሮ እዚህ ደጃፍዎ ላልገኝ ቃል እገባልዎታለሁ » ብላ ከተቀመጠችበት ተነስታ ወ/ሮ በላይነሽን ሳትጠብቅ ወጥታ እየበረረች ወደ ቤቷ ሄደች ::

*   *   *

ወ/ሮ በላይነሽ ሕሲና መኝታ ቤቷ ውስጥ ገብታ ነበር የደረሱት :: መኝታ ቤት ገብተው ሕሲናን ካዩዋት በኋላ ለጥቂት ጊዜያት ባሉበት ቆመው በዝምታ አስተዋሉአት :: እሷም ንዴቷ ስላልበረደላት ለመናገር አልቃጣችም :: በዝምታ አልፋቸው ወደ ሳሎን በመሄድ በመጽሐፍ መደርደሪያ ካሉት መጽሐፍት አንዱን ወጣ አድርጋ ገለጠች :: መጽሐፉን ታያለች እንጂ እያነበበችው አልነበረም :: የገለጠችውን መጽሐፍ አትኩራ እየተመለከተች የምታስበው ቀደም ሲል ስለፈጸመችው ድርጊት ነበር :: በአንድ በኩል በታላላቆችዋ ፊት ያን ንግግር ማድረግዋ ቢቆጫትም በሌላ በኩል በወ/ሮ አባይነሽ ላይ በወሰደችው እርምጃ ረካች :: ወ/ሮ በላይነሽ ከመኝታ ክፍላቸው ወጥተው ሕሲና አጠገብ ሄደው በመቀመጥ በዝምታ ተመለከቷት :: እሷም መጽሐፍዋን እየተመለከተች ትንሽ ከቆየች በኋላ ያሉበት ሁኔታ ስለከበዳት በንግግር ለማቃለል ያህል « አጠፋሁ እንዴ እቴቴ በላይነሽ ? » በማለት ጠየቀቻቸው ::

ወ/ሮ በላይነሽ እራሳቸውን በአሉታ እየነቀነቁ ፣ በሀዘን ዓይን በመመልከት « ደግም አይደል ልጄ ታላላቆችሽን መግፋት » አሏት ::

« ምኑን ገፋኋቸው ? ገፉኝ እንጂ :: ከመቼ ወዲህ ነው እሳቸው የእኔን ደህንነት ፈላጊ ሆነው ትዳር ሲመሰርቱልኝ ያሰቡት ?

እንዲያው ለራሳቸው ብለው ነው እንጂ ነጋዴ አጋብተው የራሳቸውን ንግድ በጎን ለማቀላጠፍ ። ለውማ ቢሆኑ ኖሮ የኔን ትምህርት ከማጥላላትና በህይወቴ ምንም እንዳልሰራሁ ከመቁጠር አይዞሽ ፣ በርቺ ፣ ተማሪ ፣ አይሉኝም ? እሳቸው ዕድሜያቸውን በተንኮል የጨረሱ ምንጊዜም ቢሆን ለውን ከመተናኮል ወደኋላ አይሉም። ከማን ቢቆጥሩኝ ነው ከአከሌ ነጋዴ ጋር አስተዋውቅሻለሁ ሀብታም ነው የሚሉት ? » በማለት ቁጣዋን እንደገና ለወ/ሮ በላይነሽ ለመግለጽ ሞከረች ።

« ለምን በክፉ ታስቢዋለሽ ልጄ ! እሳቸው ለአንቺ ደግ ለመዋል ብለው ይሆናል ። የአንቺን ሀሳብ የት አወቁ ? » በማለት ለማብረድ ሞከሩ ።

ሕሊና በንዴት ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ተነሳችና « የት ያውቃሉ የእሳቸውን ዘዴ ? እቴቴ በላይነሽ ! » አለች ድምጿን ዘለግ አድርጋ ። « እሳቸው የብዙ መጥፎ ታሪክ ክምችት ናቸው ። በእሳቸው ዘንድ ደግነትና ሀቀኝነት ቦታ የላቸውም ። እንግዲህ የዛሬውን አርእስታቸውን ላብራራልዎት ። « አሰፋ » የሚሉት እውነትም የሀብታም ነጋዴ ልጅ ነው ። ተወልዶ ያደገው እዚሁ አቃቂ ነው ። አሁን ትምህርት እንቢ ብሎ ከዘጠነኛ ክፍል ኮብልሎ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቷል ። ይህ አሰፋ የተባለው ከት/ቤታችን እንኳን ሁለት ሴት ልጆችን አገባችኋለሁ በማለት ከትምህርታቸው አሰናክሎአቸዋል ። አሁን የት እንዳሉ አይታወቅም ። አንደኛዋን ልጅ አውቃታለሁ ። ከዚሁ ከገጠር ነው የምትመጣው ።

« የአንድ ገበሬ ልጅ ነች ። በትምህርቷ ጎበዝ ነበረች ። ነገር ግን ምን ያደርጋል ፣ የዕድል ነገር ሆኖ ከዚህ ከአልባሌ ሰው ጋር አጋጠማት ። እንዲሁ በአንዳንድ ብርቅርቅ ነገሮች በመደለል ይዟት አሸሸ ገዳሜ ሲል ከረመና ልጅቱ እንደድንገት ስታረግዝ አባትነቱን ይክድና ዘወር በይ አላት ። ከቀን ወደ ቀን ሆዷ እየገፋ ሲመጣ ልጅቱ

ትምህርቷን ለማቋረጥ ተገደደች ። በመጨረሻም ከነአካቴው ሀገር ጥላ ሸሸች ። እንግዲህ ይህን ሰው ነው የጨዋ ልጅ ፣ ሀብታም ነጋዴ እያሉ ሊያጋቡኝ ያዘጋጁልኝ ። »

« ታዲያ አክስትሽ ይህን ሁሉ የት ያውቃሉ ብለሽ ነው ? እሳቸው የሚያውቁት አባትየውን » ሲሉ ሊሞግቷት ሞከሩ ።

« አይ እቴቴ በላይነሽ ! ስለዚህ ልጅ አብጠርጥረው ነው የሚያውቁት ። ሆኖም እሳቸው ምን ቸገራቸው አገባሁ ብሎ የእኔን ዕድል አበላሽቶ ቢተወኝ ። መሄጃ የሌለኝ እንደገና ወደ እሳቸው ቤት ገብቼ መጫወቻቸው ለማድረግ ነው እቅዳቸው ። እንዲያውም እኔን ጥሩ ትዳር ሊመሰርት ከሚችል ሰው ጋር እንድጋባም አይፈልጉም ። ምክንያቱም ከጥሩ ሰው ትርፍ አያገኙበትም ። እሳቸው ሁለንተናቸው የተመሠረተው በመቸርቸር ላይ ነው ።ህይወታቸውስ የተመሠረተው እንካ አትርፊህ አምጣ በሚለው ዘይቤ አይደል ! » ስትል እያንገሸገሻት ተናገረች ።

« እሺ ! ሕሊና ያልሽው ሁሉ ይሁን እንበል ። ዞሮ ዞሮ ማግባት አለብሽ እኮ » አሏት ። ሕሊና ፈገግ ለማለት እየሞከረች ፣ እጆችዋን ወደኋላዋ አጠላልፋ ዓይኖችዋን ኮርኒሱ ላይ ተክላ « እቴቴ በላይነሽ አሁን ተማሪ ነኝ ፣ ስለዚህ ጉዳይ አስቤም አላውቅም ። ግን አንድ ነገር አውቃለሁ ። በህይወቴ ከጋሼ ያሬድ የሚለየኝ ነገር ቢመጣ በክፉ ነው የምቀበለው ። ለማንኛውም ጊዜ ይፈታዋል » ብላ ባሉበት በልጅነት ዓይነት ስሜት አንገታቸው ላይ ተጠመጠመች ። እሳቸውም እንደ ቀልድ አድርገው « አንቺ ከያሬድ አልለይም ትያለሽ ከኔስ ጋር እንዴት ነው ? መቼ ነው የምንለያየው ? » በማለት ሲጠይቋት ደነገጠች ።

« እርስዎና እኔማ ተለያይተን ተገናኝተናል ፤ ሁለተኛ መለያየት ግን አይኖርም » አለቻቸው በእርግጠኝነት ስሜት ።

* * *

ክረምቱ አለፈ ። መስከረም ጠባ ። የአደይ አበባ በየቦታው ፈካ ። የጠዋት ፀሐይ ምድሩን በብርሃንዋ አድምቃዋለች ። ከታክሲው እንደወረዱ ሀሰን በሁለት እጁ ሻንጣ አንጠልጥሎ ፣ ሕሊና አንድ ተንጠልጣይ ባለ ጌጥ ዘንቢል ይዛ ተከታትለው ወደ ግቢው ዘለቁ ። በበሩ ላይ በተሰራው ቀስተደመና « የኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ » የሚል ጽሑፍ በትልቁ ተጽፏል ።

ሀሰን ፊትለፊት ከቆመው ዘበኛ ጋር የተወሰነ ጊዜ ያህል ተነጋገረና ወደ ሕሊና ዘወር ብሎ እንድትከተለው ምልክት አሳያት ። ተያይዘው የተማሪዎች ጉዳይ ክትትል ቢሮ ቀረቡ ። የተጠየቀችውን ማስረጃ ካቀረበች በኋላ የተመደበችበትን የመኝታ ክፍል የሚገልፅ ደብዳቤ ተሰጣት ። ጓዟን ተሸክመው ወደዚያው ሲያመሩ ወደ አዲስ ኑሮ በመግባትዋ ትንሽ ቅሬታ የተሰማት ይመስል ነበር፡፡ ሆኖም ምንም አማራጭ አልነበራትም ። መማር አለባት ። የተመደበላትን መኝታ ተረክባ ዕቃዎቿን እስከምታስናዳ ሀሰን የትምህርት ቤቱን ግቢ እየጎበኘ ጠበቃት ።

« በይ እንግዲህ እዚህ መግባት ነው የምፈልገው ብለሻል ። ይኸው መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ » አለና ለጥቂት ጊዜ ሊያጠናት ሞከረና « ምነው ቅር አለሽ ? በምርጫሽ ተፀፀትሽ እንዴ ? » ሲል ጠየቃት ። እሷም አንገቷን ቀና አድርጋ ፈገግ አለችና « እንዲያውም! በምርጫዬ በመመደቤ በጣም ነው ደስ ያለኝ ። ነገር ግን እኔን ያሳሰበኝ ከእቴቴ በላይነሽ መለየቴ ነው ። አሁን እንዴት አድርጌ ልለምደው ነው ? » አለችው አንገቷን ቀና አድርጋ በፈገግታ እያየችው ።

« እንግዲህ ሆድ አይባስሽ ? እሳቸው ምን ይሆናሉ ብለሽ ነው? ይልቁንስ ለራስሽ አስቢ በዚህ ላይ በየሣምንቱ እየተመላለሽ መጠየቅ ትችያለሽ ። » ሲል አፅናናት ፈገግ እንዳለ ። « አይ ጋሼ ሀሰን እኔማ ወድጄ የገባሁበት ነው ። ከእንግዲህ ወዲህ ልጅነት አይመለስም ። ትምህርቴን መከታተል ነው እንጂ ። »

« መቼ መጥቼ ልውሰድሽ ? የእኛን ቤት ማየት አሰብሽ እነእማዬ ካላመጣሀት እያሉ አስቸግረውኛል » አላት ።

« እንግዲህ መጀመሪያ እስኪ ከትምህርቴም ከኑሮውም ጋር ልለማመድና እናስብበታለን » አለችው ። ቀጥላም « ጋሼ ሀሰን መቼም በጣም ነው የማመሰግነው ፤ በል እንግዲህ ለከሰዓት ሥራ እንዳይረፍድብህ ። » ስትል ለስንብት ሰላምታ እጅዋን ዘረጋች ። እሱም በጥሞና እያያትና እጇን እንደጨበጠ « አይዞሽ ሕሊና በርቺ ። የሚቸግርሽ ነገር ካለ በስጠሁሽ ስልክ ቁጥር ደውይልኝ » አለና መንገዱን ጀመረ ።

« ደህና ዋል ። ለእቴቴ በላይነሽ በደህና መድረሴን ንገራቸው፡፡ አይዞዎት አታስቡ ሳምንት መጥቼ እጠይቅዎታለሁ በልልኝ » አለች እንዲሰማው ድምጿን ከፍ አድርጋ ። ሕሊና ወደ ሴቶች የመኝታ ህንፃ ስትመለስ ፣ ክፍሎቹ ሁሉ በገቢ ተማሪዎች ተወረው ነበር ። በአጭር ጊዜ ጓደኝነት ፣ እርስ በእርስ መተዋወቅ ፣ እልጋ ማንጠፍ ፣ መተጋገዝ . . . ተጀምሯል ።

ሕሊና ክፍሏ እንደገባች ከአንደኛው ሻንጣዋ ውስጥ አንሶላና የአልጋ ልብስ አውጥታ የተመደበላትን አልጋ ማንጠፍ ጀመረች ። በዚህ ወቅት አንድ ጠየም ያለች መልከ መልካም ልጃገረድ ሕሊና የምታነጥፈውን አንሶላ ከአንድ በኩል እያገዘቻት ንግግር ጀመሩ ።

« አሁን ገና ነው የመጣሽው ? » ስትል ሕሊናን ጠየቀቻት አዲሷ ልጅ ። « አዎ ቤቴ ቅርብ ስለሆነ ለምን ከዘመዶቼ ጋር ትንሽ

አልቆይም ብዬ ዛሬ መጣሁ ፡፡ አሁንም በስንት መከራ ሳልፈልግ በግድ ነው የመጣሁት » አለች ፡፡

« የት ነው ሰፈርሽ ? »

« አቃቂ ፡፡ »

« ውይ ታድለሽ እኔ የመጣሁት ከከንባታና ሐዲያ ነው ፡፡ ቤተሰቦቼ የሚኖሩት ሆሳዕና ነው ፡፡ »

« ሥሜ አልማዝ ኤርሞሎ ይባላል እንተዋወቅ » በማለት እጇን ዘረጋችላት ፡፡

« እኔ ደግሞ ሕሊና እባላለሁ » በማለት ተጨባበጡ ፡፡

ከዚያን ቀን ጀምሮ አልማዝና ሕሊና ጓደኛሞች ሆኑ ፡፡ የሕሊናና የአልማዝ ፀባይ በአብዛኛው ይመሳሰላል ፡፡ ሁለቱም ቢሆኑ ሰውን በቶሎ መልመድ አይችሉም ፡፡ የእነሱ የራሳቸው ግንኙነት እንኳን ከጊዜ ብዛት እየደረጀ መጣ እንጂ በመጀመሪያው ሰሞን ያዝ ለቀቅ ያለ ፣ በቀዘቀዘ መሠረት ላይ የተጣለ ነበረ ፡፡ ሆኖም ቀስ በቀስ እየሞቀና ግንኙነታቸው እየተጠናከረ መጣ ፡፡

ሕሊና የመጀመሪያው የትምህርት ቀን በጣም ከብዷት ነበር፡፡ በኮሌጅ የሚሰጠውን የትምህርት ዓይነትና ብዛት በስሙ ብቻ በመስማት በጣም ፈርታ ነበር ፡፡ በዚህ ላይ በእሷ የትምህርት ዘርፍ የተመደቡት በሙሉ ወንዶች ነበሩ ፡፡ ወንዶቹን ስመቅረብ ፍላጎት አልነበራትም ፡፡ እናም ሀሳቧን እንኳ በመካፈል የምትረዳት አንድ የሴት ጓደኛ አጠገብዋ አላገኘችም ፡፡ ነገር ግን ይህ ሁኔታ ለብዙ ጊዜ አልቀጠለም ፡፡ ትምህርቱ ተጀምሮ ጥቂት ቀናት እንደተካሄደ ሕሊና በትምህርት ክፍሏ የሚገኙትን ወንዶች ልጆች እንደማንኛውም የሴት ጓደኛ በመቅረብ አብሮ መወያየትና የሚሰጡአትን ሥራዎች ተባብሬ በመሥራት ቀደም ሲል የነበራትን ፍርሃት አስወግዳ በብዙ ነገር ተለወጠች ፡፡

የመጀመሪያዎቹን ሁለት ሣምንታት ከኮሌጅ ቅጥር ግቢው ሳትወጣ ቆየች ፡፡ አልፎ አልፎ ከአልማዝ ጋር ግቢው ውስጥ ደስ ወደአላቸው ቦታ በመሄድ ለመዝናናት ይሞክሩ ነበር ፡፡ ሁለቱ ጓደኛሞች ከመመገቢያ ሰዓትና ከትምህርት ውጪ ያለውን ጊዜያቸውን አብረው ነበር የሚያሳልፉት ፡፡በወል የትምህርት ዘርፍ ላይ ሲገናኙም አንድ ላይ ቦታ ፈልገው ይቀመጡ ነበር ፡፡ ራሳቸውን ከኮሌጁ ባህሪ ጋር ካላመዱ በኋላ አቃቂ ሄደው አንድ ቀን አድረው ተመለሱ ፡፡ ሕሊና በትምህርት ቤት ውስጥ ባለው የክልል ወጣት ማህበር ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ ጀመረች ፡፡ በስብሰባዎች ላይ በምታቀርበው የበሰለ ሀሳብና በሥነ ምግባርዋ የተሰጣት አክብሮት ከፍተኛ ሆነ ፡፡ የት/ቤት መሠረታዊ የወጣቶች ማህበር ውስጥ በኮሚቴ አባልነት እንድትሠራ ተመረጠች ፡፡ በትምህርቷ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ በቃች ፡፡ በመምህሮቿ ዘንድ እንደ ምሳሌ የምትጠቀስ ተማሪ ሆነች ፡፡

አንድ ቀን አልማዝ ከምሳ በኋላ ባለው የዕረፍት ጊዜ ለሕሊና ከውጭ የተላከ የታሸገ ፖስታ ሰጠቻት ፡፡ ሕሊና የያሬድ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀባትም ፡፡ ልቧ እየዘለለባት በችኮላ ቀዳ ማንበብ ጀመረች ፡፡

« ሕሊና በችኮላ የፃፍኩት ደብዳቤ ስለሆነ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ ፡፡ ሆኖም በፈተና ላይ ስለሆንን ጊዜ ስለአጠረኝ መሆኑን ከተረዳሽ የጠየኩትን እንደማትነሽኝ ተስፋ አደርጋለሁ ፡፡ ይሄውልሽ የመጨረሻ ፈተናችንን እየወሰድን ነው ፡፡ ስመምጣት ከእንግዲህ የሚቀረን ጊዜ በወራት አነስተኛ ጊዜ መሆኑን ልገልፅልሽ እወዳለሁ ፡፡ ሕሊና ከአንቺ ጋር መገናኘቱ ህልም ህልም ነው የሚመስለኝ፡፡ ጊዜው እየረዘመ ሲመጣ ሰው የተለየውን እየረሳ ይሄዳል ፡፡ ሆኖም የኔ በተቃራኒው

መርሳት ሳይሆን ማስታወሱ ነው ያገረሸብኝ ። ሕሊና እንቺም እኔ ስመጣ ፈተናሽን ጨርሰሽ የክረምት የዕረፍት ጊዜ ስለሚሆን ናፍቆታችንን ለመወጣት ብዙ ጊዜ እንደሚኖረን ተስፋ አደርጋለሁ። ሕሊና ጤናዬ የሰጋር ፈረስ ያህል ገስግሶ ለመምጣት ከመዘጋጀት በስተቀር ጤንነቴ የተሟላ ነው ። ሀሳቤ ዘወትር ከእናንተ ጋር ነው ። ለማንኛውም ስመጣ በሠፊው እናወራዋለን ። ጤንነትሽን ጠብቂ ፤ ትምህርትሽን በርቺና ተማሪ ። መልካም የትምህርት ጊዜ ።

ያንቺው ያሬድ ።

ሕሊና ደብዳቤውን ከጨረሰች በኋላ ቀና ብላ ወደ ደረቷ አስጠጋች ። « እፎይ ታድዬ ! » ብላ በረጅሙ ስትተነፍስ ሁሉ አጠገቧ ቆማ የነበረችው አልማዝን አላየቻትም ። አልማዝ ጠጋ ብላ ሕሊናን እየተመለከተች « እጮኛሽ ነው ? » ስትል ቀስ ብላ ጠየቀቻት አጠገቧ አልጋው ጫፍ ላይ እየተቀመጠች ። ዞር ብላ አልማዝን ለጥቂት ጊዜ ካየቻት በኋላ « ወንድሜ ነው ። አቃቂ ፎተግራፉን ያሳየሁሽ » አለቻት ።

ሕሊና አቃቂ ተመልሳ የክረምት ዕረፍቷን የመጀመሪያ ሣምንት አገባደለች ። ወ/ሮ በላይነሽ የሕሊናን ተመልሶ መምጣት እንደ ትልቅ ደስታ ነበር የቆጠሩት ። መቁጠር ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ለቀሰብ ከሚሰጣቸው የወር ሂሳብ ላይ ቀናንሰው አንድ ትልቅ በግ ገዝተው መቀበያ ደም አፍስሰዋል ። ሕሊና እንደዚህ ዓይነት ድግስ ይሆናል ብላ አላሰበችም ነበር ። በመጀመሪያው ቀን ሀሰን በወ/ሮ በላይነሽ ትዕዛዝ አዘል ልመና ለእራት ግብዣ አቃቂ መጥቶ ነበር ።

የቅርብ ጎረቤቶቻቸው ፣ የኩቻ እናትና አባት የደስታቸው ተካፋይ ሆነዋል ። ይኸ ሁሉ የእቴቴ በላይነሽ ስሜት ነው ። ለሕሊና ግን ምንም አልነበረም ። ጋባዥዎችዋን ለማስደሰት ስትል ከምታደርገው እንቅስቃሴ የዘለለ አይደለም ። የእሷ ደስታ ያሬድ ሲኖር ነው ። እናም ደስታዋ ደስታ ይሆን ዘንድ የያሬድን መምጣት በመጠበቅ በተስፋ ተሞልታለች ።

ሐምሌም እንደ ሰኔ ሊሰናበት አንድ ሳምንት ቀረው ። የያሬድ ነገር ግን ሽታውም በአካባቢውም አልደረሰም ። ሕሊና እጅግ ተረበሸች ። ሀሰን ጭንቀቷን ተረድቶ ስለነበር ለትምህርት ከያሬድ ጋር ከተላኩት አንዱ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ አግኝቶት ስለያሬድ ሁኔታ ጠይቆት ነበር ።

« ሕሊና ያሬድ ሐምሌ 27 ነው የሚመጣው ። አብሮት የነበረው ጓደኛው የአውሮፕላን ትኬት በማጣቱ ነው ወደ ኋላ የቀረው ብሎኛል » ሲል ሊያፅናናት ሞከረ ። ለሕሊና ግን የጊዜ ሆድ እንደ ላስቲክ በመሳብ ሐምሌ 27ን ያራቀው መሰላት ። ቀኑ እንዲመሽላትና የሚቀጥለው ቀን በቶሎ እንዲሰወጥ እራስዋን በስራ ጠመደች ።

የጊዜ ዕርዝመትና እጥረት እንደባለቤቱ ነው ። ለሕሊና እንደ ላስቲክ የሚሳበው ጊዜ ለሌላ ሰው ደግሞ ቀኑ እጥሮ ሳያውቁት ሊያልፍባቸው ይችላል ። ሆኖም ተፈጥሮ ለማንም አታዳላም ኡደቷን ጠብቃ በጊዜ ቦይ ስትፈስ ቆይታ ሐምሌ 27 ላይ ስትደርስ ጭራሽ የቆመች መሰለች ።

*   *   *

እንዳይነጋ የለም ነጋ ። ጊዜ ጊዜን አምጦ ጊዜን ወልዶ አደረሰ ። ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ሕሲና እራስዋን አስማምራ ጉዞዋን ወደ አዲስ አበባ አመራች ። ከአቃቂ በታክሲ ቦሌ ስትደርስ በየቦታው በርካታ ሰዎች ተሰብስበው ታዩዋት ። ሲቃና ጉጉት እየተናነቃት ፣ ከቦታ ቦታ እየተሯሯጠች ሀሰንን ለማግኘት ሞከረች። ሀሰን ግን በቦታው የለም ። ዋናው መግቢያ በር ላይ መጠበቅ ጀመረች። መኪና በቆመ ቁጥር ሀሰን የሚወጣ እየመሰላት ፤ ግን ደግሞ ሌላ ሰው እየሆነባት ሺህ ዓመታት የሆነባትን ያህል በትዕግስት ጠበቀችው ። እየቆየች ፣ እራሷን እያረጋጋች ስትሄድ የሆነ ስጋት በአዕምሮዋ ውስጥ አንዣበበ ።

« ጋሼ ሀሰን ለእኔ በማዘን ዋሽቶኛል ማለት ነው ። አሁን የማይመጣው በነገሩ ስላፈረበት ይሆን ? » ስትል አሰላሰለች ።

« የለም አያደርገውም ፤ ለምን ይዋሻል ? ውሎ አድሮ ለሚገለፅ ነገር ! ጋሼ ሀሰን እንደዚህ ዓይነት ቀላል ሰው አይደለም » እያለች እራሷን ለማሳመን ታገለች ። በእርግጥ ሀሰን ቃልአባይ አልነበረም ። ከቀጠሮአቸው ሰዓት ቀድሞ ደርሶ ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ከመኪና ሲወጣ ሕሲና በሩቁ አየችው ። ሕሲና ሰውነቷ ሁሉ በድን ሆነባት ። መንቀሳቀስ አልቻለችም ። ባለችበት ደርቃ ቀረች ። ዓይኖችዋ ብቻ የሰዎቹን ወደእሷ መቅረብ ተጠባበቁ ። ሀሰን አጠገቧ እንደደረሰ ሠላምታ አቀረበላት ። እራሷን ስታረጋጋ ሁኔታው ተገለጸላት ።

ቀጠሮአቸው ሀሰን ያሬድን ሊያመጣላት ሳይሆን አብረው ለመቀበል ነበር ።

« ተዋወቁ ፤ የእኔም የያሬድም የጋራ ጓደኛችን ነው » አለ ሀሰን ።

« ፀጋው እባላለሁ » አለና ለሕሲና እጁን ዘረጋ ።

« ሕሲና »

ጊዜው ገና ነበር ። ሦስቱም ለመቆያ ያህል አቅራቢያቸው ወደ ነበረው ካፍቴሪያ አመሩ ። ሀሰንና ፀጋው ቡና በወተት አዘዙ ። ሕሲና ግን ምንም መቅመስ ባትፈልግም ደረቅ ሻይ ብቻ እንዲመጣላት አዘዘች ። ሠዓቱ ነጎደ ። አራት ሰዓት ደረሰ ። የሕሲና መንፈስ መረበሽ ጀመረ ። በዚሁ መካከል የትልቅ አውሮፕላን ድምጽ ተሰማ ። ሕሲና ባለችበት ቆማ የሰማችውን ድምጽ ለማረጋገጥ ጆሮዋን አቀናች ። ፀጋው እነ ሕሲና ወደ ቆሙበት እራመድ እራመድ ብሎ « ኢንተርፍሎግ ነው » በማለት አበሰረ ።

ሕሲና በውበት ጥበብ እንደ ጠዋት ጮራ ፈካች ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የፈዘዙት ዓይኖችዋ እንደብርሃን መብራት ጀመሩ። ሕሲና ያሬድ ከአውሮፕላን ሲወርድ የሚታይበትን ቦታ መርጣ በጉጉት ሲቃ ተይዛ ቆመች ። አውሮፕላኑ መንገደኞቹን ማውረድ ሲጀምር ፀጋው ፣ ሀሰንና ሕሲና ዓይናቸው እስኪደክም ድረስ በርቀት የሚወርዱትን ሰዎች አንድ በአንድ ተመለከቱ ።

መጀመሪያ የወረደው የውጭ ሀገር ዜጋ ነበር ። ሁለተኛ፣ ሶስተኛ አሁንም የለም ። የሕሲና የልብ ትርታ እየጨምረ መጣ ። መላ ሰውነቷ ሲርገፈገፍ ለተመለከተ ሰው የበሽታ እንጂ የጤና ነው ለማለት አያስደፍርም ። ሰባተኛ . . . ፣ ስምንተኛ ሰው በአውሮፕላኑ ተንቀሳቃሽ ደረጃ በመውረድ ላይ ነበር ። አሁንም ያሬድ የለም ። የሕሲና ፊት በወረደው ሰው ቁጥር ልክ እንደ ሲኒማ ቤት መብራት ቀስ እያለ እየጨለመ ፣ ፊቷ እየጠወለገ ፣ ዓይኖችዋ ከዳናቸውን እየለበሉና እያነሉ ሲሄዱ ተሰማት ። የቀራት የሞኝ ተስፈኝነት ብቻ ነበር። . . . አሥራ አራት . . . አሥራ አምስተኛ ሰው በመውረድ ላይ እንዳለ ሕሲና እንደ ሕፃን ልጅ እየዘለለች « ጋሽ ያሬድ . . . ጋሽ ያሬድ ! » እያለች ጮኸች ።

ሒሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ደስታቸውን ለመግለፅ ፣ « እንኳን ደህና መጣህ » ለማለት የሚመጡትን የሥራ ጓደኞቹንና ጎረቤቱን ሳይታክቱ በማስተናገድ ለአንድ ሳምንት ያህል ቆዩ ። የሰው ብዛት ሒሊናን ከያሬድ ጋር ለብቻ ለመጫወት ዕድል አልሰጣትም ። ሌላው ቀርቶ የዓይኖቿን ረሃብ ለማስታገስ አልቻለችም ። መቼም ሥራ ሥራ ነውና ያሬድ ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ለመሥሪያ ቤቱ መድረሱን ማስታወቅ ነበረበት ። ቅሬታ እየተሰማት በሳምንቱ መጀመሪያ ሰኞ ዕለት ያሬድን እስከ መኪና ተራ ሸኝታው ተመለሰች ።

ያሬድ በፊት የነበረው ጸባዩ አልተለወጠም ። ሆኖም ዝምታን አበዛ ። ጎትጉታ እንዲያጫውታት ካላደረገችው በስተቀር እራሱ የጨዋታ መነሻ ፈጥሮ መቀጠል አይፈልግም ። ነገር ግን ሒሊና እንዲናገርና እንዲያወራት ስትል ብቻ ስለ ጥቃቅን ነገሮች ሳይቀር ለማንሳት ብትሞክርም የሚያስደስት ውጤት አልነበረውም ።

በዚህ ሁኔታ ናፍቆትዋን ሳትወጣው አዲስ አበባ ሄደ ። ከአዲስ አበባ ሲመለስ ይበልጥ ተለውጦ ፣ ጠቁሮ ፣ ከስቶ ፣ ገርጥቶ ነበር ።

« ሒሊና መቼም አሁንም ደስ አይልሽ ይሆናል ። ሆኖም መሆን ያለበት ነገር ነው . . . » አለና ሀሳቡን ሳይጨርስ ወንበር ጎተት አድርጎ ተቀመጠ ። ሒሊና በማታውቀው ጭንቀት ጭንቅላቷ እንደተወጠረ አጠገቡ አረፍ አለች ።

« እንዴት አድርጌ ልንገርሽ ? »

« እንደዚሁ ዝም ብለህ ንገረኝ ጋሼ ያሬድ ሙት አልፈራም » አለችው ።

« አትፈሪም ? እውነትሽን ነው ! »

« በቃ አዎ ! ብፈራስ የት እደርሳለሁ ። »

« ይኸውልሽ እንደገና ወደ ሌላ ቦታ ተቀይሬ መሄዴ ነው » አላት ።

« ደግሞ የት ልትሄድ ነው ? ትፈራለች ብለህ ነው የምትቀልድብኝ ? » በማለት ሆድ ባሳትና እንደማኩረፍ አለች ።

ያሬድ የጀመረውን ቶሎ ለመጨረስ ስለፈለገ « እውነቴን ነው አሁን የተመደብኩት ኮምቦልቻ ወሎ ውስጥ ነው ። አስቸኳይ ነገር ሳይፈጠር አይቀርም ። አለቃዬ እንዲያውም አርፍደሃል ነገውኑ እንድትሄድ ብለው ነው ያዘዙኝ » አለና ፀጥ አለ ። ከዚህ በኋላ ሒሊና የምትወደው ዘመዷ እንደሞተባት ሁሉ የለቅሶ ጩኸትዋን ማልቀስ ጀመረች ። ያሬድ አቅፎ ሊያባብላት ሞከረ ።

« ወይኔ ዕድሌ ! ወይኔ ዕድሌ ! » ልቧ ተሰብሮ ነበር ። እጆቿን ጠረጴዛ ላይ አስደግፋ ፊቷን በእጆቿ መሃል ቀብራ ለረጅም ሰዓታት ስታለቅስ ቆየች ። ወ/ሮ በላይነሽና የኩቻ እናት ሊያስቆሟት ታገሉ ፤ አልቻሉም ። በመጨረሻ ያሬድንም ሆድ ባሰው ።

« እኔ አንቺ ስታለቅሺ ሆድ ይብሰኛል ። እንደዚሁ ሳልናገር ብጠፋ ኑሮ ይሻልሽ ነበር ? » ሲል ተቆጣ ። ቁጣው ፈጣን መልስ አስከተለ ። ለቅሶዋን ለመቆጣጠር ሞከረች ። ሆኖም ተረጋግታ መቀመጥ አልቻለችም ። በህይወቷ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር የዚህ ዓይነት ራስ ምታት ያመማት ። ያሬድና በላይነሽ ደጋግፈው አልጋ ላይ አስተኟት ።

ከእንቅልፏ የቀሰቀሳት ያሬድ ነበር ። የእራት ሰዓት በመድረሱና የጤንነቷም ሁኔታ ስላሳሰበው ነበር እንድትነሳ ያደረገው። አልጋዋ ላይ ተኝታ ትንሽ እንቅስቃሴ ካደረገች በኋላ ፈጠን ብላ ወረደች ። ያሬድ በእጁ አቅፎ ወንበር ስቦ አስቀመጣት ። ወ/ሮ በላይነሽ ምግብ አቀረቡና ሒሊናን በማጉረስ እራቷን አበሏት ። እራት ከተበላ በኋላ ያሬድ እንድትተኛ ለመናት ።

« አንተ ነገ እሄዳለሁ እያልክ ለምኑ ነው መኝታ ? » አለችው በቅሬታ ።

« እራስሽን ያምሻል ተኝተሽ እንጫወታለን » አላት ።

« አልፎልኛል ። የራስ ህመምም እንቅልፍም የለብኝ » አለችው ።

« እንግዲያውስ ተቀምጠን እናውራ ? » በማለት የለበሰውን ጋቢ እያስተካከለ « በይ ጨዋታውን አምጪ » አላት ።

ሕሊና የፈለገችው ጨዋታ ሳይሆን ያሬድን ቁጭ ብላ ማየት ነበር ። ፊቷን በሁለት እጆቿዋ መሀል ቀብራ ክንዷን በጠረጴዛው ላይ አንተርሳ አተኩራ ዓይን ዓይኑን ማየት ጀመረች ። ያሬድን ቀደም ብሎ ውጪ ከመሄዱ በፊት የነበረውን ፀባይ በማንፀባረቋ እየተገረመና እየተደሰተ ፊቷን በዓይኖቹ ሲዳስሳት ቢሞክርም ብዙ ለመቆየት አለቻለም ። የሕሊና የራስ ህመም ምቀኛ ሆነበት ። በህመም ስሜት እራሷን ስታወዛውዝ ከኄደበት ሀሳብ ነቃ ።

« ምነው አመመሽ ? ሄጂና ጋደም በይ » አላት ። ነገ የምትሄድ ከሆነ ከአንተ ጋር እያወራሁ ነው የማድረው » አለችው ጠንከር ባለ አነጋገር ።

« አይሆን . . . አይሆንም ብያለሁ . . . » እራሱን እየነቀነቀ ተናገረ ።

* * *

ያሬድ የአቃቂ ቤቱን ለቀበሌው አስረክቦ ኮምቦልቻ ከገባ ስድስተኛ ወሩን ያዘ ። የሚኖርበት ቤት መንግስት ነበር የሰጠው ። አልፎ አልፎ ወደ አዲስ አበባ ብቅ ብሎ ከሕሊና ጋር ቆይቶ ይመለሳል ። ኮምቦልቻ ሄዳ ቤቱን ያየችው በፋሲካ የዕረፍት ጊዜዋ አምስት ቀናት ብቻ ነበር ። ይህን የፋሲካ በዓል ያሬድ ከውጭ የመጣበትን ዕለት ያህል ነበር በጉጉት የጠበቀችው ።

በፋሲካው ዝግ ሰሞን ያሬድና ሕሊና ተያይዘው ቀኑን ሙሉ ሲዞሩ ነበር የከረሙት ። ለሕሊና ሲል የአምስት ቀን ፈቃድ ወስደ ። የፈለገችውን ሁሉ በማድረግ ጊዜውን አሳለፈ ። ስለሕሊና እያሰበ ከራሱ ጋር የውጣ ውረድ ትግሎችን አካሄደ ። አምስቱን የዕረፍት ቀናት በደስታ አሳልፋ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰች ። አዲስ አበባ እንደ ያሬድ የቅርብ ረዳት ሆነው የሚቀርቧት ሀሰንና ቤተሰቦቹ ነበሩ። በሀሰን በጎ አድራጎትና አቀባበል ከያሬድ ጋር ያላቸውን የፀባይ አንድነት ታደንቃለች ። ሆኖም ሀሰን ችኩልና በሚያደርገው ነገር ሁሉ በጣም ፈጣን በመሆኑ ከያሬድ ይለያል ። ቢሆንም ሕሊና በዚህ ጠባዩ ሀሰንን አልጠላችውም ።

አንድ ቀን ሀሰን ሕሊናን ለማዝናናት በማምንቱ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ወደ መምህራን ማሠልጠኛ መጣ ። ቀጠሮው ቀደም የተያዘ ስለነበር ሕሊና እራስዋን በደንብ አዘጋጅታ ነበር የጠበቀችው ። በቅርብ የገዛትን አሮጌ ቮልስ መኪና ይዞ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት ቆሞ ጠበቃት ። በትልቁ በር በኩል ስትወጣ ሀሰን ከመኪናው ወርዶ እንደእንግዳ ሴት ተመለከታት ። አለባበሷ ለሀሰን አዲስ ነበር ።

የፀጉር አሰራርዋና አለባበስዋ እጅግ ዘመናዊ የሚሉት ዓይነት ሆነበት ። ሕሊና ውብ ሆና ታየችው ። መኪናውን ከፍቶ ሕሊናን ካስገባት በኋላ ይዟት ከነፈ ። ቃል ሳይተነፍሱ ብዙ ከሄዱ በኋላ « ዛሬ ደግሞ ልዕልት መስለሻል ሕሊና » በማለት ዘወር ብሎ መልከት አደርጋት ።

« ስለ አስተያየትህ እመሰግናለሁ » አለችው ውስጧን ሀፍረት እየተሰማት ። ሀሰን የመኪና አነዳዱን ፍጥነት ጨመረ ። መኪና ውስጥ ከሕሊና ጋር ብዙ ውይይት አላስፈለገውም ። ከከተማው ውጪ ወደ አምቦ መንገድ ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ወደ ቀኝ በመታጠፍ ከአንድ ግቢ ውስጥ ገባና መኪናውን አቆመ ።

« በይ እንግዲህ እዚህ ትንሽ እንቆይና ወደ እነ እማዬ እወስድሻለሁ » ሲላት ሕሊና የመኪናውን በር ከፍታ ወጣች ። ትንሽ ዘግየት ብሎ የመኪናውን መዝጊያ በደንብ መዘጋቱን ካረጋገጠ በኋላ እንሂድ በሚል ዓይነት ጭንቅላቱን አወዛወዘ ። ወደ አንዲት ብቸኛ ጎጆ ቤት ውስጥ ገብተው ፊት ለፊት ተቀመጡ ። ሀሰን በጎጆው ምሰሶ ላይ የተንጠለጠለውን መጥሪያ እየተጫነ « እንግዲህ ዛሬ ከቢራ በስተቀር ይነስም ይብዛም መጠጣት አይፈቀድም » አላት ።

« ጋባዥ ነው ተጋባዥ የመጀመሪያ ምርጫ የሚሰጠው ? » በማለት ፈገግ እንዳለች ተመለከተችው ።

« ይቅርታ ይደረግልኝ የእንቺ ግብዣ ሲሆን ምርጫውን እሰጥሻለሁ » ከማለቱ አስተናጋጁ ከተፍ አለ ። ሀሰን ከኪሱ ቦርሳውን አውጥቶ « አራት ቢራ » በማለት አሥር ብር መዘዘና ለአስተናጋጁ ሰጠው ። ሕሊና አፏን በድንጋጤ ከፍታ « አንዴ ይሄ ሁሉ ለእኔ ? እኔ እንድ ይበቃኛል » በማለት ወደ አስተናጋጁ ዞረች ።

« ሁለት ብቻ » አለችው ።

« ብድሬ ዓይነትን እንጂ ብዛት አይጨምርም » በማለት ወደ አስተናጋጁ መለስ ብሎ « ተስማምቻለሁ ፣ ሁለት ለመንደርደሪያ

ይበቃል » ሲል አዘዘው ። ከዚያም ሕሊናን እየተመለከተ « እንግዲህ መምህርት ሕሊና ትምህርትዎን ሊጨርሱ ወር ብቻ ነው የቀረዎት » አላት ።

« እፎይ » በማለት በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ « ልገላገል ነው» አለችው ።

« ከትምህርቱ ዓለም የሥራው ዓለም ይሻላል ብለሽ ነው ? የሥራው ዓለም ይሰለቻል ፣ ይደክማል ፣ ኑሮውም ብዙ ያሳስባል ። ተማሪ ግን ምን አለበት ? እንዳይሰለቸው በየቀኑ የሚቀርብለት ትምህርት አዳዲስ ነው ። እንዳይደክመው ለማወቅ ያለው ፍላጎት ከድካሙ እንዲወገድ ብርታት ይሰጠዋል » በማለት ንግግሩን ጀመረ።

« እሱስ ልክ ነው አሁን ይመስላል እንጂ የትምህርት ቤት ጊዜ አልቆ ወደ ሥራ ስንሰማራ እንዴት እንደሚያስጠላ ይታየኛል ። ሌላው ቀርቶ በት/ቤት ያፈራናቸውን ጓደኞቻችንን ተለይተን አዲስ የሥራ ጓደኞች መመሥረት ከባድ ነው የሚመስለኝ » አለችው በሀሳቡ በመስማማት ።

ሀሰን የሕሊናን ፊት ቀረብ ራቅ እያለ በመፈተሽ « ሕሊና አሁን ከጨረሽ የወደፊቱ ዕቅድሽ ምንድነው ? » አላት ። ዓይኖችዋን ከሀሰን ወደ ሌላ አቅጣጫ በማንከራተት ረዘም ላሉ ሴኮንዶች ካለበች በኋላ « ምን ዕቅድ አለኝ ። እንደ እኔማ ከነጋሼ ያሬድ ጋር ተደባልቄ እንደድሮዬ መኖር ነው » አለችው ።

« መቼ ሰው ሁሉ እንደተመኘው ይሆንለታል ። የሁሉም ምኞት የተለያየ ነው ። ምኞትና ሥራ ታዲያ እንደ አጋጣሚ አልፎ አልፎ በአንድ ላይ ተቀናጅተው ይገኙ እንጂ አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱ ለፈላጊው አራምባና ቆቦ ናቸው » በማለት ትንሽ አመነታና « ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝና ለእኔ ተገቢ መስሎ የታየኝን ግን የማይገባ ጥያቄ ልጠይቅሽ ፣ ምንመስለሽ ጥያቄዬ ግራ እንዳይሆንብሽ በማለት ነው » አላት ።

« ጠይቀኝ የማውቀው ከሆነ እመልስልሃለሁ » አለችው ጥያቄውን ለመስማት በመጓጓት ። ወደ መሬት አቀርቅሮ « ጥያቄው አንቺንና ያሬድን የሚመለከት ነው ። እም . . . ም. . . .ም. . . ስለአንቺና ስለ ያሬድ ግንኙነት ልትነግሪኝ ፈቃደኛ ነሽ ? » አለና ያስጨነቀው ይመስል ተነፈሰ ። « አልገባኝም ፤ ግንኙነት ስትል ምን ማለትህ ነው ? » በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መለሰችለት ፣ አቀራረቡ ግራ ገብቷት ።

« ግንኙነት ማለቴ እንግዲህ አለ አይደል . . . . » በማለት ጥቂት በማለሳለል አቅማማና « ግንኙነት ማለቴ . . . . አሁን ትምህርትሽን ስትጨርሺ ከያሬድ ጋር ትጋባላችሁ ? » በማለት ሲፈራ ሲቸር ጠየቃት ። ሕሊና ከልቧ ከት ብላ በመሳቅ ደጋግማ ሀሰንን ተመለከተችው ። « ጥያቄው የሚያስቅ ነው እንዴ ? » አለና የምንተዕፍረቱን አብሮአት በመሳቅ አይነት ፈገግ አለ ።

« አይ አንተ ! » አረፍ እንደማለት አለች « ለመሆኑ ለምን ጠየከኝ ? » ስትል ጠየቀችው ።

« መጀመሪያ ለጠየኩት መልስ ስጪኝና እኔ እቀጥላለሁ አላት።

« እኔና ጋሼ ያሬድ እህትና ወንድም ነን ። ለወደፊቱም የዚህ አይነት ግንኙነት የሚኖረን ይመስለኛል » ።

« እስኪ ሙት በይኝ ! » ሲል መሀላ እንድታደርግለት የቀኝ እጁን ዘረጋላት ።

« መሀላው ለምኑ ነው ? በእውነት የነገርኩህ ሀቅ ነው አለችው ፣ ሀሰን አመናት ።» ከዚህ በኋላ ያለውን ጊዜ በሳቅና በቀልድ፣ በጨዋታ አሳለፈ ። ድሮ ሕሊና ከምታውቀው በላይ የውስጥ ስሜቱን በማውጣት እሷን ለማሳቅና ለማስደሰት ሞከረ ። ሕሊና ሳታስበው ሶስተኛ ቢራ በማገባደድ ላይ ነበረች ።

* * *

የሕሊና የምረቃ ቀን በመቃረቡ ያሬድና ወ/ሮ በላይነሽ ከኮምቦልቻ ከመጡ ሁለት ቀን ሆኖአቸዋል ። ሕሊና በግቢው ውስጥ በነበረችቦት ወቅት የተረከበቻቸው የትምህርት መሣሪያዎችና የወጣት ማህበሩን ንብረት ለማስረከብ ወዲያና ወዲህ ስለምትራወጥ ከነያሬድ ጋር በውጉ ተገናኝታ ለመጫወት ጊዜ አልነበራትም ። ማታ ማታ ፣ ከሥራ በኋላ ሀሰንና ያሬድ በሀሰን መኪና ሕሊናን ወደ ከተማ ወስደው ትንሽ አመሻሽተው ወደ ት/ቤት ስለሚመልሷት በዚህ ለመፅናናት ሞከረች ።

የምረቃው ቀን ያሬድ ፣ ሀሰንና ወ/ሮ በላይነሽ የክት ልብሳቸውን ለብሰው ከሌሎች የተማሪ ቤተሰቦች ጋር በመሆን በአዳራሽ ውስጥ እንደተቀመጡ ሕሊና የተሰጣትን የመመረቂያ ልብስ ለብሳ ከጓደኞችዋ ጋር አብራ ስትገባ ያሬድ በዓይኑ ቃኛት ። የዲፕሎማ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት መናገር የሚገባቸው የተቋሙ የበላይ አካሎች ንግግር አድርገው በመጨረሻ በትምህርት ዘመናቸው ከትምህርት ቤቱ የሥራ መስክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ተማሪዎች ሽልማት ሲሰጥ የሕሊና ሥም በሶስተኛ ደረጃ እንደተጠራ በአዳራሹ የተሰበሰቡት ተማሪዎችና መምህራን ከፍተኛ ጭብጨባ በማድረግ አድናቆታቸውን ሲገልጹላት ያሬድ መላ ሰውነቱን ደስታ ነዘረው ። ሽልማቱን ከተቀበለች በኋላ መለስ ብላ ወደ እነ ያሬድ አቅጣጫ ቆማ ስትመለከት ያሬድ በሩቁ ሲከታተላት ነበረና ከመቀመጫው ተነስቶ አጨበጨበ ።

አጠገቡ ከተቀመጡት ከወ/ሮ በላይነሽ አበባና አንድ በወረቀት የተሸፈነ ስጦታ ተቀብሎ አገላብጦ ከሳማት በኋላ አበረከተላት ። ሕሊናም ጎንበስ በማለት ስጦታውን ከተቀበለችው በኋላ እሷም በተራዋ ያሬድን አቅፋ ጉንጮቹን አገላብጣ ሳመችው ።

የሕሊና የምረቃ በዓል በጣም የተዋበ ነበር ። በትምህርቷ የክብር ዲፕሎማ ተሸላሚ ነበረች ። በጣሙን ደስ ያሰኛት ግን ያሬድ ያበረከተላት ስጦታ ነበር ። ሕሊና ዕቃዋን ሰብስባ እነ ያሬድ ያረፉበት ሆቴል ደርሳ ያሬድ የተከራየላት መኝታ ቤት እንደገባች ሦስቱ ሰዎች የሰጡአትን ስጦታ እየፈታች ማየት ጀመረች ።

የያሬድ ስጦታ ሁለት ከወርቅ የተሠሩ ጌጦች ነበር ። የአንገት ሀብልና የጆሮ ጉትቻ ። የሀሰን ስጦታ ደግሞ የወርቅ ቀለበት ሆኖ በላዩ ላይ በጥቁር ድንጋይ የእሷ ሥም የተፃፈበትና ከሥሩ የሀሰንን ሥም የያዘ ነበር ። ሦስተኛው ስጦታ የወ/ሮ በላይነሽ ሲሆን መጠኑ ከሁሉም የሚበልጥ በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ ነበር ። በጥሩ የእጅ ፈትል የተሰራና በጥሩ አዋቂ የተጠለፈ ቀሚስና ነጠላ ነበር ። ሕሊና የሦስቱንም ሰዎች ስጦታ አልጋዋ ላይ ዘረጋጋችና ከወዲያ ወዲህ እየተሽከረከረች አስተዋለች ። የያሬድን ሀብል እያጠለቀች በመስታወት ውበቷን አስተዋለችና ፈገግ አለች ። በሀሰን ቀለበት ደስ ተሰኘች ። የወ/ሮ በላይነሽን ስጦታ ወደ መስኮቱ አስጠግታ አየችና በመገረም አይነት እራስዋን ነቀነቀች ።

በነጋታው ጠዋት ሀሰን አውቶቡስ ተራ አድርሶአቸው ለመመለስ ሊሰናበታቸው ሕሊናን በተለየ ዓይን አስተዋላት ።

« እንግዲህ ቶሎ እንድትመጪ ድልድላችሁ በነሐሴ ውስጥ ነው ። ጥሩ ጥሩ ዕጣ ይወጣና ዝቃጩ እንዳይደርስሽ ። » በማለት ቶሎ መጥታ ለማየት ያለውን ፍላጎት በተዘዋዋሪ መንገድ ገለፀላት ። ሕሊና በአውቶቡስ ጉዞዋ ወቅት እያሰላሰለች የምትሄደው ስለተደረገላት ስጦታና ስለትርጉማቸው ነበር ። ያሬድ የሰጣት እንደጠበቀችው እህትነቷን የሚያረጋግጥላት ነበር ። ወ/ሮ በላይነሽም እናትነታቸውን የሚያረጋግጥ ስጦታ ነበር ያደረጉላት ። ሀሰን የሰጣት ስጦታ ትርጉም ግን ለሕሊና ግራ ነበር ። በተለይ የስሙ በቀለበቱ ላይ መስፈር ጥርጣሬዋን አሰፋው ።

ሕሊና በኮምቦልቻ ቆይታዋ የሐምሌ ወር አልቆ ነሐሴ ሲጀምር መሄጃዋ እየተቃረበ በሄደ ቁጥር የፍርሃትና የሀዘን ዳመና አንዣበበባት ። ብዙ ጊዜ ስለ ያሬድ ስታስብ በመማርዋ ትበሳጫለች። ለያሬድ ምግብ አብሳይ ሆና እንደ ወ/ሮ በላይነሽ አብራው ብትኖር ምኞትዋ ነበር ። የያሬድም ሀሳብ ተመሳሳይ ቢሆንም አብሮ ለመኖር የመረጠው አቅጣጫ ግን ትምህርቷን ጨርሳ እንዳትለየውና በሌላ መልኩ ነበር ።

አንድ ቀን ያሬድ ከሥራ ተመልሶ ወደቤቱ ሲመጣ እንደተለመደው አብረው ሲስቁና ሲጫወቱ ከቆዩ በኋላ በቤቱ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ። ወ/ሮ በላይነሽና ያሬድ ተያይተው በዓይን ቋንቋ ሲነጋገሩ ወ/ሮ በላይነሽ ያሬድንና ሕሊናን ሳሎን ትተው « ሕሊና እንግዲህ ትምህርቱ አለቀ አሁንስ ? » አሉና ወደ ጓዳ ገቡ።

ያሬድ ሕሊናን ትኩር ብሎ በመመልከት ፈገግ አለና ዓይኖችዋን እያነበበ ሳለ ሕሊናም ይህ አስተያየቱ አዲስ ባለመሆኑ በተለመደው ፈገግታዋ አፀፋውን መለሰችለት ። አመለካከቱ የመሰያያ ቀናቸው መድረሱን የሚነግራት መሰላት ። ለያሬድ ግን ለዘለአለም አንድ ላይ የሚሆኑበት ቀን መቃረቡ እየታየው ፤ « የምረቃ ስጦታሽን በሙሉ አልሰጠሁሽም ። ዛሬ ልሰጥሽ ወስኛለሁ » በማለት ብድግ ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባና በእጁ ሁለት ትንሽ ነጫጭ ሳጥን መሳይ ነገሮችን ይዞ ጠረጴዛው ላይ ነጣጥሎ አስቀመጣቸው ።

ቀና ብሎ ሕሊናን እየተመለከተ « በይ እንግዲህ ምረጭ » አላት ። የያሬድ ሁኔታ ግራ አጋባት ።

« ምኑን ነው የምመርጠው ? » በማለት ወደ ሳጥኖቹ መልከት አድርጋ ቀና ብላ ያሬድን አስተዋለችው ።

« ከእነኚህ ከሁለት ሳጥኖች አንደኛው ለአንቺ ነው ። መርጠሽ ውሰጅ » በማለት ሳጥኖቹን እንደዕጣ ዓይነት በማለዋወጥ ሕሊናን በሚያደነጋግር ሁኔታ አስቀመጣቸው ።

« በይ ምረጭ » አላት ::

እጇን ዘረጋችና አንደኛውን ሳጥን ብድግ አድርጋ «ይሄው» ስትል ለያሬድ እንደመስጠት ዘረጋችለት :: ያሬድ የቀረውን ሣጥን ለራሱ እየወሰደ « ከፈችው እንጂ ምን ትጠብቂያለሽ ? » አላት በፈገግታ ::

ሕሊና የስጦታውን ክዳን ከፍታ ውስጡ ያለውን ቀለበት እንዳየችው ትርጉሙ ወዲያውኑ ገባት :: ፊቷ በአንድ አፍታ ተለዋውጦ ዓይኖችዋ የሀዘን ዳመና ጋረዳቸው :: አጠገብዋ የቆመውን ሰው በጥላቻ ለማባረር የተዘጋጁ መሰሉ :: ሳጥኑን እንደነበር አድርጋ ከደነችና ወደነበረበት ቦታ መልሳ በዝምታ እንባዋን እያፈሰሰች ወደ ወ/ሮ በላይነሽ ሸሸች :: ያልጠበቀችው ነገር ስለተፈጸመ የህይወቷ መሠረት የተናጋ መሰላት ::

ሌሊቱን ወ/ሮ በላይነሽ በማባበልና በማፅናናት አሳልፈው ሲነጋ በጠዋት ዕቃዋን ጠቅልላ ለጉዞ ተዘጋጀች :: ያሬድ ከሳሎን መኝታ ቤት እየተመላለሰ ዕንቅልፍ ሳይወስደው ነበር የነጋለት :: መነሳቷን ሲመለከት ወዳለችበት ክፍል ገባ :: ልታየው አልወደደችም:: አንገቷን ወደ መሬት አቀርቅራ እጆቿን እያሻሸች ቆማ ያሬድ የሚለውን ጠበቀች ::

« ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝ በጣም ቸኩልኩ መሰለኝ » ሲል ለመናት ::

* * *

ጊዜው መሸትሸት ሲል አዲስ አበባ አውቶቡስ መናኸሪያ ከሌሎች ተሳፋሪዎች ጋር በመሆን ደረሰች :: ወቅቱ ክረምት ስለነበረ ዝናቡ እያካፋ ፣ ሰው በየፊናው መጠለያ ለመፈለግ በመሯሯጥ ላይ ነበር :: ታክሲዎች በአካባቢው ቆመው ከክፍለሀገር የሚመጡትን እንግዶች ለመቀበል ተራ ላይ ናቸው ::

ሀሰን ጃንጥላ ይዞ አዲስ የደረሰውን አውቶቡስ የሰሌዳ ቁጥር ለማንበብ ተጣደፈ :: በሰሌዳው ላይ « ደሴ አዲስ አበባ » የሚል ፅሁፍ ነበረበት :: ወደ አውቶቢሱ ተጠግቶ ከሌሎች እንግዳ ተቀባዮች ጋር ተቀላቅሎ ፣ በሁለቱም በር የሚወርዱትን ተሳፋሪዎች ተመለከተ:: አያት የሆነ ስሜት ወረረው :: በአካባቢው ያሉትን ሰዎች እየገፈታተረ ወደፊት ሄደ :: « ሕሊና ! ሕሊና ! ቆይ እስኪ መንገድ ! ሕሊና ! እዚህ ነኝ ! ወደዚህ » ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተጣራ :: ከላይ ደረብ ያደረገችውን ነጠላ መሳይ ድሪያ ወለቅ አድርጋ የሀሰን ድምፅ ወደሰማችበት አቅጣጫ ፊቷን መለስ አደረገች ::

ሀሰን እንደ አበያ በሬ ፊቱ የቆመውን ሁሉ እያስወገደ ወደ እርሷ ሲገሰግስ አየችው :: ምንም ጊዜው ጨልሞ ለዓይን ድንግዝግዝ ቢያደርግም የሕሊናን ደስታ ለመለየት አላዳገተውም ::

« ጋሽ ሀሰን መልዕክቱን ቶሎ አገኘህ ? እኔኮ አታገኘውም ብዬ ፈርቼ ነበር :: . . . . .» አለችው ሕሊና ንግግሯን አጠር አድርጋ ::

« ሁሉም ደርሶኛል :: ስምቻለሁ :: ዕቃሽን እንሰብስብ » አላት ፣ ተረጋግቶ ለመጫወት አልተመቸውም ነበር :: ዕቃዋን በሀሰን መኪና ጭነው ጉዞዋቸውን ወደ ቤት ቀጠሉ ::

« ምነው አዲስ አበባ ናፈቀሽ ? እረፍቱን ሳትጨርሺ ተመለሽ» አላት ፤ የተወሰነ ርቀት ከሄዱ በኋላ ።

« ገጠር ምኑ ደስ ይላል ? » አለች ።

« ኮምቦልቻ ገጠር ከሆነ የምትሄጅበትስ ምን ይሆን ? »

« አባባሌ ፤ ገጠርን በመጥላት ወይም በመፍራት እንዳይመስልህ ። »

« ሒሊና የምትይው የገባኛል ። ግን ለምን እውነቱን አትናገሪም ?

« ምኑን ነው የምነግርህ ? » በቁጣ ነበር የተናገረችው ።

« አይ ሒሊና ፤ ለምን እንደ ልጅ ትሆኛለሽ ? ሁሉንም ነገር ሰምቼዋለሁ ። »

« ምንድን ነው የሰማህው አለችው ግንባሯን ቋጥራ

ሀሰን የጀመሩትን ንግግር አቋርጦ « እነማማ መቼም ደጅ ቆመው ነው የሚጠብቁን አላት ።

« ውይ ! እረስቼ ሳልጠይቅህ ፤ ፋጡማ ወለደች ? »

« ያውም ባለ አራት ኪሎ ጠንበለል ። »

« እንኳን ደስ ያለህ ! » መቼም ምንም ወንድ ብትሆን ለእህትህ መጨነቅህ አይቀርም ። ደስታውን ተቀብያለሁ ። ጭንቀቱ ግን በእናንተ ቢበቃ ይሻላል ። አለ ሀሰን የመኪናውን ጡሩምባ ደጋግሞ በማጮህ ። የግቢው በር ተከፈተ ። በሰንብት የተለያዩት በመሳሳም ተገናኙ ። የሒሊናን ስም የሚጠሩ ብዙ ሆኑ ።

ሒሊና ከኮምቦልቻ መልስ ሦስተኛውን ሌሊት አገባደደች ። ከሀሰን ጋርም ውል የሌለው ግንኙነት ፈጠሩ ። በጠዋት ስትነሳ በዕለቱ ከሀሰን ጋር የነበራትን የሽርሽር ጉዞ እያሰበች ነበር ።

« በጣም ነው የምትገርሚኝ » አላት ሀሰን ፤ መኪናውን ጥግ አስይዞ እያቆመ ።

« ሽርሽሩ ቦታ ደረስን እንዴ ? » አለችው የተናገረውን እንዳልሰማች ሁሉ ።

« ከመድረሳችን በፊት ትንሽ እንነጋገር ብዬ ነው ። ሒሊና ለምን ነበር ያኔ የደበቅሽኝ እስኪ በአባትሽ ንገሪኝ ። »

« ምኑን ? »

« ከያሬድ ጋር ስለነበራችሁ ግንኙነት ? »

« ታዲያ የደበኩህ የትኛውን ነው ? »

« እሺ ፤ ግን ለምን ተቀያየማችሁ ? ምስጢር ካልሆነ ብትነግሪኝ ? »

« ምን ያደርግልሃል ? ጋሼ ያሬድ የነገረህ አይበቃም ? »

« እሱማ ያለኝ እም . .ም. .ም» ቃላቶቹን ለማውጣት ተናንቀው ውስጡ ነደደ ።

« በቃ ! ተይው ምን አስጨነቀን » አላት በስጨት ብሎ ።

« ታዲያ ምን አበሳጨህ ? » አለችው በግርምት

« እንዴት አልበሳጭ ሒሊና ? » ሒሊና እንዴት አይገባሽም ? ያሬድኮ ጓደኛዬ ነው ። ይህን ሀሳቡን ቀደም ብሎ ቢነግረኝ ኖሮ ለሁላችንም ጥሩ ነበር ። የዛን ቀን የነገረኝን ለማመን አልቻልኩም ። እንዴት ብዬ ልግለፅልሽ ሒሊና » ከመምህሩ መልስ የሚጠብቅ ተማሪ መስሎ ነበር የጠየቃት ።

« እኔ እንጃ » አለችው ።

« አይ ሒሊና ! ሒሊና ! እንዴት አድርጌ ላስረዳሽ ? » በማለት ወንበሩ ላይ ደገፍ ብሎ ወደ መኪናው ጣሪያ ተመለከተ ።

እጇን ወንበሩ ላይ አሳርፋ በመንተራስ ፊቷን ወደ ሀሰን መልሳ በትኩረት እንቅስቃሴውን አየች ። ጭንቀቱ ከየትኛው አቅጣጫ እንደመነጨ ለማወቅ የነበራት ጉጉት በውስጧ ይበልጥ እያንሰራራ መጣ ። ግን እሷ ቀድማ ልታነሳ አልፈለገችም ። ሀሰን በቀጥታ ለሚጠይቀው ጥያቄ መልስ ራሷን አዘጋጀች ።

« ስሚ ሕሊና ያሬድን አላገባም አልሽ ። ለምን ብዬ መጠየቅ አግባብ የለውም ። የሆነው ሆኖ ። ከነጭራሹ ሳታገቢ ትኖሪያለሽ ብዬ አላምንም » አላት ። « ጋሼ ሀሰን ፣ ሀሳብህ ይገባኛል ። ለእኔ እንደ ጋሼ ያሬድ በሁለንተናው ምቹ የሆነ ባል ማግኘት አልችልም ። ነገር ግን ጋሼ ያሬድ ለሰራልኝ ውለታ አፀፋውን በጉዳት እንድመልስለት አልፈልግም ። እሱ ጥሩ ባል ሲሆን ይችላል ። እኔ ግን ለሱ ጥሩ ሚስት ለመሆን መቻሌን እጠራጠራለሁ ። » አለችው።

የመጀመሪያ ፍቅር መቼም በደስታ ባህር እንደመዋኘት ሊያጓጓ ይችላል ። ፍቅር ሲያረጅና ቀኑ እየረዘመ ሲሄድ እየቀዘቀዘ ያልፋል ። በወንድምነትና በእህትነት የዳበረውን መውደድ በአዲሱ የባልና የሚስት ፍቅር ሲተካ እንዳይጠወልግብን ፈራሁ ። ለምሳሌ እንበል ጋሼ ሀሰን አሁን ፋጡማን አግባ ቢሉህ እሺ ትላለህ ? » አንገቷን ሰብር አድርጋ አየችው ።

« ምን ማለትሽ ነው ? እንዴት ተደርጎ ? » ዓይኑን ጨፍኖ እራሱን እየነቀነቀ ቀጠለ « ሕሊና እዚህ ላይ ተሳስተሻል ፣ የፍቅርን ምስጢር የተረዳሽ አልመሰለኝም ። ለጤነኛ ባልና ሚስት ፍቅር እንደ ጤዛ አይረግፍም ፣ አይጠወልግም ። ፍቅር በዕድሜ ከአንዱ አይነት ወደ ሌላው ይሸጋገራል » ተክዛ የምታየውን ሕሊናን ትኩር ብሎ በመመልከት ነበር ያሚናገረው ። « ሕሊና ለሁሉም ሂደት ዕድሜ አለው ። ፅድሜ ያልተገኘለት ለራሱ ለጊዜ ብቻ ነው ።

« ጋሼ ሀሰን ፣ ጋሼ ያሬድን በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ አስበልጬ እወደዋለሁ ። ነገር ግን ይህ መውደድ ለሱ እንደገባው ለእኔ አልተከሰተልኝም ። እንግዲህ ጋሼ ያሬድ እንደተመኘው ሁሉ ለማድረግ ወንድምነቱን ፍፁም መርሳት ይኖርብኛል ። ወንድምነቱን ትቼ ፍቅሩን ሳውቅ ያኔ ለሚስትነት እበቃ ይሆናል ። ጊዜ የማይሽረው ትዝታ የለም ። ከሀዘኑ እንዲፅናና እሰላ እንደደረስኩ ደብዳቤ እፅፍለታለሁ » አለችው ።

ምዕራፍ አምስት

ሕሊና ከሀሰን ጋር ከአዲስ አበባ ተነስታ አሰላ ገባች ። አብረው አካባቢውን ተዘዋውረው ጎበኙ ። « ደስ የምትል ከተማ ነች» አለ ሀሰን አካባቢውን ዞር ዞር ብሎ እያየ ።

« ከተማውስ ደስ ማለት ደስ ይላል ፤ ግን ምን እንደሆነ አላውቅም ብቸኝነት ፣ ባዶነት ይሰማኛል » አለችው ።

« አዲስ ቦታ ሲገቡ ሁልጊዜ ማንኛውም ሰው የሚሰማው ስሜት ነው ። አይዞሽ ፤ እየቆየሽ ስትሄጂ ትለምጃለሽ » አለ ሀሰን በማፅናናት መልክ ። ግን ሕሊና ራሷን ማፅናናት አልቻለችም ። የሀሰን ንግግር ይበልጥ ሆዷን አባባው ። ሳታስበው እንባዋ ገነፈለ ። ሀሰን የራሱ ስሜት እየታገለው ፤ ሕሊናን ለማበረታታት ሲል ወደ ውስጥ ለመዋጥ እየጣረ « ደስ ሲልሽ ሲገባ ማልቀሱን ምን አመጣው ሕሊና ? ! » ሲል የቁጣ ዓይነት ንግግር ተነፈሰ ። « ወድጄ አይደለም ሀሰን ። ዝም ብሎ እምባዬ ይመጣል ። ላለማልቀስ ወስኜ ነበር ግን እንባዬን ልገታው አልቻልኩም » አለችና ሁለት እጆቿን ፊት ለፊቷ ዘረጋች ተስፋ በመቁረጥ መልክ ። ሀሰን እጆቹን በደመነፍስ ዘረጋላት ። የሚያደርገው ሁሉ ከቁጥጥሩ ውጪ ነበር ። በሕሊና ፊት ላይ እየገነፈለ የሚፈሰውን እንባዋን በእጆቹ ጠራረገላት። ፊቷን ወደ ራሱ ጠጋ አድርጎ ጉንጯ ላይ ሳም አደረጋት።

እጆቹን በአንገቷ አሳልፎ አቀፋት ። ሕሊና እንደ ህፃን ልጅ ፊቷን አንገቱ ስር ቀብራ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። ከቆይታ በኋላ ከህልሟ የነቃች ይመስል ሀሰን በሰጣት መሀረብ ፊቷን እየጠራረገች ፤

« አሁን ደህና ነኝ . . . እንሂድ » አለች ።

ሀሰን መኪናውን አስነሳ ለመንዳት ግን አልሞከረም ። ለጥቂት ጊዜያት የሕሊናን ፊት በዓይኖቹ ዳሰሰ ።

« መቼም ያሬድ ላይ አልፈርድበትም » አለ ለራሱ በመናገር መልክ ። ዓይኖቿ ከዕንባ ያልፀዱት ሒሊና ሀሰንን በፈገግታ ገርመም አደረገችው ። በመሀከላቸው ዝምታ ሰፈነ ። ሀሰን ወደ ሒሊና ፊቱን ሳይመልስ መንገድ መንገዱን እያየ ለብዙ ጊዜ ነዳ ። በሀሳብ ተውጦ ነበር ። ከሒሊና ጋር የተፈጠረው ስሜታዊ መቀራረብ እውን ሆኖ ታየው ። ያሬድን አሰበው ። በደፈናው እንደሚወዳት ነው የነገረው ። እሷም ወንድሜ ነው ብላዋለች ። ከዚህ በላይ ምን ማወቅ ያስፈልጋል ? እራሱን ለማሳመን ሞከረ ።

« እኔ አላምንም ! ከእንግዲህ እዚህ አዲስ ከተማ አዲስ ህይወት ጀመርኩ ማለት ነው ? » ስትል ሒሊና እራሷን ጠየቀች ።

« አይዞሽ ! እንዲህ እየተባለ ነው የሚለመደው » አላት ሀሰን ቃሉን ከፍ አድርጐ ፤ እኔም ለሦስት ቀን ከአንቺ ጋር ነኝ « እውነትህን ነው ? » ስትል በጉጉት መልክ ጠየቀችው ።

« አዎ እውነቴን ነው አንቺን ደስ የሚልሽ ከሆነ ? » አለ ሀሰን በጥያቄ መልክ ። « በጣም ነው ደስ የሚለኝ » አለች በረጅሙ ተንፍሳ ጭንቀቷን በመገላገል ዓይነት ። ሒሊና የተከራየችው ጠበብ ያለ ሁለት ክፍል ያለው ቤት ነው ። ጐረቤቶቿ እንግዳ መሆኗን ስላወቁ የተቻላቸውን ድጋፍ ለመስጠትና ለማለማመድ ሞከሩ ። የሒሊና ጐረቤቶች ብዙዎቹ መምህራን ናቸው ። ሒሊና ጥቂቶቹን በት/ቤት አካባቢ ተዋውቃቸዋለች ። መምህርት ከበቡሽ ከሒሊና ቀደም ብላ ከአንድ ዓመት በፊት ከኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ተመርቃ በአርሲ ክፍለ ሀገር አርባ ጉጉ ከተማ ተመድባ ለአንድ ዓመት ስታስተምር ከቆየች በኋላ የዝውውር ዕድል አግኝታ አሰላ ተመደበች ።

ከሒሊና ጋር በማሰልጠኛ ት/ቤት በዓይን ይተዋወቁ እንጂ ንግግር አልነበራቸውም ። የመምህራን የትውውቅ ስብሰባ ተጠርቶ መምህራን በመሰብሰብ ላይ እንዳሉ ሒሊና ከከበቡሽ ጋር ተገናኘች ።

በፊት በዓይን ከመተያየት በስተቀር ቅርርብ አልነበራቸውም ። አሁን ግን ሲተያዩ እንደአብሮ አደግ ጓደኛሞች ተቃቅፈው ተሳሳሙ።። ቀጥላ ከሁለት ወንድ መምህራን ጋር ተዋወቀች ።

« አበራ » ፣ « ታከለ » ብለው ተዋወቋት ።

« መቼም ይህ ይሆናል ብዬ አልጠበኩም » አለች ከበቡሽ ፈገግታ በፈገግታ ሆና ።

« ይኸውልሽ የማያልቅ ነገር የለም ትምህርቱን ጨርሼ እዚህ ተመደብኩ » አለች ሒሊና ።

« መቼም ዕድለኛ ነሽ ቀጥታ እዚህ መመደብሽ ። . . . . »

« ወደ ስብሰባ ክፍል ! ወደ ስብሰባ ክፍል ! » በማለት እጃቸውን ያጨበጨቡት ምክትል ርዕሰ መምህሩ ነበሩ ።

« አሁን ታዲያ የት አረፍሽ ? » አለች ከበቡሽ ።

« ቤት ተከራየሁ እነ መምህር ድሪባ ሠፈር » አለች ሒሊና ።

« እንዴ ምን ማለትሽ ነው ? ከግራ ሦስተኛው ክፍል የእኔ ቤት እኮ ነው ። እኔ አላምንም » አለቻት ከበቡሽ ።

« ታዲያ ዕቃዬን ሳጓጉዝ ለምን አላየሁሽም ለማደሩ እንኳ ዛሬ የመጀመሪያ ቀኔ ነው » አለች ሒሊና ።

« ሰሞኑን ሠፈር ውስጥ አልነበርኩም ። አዳሬም ውሎዬም ውጪ ሆኗል ። » አለች ከበቡሽ ፤ ፊት ለፊቷ የተቀመጠውን አበራን በዓይኗ እየቃኘች ።

የት/ቤቱ አጠቃላይ ስብሰባ የዓመቱ መጀመሪያ በመሆኑ አጠር ያለ ውይይት ነበር ። ዓላማውም አዲስና ነባር መምህራንን የት/ቤት የሥራ ዘርፍ ማስተዋወቅና የአዲሱን ዓመት የትምህርት አጀማመር ፕሮግራም ያጠቃልላል ። ከስብሰባ በኋላ ለመምህራን ነፃ ጊዜ ተሰጥቶ የግል መሰናዶ እንዲያደርጉ ርዕሰ መምህሩ ፈቀዱ ።

« እንደ ድሮ መስሎሻል ። አሁንማ ተግ ብዬ አታይም አሰባበሴም አነጋገሬም ተለውጦ ። » አለች ከበቡሽ የለበሰችው ረዥም

ቀሚ.ስና የተጫመተችው ነጠላ መሳይ ተረከዝ አልባ ጫማ ለሕሊና እያሳየች ፡፡

« አየሁ እኮ ፡፡ መጀመሪያ ሳይሽ እንኳ ሳላውቅሽ ጥቂት ጊዜ ፈጅቶብኝ ነበር ፡፡ ቢሆንም ያምርብሻል ፡፡ » አለቻት ሕሊና የከበቡሽን ስሜት እንዳትጐዳ በፍርሃት ዓይነት ፡፡

« አምሮብሻል ! ሕሊና አብደሻል እንዴ ? ምን ያምርብኛል የገጠር ኑሮ ሰባብሮኝ ፡፡ አይዞሽ አትፍሪ እውነቱን ብትነግሪኝ አይቆርጠኝ ፤ አይፈልጠኝ ፡፡ ድሮ እንደ መጣሁ ነበር ቀን ከሌሊት ለቅሶ ፡፡ አንድ ወቅትማ ሥራውን ሁሉ ትቼ ከዘመዶቼ ጋር ተቀላቅዬ ልረፈው ብዬ ነበር ፡፡ ለሁሉም ልምድ ያላቸው መምህራን ምክር አዳነኝ » አለች ከበቡሽ አጠገቧ አብሯት በመራመድ ላይ ያለውን አበራን በፈገግታ እየተመለከተች ፡፡

« ምን ታይኛለሽ ? አንቺ ራስሽ ቀላል ሰው ነሽ እንዴ . . . እኛ ቢበዛ የሞራል ድጋፍ እንጂ ምን አደረግን ? » አለ አበራ ውለታውን በማቃለል ዓይነት ፡፡

« የሞራል ድጋፍ እኮ ነው ትልቁ ነገር ! ሌላው ሁሉ ሁለተኛ ደረጃ ነው ፡፡ » አለች ሕሊና ፡፡

« በሉ እንግዲህ እራት ዛሬ እኔ ጋ ነው የምንበላው ፡፡ ከአሁኑ ልንገራችሁ ብዬ ነው ፡፡ ሁላችሁም እንድትመጡ ተጋብዛችኋል » አለች ከበቡሽ ፡፡

* * *

ወይዘሮ በላይነሽ በያሬድ እርዳታ በመጨረሻው የአለላ በራሪ ተሳፍረው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ፡፡ ዕድሜ የተጫናቸው አዛውንት አጠገባቸው የተቀመጡትን ወ/ሮ መኪናው በቆመ ቁጥር « የት ነው ያለነው ? ይህ ከተማ ማን ይባላል ? » በማለት ለመረዳት እየሞከሩ አቃቂ ሲደርሱ የእርሳቸውና የሕሊና የአቃቂ ጉዞ ትዝ አላቸው ፡፡ ወ/ሮ አባይነሽም አቃቂ በህይወት እንዳሉ ከያሬድ ሰምተው ነበር ፡፡

« ምንኛ የታደሉ ናቸው » ብለው ስለወይዘሮ አባይነሽ አሰቡ፡፡ በዓለም በደስታ ኖረው ሲበቃቸው ደግሞ በቃኝ ብለው መነኩሉ ፡፡ እግዚአብሄር ለንስሀ አበቃቸው ፡፡ » አሉና መልሰው የራሳቸውን ሁኔታ አሰላሰሉ ፡፡ ከሕሊና ጋር በዓይነ ሥጋ ከተገናኙ ዘጠኝ ወራት አለፈ ፡፡ አልፎ አልፎ ያሬድ ለሕሊና የሚፅፍላትን ደብዳቤ ያነብላቸዋል ፡፡ የሱን ሀሳብ ሰምተው ፣ የግላቸውን ስሜት ውጠው ያለምንም ተጨማሪ አስተያየት መለያየትን ልምድ አድርገውት ነበር ፡፡

ለወ/ሮ በላይነሽ የያሬድና የሕሊና ጥል ግልፅ ነበር ፡፡ ጣልቃ መግባቱ ነገሩን ማባባስ መስሎ ስለታያቸው ጉዳዩን በውስጣቸው እያመነዠኩ ኖሩ ፡፡ ያሬድ ከእርሳቸው ጋር ያለው ግንኙነት አልተለወጠም ፡፡ ሆኖም የሕሊና ሥም በየምክንያቱ በተነሳ ቁጥር የያሬድ ስሜት መልካም እንዳልነበረ ያውቁታል ፡፡ ሕሊናን ለማየት በጉጉት እየጠበቁ ፤ በሀሳብ ተውጠው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ፡፡

« ዕቃዎቻችሁን ፣ በርሳና ሻንጣዎቻችሁን ሸክፉ ፤ አሰላ ደርሰናል፡፡ » በማለት ግራና ቀኝ እየተመለከተ ወደ ወይዘሮ በላይነሽ አመራ የሾፌሩ ረዳት ፡፡

« እማማ አሰላ ማለት ይሄ ነው ፡፡ ልጅዎ አደራ ብሉኛል ፡፡

አደራ በላተኛ እንዳልሆን ። » በእጃቸው ይዘውት የነበረውን ቋጠሮ ተቀበላቸው ። ከመኪናው በመውረድ ላይ እንዳሉ ሕሊና ሮጣ አቀፈቻቸው ።

« እማማ በላይነሽ ! እኔ አላምንም . . . » ወ/ሮ በላይነሽ መናገር አልቻሉም ። ተቃቅፈው ተላቀሱ ። አገላብጠው የሕሊናን ፊት ቃኙ ። ሕሊናም አፀፋውን መለሰች ።

« ጎብዘዋል እዚህ ድረስ ብቻዎትን መጡ ! » አለች ሕሊና አፏን በእጇ ይዛ ያየችውን ባለማመን ።

« ሕሊና አንቺ በህይወት እስካለሽ እኔ ምን እሆናለሁ ። ብቻ እግዚአብሄር ውለታሽን ይክፈልሽ ። . . . ሳይደግስ አይጣላም ። » አሉ በተቆራረጠ ስሜት ሕሊናን በስስት እየተመለከቱ ።

« እርሶዎ እኮ እማማ በላይነሽ ለእኔ እናቴም አባቴም ነዎት።። ስለእኔ እርሶዎ የሚያውቁትን ያህል ማን ያውቃል ? በሞት እና በህይወት መካከል እያለን ፤ አባቴና እኔ ቤትዎትን እንደቤታችን አድርገን ፤ በሉ ይተውት በሉ ይተውት ! . . . » ሕሊና ፊቷን ወደምድር ደፋች ።

« በይ እንግዲህ ያለፈው አለፈ ፤ ተመስገን ነው የሚባለው » አሉ የሕሊናን እጆች በእጃቸው ይዘው ። « ጥሩ ቤት አግኝተሻል ። ደግሞ እውቶብስ ማቆሚያ አጠገብ ። ሀገሩም ጥሩ ነው ። የስንዴና የቅቤ ሀገር መሆኑን ድሮ እሰማ ነበር ። » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ ሕሊናን ከገባችበት የሀሳብ እዘቅት ለመመለስ በመጣር ።

« ሀገሩስ ደህና ነው ። ግን ከእናንተ ተለይቼ እርቄ መኖሬን በጣም ነው የጠላሁት ፤ ምን ያደርጋል ? » አለች ሕሊና ።

« እሱም እግዚአብሔር ይስጠው ፣ አዲሳአበባ ድረስ ነድቶ አደረሰኝ ። » አሉ ስሙን ሳይጠቅሱ ። ያሬድ ማለታቸው ነበር ።

« ለመሆኑ ደህና ነው ? እስካሁን ሳልጠይቅዎት » አለች ሕሊና መልሱን ከንግግራቸው ይልቅ ከገፅታቸው ለማንበብ በመጣር።።

« በጣም ደህና ነው ። ወደዚህ መምጣቴን እንዳወቀ ዛሬ እፅፋለሁ ነገ ሲል ሥራ በዝቶበት ጊዜም አላገኘም ። » በማለት በፍጥነት ፊታቸውን ከሕሊና አዞሩ ።

« ወደ እዚህ ልመጣ ስል ፤ ሌሊቱን በሙሉ ወረቀትና ብዕር ይዞ ምግብ ቤት ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ አደረ ። ጠዋት ተነስተን ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ የፃፈው ለአንቺ ከሆነ ይሰጠኛል ብዬ ጠብቄው ነበር ግን የሰጠኝ ነገር አልነበረም » አሏት ። ቀጥለውም « የአክስትሽን የእማሆይን ወሬ ትሰሚያለሽ ? » ሲሉ ጠየቋት ።

« አዎ እሰማለሁ ። ሁለት ጊዜ ሄጄ አይቼአቸዋለሁ ። አሁን ወደ ቤተክርስቲያን ተጠግተዋል ። ከተማ ለመኖር አልፈልግም አሉ።። ለጤናቸው በጣም ደህና ናቸው ። » አለች ሕሊና አፍንጫዋን በእጇ መዳፍ እየጠራረገች ።

ወ/ሮ በላይነሽ ከያሬድ ተለይተው ሕሊና ጋር መኖር ከጀመሩ አራት ወራት አለፉ ። በእነኚህ ወራቶች ውስጥ የሕሊና ህይወት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ቢጥሩም ፤ ካወቁአቸው ነገሮች የኑሮዋ ምስጢር እንደሚበዛ ገመቱ ።

ሕሊና አልፎ አልፎ ቅዳሜና እሁድ እሳቸው እንዳይሰጉ አፅናንታ ፣ የምትመለስበትን ጊዜ ነግራ ፣ ለአዳር ከመውጣቷ ውጪ የሚያውቁት ነገር አልነበረም ። ሆኖም ከጓደኛዋ ከከበቡሽ ጋር ሲያወሩ ለጆሮአቸው የሚደርሳቸው ወሬ ይቀፋቸው ነበር ። ስለሁሉም ነገር አንስተው ለመጫወት ብዙ ጣሩ ። ሆኖም ጊዜ ሲኖራት ሕሊና ብቻዋን ሆና አታውቅም ። ከበቡሽ ስትጠፋ አበራ ፤ አበራ ከሌለ ደግሞ ታከለ ወይንም ሌሎች መምህራን ከጎረቤት እየመጡ አስቸገሯቸው ።

« ሕሊና መሄጃዬ እንግዲህ እየተቃረበ ነው ። ያሬድ ቶሎ እንድመለስ ነግሮኝ ነው የሸኘኝ ። በወጉ ሳናወራና ሳንጫወት ጊዜው አለፈ ። እኔ መቼም አንድ ቀን እንኳን ያደርኩ አልመሰለኝም ። »

ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ መውደዳቸውንም ቅሬታቸውንም ገለጹ ። ሕሊና በሰማችው ተደናግጣ ያነሳችውን ቦርሳ ጥላ አጠገቧ ወደ አለው ወንበር ተራምዳ ተቀመጠች ።

« ለምን ይሄዳሉ ? እኔ እኮ ወደዚህ የመጡት ከእኔ ጋር ይኖራሉ ብዬ ነበር ። ምን ተፈጠረ ? » በማለት ሕሊና ጠየቀች ።

« ልጄ ! ምንም ነገር አልተፈጠረም ። መጀመሪያ አመጣጤ ለሦስት ወር ብቻ ካንቺ ጋር እንድቆይ ነው » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ ጥቂት አሰብ አድርገው ። « ያሬድም ፈቃድ የሰጠኝ ለሦስት ወር ነበር ። ይኼው አሁን አምስተኛ ወሬን ይዣለሁ ። » ብለው ወንበር ላይ አረፍ አሉ ።

« ምርጫዎ እርሱ ከሆነ እንግዲህ ምን አደርጋለሁ » አለች ሕሊና ስለማን እንደምትናገር ድፍን አድርጋ ።

« ልጄ ! ልጄ ! ምርጫዬስ አይደለም ግን ቃል ቃል ነው ። እንደምመለስ ነግሬዋለሁ ። » አሉ የሕሊናና የያሬድ መጨረሻ እንዲህ መሆኑ ውስጣቸውን እየበላቸው ። ለተወሰነ ጊዜ በቤቱ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ። ወ/ሮ በላይነሽ ወደ ሕሊና ቢመለከቱም ሕሊና ግን ዓይኖቿን አሸሸች ። እጇን ጨብጣ ማለት የምትፈልገውን በውስጧ አምቃ ያዘች ።

« ልጄ ሆይ ሕሊና መቼም ተራራቅን እንጂ አልተለያየንም ፤ ፍላጎትሽ ምን እንደሆነ ይገባኛል ። አሁን ጉልበቴ ዝሎ አልታዘዝ አላለኝም ። ሠርቼ መብላቱን አላቆምም ። ግድ የለሽም የጡረታዬ ጊዜ ሩቅ አይደለም ። ያኔ አስለችሻለሁ ። » አሉ ሕሊናን ለማረጋጋት በመፈለግ ። « ይልቁንስ ፈጠን ፈጠን ብለሽ ባሉን አምጪና ሠርጉን ልደግስ ። »

« አይ እማማ በላይነሽ ፤ እኔ የሚገርመኝ ይህ ደግ ልብዎ ዕድሜ በጨመረ ቁጥር እየታደሰና እየጎለበተ ነው የሚሄደው ። » አለች ሕሊና መርበትበቱ ትቷት ፈገግታ ተላብሳ ።

« ይልቁንስ በይማ ንገሪኝ እርሱ ማን ነው ? » ብለው ጠየቁ። ሕሊናን በትኩረት እያይዋት ። ሕሊና መልስ መስጠት አልቻለችም ። መሬት መሬቱን እያየች ፣ እጇን እያፍተለተለች በሁለት ጉልበቶቿ መሀከል ጨብጣ ያዘች ። ወ/ሮ በላይነሽ ጉዳዩ እንዳስጨነቃት ተረዱ ።

« ልጄ ግድየለም ለመንገር ካልፈለግሽ ። » በማለት ከተቀመጡበት ለመነሳት ሞከሩ ። ሕሊና በእጇ ይዛ ከተቀመጡበት እንዲቆዩ ጋበዘቻቸው ።

« ለመንገር አለመፈለግ አይደለም ፤ ብነግርዎት ደስ አይልዎትም ብዬ ነው ። » አለች ሕሊና በሀፍረት ዓይነት ።

« ልጄ አንቺ ያደረግሽው ደግሞ ምኑ ይጠላል ። ግድ የለሽም ተናገሪ ልስማው » አሉ ። ፊታቸውን አስገው በጉጉት መልክ ወደ ሕሊና እየተመለከቱ ።

« ያውቁታል ! » ከማለቷ ወ/ሮ በላይነሽ ኩምሽሽ አሉ ። ላፍታ ሁኔታቸው ተለዋወጠ ። የሰሙትን ባለማመን አንዳች ነገር እንደጠፋበት ሰው ከግራ ወደ ቀኝ ቃኙ ።

« ጠርጥሬያለሁ አንቺና ጓደኛሽ ስታወሩ ። ሀሰን የእኛው ነው ? » ከንፈራቸው እየተርበተበተ ፤ ምላሳቸው ተሳስሮ ወ/ሮ በላይነሽ የጠሩትን ሥም በግድ ተናገሩ ። ሕሊና አንገቷን ወደመሬት ደፋች ።

* * *

ወ/ሮ በላይነሽ ከአሰላ ወደ ያሬድ ተመለሱ ። ሕሊና ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር መለያየቱ ከባድ ሆኖ ብታገኘውም ቅሉ ከሀሰን ጋር ለጀመረችው ግንኙነት ብቸኝነቱ ስለሚሻላት ተፅናናች ። ሆኖም ከእንግዲህ ከሀሰን ጋር ያላት ግንኙነት ለብዙ ጊዜ ምስጢራዊ ሆኖ እንደማይቆይ ተረዳች ። ወ/ሮ በላይነሽ ለእርሷ ባላቸው አክብሮትና ፍቅር ሲሉ ጉዳዩን በሽማግሌ ለማስተካከል ሀሳብ አቅርበው ነበር ። ሆኖም ሕሊና የእርሷንና የያሬድን መቀያየም ከእነ ምክንያቱ የግል ምስጢሯ አድርጋ በመውሰድ ሽማግሌ በመላክ ላይ አልተስማማችም ። በሌላ በኩል ደግሞ በእርሷና በሀሰን መሀከል ያለው ግንኙነት ሊያብብና ሊፈካ አልቻለም ። በቤትና በአልቤርጐ ብቻ ተወስኖ መቅረቱ አሳሰባት ።

ሕሊና አንድ ቅዳሜ በሀሰን ጋባዥነት ወደ አዲስ አበባ መጣች። ሀሰን ሕሊናን ከአውቶቡስ ተራ ተቀብሎ ወደ ሾላ ጉዞአቸውን አቀኑ ።

« ዛሬ በጣም ነው አውቶቡሱ የዘገየው ምነው ምን አጋጠማችሁ ? » ሲል ጠየቀ ሀሰን ወደ ሕሊና ሳይዞር ፣ የሚሄድበትን አቅጣጫ ላስመሳት ።

« የግል መኪና መስሰህ አውቶቡስ እኮ ነው ። » አለች ኮስተር ብላ ፣ መቀመጫዋ ላይ እየተስተካከለች ።

« እንዲያውም ላስመምጣት ወስኜ ነበር ። አንተን ላለማስቀየም ብዬ መጣሁ እንጂ ። » እኔ እኮ ለአንቺ በማሰብ ነው ! ለምን ዘገየ ብሎ መጠየቅ ይህን ሁሉ ውርጅብኝ አያስከትልም ። »

ሀሰን በፈገግታ ሕሊናን አየ ። እጁን በሕሊና ትከሻ ላይ ጣል አደረገ ። ሕሊና ትከሻዋ ላይ ያረፈውን የሀሰንን እጅ በቀስታ አስወገደች ። ቀሪው የሾላ መንገዳቸው በዝምታ ተውጦ አለፈ ።

« ዛሬ ላስመብላት የወሰንሽ ይመስላል ። » አለ ሀሰን አልጋው ጫፍ ላይ ወደተቀመጠችው ሕሊና እየተመለከተ ።

« እስከመቼ ነው ዝም የምንባባለው ? ምን ተፈጠረ ? እረ አንድ በይ እንጂ ! » ብሎ ጉንዋ ሄዶ ተቀመጠ ። ክንዱን አንገቷ ላይ አሳረፈ ። ዓይኖቿን በዓይኖቹ ፈለገ ። ሕሊና በሀሳብ ርቃ ስለነበር አልሰማችውም ። በዓይኗ ገርምማው እጁን አስወግዳ ከተቀመጠችበት ተነስታ በነጭ ስስ መጋረጃ ወደ ተሸፈነው መስኮት በቀስታ አመራች ። ሀሰን ተስፋ ባስመቁረጥ ተከተላት ። እኮ በይ እንጂ ምን አደረኩ ? አለ ለሁለተኛ ጊዜ ። ድንገት ፊቷን ወደ ፊቱ መለሰች ። ዓይኖቻቸው ተፋጠጡ ።

« እስቲ ንገረኝ በርግጥ ትወደኛለህ ? » ስትል ጮኸችበት ።

«አዎ እወድሻለሁ። ምን ዓይነት ጥያቄ ነው የምትጠይቂኝ?» የሀሰን ዓይኖች ተርገበገቡ ። ከንፈሮቹ ተርበተበቱ ።

« በእርግጥ እወድሻለሁ » አለ በለሰለሰ ድምጽ ። ዓይኖቹን ከድኖ ወደ ሕሊና ተጠጋ ። ከንፈሩ ከከንፈሯ ፣ ትንፋሹ ከትንፋሿ ጋር ተዋሃደ ። ስሜታቸው አሸንፏቸው ተያይዘው አልጋው ላይ ወደቁ ። ያነሱትን ጉዳይ ረሱ ። አካላቸው አንድ ሆነ ። እኩል ሌሊት አለፈ ። ሕሊና አልጋው ላይ ተጋደመች እንጂ ዕንቅልፍ አልወሰዳትም ። የእርሷ መገላበጥ ደግሞ ሀሰንን ዕረፍት ነሳው ። ድካሙና የሰውነት ዝለቱ አለቀቀውም ።

« ምነው አልደከመሽም ፣ ለምን አትተኚም? በማለት ተንጠራራ ። ፊዘዝ ባለው መብራት የሕሊናን ፊት ለማየት ሞከረ ።

« ዕንቅልፍ እንቢ አለኝ » አለች ። ፊቷን ወደ ግድግዳው አዙራ ጀርባዋን ለሀሰን ሰጠች ።

« ምን እያሰብሽ ነው ? ለምን ብቻሽን ትጨነቂያለሽ ? » ሀሰን የራሱ ጥያቄ ከእንቅልፉ ሙሉ ለሙሉ አነቃው ።

« ሀሰን ምንም ሳትደብቅ ንገረኝ ፣ እማማ በሳይነሽ አሰላ ከመጡ በኋላ እንደድሮህ አይደለህም ። እመጣለሁ ብለህ ትቀራለህ ። እኔ ካልደወልኩ ስልክ እንኳን መደወል ትተሃል ። ይህ ከምን የመጣ ነው ? » በማለት ፊቷን በእጆቿ አንተርሳ ወደ ሀሰን ተመለከተች ። ሀሰን ለጥያቄዋ መልስ ለመስጠት አልቸኮለም ። ጥቂት አሰብ አድርጎ ፣

« ሕሊና ምክንያቱን ደግሜ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ ። ሥራ ስለሚበዛብኝ ነው ብዬሻለሁ ። የሌለ ምክንያት አልፈጥር ፣ እንግዲህ ምን ብዬ ልንገርሽ ? » አለ ትርጉም በማይሰጥ አመለካከት ሕሊናን እያስተዋለ ።

« ድሮም ሥራ ይበዛብኛል ትላለህ ፤ ሆኖም የአሁኑ ለብቻው ነው » አለች የተናገራትን ባለመቀበል ። « እንግዲህ ከዚህ የበለጠ ምንም ማድረግ አልችልም ። በሌለ ነገር መጨነቅ ከፈለግሽ መቀጠል ትችያለሽ » አለ ሀሰን ቆጣ ብሎ ። ፊቱን ከሕሊና አዙሮ ራሱን ለመኝታ አመቻቸ ።

« እሺ ያልከውን ልቀበለው ፣ ነገር ግን ለምንድነው የእኛን ግንኙነት ጋሼ ያሬድ እንዲያውቅ የማትፈልገው ? » አለች ። « ዛሬ

ሕሊና ምን ነካሽ ? ደግሞ ምን ብዬ ነው የምነግረው ? እስቲ አንቺም አስቢው » በማለት ቆጣ ብሎ መለሰላት ። « ምንም አልነካኝ ። ምን የነካኝ ይመስልሃል ? ያለውን የተደረገውን ለምን አትነግረውም ነው ያልኩት ። ጓደኛህ ነው ። እኔም ሆንኩ አንተ ልናከብረው ይገባል » አለች እሷም ቆጣ ብላ ።

ሀሰን ሕሊናን ረሳና ውስጡን ለማየት ሞከረ ። አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋሉ ዓይኖቹን ኮርኒሱ ላይ ተክሎ በሀሳብ ተዋጠ ። ውስጡ የሕሊና ሀሳብ ትክክል እንደሆነ ሹክ አለው ። ግን እውነት አይደለም ። ሕሊናን ከድብብቆሽ ጨዋታ በላይ እጅግም አስቧት አያውቅም ። ስለትዳር ፣ ስለቁምነገር ባሰበ ቁጥር ሙና ትመጣበታለች ። የያሬድ ጉዳይ ያሳስበዋል ፤ ለሕሊና ይፈራል ።

* * *

ፈንጠር ካለው ወንበር ላይ ተቀምጦ በሳሉን በር በኩል የሚወጣ የሚገባውን ሰው በታዛቢነት የሚመለከት ይመስል ነበር ። የቀረበለትን ለስላሳ ለማንሳት እጁን ሲዘረጋ ከአስተናጋጅዋ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ ። በሀፍረት ፈገግታ ፊቷን አድምቃ የሚስለመለሙ ዓይኖቿን የግዷን ከዓይኖቹ ላይ ነቀለች ። ገራ በመጋባት ለአፍታ ቆም ብላ ወደሚቀጥለው እንግዳ አመራች ። የመስፍን ዓይኖች እብረዋት ተንከራተቱ ።

የመስፍን የቤት እያት ወ/ሮ ባልከፋሽ ካረፉ አራተኛ ቀናቸው ነበር ። ለመስፍን ከመላ ቤተሰቡ ጋር በመሆን ለሀዘን ተካፋይነት የመጡትን እንግዶች መቀበልና ማስተናገድ ብሎም ማስናበት እንደ አዲስ የህይወት ልምድ ነበር ። በአንድ ቦታ ተቀምጦ የባጡን የቆጡን፣ ያለውንና የሚመጣውን መወያየት ከተለየው ዓመታት አለፉ ።

መስፍን በ16 ዓመቱ የፈረንሳይ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለ አባቱ ቀኝአዝማች ደርብ ወደ ፈረንሳይ ሄዶ ትምህርቱን እንዲቀጥል ወሰኑ ። በፈረንሳይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ታላቅ ወንድሙ ሙሉጌታ ደርብ ወደ አሜሪካ ጋበዘው። መስፍን የአሜሪካ ኑሮ በጣም ስለአጓጓው ትምህርቱን አሜሪካ እንዲጨርስ ከወንድሙ ከሙሉጌታ ጋር ተስማሙ ።

በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ ተካሄደ ። ቀኝአዝማች ደርብ ለውጡን ባለመቀበል ኮብልለው ወደ ጫካ ገቡ ። መስፍን የአባቱን ሁኔታ ሲሰማ የመመለሱን ጉዳይ አዘገየው ። የሀገር ቤት ሁኔታ እስከሚረጋጋ አሜሪካ ለመኖር ወሰነ ። ወደ ሀገሩ ሳይመለስ ሃያ ሰባት ዓመታት ቆየ ። በእናቱ በወ/ሮ እጅጋየሁ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ምክንያት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ነበር ። ሆኖም ወደ ሀገር ከገባ በኋላ አንዱን ነገር ሌላው ሲጎትተው ለጥቂት ወራት ለመቆየት ወሰነ ። ከሁሉም በላይ ያብከነከነው የአባቱ ጉዳይ ነበር ።

ከለውጡ በኋላ ጫካ እንደገቡ ይነገር እንጂ መሞት መኖራቸው ሳይታወቅ በእንጥልጥል መቅረቱ ዕንቅልፍ የነሳው ትልቅ በሽታ ነበር ። ነገር አዋቂዎች ቢጠይቅ ፣ ጓደኞቻቸውን ቢያወያይ የተጨበጠ መልስ አላገኘም ። በቤተሰቡ ላይ የደረሰውን መበታተንና መጎሳቆል አሜሪካን ሆኖ የሰማውና በተቻለው ሁሉ ድጋፍ ለመስጠት ጥረት ያደረገ በመሆኑ በመጠኑ የህሊና ሠላም ለማግኘት ችሏል ። ወንድሞቹና እህቶቹ ከአካባቢው ጋር ተመሳስለውና ተጋብተው ድሮ ከነበራቸው የከበርቴ ኑሮና አስተሳሰብ ርቀው ነበር ያገኛቸው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሀገሩ እንደገባ የሚያየው ሁሉ የፈራረሰና ያረጀ፣ ሰው ሁሉ እስረኛ ነበር የመሰለው ።

መስፍን ልጅቷን ከዚህ ቀደም ያየበትን ቦታ መልሶ መላልሶ ለማስታወስ ሞከረ ። በሀሳቡ « አበራ አስተዋወቀን ልበል ? በቀደም

የቀብሩ ዕለት ማሳረጊያው ላይ ነበረች እሷ አይደለችም ። ያቺ ምስጢረ የምትባል የአበራ ጓደኛ ነች ። ግን አይመሳሰሉም ? ኖ . . ኖ . . ይህችኛዋ ዘለግና ረጋ ያለች ቆንጆ ነች ። ምስጢረ ግን ተጫዋች ነች ። ምናልባት እህትማማቾች እንዳይሆኑ . . . » በማለት በሀሳቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ቆየ ። ወጣቷ በዝርግ ስህን ቆሎ ይዛ ከጓዳ በር ብቅ አለች ። አዲስ ወደገቡት እንግዶች አመራች ። መስፍን ሀሳቡን አላቋረጠም ።

« እግር አጣጣሏ እንኳ ያስታውቃል ፤ ዝግ ያለች ነች። አመለካከቷ ዓይን አፋርነቷ የጨዋ መልክ ሰጥቷታል ፤ ይቺን ያፈቀረ ፣ የወደደ መቼም የታደለ ነው ። ኖ . . ኖ . . አይደለም ማፍቀር እንጂ መውደድ አንድ ወጥ ከሆነ አደገኛ ነው . . . » ሲተዋወቃት ወሰነ ። ያለበት የሀዘን ሁኔታ ይፍቀድ አይፍቀድ ግን ተጠራጠረ ።

ሀዘንተኛው በተቀመጠበት ትልቁ ሳሎን አዛውንት እናቶች ፣ ቀሳውስት ፣ ወንደላጤውና ሴተላጤው በየፊናቸው ተከፋፍለው የግል ጭውውታቸውን በደራ ሁኔታ ተያይዘውታል ። አስተናጋጆቹ ከቆሎ፣ ዳቦ ፣ ንፍሮ አንስቶ እስከ ቡና ፣ ቢራና ለስላሳ አቀረቡ ።

የአንዱ ወገን ስብስብ ቀልድ መሳይ ጣል በማድረግ ቤተሰቡ መለስ ብለው መኖር ፣ ማዘን ፣ መደሰት ፣ መተከዝ በሰው ህይወት ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ህግጋት መሆናቸውን እንዲያጤኑ ፣ እንዲሁም ከሀዘናቸው እንዲፅናኑ ረዳቸው ። ቄሱ የማፅናኛ ቡራኬና የነብስ ይማር ፀሎት ሲያደርጉ ፣ አዛውንቱ ታሪክን ከሟች ጋር በማያያዝ ያሳለፉትን ህይወት በማወዳደር አነሱ ። ሌላው ተሳታፊ በቀልዱና በቴያትራዊ ድርጊት በመሳተፍ ቤተሰቡን አዝናኑ ።

ከጓዳ በር አንድ መልከ መልካም መሀከለኛ ዕድሜ ላይ ያሉ ወ/ሮ በዝርግ ሰሀን ያልተከፈተ ቢራና ለስላሳ ይዘው ወጣ አሉ ። እርሳቸው በሚያልፉበት በኩል የተቀመጡት አዛውንት ፣ ሽማግሌ ፣

እናቶች፣ አባቶች ሁሉም በአንድነት በሳቅ ፈነዱ :: ሁሉም ትኩረቱን ወደ አሳሳፊዋ ወይዘሮ አደረገ :: የኋላቸውን ለማየት ዕድሉን ያገኙ ሁሉ በሳቅ ፈነደቁ :: ወይዘሮዋ በተፈጠረው ነገር በመደናገጥ ዓይናቸውን ወደ ራሳቸውና ወደሚስቀው ሰው መለስ መለስ በማድረግ « ምን የሚያስቅ ነገር ተገኘ ? » በማለት ጠየቁ :: እንደሳቸው ግራ የተጋባው መስፍን ብቻ ነበር :: ከመቀመጫው አፈፍ ብሎ ተነስቶ ከኋላቸው በመርፌ ቁልፍ ነጠላቸው ላይ የተያያዘውን ጅራት መሳይ የአሻንጉሊት ቁራጭ ለማንሳት ሞከረ :: ግራ የተጋቡት ወይዘሮ « ምን ልታደርግ ነው ? » በማለት ቀሚሳቸውን ወደ ራሳቸው ሰበሰቡ ::

« እላይዎ ላይ አንድ ነገር አለ :: እርሱን ለማንሳት ነው » አላቸው መስፍን :: ወይዘሮዋ መስፍንን እየገላመጡ የሳቁን ግርግር አቋርጠው እየተመናጨቁ ወደ መጡበት ጎዳ ተመለሱ :: መስፍን በቆመበት

« ምን አደረግኩ ? ቆሻሻን ከሰው ላይ ማንሳት ያስነውራል እንዴ ? » በማለት ራሱን ጠየቀ :: ሳያስበው ግራ እንደተጋባ ወደውጪ ወጣ :: ወጣቷ ሁኔታውን ትከታተል ስለነበር ተከተለችው:: ወንድሙ አበራም ሠለሰ ::

« መስፍን ምነው ምን ሆንክ ? » ሲል አበራ በመካከላቸው የቆመችውን ሴት እያየ ጠየቀ ::

« ምንም ! ምን የሆንኩ ይመስልሃል ? » አለ መስፍን ::

« በሰው ሳቅ ተቀይመው ነው ? » አለች :: አንቱታዋ ለመስፍን በአክብሮትም ሆነ ፣ በሌላ መልኩ አላስደሰተውም ::

« መስፍን ባህላችንን ታውቀው የለ » አለ አበራ ::

« ተወው አውቃለሁ :: ጥፋቱ የእኔ ነው :: በማላውቀው ነገር ዘው ብዬ መግባቴ ፣ ምን ታደርገዋለህ ለገዛ ባህልህ እንግዳ

ስትሆን ፣ መቼ ይሆን ይህን ባህል ተምሬ የምጨርሰው ? » አለ መስፍን በድርጊቱ በመፀፀት መልክ እራሱን እየነቀነቀ ::

« በነገራችን ላይ ከመስፍን ጋር አልተዋወቃችሁም ? ይቅርታ በቅርብ ከአሜሪካ የመጣው ታላቅ ወንድሜ መስፍን ማለት እሱ ነው . . . ሕሊና ከታወቁት የትምህርት ቤቱ መምህርት አንዷ ናት ተዋወቁ » አለ ::

« በዝና ሰምቻለሁ :: አበራ ስለእርስዎ ብዙ ያወራል » ብላ እጇን ዘረጋች እንደ መጨበጥ ዓይነት ::

« ኧረ አንተ በይ :: እርስዎታው ከበደኝ :: አበራ ስለ እኔ ብዙ ያወራል :: በመጥፎ ነው ወይስ በጥሩ ? » ሲል ጠየቀ በማፌዝ መልክ ::

« ስለአንተ ምን መጥፎ ነገር ይወራል ? የምትኖረው አሜሪካ ፣ የምትሄደው በመኪና ፣ የምትበላው ወደል ሀምበርገር ፣ አንድ መስመር የያዘ ህይወት ፣ ግርግር የሌለብህ ፤ » አለ አበራ ከሕሊና መልስ ቀድሞ ::

« እርሱን ተወው ! . . . » አለና የአበራን ዲስኩር ትቶ ወደ ሕሊና ፊቱን መለሰና « ታዲያ መምህርት ማስተማር እንዴት ይዞሻል ? » አላት ::

« ማስተማር ቀላል ነው :: የተሰበሰቡ ተማሪዎችን በተወሰነ የትምህርት መስክ በተሰጠው መፅሀፍ መሠረት መምራት ምን ያቅታል ? ከማስተማሩ ይልቅ መማሩ ነው ከባድ » አለች አንድ ጊዜ መስፍንን ሌላ ጊዜ አበራን አፈራርቃ እያየች ::

« መምህርት መማር የሰለቸሽ ትመስያለሽ ? እንዴት ታድለሻል ? . . . አለ መስፍን :: « በህይወቴ እንደመማር የምወደው ነገር ያለ አይመስለኝም :: ሆኖም ፍላጎቴን ለማሟላት በቂ ሀብት የለኝም እንጂ አለመማር ምንጊዜም ምርጫዬ አልነበረም ፣ አይሆንምም :: » ስትል ሕሊና ነገሩን በጥሞና ለማስረዳት ሞከረች ::

መስፍን የስኮሰውን ሲጋራ አልጨረሰም ። አንድ ኮረዳ ከቤት ውስጥ በበር ወጣ ብላ « ጋሼ አበራ እራት ሊቀርብ ነው » በማለት ተጣራች። ሳሎን እንደገቡ ሒሲናና አበራ በሩ አጠገብ ሲቆሙ መስፍን መሀል ለመሀል አቋርጦ ወደ መቀመጫው አመራ ።

« የሞቱትን ነፍስ ይማርልን ። አቡነ ዘበሠማያት እንበል ።» ብለው ጋቢያቸውን አጣፍተው መስቀላቸውን ደግነው የቆሙት ባለ ነጭ ትልቅ ጥምጣም አዛውንት ቄስ ዓይናቸውን መስፍን ላይ አሳርፈው ነበር ። ቃለቡራኬው እንዳለቀ ሒሲና ወደ ጓዳ ገባች ። አበራ ወደ ቀድሞ መቀመጫው ተመልሶ እራት መብላት ጀመረ ።

« ብዙ ማውራት አልቻልኩም እንጂ መምህርት በጣም ኢንተረስቲንግ ልጅ ሳትሆን አትቀርም » አለው አበራን መኝታቸውን እያዘጋጁ ።

« ሒሲና በጣም ጥሩ ሰው ነች ። የልጅ አዋቂ ነች ። ያወቃት ሁሉ ይወዳታል ። » በማለት አበራ ስለ ሒሲና ያለውን አድናቆት ገለጹለት ።

« ልጅ ማለት ፣ ዕድሜዋ ምን ያህል ቢሆን ነው ? » ሲል መስፍን አበራን ጠየቀው ።

« ዕድሜ ምን ያደርጋል ? አንደበቷና አስተሳሰቧ የሊቅ ያህል ነው ። ከዕድሜዋ በላይ የምታስብ ልጅ ናት » አበራ አድናቆቱን በመቀጠል ተናገረ ።

« እኮ ዕድሜዋ ስንት ይሆን ? »

« ምነው ዕድሜዋን አጥብቀህ ጠየቅከኝ ? ምን አስበሃል ? »

« ምን አስባለሁ ? እንዲሁ ለማወቅ ያህል ነው ። አንተ ምነው . . . በመሀከላችሁ ነገር አለ እንዴ ? »

ሒሲና ወደ ቤት ስትሄድ ስለመስፍን ማሰቧን ማቆም አልቻለችም ። ከስሜቷ ጋር በሀሳብ እየተከራከረች መኖሪያ ሰፈሯ ደረሰች ። የቀኑ ድካም የተጫጫናት ሒሲና አጠገቧ ባለው ሶፋ

ወንበር ላይ በረጅሙ ተንፍሳ ተቀመጠች ። ጣሪያ ጣሪያውን እያየች በሀሳብ ማዕበል ተዋጠች ።

« ትልቅ ሰው ነው አንቱታዬን ለምን ጠላው ? ዝምተኛ ይመስላል ። የአበራ ታላቅ ወንድም ? አበራ ነው ታላቅ የሚመስለው። አበራ መልኩ ተጉሳቁሏል ። ሽበትም ወጋ ወጋ አድርጎታል ። መቼም ድሉት ህይወት ነው ። ገምች ቢሉኝ ከ35 ዓመት ያነስ እንጂ የበለጠ አላደርገውም ። የተማረ መሆን አለበት ። እንግሊዘኛው . . . ግን በእንግሊዘኛ የተናገረ ሁሉ የተማረ ነው ማለት ነው ? » ሒሲና ለጥያቄዋ ሁሉ መልስ ማግኘት አልፈለገችም። በሀሳቧ ብዙ ለመግፋት አልቻለችም ። በአለችበት ዕንቅልፍ ይዟት ሄደ ።

* * *

አልጋዋ ላይ አረፍ ብላ ነበር ደብዳቤውን ማንበብ የጀመረችው። ባልጠበቀችው ሁኔታ የልብ ትርታዋ እየጨመረና እጇ እየተርበተበተ ነበር ደብዳቤውን የከፈተችው ።

« ሃይ ሒሲና እንደምን ሰንብተሻል ። መቼም ይህ ደብዳቤ ሲደርስሽ ሳትገረሚ አትቀሪም ። በቅድሚያ የቤተሰባችን የሀዘን ተካፋይ በመሆንሽና ስላደረግሽው ከፍተኛ የጉልበትና የኢሞሽናል ድጋፍ በጣሙን አመሰግናለሁ ። እግዚአብሄር ይስጥልኝ ። ሒሲና ታናሽ ወንድሜን አበራን በጣም እወደዋለሁ ። እንዲህ ያለች ውብና አስተዋይ ጓደኛ በማግኘቱ በጣም ደስ ብሉኛል ። በሁለት ቀን ግንኙነት ወቅት የተጫወትናቸው ቁም ነገሮች ሁሉ እስከአሁን ትዝ ይሉኛል ። ከአንቺ ጋር ለመቀራረብ ሁኔታዎች

ባያመቹኝም ለወደፊቱ በደብዳቤ ይበልጥ እንደምንቀራረብ ተስፋ አደርጋለሁ :: የአንቺ ዓይነት ጓደኛ ለማግኘት የዘወትር ምኞቴ ነው :: ሆኖም ምኞት ብቻ ሆኖ ቀረ :: እዚህ ሀገር ሁሉ ነገር ሞልቶ ተርፎ የራስ የሆነ አስተማማኝ ጓደኛ ለማግኘት ግን አይቻልም :: ይህም በመሆኑ ህይወቴ የሙሉ ጎዶሎ ሆኖ ብዙ ጊዜ ያሳስበኛል:: ሕሊና ስለእኔ ስፅፍልሽ እንደማትቀየሚኝ እርግጠኛ ነኝ :: ሆኖም የልቤን ለምን እንደማወራልሽ አላውቅም :: ሕሊና ደብዳቤውን ከአበራ ጋር አጣምሬ የላኩት አድራሻሽ ስለሌለኝ ነው :: ለወደፊቱ በዚህ አድራሻ ብትፅፊልኝ በግልሽ ልፅፍልሽ እሞክራለሁ :: ለማንኛውም ስለ አስተዋፅዖሽ ደጋግሜ ላመሰግንሽ እወዳለሁ ::

አድራሻዬ ፤ Mesfin Derib
6540 N. Willson St.
Chicago, IL .70313
U.S.A

በይ እንግዲህ መልካም የሥራ ጊዜ እመኝልሻለሁ :: »

መስፍን ደርብ ::

ሳምንቱ እንደቀላል አለፈ :: « መቼም የአለፈው ሳምንት እንደማይደገም እርግጠኛ ነኝ » አለች ሕሊና ለከበቡሽ አብረው በጉዞ ላይ ነበሩ :: « ሳምንቱ ብቻ ትያለሽ ወሩ ባጠቃላይ ምን እንደሆነ እንጃ የሚያልፍ አይመስልም :: » ከበቡሽ የሕሊናን አባባል አረጋገጠች ::

« ቅዳሜ ምን ትሰሪያለሽ ? ለምን እኔ ጋ መጥተሽ አንውልም ? » አለች ከበቡሽ በመጋበዝ መልክ ::

« ውይ በጣም ጥሩ ነበር :: ነገር ግን ሀሰን እመጣለሁ ብሏል:: እሱ ምን ዕቅድ እንዳለው አላውቅም :: ብቻ ለማንኛውም እነጋግረዋለሁ :: ግን ለእኔ ብለሽ የራስሽን ሥራ እንዳትተይ » አለች ሕሊና :: « ወር ሞላው እንዴ ከመጣ ? » አለች ከበቡሽ ደስ በማይል መልክ ፊቷን እንጓጣ ::

« ምነው ለምን ጠላሽው ? ሀሰን እኮ በጣም ጥሩ ሰው ነው::» አለች ሕሊና አተኩራ ወደ ከበቡሽ በመመልከት :: « ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝና ሀሰን ደህና ሰው ሊሆን ይችላል :: ግን ይቅርታሽን እሱን መውደድ ? መቼም ፍቅር እውር ነው ይባላል :: » አለች በማሽሟጠጥ መልክ ::

« መቼም አይጣል ነው :: አንቺ አፍ የገባ :: በሀሰን ላይ መቼም ከአየሽው ጀምሮ ሰፍረሽበታል :: በይ እንግዲህ ወረድ በይልኝ » አለች ሕሊና በማፌዝ ::

« እኔ ምን ቸገረኝ :: እስቲ ተመልከቺ ይህችን የመሰለች ቆንጆ ! ሁሉም የሚመኝሽ ፣ ምን ከዚህ ጡሩራ ጋር አጣበቀሽ :: » አለች ከበቡሽ የሕሊናን ገፅታ ሙሉ በሙሉ በመቃኘት ::

« ምናልባት አስደግሞብሽ ይሆን ? »

« ኧረ አፈር ብዬ እቴ ምን ያለሽ ነሽ ? የምን ድግምት አመጣሽብኝ ? » አለች ሕሊና መንገድ መንገዷን እያየች ::

« በይ በዚህ ይለፍ . . . ዘለዓለም በዚህ ነገር መቼም እንደተጨቃጨቅን ልንኖር ነው ። » አለች ከበቡሽ ጉዳዩን ላለማንሳት በመወሰን መልክ ። ለጥቂት ደቂቃ አብረው በዝምታ ተጓዙ ።

ከበቡሽ ፊቷን ወደ ሕሊና መለስ አድርጋ « ከነከነኝ እባክሽን፣ ያልሽውን በይ እንጂ ዛሬ ሳልጠይቅሽ ብተው ለሊት ዕንቅልፍ አይወስደኝም ። ከዛ በፊት ግን ለምጠይቅሽ ጥያቄ ምላሽ እንደምትሰጪኝ ቃል ግቢልኝ » አለች ከበቡሽ ።

« ጠይቂኝ እመልስልሻለሁ ። ቃል ግን አልገባም ። ድንገት የማላውቀውን ጥያቄ ብትጠይቂኝና ሳላውቅም ብልሽስ ? » አለች ሕሊና ሀፍረት በተሞላበት ፈገግታ ።

« ምንም ሳትደብቂኝ እስቲ ንገሪኝ በምኑ ወደድሽው ? መልኩ፣ ገንዘቡ ፣ ፀባዩ ወይንስ ሰጨዋታ ያህል . . . ከወደድሽው ደግሞ ለምን አታገቢውም ? እስከመቼ ምስጢራዊ ግንኙነት አድርገሽ ትኖሪያለሽ ? » ከበቡሽ የጠየቀቻት ፍጥነት በተሞላበት አባባል ነበር።

« ለመሆኑ መውደዴን እንዴት ገመትሽ ? ለማንኛውም ለጥያቄዎችሽ ለጊዜው አጥጋቢ መልስ የለኝም ። ሆኖም ስለእኔ በመቆርቆርሽ በጣም አመሰግናለሁ » አለች ሕሊና በመልሷ ከከበቡሽ ይልቅ ራሷ በመገረም ።

« ሕሊና ይቅርታ ስለምወድሽና እንደራሴ ስለማይሽ ነው ይህን ያልኩት ። አትቀየሚኝ ። ሁለተኛ ስለዚህ ጉዳይ አላነሳብሽም » አለች በጥያቄዋና በአባባሏ የሕሊናን ስሜት የጎዳች መሰላት ። አበራ ጣደፍ ጣደፍ ብሎ ወደ ክፍሉ በመግባት ላይ ሳለ ሕሊና በሥሙ ጠራችው ።

« ቆየኝ ፣ ቆየኝ ፣ ዛሬ ማታ ምን ትሰራለህ ? ለብርቱ ጉዳይ እፈልግሃለሁ » ይመችሃል ? አለችው ።

« አፍኮርስ ሕሊና ምነው በደህና ? » በማለት ግራ በመጋባት መለሰላት ።

« ደህና ነኝ ። ለብርቱ ጉዳይ ማለት የማማክርህ ነገር ስላለኝ ነው » በማለት ስሜቷን ከአበራ ለመደበቅ ወደ መሬት አተኮረች ። ሁሉቱም አብረው አልቆዩም ። ፍጹማዊ የመተማመን ገፅታቸውን ተለዋውጠው ወደየክፍላቸው አመሩ ።

ሕሊና በውስጧ ተከድኖ የበሰለውን የሀሰንን ግንኙነት ትርጉም ለመስጠት ካልተመለሱ ጥያቄዎች ጋር ስትታገል ከቆየች ሰነበተች ። ብቻዋን ያለአማካሪ እነኚህን እንቆቅልሾች መፍታትና ጥያቄዎችን መመለስ አቃታት ። ሆኖም ጥረት ከማድረግ አልተቆጠበችም ። ሀሳቧ ሁሉ ዞሮ ተዳምሮ ወደዚሁ ስለሚያመራ ከውጭው ዓለም ጋር ያላት ግንኙነት ሁሉ የተቆጠበ ሆነ ። የሥራ ጓደኞቿና በቅርብ የሚያውቋት ሁሉ « ምነው ? ምን ሆነሻል ? ሀሳብሽ ርቆ የሄደ ይመስላል ። የሚወራልሽን አትሰሚም ፣ ማዳመጥ ትተሻል ። ግድ አይሰጥሽም ። » በማለት ግንኙነታቸውን እያሳሱ መጡ ።

ሕሊና ጉዳቷን በቀላሉ ለሌላ ሰው የማታወያይና ዕርዳታ መጠየቅ አግባብነት የሌለው ተግባር ነው ብላ የምታምን ሰው ነች ። « ራስን መቻል በሁሉም አቅጣጫ » የሚለውን የአባቷን ምክር የዕለት ተዕለት ተግባሯ ሆነ ። ግን ይሄ ለብቻው ነው ። እራሴን አሳልፌ ለጥቼ መመለሻ ጠፋ . . . ምኑን ነው የወደድኩት ? ደግሞስ እሱ ስለወደፊቱ ቀርቶ ስለነገም ማውራት አይፈልግም ። እኔስ ራሴ ብሆን ስለወደፊት ታይቶኝ ወይም አስቤበት አውቃለሁ ? . . . የቀን ተቀን ኑሮ ብቻ ነው በሀሳቤ የሚመጣው ። እንዴት ሆኖ ነበር እኔና ሀሰን እዚህ ደረጃ ላይ የደረስነው ? . . . ከበቡሽ እውነቷን ነው ። አሁን ሀሰን ላግባሽ ቢለኝ ? . . . ሕሊና ሀሳቧን አልጨረሰችም ፤ ተማሪዎቿ የሰጠቻቸውን የክፍል ሥራ ጨርሰው ወደ ጠረጴዛዋ መቅረብ ጀመሩ ።

* * *

« በመጠኑም ቢሆን አስደነገጥሽኝ ። እኔ መቼም ምን ተፈጠረ ብዬ ነበር ። በእኔ በኩል የተሰነዘረ አፍ እላፊ እንዳለ ብዬ ሲያብከነክነኝ ዋለ ። ጊዜ አግኝቼ ልጠይቅሽ ቸኩዬ ነበር ። ዳሩ ምን ያደርጋል አንቺ እንደሆንሽ ልብሽ መንኗል ። » አላት አበራ ሕሊና ቤት ሶፋ ላይ ተመቻችቶ ተቀምጦ ።

« አበራ ደግሞ ትንሹን ትልቅ ታደርጋለህ ። እኔ የጠራሁህ የወንድምነት ምክር ልጠይቅህ ነው ። ከዚያ በፊት ግን ሻይ ላቅርብ ። » አለች ሕሊና ወደ ጓዳ እየተራመደች ።

« ቆንጆ ሻይ ነው ። መቼም የአንቺን ሻይ የሚስተካከል የለም ። ለመሆኑ ምን ዓይነት ቅመም ነው የምትጨምሪበት ? » አለ አበራ ሕሊናን በማድነቅ ።

« ማ ! ማ ! ማ ! ይሄ ደግሞ ምንድነው ? » የቀረበለትን የቋንጣና የድርቆሽ ፍርፍር በዓይኑ እየፈተሸ ።

« አንተ መቼም ትንሹን ትልቅ ማድረግ ልማድህ ነው ። በባዶ አፍ እንዳላደርቅህ ብዬ ነው ። » አለች ሕሊና ውኃና የእጅ ማስታጠቢያ ይዛ እስታጠበችው ።

« አንተና ከበቡሽ መቼም ታድላችኋል ። » ስትል ንግግሯን ጀመረች ። « በማንኛውም መልኩ ተሳስባችሁ እና ተግባብታችሁ ይሄን ያህል ጊዜ መቆየታችሁ የሚያስቀና ነው ። መቼም ይህን ለማድረግ መቻል በጣም አስተዋይ መሆን ያሻል ። . . . ይሄውልህ እንደምታውቀው ሀሰንና እኔ ትርጉም ልሰጠው በማልችለው ግንኙነት ስንዳክር ሦስተኛ ዓመታችንን ያዝን ። አሁን ግን ሳስበው በህይወቴ ብዙ ጥፋት እንዳጠፋሁ ይሰማኛል ። ሀሰን የያሬድ ጓደኛ መሆኑን አጫውቼሃለሁ። ግንኙነታችን በምስጢር እንዲቆይ ይፈልጋል ።

ለምን በግልጽ ጓደኛሞች ለመሆን እንዳልቻልን ስጠይቀው « ነገሩ ውስብስብ ነው አይገባሽም » በማለት ጥያቄዬን ችላ ይለዋል ። እኔ ይህ የድብቅ ህይወት በጣም ነው የሰለቸኝ ። ሀሰን መጥፎ ሰው አይደለም ። ጥሩ ሰው ነው ። ሆኖም ትውውቃችን በእኔ ቤትና በሆቴል መኝታ ቤት ተወስኖ ቀረ ። ሀሰንና እኔ ከዚህ ውጭ ምን እንደምንመስል አልተያየንም ። በአጠቃላይ ከመኝታ ውጪ ሀሰን ምን ዓይነት ነው ብትለኝ ይሄ ነው ብዬ መመለስ አልችልም ። አልፎ አልፎ ሲመጣ ከምናወራበት ሰዓት በዝምታ የምናሳልፈው ጊዜ ይበልጣል ። » አለች ሕሊና እጆቿን እያፍተለተለች ዕንባ ያቀረዘዙትን ዓይኖቿን በጠረጴዛው ላይ አሳርፋ።

አበራ ሕሊናን በተመስጦና በሀዘኔታ አዳመጠ ። « ለመሆኑ ለእኔ እንደነገርሽኝ ሁሉ ለእርሱ ለማስረዳት ሞክረሻል ? » ሲል ጠየቀ ።

« መሞከሩን ሞክሬ ነበር ። ነገር ግን እሱ በእዚህ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ፈቃደኛ አይደለም ። ከዚያም አልፎ ጥያቄዬን ላለመመለስ እመጣለሁ ባለው ቀን ይቀራል ። ወይንም ምክንያት ይፈጥራል ። ደክሞኛል ፣ አሞኛል ፣ ዛሬ ጥሩ ቀን አይደለም ፣ መቼም የማይለው የለም ። ባለፈው ሳምንት እንደመጣ በቁምነገር እንድንነጋገር ጠየኩት። በመጨረሻም ለጥያቄዬ ምክንያት አድርጐ አልበርጐ አድሮ ደህና ዋይ ሳይለኝ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ። እዚህ እምቢ ያለውን አዲስ አበባ ደርሶ ስልክ ደውሎ « ይቅርታ አድርጊልኝ ። ያንቺ ጥያቄ አይደለም ያናደደኝ ፤ ሥራ ላይ ተናድጄ ስለነበር ። ወደ አንቺ ስመጣ ንዴቴን መቆጣጠር አቅቶኝ ነው » ብሎ በመሀላ ተገዘተ ። አለች ዕንባዋን በእጆቿ እየጠራረገች ።

« ታዲያ አንቺ ምን መለስሽለት ? » አበራ ጠየቀ ለመልሱ በመጓጓት ።

« ምን ልበለው ? ይቅርታ አድርጌአለሁ ፤ አላደረግሁም አላልኩም ። በትምህርት ቤቱ ስልክ ስለደወለ ብዙም ለመናገር አልቻልኩም ። አጠገቤ ሰዎች በመኖራቸው እሺ እሺ ብዬ ስልኩን ዘጋሁት ። ግን እርሱ በሚቀጥለው የሳምንት ማለቂያ እመጣለሁ ያኔ እንነጋገርበታለን ብሏል ። እውነት ከሆነ » አለችና ዕንባ ባልተለየው ዓይኖቿ ወደ አበራ ተመለከተች ። አበራ የሕሊና ጉዳይ ምንም ያህል ቢያብከነክነውም ቅሉ በሀሳቡ ሁለት የተለያዩ ቅራኔዎች ነበሩ ።

« በጣም ትወደዋለች ፤ በጣም ትጠላዋለች » ቅራኔዎችን ማረጋገጥ አልሞከረም ። የማብራሪያ ጥያቄዎችን በመወርወር ጣልቃ ሳይገባ ሕሊናን አዳመጠ ።

« ታዲያ ሲመጣ ዕቅድሽ ምንድነው ? » በማለት ሕሊናን ጠየቀ ።

« እኔ እንጃ ፤ ግራ ገብቶኛል ። በእውነት ሀሰን ችግሩ ምን እንደሆነ ለመረዳት እፈልጋለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ የሚለውን ብቻ ከማዳመጥ እኔም ራሴ ማድረግ የምችለውን ማወቅ አለብኝ ብዬ ገመትኩ ። . . . . . እሱ ግድ የለውም ብዬ እንዳልደመድም ይሄው ውሎ አላደረም ስልክ በእስቸኳይ ደወለ ። ይሁን ብቻ በእርግጥ ጭንቀት አለበት ። ጭንቀቱ ግን ለከፋ ይሁን ለደግ ለይቼ ለማወቅ አልቻልኩም ። የእርሱ ጭንቀት ነው ወደ እኔ ተጋብቶ ግንኙነታችንን ሁሉ ጥርጣሬ ላይ የጣለው » ብላ ከመጨረሷ አበራ ፒሙን አሸት አሸት አድርጐ አቋረጣት ።

« አንቺ ትጠረጥሪዋለሽ ወይንስ እርሱ ይጠረጥርሻል ? » ሲል ጠየቃት ። ሕሊና መልስ ለመስጠት አልቻለችም ።

« የእርሱን አላውቅም . . . እኔ ግን ግንኙነታችን ትክክል ነው አይደለም ብዬ እጠራጠራለሁ ። ሌላው ግንኙነታችን የእኔ ፍላጎት ብቻ ይመስለኛል ። ሀሰን ግን እኔን ላለማስቀየም ብሎ ቀጠለበት» በማለት አንገቷን ገደድ አድርጋ ወደ አበራ ተመለከተች።

« እውነትም ውስብስብ » አለ አበራ በረጅሙ ተንፍሶ በመንጠራራት ዓይነት ።

« ለመሆኑ ልትቀርቢው የምትችይ ጓደኛ የለውም ? » ሲል አበራ ጠየቃት ።

« ያሬድ ነው ፤ እኔ የማውቀው የቅርብ ጓደኛው ። ከያሬድ ሌላ ማንንም አላውቅም ።ባውቃቸውስ ምን ብዬ ልነግራቸው ነው? » አለች ሕሊና ለራሷ በመናገር ዓይነት ።

ሕሊና እኔም ግራ ገባኝ ። በነገርሽኝ ላይ ተመርኩዤ ምክሬን ብለግስሽ እንዳላሳስትሽ ፈራሁ ። የሰማሁት አንቺን ብቻ ነው ። ከሀሰን ጋር እምብዛም ተነጋግረን አናውቅም ። ለማውራትና በቅርቡ ለመተዋወቅ እንኳን አልበቃንም ። ታዲያ በዚህ ላይ ምክር መስጠት ማለት ነገርን ሳይበስል በአጭሩ መቅጨት እንዳይሆን ሰጋሁ ። » አለና ስሜቷን ለማንበብ ወደ ሕሊና ዓይኖች አተኮረ ።

« እሮይ ! » በማለት ሕሊና በረጅሙ ተነፈሰች ።

« ለአንተ በመናገሬ ትንሽ ቀለል አለኝ ። አበራ ምን ያህል እንዳስጨነቀኝ አታውቅም ። የማይርቁት ወዳጅ ሆነብኝ ። ራሴ ተቸግሬ አንተንም አስቸገርኩ ። ከአንተ አልፎ ከበቡሽ እንኳን ተጨንቃ ልትሞት ነው ። » ከማለቷ አበራ ዘና ብሎ « ለከበቡሽ ነገርሻት እንዴ ? » ሲል ጠየቃት ።

« እንዴት እንደሆነ አላውቅም ከበቡሽ ስሜቴን በሙሉ ታውቃለች ። ሀሳቤን እንዴት እንደምታነብ ግን ማግኘት አቃተኝ ። አንዳንዴ መስማት የማልፈልገውን እንዳትነግረኝ እፈራለሁ ። »

* * *

ሕሊና በትምህርት ቤቱ በኩል የተላከላት ደብዳቤ ከማን እንደሆነ ለማወቅ ጓጓች ። ቀደም ሲል ደብዳቤ የሚደርሳት በፖስታ ቤት በኩል በተከራየችው ሳጥን ነበር ። በትምህርት ቤቱ በኩል ፖስታ መለዋወጥ ያቆመችው ቀደም ሲል የሚላኩላት ደብዳቤዎች ያለ አድራሻ እየተሰወሩ በመቸገሯ ነው ። ሥሟ በተለጠፈው ዝርዝር ውስጥ መኖሩን የነገረቻት ከበቡሽ ነበረች ።

ከበቡሽ ትቀልዳለች ። . . . ይኼ ደግሞ ሌላ የመመርመሪያ ዘዴዋ ነው ብላ በማሰብ የከበቡሽን ንግግር አልተቀበለችውም ነበር ።

« እውነቴን እኮ ነው የምነግርሽ ! ሂጂና ተመልከቺ ። » አለች ከበቡሽ ኮስተር ብላ ። ሕሊና እየሳቀች ቀና ብላ ከበቡሽን አየቻት ። ፊቷ ላይ የቀልድ ምልክት እንዳለ ለማወቅ በትኩረት አጤነቻት ። የዛሬው አቀራረቧ ከሌላው ቀን ለየት አለባት ።

ሕሊና ደብዳቤውን እስከምታገኝ አላመነችም ነበር ። ደብዳቤውን ለማግኘት የጠዋቱን አጋማሽ የዕረፍት ጊዜ መጠበቅ ነበረባት ። አማራጭ አላገኘችም ። ወደ ክፍሏ ገባች ። ፖስታ አዳይ ወደሆኑት የትምህርት ቤቱ ፀሃፊ ቢሮ ስትቀርብ እርሷ የመጀመሪያ ሰው ነበረች ። ፖስታውን እንዳገኘች ወዲያውኑ አድራሻውን ለማየት ሞከረች ። ፍጹም ያልጠበቀችው ደብዳቤ ! ተገረመች ። ፖስታው የተላከው ከአሜሪካ ነበር ። ፀሀፊውም መስፍን ነው ። ሕሊና ቀደም ሲል ለፃፈው መልስ አልመለሰችም ። በአጠቃላይ ሁኔታው ግራ በመጋባት በዝምታ ለማለፍ ወስነች ። ይህ ሁለተኛ ደብዳቤ ሲደርሳት መስፍን ጠበቅ ያለ ግንኙነት መፈለጉን ገመተች ። ባለችበት ቆማ ግራ በመጋባት ደብዳቤውን ከፍታ ማንበብ ጀመረች ።

« ሠላም ሕሊና እንደምን ሠንብተሻል ። ስለጤንነትሽ አበራ ሁልጊዜ ከሚፅፍልኝ ደብዳቤ መረዳት ችያለሁ ። እስከ አሁን አበራ ከሚሰጥሽ መልዕክቶች የእኔን ደህንነት እንደተረዳሽ እርግጠኛ ነኝ ። የፖስታ ሣጥን ቁጥርሽን ባለማግኘቴ በትምህርት ቤት በኩል ልፅፍልሽ ወሰንኩ ። « ሕሊና እሰላ የመጣሁ ጊዜ ብዙ ነገሮች ሳይገቡኝ ላይ ላዩን ጋልቤ ነው የተመለስኩት ። በችኮላ ብዙ ስመሥራት ጣርኩኝ:: አሁን ከአበራ ጋር ስንፃፃፍ ነው ስለ አንቺና አበራ ግንኙነት በከፊል ለመረዳት የበቃሁት ። »

« ሕሊና ! ምነው ሙጥኝ አለብኝ አትበይኝና የፃፍኩልሽ መፃፍ ስለፈለግኩና በማላውቀው መንገድ አንዳች ግፊት ስለሚገፋፋኝ ነው ። ይህ ግፊት ምንድነው ብትይኝ ልነግርሽ አልችልም ። ሕሊና እዚህ ኑሮዬ ጥሩ ነው ። እሰራለሁ ፣ እኖራለሁ ፣ አልፎ አልፎም እማራለሁ ። ሕሊና እባክሽን ፃፊልኝ:: በመፃፍሽ ደብደቤዬን ለመቀበል ፈቃደኛ እንደሆንሽ ለመረዳት እችላለሁ ። በተረፈ ለውለታሽ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በአበራ በኩል ትንሽ ስጦታ ልኬልሻለሁ ። እንግዲህ ደብዳቤሽን በጉጉት እጠብቃለሁ ።

አድራሻዬም፤ Mesfin Derib

6540 N. Willson St.

Chicago, IL .70313

U.S.A

ያንቺው ናፋቂ መስፍን ደርብ ።

ሕሊና ፊቷ በፈገግታ ተሞላ ። በሀሳቧ « ከዚህ በኋላስ . . . የሚቀጥለው » ስትል አሰበች ። ጊዜም አላጠፋች ። ወዲያውኑ ወደ አበራ ክፍል ሄደች ። ቤቷ ቀጠረችው ።

አበራ እንደወትሮው ሠላምታውን አጋኖ « እዚህ ቤቶች » በማለት ወደ ሕሊና ቤት ገባ ። ሕሊና ተቀምጣ ከተማሪዎቿ የሰበሰበችውን ወረቀት በማረም ላይ ነበረች ። « ሃይ አቤ ግባ » በማለት ከመቀመጫዋ ተነሥታ ተቀበለችው ። ሻይ ቡና በመጠየቅ ለማስተናገድ ሞከረች ። ሆኖም አበራ ግብዣዋን አልተቀበለም ።

« ከበቡሽ ትጠብቀኛለች ፤ ቶሎ እንድትመለስ ስላለችኝ ሌላ ጦርነት ከመከፈቱ በፊት » በማለት ወደ ሕሊና ተመለከተ ።

« አበራ ዛሬ ከመስፍን ደብዳቤ ደረሰኝ ። » ፊት ለፊት ተከማችተው ከሚገኙት ወረቀቶች መሀከል ገልበጥ ገልበጥ አድርጋ ፖስታውን ለአበራ ሰጠችው ። አበራ ደብዳቤውን ሲያነብ በትኩረት ተመለከተች ። በሚያነብበት ሰዓት ከፊቱ ላይ ስሜቱን ለማንበብ ሞከረች ። አንብቦ እንደጨረሰ ደብዳቤውን በማቀበል መልክ እጁን ወደ ሕሊና ዘረጋ ።

« አዎ መስፍን በደብዳቤዎቹ ላይ ስለአንቺ አንስቶ የማያውቅበት ጊዜ የለም » አለ የመስፍንን የደብዳቤ ሃሳብ በማረጋገጥ ። « ምን እንደነካው አላውቅም ። አንቺን ካየ ጀምሮ ወሬው ሁሉ ሕሊና ሕሊና ነው ። በጣም ያሳዝናል ። ቀደም ብዬ ፅፌለት ነበር ። ስለአንቺ ለማስረዳት ሞክርኩ ። ግን የሰማኝ አልመሰለኝም ። ሕሊና ለዚህ አሳፋሪ ድርጊት በጣም ይቅርታ አድርጊልኝ ። እኔ ነኝ በገዛ እጄ አስተዋውቄ እዚህ ውስጥ የከተትኩሽ ። » አለ አበራ ወደ መሬት አቀርቅሮ በወንድሙ ድርጊት እየተፀፀተ ።

« ምን ማለትህ ነው አበራ? የወንድምህ ድርጊት እኮ ትክክለኛ ነው ። ልታፍርበት ወይንም ልትፀፀትበት የሚገባ አይደለም ። ተዋወቅኝ ፤ የበለጠ ለመተዋወቅ ደግሞ ፈለገ ። በግድ ይሁን ሁኚ ብሎ አላስገደደኝም ። » አለች ሕሊና ወደ አበራ በቀዘቀዘ ስሜት እየተመለከተች ።

« እውነትሽን ነው ? » አበራ የሰማውን ባለማመን ዓይኖቹን ፈጠጥ አድርጐ በድንጋጤ « እኔ ምን ትለኛለች ብዬ ያለውን ሁሉ ደብቄ ነበር ። በአንቺና በሀሰን መሀከል ያለውን ግንኙነት የሚያደፈርስ መስሎኝ ነው እስከሁን መስፍን ያለውን መግለፅ ያልቻልኩት ። ሌላው . . . » የተናገረውን አልጨረሰም ።

ሕሊና ማለት የፈለገውን እንዲጨርስ « ምን አሳፈረህ ? እኔ እኮ ልጅ አይደለሁም። ይልቅስ ንገረኝና ልስማው » በማለት ገፋፋችው ።

« ሕሊና መስፍንን አታውቂውም ። አንቺ በጣም ጥሩ ሰው ነሽ ። በማይሆን ነገር እንዳያስቀይምሽ ለአንቺ በማሰብ ነው የፃፈውን ያላሳየሁሽ » በማለት ኮስተር ብሎ ነገራት ።

« ወንድምህ ለእኔ መጥፎ እንደማይመኝ አውቃለሁ ። ደግሞስ ደብዳቤ መፃፃፍ ምንም ማለት አይደለም ። መስፍን ከፃፋቸው ሁለት ደብዳቤዎች እንደተረዳሁት በሁለታችን መሀከል የምንፈጥረው ግንኙነት በመፃፃፍ ላይ የተመሠረተ ጓደኝነት ነው ። አንተ የምታውቀው ሌላ ነገር ካለ ንገረኝ » አለች ሕሊና ።

አበራ ጥቂት አመንትቶ « የመስፍን ጥያቄ ከዚያ በላይ ሳይሆን ይቀራል ብለሽ ነው ? » ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰላት ።

« አበራ ! አበራ ! » አለች ሕሊና እራሷን በአሉታ እየነቀነቀች ። « ምንድነው ምስጢሩ ? ለምንድነው ወንድምህን የማታምነው ? ለእኔ ለመንገር ያልፈለግከው ነገር አለ ። በእውነት ጓደኛሞች ከሆንን ለምን ደፍረህ አትነግረኝም ? » አለች በቁጣ ወደ አበራ አተኩራ ።

« ሕሊና እንዲህ እንደምትይው ቀላል አይደለም ። መስፍን በጣም ይወድሻል ። እኔና መስፍን በልጅነታችን ነው የተለያየነው ። አስተዳደጋችን የሠማይና የመሬት ያህል የተራራቀ ነው ። መስፍን በሁለንተናው ኢትዮጵያዊ አይደለም ። አስተሳሰቡ ፣ ባህሉና የቀን ተቀን ህይወቱ ከእኛ በጣም የተለየ ነው ። ማለቴ ከእኔና ከአንቺ ማለቴ ነው ። ባለፈው እዚህ በነበረበት ወቅት ሁኔታውን እንዳየሁት መስፍንን እንደማላውቀው ለመረዳት ችያለሁ ። መስፍንን ጠለቅ አርገሽ ብታውቂው በደብዳቤ ከተረዳሽው እሱነቱ እጅግ በጣም የተለየ ባህሪ ነው ያለው ። አንቺ እንግዲህ የምታውቂው መስፍን የደብዳቤውን ነው ። ለማንኛውም ነገርኩሽ ፤ መስፍን ለአንቺ ያለው ስሜት ከደብዳቤው በላይ ነው ። ለሁሉም ባለቤቷ አንቺው ነሽ አስቢበት » ንግግሩን ጨርሶ ሕሊናን አስተዋለ።።

ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተለያየ ሰው ድርጊቷን አጥብቆ ፈተሸ።። ፊት ለፊት የተቀመጠችው ውብ ሴት ከሚያውቀው የማያውቀው ፀባይዋ እንደሚበልጥ ተረዳ ።

የተማረውን የሥነ ባህርይ ትምህርት ለመጠቀም ሞከረ ። ለምን ይህችን ውብ ቀንጆ መሰል ጓደኛ አጣች ። . . . ምን ጎደላት ? ከሀሰን ጋር ያላቸው ግንኙነት ለምን ወጣ ገባ ሆነ ? ጥያቄውን ለሕሊና ለማቅረብ ቃጣ ። የተጠራሁት ምክር ለመለገስ ። አሁን ዘልዬ የራሴን ጥያቄ ጣልቃ ማስገባት ምን ፋይዳ ይፈጥራል ? ያሰበውን ከመናገር ተቆጠበ ። « ሕሊና በደብዳቤው ላይ የተጠቀሰው ስጦታ አልደረሰኝም ። ሲደርሰኝ አመጣልሻለሁ » አለና ከመቀመጫው ተነስቶ ለመሄድ ተዘጋጀ ።

« እግዚአብሄር ይስጥልኝ ። አበራ መቼም ምክርህ በጣም ነው የረዳኝ ። ከአንተ የበለጠ የምቀርበው ወንድም ስለሌለኝ ነው ያስቸገርኩህ ። ቅር እንደማይልህ እርግጠኛ ነኝ ። » አለች ለመሸኘት ወደ በሩ እያመራች ።

« ከአንድ ሰው ይልቅ ሁለት ሆነው ያሰቡትና ያቀዱት ይሻላል ። የወንዱን ባህርይ ወንዱ የሴትን ደግሞ ሴቷ ናቸው የበለጠ ጠልቀው ሊያዩና እንቆቅልሹን ሊፈቱ የሚችሉት ። ምክር መጠየቅ ብልህነት ነው ። ምን ጊዜም ከአንቺው ጋር ነኝ ። ሲያስፈልግሽ ከመጠየቅ ወደ ኋላ አትበይ ። » በማለት ተሰናብቷት ወደ ጨለማው ተሰወረ ።

ሕሊና ስለ መስፍን ያላትን ሀሳብ ለማሰባሰብ ከፍተኛ ጥረት አደረገች ። ሆኖም የሀሰን ግንኙነት ጣልቃ እየገባ ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት እንድታወዳድር ገፋፋት ። ደጋግማ የምታስበው የሀሰን ከእርሷ መሸሽና የመስፍን የመቅረብን ፍላጎት ነበር ። ሀሰን አልፎ አልፎ አሰላ ብቅ ቢልም ለአንድ ቀን አዳር ወይንም ውሎውን በደርሶ መልስ ተወስኖ ንግግራቸው ደግሞ ከመግባባት ይልቅ ልዩነታቸው ላይ ያተኮረ ሆነ ።

ይህ ለዛ ያጣ ግንኙነት መቋረጥ እንዳለበት አመነች ። ከሀሰን ጋር የምታደርገውን ማናቸውንም ውይይት ያሰበችውን በቀላሉ ግብ ለማድረስ የሚያስችል መድረክ ለማድረግ ከወሰነች ከረመች ። ሀሰንን ለማየት ያላትን ፍላጎት እስከመጨረሻው መግደል ግን አልቻለችም።። « ገድ የለም ጊዜ ያመጣውን ጊዜ ይሽረዋል ። » በማለት ስሜቷን ማስታመሙን ቀጠለችበት ።

ሕሊና ለሀሰን ግንኙነት መቀዝቀዝ ትርጉም መስጠትና ለብዙ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የቻለችው ለሁለተኛ ጊዜ ሊጎበኟት ከመጡት ወ/ሮ በላይነሽ ጋር በተወያየችበት ጊዜ ነበር ። ወ/ሮ በላይነሽ ቡና አፍልተው ፣ ቂጣውን ገዝግዘው ዕጣንና ፣ ሠንደል አጭሰው የሕሊናን መምጣት ጠበቁ ። ምንም እንኳን ሕሊና ቡና ጠጪ ባትሆንም ትሉ ወ/ሮ በላይነሽን በማጀብ ከአቦል እስከ በረካ መሳተፍ ልማድ አደረገች ። ከቡናውም ይልቅ የወ/ሮ በላይነሽ ቁምነገር አዘል ወሬዎች አዝናኝና ትምህርት አዘል እንደሆኑ ሕሊና

እምነቷ ነው ። ከሥራ እንደገባች « እማማ በላይነሽ የዛሬው ደግሞ ለብቻ ነው ። ቤቱ ሁሉ እንዴት ደስ ደስ ይላል ? » አለች የሚማርከውን የዕጣን ሽታ በአፍንጫዋ እየሳበች ።

« ታዲያ ጎረቤቶቹ ተጠሩ ? » ብላ ጠየቀች ።

« የመባቻን ቡና ከሰው ጋር አይካፈሉም ። የቤተሰብ ቡና ነው » አሏት ። ሕሊና የያዘችውን አስቀምጣ ፣ የሥራ ልብሷን ቀይራ ፣ ዱካዋን አቅርባ ፣ ወ/ሮ በላይነሽ ፊት ለፊት ተቀመጠች ። ቡናው የሆነ ነገር እንዳለበት ከወ/ሮ በላይነሽ ሁኔታ ተረዳች ።

« እንግዲህ ልጄ ዕድሜዬ እየገፋ ጉልበቴ እየሸሸ ነው ። ምኞቴ የአንቺን ሠርግ ደግሼ ልጅሽን አቅፌ ለማየት ነበረ ። ሆኖም አንቺ ትዳር ያሰብሽ አትመስይም » አሉ ሕሊናን በትኩረት እያዩ ።

« ለመሆኑ ከሀሰን ጋር እንዴት ናችሁ ? » ብለው ጠየቋት።

« አይ እማማ በላይነሽ ! » አለች ፈገግ ብላ መሬት መሬት እያየች ። « ባሉ መች ተገኘ ብለው ነው ? የሀሰንን ነገር ተውት ። ተወርቶ አያልቅም ። » አለች ሁለት እጆቿን አጣምራ በመንጠራራት ዓይነት ።

« ልጄ ከአንቺ እስኪመጣ ነበር የጠበኩት ። ያለ አቻ ጋብቻ» አሉ ዝግ ብለው ለራሳቸው በመናገር ። የእርሱ ሃይማኖት እኮ ከሁለት ሚስት በላይ ማግባት ይፈቅድለታል ። ለጥቂት ጊዜ አሰብ አድርገው « አባትሽ ጥሩ ክርስቲያን ነበር ። የእግዚአብሄርን ሥም ከአፉ ነጥሎ አያውቅም » አሉ ዓይናቸውን ከሕሊና ላይ አንስተው ወደመሬት በመመልከት በትዝታ ወደኋላ ተጉዘው « ሀሰን ለመሆኑ ሌላ ሴት እንዳለው ነግሮሻል ? » ሲሉ ጥያቄአቸውን በማመንታት ሰነዘሩ ።

የሕሊና ዓይኖች ፈጠጡ ። የወ/ሮ በላይነሽ ጥያቄ ከእንቅልፏ እንዳባነናት ዓይነት « ምን አሉ እማማ ? » ብላ ጮኸች ።

« ምነው እንግዳ ሆንሽ ? » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ በመጠራጠር።

« አውርቶልሽ አያውቅም ማለት ነው ? ማን ነበር ያሉኝ እቴ? » ፊታቸውን ዞር ዞር አድርገው ለማስታወስ ሞከሩ ።

« እማማ ማን ነገረዎት ? » ስትል በኃይል ተነፈሰች ።

« ኧረግ ኧረግ ሁሉ የሚያወራውን ? እኔ እኮ እንዲህ ሞኝ አትመስይኝም ። ግና ምን ያደርጋል ጆሮ ለባለቤቱ ባዕድ ነው ይባል የለ » አሉ ።

ለሕሊና የወ/ሮ በላይነሽ አባባል በሁለንተናው ብዙ እንቆቅልሾችን የሚፈታ በመሆኑ ብዙ ጥያቄ አልጠየቀችም ። በውስጧ ትርጉም ልትሰጠው የማትችለው አንዳች ስሜት ተሰማት ። ከተቀመጠችበት በመነሳት ተንደርድራ መኝታ ቤቷ ገብታ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

« እኔ አፈር ልብላ ! አፈር ልብላ ! ምን አደረኩ ? » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ በድርጊታቸው ተፀፅተው ። ወደ ሕሊና መኝታ ቤት ፈጠን ብለው ገቡ ። ወ/ሮ በላይነሽ ቀደም ሲል የተናገሩትን በመፃረር ሕሊናን ለማጽናናት ሞከሩ ። « ሲሉ ሰማሁ እንጂ መች አረጋገጥኩ? አሉባልታ ነው ። በቅናት ሰዎች የሚያስወሩት ሊሆን ይችላል » በማለት ዘላበዱ ። ነገር ግን ሕሊናን ከማልቀስ ሊያግዷት አልቻሉም።

« ቀድሞውኑ አውቄአለሁ እርሶም የጠረጠርኩትን ነው ያረጋገጡልኝ » በማለት አምርራ አዘነች ።

« ኧረ ጎረቤት ምን ይላል ? በይ ዝም በይ » ዓይናቸውን በነጠላቸው ጫፍ እየጠራረጉ በማፅናናት መልክ የሕሊናን ፀጉር አሻሹ። የወ/ሮ በላይነሽ ቁልፍ ቃል የሕሊናን ለቅሶ ለጊዜው ገታው። በቤቱ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ። « በይ ተነሽ ፊትሽን ታጠቢ ። ይልቁንስ ነቃ በይና ቡናችንን እንጠጣ ። በመባቻ ያለቀሰ እስከ

ባለእግዝአብሄር እይፈታም ይባላል ፤ ይቅር ያብልሽ ። » እሱ አመስካከታቸውን ወደ ሰማይ ፤ እጆቻቸውን ወደ ፊት ለፊት አጣፍተው እምላክን በመለመን መልክ ።

ሒሊና ከተጋደመችበት ከወ/ሮ በላይነሽ ጭን ላይ በረጅሙ ተንፍሳ ተነሳች ። በእጆቿ ዓይኖቿን ጠራርጋ ወ/ሮ በላይነሽን በመተከዝ መልክ አትኩራ ተመለከተች ። ፊቷን ታጥባ ነቃ ነቃ በማለት ዱካዋ ላይ ተቀምጣ ቡና መጠጣት ጀመረች ።

ወ/ሮ በላይነሽ አቦል ቡና ከመቀዳቱ በፊት የቀረበውን የእንጀራ ቡና ቁርስ በፀሎት አስቀድመው ቆረሱ ። « በል አስቲ አንተ ታውቃለህ ። ለምትለውና ለምትሰራው መቼም ምክንያት አለህ ። ከአንተ የሚሰወር ምን አለ ? » በማለት በሚቀዱት ቡና ጣልቃ ወደ ሠማይ እያንጋጠጡ እምላክን ተማፀኑ ።

« መቼም እማማ በላይነሽ የእግዜር መላክተኞች በምድር ላይ አሉ ቢባል እርስዎ አንዷ ነዎት እል ነበር ። በዛሬው ቀን የነገሩኝ መልዕክት ከምንጊዜውም የበለጠ ነፍስ እድን ነው ። በወቅቱ የመጣ መልዕክት ነው እግዚአብሄር ይስጥልኝ ። ሌላ ምን እላለሁ ። » አለች ሒሊና ወ/ሮ በላይነሽን በትኩረት እያየች ።

« ምን አደረግኩ ? እሳዘንኩሽ ልጄን በማያገባኝና በማላውቀው ነገር ገብቼ ይቅር በይኝ » አሉና ቡናቸውን ፉት ብለው አጣጣሙ።

« ለዓመታት ሲያስጨንቀኝ የነበረውን በሽታ ነው ምህረቱን የሰጡኝ ። ለዓመታት ትልቅ እንቆቅልሽ ሆኖብኝ ብመከር ፣ ብዘክር፣ መልስ ላገኝለት ያልቻልኩትን ጥያቄ እርስዎ ከመቅፅበት ፈቱት ።

እማማ የዛሬው የእኔ ለቅሶ በብዛት የደስታ በጥቂቱ የሀዘን ስሜት ነው ። የተደሰትኩት ከገባሁበት አዘቅት እራሴን ነፃ ለማድረግ መቻሌ ነው ። ያመንኩትና የወደድኩት ሰው የማይታመን ፣ የማይወደድ መሆኑን ሳውቅ ምን ያህል ሞኝና ተላላ እንደነበርኩ ተገነዘብኩ ። አብሬው ያሳለፍኳቸውን ጊዜያቶች ስገመግም አዘንኩ ።

በህይወቴ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ ትምህርት ነው የምቆጥረው ። » በማለት ጎንበስ ብላ የወ/ሮ በላይነሽን ሁለት እጆች በእጆቿ ያዘች ።

« እማማ ! ነፍሴ ስትጨነቅ ምህረት ያመጡላት እርስዎ ነዎት ። ውለታዎን ምን ጊዜም ልከፍለው አልችልም ። እግዚአብሄር ይክፈልዎ ። » በማለት ጉንጫቸውን አገላብጣ ሳመቻቸው ።

« ልጄ ! ምን አደረኩልሽ ? አንቺ ነሽ እንጂ የተባረክሽ ከልብስ ልብስ አልቀረ ፣ በየጊዜው ገንዘብ ሳይቀር ምንም ሳይጎድልብኝ በአንቺ ሥም እኮ ነው የምኖረው » በማለት ወ/ሮ በላይነሽ በተራቸው ጉንጮቿን አገላብጠው ሳሙ ።

ምዕራፍ ስድስት

በሕሊና ህይወት የተከሰተው ታላቁ ማዕበል ካለፈ ሳምንታት ተቆጠሩ ። ለሀሰን የግንኙነት መደምደሚያ ለመስፍን ደግሞ ለደብዳቤው መልስ ፃፈች ። ለሀሰን በፃፈችው ደብዳቤ ምንም ማብራሪያ አልጨመረችም ። ቀዘቀዝ ባለ መልኩ ሀሰን እርሷን ማየት፣ ስልክ መደወል ወይም ደብዳቤ መፃፍ እንዲያቆም ጠየቀች ። በት/ቤት በኩል ሁለት ጊዜ ስልክ ቢደውልም ማንነቱን ካረጋገጠች በኃላ ለማነጋገር ፈቃደኛ እንዳልሆነች ገልፃ ስልኩ ተዘጋ ።

ለመስፍን በአጠቃላይ መልኩ ጋባዥ የሆነ ደብዳቤ ስትፅፍ ፤ በመልስ የደረሳት ደብዳቤ ግን ዝርዝር የያዘ ፣ ስለመስፍን ፍላጎት የሚያስረዳ ሆኖ ጥያቄ አዘል ነበር ። የሕሊናን ትኩረት በከፍተኛ ደረጃ የሳበው ግን በመስፍን ደብዳቤ ላይ የተሰነዘሩት በሁለት ዐረፍተ ነገሮች የቀረበው መልዕክት ነበር ።

« ሕሊና ለትምህርት በጣም ጉጉት እንዳለሽ ባለፈው ጊዜ ስንወያይ ገልፀሽልኛል ። ይኸውልሽ ቁምነገር አልረሳም ። እዚህ እኛ ጋ አንድ ኮሌጅ አለ ብዙ የውጪ ሀገር ተማሪዎችን እየተቀበለ ያስተናግዳል ። የምትፈልጊ ከሆነ የመግቢያ ማመልከቻ ቅፅ በሚቀጥለው ጊዜ እልክልሻለሁ ። ሞልተሽ ላኪና እኔ እዚህ እከታተልልሻለሁ ። »

ሕሊና በዚህ አጭር ጊዜ ትውውቅ መስፍን ይህን ዓይነት ውለታ ለእርሷ ለማድረግ የፈለገበትን ምክንያት ብትጠራጠርም ከነበረችበት ሁኔታ በአሸናፊነት ለመወጣትና የትምህርት ጥሟን ለማርካት የሚያስችል ብቸኛ ዕድል በመሆኑ ፤ ያለአንዳች ቅሬታ ግብዣውን ተቀበለች ። ለደብዳቤውም መልስ ሳይውል ሳያድር ፃፈች፡፡ ሕሊና በምታደርገው ሁሉ ደስተኛ ሆነች ። አካባቢዋ አብረዋት የሚውሉ የሥራና የግል ጓደኞቿ የሕሊናን የባህሪ ለውጥ

በቀላሉ ተገነዘቡ ። ለለውጡ ምክንያት ምን እንደሆነ የተመራመሩት ግን ጥቂቶች ብቻ ነበሩ ። የቅርብ ጓደኛዋ ከበቡሽ በሕሊና ለውጥ ተደሰተች ።

« ሕሊና እስካሁን የጋን መብራት ሆኖ የቆየው ውበትሽና የጨዋታ ስልትሽ ሊወጣ እንዴት እንዳደመቀሽ አታውቂም ? ምነው እንቺን ባደረገኝ ። ያየሽ ሁሉ ይመኝሻል » በማለት ከበቡሽ ሕሊናን አሞገሰቻት ።

አበራ የወንድሙና የሕሊና ግንኙነት ደረጃው ከፍ ባለ ቁጥር እየከፋው መጣ ። እልፎ አልፎም ይህን ስሜቱን ግልፅ በማድረግ ሕሊናን « እስቲ አትቸኩይ ! ቀስ በይ ! » በማለት የሚሰጠው ምክር ከማበረታታት የተቆጠበና የቀዘቀዘ ሆነ ። ከሁሉም ለሕሊና ዕንቅቅልሽ የሆነባት ግን በጣም የሚቀርቧት ሁለቱ የመስፍን ታናናሽ እህቶቹ ናቸው ። ወዳጅነታቸው የደራ ከመሆኑም ባሻገር በዕድሜ እኩያሞች በመሆናቸው ከሥራ ውጪ በሚደረገው ማህበራዊ ተሳትፎ በየጊዜው ስለሚያገናኛቸው ቅርርባቸው የሰፋ ነበር ። ከወንድማቸው ጋር ያላት ግንኙነት እየጠነከረ ሊመጣ እህትማማቾቹ ሕሊናን እየራቁና ብሎም በግልፅ እየተፃረሩ መጡ ።

ሕሊና ለአድራጎታቸው ካላት ልምድና ከምታገኘው ምክር እንፃር ልማዳዊ የእህትነት ስሜት ነው በማለት ለማቀዝቀዝ ሞከረች፡፡ ሆኖም ይህ እሉታዊ ስሜት በጥቂት የቤተሰቡ አባላት ሳይወሰን ጠቅላላውን ቤተሰብ በመበከሉ ሕሊና በዝምታ ልታልፈው አልቻለችም ።

« ከበቡሽ የአበራ ቤተሰቦች ለምንድነው እንዲህ የጠሉኝ » በማለት ሕሊና በአንድ አጋጣሚ ከበቡሽን ጠየቀቻት ።

« እባክሽ ተያቸው እነርሱ ዓመላቸው ናቸው ። አንቺን ብቻ አይምሰልሽ እኔንም ያንገበግቡኛል ። እንዳላወቀ መዝጋት ነው » አለች ከበቡሽ ለጉዳዩ ብዙም ክብደት ባለመስጠት ።

« አበራ-ንም ጭምር እኮ ነው የምልሽ እሱን ደግሞ ምን እንዳደረኩት አልገባኝም ? » አለቻት ::

« አይገባሽም እንዴ ? ጉዳዩ አንቺ ከመስፍን ጋር በመፃፃፍሽ የመላውን ቤተሰብ ዕቅድ ነው ያበላሸሽው :: » አለች ከበቡሽ ::

« እንዴ ! ምን ማለትሽ ነው የቤተሰቡን ዕቅድ አበላሸሽ ስትይ? እኔ ምን አድርጌ አበላሻለሁ ? »

« ሕሊና ምኝ ነሽ ልበል ? መስፍን ለአንቺ ዝም ብሎ የሚፅፍ ይመስልሻል ? እስቲ ንገሪኝ በሣምንት አንድ ጊዜ ደብዳቤ ፤ በወር አንድ ጊዜ ስጦታ የሚልክልሽ ? ንገሪኝ ! እስቲ አንቺ እንደሚገባሽ የመፃፃፍ በሽታ አለበት ብለሽ ታምኛለሽ ? ስለወደደሽ ነው ! ከአንቺ ጋር ለመኖር ስለሚያስብ ነው :: ሌላ ምንም ምክንያት የለውም :: ሕሊና ይግባሽ » አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ ::

« እሺ ገባኝ ልበል :: ታዲያ ወንድማቸው እኔን ቢወድ እነርሱ ምናቸው ተነካ ? አነስኩብት ? በዛሁበት ? እኔ እኮ ግራ ገባኝ» አለች እራሷን እያወዛወዘች ::

« አንቺን ወደደ ማለት ሁለንተናው ወደ አንቺ ዞረ ማለት ነው :: ቀድሞ ለእህቶቹ የሚጽፈው ደብዳቤና ስጦታ አሁን ለአንቺ ሆነ :: ከሁሉም ከባዱ ግን አማከለች ወደ አሜሪካ የሚቀጥለው ዓመት ለመሄድ ተዘጋጅታ ነበር :: ይወስዳት የነበረ ወንድሟ መስፍን፤ አሁን የሚወስደው ማንን እንደሆነ አይታወቅም :: ቤተሰቡ የሚጠረጥረው አንቺን ነው :: » ከበቡሽ ወደ ሕሊና እየቸና ቆመች ::

« ሕሊና ስሚ መቼም አንቺ የዋህ ሴት ነሽ :: ሁሉም ወዳጅሽ ነው :: ያለውን ሁኔታ ስነግርሽ እንዳትደነግጪ በጣም ተጠንቀቂ :: ከመስፍን ቤተሰቦች ራቅ በይ :: ሊጎዱሽ ይችላሉ » በማለት ጥቂት አሰበች :: « አበራ ጓደኛዬ ነው እወደዋለሁ :: እርሱንም ቢሆን አንድ የተረጋገጠ ነገር እስከሚኖር ድረስ ተጠንቀቂው :: » በማለት የሕሊናን እጅ በእጆቿ በደግ አመስካከት

ዳሰሰች :: ሕሊና በፀጥታ ከማዳመጥ በስተቀር መልስ ለመስጠት አልቻኮለችም :: የሰማችውን ማብሰልሰል መረጠች ::

« ይገርማል አንቺ የምትይው ሁሉ አይቀርም ከአንዱ ወጣሁ ስል ደግሞ ወደዚህ ተሸጋገርኩ :: ከእሳት ወደ ረመጥ ይሉሻል ይሄ ነው :: ህሰንን ተገላገልኩ ስል የመስፍን ዘመዶች ደግሞ ሰፈሩብኝ :: እኔስ ምን ይሻለኛል :: ዕድሌ ይሆን ? » በማለት ራሷን ጠየቀች ::

« ዕድልሽማ ቆንጆ ዕድል ነው :: ሰዎች ግን የአንቺን ዕድል ለመቀማት ይራሯጣሉ :: እግዚአብሄር በጣም ይወድሻል ልታምኚበትና ልትፀልይ ይገባሻል » አለች ከበቡሽ የተማረረችውን ሕሊናን በማፅናናት ::

« ተጠንቀቂ ስልሽ በጣም አትቅረቢያቸው ፤ ከቀረብሽ ደግሞ ቅርበትሽ በጥንቃቄ ይሁን ማለቴ ነው :: አይዞሽ እንግዲህ በመንግስት ህገር ምን ማድረግ ይችላሉ :: መስፍን መጣብሽ እንጂ አንቺ የሙጥኝ ብለሽ አልሄድሽበት ምን አስጨነቀሽ አለቻት :: »

« የእርሱ መፃፍ ቢቀርብኝስ ? የእርሱ ስጦታ መጥቶ የትኛ ውን ግንብ ሊገነባልኝ ነው ? ቀርቶስ የትኛውን ግንብ እንዳያፈርስብኝ? ዛሬውኑ አቋርጥ ፤ ገንዘብህን ለእኔ ከምታባክነው ዘመዶችህን እርዳበት ብዬ እፅፍለታለሁ » አለች ሕሊና የተናገረችውን ራሷን ለማሳመን በመሞከር ::

« እኔ አንቺን ብሆን ያልሽውን አላደርግም :: እንደዚያ ብትይ ነገሩን ማባባስ ነው :: መስፍን ይሄን ሲሰማ ዘመዶቹን ከእነጭራሹ ነው የሚዘጋው :: ይልቁንስ የአንቺ መፃፍ አልፎ አልፎ ጣል ጣል የሚያደርገውን ደብዳቤ እንዲቀጥል ይረዳል :: እነርሱም ሰጊዜው ነው እንደዚህ የሚሆኑት :: ቁርጡን ሲያውቁ ይለይላቸዋል :: ይልቁንስ ከአንቺ ጋር መስማማቱ ሳያዋጣቸው ይቀራል ብለሽ ነው::» በማለት ከበቡሽ ጥቂት እንደተራመዱ ቆም አለች ::

« መጀመሪያ ከአበራ ጋር ስሆን ዘመዶቹ ያላወሩት ነገር አልነበረም ። ቤት ተከራይቶ ከእህቶቹ ቤት ሲወጣ እዬዬ ብለው አለቀሱ ። በእናትና በአባታቸው አፅም አስገዘቱት ። እኔ ደግሞ ድርቅ አልኩ ። የራስህ ቤት ከሌለህ ለው ቤት እየመጣሁ አልውልም፣ አላርፍም ፣ ገረድ አይደለሁም ግልምጫና ስድብ የሚደርስብኝ አልኩት ። እርግጥ ለእርሱ ከባድ ምርጫ ነበር ፣ አውቃለሁ ። ለእኔም እንደዚሁ ። ያኔ ይህንን እርምጃ ባልወሰድ እስካሁን አብረን አንቆይም ነበር ። ቤት ተከራይቶ ከወጣ ወዲህ የጥል መነሻው ሁሉ ተወገደ ። የምንከራከርበት ጉዳይ የለም ። በእርግጥ የአበራና የመስፍን ጉዳይ እንኳ የተለያየ ነው ። » ብላ ዝም አለች ከዚህ በላይ ለመቀጠል አልፈለገችም ነበር ።

« እንዴት ነው የተለየ ነው ስትይ ? » አለቻት ሕሊና ።

« አበራን እህቶቹ በእውነት ይወዱታል ። አብረው በመኖራቸው ፣ ክፉውንና ደጉን አብረው በማሳለፋቸው እንዲለያቸው አይፈልጉም ። አበራ ለቤተሰቡ የአባትን ያህል መንፈሳዊ ድጋፍ የሚሰጥ አውራ ነው ። በእርግጥ መስፍን ወንድማቸው ቢሆንም ያበራን ያህል ጣዕሙን አያውቁትም ። ለችግራቸው ደራሽ ነው ። የቤተሰቡን የገንዘብ ፍላጎት ከወንድሙ ከሙሉጌታ ጋር በመሆን ለማሟላት ጥረዋል ። ሁሉቱም ወንድሞቻቸው ናቸው ፣ እንዳየደረጃቸውና እንደየቅርበታቸው ይወዷቸዋል ። » አለች ከበቡሽ ንግግሯን በመደምደም ። በመሀከላቸው ፀጥታ ሰፈነ ። በየቤታቸው እስከሚደርሱ ሁለቱም በፍጥነት ተራመዱ ። ሕሊና ቤቷ ገባች ። እረፍ ብላ ከበቡሽ ስለነገረቻት አባባል ጠልቃ አሰበች ።

« አበራ እንዴት እንደዚህ ያስባል ? የመሰለኝና የገመትኩት ለእኔ እንደሚቀረቀርልኝ ነበር ። ምን ነካው ? የሌሎቹ ሁሉ ማደም ከበቡሽ እንዳለችው ከሆነ ይገባኛል ። ሌላ ምክንያት እንዳይኖራቸው

እንጂ ። አይ አበራ ! . . . እንዴት ያናድዳል ? » አለችና መልሳ ጥቂት አሰብ አደረገች ። የሆነ ሀሳብ ብልጭ አለባት ።

« ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው ። ለምን ራሴ አልጠይቀውም ። እንዲያውም አባባሉ ለሚቀጥለው እርምጃ ያዘጋጀኛል ። » በማለት አበራን ጠርታ ለማነጋገር ወሰነች ። ከትምህርት ቤት መልስ ከሥራ በኋላ ተቀጣጥረው ሕሊና ቤቷ ቁጭ ብላ ስትጠብቅ የመጣው አበራ አልነበረም ። በምትኩ ከበቡሽን ነበር የላከው ። ከበቡሽ እንኳክታ ስትገባ ሕሊና ደነገጠች ።

« ምን ሆነ አበራ ? » ብላ ከበቡሽን ጠየቀቻት ። ከበቡሽ ወዲያውኑ ለጥያቄዋ መልስ አልሰጠችም ። ተመቻችታ ወንበር ላይ ተቀመጠች ።

« ምንም አልሆነም ። ሆኖም መምጣት አልቻለም ። ስለዚህ እኔን ላከኝ ። ይቅርታ አስቸኳይ ነገር አጋጥሞኝ እህቴ ጋ ሄጃለሁ ። የዛሬውን ቀጠሮ ወደ ሌላ ቀን እንድታስተላልፊው ብሎሻል » በማለት መልዕክቱን ለሕሊና ከነገረቻት በኋላ « አበራ ምንም ማድረግ አይችልም ። አንቺ ቤት ሲወጣና ሲገባ ቢያዩት እህቶቹ ጥምድ አድርገው ነው የሚይዙት ። ዛሬ ልነግርሽ አልችልም ። ምን ያህል እንደተጨነቀ ። አበራ ክፉ ነገር ባያስብም በአንቺ ምክንያት ከእህቶቹ ጋር መቀያየም አይፈልግም ። » በማለት የራሷን አስተያየት ከመልዕክቱ በስተጀርባ አከለችበት ።

« ከበቡሽ በጣም አመሰግንሻለሁ ። በመምጣትሽ ቅርም አይለኝ ። ለማንኛውም ቢሆን የቦታ ምርጫ ነው እንጂ ትምህርት ቤትም ቢሆን ላነጋግረው እችላለሁ ። ምርጫ ከሌለኝ የማደርገው በአለችኝ የምሳ ሠዓት ብቻኛ ቦታ ፈልጎ ማነጋገር ነው ። እስከመቼ ድረስ ሆድና ጀርባ እንሆናለን ። » አለች ሕሊና ቁጡ ስሜቷን እየገለፀች ።

ከበቡሽ ከፊል የማዘን ፣ ከፊል መገረም በተሞላው አመለካከት ወደ ሕሊና ተመለከተች ። « ሕሊና ትክክል ነው ብለሽ የምታስቢውን እርምጃ ውሰጂ ። እኔ መቼም በጓደኝነቴ ሙሉ ድጋፌን እሰጥሻለሁ ። »

አበራ ትምህርት ቤት የደረሰው ዘግይቶ ነበር ። ሕሊና ወደ ክፍል ለመግባት አልቸኮለችም ። ጠበቀችው ። « እንደምን አደርሽ ሕሊና ? ምነው በደህና ነው እዚህ የቆምሽው ? »

« ደህና ነኝ አበራ ። ለማኝ ዛሬ በምሳ ሰዓት ብቻህን እፈልግሃለሁ ። ካልሆነ ደግሞ አሁን የምትችል ከሆነ ላነጋግርህ ። »

« ምነው በጤና ? ምን ተፈጠረ ? » አለ ሕሊናን በቅርበትና በትኩረት ሁኔታዋን ለማንበብ ፊቷን እየተመለከተ ።

« ብዙ የረበሸኝ ነገር ስለአለ ያለአንተ ብቻዬን የምፈታው ስለአልሆነ . . . » ሕሊና ያሰበችውን አልጨረሰችም ። ፊቷን ከአበራ አዞረች ። ዐርሳዋን ከፍቷ መሀረብ አወጣች ።

« ብቻ እፈልግሃለሁ ለማንኛውም ! . . . . » መቀጠል አልቻለችም ። ፀጥግነት ወደ ክፍሏ መራመድ ጀመረች ። « ቆይ እንጂ ሕሊና ምነው ምን ሆነሻል ? » አበራ በመደናገጥ የሕሊናን እጅ ይዞ ለማቆም ሞከረ ።

« ተወኝ አበራ ፤ ተወኝ ! ተወኝ ! በቃ ! በኋላ በምሳ ሰዓት እንነጋገራለን ፤ አሁን አልቻልኩም ። » ብላ መንገዷን ቀጠለች ። አበራ ባለበት ፊዞ ሕሊናን በዓይኑ ተከተላት ።

ምሳ ለዓት ጎን ለጎን ተቀምጠው በመነጋገር ላይ እንዳሉ ምሳ አልበላም ያለችውን ሕሊናን በማባበል ዓይነት « ሕሊና ምነው እንደዚህ ትሆኚያለሽ ? » ሲል ጠየቃት ።

« ምንም መብላት አላሰኘኝም ። ይልቁንስ ጊዜ ሳናጠፋ ወደ ቁምነገሩ ልግባ ። አበራ የአንተን አላውቅም እኔ መቼም የማይህ እንደ ወንድሜ ነው ። ለዚህ ነው ቀደም ሲል የግሌን ምስጢር

ገልጬ ያዋየሁህ ፤ ምክርህን እንድትሰጠኝ የጠየቅኩህም ፤ ያስቸገርኩህም ። አሁን ግን ባላወቅሁት ምክንያት እየራቅከኝና እየዘጋኸኝ መጣህ ። በተለይም ከመስፍን ጋር በደብዳቤ ከተቀራረብን ወዲህ ከእነጭራሹ እኔን ማነጋገር እንኳ አስጠላህ ። አንተ ብቻ አይደለህም ። ድሮ ከአጠገቤ የማይጠፉት እህቶችህ እነ አማከለች እንኳ ሲያዩኝ መንገድ ቀይረው ነው የሚሄዱት ። አሁን የምጠይቅህ ብዙ ነገር አይደለም ጥፋቴ ምንድነው ? »

« ምንም ጥፋት የለሽም ። እኔም ይኼ ነው ብዬ የምነግርሽ ነገር የለም ። »

« ምንም ነገር የለም ስትል . . . ልነግርሽ አልፈልግም ማለትህ ነው ። ወይስ የምትለው እውነት . . . »

« አየሽ ሕሊና » አበራ የሚቀጥለውን ለማለት ጥቂት አሰበ።

« ሕሊና - ሕሊና . . . » አበራ ራሱን በሐዘኔታ ነቀነቀ ።

« ከዬት ልጀምር ! . . . በርግጥ ከአንቺ ጋር የማደርገውን ቀረቤታ ቀንሻለሁ ።በአንቺና በመስፍን መሀከል የሚካሄደው ግንኙነት ብዙ እንዳይራመድ እፈልጋለሁ ። ከተራመደ ደግሞ በእኔ አማካኝነት እንዳይሆን የተቻለኝን ሁሉ እሞክራለሁ ። »

« እኮ ለምን ? » ስትል ሕሊና ግራ በመጋባት አበራን ጠየቀችው ።

« ሕሊና እንደእኔ ሁሉም ነገር እንዳለ ቢታይሽ ደስ ይለኝ ነበር ። ምን ብዬ ልንገርሽ ። ብዙው ነገር ከቤተሰብ ጋር የተያያዘ ነው ። ያንን ደግሞ ግልፅ አድርጌ ከአንቺ ጋር ማውራት በጣም ይከብደኛል ። አንድም ከአንቺ የምርቅበት ምክንያት ይህ ነው ። »

« አታምነኝም ? »

« ሕሊና ማመን አለማመን አይደለም ። እንዴት ብዬ ላስረዳሽ ። የእኔ ቤተሰቦች በጣም የተቀራረቡና ለውጪ ሰው ዝግ አስተሳሰብ የሚከተሉ ናቸው ። አስተዳደጋችን « መጀመሪያ ራስ ፣

ከዚያ ወንድም ፣ እህት ፣ ከዚያ የተረፈ ትርፍ ነው » በሚል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው ። አሁን የምታይን ታዲያ የዚያ ርዝራዥ ነን።

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የራሱን ህይወት መኖር አልጀመረም ። የቤተሰብ የጋራ ኑሮ አሁንም በእኛ ዘንድ እንደቀጠለ ነው ። በቤተሰባችን ለቤተሰብ አባላት እኛ የሚለው ቃል ተግባራዊ በመሆኑ ግንኙነቶች ከውጪ ሰው ወደ ቤተሰቡ ሲስነዘሩ የሚቆጠረው እንደሰርጎ ገብና ተቀናቃኝ ነው ። ቤተሰቡ ባለው አቅምና ችሎታ በአንድነት ይህን ሰርጎ ገብ ይቋቋማል ። ሕሊና ይኸውልሽ ታዲያ ከአራት ወንድማማቾች አንድ ብቻዬን ከስድስት እህቶቼ ጋር በዚህ ፍልሚያ መካከል አለሁ ። » . . . አበራ ራሱን ነቀነቀ ። ተስፋ በመቁረጥ መልክ ዓይኖቹን ወደ መሬት ተክሎ « ይህን ሁሉ እንዳስተናግድ አደራው በእኔ ትከሻ ላይ ነው የወደቀው ። »

« ታዲያ መስፍን እዚህ ውስጥ ምን አገባው ? »

« መስፍን የቤተሰቡ አባል ነው ። ቀደም ሲል የገባው ቃል ነበር ። ቃሉን አልፈፀመም ። ለመስፍን ይህ አዲስ ነገር አይደለም ። እርሱ የመሰለውን ነው የሚያደርገው ። ስለዚህ ቤተሰቡ በገባው ቃል መሠረት መስፍንን ለማስገደድ ባለመቻላቸው ሀሳቡን መቃወምና ማፍረስ ላይ አተኮሩ ። »

« ታዲያ ይሄ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው ? »

« ሕሊና ባለፈው ጊዜ ስለመስፍን ደብዳቤ ስንነጋገር የነገርኩሽ መሰለኝ ። መስፍን ስለአንቺ ያለው ስሜት ዘለዓለማዊ ነው። በመፃፍ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም ።

« ለቤተሰቡ በፃፈው ደብዳቤ ስለ ሠርግና ስለመሳሰለው አውስቷል ። ቤተሰቡ ትኩረቱን ወደ ሌላ ለመለወጥ የተለያዩ ደብዳቤዎችን ቢያዥጎደጉዱም መስፍን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የሚፅፈው ስለ ትዳር እና ስለወደፊት ኑሮው ነው ። ማለትም

መስፍን ሁልጊዜ በደብዳቤው ስለአንቺ ነው የሚያወሳው ። ቤተሰቡ ይህ አሳስቦታል ። »

« ያልከው በሙሉ ትክክል ነው እንበል ፤ ግን የአንተንና የእኔን ግንኙነት ምን አሻከረው ? »

« በአንቺ ምክንያት ነው መስፍን የተለወጠው ። ለእኔ አትንገሪኝ አውቃለሁ ። ሕሊና አንቺን እንደ ራሴ ነው የማውቅሽ ። መስፍንን ጥሩ ያልሆነ ነገር መከረሽ እንደማትለውጪው አውቃለሁ። ሆኖም ቤተሰቡ እንደእኔ አይገባውም ። የእኔ ከአንቺ ጋር መቀራረብ ቤተሰቡን መበታተን ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በያዙት መጥፎ አስተሳሰብ እንዲቀጥሉ መገፋፋት ነው ። ግን አሁን ባለው ሁኔታ ሳንዘጋጋ ሀሳባችንን ልናስታርቅና ጤናማ ግንኙነት እንዲመሠረት ለማድረግ እንችላለን ። ካንቺ ጋር እንደድሮው የነበረን ግንኙነት መቀጠሉን ካወቁ ለኔም እንደአንቺው በሩን ይዘጋሉ ። ይህ ለሁሉም አይበጅም ። »

ስለዚህ ከእኔ ጋር መነጋገሩን ያቆምከው የቤተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ ስትል ነው ? »

« አዎን የቤተሰቡንም የአንቺንም ደህንነት ለመጠበቅ ነው ።» አበራ ወደ ሕሊና በእርግጠኝነት ተመለከተ ።

« አልገባኝም ። »

« ለማንኛውም በደፈናው ለጥቂት ጊዜያት ሁኔታዎች እስከሚረጋጉ የእኔና የአንቺ ግንኙነት የቀዘቀዘ ይሆናል ። አንቺን በመጥላቴ ወይንም ቤተሰቤን በመደገፌ ሳይሆን ለሁላችንም ደህንነትና ሁኔታዎችን በጤናማ መልክ ለማረጋጋት የግንኙነታችን መቀዝቀዝ አስፈላጊ ነው ። »

« ቀዘቀዘ ማለት ከእነ ጭራሹ መነጋገር አንችልም ? »

« ትምህርት ቤት »

« ትምህርት ቤት መነጋገር ከተቻለ እርሱም ተስፋ ነው ። »

« በጥቂቱ »

« ከከበቡሽ ጋርም መነጋገር ክልክል ነው እንዳትለኝ » አለች ሕሊና ፈገግ ብላ በማሾፍ መልክ ።

« ከበቡሽን ማን ያግዳታል ። በፍቃዷ የምትኖር . . . ተይ ቢሏትም በጀ አትል ። . . .» ጥቂት አመነታ ። « እኔና አንቺ ዓላማ አለን ። »

« ምን ማለት ነው ? ዓላማ ስትል ? ነገሩ ጠጠረብኝ »

« ቤተሰቡ የአንቺና የመስፍን ግንኙነት የግላችሁ መሆኑን እንዲረዱትና እንዲቀበሉት ማድረግ ማለቴ ነው ። »

« እኔ የቤተሰቡን አስተሳሰብ እንዴት አድርጌ ነው የምለውጠው ? »

« እርሱን እንገዲህ ጊዜው ሲደርስ እናያለን ። ለጊዜው የምጠይቅሽ ግን ሁኔታውን አጢነሽ እንድታይውና በተቻለ መጠን ለመስፍን ስትፅፊ ጉዳዩን ላለማንሳት ሞክሪ ። እርሱ ከሰማ ነገር ተበላሸ ማለት ነው ። »

* * *

በመስፍንና በሕሊና መሀከል የሚካሄደው የደብደቤ ግንኙነት ቀጠለ ። የግንኙነታቸው ደረጃና ዓይነት ከፍ እያለና እየጠበቀ በመምጣቱ በአካባቢያቸው ያሉ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ወገን ለይተው የግንኙነቱ ደጋፊና ነቃፊ በመሆን ከሕሊና ጋር ያላቸውን ቅርበት አስተካከሉ ። የሕሊናና የሀሰንም ግንኙነት እንደዚሁ በቀላሉ ሊሸነገል አልቻለም ። ሕሊና በቆራጥነት ግንኙነቱን ለማቋረጥ ብትጥርም የሀሰን ፍላጎት ግን ቀኑ እየገፋ በሄደ ቁጥር ሕሊናን መልሶ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ የነበረው ቆራጥነት እየናረና እየጎለበተ መጣ ።

ሀሰን ወደ አሰላ በመመላለስ ከሕሊና ጋር ቅርበት አላቸው ብሎ ያሰባቸውን ሰዎች ፊትለፊት በማነጋገር ለማስረዳት ሞከረ ። በሀሰን መመዘኛ የሕሊና የቅርብ ጓደኛ አበራ ነው ። ቢያማክረው ችግሩ እንደሚቀረፍ አሰበ ። የሀሰን እንደገና ማንሰራራትና በአካባቢው ማንጃበብ ጤና የነሳው ሕሊናን ብቻ አልነበረም ። የመስፍንና የሕሊናን ግንኙነት ለሚደግፍ ሁሉ እንደመጥፎ ክስተትና በራሳቸው ላይ እንደተሰነዘረ ጥቃት አድርገው ቆጠሩ ። ለአበራ ሕሊና የቅርብ ጓደኛ ብቻ አይደለችም ። መሰፍን በሁሉም ነገር ሕሊናን ለአበራ አደራ ሰጥቶታል ። እርሱም የተሰጠውን አደራ በቀላሉ አላየውም ። ማንኛውም በሕሊና ላይ የሚሰነዘር ጥቃት በቀጥታ ስለሚመለከተው በተቻለው ሁሉ ጥቃቷን የማስወገድ ወይንም የመከላከል ኃላፊነት እሱ ላይ ሆነ ።

ሕሊናና የመስፍን ቤተሰቦች በመሀከላቸው ያለውን ቅራኔ በከፊል በማስወገድ ለመነጋገር ያላቸውን ፍላጎት አሰፉ ። ሕሊና ለአበራ ከሀሰን ጋር የነበራትን ግንኙነትና ግጭት በመግለፅ ቀደም

ሲል እንዲያውቅ ያደረገች በመሆኑ ሀሰንን ለመቋቋም በምታደርገው ትግል ሁሉ በሙሉ ልብ ተባባሪዋ በመሆን ከሀሰን ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ስለሁኔታው ለማስረዳት ሞከረ ።

« ሀሰን ለግንኙነታችሁ መቀጠል የበኩሉን ጥሬ ነበር ። ሆኖም ሕሊና ግንኙነቱ እንዲቀጥል አትፈልግም » በማለት ወደ ቤቷ መምጣቱን እንዲያቆም ሀሰንን መከረው ። ሀሰን ግን « እወዳታለሁ ። ከእርሷ ጋር ለመሆን ፍላጎት አለኝ ። ስለ አጠፋሁት ሁሉ ይቅርታ እጠይቃታለሁ » ሲል ተከራከረ ። ሆኖም ሕሊናን አግኝቶ ስለሁኔታው ሊያነጋግራት አልቻለም ።

ፀሀይዋ በመጥለቅ ላይ ነበረች ። ቀኑ አልፎ ወደ ጨለማው እያዘገመ ነው ። ሰዎች የቀን ሥራቸውን ፈፅመው ወደየቤታቸው በመግባት ላይ ናቸው ። ሕሊና ከትምህርት ቤት ተመልሳ ፣ ልብስ ቀይራ ወደ ማጀት ለመግባት እየተዘጋጀች ነበር ። ገርበብ ባለው የቤቷ በር የሚገባ ሰው አየች ። ከሩቁ ለመለየት ባለመቻሏ « ማን ነው ? » በማለት እየተጣራች ወደ በሩ ቀረበች ። ያየችውን ጥላ በመሸሽ መልክ ወደ በሩ በፍጥነት አመራች ። « ሕሊና አትደንግጪ፣ ሀሰን ነኝ ላነጋግርሽ ስለፈለኩ ነው » በማለት በበሩ መሀከል ቆሞ የምትሸሸውን ሕሊናን ለማስቆም ሞከረ ።

« ላነጋግርህ አልፈልግም ። ለምን እዚህ ትመጣለህ ? » ስትል ጮኸችበት ።

« ቆይ እንጂ ፣ ለምን እንደዚህ ትሆኛለሽ ? » በማለት እጇን በሁለት እጆቹ ጠበቅ አድርጎ ይዞ በመለማመጥ መልክ ጠየቀ ።

« አትያዘኝ ፤ ልቀቀኝ ፤ ከቤቴ ውጣልኝ ነው የምልህ ! ላነጋግርህ አልፈልግም ብዬሃለሁ ፤ እጄን ጎዳኸኝ » ጉዳቷን ለማሳየት ፊቷን አጨማደደች ።

« ኧረ ጎረቤት ምን ይልሻል ? አትጩሂ ፤ ቀስ ብለሽ አትናገሪም ? »

« ምንም ቀስ ማለት የለም ። ውጣልኝ ብዬሃለሁ ሌላ ነገር ሳይመጣ ! » እርዳታ በመፈለግ ሕሊና ድምጿን ከፍ አድርጋ በመጮህ ተናገረች ።

« የእንቺ ጩኸት ምንም ነገር አይፈጥርም ። ይልቁንስ የምለውን አዳምጪ ። እዚህ የመቆየት ሀሳብ የለኝም ። »

« አልፈልግም ። አላዳምጥህም ብዬሃለሁ ። አንተ ሰውዬ ልቀቀኝ ። »

በበሩ በኩል ሁለት ሰዎች ተሯሩጠው ገቡ ። ግርግሩ ብዙም አልቆየም ። ሀሰን ቤቱን ለቆ ወጣ ። በገላጋይነት የመጡት ወደ የቤታቸው ተመለሱ ። ይህ የሀሰን ድርጊት ለሕሊና አዲስ ክስተት ነበር ። ሀሰን ከዚህ በፊት በጉልበቱ ለመጠቀም ሞክሮ አያውቅም ነበር ። « ሰዎቹ ባይደርሱ ኖሮ ምን ሊያደርግ ነበር ። ላነጋግርሽ ፣ ምን ያነጋግረኛል ? አልፈልግም ማለት አይገባውም ! » ሕሊና የሀሰን ድርጊት ቢቀጥል ወዴት እንደሚያመራ አላወቀችም ። ፍርሃቷን ውጣ ፣ ሀፍረቷን ሸፍና ለማሳለፍ ወሰነች ።

እንቅልፍ አልወሰዳትም ። በሯ የተንኳኳ መሰላት ። ወደ በሩ ጠጋ ብላ አዳመጠች ። ሆኖም ምንም ድምጽ ለመስማት አልቻለችም። ወደ መኝታዋ ተመልሳ ለመተኛት ሞከረች ። በመስኮት በኩል የመንኳኳት ድምፅ የሰማች ስለመሰላት ወደ መስኮቱ ጠጋ ብላ ለማዳመጥ ሞከረች ። ሆኖም የሰማችውን ደግማ መስማት አልቻለችም ። ተመልሳ አልጋዋ ላይ ተኛች ። ለሦስተኛ ግዜ የሰማችው ድምፅ ግን በጣም አስደንጋጭ ነበር ። በመኝታ ቤቷ አቅራቢያ የነበረው መስኮት በድንጋይ እሩምታ ተደበደበ ። ሕሊና ለመደበቅ ወደ አልጋዋ ስር ቶሎ ብላ ገባች ። ከሁለት ተከታታይ የድንጋይ ናዳ በኋላ አካባቢው ፀጥ አለ ።

ሕሊና ለውነቷ ዛለ ተንቀጠቀጠች ። የምትይዘውና የምትጨብጠው ጠፋት ። ሀሳቧ ርቆ ሄደ ። በህይወቷ የሰማችውን

አሰቃቂ የግድያ ወንጀል አስታወሰች ። የራሷን ሁኔታ ከዚህ አሰቃቂ ወንጀል ጋር በማመሳሰል ፍርሀቷን አናረች ። ቶሎ ቶሎ እየተነፈሰች አልጋዋ ሥር ያለ አንዳች ነገር ፈለገች ። እጆቿን ወዲያና ወዲህ እያወራጨች ዳሰሰች ። እንደድንገት እጇ ራቅ ብሎ በተቀመጠ ቋጠሮ ላይ አረፈ ። ፍርሃቱ ለቋት ሠላም ሰፈነ ። የነካችውን ከረጢት ወደራሷ አቀረበችና አቀፈችው ። ወዙን አሸተተች ። ከአልጋው ስር ወጣ ብላ ከረጢቱን ለመክፈት ሞከረች ። አጠገቧ ያለውን መብራት አብርታ ከከረጢቱ ውስጥ ያወጣችውን የአባቷን መጥረቢያ ወደ ራሷ አቅርባ አልጋው ላይ ተቀመጠች ። አካባቢዋን ትታ በሀሳብ ማዕበል እርቃ ሄደች ።

«አባዬ እባክህን እርዳኝ ፤ ከዚህ ሁሉ መዓት አውጣኝ » በማለት በእጇ የያዘችውን መጥረቢያ እንደቅርብ ሰው አቅፋ ማልቀስ ጀመረች ። ድንገት የሕሊና በር ተንኳኳ ። ከውጪ ከሚጠራው ድምፅ ለእርሷ ዕርዳታ የመጡ መሆናቸውን አበሰራት ።

በሩን በጉጉት ስትከፍት መምህር ዲሪባ ከሌሎች የሠፈሩ ሰዎች ጋር በመሆን « ደህና ነሽ ! ደህና ነሽ ! » በማለት ጠየቋት ። በተደናገጠ መልክ ቀርበው ሕሊናን ተመለከቱ ። ሕሊና ደህንነቷን ገልፃ እንዲተመጡ ጋበዘች ። ከመሀከላቸው አንደኛው ቀደም ሲል በሀሰንና በሕሊና መሀከል ለተፈጠረው ግጭት በገላጋይነት የቀረበ ነበር ።

« ይህ ሰው ሌላ ነገር ሊያደርግ ስለሚችል አሁኑኑ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደሽ ለምን ክስ አትመሰርችም ? » በማለት ጠየቀ ። ጎረቤቱ የሕሊና መነካት ብቻ ሳይሆን የሰፈሩ ፀጥታ መነሳት ጉዳይ እንዳሳሰበው ገለፀ ።

« በይ ልብስሽን ቀይሪና እኔና ድሪባ እንሸኝሻለን » በማለት ለጊዜው ወደየቤታቸው ተመለሱ ። ሕሊና በአድራጎቷ ቅር እያላት ሁለቱን ሰዎች ተከትላ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተያይዘው ሄዱ ። ሕሊና

ፖሊስ ላቀረበላት ጥያቄ አጠቃላይ መልስ በመስጠት በዕለት ሁኔታ ላይ ስፍሮ እንዲቀመጥ ጠየቀች ።

ፖሊሱ « የሚጠረጥሩት ሰው አለ ? » ብሎ ለጠየቃት ጥያቄ ምንም መልስ አልሰጠችም ።

« ለህይወቴ እፈራለሁ ሲሉ ጉዳት ሊያደርስብኝ ይችላል የሚሉትን ወገን ካልጠቆሙን በምን ዓይነት ዘዴ ልንረዳዎት እንችላለን ? » በማለት ከመፃፍ ተገትቶ በመገረም ሕሊናን ተመለከተ። በሀሰንና በሕሊና መሀከል በተፈጠረው ግጭት በገላጋይነት ከነበሩት ሰዎች ውስጥ አንድ አዛውንት ብድግ ብለው ፤

« ለምን ትደብቂያለሽ ? ምን ያለችው ነች እያ ? ተናገሪ እንጂ ! » አሉ በሕሊና ዝምታ በመናደድ ቆጣ ብለው ።

« ምኑን ነው የምናገረው ? ማን ብዬ ? » እጇን ዘርግታ ግራ በተጋባ መልክ ወደ አዛውንቱ ሰው ተመለከተች ።

« ንሳማ ፖሊስ ነገሩ ወዲህ ነው ። ቀደም ሲል እዚህ ቤት አምባጓሮ ተፈጥሮ ነበር » በማለት ለማስረዳት ሲሞክሩ ፖሊሱ አቋረጣቸው ።

« ቃሉ ከተበዳይ መምጣት አለበት ። የእርስዎ ምስክርነት እዚህ ላይ ሊሰፍር አይችልም ። ነገረ ፈጅ ነኝ የሚሉ ከሆነ በህጋዊ ፍርድ ቤት ውክልናዎ ሲረጋገጥ እንነጋገራለን ። መምህርት በደረሰብዎ በደል ተጠያቂ የሚሆን ወይንም የሚጠረጥሩት ግለሰብ የለም ነው የሚሉት ? » ሲል ፊቱን ወደ ሕሊና አዞረ ።

ሕሊና ጥቂት አሰብ አድርጋ « በአሁኑ ወቅት በእርግጠኝነት የማውቀው ሰው የለም ። ጥርጣሬዬ ግን ሊሆንም ላይሆንም ስለሚችል ቃሌን ለመስጠት በጣም እቸገራለሁ ። »

« በዕለት ሁኔታ ላይ የሰጡት ቃል ሰፍሯል ፤ ያንብቡት ።» በማለት ፖሊሱ በቅጹ ላይ የተሞላውን ወደ ሕሊና አሳለፈ ። ሕሊና አንብባ መጨረሷን እንዳረጋገጠ

« ይህ ቃልዎ ነው ። ፊርማዎን እዚህ ላይ ያስፍሩ ። በአካባቢው ላሉት ሮንዶች በዓይነ ቁራኛ እንዲጠብቁ አስፈላጊው ትዕዛዝ ይሰጣል ። »

* * *

ሕሊና በሀሳብ ተውጣ በፖሊስ ጣቢያው ውስጥ ስለተነሱት ጥያቄዎች አብሰለሰለች ። « ሀሰን ምን ብሎ ድንጋይ ይወረውራል ? ይህን መሰል ፀባይ ከዚህ ቀደም ሰምቼም አይቼም አላውቅም ። እኔን ለመጉዳት ቢፈልግ እንደያዘኝ ለምን አልደበደበኝም ነበር ? ። . . . ፈፅሞ ሀሰን ምንም ያህል ቢናደድ የዚህ ዓይነት ነገር በእኔ ላይ አይፈፅምም ። » በማለት ሀሰን በትግሉ ወቅት የያዛትን የእጇን ክፍል ዳሰሰች ።

« ሀሰን እንደዚህ ጨክኖ በጉልበት ይዞኝ አያውቅም ነበር ፤ ምን ነካው ? ለምን እንደዚህ ያደርጋል ? » አበራ የሕሊናን አቤቱታ በፀጥታ አዳመጠ ።

« እንዳልሽው ሀሰን ይኼን የሚያደርግ አይመስለኝም ። » አለ ሕሊና ያለችውን በማረጋገጥ « እርግጠኛ ነሽ ከሌላ ሰው ጋር ምንም ግጭት የለሽም ? » በማለት ጠየቀ ። ሕሊና ሀሳቧን በማንበብ ዓይነት ጥቂት ተከዘች ። እራሷን በእሉታ ነቀነቀች ።

« ከሀሰን ሌላ እኔ የማውቀው ወይም የማስታውሰው ምንም ጥል የለኝም » አለች በእርግጠኝነት ።

« ከሀሰን ሌላ ይህን ሁኔታ የሚፈታ ከሌለ ብጠይቀው ፈቃደኛ ነሽ ? » በማለት አበራ ጠየቃት ።

« ለምን እንተወውም ። አንተን እዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ ማስገባት አልፈልግም። »

« ስለ እኔ አታስቢ ። ሀሰንና እኔ እኮ በቀላሉ መወያየት

የምንችል መሰለኝ . . . » አላት ። ዝም አለችው ። አበራ ቀጠለ « ምን ዝም ትያለሽ ? ይኼ እኮ በዝምታ የሚታለፍ ቀላል ነገር አይደለም ። ጠላትሽን ማወቅና መለየት አለብሽ ። አለበለዚያ ነገ የሚፈፀምብሽን ወንጀል በምን ልታውቂ ትችያለሽ ። ደግሞ አይዞሽ ። እኔ ምንም አልሆንም ። »

« አበራ በእኔ ሀጢያት አንተን ልማግድህ አልፈልግም . . . » አለች እያመነታች ። አበራ ጊዜ አላጠፋም ከሕሊና ተሰናብቶ ሀሰን አለበት ብሎ ወደአመነበት ሆቴል አመራ ። ከሀሰን ጋር በሠላም ጨረሰ ።

« ሕሊና ልክ ነሽ ፤ ሀሰን አይደለም ። ጠየኩት ። አንቺ ጋ የመጣው ስለአጠፋው ጥፋት ይቅርታ ሊጠይቅሽ ነው እንጂ ለሌላ ጉዳይ አልነበረም ። አስላ የቆየውም አንቺን በግል አግኝቶ ይቅርታ እስከሚጠይቅሽ ነበር ። ጉዳዩን ስነግረው በጣም ነው ያዘነው ። የእኔ እዚህ መሆን የሚያስፈራት ከሆነ ዛሬውኑ ለቅቄ እሄዳለሁ ብሏል ። በእኔ ግምት ወርዋሪው ሀሰን አይደለም ። ሕሊና ጉዳዩን እስከምናጣራ ለምን ከእኛ ጋር አትሆኚም ? ቤቱ እንደሆነ ለሁላችንም ይበቃል ። »

ሕሊና መልስ ከመስጠት ተቆጠበች ። መልስ ለመስጠት የተቸገረችበት አንዳች ነገር እንዳለ ተረዳ « ለምን አትናገሪም ! »

« እምቢ ማለት አልፈልግም ፤ እንዳላስቀይምህ ። አበራ እዚህ ብሆን ምንም አይነካኝም ። አሁን በርትቻለሁ ። ሌላው ደግሞ ይህን የሚያደርጉ ሰዎችን በዓይኔ ማየት እፈልጋለሁ ። ከዚህ ከሄድኩ ማየት አልችልም » ስትል ተሟገተችው ።

« በቃ ምን ጊዜም ለመምጣት ከፈለግሽ በሩ ክፍት ነው » አላት በሀሳቧ መፅናቷን ከተረዳ በኋላ ።

«አበራ ስለሰጠኸኝ ድጋፍ በጣም ነው የማመሰግንህ ። በጣም ነው ያኮራኸኝ ። ሌላም ነገር ብሆን አጠገቤ ተቆርቋሪ ሰው እንዳለ ተማመንኩ ። እግዝአብሔር ውለታህን ይክፈልህ ። »

« ምስጋናው በዛብኝ ። በጣም ሞቀኝ ። » አለ አበራ የሰራውን አጋና እንደትልቅ በመቁጠሯ ። « ሕሊና ለአንቺ መቼም ብርጭቆ ቢያቀብሉሽ እንደ ትልቅ ድጋፍ ነው የምትቆጥሪው። አንቺና እኔ እኮ ከእንግዲህ ሥጋና ደም ነን ። በነገራችን ላይ መስፍን የጠየቀው ጥያቄ እንዴት ሆነ ? »

« እርሱ የማይጠይቀው ነገር የለም ። ስለየትኛው ጥያቄ ነው የምታወራው ? »

« ከሁሉም ስለሚበልጠው ጥያቄ ! አትሽኮርመሚ ። ስለምን እንደማወራ ታውቂያለሽ ። »

« ምን ብዬ እመልስለታለሁ ። እኔ እኮ አበራ ሁሉ ነገር ተፋጠነብኝ ። ነገሮች ሁሉ በአንድ ጊዜ ሲመጡ የማስበው ሁሉ ተምታታብኝ ። »

« እሺ ወይም እምቢ ማለት ይህን ያህል ጊዜ አያስፈልገውም። ይልቁንም ስመምጣት እያቀደ ስለሆነ ቶሎ ፃፊለትና አስፈላጊውን ነገር ቶሎ ቶሎ ፈፅመን ተያይዛችሁ ወደ እዚያው ብትሄዱ ጥሩ ነው ። እኛም የግል ህይወታችንን እንኑርበት ። »

ሕሊና በሀሳብ ተውጣ ከአበራ ራቀች ። የአባቷ ማስታወሻ ከሆነው መጥረቢያ መለየት አትፈልግም ። ሌላው ደግሞ እማማ በላይነሽ ከያሬድ ጋር ለጊዜው ይኑሩ እንጂ ኃላፊነቱ የራሷ እንደሆነ አሰላሰለች። ከያሬድ ጋር ያላትን ግንኙነት መቋጫ ሳታደርግለት እንደዚሁ እንደተንጠለጠለ መተው ለያሬድም ለራሷም እንደማይበጅ አመነች ። የአክስቷ የእማሆይ አባይነሽ ጉዳይም በጥቂቱ አሳሰባት ። ከሁሉ በላይ ግን አጥብቆ ያሳሰባት ከማታውቀው ሰው ጋር ተያይዛ ወደማታውቀው ሀገር ተጠቃላ የመሄዱ ጉዳይ ነበር ።

መስፍንን በመልክ ያየችው ለሁለት ቀናት ነው ። አብዛኛው ትውውቃቸው በመፃፃፍ ላይ የተመሠረተ ነው ። እንደ ወንድሙ አባባል መስፍን ከቤተሰቡ ሁሉ ለየት ያለና የራሱ የኑሮ ዘይቤን የሚከተል ሰው ነው ። ባደረጉት የፅሁፍ መለዋወጥ ምንም ያህል የናረ ግጭት ባይኖራቸውም በአስተሳሰብ ርቀት እንዳላቸው ለሕሊና ግልፅ ነበር ። ለማንኛውም መስፍን ሃሳቧን እንድትቋጭና መልሱን በቶሎ እንድትፅፍለት ስለአሳሰባት ጉዳዩን ለብዙ ጊዜ ማዘግየት እንደማትችል አሰበች ። ነገሮች የተበታተኑ ቢሆንም ይህ ዕድል የትምህርት ጥማቷን ለማርካት እና ለወደፊቱ የኑሮዋ ማማር ወሳኝነት እንዳለው ገመተች ። ስለ ጉዳዩ ያወቁ የቅርብ ጓደኞቿ « ዕድለኛ ነሽ ምነው እንችን ባደረገኝ » በማለት ለመሄድ ያላትን ጉጉት አስፋሏት ።

« ሁሉንም ጥሎ መሄድ ከኃላፊነት መሸሽ አይደለም ። ለምን እንደዚህ እንደማስብ አላውቅም ። በሄድኩበት ሁሉ የቅርብ ሰዎች ሀሳብ አብሮኝ ይጓዛል ። ከዚህ ሄድኩ ማለት ራቅኳቸው እንጂ በሀሳብ እርግፍ አድርጌ ከአልተውኳቸውም እዚህ ሆኜ የምረዳቸውን ያህል እዛም ሆኜ ማድረግ አልችልም ? » ስትል አሰበች ። ወደ ኋላም መለስ ብላ ያሬድ ወደ ጀርመን ለትምህርት በሄደበት ጊዜ እንዴት በወኪል እርሷንና ወ/ሮ በላይነሽን ሲረዳ እንደነበረ አስታወሰች ። ዘዴውን መጠቀም ይቻላል ። ማን አለ የሚታመን ፣ የእኔን ዘመዶች በውክልና ሊረዳ ፈቃደኛ የሚሆን ? » የመጀመሪያው ሰው በኃላፊነቱ ብቁ ነው ብላ ያቀረበችው አበራን ነበር ። « ግን እርሱ ደግሞ ብዙ ውክልናና ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው ። በእርግጥ ብጠይቀው እሺ ብሎ ይቀበላል ። ሆኖም በእኔ በኩል ትክክል አይሆንም » ብላ ሀሳቧን ሰረዘች ።

በሁለተኛ ደረጃ ያሰበችው ሰው ከበቡሽን ነበር ። « ከበቡሽ ሴተላጤ ነች ። ለመሰላት ግን ቁም ነገረኛ ነች ። እንዲያውም

ርህሩህና ለእናቶች እንክብካቤ ሁነኛ ሰው ነች ። እኔ የምላት መቼም በገንዘብ እርዷልኝ አይደለም ። ገንዘቡን አድርሳ አንዳንዴ እንድትጠይቃቸው ነው እንጂ ሌላ ምን ታደርጋለች ። . . . ብቻ እስቲ ለማንኛውም . . .ይህ እንኳ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም ። »

ሕሊና ሀሳቧን አልደመደመችም ። በህይወቷ ቃላት ቦታ ያለውና ለብዙ ጊዜ አብሯት ሲንከራተት የኖረውን የአባቷን ብቸኛ ቅሪት ማስታወሻ የቁምነገር ምንጭና ከነበረው ወደ አለውና ወደሚመጣው መሸጋገሪያ የሆነውን መጥረቢያ ጉዳይ በትካዜ አሰበች።።

« ያለእርሱ እንዴት እኖራለሁ ? ክፉ ፈተና ሲደርስብኝ ፣ መኖር አስጠልቶኝ ለህይወቴ ትርጉም ሳጣ ፣ አዲስ ክስተት ተፈጥሮ ለመሳተፍ ላለመሳተፍ ሳመነታ ፣ ማንነቴን ለማወቅ ስጥርና ሳረጋግጥ ፣ አብሮኝ የኖረ ምልክቴ ነው » በማለት በሀሳብ ሰጥማ ስለ አባቷ ያላትን አክብሮትና ጥልቅ ፍቅር በህሊናዋ ቃኘች ።

* * *

ግርግሩ ደርቶ ፣ ሁሉም ሰው የክት ልብሱን ለብሶ ፣ ዘመድ አዝማድ ተጠራርቶ ፣ በየፊናው ተከፋፍሎ ፣ ከበሮ እየተደለቀ ፣ ዘፈኑ ደርቶ « ውሸቱን ነው ፣ ነጠላው ነው » በመባባል አይረሴውን የሀገር ባህል ዜማ አዜሙ ። የትከሻ ፣ የወገብና ፣ የአንገት ስብቆሽ ፈተና ተካሄደ ። አንዱ ሲደክመው ሌላው እየተተካ ፣ ሴት ከወንድ እየተቀባበለና እየተወዳደረ የቀሰበቱን ቀን ሞቅ አደረጉት ። ጎላ ጎላ ያለ ጥበብ ለብሰው ፣ በተለያዩ የሀገር ባህል መጠጥና ምግብ በተዋበው አንደኛው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጡ ሦስቱ ሴቶች በዳስ ውስጥ የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ ማረኩ ። ከሁሉም በላይ ግን በውበቷና በአቋሟ ጎላ ብላ የታየችው ሕሊና ነበረች ።

ሕሊና ከአጀቧት ሴቶች ለየት ያለ ጥበብ ለብሳለች ። ዓይኗን ሰበር አድርጋ ፣ አልፎ አልፎ በዳስ ውስጥ ለምታውቃቸው ሰዎች ፈገግታዋን ትሰጥ እንጂ ጠቅላላ ሁኔታዋ ትካዜ የተሞላበት ነበረ ። ሚዜዎቿ አማከለችና ከበቡሽ የውበቷ መቋጫ የሆነውን የሕሊናን ፈገግታ በተደጋጋሚ ለማምጣት ሲሉ ቀልድና ጨዋታ ጣልቃ ለማስገባት ጣሩ ።

የሕሊናን ትኩረት የሳበው የዘፈኑ ፣ የጭፈራው ፣ የምግቡ፣ የመጠጡና ሌሎች አጠገቧ የነበሩት ያማሩና የተዋቡ ሰዎች አልነበሩም ። ከሁለት ጠረጴዛ ባሻገር በድጋፍ የተቀመጡት የሁለት ሰዎች ሁኔታ ነበር ። ወገባቸው ጎብጦ ፣ ሰውነታቸው አጥሮ ፣ ዓይናቸው ደክሞ ጠረጴዛ ላይ በመደገፍና በመተኛት መካከል በትግል የነበሩት እማሆይ አባይነሽ ዓይናቸው ከማልቀስ አልተቆጠበም ። ያለ የሌለ ኃይላቸውን አጠራቅመው መላ ትኩረታቸውን ወደ ሕሊና አቅጣጫ ተክለው ነበር ።

« ደግሞ ደጋግሞ ይስጥሽ ፣ ይባርክሽ ፣ ድሮም የተባረክሽ ነሽ » ሲሉ መርቀው እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ሰነዘሩ ። አጠገባቸው የተቀመጡት አዛውንት ሴት ወ/ሮ በላይነሽ የእማሆይን አባባል በመድገም « አሜን ፣ አሜን » በማለት አልፎ አልፎ የተዝረከረከውን የእማሆይን ነጠላ በመሰብሰብ አገዙ ።

ለሒሊና ይህ የቀለበት ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ በራሷ ሥም የተደረገ ድግስ ነው ። በድግስ ተሳታፊ ከሆኑት ሰዎች ሁሉ ስለ እርሷ መሰረተ ህይወት የሚያውቁ ሁለት ሰዎች ብቻ በመሆናቸው ለራሷ በማዘን አሰላሰለች ።

« እግዚአብሔር እንዴት የሚያዳላ አምላክ ነው ? እኔን ያለ አባት ፣ እናት ፣ እህት ፣ ወንድምና ወገን ያስቀረኝ ? በአንፃሩ መስፍን አባቱና እናቱ በህይወት ባይኖሩም ዘመደና ወገን ብዙ ነው ። የሰው ነገር ይገርማል ። መቼም ተመስገን ማለት ነው ስትል አለበች። ወደ ኋላ መለስ ብላ ከልጅነት እስከአውቀት የነበረውን ህይወቷን ቃኘች ። ክፉውንና ደጉን ፣ የመከራና የደስታ ዘመን በማፈራረቅ ዳሰሰች ። በክፉ ቀን የረዷትን ሰዎች ሁሉ አስታወሰች ። የአባቷ ምትክ ሆኖ ያስተማራትን ታላቅ ባለውለታዋ የሆነውን ያሬድን አሰበች ። በዚህም ታላቅ ቀን አጠገቧ ባለመኖሩ አዘነች ። ሆኖም እንደዚህ ዓይነቱ በዓል ላይ ና ብሎ መጥራቱ ስሜቱን መጉዳት መሆኑን በመገንዘብ በአድራጎቷ ተፅናናች ።

የመስፍን ጥሪ ነበር ሒሊናን ከሀሳቧ ያነቃት ። . . . « ምነው ዝም አልሽ ? ተጫወች እንጂ » አለት ። ሒሊና ቀና ብላ መስፍንን አየችው ። በመገመገም መልክ ፈተሸችው ።

« ምነው አማርኩብሽ ? » አለ መስፍን በፌዝ ። ሒሊና ግን ከማማር አለማማር ደረጃ ልቃ ሄዳለች ። ከመስፍን ጋር ለዘለቄታው አብረው ለመኖር መቁረጧ በእርግጠኝነት ስለመሆኑ ራሷን ጠየቀች።

« መቼ አወቅሁት » ማንነቱን በበለጠ ለማወቅና . . . ስሜቷን ለማረጋጋት ከየት መነሳት እንዳለባት አሰበች ። « በእርግጥ ካለሁበት ወደ ሚቀጥለው ለመሸጋገር መስፍንን ማግባት አማራጭ የለውም ። » በማለት ለጊዜው እራሷን አፅናናች ።

ለረጅም ጊዜ በሀዘን ተውጠው ለብዙ ዓመታት ደስታን መጎናፀፍ ያልቻሉት የመስፍን ቤተሰቦች ይህ የቀለበት ድግስ የመጀመሪያ የለውጥ ምልክት ነው ብለው ስለአመኑ ሞቅ ያለና የተትረፈረፈ እንዲሆን ጥረት አደረጉ ። አዝማሪው ፣ አቀንቃኙና እስክስታ ወራጁ በመፈራረቅ ለዝግጅቱ ማማር የድርሻቸውን አስተዋጽኦ አደረጉ ። የአሰላ ከተማና በአካባቢው ያሉት የገጠር ነዋሪዎች በብዛት በሠርጉ ላይ ተገኙ ። መምህርት ሒሊና በት/ቤቱ ከታወቁት መምህራን አንዷ በመሆኗ የሚያውቋትና ስለአጋጣሚት ዕድል የሰሙ ሁሉ ያለ ጥሪ ወደ ቀለበት ቦታ በመምጣት በሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገኙ ።

በወቅቱ ከአሰላ ባል አግብቶ ወደ አሜሪካ መሄድ ጥቂቶች የሚያገኙት ዕድል ነው ። ስለሆነም ይህ የቀለበት ቀን የከተማው ታላቅ ዜና ሆነ ። በቀኑ ሒሊናን ያዩና በድግሱ ላይ የተገኙ ወጣት ሴት ልጆች ሁሉ ዕድሉን ተመኙ ።

« አይ ዱ ኖት ብሊቭ ዚስ ! ምን ማለትህ ነው አበራ ፣ ይሄ ሠርግ ነው እንጂ ቀለበት አይደለም » አለ መስፍን ለአፍታ የተጠጋውን አበራን ወደ ራሱ ጠርቶ ።

« ምን ተደረገ ። እህቶችህ ናቸው የደገሱት ። ልትኮራባቸው ይገባሃል » አለ ።

መስፍን ሳግ ያዘው ። አጠገቡ ሊሆኑ ያልቻሉትን አባቱንና እናቱን አስታወሰ ። አበራን ወደ ራሱ አስጠግቶ አቀፈው ።

« ሳንክ ዩ አበራ ። እኔ ይህ ሁሉ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ። ሁሉም የሆነው በአንተ ነው » በማለት ወደ ሒሊና ተመለከተ ።

ስሜቱ አሸንፎት በጉንጮቹ ላይ እንባው መውረድ ጀመረ ። በአድራጎቱ የተደናገጠው አበራ ወንድሙን በማፅናናት ከዳሱ ይዞት በፍጥነት ወጣ ። ወደ መኖሪያ ቤት ገቡ ። መስፍን ለቅሶውን ሊገታ አልቻለም ።

« አባቴ ፣ እናቴ . . . ምነው የዛሬዋን ቀን አብራችሁኝ ሆናችሁ ደስታዬን በተካፈላችሁ ። » በማለት ሥማቸውን በመጥራት አስቀሰ ። አጠገቡ የነበሩት አበራና ሕሊና ራሳቸውን በማጠናከር ሊያፅናኑት ሞከሩ ። ሕሊና በማፅናናቱ ብዙም አልገፋችም ። የመስፍን እባባል ብሶቷን አንሮት እንባዋ መርገፍ ጀመረ ። በቤቱ ውስጥ ሕሊናንና መስፍንን ተከትለው የገቡት ሰዎች በአፅናኝና ተፅናኝ ተከፈሉ ። በማጀት አካባቢም ምግብና መጠጥ በማቀበል ላይ የነበሩት የመስፍን እህቶች ተደናግጠው ወደ ሳሎን ተሯሯጡ ። የወንድሞቻቸውን ለቅሶ እንደሰሙ ሁሉም ተቃቅፈው ሀዘናቸውን ገለጹ ። የታላቅ ወንድማቸው የሙሉጌታ ድምፅ ነበር ለቅሶውን ያቆመው ።

« ዋት ኢዝ ጎይንግ ኦን ? ምን ነካችሁ ? ሼም ኦን ዩ » ሙሉጌታ ድምፁን ከፍ አድርጐ ተናገረ ። ወደ መስፍን ፈጥኖ በመሄድ « ዜይ ዲዘርቭ ቤተር ! ምን ሆንክ ብለህ ነው የምታስቅሰው? እነርሱን በዚህ ወቅት በፀሎት ማስታወስ ነው እንጂ መልሰህ ልታመጣቸው ነው ? ምን ዓይነቱ ነህ ? » ሙሉጌታ በመናደድ መስፍንን በእጆቹ ይዞ ነቀነቀው ።

« አይ ካን ኖት ኸሪቴንድ ። እራሴን ለማባበል ብሞክርም አልቻልኩም ። ውስጤ ነደደ ። አባዬና እማዬ ቢኖሩ ኖሮ የዛሬው ደስታዬ እጥፍ ይሆን ነበር ። የእነርሱ አለመኖር ደስታዬን ግማሽ አድርጎት ። ቁጭቱ አልወጣልህ አለኝ » አለ መስፍን ዓይኑን እየጠራረገ ።

« አንተን የሚሰማህ ስሜት እኔን አይሰማኝ መሰለህ ? የእነርሱ ያለመኖር ሁላችንንም ይቆጨናል ። ሆኖም መፅናናት ያለበህ እነርሱ የሚፈልጉትን ከግብ ለማድረስ በመቻልህ መንፈሳቸውን ደስ እንዳሰኘህ መቁጠር አለብህ ። የአንተ ለቅሶ ለራስህ አዝነህ ሌላውንም ማሳዘን ነው ። ከአሜሪካን ሀገር እዚህ ድረስ የመጣነው መላው ቤተሰቡ የደስታህ ተካፋይ እንዲሆን ነው እንጂ ሙሾ እንድታወርድ አይደለም ። ስማ መስፍን ! ቤተሰቡ ከዘመናት ሀዘን በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘው ደስታ ነው ። ለእነርሱ ይህ አዲስ ምዕራፍ ነው ። ለወደፊቱ በዚህ እንዲገፋ አግዛቸው ። በል ውጣ ወደ ዳሱ ሰው እየጠበቀህ ነው ። »

ሙሉጌታ ወደ ሕሊና ዞር አለ ። እርሷም ብትሆን ፊቷ ቀልቶ ፣ ዓይኖቿ ዕንባ አዝለው ፣ አፍንጫዋ ተዘግቶ ሳግ ይተናነቃት ነበር ። ወደ ሙሉጌታ እያየች « ይቅርታ እራሴን መቆጣጠር ስላልቻልኩ ነው » አለችው ።

« አንቺ ደግሞ ተው ብለሽ እንደማፅናናት ነገር ታባብሻለሽ ? ። » በታላቅ ወንድሙ ግሳፄ ሁሉም በየፊናቸው ሊበታተኑ ሕሊናና መስፍንም ተያይዘው ወደ ተጣለው ድንኳን ገቡ ።

የድንኳኑ ግብር ቀደም ሲል በተከሰተው ለቅሶ አልተረበሸም ። አዲስ ገቢው በምግብና በመጠጥ ሲስተናገድ የነሸጠው ደግሞ መሀል በከበባ ወደ ደመቀው ዘፈን ተቀላቀለ ። የቀሰበቱ ድግስ ጉድ እየተባለ ከሚነሱት ከመንደሩ ወሬዎች አንዱ ሆነ ። በሽርሽሩ ወደ ሃያ ሦስት መኪና የተሳተፉበት ፣ የአስላ ከተማ ዳር እስከ ዳር የተጠራበት ፣ በሥም ቀሰበት ተባለ እንጂ ለመስፍንና ለሕሊና ሌላ ድግስ እንደማይኖር ግልፅ ነበር ።

ሕሊናን ወደ አሜሪካን ለመውሰድ መስፍን ህጋዊ የጋብቻ ወረቀት ከማመልከቻ ጋር ማስገባት አለበት ። ዋናውን የጋብቻ ወረቀት ከእራት ቀናት በኋላ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ተቀበሉ ።

« በቃ አለቀ ማለት ነው ? » አለች ሕሊና የጉዳዮ መፋጠን አስገርሟት አብረዋት የነበሩትን አበራና መስፍንን እፈራርቃ እያየች::

« ሌላ ምን ትጠብቂያለሽ ፣ ዋናው ይህ ነበር :: በቀላሉ አለቀልን » አለ መስፍን ::

« ይህስ አለቀ የሚቀጥለው ደግሞ ምንድን ነው ? » ሲል አበራ መስፍንን ጠየቀው ::

« ከዚህ በኋላ በኤምባሲው በኩል ፕሮሰስ ማድረግ ነው :: ኤምባሲ ከመግባቱ በፊት ግን እኔ ማመልከቻውን በመኖሪያ ቦታዬ ሆኜ ማስገባት አለበኝ :: » ከባድ ይመስላል አይደል ? የእኛን ሀገር ውጣ ውረድ ካለፍን ሌላው እንኳ እስከዚህ አይከብድም » አለ መስፍን ::

« ስንት ጊዜ ይፈጃል ከዚህ በኋላ ? » ሕሊና መስፍንን ጠየቀችው ::

« ከሦስት እስከ ስድስት ወር ከዚያ እንግዲህ ጓዝሽን ጠቅልለሽ መምጣት ነው :: » አለ መስፍን ፈገግ ብሎ ::

« እኔ አላምንም ስድስት ወር ብቻ ! » ሕሊና አፏን ከፍታ በመገረም ዓይነት አበራን አየችው ::

« ምነው ለመሄድ ቸኩልሽ እንዴ ? » አላት አበራ ::

« ችኮላ አይደለም :: በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መፈፀም ያለብኝን ነገሮች ሳስብ . . .ጊዜው እንዴት እንደሚበቃኝ አላውቅም! »

« ሀሳብ አታጨቂም ደግሞ ምን ቀረ ? ሥራ ብዙ ነሽ » አለ አበራ፤ ሕሊና ያሰበችውን እንድትናገር በመገፋፋት ::

« እማማ በላይነሽ ፣ የአክስቴ የድሮው ቤት መታደስ አለበት፤ እዚህ በጅምር የቀሩትን ነገሮች ቦታ ቦታ ማስያዝ አለብኝ :: » በማለት ሀሳቧን በጥቅሉ አካፈለችው ::

« ታዲያ ይህን ለማድረግ አንቺ እዚህ መኖር አለብሽ ? በወኪል ሊሰራ የሚችል ነገር እኮ ነው » አለ አበራ አነጋገሩ መስፍንንም ጉዳዩ እንደሚመለከተው አድርጎ ::

« ሕሊና መቼም ስለቤተሰቦችሽ የነገርሽኝ ነገር በጣም የሚያሳዝን ነው :: ሆኖም ይህ ችግር በአንድ ቀን የሚቀረፍ ጉዳይ አይደለም :: አብሮን የሚኖር ጉዳይ ነው :: ስለዚህ አሜሪካ እሄዳለሁ ብለሽ ካሰብሽ ሆድሽን ሠፋ ማደረግ አለብሽ :: ብዙ ነገሮችን በአንድ ጊዜ ለማስተካከል ባትችዪ እንኳን ቀስ በቀስ የሚሆን ይመስለኛል ::»

« መስፍን እዚህ ላይ ልክ ነህ :: ስለ ቤቱ ተነጋግረናል :: ዝርዝሩን ከበቡሽ ባለችበት እንነጋራለን :: ብዙ የሚያሳስብሽ ነገር የለም :: አሜሪካን ሄድሽ ማለት ሠማይ ቤት ገባሽ ማለት አይደለም:: በየጊዜው ብቅ ማለት ትችያለሽ » ብሎ ወደ መስፍን ተመለከተ ፤ ከእርሷ የበለጠ ጉዳዩ የመስፍን እንደሆነ ለማረጋገጥ ::

* * *

መስፍን ጉዳዩን ፈፅሞ ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ ሕሊና ኑሮዋን ለመለወጥ ከመስፍን ቤተሰቦች ጋር ተቀላቀለች :: ኑሮዋ ያበበ፤ የፈካና በቤተሰቡም ተደማጭና ተወዳጅ ሆነች :: ቤተሰቡ በእርሷ እርሷም በቤተሰቡ ችግር ላይ መወያየትና ድጋፍ መስጠት ልማዳዊ የቀን ተቀን ህይወቷ ሆነ :: የመስፍን ደብዳቤ ፣ ሌላም ለቤተሰቡ መከፋፈል ያለበት ገንዘብ የሚላከው በሕሊና ሥም ሆነ :: አማከለች ሕሊና ወደ አሜሪካ ስትሄድ አብራ ለመሄድ ተስፋ በማድረግ ከሕሊና ጋር ያላት ቅርበት ከምንጊዜውም የበለጠ ተጠናከረ::

« አንድ ትልቅ ምስጢር ብነግርሽ ለማንም አትናገሪም ? » አለች አማከለች እጠገቧ ተቀምጣ ስነበረችው ሕሊና ::

« ምንድነው ምስጢሩ ፣ የፈራሁት ነገር እንዳይሆን » አለች ሕሊና ዓይኖቿን አፍጥጣ አፏን ከፍታ ::

« ስለ እኔ አይደለም ፣ ስለ አንቺ ፣ ስለ ራስሽ ነው :: ከብዙ ጊዜ በፊት የተፈፀመና ያለፈ ነው :: »

« አሁን በዚህ ጨዋታ መሀከል ለምን አመጣሽው ? የምናወራው ስለ አንቺ ቦይ ፍሬንዶች ነው » አለች ሕሊና የነገሩን አለመገጣጠም በመጠራጠር ::

« እሱን ልነግርሽ ነው :: ስለ መሬሳና እኔ ጥል ስነግርሽ ሁሉን ነገር አልነገርኩሽም :: የተጣላነው ከእርሱ ጋር አልሆንም ስለአልኩ አይደለም :: እርሱ ነው የመጀመሪያ እውነተኛው ቦይፍሬንዴ :: »

« አረገዝሽ እንዴ ? » ስትል ሕሊና ጠየቀች :: አማከለች ራሷን በአሉታ ነቀነቀች ::

« ስለእሱ አይደለም የማወራልሽ :: እንዴት ብዬ ልጀምርልሽ ? » አለች አማከለች እጆቿን እያፍተለተለች ::

« ምን አስጨነቀሽ ? ተናገሪውና ይውጣልሽ » ሕሊና አማከለች እንድትናገር ገፋፋቻት ::

« እንዳትናደጂ ፣ እንዳትቀጪ ቃል ግቢልኝ »

« እባክሽ አትጨነቂ እኔ ለማንም አላወራም »

« ያኔ ድንጋይ የተወረወረብሽ ጊዜ ታስታውሻለሽ » አማከለች መሬት መሬት ተመለከተች « እነ መሬሳ ነበሩ ያኔ የወረወሩብሽ »

« ምን ! ለምን ? »

« መሬሳ እኔ አሜሪካ ስሄድ እኔን ተከትሎ የመውጣት ሀሳብ ነበረው :: በመሀል የአንቺ መምጣት ጋሼ መስፍን እኔን ለመውሰድ የገባውን ቃል አጨለመው :: ታዲያ መሬሳና ጓደኞቹ ይህንን ሲሰሙ ቆይ እንሰራላታለን ብለው ሲፎክሩ ነበር :: ሕሊና እመኚኝ እኔ እዚህ

ውስጥ አልነበርኩበትም :: በወቅቱ መሬሳ ሲነግረኝ በጣም ነው ያናደደኝ :: »

« የመስፍንን እና የእኔን ግንኙነት እንዴት ሊያውቅ ቻለ ? » አማከለች ጥያቄውን መመለስ አልፈለገችም :: ዓይኖቿን ሰበረች :: የሕሊና ጥያቄ አሳፈራት ::

« እንዴት እንደዚህ ያደርጋል ? እኔ መሬሳ በጣም ጥሩ ልጅ ነው እያልኩ ሁልጊዜ ከአበራ ጋር እጣላለሁ :: አሁንም አበራ ፈፅሞ አያውቅም ፣ ይጠራጠራል እንጂ :: ሕሊና አደራ አበራ እንዳያውቅ:: መሬሳ እንደሆነ ብዙ ዱርዬ ጓደኞች አሉት ከነገርሽው ይገዳደላሉ :: »

« ምን ብዬ እነግረዋለሁ ? »

« ምናልባት ሳታውቂ በጨዋታ መሀል ለአበራ እንዳትነግሪው ብዬ ነው :: አየሽ በጊዜው ይህ ነበር ያጣላን :: ከዚያን ቀን በኋላ ከእርሱ ጋር መውጣቱን አቆምኩ :: እገድልሻለሁ ብሎ መሄጃ መቀመጫ ሲያሳጣኝ ከእነ ሳምሶን ጋር መሆን ጀመርኩ :: የእነ መሬሳ ግሩፕ የእነ ሳምሶምን ግሩፕ በጣም ስለሚፈሯቸው ሳምሶን አነጋግሮት ነው መሬሳ አፉን የዘጋው እንጂ ሊደበድበኝ ፈልጎ ነበር::»

« እኔንስ ይበለኝ :: ግን አንድ የዋህ ሰው በመሀል ቢጎዳ ኖሮ ያሳዝን ነበር » አለች በድፍኑ ::

« እነ ሳምሶን ዋጋቸውን ሰጥተዋቸዋል »

« ምን ማለትሽ ነው ? »

« አንድ ወቅት ላይ ት/ቤት ለሁለት ወራት በተከታታይ የቀረ ጊዜ እኮ ተደብድቦ ነው ሆስፒታል ተኝቶ የወጣው :: እነ ሳምሶን ለሦስት ቀን ታስረው በሽማግሌ ነው የታረቁት :: »

« በእኔ ምክንያት እንዳይሆን ? »

« እ . . . እ . . ርሱ ብቻ አይደለም :: እኔንም መንገድ ላይ እየጠበቁ በድንጋይ ሲያሯሩጡኝ ነበር :: »

« ለአበራ አትነግሪውም ነበር ? »

« ሕሊና ! እኛን እዚህ ሀገር ብዙ ሰው የሚቆጥረን እንደ ባይተዋር ነው ፡፡ መጤ ፣ የአድሃሪ ልጅ የማይፈጥሩልን ሥም የለም፡፡ ታዲያ ለአበራ ብነግረው በእልህ ከመሬሣ ጋር ብቻ አይደለም የሚጣላው ፣ ከሀገሩ ሰው ጭምር ነው ፡፡ አባቱን ታውቂያቸዋለሽ ፣ ጊዜ የሰጣቸው የታወቁ ነጋዴ ናቸው ፡፡ »

« ወይኔ እህቴን ይህን ሁሉ ይዘሽ እስከዛሬ ታዲያ ለምን አልነገርሽኝም ? »

« ፈራሁሽ »

« ለምን ትፈሪኛለሽ ? እህትሽ እኮ ነኝ »

አማከለች እጇን እያፍተለተለች በማፈር መልክ ፤ « አንድ ሰሞን ታስታውሺ እንደሆነ ቤተሰቡ የእንቺንና የጋሼን ግንኙነት ሲሰሙ በመጥፎ ነበረ የሚያዩሽ ፡፡ ከእንቺ ጋር ማንም ሰው እንዳትነጋገሩ ስለተባለ ሁኔታውን በወቅቱ ልነግርሽ አልቻልኩም ፡፡

ከዚያ ደግሞ ሁኔታው ሲሻሻል አሁን እኔ እንዳለሁበት አድርጋ ብትወስደውስ ብዬ ከመናገር ተቆጠብኩ ፡፡ »

« አሁን ታዲያ ለምን ትነግሪኛለሽ ? » ሕሊና በፈገግታ አማከለችን ጠየቀች ፡፡

« አሁንማ አውቄሻለሁ ፡፡ ደግሞ ይህንን በሆዴ ይዤ ሳልነግርሽ ወደ አሜሪካ ብትሄጂ የሚሆነው ነገር አይታወቅም ፡፡ ምነው ያኔ ነግሬያት ብሆን ብዬ ይቆጨኛል ፡፡ »

« አማከለች መቼም በጣም ነው የማመሰግንሽ ፡፡ የዛሬው ንግግራችን በሁለታችን መሀከል የሚቀር ምስጢር ነው ፡፡ »

* * *

በዋይታውና በሁካታው ተሳታፊ ለሆኑት ሁሉ አንዱ ሌላውን ለማዳመጥ የማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ ፡፡ ሳግ ፣ ለቅሶ ፣ መተቃቀፍ ፣ መሳሳም ምርቃትና ጥሩ ቃል ተደረገ ፡፡ ተነገረ ፡፡ ለሕሊና ከሰዎች ተለይቶ ወደ ማስተናገጃው መግባት ከባድ ሆነባት ፡፡ ከአንዱ ወደ ሌላው እየተንፈቀፈቀች ጉንጯቸውን ሳመች ፡፡ መጨረሻ ላይ የደረሰችው ግን በቀላሉ አልተላቀቁም ፡፡ ጨምድደው ይዘው የታገሏት ወ/ሮ በላይነሽ ነበሩ ፡፡

« ለማን ጥለሽኝ ነው የምትሄጅው ልጄ ? » በማለት ደጋግመው ጠየቁ ፡፡

ሕሊና በለቅሶ ምክንያት ለመፅናናት ባለመቻሏ በገላጋይነት እየገፋፋ እንድትሄድ ያደረገው አበራ ነበር ፡፡ የሕሊናን ሁኔታ ያዩ ሁሉ አዘኑ ፡፡ ገሚሶቹም ዳር ቆመው ከንፈራቸውን መጠጡ ፡፡ ወደ ትኬት መቁረጫው በግማሽ ልብ ቀርባ የተጠየቀችውን ፓስፖርትና የወረቀት ማስረጃ በመስጠት በትንሹ በር በኩል በመስታወት ወደ ውጪ ተመለከተች ፡፡ ለሽኝት የመጡት ሰዎች አንድ በአንድ ከነበሩበት ቦታ እየለቀቁ ሄዱ ፡፡ ሕሊና በሩቅ ያየቻቸው አበራ ፣ ከበቡሽና ወ/ሮ በላይነሽ ነበሩ ፡፡ ላለማልቀስ በመወሰን ፊቷን አዞረች፡፡ በአካባቢው የነበረው አንድ ሠራተኛ ወደ ሕሊና ቀርቦ አንድ ፖስታ ሰጣት ፡፡

« ይኼ ደግሞ ምንድነው ? » በማለት ጠየቀች ፡፡

« ስምሽ ሕሊና ነው አይደለም ? » አለ ለማረጋገጥ ፡፡

« አዎ ሕሊና ነው ፡፡ ፖስታው ምንድነው ? »

« ከሸኚዎቹ አንዱ እንዳቀብልሽ ስለጠየቀኝ ነው ፡፡ »

ሕሊና በዚህ ውጣ ውረድ ብዙ ለመጠየቅ አልፈለገችም ፡፡ የተሰጣትን ፖስታ ሳታነብ ቦርሳዋ ውስጥ ከታ ፈጠን ብላ የቆመው

ፖሊስ ወደ አሳያት አቅጣጫ ተራመደች ። የምታውቀውን እየራቀች ወደማታውቀው ቀረበች ። አዲሱን መስክ እያሰሰች በማረፊያ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ቃኘች ። ወጣት ፣ ሽማግሌ ፣ ደካማ ፣ ጎበዝ፣ አንዱ ሌላውን እያገዘ ወደ ፊት ተጓዘ ። የፍተሻውን ቦታ አልፈው የመጨረሻ ማረፊያ ቦታ ደረሱ ። አጠገቧ የነበሩ አዛውንት ሴት ነበሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተሳፋሪዎች ውስጥ ያነጋገሯት ።

« አይዞሽ ልጄ አይዞሽ ! እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ስሄድ ሆዴ ባብቶ ጨለማ ነበር የመሰለኝ ። አሁን ይኸው የውኃ መንገድ አድርጌው በየዓመቱ እመላለሳለሁ ። »

ሕሊና እኚህን አዛውንት ቀደም ብላ በግርግሩ ወቅት በመሸኘት ላይ እንዳሉ አስታወሰች ።

« አይ እማማ ከባድ ነው ። የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ። . . . እርስዎ ወዴት ነው የሚሄዱት » ስትል ጠየቀች ።

« ወደ ልጄ ነው ። ልጄ አሜሪካ ሀገር ነው የሚኖረው ። »

«ታዲያ ብቻዎትን ? » ሕሊና መገረሟን መደበቅ አልቻለችም።

« ምን አለ ብለሽ ነው ሁሉም ነገር የተዘጋጀ ነው ። ግራ የሚገባ ነገር የለም » አሉ ።

« ጎበዝ ነዎት ። »

« አንቺም አንድ ጊዜ ካየሺው ትለምጂዋለሽ ። »

የአይሮፕላኑ አስተናጋጅ የመተላለፊያ በር ከፍታ ተሳፋሪዎች ቦርዲንግ ፓስ እንዲያዘጋጁ ጠየቀች ። ሁሉም ተሰልፈው የቁጥጥሩን በር እያለፉ ወደ አይሮፕላኑ በሚያደርሳቸው አውቶቢስ መሳፈር ጀመሩ ። ሕሊና ሥሟን ከሩቅ የሚጣራ ድምፅ ሰማች ። ድምፅ ከወደመጣበት አቅጣጫ ተመለከተች ። ሆኖም ምንጩን ማግኘት አልቻለችም ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጥሪው ቀጠለ ።

ሕሊና ወደ አቅጣጫው በማየት ላይ እንዳለች አጠገቧ የነበረው አንድ ወጣት የድምፁን ምንጭ ጠቆማት ። ሕሊና ጥቂት አመነታች ። ሰገነቱ ላይ በርቀት የቆመውን ሰው በቅጡ ልትለየው አልቻለችም ። እጇን ከዓይኖቿ በላይ ጥላ ለማነጣጠር ሞከረች ።

« ያሬድ ነኝ ! ያሬድ ነኝ ! »

ሕሊና የሰማችውን አላመነችም ። እጆቿን አወራጭታ ። ወደ ልቧ ሰበሰበች ። አፏን በመዳፏ ሸፍና ባግራሞት ፈዛ ቀረች ። እንባ እየተናነቃት በአድራጎቷ በከፊል የውስጥ ስሜቷን ለመግለፅ ሞከረች ። እጆቿን ወደ ሠማይ ዘርግታ ሰላምታ በመስጠት ዓይነት አውለበለበች ።

« ጋሼ ያሬድ ! ጋሼ ያሬድ ! » ብላ ደጋግማ ተጣራች ። ዓይኖቿን ያሬድ ላይ ተክላ በድን ሰውነቷን እየጎተተች አውቶቡሱ ውስጥ ገባች ።

* * *

ሕሊና በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ምድርን ለቃ በአየር ላይ ተንሳፈፈች ። ምቾት አልሰጣትም ነበር ። መላ ሠውነቷ ተረበሸ ። አቅለሸለሻት ። ያለችበትን እንደመርሳት ሲከጅላት ዓይኖችዋን ጨፍና የተቀመጠችበትን ወንበር ጨምድዳ ያዘች ።

አንዳች ነገር ልቧን ለለበው አፈር ፈጭታ ያደገችበትን ክፉና ደጉን ያሳለፈችበትን ሀገሯን ለቃ መሄዷ ሲታሰባት ሆዷ ባባ ፣ ባዶነት ተሰማት ። አውሮፕላኑ ሠማይ ላይ ዘልቆ የተረጋጋ በረራ እንደጀመረ ዓይኖቿን ገልጣ በረጅሙ ተነፈሰች ። እየቆየች ስትሄድ ሁሉንም ሁኔታ እየተላመደችው መጣች ። ሁሉንም ነገር እረስታ እንቅልፍ ይዟት ጭልጥ አለ ። እንደተኛች ፍራንክፈርት ደረሰች ። ከቆይታ በኋላ የችካጎ ጉዞ ተጀመረ ።

ሕሊና ያለፈውን በትካዜ እያሰበች የወደፊቱን በደስታ ለመቀበል ከወዲሁ ተዘጋጀች ። የአውሮፕላኑ አስተናጋጅ ያመጣችላትን ለስላሳና ቁርስ መሳይ በመመገብ ጉዞዋን ቀጠለች ። በሚችጋን ሀይቅ ውብት እንደተሳበች አውሮፕላኑ ችካጎ ደረሰ ። ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባት ብዙም አላሳሰባትም ።

መስፍን ጠቃሚ መረጃ ሰጥቷት ነበር ። የፍተሻው ሥነ-ስርዓት እንዳለቀ ለውጭ አገር ዜጎች በተመደበው በር በኩል ስትወጣ የሆነ ነገር ስሜቷን ሰረቃት ።

ምዕራፍ ሰባት

« ሕሊና ! ሕሊና » የሚል ድምጽ ስትሰማ እንደመባነን አለች ። መስፍን ነበር ። ታላቅ ደስታ እየተሰማት ተቃቅፈው ተሳሳሙ ። ሕሊና የደስታ ፣ የናፍቆትና የተስፋ ሣቅ የተዋሃደው ዕንባ እያነባች ከመስፍን ጋር ደጋግመው ተቃቀፉ ። መስፍን በአለባበስም ሆነ በአቋሙ ተለዋውጦ ነበር ያገኘችው ። በዒሙና በራስ ፀጉሩ ላይ የነበረው ሽበት ጨርሶ ጠቁሯል ። ቆዳው ከጠይምነት ወደ ቀላት ተለውጧል ።

መልካም ቃና ያለው ሽታ ተላብሷል ፣ የለበሰው ጥቁር ሱፍ፤ የተጫመተው ጫማ ከረባቱና ሸሚዙ ሕሊና ከዚህ በፊት ካየቻቸው ሁሉ በዓይነቱ የላቀ ነበር ። መስፍን እጇን እንደያዘ ወደ አንድ ሸንጣም ረጅም ባለአራት በር ሌሞ መኪና ወሰዳት ። አንድ ዩኒፎርም የለበሰ ሹፌር ከፈተላቸው ። መስፍን ደግፏት መኪናው ውስጥ ገባች ።

ሕሊና የመኪናው የውስጥ ስፋትና ሁኔታ የጠበቀችው ፣ ወይም የገመተችው ዓይነት አልነበረም ። ከመጠየቅ መቆጠብ አልቻለችም « ምንድነው » ? ብላ ጠየቀች ግራ በመጋባት ። መልስ አልሰጣትም ። ደግማ መጠየቁን ፈርታ አፏን ከፍታ መስፍን የሚሰራውን ተመለከተች ። መስፍን መቀመጫው ላይ ያለውን ቁልፍ መሳይ ሲነካ ፊት ለፊት የነበረው ወንበር ተገልብጦ ወደ ቴሌቪዥንነት ተቀየረ ። ወድያውኑ ፊልም ማየት እንደጀመሩ መስፍን ጎኑ የነበረውን የግድግዳ ሳጥን ከፈት አድርጎ ፣ በተሽከርካሪ መደርደሪያ ላይ የተቀመጠውን የመጠጥ ዓይነት በመጠቆም ፣

« ምን ልታዘዝ » አላት ።

« በጣም ነው የተለወጥከው » አለችው በፈገግታ

« ፎር ጉድ አር ባድ »

« በጣም ነው ያማረብህ »

« ሳንክ ዩ »

መስፍን የሕሊናን መምጣት አስመልክቶ ከጓደኞቹ ጋር ትንሽ ድግስ መሳይ አዘጋጅቶ ነበር ፡፡ የሀገር ባህል ሙዚቃ ፣ ምግብና መጠጥ በየዓይነቱ ተዘጋጅቶ ፣ የቅርብ ሴትና ወንድ ጓደኞቹ በቤቱ ውስጥ ጉድ ጉድ እያሉ ጠበቋአቸው ፡፡ ሕሊናን ለመቀበል ከመጡት ሰዎች ውስጥ ህፃናት ፣ አዋቂ ፣ ጥቂትም ቢሆን አዛውንቶችን ያካተተ ነበር ፡፡ በዚህ ባዕድና ሩቅ ሀገር የዚህን ዓይነት ኢትዮጵያዊያን ስብሰብ መኖር ፣ የመኖር ተስፋዋን ብሩህ አድርጎት ብቸኛ አልሆንም ስትል ራሷን አፅናንታ ደስ ብሏት ከሁሉም ጋር ተዋወቀች ፡፡

አበበ ፣ ገረመው ፣ ዘስላሴ ፣ መልካሙ ፣ ፋጡማ ፣ የምስራች ፣ አጥናፉ ፣ ዩኒ ፣ ቴዲ ፣ ሣራ ፣ ተርማን ፣ ሚሚ ፣ ራሄል ፣ አንደርሰን . . . ሕሊና በጥቂቱ በቤቱ ውስጥ የተዋወቀቻቸው ሰዎች ነበሩ ፡፡ ከሙሉጌታ ቤተሰቦች ጋር ይበልጥ ተዋወቀች ፡፡ ባለቤቱ ዲና አንደርሰን አባቷ ነጭ አሜሪካዊ ሲሆን እናቷ ደግሞ አፍሪካዊ አሜሪካዊት ናት ፡፡ ሄለንና ማትያስ የሚባሉ የአስራ ሦስትና የአስራ አምስት ዓመት ልጆች አሏቸው ፡፡ ሙሉጌታ ግብዣው ላይ በሥራ ምክንያት አልተገኘም ነበር ፡፡

ከዲና ጋር አቅሟ በፈቀደው መጠን ባካበተችው እንግሊዘኛ ለመነጋገር ሞከረች ፡፡ የዲና አነጋገር ለሕሊና ጆሮ ፈጣን በመሆኑ አልፎ አልፎ የዲና ጥያቄ ወይንም አባባል ትርጉም የሚያገኘው አጠገቧ በተቀመጠው መስፍን አማካኝነት ነበር ፡፡ ዲና ሀገር ቤት ስለአሉት የሙሉጌታ ዘመዶች ሥም እያነሣች ጠየቀች ፡፡ ሄለንና ማትያስ አማረኛ ስለማይገባቸው አጎታቸው የሚነግራቸውን በመስማት በውይይቱ ለመሳተፍ ሞከሩ ፡፡ በቤቱ ውስጥ ከተሰበሰቡት ሰዎች መሀከል አንድ በሕሊና ዕድሜ የምትገኝ መልከ መልካም ሴት

ከሕሊና ጎን በመቀመጥ « ሕሊና የደከመሽ ትመስያለሽ ፤ ረጅም መንገድ ነው የመጣሽው ፣ ማረፍ ከፈለግሽ » አለቻት ፡፡

« ግድ የለም እስከዚህም አልደከመኝም ፡፡ »

« ራሄል እውነቷን ነው ፡፡ ማረፍ አለብሽ » አለና መስፍን ወደ መኝታ ክፍል ወሰዳት ፡፡ መስፍን አካባቢውን አስተዋውቆ ፣ የመኝታ በሩን በር ዘግቶ ወደ እንግዳ ክፍል ተመለሰ ፡፡ ሕሊና የቤቱን ንፅህና አደነቀች ፡፡ የሽንት ቤቱን ውበት ፣ ከጥርስ መፋቂያ እስከ የፊት ሳሙና ፣ ቅባትና ሽቶዎች የነበረውን የዓይነት ስውጥ ተመስጣ ተመለከተች ፡፡ ፊቷን ውሀ አስነክታ በፎጣ አድርቃ ፡፡ ወደ መኝታ ቤት ገብታ አልጋው ላይ እንዳረፈች ድካሟ ተሰማት ፡፡ የምታየውን ውብና ድንቅ ነገር እያሰበች በተጋደመችበት ዕንቅልፍ አሸነፋት ፡፡

ከዕንቅልፏ የቀሰቀሰቻት ራሄል ነበረች ፡፡ « ኦ ማይ ጋድ ፤ በጣም ደክሞሻል ማለት ነው ፡፡ ተነሺ የራት ሰዓት ደርሷል እንግዶች ይጠብቁሻል ፡፡ » ሕሊና ደጋግማ ተንጠራርታ ፤ ዓይኖቿን እያሻሸች አፋሸከች ፡፡

« ስንት ሰዓት ሆነ ፤ ነጋ እንዴ ? » አለቻት ፡፡

« እየመሸ ነው ፡፡ ከዚህ የታይም ለውጥ ጋር አደስት እስከምታደርጊ ኢት ቴክስ ኤ ዋይል » ራሄል ቀልጠፍ ብላ የሽንት ቤቱን መብራት አበራች ፡፡

« ሻወር ውሰጂና ልብስሽን ለውጭ ፤ ይቀልሻል ፡፡ »

ራሄል ወደ መታጠቢያው ክፍል ገብታ የውሃውን ሙቀት በእጇ ለካች፡፡ ስትመለስ ሕሊና ሻንጣዋን ለመክፈት በትግል ላይ ነበረች ፡፡

« አይዞሽ ትለምጂዋለሽ ፡፡ እኔ ፈርስት ታይም ስመጣ እንደዚሁ ግራ ገብቶኝ ነበር ፡፡ ጀስት ቴኪኢት ኢዚ ሌላው ሁሉም ነገር ቀስ በቀስ ይመጣል ፡፡ » አለችና ሻንጣ በመክፈት ረዳቻት ፡፡

ሕሊና የራሄል አድራጎት እየገረማት ወደ ሻወር ገባች ። ይሆናል ስትል ለማሰብ ሞከረች ። የራሄል ቀልጣፋነትና ግልፅነት ለኢትዮጵያውያን አዲስ እንደሆነ ስታስብ ከበቡሽ ታወሰቻት ። ከበቡሽ በትምህርት ቤት አካባቢ በነበረችበት ወቅት ከራሄል ጋር በብዙ ነገራቸው እንደሚመሳሰሉ ገመተች ። ሕሊና ከሻወር እንደወጣች ልብሷን ለብሳ ፀጉሯን ስታበጥር ራሄል የሕሊናን ልብስ ቁም ሳጥን ውስጥ በማደራጀት ላይ ነበረች ።

« ይሄ በጣም የሚያምር ልብስ ነው መቼም ውድ መሆን አለበት » አለቻት ራሄል አንድ የሀበሻ ጥበብ ቀሚስ በእጆቿ ይዛ አገላብጣ እየተመለከተች ።

« ያምራል አይደል ? ግን የሚገርምሽ በጣምም ውድ አይደለም ። ወደ ሦስት መቶ የኢትዮጵያ ብር ነው የከፈልኩት » አለች ሕሊና ፊቷን ከመስታወቱ ሳታዞር ፀጉሯን እያበጠረች ።

« አ - ያ - ሦስት መቶ ብር ብቻ » አለች ራሄል በመገረም።

« አዎ ሦስት መቶ ብር ብቻ ነው ። ከወደድሽው ልትወስጂው ትችያለሽ እኔ ሌላ አለኝ » አለቻት ።

« ኦ ኖ ምን ማለትሽ ነው ? ለምን ትሰጭኛለሽ ። አሜሪካን ሀገር በነፃ መስጠት የለም ። ባይሆን ትርፍ ከለሽ እገዛሻለሁ ። »

ሕሊና ግማሽ ልብሷን በማውለቅ ላይ እንዳለች የመኝታ ቤቱ በር ተንኳኳ ።

* * *

መስፍን መታጠቢያ ክፍል እንደገባ ሕሊና ሰውነቷን ለማሳረፍ ሶፋ ላይ ተጋድማ ከራሷ ጋር ሀሳብ ውስጥ ገባች ። አሜሪካ ሀገር መኖሯ ህልም እየሆነባት በተራመደች ቁጥር የምታያቸው አዳዲስ ነገሮች ሀሳቧን በመሻማት ስለ ግል ኑሮዋና ከመስፍን ጋር ስለአላት ግንኙነት በቅጡ እንዳታጤን አደረጓት ። ከመጣች ሦስት ሣምንታት ሆኗታል ። በዚህን ጊዜ ውስጥ ከመስፍን ጋር ጠዋት ከቤት የወጡ የሚመለሱት ሲመሽ ነበር ። አልፎ አልፎም በመስፍን ጓደኞች በሚደረግ የመልስ ጥሪ በመገኘት ለጓደኞቻቸው ያላቸውን አክብሮት በመግለፅ አሳለፉ ።

ሕሊና ለአሜሪካን ኑሮ ካላት ታላቅ አድናቆት ባሻገር የተፈታተናት የአሜሪካን ሀገር ምግቡ ነበር ። ዶሮው ፣ ሥጋው ፣ እንቁላሉ በአጠቃላይ ጣፋጭነት የበዛው ምግብ ከለመደችው ኮስተር፣ ጠንከር ካለው የሀገር ቤት ምግብ ጋር ሊመሳሰልላት አልቻለችም ። በተፈጥሮ የተገኘ ለመሆኑ ተጠራጠረች ። መስፍን ታጥቦ የቤት ልብሱን ለውጦ ወደ ሳሎን ሲገባ ሕሊና በፈገግታ ተቀበለችው ።

« ጺምህን ለምን ተላጨኸው ? በጣም ነበር የሚያምርብህ » አለች የቀድሞ ፊቱ መለወጡን አይታ ።

« ለለውጥ ያህል ብዬ ነው » በማለት የተላጨ ፊቱን በእጁ እያሻሸ ፈገግታውን ለገሳት ።

« ራትህን ላቅርብልህ ? » ሕሊና ከተጋደመችበት ተነስታ ወደ ኩሽና ስትሄድ ፣

« አንቺስ አትበይም ? »

« እኔ ቀን የበላሁት እስካሁን አልጎደለም ። »

« ቀን መቼ በላን ? ጠዋት ቁርስ ያደረግነውን ነው ? » መስፍን ለማረጋገጥ ወደ ሕሊና ተመለከተ ::

« የዚህ ሀገር ቁርስ የእኛ ሀገር ምሳ ነው :: »

« ሃኒ እዚህ ሀገር ምግብ ካልበላሽ ጥሩ አይደለም :: አሁን እንኳ በጋ ነው በክረምቱ ወቅት መንቃነቅ አትችይም :: ከአሁኑ መልመድ አለብሽ » አላት ::

« ምግቡ በጣም አስጠልቶኛል :: ከዳቦ በስተቀር ሌላው ነገር ሁሉ አልዋጥልሽ እያለ አስቸገረኝ :: ቢሆንም ለመልመድ እየሞከርኩኝ ነው :: »

« አይዞሽ ትለምጂያለሽ :: አብዛኛው ሰው አዲስ እንደመጣ ይህ ችግር አለበት » አለ መስፍን ጭንቀቷን ከፊቷ ላይ እያነበበ ::

ሕሊና ኩሽና ውስጥ ጉድ ጉድ ብላ የተቻላትን አብስላ እራት አቀረበች :: መስፍን እያደነቀና እያጣጣመ ተመገበ ::

« መቼም ዕድለኛ ነኝ ሃኒ :: ይህን የመሰለ ምግብ መብላት ከተመኘሁ ቆየሁ :: አሁን እውን ሆኖ በራስ ሰው ሲዘጋጅና ሲቀርብ እንዴት ደስ ይላል በማለት ሕሊናን ሳማት ::

« አይ ላብ ዩ » በማለት እጁን ለመታጠብ ወደ ውስጥ ገባ :: ሕሊና ገበታውን አንስታ የተበላበትንና የተጠጣበትን ስሀንና ብርጭቆ አጣጥባ ተራዋን ወደ መኝታ ቤት ገብታ ልብስ ቀይራ ሳሎን ተቀምጦ የቴሌቪዥን ፕሮግራም የሚከታተለውን መስፍንን ተቀላቀለች :: የወቅቱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለአዋቂዎች ብቻ የተዘጋጀ በግልፅ የሁለት ፍቅረኛሞችን ግንኙነት የሚገልጽ ትዕይንት ነበር ::

« አሁን ካልጠፉ ነገር ይህን ሙያ ብለው በቴሌቪዥን ያስተላልፋሉ ? » አለች ሕሊና ትዕይንቱን እየተፀየፈች ::

« ኦ ሃኒ ዋት ኢዝ ባድ አባውት ዚስ ? ይኼ እኮ ማንኛውም ጤናማ ሰው የሚያደርገውና የሚፈፅመው ነው :: መሳሳምና መተሻሸት ምን ነውር አለው ? » ሕሊናን በጥያቄ መልክ አያት ::

« ለሁሉም ቦታ አለው :: የሰው ልጅ የሚሠራውና የሚያደርገው ነገር ሁሉ አደባባይ መውጣት አለበት እንዴ ? » በማለት የቴሌቪዥኑ ትዕይንት እስከሚያልፍ ላለማየት ወሰነች ::

« እባክሽ ቁጭ በይ ሃኒ ፣ ፕሮግራሙ ካልጣመሽ እንደዚሁ እናውራ » አለ መስፍን ለመሄድ ስትቃጣ የሌሊት ልብሷን ይዞ እየጎተታት ::

« ስለዚህ ነገር አሁን ማውራት አልፈልግም :: » በእጇ ወደ ቴሌቪዥኑ እያመለከተች « ሌላ ምን ወሬ አለ ? » ጥያቄዋን ሳትጨርስ መስፍን በተጋደመበት ሶፋ ላይ ቁጭ አለች ::

« ጊዜ አግኝተን አልተጫወትንም :: እንዴት ነው አሜሪካን ተስማማሽ ? » ከዓይኖቿ ለማንበብ በመሞከር ዓይን ዓይኗን ተመለከተ ::

« አሜሪካን ጥሩ ሀገር ነው :: በሥልጣኔያቸው በጣም መጥቀው ሄደዋል ፣ ሀብታሞች ናቸው :: መቼም የእኔም ሀገር እንዲህ በሆነልኝ ብሎ ያስመኛል :: ከምግቡ በስተቀር ብዙ ነገር ተስማምቶኛል :: አንተስ ምን ይመስልሃል ? የለመድከ አይመስልህም ? » ሕሊና መስፍንን ድንገት ጠየቀችው ::

« ሃኒ ኦፍ ኮርስ ኢት ኢዝ ዋን ሀንድረድ ፐርሰንት ሳክሰስ » በማለት ትከሻዋን መታ መታ አደረገ ::

« ለዚህ ሁሉ ስለ አበቃኸኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው :: ከዚህ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ለመግባት እዘጋጃለሁ » አለች ሕሊና ::

« ቴክ ዩር ታይም :: ትምህርት ቤት አሁን ዝግ ስለሆነ ጊዜው ሲደርስ ትመዘገቢያለሽ :: እስከዚያው ሀገሩንና ሰውን መልመድ ነው » አለ ምሥጋናዋን ከተቀበለ በኋላ ::

« ራሄል ቋንቋ ለማስተማር ምዝገባ እየተካሄደ ነው ፣ መጥቼ እወስድሻለሁ እዚሁ ቅርብ ትምህርት አለ ነው ያለችኝ :: ሥሙን እንኳ ጠርታልኛ ነበር » አለች ::

« ኦ ሃኒ ፤ የራሄልን ነገር ሲሪየስ አድርገሽ አትውሰጂ ። እርሷ የምትናገረውን አታውቅም ። ኢግኖር ኢት » በማለት በብስጭት ራሱን በእጆቹ ዳበሰ ።

« ምነው ያማታል እንዴ ? » ሕሊና በመስፍን አባባል ተደናግጣ ጠየቀችው ። እርሷም የጠረጠረችው ነበራት ።

« ኦ ኖ ሃኒ እንደእርሱ ማለቴ ሳይሆን መቼም እዚህ ሀገር የቆየ ሰው ዞር ያላለበት ማን አለ ። ከልቸር ሾክ ያልበታተነውና ያላቆሰለው ጥቂቱን ነው ፤ ማለቴ ከአደግንበትና ከነበርንበት ወደ አዲሱ ባህል ስንገባ ብዙ ውጣ ውረድ ስላለፍን ሳምታይምስ የምንለውን እንኳ አናውቅም ። » መስፍን ከራሄል አልፎ ሁኔታውን በማጠቃለል ተናገረ ።

« ሰውጥ ስትል ባህል ፣ አሰባበስ ፣ አበላል ፣ አነጋገር ፣ አኗኗር . . . አልገባኝም ? » ሕሊና በጥሞና መስፍን እንዲያስረዳት ጠየቀች ።

« ያልሽውን ሁሉ ያጠቃልላል ። ሆኖም ከዚያም አልፎ ሌሎች ብዙ ነገሮችን ይመለከታል ። እንደህ በቀላሉ ማስረዳት የምችለው ነገር አይደለም ። እንግዲህ እዚህ ከመጣሽ ለወደፊቱ በየቀኑ አንችንም ያጋጥምሻል ። ያኔ ሁኔታውን ኢንዲቴል እናወራለን። አሁን በቀላሉ ይኼ ነው ብዬ ባወራልሽ ለወደፊቱ ለሚያጋጥምሽ ሁሉ መልካም አስተሳሰብ አይኖርሽም ። » መስፍን የቴሌቪዥኑን አንቴና አስተካክሎ ተመልሶ ሶፋው ላይ ተቀመጠ ።

« መቼም አሁንም ይኼ ለውጥ የሚባለው እንዴት አድርጎ የሰውን ሁኔታ እንደሚነካ ለማወቅ እፈልጋለሁ ። ብዙ ጊዜ ሀገር ቤት ያሉ ሰዎች ውጪ ደርሰው ሲመለሱ ስለነበሩበት ሀገር ሲያወሩ ከባድ ነው ። ሁሉ ነገር አለ ግን የባህሉ ግጭት ከፍተኛ በመሆኑ መኖር አልቻልንም » ይላሉ ። እስካሁን እንዳየሁት ከሆነ ይህን ያህል

የሚያስመርር አይደለም ። » አለች ሕሊና ጥያቄውን በሀሳብ መልክ ለመስፍን በማካፈል ።

« ሃኒ ዶንት ሃሪ ፤ ትደርሺበታለሽ ። ለካስ ከልቸር ሾክ ማለት ይኼ ነበር ? » በማለት ራስሽ ይገባሻል ። እኔ መቼም አሁን ይኼ ነው ብዬ አልነግርሽም ። እሱን ያለፈ ሰው እዚህ ሀገር የመኖር ዕድሉ ሠፊና ብሩህ ነው ። ከባዱ ያቺን ወቅት በትዕግሥት ለማለፍ መቻል ነው » አለ ድካም በተጫጫነው ድምፅ ። ሕሊና የመስፍንን መዳከም በመገንዘብ የሳሎኑን መብራት አጥፍታ ወደ መኝታ ቤት ገባች ። መስፍን ጥቂት የቴሌቭዥን ዜናዎችን አዳምጦ ሕሊናን ተከተላት ።

ሕሊና ለመጀመሪያ ጊዜ ለብቻዋ ቤት ውስጥ ሥራ በመሥራት ጊዜዋን አሳለፈች ። መስፍን ወደ አዲሱ የሥራ ቦታው ሄዶ የሚመለሰው መሽትሽት ሲል ነው ። የቤት ሥራዋን ፈፅማ በሻንጣ ውስጥ የቀሩትን የሀገር ቤት ዕቃዋን ቦታ ቦታ ማስያዝ ጀመረች ። ሁለቱ ትላልቅ ሻንጣዎች ውስጥ የነበሩትን ዕቃዎቿን በታትና ለእርሷ በተመደበላት ቁምሣጥን ስታስቀምጥ ለቤቱ ያመጣችውን ባህል ነክ ጌጦች በየግድግዳው ለጣጠፈች ። በእጅ ቦርሳዋ ውስጥ የነበሩትን ወረቀቶች ስትበታትን ። ከውስጡ በቁም የተነሳችውን ፎቶግራፍ አውጥታ ወደ ደረቷ አስጠግታ አቅፋ ደጋግማ ሳመችው ።

በእርግጥ ፎቶግራፉ የእራሷ በመሆኑ አልነበረም አቅፋ የሳመችው ። ፎቶግራፉ የአባቷ መጥረቢያ ነበረበት ።

« አባዬ ይቅርታ ያወረስከኝን መጥረቢያ ከራሴ ጋር ይዤ ለመምጣት አልቻልኩም ። »

ሕሊና ሀሳቧን ወደ ሀገር ቤት መለሰች ። የአባቷን መጥረቢያ በአደራ የተወችው ለወ/ሮ በላይነሽ ነበር ። የመጥረቢያውን ምስጢር

በወጉ የሚያውቁ እርሳቸውና ያሬድ ብቻ ናቸው ። ወ/ሮ በላይነሽ የእርሷንና የአባቷን ፍቅር በህይወት የተመለከቱ ፣ የተካፈሉ ናቸው።

« እማማ በላይነሽ እናቴ ናቸው ። የእኔ ማለት የራሳቸው ነው » በማለት እራሷን ለማረጋጋት ሞከረች ። ከቦርሳዋ ውስጥ ፓስፖርትና የጋብቻ ወረቀትም ነበር ። በቅጡ ሰብስባ አልጋው አጠገብ ካለው መለስተኛ » ሳጥን አስገብታ ቆለፈች ። በአጋጣሚው የኢትዮጵያ ብር ፣ ሳንቲሞችና ቁርጥራጭ ወረቀቶችን ለየች ።

« ለሕሊና » የሚለውን ፖስታ ለመወርወር ከቃጣች በኋላ ማን እንደሰጣት ለማስታወስ ሞከረች ። ፖስታውን ይዛ ጥቂት አሰላሰለች እና ከፈተችው ። ከውስጡ ሦስት ባለ መቶ ዶላር ኖት ከአንድ ገፅ ደብዳቤ ጋር አወጣች ። በመገረም ስሜት ተውጣ ደብዳቤውን ገልጣ ማንበብ ጀመረች ።

« ሠላም ሕሊና ! መቼም ይህን ደብዳቤ ስታነቢ ሳይገርምሽ አይቀርም ። መለያየት ካደረግንበት ጊዜ ጀምሮ ጤንነትሽን በእማማ በላይነሽ በኩል ሰምቻለሁ ። ይህን ዕድል ማግኘትሽን ስሰማ ከልብ የመነጨ ደስታ ነው የተሰማኝ ። ስለአለፈው ህይወታችን ሳላነሳ የዘነጋሁበት ቀን በጣም ጥቂት ፣ የተወሰኑ ናቸው ። የተለያየንበትን ቀን እየረገምኩ የምንገናኝበትን ቀን እያለምኩ እስከዛሬ ቆየሁ ። ከሀገር ለቀሽ ለመሄድ መነሳትሽን ስሰማ በእኔ በኩል አንቺን ለማግኘት ያለኝ ተስፋ ቢጨልምም የአንቺ የወደፊት ተስፋ ብሩህ በመሆኑ ደስታዬ ከመጠን ያለፈ ነው ። ሕሊና ! ለአንቺ ያለኝ ፍላጎት ከተገናኘ ንበት ቀን ጀምሮ እስካሁን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም ። ባይገርምሽ ያቺ ቀን ለኔ የማትረሳ ናት ምክኒያቱም ሁሌ በደለኛነት ይሰማኛል በወቅቱ ራሴን በጣም ጠልቼው ነበር ። ሕሊ . . የወደዱትን ማጣት የተመኙትን መነፈግ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ የደረስበት ነው የሚያውቀው ። መወሰን አቅቶኝ በልንገራት አልንገራት ውስጥ ሲታመስ ፣ ሲንገላታ በለቀቀን የኖርኳቸው ቀናቶች ሲታሰቡኝ ሀዘኔ እጥፍ ነው። ወንድምኔቴን እምነሽ በተቀመጥሽበት ሠአት ባላለብሽው እና ባልገመትሽው ሁኔታ ፍቅሬን መግለፄ በእርግጥም ጥፋተኛ ነኝ ። ርቀሽኝ ስትሄጂ ይቅርታሽን ሳላገኝ በመሄድሽ ሁሌም ልቤ ይደማል እዝናለሁ ። መቼም ሕሊዬ ይቅርታሽን እንደማትነፍጊኝ ተስፋ አለኝ ። አሁንም እንደ አንቺ ፍላጎት ወንድምነቴን ለመቀበል እራሴን በማስታመም ላይ ነኝ ። አልዋሽም ብዙም አልተራመድኩም ። እስቲ እንግዲህ ጊዜና ርቀት ይሽረው እንደሆን በዚህ ልሞክረው ።

« ሕሊና የዚህ ደብደቤ መሠረተ ሀሳብ ይቅርታ ለመጠየቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ ለመኖር ማገገሚያ ይሆን ዘንድ ደብዳቤሽ እንዳይለየኝ ለማለት ነው ። ለማንኛውም ለእማማ በላይነሽና ለእማሆይ ብዙም አታስቢ ። እኛው ዘንድ ስለአሉ የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ እሞክራለሁ ። አደራ ራስሽን ተንከባከቢ ። በተረፈ ይህችን አነስተኛ ስጦታ አሜሪካን ስትገቢ ለታክሲ ተጠቀሚበት ።

ያንቺው ናፋቂ ያሬድ ።

ሕሊና የአነበበችውን አላመነችም ፡፡ ሀዘንና ደስታ የተቀላቀለበት ዕንባዋን አነባች፡፡ ደብዳቤውን በሁለት እጆቿ እንደያዘች ተከዘች ፡፡ በመጨረሻው ገፁዋ ላይ ያሬድ ለአፍታ ያህል ያደረገውን የርቀት ስንበት በዓይነ ሕሊናዋ ቃኘች ፡፡

« አይ ጋሼ ያሬድ ! አይ ጋሼ ያሬድ ! » ስትል ራሷን ነቀነቀች ፡፡ ስለ ደግነቱ ፣ ጨዋነቱ ፣ ግልፅነቱና ለሷ ያለው ስሜት አለመቀዝቀዙ ፣ እራሱን በጥፋተኝነት ስሜት አቅርቦ ይቅርታ በመጠየቁ አዘነች ፡፡ በትካዜ ባህር ተውጣ ፣

« ለምን እንደዚህ ይሆናል ? » በማለት ራሷን ጠየቀች ፡፡ ለአንድ አፍታ ያሬድን በመስፍን ለውጣ ለማየት ሞከረች ፡፡

« በስመአብ ! » አለች ፡፡ ሀሳቧ እውን መስሏት ዘገነናት ፡፡ ያሬድን በያሬድነቱ እንዳለ ይዞ መኖሩን መረጠች ፡፡ ለደብዳቤው መልስ ለመስጠት ሀሳቧን በማደራጀት ላይ እንዳለች መስፍን በሩን ከፍቶ ገባ ፡፡

*   *   *

ሕሊና በትሩማን ኮሌጅ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርቷን መከታተል ከጀመረች ሁለት ወራት ሆናት ፡፡ እንግሊዘኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ የአሜሪካን ነዋሪዎች የሚሰጠው ይህ ፕሮግራም ለሕሊና አስቸጋሪ አልነበረም ፡፡ የሕሊናን የትምህርት ቅልጥፍና የተረዳው ሙሉጌታ ጥረቷን ለማበረታታት ምክሩን ለገሠ ፡፡ በየጊዜው ስለ ትምህርት ያላትን ጥያቄ በማብራራት ሳይሰለች ዕድገቷን መከታተል ቀጠለ ፡፡ ሙሉጌታ ለሕሊና ትምህርት ብቻ ሳይሆን ሥራንም በሚመለከት እንደመረጃ ማዕከል ሆኖ አገለገላት ፡፡

« እኔ እዚህ ሀገር ስመጣ መምህር ነበርኩ ፡፡ ከቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ በጂኦግራፊ ተመርቄ ሀገር ቤት ሦስት ዓመት

ከሰራሁ በኋላ ወደ እዚህ መጣሁ ፡፡ ሕሊና አይዞሽ ! መምህር ለነበረ ሰው የዚህ ሀገር ትምህርት ይቀለዋል » በማለት አበረታታት ፡፡ ቀጥሎም « . . . እየሠራሽ መማር ትችያለሽ ፡፡ ለማንኛውም ሠርትፊኬትሽን ለአፕሬዛል ለምን ለፕሪንግፊልድ አትልኪም ? »

« ጋሼ ሙሉጌታ ይሆናል ብለህ ነው ? » ሕሊና ችሎታዋን በመጠራጠር ሙሉጌታን ጠየቀችው ፡፡

« ከሆነ ይሆናል ፡፡ ካልሆነ ደግሞ ምን ታጪያለሽ ? ቢያንስ ቢያንስ ሁኔታውን ለማሟላት የሚያስፈልግሽን ይጠቁምሻል » በማለት የሕሊናን ፍላጎት ለማነሳሳት ሞከረ ፡፡

« እሺ እስቲ እሞክራለሁ ፡፡ግን አድራሻውን ከየት አገኛለሁ?»

« እኔ አመጣልሻለሁ ፡፡ ፎርሙን ሞልተሽ ለመስፍን ብትሰጪው ይልክልሻል » በማለት ሙሉጌታ ወደ መስፍን ተመለከተ፡፡

« ኖ ፕሮብሌም እልክልሻለሁ » መስፍን ታላቅ ወንድሙ የተናገረውን ተቀበለ ፡፡

ሕሊና የአሜሪካንን ኑሮ በመታገል ላይ እያለች ከትምህርቱ አልፎ ወደ ሥራ ዓለም መግባቱን በጣም ፈራች ፡፡

« ሥራ ቢሠራስ ምን ዓይነት ሥራ ይገኛል ? እኔ የተማርኩት ማስተማር ፤የሰራሁት በመምህርነት ፤ በእኔ ትምህርትና የሥራ ልምድ መጠን ምን ልሆን እችላለሁ ? » ሕሊና በሀሳቧ ጥያቄዎችን ብታብሰለስልም መልሱን ማግኘት አልቻለችም ፡፡

« ሁኔታውን እንደአመጣጡ መቀበል ነው እንጂ አማራጭ የለኝም » በማለት ነገሮችን በደፈናው ለመተው ሞከረች ፡፡

« ጋሼ እዚህ ሀገር ማስተማር አይከብዳትም ብለህ ነው ? » በማለት መስፍን ወንድሙን ጠየቀ ፡፡

« መክበድ ስትል ? » ሙሉጌታ ጥያቄውን እንዲያብራራ ጠበቀ ፡፡

« ጋሼ ያኔ ስታወራ አንተ የነበርክበት ትምህርት ቤት ተማሪዎቹ አስቸጋሪዎች ናቸው ። እንኳን ለእኛ ሀገር መምህራን ቀርቶ ለሀገሬው መምህራኖችም በጣም ያስቸግራሉ ስትል ነበር » አለ መስፍን ጥያቄውን አብራርቶ ። « መስፍን ! እዚህ ሀገር የማይከብድ ሥራ ምን አለ ? ሁሉም ነገር ከባድና ጥረት የሚጠይቅ ነው ። ዲግሪው ይለያይ እንጂ ሕሊና ከመምህርነት ውጪ ሌላ የሥራ ልምድ የላትም ። ፓርኪንግ ወይም ቤቢ ሲት ካልሆነ ፤ እሱም ቢሆን የራሱ የሆነ ችግር አለው ። »

ሕሊና የሁለቱን ንግግር ለማቋረጥ አልሞከረችም ። መስፍን ያለበችውን ስለጠየቀ በጥሞና የሚናገሩትን ማዳመጥ መረጠች ። ሕሊና የሚያስፈልጋት ወጣ ብላ የሥራውን መስክ ማየትና መለማመድ ነው ። ቀላልና ከባድ ምርጫ የሚመጣው ሁሉንም ስታውቅ መሰለኝ ። » ለሁሉም የመጀመሪያው የት አለ የሚለው አባባል ወቅታዊ መሆኑን በማሰብ ከባዱንም ቀላሉንም ማየቱ ደግሞ ራስን ለማመዛዘንና አካባቢዋን ለመቀበል እንደሚረዳት አብሰሰለች ።

« ጋሼ ያልከው እውነት ነው ። ሌት አስ ሆፕ ፎር ዘ ቤተር»

መስፍን በታላቅ ወንድሙ አባባል ተስማማ ። ሕሊና የወንድማማቾቹ ንግግር እንዲቀጥል ብትፈልግም ሁለቱም ጉዳዩን በማንጠልጠል አቋርጠው ወደ ሌላ አርዕስት ተሸጋገሩ ። ሙሉጌታ ቤት ስለተዘጋጀው ግብዣና ስለተጠሩት እንግዶች ዝርዝር ማውራት ጀመረ ። በዝርዝሩ ውስጥ ሙሉጌታ ራሄልን መጋበዙን ገለፀ ። መስፍን የራሄልን መጋበዝ በደስታ አልተቀበለውም ።

« ጋሼ ደግሞ ዋት ጉድ ካን ሺ ቢ ፤ ለምን ትጠራታለህ » በማለት ስሜቱን ገለፀ ።

« አንተ በቤትህ የምትፈልገውን ጋብዝ ። እኔም በቤቴ የፈለኩትን መጋበዝ ምርጫዬ ነው » አለ ሙሉጌታ በከፊል ቁጣ ቃል።

« ማለቴ እኮ . . . »መስፍን ማለት የፈለገውን አልጨረሰም።

« መስፍን የምትለው ገብቶኛል ። ኢት ኢዝ ኦል ቢሃይንድ፣ ዩ ኒድ ቱ ፎርጌት ኤንድ ፎር ጊቭ » ሙሉጌታ ወደ ሕሊና ተመለከተ። ግራ የተጋባችው ሕሊና ስለምን እንደሚነጋገሩ አላወቀችም ።

« ይቅርታ ነገሩ አንቺን አይመለከትም ። አንቺ በማታውቂው ነገር ፊትሽ ላይ መጨቃጨቃችን አግባብ እንዳልሆነ አውቃለሁ ። »

የሙሉጌታ የይቅርታ ጥያቄ የሕሊናን በሀሳብ መዋጥ ባያስቀረውም ከሁለቱ ወንድማማቾች ክርክር ፤ ቀደም ሲል ካየችው የራሄል ሁኔታና መስፍን ስለ ራሄል ከነገራት ተነስታ ሀሳብ ውስጥ ገባች ።

« ምንድነው ምስጢሩ ፤ መስፍን ራሄል ላይ እንዲህ ዓይነት መጥፎ አመለካከት እንዲኖረው ያደረገው ? ለምን መስፍን ከራሄል ጋር እንዳልገጥም ይከላከላል ? ሙሉጌታስ ለምን ለራሄል አገዘ ? » ስትል አሰበች ። ለጥያቄዋ መልስ ለማግኘት ብትጥርም ብዙ መራመድ አልቻለችም ።

« ጋሼ ደግሞ እኔ ያላሰብኩትን ነው ዝም ብለህ እንዳመጣልህ የምትናገረው ። በል በቃህ እዚህ ላይ እንተወው ። »

መስፍን ንግግሩ እንዲቀጥል አልፈለገም ። ራሱን እያሻሸ ብስጭቱን በማርጎምጎም ገለፀ ።

« ማይ ሚስቴክ ! እሺ ትቼዋለሁ ። . . . « ሌላ ጨዋታ አምጡ ። »

ሙሉጌታ ያደፈረሰውን ሠላም መልሶ ለማምጣት ጥረት ቢያደርግም ሕሊና ሁለቱን ወንድማማቾች ትታ ወደ መኝታ ቤቷ አመራች።

* * *

« በጣም ለምናፍቃችሁ ውድ እናቴ እማማ በላይነሽ :: ውድ አክስቴ እማሆይ አባይነሽ :: ከተለያየንበት ቀንና ሰዓት ጀምሮ ለጤንነታችሁ እንደምን ሠንብታችኋል :: እኔ እግዚአብሄር ይመስገን በጣሙን ደህና ነኝ :: ባለፈው ጊዜ ለከበቡሽ ስልክ ደውዬ መልዕክት እንድታደርስልኝ ነግሬአት ነበር :: በሠላም መድረሴንም ሳትነግራችሁ እንደማትቀር ተስፋ አለኝ:: ውድ ዘመዶቼ ፣ ከእናንተ ተለይቶ ርቆ መኖር በጣም ይከፋል :: ሆኖም እዚህ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስላሉ በእነርሱ እፅናናለሁ ::

አክስቴ እማሆይ እንዴት ናቸው ? ከህመማቸው እያገገሙ ነው ወይ ? ችግር ካለ ፃፉልኝ :: ስለ እኔ አታስቡ :: ሀገሩ በጣም ተስማምቶኛል :: ትምህርቴንም እየተማርኩ ነው :: ከሰሞኑ ደግሞ ሥራ ሳልጀምር አልቀርም :: መስፍን በሁሉም ነገር ያግዘኛል ፤ በጣም ጥሩ ሰው ነው ::

« እማማ በላይነሽ :: ጋሼ ያሬድ ወደ እዚህ ስመጣ አይሮኘላን ማረፊያ መጥቶ ነበር :: ደብዳቤ በሰው በኩል እዚያው ቦሌ እያለሁ ልኮልኛል :: መቼም በጣም ነው የተሰማኝ :: ለማንኛውም ይህን ደብዳቤ ስፅፍ ለእርሱም እፅፍለታለሁ :: በደብዳቤው ላይ እየመጣ እንደሚጠይቃችሁ ነግሮኛል :: እማማ በላይነሽ እደራ ጤንነታችሁን ጠብቁ :: አክስቴም ሀኪም ቤት እንዲሄዱ ምከሯቸው :: ለማንኛውም

የገንዘብ ችግር ካጋጠማችሁ ከበቡሽን ጠይቁ :: ደብዳቤ ለመላክ ከፈለጋችሁ ከበቡሽ ስትመጣ ፅፋችሁ ብትሰጧት ትልክልኛለች :: እማማ በላይነሽ በተረፈ በሚቀጥለው ደብዳቤ እስከምንገናኝ አምላክ በሠላም ጠብቆ ያቆየን :: »

የመጀመሪያውን ደብዳቤ ፅፋ ከጨረሰች በኋላ የሚቀጥለውን ለመፃፍ ራሷን አዘጋጀች ::

« ሠላም ጋሼ ያሬድ :: እንደምን ሠንብተሃል ? . . . » ሕሊና መፃፏን አቁማ ዐረፍተ ነገሩን ለራሷ አነበበች :: አልወደደችውም :: ቀዳ ጣለችው :: ደብዳቤውን እንዴት መጀመር እንዳለባት አሰበች :: በጣም ቀዝቃዛ ደብዳቤ በጣምም ሞቅ ያለ ሠላምታ ለመፃፍ አልፈለገችም :: የመጀመሪያ ደብዳቤዋ እውነተኛ ስሜቷን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ተጠራጠረች :: ስለ ራሷ ብዙ ማውራት አልወደደችም :: ሀሳቧን ሳትቋጭ ደብዳቤውን ለመጀመር ብዕሯን አስተካከለች ::

« በጣም ለምናፍቅህ ወንድሜ ጋሼ ያሬድ :: ለጤናህ እንደምን ሠንብተሃል ? እኔ ይኸው አሜሪካ ገብቼ መኖር ጀምሬአለሁ :: ጋሼ ያሬድ የሰጠኸኝን ፖስታ የተመለከትኩት እዚህ ከደረስኩ በኋላ ነው :: እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፣ አመሰግናለሁ :: ቀድሞ ያደረክልኝ ሁሉ አንሶ ይህን ተጨማሪ ውለታ ስትጨምርብኝ በጣም ነው የከበደኝ :: ቁም ነገር አዘል የይቅርታ ደብዳቤህ ደርሶኛል :: የፃፍክልኝን በጥሞና አንብቤዋለሁ :: ጋሽ ያሬድ ለአንተ ይቅርታን የሚነፍግ ልብ የለኝም :: እራስህን ልትወቅሰውና ልትኮንነው ፣ ጥፋተኝነት ሊሰማህ

አይገባም ። የትላቱን ለትላንት ትተን ዛሬን እንኑራት በኔ በኩል ልቤ ላንተ ይቅርታን ለመስጠት የፀዳች ናት ። መቼም ቢሆን ላንተ ያለኝ ፍቅርና አክብሮት አይለወጥም ። ከምንም እና ከማንም በላይ ይምወድህና የማከብርህ እህትህ ነኝ ። ሀሳብህን ለማስታረቅ የምታደርገው ጥረት አበረታች ነው ። ጋሼ ያሬድ በዚህ ጥረትህ አጠገብህ ሆኜ ብረዳህ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር ። ሆኖም የእግዚአብሔር ፈቃድ አልሆነም ። የመጣሁ ቀን በርቀት ሳይህ በጣም ነው ደስ ያለኝ ። ምንም ያህል ብንራራቅም የሰጠኸኝ ሠላምታ ከልብ የመነጨ መሆኑን አልጠራጠርም ። ጋሼ ያሬድ ! ሀገሩ በጣም ተስማምቶኛል ።

ባለቤቴም ጥሩ ሰው ነው ። በደግነቱ አንተን ያስታውሰኛል ። ትምህርቴንም ጀምሬአለሁ ። በተረፈ ስለ አደረክልኝ ስጦታ ደግሜ ደጋግሜ አመሰግናለሁ። በሚቀጥለው ደብዳቤ እስከምንገናኝ እግዝአብሔር በሠላም ይጠብቀን ። »

ያንተው እህት ሒሊና።

ሒሊና ለከበቡሽና ለአበራ ደብዳቤ ፃፈች ።

« ከበቡሽ ስለምታደርጊው ታላቅ ዕርዳታ በጣም አመሰግናለሁ ። እግዚአብሄር ውለታሽን ይክፈልሽ ። »

« አበራ መቼም እዚያ እያለሁ የምትለው ነገር ሁሉ አሁን እየገባኝ መጣ ። ያኔ አላመንኩህም ነበር። በአጠቃላይ አጠገቤ ሆነህ ስለሰጠኸኝ ምክርና

ድጋፍ ምን ጊዜም ባለውለታዬ ነህ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ። »

የፃፈችው በተለያየ ወረቀት ቢሆንም ፖስታው ግን አንድ ነበር። ለሁለቱም የወረወረችው ጥያቄም ነበር ።

« ከበቡሽ በአንቺና በአበራ መሀከል ምን አዲስ ነገር አለ ? ለውጥ ካለ አደራ ፃፊልኝ እንድዘጋጅበት ። »

ሒሊና ደብዳቤዋን ከጨረሰች በኋላ ለሚቀጥለው የትምህርት ቀን ራሷን ማዘጋጀት ጀመረች ።

ሒሊና በኢሊኖይዝ ስቴት ውስጥ ለማስተማር ስፕሪንግ ፊልድ የላከችው የፈቃድ ጥያቄ ቅፅ የያዘ ፖስታ መጣላት ። በችኩላ ፖስታውን ከፍታ ስትመለከተው ደብዳቤው ለማስተማር ፈቃድ እንደሚሰጣት ገልጾ ከዚህ ቀደም የሰራችባቸውን ትምህርት ቤቶች ዝርዝርና የትምህርት ውጤት ማስረጃዎቿን እንድትልክ የሚጠይቅ ነበር ። ሒሊና ደግማ ደጋግማ ካነበበች በኋላ ከመስፍን ጋር በመማከር ለሙሉጌታ ስልክ ደወለለት ። ሙሉጌታ የተጠየቀችውን በፍጥነት እንድትልክ ነገራት ። የሒሊና ችግር ግን ካስተማረችባቸው ትምህርት ቤቶች ምንም ዓይነት ማስረጃ ይዛ አለማምጣቷ ነበር ። ይህንኑ በመጠቆም ሙሉጌታ እንዲረዳት ጠየቀችው ። ከሙሉጌታ ጋር በሚቀጥለው ቅዳሜ ለመገናኘት ተቀጣጥረው የስልኩን ግንኙነት ጨረሱ ።

ሒሊና የእንግሊዘኛ መደበኛ ትምህርቷን አጠናቅቃ ለከፍተኛ ትምህርት ብቁ የሚያደርጋትን ቅድመ ዝግጅት ጀመረች ። ስፕሪንግፊልድ የላከላት ፈቃድ የተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶችን በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንድታጠናቅቅ ጠቅሶ በተተኪ አስተማሪነት ለመሥራት ብቁ መሆኗን አረጋገጠ ። ከፈቃዱ ጋር ፣ ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆነች ወደ አካባቢዋ የትምህርት ዲስትሪክት

እንድትሄድ ጠቁሞ ስወደፊት በመደበኛ አስተማሪነት ስመቀጠል የተጠቀሱትን መረጃዎች ስታሟላ ስቢሮው እንድትፅፍ የሚል ነበር።

ሕሊና እውነተኛው የአሜሪካን ኑሮ ምን እንደሚመስል ስማወቅ እንድትችል ሁኔታዎች ጋበዟት ። ትምህርት ቤቱ በምትኖርበት አካባቢ ስስሆነ ምንም ዓይነት መጓጓዣ አላስፈለጋትም። በመንገድ ላይ የሚሽኮስኮሱት የስዎች ዓይነት ግን ሠላም ሊሰጣት አልቻሰም ። የስዎቹ አቋማዊ ሁኔታ ፣ አሰባበስ ፣ ሀይጅን ፣ አነጋገር፣ ከስመደችው አካባቢ ስዎች ሁሉ የተለዩ በመሆናቸው በመንገዱ ባስፈች ቁጥር ሠውነቷ ይሳቀቃል ። በአካባቢው የአእምሮ በሽተኞች የሚኖሩበት ሁስት ትላልቅ ህንፃዎች አሉ ።

በእነኚህ ህንፃዎች የሚኖሩት እነዚህ በሽተኞች በመንገድ ላይ፣ በምግብ ቤቶችና በተስያዩ የንግድ መደብሮች ያስገደብ ስስሚዘዋወሩ ስሕሊና የቀን ተቀን የትምህርት ጉዞ ስአንዳአንድ የባህል ትውውቅ መድረክ ሆኑ ። ፍርሃት ፣ ርህራሄ ፣ መሸነፍና ተስፋ መቁረጥ በሕሊና ሀሳብ የሚወጣና የሚወርድ የዕስት ተዕስት ክስተት ሆነ ።

ሕሊና የአእምሮ በሽተኛን በመሸሽ ወይንም መንገድ በመልቀቅ ማስተናገድ እንጂ በሽተኛ በመድሃኒት ድጋፍ እንደማገኘውም ጤነኛ ሰው ሊሆን ይችላል ብላ አትገምትም ። በሽተኞቹን ባየች ቁጥር መንገድ መልቀቅ ምርጫዋ ነበር ። ሆኖም የስው እንቅስቃሴ ስዚህ የሚመች አልነበረም ። ሁኔታው ሰቀቀን ሆነባት ።

መስፍንና ሕሊና በሳሎናቸው ውስጥ ሆነው በመዝናናት ላይ እንዳሉ በአንዱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስስ ቤት አልባ ስዎች የኑሮ ሁኔታ የሚያስረዳ ትዕይንት ተመስከቱ ።

« እንዴት ያሳዝናሉ ? » በማስት መስፍን ስስ አዩት አንድ ቤት አልባ ሽማግሌ ስሜቱን ገስፀ ።

« ከማሳዘን አልፎ ያስፈራል » አስች ። ሕሊና ፊቷን ከቴሌቪዥኑ በማዞር ።

« ምኑ ነው የሚያስፈራው ? ድህነቱ ? » በሕሊና አባባል በመገረም ጠየቃት ።

« ሁሉም ነገር ። አመስካከታቸው ፣ አስባበሳቸው የዚህ ዓይነት ስዎች ምን እንደሚያደርጉ አይታወቅም ። እነኚህን በሩቁ ነው » አስች ስመስፍን ጥያቄ መልስ ስመስጠት በመሞከር ።

« ሕሊና እዚህ ሀገር ማንኛችንም ብንሆን ዛሬ ያስንን ነገ ልናጣ እንችላስን ። ሆምሰስ መሆን እዚህ ሀገር ህገ ወጥ እንድትሆኚ አይገፋፋም እንዲያውም ስብዙ ስዎች እንደ ኑሮ ምርጫቸው ሊሆን አብዛኛዎቹ ሃርምስስ ናቸው ። »

« እዚህ ሀገር የተትረፈረፈ ሥራ ሠርቶ መብላት እያስ አስመሥራትን መርጦ መቸገርን የሚመርጥ ሰው ጤነኛ ነው ብዬ አላምንም » አስች ሕሊና ።

« እዚህ ሀገር የእያንዳንዱ ሰው የኑሮ ምርጫ በህግ የተከበረ ነው ። የሌላውን ዜጋና ነዋሪ መብት እስካልነኩ ፣ ዘ ሪች ፣ ዘ ፑር፣ ዘ ሆመስስ ህይወታቸውን በየፈርጁ እንደፈስጉት መምራት ይችላሉ» በማስት መስፍን ሊያስረዳት ሞከረ ።

« ስዚህ ነው በየቦታው ተሰቀው ሰውን መሄጃ ማሳሰፊያ ያሳጡት ? » አስች ቆጣ ብላ ።

« ምን አስቆጣሽ ? በግል ጉዳት ያደረሰብሽ ሰው አስ ወይስ ስሜትሽን የጎዳ ? ከአነጋገርሽ በደል የተፈፀመብሽ ነው የምትመስይው » አስ በሕሊና አነጋገር ተደናግጦ ።

ሕሊና ስሜቷን ስመግስፅ ሳትቸኩል በዝምታ በመስኮት በኩል ወደ ውጪ ተመስከተች ። ወደ ትምህርት ቤት የምትሄድበት መንገድ በትይዩ ግልፅ ሆኖ የመንገዱ መብራቶች በርተዋል ።

« ና ተመልከት » በማስት መስፍን ያየችውን እንዲመስከት ጋበዘችው ። በርቀት አንድ ሰው መኪና መንገዱን መልሶ መላልሶ በፍጥነት እያቋረጠ ሠማይ ሠማዩን እያየና እየቃበዘ ስአፍታ ቆሞ

ራሱን በኃይል እየነቀነቀ መንገድ ማቋረጡን ቀጠለ :: መስፍን ፣ ሕሊና ይህን እንዲመለከት ለምን እንደጋበዘችው አልገባውም ::

« ኤንደ ዘን ዋት » ? በማለት እጁን አወራጨ :: ግራ እንደገባው ለመግለፅ ሞከረ ::

« ተመልከት ያልኩህ የለውዬውን ሁኔታ እንድታይ ነው :: አንተ ምናልባት በመኪና ስለምትመላለስ ፊት ለፊት ላያጋጥሙህ ይችላሉ :: ለእኔ ግን የቀን ተቀን ስቃይ ነው የሆነብኝ :: እነርሱን ባየሁ ቁጥር የምገባበት ይጠፋኛል :: . . . »

ሕሊና ሳግ እያቋረጣት ስሜቷን በንግግር መግለጽ አልቻለችም :: መስፍን ሕሊና የተናገረችውን አብሰለሰለ :: መንገዱ ላይ ያየው የአእምሮ በሽተኛ ሁኔታ እና የእርሷ ፍርሃት ከምን የመነጨ እንደሆነ አልገባውም :: ሁለቱን ሁኔታዎች ለማያያዝ ጥረት በማድረግ « አሁንም የምትይው አልገባኝም :: ዋት ሜክስ ዩ ሶ ሴንስቲቭ እና ከአንቺ ትምህርት ቤት መሄድ ጋር ምን አያያዘው ? ሊገባኝ አልቻለም »

« እኔ በጣም ያስፈሩኛል :: ዘለው የሚያንቁኝ ነው የሚመስለኝ :: አንዳንዶቹ ዓይኖቻቸውን አፍጥጠውና አቅልተው አንዳች ነገር እንደገፋቸው በቀጥታ ወደ እኔ ይመጣሉ :: ታዲያ ያለኝ አማራጭ መሸሽ ብቻ ነው :: ጥቂቶቹ ተከታትለው ሲያባርሩኝ ወደ ሱቅ ተጠግቼ ነው የማሳልፋቸው :: »

ሕሊና ፍርሃቷን በማሳነስ ለመስፍን ገለፀችለት :: መስፍን በጥሞና አዳመጠ :: በአድራጎቷ መሳቅ ቢከጅለውም የነገሩን ክብደት በማጤንና ስሜቷን ላለመጉዳት በዝምታው ፀና :: ሆኖም የሕሊና አገላለፅ ፊት ለፊቱ ተደቅኖ ለነበረው ጥያቄ ግማሽ መልስ እንደሆነ ተረዳ ::

« ይህ ለሕሊና ኤ ፓርት ኦፍ ከልቸር ሾክ ነው » አለ ለራሱ ::

« ሕሊና ስሚኝ » መስፍን የሕሊናን ሁለት እጆች ይዞ ሶፋ ላይ እንድትቀመጥ አደረገ :: « እዚህ ሀገር የአእምሮ በሽተኞች በሚገባ ይታከማሉ :: ራሳቸውንና ህብረተሰቡን ጎጂ ሆነው ከተገኙ ወደ ሀኪም ቤት ይወሰዳሉ :: ሀኪሙ ጎጂ አይደሉም ብሎ እስከአሳረጋገጠ ድረስ ሆስፒታሉ ውስጥ እየተጠበቁ ህክምና ይደረግላቸዋል :: አሁን በመንገድ ላይ የምታያቸው በሽተኞች ታክመው ሀኪም ሃርምለስ ናቸው ብሎ ሰርቲፋይ ያደረጋቸው ናቸው:: »

ለሕሊና የመስፍን አገላለፅ አልተዋጠላትም :: « ከታከሙና ከዳኑ ታዲያ ለምን እንደማንኛውም ጤነኛ ሰው አይሆኑም ? »

« አይ ሚን ሃርምለስ ዳዝ ኖት ኢንክሉድ ዞስ ቢይንግ ኪዩርድ :: ሰውን አይተናኮሉም ማለት ነው እንጂ እንደ እኔና እንደ አንቺ ጤነኛ ሆነው የቀን ተቀን ህይወታቸውን አይመሩም :: »

« ከዚህ የበለጠ መተናኮል አይገባኝም :: »

ሕሊና በመስፍን አባባል በአጠቃላይ አለመስማማቷን ገለፀች:: መስፍን የሕሊና ጭንቀት ከግል የመነጨ መሆኑን ቢረዳም ሕሊና በውጭ የምታየውን ተቀብላ ከራሷ ልምድ ጋር ለማዋሀድ የግል መለኪያ እንዳላት ገባው :: ይህ መለኪያ ከሰዎች የኑሮ ዘይቤ ፣ ከህብረተሰቡ የጋራ ብሎም ከግለሰቡ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት የሚመነጭ ነው :: ሀሳቡን ጥሎ አጠገቡ የተቀመጠችውን ሕሊናን ተመለከተ :: ከአነጋገሯ ንፁህና የዋህ እንደበቷን አደነቀ :: ቢሆንም ተስፋ የቆረጠ መሳይ አመለካከቷ መስፍንን አሳዘነው :: አስተሳሰቧን ቀይሮ ከአካባቢው ጋር ለማመሳሰል የሚያበቃትን ፈጣን ለውጥ እንዲያጋጥማት ተመኘ :: ሆኖም የሰዎች ዓለም እንደግለሰቡ የህይወት ታሪክ የተወሰነ መሆኑን ሲረዳ ምኞቱ በቀላሉና በፍጥነት ሊፈጸም እንደማይችል ገመተ ::

« ዩ ሜይ ቢ ራይት ። መንገድ ላይ ያየሻቸው ሰዎች የአእምሮ በሽተኞች ብቻ አይደሉም ። እዚያ መንገድ ላይ በልዩ ልዩ የአእምሮ አደንዛዥ ዕፅ መርዞች የተበከሉ ሰዎችም ጭምር ይገኛሉ ። ለማንኛውም ከዚህ ትምህርት ቤቱ ድረስ ያለው መንገድ ቅርብ ቢሆንም እኔ አደርስሻለሁ ። ካልሆነም አውቶቡስ ትጠቀሚያለሽ » አለ መስፍን ሕሊናን ከአጋጠማት ችግር ሊረዳት በማሰብ ። ሆኖም ይህ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ እንደማይሆን መስፍን እርግጠኛ ነበር ።

የሕሊና የወደፊት የኑሮ ሁኔታ አሳሰበው ። እርሷ የመንግሥት ትምህርት ቤት ለማስተማር ከርዕሳነ መምህራን ጋር የቃለ መጠይቅ ቀጠሮ በማድረግ ላይ እንደሆነች ያውቃል ። አብዛኞቹ ተተኪ መምህራን የሚያስፈልጉዋቸው ትምህርት ቤቶች ከከተማው በስተደቡብ በኩል የሚገኙ ናቸው ። መስፍን አብዛኛዎቹ ከደቡብ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች ቁጡና ለወንጀል የተጋለጡ መሆናቸውን ከሚሰማውና ከሚያየው መገንዘብ ችሏል ። ሕሊና ወደ እዚህ አካባቢ ስትመላለስ ስለሚያጋጥሟት ሁኔታዎች አሳሰበው ። « የሠፈራቸው ቀለል ያለው ትዕይንት ያስበረገጋት ከበድ ከሚሉት የህይወት ልምዶች ጋር እንዴት መላመድ እንደምትችል መስፍን ግራ ገባው ። ሺ ኒድስ ቱ ጎ ፎር ፕሮፌሽናል ካውንስሊንግ ። » ሀሳቡን ለሕሊና ለማካፈል ወሰነ ።

« ሕሊና ዜር አር ፕሮፌሽናልስ ሁ ካን ሄልፕ ዩ ኢን ዚስ ሪጋርድ » በአባባሉ ሕሊናን እንዳያስቀይም በመጠንቀቅ ጉዳዩን በማጠቃለል ተናገረ ።

« እርዳታ ስትል ምን ዓይነት ? »

« ማለቴ አጀስትመንት ፕሮብሌም ፤ ሀገሩን ለመልመድ ችግር ላለባቸው ሰዎች ፕሮፌሽናል ምክር የሚሰጡ ማለቴ ነው ። »

« አሁንም አልገባኝም ። እኔ ነኝ ችግር ያለብኝ ወይስ መንገድ ላይ የተኮለኮሉት . . . ? » ለማለት የፈለገችውን አልጨረሰችም ከራሷ ጋር ማውራት ጀመረች ።

« የተናገርኩት አንቺን ለማስቀየም አይደለም ። ድንገት ሀገሩን ለመልመድ ችግር ካጋጠመሽ አዋቂዎችን ማማከር አይከፋም በማለት ነው ። አያስፈልገኝም ካልሽ ምርጫው የአንቺ ነው ። »

መስፍን ስለ ጉዳዩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሕሊና ጋር በመወያየቱ ደስ ስለአለው የእርሷ ቅሬታ አላሳሰበውም ።

« ለምን እቀየማለሁ በእርግጥ አንተ የመሰለህን ብትናገርም ምክርህ ግን አልገባኝም » አለች ። ይበልጥ ለማወቅ ጉጉት እያደረባት::

« የምልሽ ምክር በቀጥታ አይደለም ። ካውንስሊንግ ማለቴ ነው ። እንደሚመስለኝ ዚስ ማይት ሄልፕ ዩ ቱ አጀስት ቱ ዩር ሶሻል ኢንቫይሮመንት ። የዚህ ሀገር ሰዎች ከአቅማቸው በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥማቸው ካውንስሊንግ ። ይሰራ አይሰራ እኔ አላውቅም ። ሆኖም ላመነበት እንደሚሰራ አልጠራጠርም ። »

* * *

« ታዲያስ ሥራ እንዴት ነው ? » ስትል ሕሊና ራሄልን ከሠላምታ ልውውጥ በኋላ ጠየቀቻት ።

« ኢት ኢዝ ግሬት ! አንቺስ ትምህርቱ እንዴት እያደረገሽ ነው ? መቼም የዚህ ሀገር ትምህርት ማለቂያ የለውም » ራሄል የምትሄድበትን አቅጣጫ እንዳትስት መሪዋን እያስተካከለች ወደ ሕሊና ተመለከተች ።

« ኦ ማይ ጋድ ! ፊትሽን ምን አደረግሽበት ? » የመኪናዋን የፀሀይ መከላከያ ገለጥ አድርጋ ወደመስተዋቱ አመለከተቻት ።

« እይው እስቲ »

« ምን ሆኖለሁ ? » ሕሊና ሁልጊዜ ከምታየው የተለየ ነገር አላየችም ። ወደ ራሄል ተመለከተች ።

« ምን አየሽ ? እኔ ምንም ማየት አልቻልኩም ። »

« ካን ዩ ሲ ዚስ ኤንድ ዚስ ? » ራሄል በጣቷ ወደ ራሷ ፊት እየጠቆመች በምሳሌ ለሕሊና ለማስረዳት ሞከረች ።

« የዚህ ሀገር ዌዘር እንኳን ላልለመደው ለለመደውም በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ መጠንቀቅ አለብሽ ። አይ ወንዶች ፣ መስፍን እንኳን ለሰው ለራሱም ግድ የለውም ። በይ አሁን ሄደን ለፊትሽና ለፀጉርሽ ተስማሚ ቅባት እንገዛለን ። »

« ከሀገር ቤት ያመጣሁት ብዙ የቅባት አይነቶች አሉኝ ። ምን ይሰራልኛል ? »

« እሱን ተይውና አሁን እንሂድ » በማለት ራሄል የተናገረችውን ለማደብዘዝ ሞከረች ። ቀጥላም « ኢት ኢዝ ኦን አወር ዌይ ፣ ደቂቃ አይፈጅም ። ትወጂዋለሽ ፤ ግድ የለሽም » አለቻትና ወደ ቁንጅና ዕቃዎች መደብር ጉዟቸውን ቀጠሉ ።

ሕሊና ለመጀመሪያ ጊዜ ሠፊና የተደራጀ የቁንጅና ዕቃዎች መደብር ውስጥ ገባች ። በውስጡ የተደረደሩት ዕቃዎች ሁሉ ማረኳት ። በሽታውና በቀለሙ ፣ በአንድነትና በብዛት በዋጋ ተለይቶ ማንኛውም ሸማች በግልፅ ሊደርስበትና ሊመለከተው በሚችልበት ቦታ ተቀምጧል ። ለቅምሻ ያህል የተከፈቱ በየዓይነቱ ማዕዛው ጥሩ የሆነ ቅባት ፣ ሽቶ ፣ የጥፍር ቀለምና ሌሎች ዕቃዎችም በየቦታው ተደርድረው የሰውን ሁሉ እይታ በመሻማት ያልገዛን እንዲገዛ ፣ የገዛን እንዲጨምር ይገፋፉሉ ። ምን ያህል መግዛት እንደምትችል ለማወቅ በቦርሳዋ የያዘችውን የገንዘብ ልክ አሰላሰለች ።

« ዕቃው በጣም ውድ ነው ። » ሕሊና ከራሄል ጋር የዕቃ ምርጫ በማድረግ የተሰማትን ተናገረች ።

« መኒ ካምስ ኤንድ ጎስ ። ተመልሶ የማይመጣው ይህ ያለሽ መልክና ዕድሜ ነው ስለሆነ በቅጡ ካልተንከባከብሽው እስከዘላለሙ ታጭዋለሽ ። »

ራሄል የሕሊናን ፍላጎት ሳትጠይቅ የሚመስላትን ሳሙናና ቅባት በያዘችው ቅርጫት ውስጥ ማስቀመጥ ጀመረች ።

« ይህ ሞይስቸራይዘር ነው ። ቆዳሽ እንዳይደርቅና ለስላሳ እንደሆነ እንዲቆይ ይረዳሻል ። በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ በዚህ ሳሙና ታጥበሽ ብትቀቢው የቆዳሽ ቀለም እየለመለመ ይመጣል ። »

« እኔ የምልሽ ዕቃዎቹ በጣም ቆንጆዎች ቢሆኑም እኔ ዛሬ ገንዘብ አልያዝኩም ። ለምን ሌላ ቀን ተመልሰን አንመጣም ? » ሕሊና በትህትና መልክ ለማስረዳት ሞከረች ።

« ኦ ጂ ! ስንት ጊዜ ላስረዳሽ ? ገንዘብ ! ገንዘብ ! ዱ ኖት ዎሪ ! እሱን ለእኔ ተይው ። እኔና አንቺ እኮ ዊ ሃቭ ሶ መኒ ቲንግስ ኢን ኮመን ዊ ኒድ ቱ ሄልፕ ኢች አዘር ። » ራሄል በፈገግታ ሕሊናን ተመለከተች ።

ሕሊና የራሄል አባባል ቁምነገር አዘል እንደሆነ ገባት ። ከእርሷ ጋር መስፍን በሌለበት በድብቅ የወጣችበት ምክንያት ሉቅ ለማየት ብቻ አልነበረም ። በበለጠ ስለ አሜሪካን ኑሮ ምስጢር ለማወቅና ከዚያም ካለፈ በራሄልና በመስፍን መሀከል ስላለው ውስጣዊ ቅራኔ ለማወቅ ፍላጎትም ነበራት ።

« ለምን እንደዚያ አልሽ ? ኢትዮጵያውያን ስለሆንን ነው ? » ራሄልን አትኩራ በማየት መልሱን ከፊቷ ለማንበብ ሞከረች ።

« እሱም አንዱ ምክኒያት ነው ። ዋናው ነገር ግን እኔና አንቺ በሥጋና በደም እንደተዋሀድን እህትማማቾች ነን ። ሕሊና ! ሁሉንም ነገር አውቃለሁ ። ሞኝ አልምሰልሽ ። አውጥቼ ባልናገረውም ከመጣሽ ጀምሮ እስከ ዛሬ ብዙ ጊዜ አብረን እንዳንሆን

መስፍን እንደሚከለክልሽ አውቃለሁ ። ያን ሲያደርግ ያለ ምክንያት አይደለም፤ ምክንያት አለው ። ጊዜው ሲደርስ እንነጋገራለን ። »

ራሄል ወደ ገንዘብ መክፈያው ተጠጋች ። ቦርሳዋን ከፍታ የብድር ካርድ አውጥታ ለካሸሯ ሰጠቻት ። ሕሊና ለዕቃው የተከፈለውን ገንዘብ ለማወቅ ጥረት አደረገች ። ለማወቅ ግን አልቻለችም ።

« ይህንን ማን ነገረሽ ? ምክንያቱም መስፍን ስለአንቺ ምንም አላለኝም ። ማን እንደነገረሽ ብትነግሪኝ ጥሩ ነበር ። » አለችና ራሄልን እያየች ስሜቷን ከገፅታዋ ለማንበብ ሞከረች ። የራሄል ገፅታ ግን ትርጉም የለሽ ባዶ ፈገግታ የተላበሰ ነበር ።

« ሕሊና ስቶፐ ኢት ! ለምን እንደዚህ ታይኛለሽ ? እንደህ በጥያቄ መልክ ሲመለከቱኝ በጣም ነው ዲስኮምፎርት የሚሰማኝ » አለች ራሄል ፈገግታዋን ወደ ሳቅ ለውጣ ። « ለነገሩ ስለ መስፍን ማንም ሰው ባይነግረኝም ክበቂ በላይ አውቀዋለሁ ። » በማሾፍ ወደ ሕሊና ተመለከተች ።

« ምን ማለትሽ ነው ? የምፈለገውን ስትይ አልገባኝም ። » ሕሊና ኮስተር ብላ ጠየቀች ።

« ሕሊና ! የነገረኝ መስፍን ይሆናል ። እኔው ለማስረዳት ልሞክር ። እኔና መስፍን ሎንግ ታይም ፍሬንድስ ነበርን ። የእኔና የመስፍን ቤተሰቦች ለረጅም ዓመት አብረው ኖረዋል ። እኔ ወደ እዚህ ሀገር ስመጣ ስፖንሰር ያደረገኝ ጋሼ ሙሉጌታ ነው ። ታዲያ ምን ብዬ ልነገርሽ እኔና መስፍን የልጅ አይሉት አዋቂ - ቦይ ፍሬንድ፣ ገርል ፍሬንድ ስንጫወት ለጥቂት ጊዜ አብረን ቆየን ። ሕሊና አደራሽን ዶንት ቴክ ኢት ሶ ሀርድ ኦን ዩር ሰልፍ ዚስ ኢዝ ኢን አወር ፓስት ። አሁን እኔና መስፍን ጥሩ ወንድምና እህት ነን ። ሁለታችንም ብንሆን በወቅቱ ብዙ አልበሰልንም ነበር ። ያኔ በየቀኑ መጣላት ፣ መፋለስ ነበር ። ጋሼ ሙሉጌታ ታዲያ « የእናንተ አብሮ

መሆን አይታየኝም ። በዚህ ዓይነት ኑሮ አንድ ቀን አንዱ ሌላውን ገድሎ ቤተሰቦቻችንን ደም ታቃባላችሁ ይቅርባችሁ » ብሎ ይመክረን ነበር ። ሁለታችንም በጉዳዩ አስበንበት ኢት ኢዝ ፎር ዘ ቤተር ብለን ተለያየን ። « ቢሳይድስ እኔና መስፍን አር ኖት ሜድ ፊር ኢች አዘር:: » አለችና አንገቷን ቀስራ ፣ አፏን ከፍታ ፣ ፊቷን አርዝማ ፣ ዓይኖቿን በልጥጣ ወደምታያት ሕሊና ተመለከተች ።

ለሕሊና ይህ መርዶ አዲስ ክስተት ሆነባት ። የራሄል ግልፅ አቀራረብ ቢሰማትም አባባሏን በእውነትነት አምኖ ለመቀበል አዳገታት:: ሕሊና ባላት ልምድ ሴቶች ከወንዶች ጋር ስላላቸው ግንኙነት እምብዛም አይወያዩም ። ከተወያዩም በጓደኝነት ፍጹማዊ ቅርበት ካላቸው ሰዎች ጋር ነው ።

« ባለቤትሽ የእኔ ወንድ ጓደኛ ነበር » ብላ በድፍረት የምታወራ ሴት አጋጥሟት ስለማታውቅ የራሄል አባባል ያልጠበቀችው ዱብ ዕዳ ነበር የሆነባት ሀሳቡን መቀበል አለመቀበሉ ቢያዳግታትም ውይይቱን መቀጠል እንዳለባት ገመተች ። ውስጣዊ ስሜቷን ለመደበቅ በመሞከር « ለመሆኑ አብራችሁ ብዙ ቆያችሁ ? ካነጋገርሽ ለመረዳት እንደቻልኩት ብዙም የተስለቻቻችሁ አይመስልም» አለች ።

« ኦ ! ያ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የዚህ ዓይነት ኮሜንት ሰው ሲሰጥ ሰማሁ ። መስልቸት ፣ መጣላት ፣ የሚለው እንኳ አልነካካንም ። ዊ ጀስት ሴተልድ አወር ዲፈረንስስ ኢን ኤ ሲቪላይዝድ ዌይ ፤ ግን ሕሊና የእውነቱን ልንገርሽ ፣ ዊን አይ ሲ ሂም ፣ አይ ሄት ሂም ! ሄት ሂም ! ሄት ሂም ! » ራሄል መሪር በሆነ ቃል ተናገረች ። የመኪናውን መሪ መታ መታ አደረገች ። ድርጊቷ አነጋገሯን አጋነነው ።

« ለምን ትጠይዋለሽ ? ያለፈ ነገር ያለፈ ነው ብለሽ በእርግጥ የምታምኚ ከሆነ ለምን እርገፍ አድርገሽ አትተይውም » አለቻት ።

የራሄልን አነጋገር ከበስተጀርባው ያዘለው መልዕክት ግልጽ አልሆነላትም ::

« ሕሊና አይገባሽም ? ሂ ኢዝ ኤ ዩዘር :: መስፍን ከራሱ በስተቀር የሚወደው ሰው የለም :: የሰውን ቅርበት የሚያውለው ለራሱ ጥቅም ነው :: ሰዎች ምኑን አይተው እንደሚቀርቡት አላውቅም :: የቀረቡት ሁሉ ቶሎ ይርቁታል :: አይ ዱ ኖት ብሌም ዘም :: ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝ የምትወጂውን ሰው ሳማልሽ ኢት ኢዝ ኦድ :: ግን ምን ላድርግ ! አይ ካንት ሄልፕ ኢት ፣ የእኔ ዕጣ አንቺ ላይ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ይሁንሽ በማለት ነው :: » ራሄል ንግግሯን ለመግታት ጥረት አደረገች ::

« ለምን ለእኔ አሁን ነገርሽኝ ? ማለቴ ለምን ዛሬ ? ሥሚ ራሄል ያልሽው በሙሉ እውነት ነው ብዬ ልቀበል :: ነገር ግን አንቺ ያልተገነዘብሽው ነገር የእኔን ሁኔታ ነው :: እኔና መስፍን አብረን ኖረን ፀባያችንን ለመተዋወቅና ለመቻቻል ያለን ትዕግስት የቱን ያህል እንደሆነ አልመዘንም :: እርሱን የማውቀው ከሚፅፍልኝና ለጥቂት ቀናት ሀገር ቤት ብቅ ሲል ባወራናቸው የተወሰኑ ነገሮች ላይ በመነሳት ነው :: ታዲያ እዚህ ሀገር ስመጣ ሁሉንም ነገር ማለቴ እምነቴን እርሱ ላይ በመጣል ይህው እስከዛሬ አብረን ስንኖር ምንም ነገር አላየሁብትም :: እኔ የማውቀው መስፍን አንቺ የሳልሽውን መስፍን አይመስልም :: ታዲያ የምትይው ከማየው ጋር ተጋጨብኝ:: ገባሽ የምልሽ ! » ራሄልን ላለማስቀየም በለሰለሰ አንደበት ተናገረች ::

« መስፍን ድንገት ነግሮሽ ይሆናል በማለት ነበር እስካሁን የቆየሁት :: ሌላው ደግሞ እንድነግርሽ የገፋፋኝ መስፍን እዚህ ሀገር ምንም ዘመድ እንደሌለሽ ስለሚያውቅ በደፈናው አምጥቶ መጫወቻ ሊያደርግሽ እንደሆነ ስለተገነዘብኩ ነው ::

« ሕሊና ! እዚህ ሀገር ስንት እንደ መስፍን ያሉ ወንዶች እንዳሉ ብነግርሽ አታምኚኝም :: ከቤተሰቦቻቸው አፈናቅለው እዚህ

አምጥተው እንደዕቃ ወዲያና ወዲህ እያደረጉ እንደፈለጉ የሚጫወቱባቸውን ሴቶች ልጆች ቤታቸው ይቁጠራቸው :: ጥቂቶቹ ከዚህ ዓይነት ወጥመድ ራሳቸውን ቢያላቅቁም ብዙዎቹ ግን ቢከትም ሆነው ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ሲሯሯጡ ይታያሉ :: ኑሮ መከራ ሆኖ ማሸነፍ ያቃታቸው ፣ ተሸንፈው ፣ መስለውና ተጎሳቁለው የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው :: የበረቱት ችግሩን ተቋቁመው ሲወጡ የተሸነፉት ደግሞ ተረተው የባሎቻቸው አገልጋይ ሆነው ቀሩ :: ስንቱን ላውራልሽ ? በእኛ ሀገር ሴቶች ላይ ይህን በተመለከተ የሚፈፀመው በደል ኢዝ ሶ ዲፕ ሰም ጎዝ ቱ ፀ ኤክስቴንት ኦፍ ከሚቲንግ ሱሳይድ ፤ አንዳንዶቹ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ህጋዊ ጋብቻ ሳይኖራቸው ተዳብለው የሚኖሩ ጥቂቶች አይደሉም :: ይህ ሁሉ ታዲያ የሚሆነው የሀገር ቤቱን የባህል ልምድ ኤክስፕሎይት በማድረግ ፣ የሴቶችን በጎና መልካም ፀባይ አብዩስ በሚያደርጉ እንደ መስፍን ባሉ ወንዶች ምክንያት ነው :: እነኚህ የሚያደርጉትን የማያውቁ ፣ ለቅርብ ርካታቸው ብቻ የገዛ እህቶቻቸውን ለስቃይ የሚዳርጉ ሰዎች መጋለጥ አለባቸው :: »

« አሁንስ የሀገሬን ካድሬዎች መሰልሽኝ :: መቼም ሁሉም ወንዶች እንዲህ ባለጌዎች አይመስሉኝም :: ማጠቃለሉ በጣም አስቸጋሪ መሰለኝ » አለች ሕሊና የራሄልን መሪር አባባል በማለሳለስ::

« አፍ ኮርስ አሉ ! ሩቅ ሳትሄጂ ጋሼ ሙሉጌታ የሚያኮራ ኢትዮጵያዊ ነው :: ሚስት ለመምረጥ እንደ አንዳንዶቹ ወንዶች ግርድናን እንደ ክራይቴሪያ አልተጠቀመም :: የባህል ልዩነት ሳያግደው ከባለቤቱ ጋር በእኩልነት ላይ የተሞረከዘ ትዳር በመመስረታቸው ወልደው ከብደው በመግባባትና በመተሳሰብ ኑሮአቸውን እየመሩ ነው :: ምንም እንኳ ባለቤቱ የውጪ ሀገር ዜጋ ብትሆንም ባህሉን አክብራ እርሱም የእርሷን አክብሮ በመተጋገዝ

ይኸው ኑሮአቸው ተስተካክሎ ይኖራሉ ። ከጋሼ ሙሉጌታ ጋር ሁለት ዓመት ቤታቸው ተቀምጫለሁ ። ለልጆቻቸውም ቤቢ ሲተር ሆኜ አንዳንድ ቀን እረዳቸዋለሁ ። አሁን አሁን ሳስበው ከጋሼ ሙሉጌታ ጋር አብሬ ባልኖር ኑሮ መስፍን አያታልለኝም ነበር ። እኔ ወንድማማቾች ናቸው ፣ ፀባያቸው ያው ተቀራራቢ ይሆናል ብዬ ነበር የተዘናጋሁት ።

« የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው የሚሉት የሀገራችን አባባል እውነት ነው ። . . . ሕሊና ብዙ ጨቀጨኩሽ ። ያስለቀሁሽ መሰለኝ . . . ኡፎይ » በማለት ራሄል በረጅሙ ተነፈሰች ። ሕሊና የራሄል ወሬ በዚህ እንዲያቋርጥ አልፈለገችም ። ያላወቀችውና ያልዳሰሰችው አዲስ ክስተት በመከፈቱ ለማወቅ ያላት ፍላጎት ጨመረ ።

« ምን ችግር አለ ? እንዲያውም አልፎ አልፎ እንደዚህ ማውራት ጥሩ ነው ። የበለጠ እንድንተዋወቅና እንድንማማር ይረዳናል ። »

« መቼም እርግጠኛ ነኝ ያወራነው በሙሉ በአንቺና በእኔ እንደሚቀር . . . ምስጢር አድርገሽ ያዥው » አለች ራሄል ።

« እርሱን ለእኔ ተይው ። ምን ብዬስ አወራለሁ ? ጉዳዩ የራሴም ጭምር ስለሆነ ሙያ በልብ ነው ። » ሕሊና የመጨረሻውን አባባል ለራሷ በመናገር ጨረሰች ።

* * *

መጠኑ ትንንሽ ሆኖ የተነደፈ ጥጥ መስሎ በስሱ የሚወርደው በረዶ መሬቱ ላይ ተጋግሮ አካባቢውን ነጭ አንሶላ የለበሰ አስመስሎታል ። የቆሙት ዛፎች ቅጠላቸው ረግፎ ፣ ቅርንጫፎቹ ደርቀው ያለምንም እንቅስቃሴ ቆመዋል ። ከመኪና በስተቀር በእግሩ ዝር የሚል ሰውም ሆነ እንስሳ የለም ። ሕሊና መስፍን የገዛላትን ካፖርት ለብሳ ፣ ከዓይኖቿ አካባቢ በስተቀር ፊቷን በተቻላት ሸፍና

ከምትኖርበት ህንፃ ወጣች ። አንድ ዘግናኝ ነገር ፊቷን እንደነካው ሁሉ በእጇ ስትዳስስ ቅዝቃዜው ከልክ አልፎ ዓይኖቿን አቃጠለው ። ፅንባ አኀርቶ የሩቁን ማየት አዳገታት። ባለችበት ቆማ « አይዞሽ ሕሊና ! የፈረንጅ ሀገር ክረምት ማለት ይህ ነው » ብላ ራሷን አፅናናች ። እንዳትንሸራተት የምትረግጠውን መሬት በጥንቃቄ እየመረጠች መራመዱን ቀጠለች ። ርቃ በሄደች ቁጥር እየቀለላት ሄደ ። ሆኖም ቅዝቃዜው ጫማዋን አልፎ እግሮቿን ሲያደነዝዘው በአካባቢዋ ከሚገኝ ሱቅ ውስጥ ገብታ የእግሮቿ ሙቀት እስኪመለስላት ጠበቀች ። ሆኖም ወደ አሰበችው ቦታ ለመድረስ ባለመቻሏ ቤቷ ተመልሳ ልብሷን አወላልቃ የቤት ውስጥ ሥራዋን ቀጠለች ።

« ምን እግዚአብሄር የተጣላው ሀገር ነው ? ብርዱ ማቆሚያ የለው ፤ ሙቀቱ ሲመጣ ደግሞ ከመጠን ያለፈ ፤ በእንደዚህ ዓይነት አየር ሰውስ እንዴት መኖር ቻለ ? ወይ ሀገሬ ! ያለንበት አይታየንም። . . . እንዴ ወጣ ብሎ ለመምጣት ሞቼ ነበር ። » በሠላም ቤት በመድረሷ ደስ አላት ። የቤቱን ሙቀት አመሰገነች ።

« የበረቱት ችግሩን ተቋቁመው ሲወጡ የተሸነፉት ደግሞ ተረተው የባሉቻቸው አገልጋይ ሆነው ቀሩ ። » ራሄል ያለችው ትዝ አላት። ወደ መኝታ ቤት ገብታ መሳቢያውን ከፍታ በጥንቃቄ የተቀመጠውን ፎቶግራፍ አወጣች ። በትከሻዋ አንግባ የተነሳችውን የአባቷን መጥረቢያ አየች ።

« አባዬ ብርታቱን ስጠኝ ። አሁን ደግሞ ይህን የመሰለ የተለየ ፈተና አጋጥሞኛል ። » በማለት ፎቶግራፉን ወደ ደረቷ አስጠግታ አቀፈችው ። ሁሉን ነገር በነበር ትታ ቁም ሳጥኑን ዘግታ ልብሷን መለባበስ ጀመረች ።

ሁለት ወፍራም ካልሲዎች ፣ የብርድ ኮፍያ ፣ ሁለት ሹራብ፣ ጃኬትና ካፖርት በላዩ ላይ ደርባ ቀስ በቀስ በበረዶ ውስጥ

እየተራመደች ወደ ትምህርት ቤቷ አቀናች ። ሕሊና በመሄድ ላይ እንዳለች በረዶው አንሸራቶ ጣላት ።

« ሕሊና በመሄድ ላይ እንዳለች በረዶው አንሸራቶ ጣላት ። «አር ዩ ኦኬ ? » ዞር ብላ አጠገቧ የነበረውን ሰው ተመለከተች ። ለዕርዳታ ለጋሹ ሁለተኛ መጠየቅ አላስፈለገውም ። የሕሊና ሁኔታ ብቻውን ገላጭ በመሆኑ « ኢት ኢዝ ኦኬ » በማለት እጇን ዘረጋችለት ። እያቃሰተች በድጋፍ ከወደቀችበት ተነስታ ራሷን እያበረታታች ወደ ትምህርት ቤት እያነከሰች ተራመደች ።

« የግፍ ግፍ በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ። ብርዱ ሳያንሰኝ መውደቄ ደግሞ . . . የተረገመ ሀገር . . . » እያለች ፣ ስለሀገሯ እያሰበች በሀሳብ ጭልጥ አለች ። ከሀሳቧ የተመለሰችው የትምህርት ቤቱን በር ከፍታ እንደገባች ነበር ። የትምህርት ቤቱ ሙቀት ፣ ብርሃንና ድሎት ሥቃዩን ከመቅፅበት እንድትረሳው አደረጋት ።

በክፍሉ ውስጥ የሕሊና መምህር ስለ « ኮምፒዩተር ፖቴንሻል ኢን ኮምኒኬሽን » በሚለው አርዕስት ላይ መግለጫ በመስጠት ላይ ነበር ። ሕሊና የመምህሩን አባባል በቀጥታ ከራሷና ከሀገሯ ጋር በማመሳሰል ምሳሌዎችን ለመጠቀም ሞከረች ።

« አዎ እውነቱን ነው ፣ ኮምፒዩተር የዓለም ሥልጣኔ የደረሰበት የግኝቶች ቁንጮ ነው ። በሠለጠነው ዓለም ኮምፒዩተር ሰዎች የቀን ተቀን ሥራቸውን ለመስራት ስለሚጠቀሙበት ኮምፒዩተር ብዙ ባለሙያዎችን በመተካት ፣ በጥራት እና በብቃት አጥጋቢ ውጤት ይሰጣል ። መዝገብ ቤት ፣ ሂሳብ ክፍል፣ ዲዛይን፣ የመሳሰሉትን ሠፊ ቦታና ብዙ የሰው ኃይል የሚያስፈልገውን ሞያ በአንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ ለማከናወን ተችሏል ። »

ሕሊና የመምህሩን ምሳሌያዊ አገላለጽ በተመስጦ ብታዳምጥም ከመጣችበትና ከነበረችበት ልምድ ጋር በማዛመድ በሀሳብ ማዕበል ውስጥ መዋዠቁን ማቆም አልቻለችም ።

« ትምህርት እንደድሎት በሚቆጠርበት . . . በሀገራችን ሥራን ከኮምፒዩተር ጋር እንዴት ለማዛመድ ይቻላል ? » ሕሊና ጥያቄውን ለሀሳቧ እንደ መንደርደሪያ በማድረግ ክፍለ ጊዜውን ጨርሳ ወደ ዕረፍት ወጣች ።

« ሃይ ሄሌ ! ኢሌን ኦ ! ኖ ፣ አይ ኦልዌይስ አይ ሃብ ኤ ዲፊካልት ታይም ኮሊንግ ዩር ኔም ራይት ። ኢዝ ኢት ኦኬ ቱ ኮል ዩ ሄሌ ? »

በእረፍት ጊዜ መቆሚያ ቦታ ሰብሰብ ብለው ከቆሙት የክፍል ተማሪዎች አንዷ ሕሊናን እንድትቀላቀል « ካም ኦን ኤሌን ! ጆይን አስ » ስትል ጋበዘቻት ።

« ዌር አር ዩ ፍሮም ? »

« ኢትዮጵያ ! »

« ዩ ኢትዮጵያንስ አር ሶ ቢውቲፉል ። አይ ዊሽ አይ አም ዋን ኦፍ ዩ ። ዩር አይስ ፣ዩር ሄር ኤንድ ከለር ! ኢት ኪልስ ሚ ።» በሀፍረት አንገቷን የደፋችውን የሕሊናን ፀጉር በማተኮር ጠጋ ብላ ተመለከተች ።

« ዊ ነቨር ሃድ ኤ ቻንስ ቱ ቶክ አይ ዶንት ኖው ማች አባውት ኢትዮጵያ ። ዘ ኦንሊ ቲንግ ዛት አይ ካን ሪኮል ኢዝ ዘ ሆረብል ፋሚን » አለች ጋባዥዋ አፍሪካ አሜሪካዊት ።

« ሃው ኢዝ ዘ ከንትሪ ናው ? » አብረው ከነበሩት አንደኛው ሕሊናን ጠየቀ ።

« ኢት ኢዝ ኦኬ » ሕሊና ጥያቄውን በማጠቃለል መለሰች ። ሕሊና በሁለቱ ሰዎች የተሰነዘረው አስተያየትና ጥያቄ ስለ ጥሩውና ስለ መጥፎው የሀገሯ ሁኔታ በከፊል እንደሚወክል አሰላሰለች ።

« ቁንጅና የሰዎችን ማንነት አይወክልም ። ቆንጆ እንደ ተመልካቹ ነው ። የቆዳ ቅላትና የፀጉር መለስለስ ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው ። ቆንጆ ፣ መጥፎ ከሰዎች አመለካከት የመነጨ ሀሳባዊ ፅንስ

እንጂ የተፈጥሮ ውጤት አይደለም » በማለት የሰማችውን በሀሳቧ ገመገመች ::

ሕሊና ዘወትር የምትበሳጭበት የተለያዩ ሰዎች ለሀገሯ እንደመለያ ምልክት የሚጠቀሙበት ረሃብ እና ችግር ነው :: ስለሀገሯ ሲጠይቋት ባህሉን ፣ ቋንቋውን ፣ የአኗኗር ዘይቤውን ሁሉንም ነገር በጥሞና ታስረዳቸዋለች :: ስለሀገሯ ያላቸውን ግንዛቤ በተቃራኒው ስታስቀምጥላቸው በጣም ይገረማሉ :: ቢሆንም ከስለሀገሯ ድህነት ፣ ጉስቁልና ፣ ኋላቀርንት ጠቆም አርገው የማያልፉበት ቀን ጥቂት ነው:: ሕሊና አብረዋት ካሉት ሰዎች ተለይታ በሀሳብ ርቃ ሄዳለች :: « እውነት ነው ፣ ሀገራችን በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ችግር መንስዔ የደረሰባትን ችግር ለመወጣት አልቻለችም :: ችግሩን ለማስወገድ አቅሙ ጠፋ :: አቅሙ ጠፋ ? ወይስ የተበታተነውን አሰባስቦ ለውጤታማነት ለማብቃት ያለመቻል ? መበታተን ፣ መቃረን ፣ አንዱ የሰራውንና የገነባውን ሌላው ማፍረስ ፣ ከመጥፎ ባህላችን አንዱ ቅሪት ይህ ነው :: »

ሕሊና አብረዋት ከቆሙት የአሜሪካን ተወላጆች ጋር ብዙ ማውራት አልቻለችም :: ሀሳቧን አሰባስባ በአዳማጭነት ተወስና ቀረች::

* * *

« ሃኒ ዩ አር ስፔንዲንግ ቱ ማች ታይም ኦን ዚስ ቲንግ :: ቤቱ ባዶ ነው የሚበላ ነገር የለም » አላት መስፍን ::

መስፍን ቅዳሜ ዕለት አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር ከመኝታው የሚነሳው አርፍዶ ነው :: ሕሊና ሌላ ክፍለ ጊዜ ስለጨመረች ቅዳሜ በጠዋት ወጥታ የምትመለሰው ወደ እኩለ ቀን ነው :: ይህ ለመስፍን ምቾቱን በጥቂቱ አዛባበት :: ቀደም ሲል የቅዳሜውን ክፍለ ጊዜ ወደ ሌላ ቀን እንድትቀይር ለማስገደድ ሞክሮ ነበር :: ሕሊና አጥብቃ በመከራከሯ ሊያሸንፉት አልቻለም :: ሆኖም ደስተኛ አልነበረም ::

« ምን ማለትህ ነው ? አሁን የምወስደው ሰብጀክት እንደከበደኝ ነግሬሃለሁ :: ማክሰኞ ፈተና ስለአለኝ መውደቅ አልፈልግም » አለች መፅሀፏን እየሰበሰበች ::

« ኖ ! ኖ ! አይ ዶንት ሚን ቱ ኦፌንድ ዩ :: ማጥናት ከፈለግሽ ማጥናት ትችያለሽ ሃኒ ! ሌትሊ አብረን የምናሳልፈው ጊዜ እየመነመነ በመምጣቱ ነው መሰለኝ አይ ፊል ጀለስ :: ትምህርቱ አንቺን ከእኔ ቀምቶ የወሰደ ነው የመሰለኝ ::

« ሉክ ! ሉክ ! » መስፍን ሁለቱን እጆቹን ዘርግቶ በየአቅጣጫው ወደተደረደረው መፅሐፍ ፣ በየቦታው ወደ ተቀመጠው ወረቀትና ደብተር እያመለከታት « ቤቱ ወደ ት/ቤት ተለውጧል ነጋ ጠባ ሩጫ ከሆነ ህይወትን መኖር የምንጀምረው መቼ ነው ? »

« ትምህርት እኮ የሰዎች ህይወት አንዱ ክፍል ነው :: ኑሮ እራሱ ያለ ትምህርት የሚሆን ስለአልሆነ ለእኔ መቼም አዲስ ነገሮችን ማወቅ የአእምሮ እርካታን ስለሚሰጠኝ በምንም አለውጠውም :: ትምህርት ያላወከውን ለማወቅ የሚያስችልህ መሣሪያ ነው :: መሰፍን ! ብዙ ጊዜ ትምህርትን በጣም አጥላልተህ ታወራለህ :: ምክንያቱን ባውቅ ግን ደስ ይለኛል :: »

« እንግዲህ ያ ዓመት የሚፈጅ ከርክርሽን ልታመጪ ነው ። አሁን ርቦኛል ያልኩሽ አንድ ቦታ ሄደን እንድንበላ ነው ። በዛውም ለቤት የሚሆን ምግብ ገዝተን እንመጣለን » አለ ።

« እንደተለመደው ርዕስ ለመለወጥ መሆኑ ይገባኛል ። ግን ይህ ጥያቄ ተንጠልጥሎ የቀረ መሆኑን እንዳትረሳ » አለችና ለመሄድ መዘጋጀት ጀመረች ።

« ኦፍ ኮርስ ላይፍ ኢት ሰልፍ ኢዝ ኢን ኤ ፔንዲንግ ስቴይተስ » በማለት መስፍን በቀልድ መልክ ተናገረ ።

« ለአንተ ሁሉም ነገር ቀልድ ነው ። » ሒሊና መስፍንን ሳሉን ትታው መኝታ ቤት ገባች ።

« ዘ ዌዘር ኢዝ ሶ ናይስ ቱደይ ። »

መስፍን ፣ ሒሊና የያዘችውን የፕላስቲክ ቋጠሮ ከእጇ ተቀብሎ ተያይዘው ወደ መኪናቸው ገቡ ። « አይ ሄት ዌን ዘ ትራፊክ ኢዝ ላይክ ዚስ ፣ መቼም ሰው ትንሽ ፀሐይ ስትወጣ አያስችላቸውም ። ሁሉም ከቤቱ መውጣት አለበት እንዴ ? » መስፍን ከፊት ለፊቱ የተኮለኮሉትን የመኪና ብዛት በማማረር ተናገረ።

« ታዲያ አንተ ምን አናደደህ ? እንደ ሀገሩ በትዕግስት ጠብቀህ መሄድ ነው እንጂ » አለችው ።

« መናደዴ እኮ አይደለም ። አስተያየት ነው »

« ካልተናደድክ አስተያየቱ አይከፋም » አለችው ።

« ሃኒ ! አይ አም ጎይንግ ቱ ቴክ ዩ ቱ ኤ ናይስ ፕሌስ » አለና ሒሊናን በእጁ ዳሰሳት ። ሒሊና የመስፍንን እጅ ከላይዋ ላይ አነሳች ። « የአንተ ተራ ነው » በማለት ወደ አረንጓዴነት የተለወጠውን የትራፊክ መብራት ተመለከተች ።

« ሒሊና ! አይ ዶንት ኖው ኋይ ሪስንትሊ እየተለወጥሽ መተሻል ። ትምህርት ይሁን ሌላ አላውቅም ። አነጋገርሽና

አስተያየትሽ ሞር ነጌቲቭ ኤንድ ሆስታየል እየሆነ መጣብኝ ። ኢዜር ኤኒ ሲንግ ሮንግ ? » ሲል ጠየቃት ።

« እንዴት ነው ተለወጥሽ ስትል ? »

« አይ ሚን . . . »

« ከሀገሩ ጋር ስለተላመድኩ ይሆናል ። »

« የአንቺ ለውጥ ግን ፌንዳሜንታል ነው ። ሉክ ሞስት ኦፍ ዘ ታይም ዊ ዲስ አግሪ ኢን አወር ኮንቨርሴሽን ፤ አስቲ አስታውሺ። እንደ መጣሽ ሰሞን ሁሉንም ነገር ተወያይተን ፣ ተስማምተን እንሰራ ነበር . . . አሁን ምን ነካሽ ? »

« እኔ የማውቀው የተለየ ለውጥ የለም ። በእርግጥ የማይመስለኝ ነገር ካለ እጠይቃለሁ ። ለመረዳትና ለማስረዳት እሞክራለሁ ። እዚህ እንደመጣሁ እንግዳ ነበርኩ ፤ የሀገሩን ባህል አላውቅም ነበር ። ስለዚህ የማላውቀውን ለማወቅ ጥረት አደርግ ነበር። አሁንም ቢሆን ሁሉን አውቃለሁ ማለቴ አይደለም ። ሆኖም እንግዳ አይደለሁም ። ቁምነገሩ ግን አንተን ለማስቀየም ሆን ብዬ ያደረኩት ነገር ስለሌለ በማደርገው ነገር ሁሉ የተቀየምክ ከሆነ ይቅርታ አድርግልኝ ። » ስትል ልታስረዳው ሞከረች ።

« ዩ ዶንት ኒድ ቱ አፖሎጃይዝ ። እኔም ብሆን አንቺን የጠየኩሽን ጥያቄ መልሼ ራሴን ብጠይቅ መልስ የማገኝለት አይመስለኝም ። ሁለታችንም ብንሆን የተለያዩ የህይወት ጎዳናዎችን ያሳለፍን በመሆኑ ለሚደርስብን ነገር ሁሉ የምንሰጠው ትርጉም ከህይወት ልምዳችን አንፃር መሆኑን አልዘነጋም ። ሲል ሒሊናን በትካዜና በቅሬታ አያት ።

« ሒሊና እኔ አንችን ለጋብቻ ሳጭሽ ፍፁማዊ ጓደኛ ትሆኚኛለሽ በማለት ነበር ። በእርግጥ በቅርበት አላወኩሽም ። ሆኖም ከሰማሁትና ካየሁት « የቤት ልጅ ናት ፤ እንደሌሎች ወዲያ ወዲህ ማለት አታውቅም » ሲሉኝ ከተሰላቸሁት ከእዚህ ሀገር የሴቶች ባህል

ተላቀቅኩ ብዬ በማሰብ አንቺን መረጥኩ ። ታዲያ ልዩነታችን እንደዚህ የሠፋ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር ። »

« ልዩነታችን እንዴት ይሰፋል ? »

« አን ሞስት አፍ ዘ ላይፍ ኢሹስ »

« ለምን ግልፅ አታደርገውም መስፍን ? »

« አጭር ጊዜ የሚበቃን አይመስለኝም ። ለማንኛውም በጥሞና ለመጫወት መኪናውን ላቁም » አለና ፍሪቻውን ወደቀኝ አሳይቶ መውጫው ላይ ወዳለው መናፈሻ ዳር አስይዞ አቆመ ።

« ሒሊና መቼም በዕድሜ ከአንቺ ጠና ያልኩ ሰው ነኝ። ስለዚህ በዚህ ዓለም ላይ ከአንቺ ረዘም ላለ ጊዜ ቆይቻለሁ ። እኔ እንቺን ሳገባ የመጀመሪያው ምኞቴ በህይወቴ ላደርገው ፈልጌ ሳላሟላ ያሳለፍኩትን ሁሉ ለመፈፀም ነበር ። ታዲያ የአንቺ የመጀመሪያ ፍላጎት ደግሞ ልጅ መውለድ ሳይሆን ትምህርት መማር ነው ። ይህ የሁለታችን ፍላጎት ያለመጣጣም በመካከላችን ያለውን ልዩነት እያጋነነና እያሠፋ በተራ ነገሮች ላይ እንኳን ለመስማማት አለመቻላችን ሁልግዜ ያሳስበኛል ። »

« መስፍን ስለ እኔ የትምህርት ፍላጎት ከመጀመሪያ ቀን ግንኙነታችን ጀምሮ እስከዛሬ ያላነሳሁበት ጊዜ አልነበረም ። እውነትህን ነው ፤ ለእኔ ከሁሉም በላይ ትምህርት ነው ። ትምህርት ከወንድ እኩል ለሴት ልጅም ጠቃሚ መሆኑን የምትረዳ ይመስለኛል። እየህ ፤ ለእኔ ትምህርት ለህይወቴ መነሻና መንደርደሪያ እውራጎዳና ነው ። የቤት ልጅ ማለት ሴት ሆና የተፈጠረች ፤ ባለመማሯና ባለማወቋ ምርጫዋ የጠበበ ባሏን ለማርካትና ፍላጎቱን ለማሟላት የተፈጠረች መሆኗን አምና የተቀበለች ማለት እንዳልሆነ ለአንተ ልነግርህ አልችልም » አለችው ኮስተር ብላ ።

« አልገባኝም ። ትዳር ፤ ትምህርትና ልጅ አንድላይ አይሄዱም ያለሽ ማን ነው ? ።

« አይ መስፍን . . . » ሒሊና ሀሳቧን ለማሰባሰብ ሞከረች ።

« ሀሳቤን እልተረዳህኝም ብዬ አልገምትም ። በተለይ እዚህ አገር ልጅ ወልዶ ማሳደግ ቀላል እንዳልሆነ ታውቃለህ እንኳን ከትምህርት ጋር ከሥራም ጋር ይከብዳል ። እየህ ጋብቻውን ፈፅመናል ። ከመውለዴ በፊት ደግሞ መማር ስለምፈልግ የእኔ ትምህርት በአንተ የልጅ መውለድ ፍላጎትህ ላይ እንቅፋት መሆኑን ጠቅሰሃል ። አንዳንድ የሀገራችን ወንዶች የሚሉትም እንደዚሁ ነው። ልጅን እንደተፈጥሮ ፀጋ በመቁጠር ማሳደጉን በጋራ ኃላፊነት እንደመወጣት ፍጹማዊ የሴቶች ኃላፊነት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ ። ሌሎቹም ሴትን ማስረገዝና ማስወለድ ሲደፈርስ የተቃረበን ትዳር ማረጋጊያና ሲሞት የተቃረበን ፍቅር ማነቃቂያ አድርገው ይጠቀሙበታል ። ማለቴ በየምክንያቱ ትዳሩ ያልተስማማትን ወይንም በፍቅሩ ያልረካችን ሴት በቁጥጥር ሥር ለማዋል ፣ የሴቶች እርግዝናና ልጅ መውለድ እነኚህ ወንዶች የማይበጠስ ሠንሰለት አድርገው ይወስዱታል ። » ። ሒሊና ለመቀጠል አልፈለገችም ለመናገር የፈለገችውን በእንጥልጥል ተወችው ።

« ኦ ማይ ጋድ . . . » መስፍን የሰማውን አላመነም ።

« እንደዚህ የተበደላችሁ አልመሰለኝም ነበር ። ሁኔታው የተጋነነ ይመስላል ። »

ይህን እኮ ነው የምልህ ! ሴቶች ስለ እኩልነት ሲያወሩና በደላቸውን ሲናገሩ ለምን የተጋነነ ይሆናል ? አንድ ነገር ግልጽ እንዲሆንልህ እፈልጋለሁ ። አንተ እኔ የማስበውን በግድ ተቀበል አልልህም ከአንተም እንደዚሁ እጠብቃለሁ ። ልዩነታችን ሊያሳድገንና ሊያስተምረን ይገባል እንጂ ሊያራርቀንና ሊያናቁረን አይገባም ። ከአንድ ምንጭ የተቀዳ ውሃ እንደ'ነሆንም አንተም አትጠብቅ እኔም አልጠብቅም ።

« አባባልሽ ብዙውን ነገር ያስረዳኝ መሰለኝ ። ታዲያ ተከሊሉ፣ የማረጅ ሰርሞኒው ፣ መሃላው ለምን ነው ? እንደአባባልሽ ከሆነ ትዳር የሚለው ቃል ደባል በሚለው ቢለወጥ ተገቢ መሰለኝ ። » መስፍን የሕሊናን አባባል በአጠቃላይ አልተቀበለም ። እውነት ነው የምልህ « እኔነቴን በተፈጠርዬ ዝቅ የሚያደርገኝና ነፃነቴን ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥ ባህልም ሆነ ሀይማኖት መሠረት የለውም ፣ በአምላክ ዘንድም ተቀባይነት አያገኝም በማለት ወደ መስፍን ተመለከተች ። መስፍን ሀሳቡን ውጦ ትንሽ አሰላሰለ ።

« እኔ እኮ አንቺን እኩል አይደለሽም ብዬ አላውቅም በማደርገው ሁሉ ክብርሽን ነቅፌ ወይንም ዘንግቼ ያለፍኩበት ጊዜ የለም ታዲያ ምን ላይ ነው እኩልነታችን የተዛባው ? »

መስፍን የእኔ አባባል በአጠቃላይ አንዳንዱ ባሕላችን በሴቶች ላይ የሚያደርገውን ተጽእኖ የሚገልጽ ነው ። አንተ ከአካባቢህ ባካበትከው ልምድ እራስህን ሞርደህ የሀገር ቤቱን ዓይን አውጣ ተጽእኖ ስልት በተሞላው ለስላሳ አቀራረብ ሸፋፍነህ ነው ያቀረብከው።

« የእኔ አባባል የገባሽ አልመሰለኝም ። ለእኔ በመጀመሪያ ደረጃ ያለ ልጅ ትዳር ምንም ትርጉም አይሰጠኝም ። ሌላው ከአንቺ ልጅ ለመውለድ የፈለኩበት ምክንያት ለአንቺው ለራስሽም ዕንቆቅልሽ አይደለም ። እወድሻለሁ ። ባለቤቴ ነሽ . . . . አይ ሆፕ ማይ አንሰር ዊል ቤሪ ማች ሳትስፋይ ዩ » ሕሊና የመስፍንን አባባል እያጣጣመች በዓይኗ ገረመመችው ።

« በእውነት . . . በእውነት . . . ትወደኛለህ ? »

« ከዚህ የበለጠ እንዴት ብዬ ልንገርሽ ? እወድሻለሁ ! . . . እወድሻለሁ በቃ ። አደባባይ ወጥቼ አዋጅ እንድለፍፍ ትፈልጊያለሽ ? »

* * *

ራሄልና ሕሊና በጠዋት ተያይዘው ለመውጣት ተዘጋጅተዋል። መስፍን የሁለቱ ግንኙነት እንዲቋረጥ ጥረት ቢያደርግም አልተሳካለትም ። ለእሱ ግልፅ ባልሆነለት ሁኔታ እጅና ጓንት ሆነዋል ። መስፍን ከመኝታው ከመነሳቱ በፊት ራሄል ቤታቸው ደረሰች ።

« ሃኒ ዩ ዲድ ኖት ቴል ሚ ዛት ዩ ሃቭ አን አፖይንትመንት ዊዝ ራሄል ! »

« ጥናት ላይ አምሽቼ ስለተኛሁ ትዝም አላለኝ ። ይቅርታ » አለችው የመለማመጥ በመሰለ አቀራረብ ።

« ቴ ኬር ዩ ቴ ገልስ » ድምፁን ከፍ አድርጐ ተናገረ ። መስፍን በተኛበት ስለራሄልና ስለሕሊና ግንኙነት አሰበ ። ራሄል ከእርሱ ጋር ስለነበራቸውና ስላላቸው ግንኙነት ለሕሊና ትነግራታለች ብሎ ጥርጣሬ ቢገባውም ሀሳቡ እራሱን መልሶ ዘገነነው ።

« ጋሼ ያለውን ምክር ብሰማ ከዚህ ሁሉ እልደርስም ነበር ። አሁንም ለምን ግልፅ እድርጌ እንደማልነግራት አላውቅም ። ምንድን ነው ወደ ኋላ ጎትቶ የያዘኝ ? እውነት ጋሼ እንደሚለው ከራሄል ጋር ፍቅር ይዞኝ ይሆን ? . . . »

ራሄል ፣ ሕሊናን ከአንድ ትልቅ ህንፃ ስር ወደሚገኝ ትልቅ የልብስ መጋዘን ይዛት ገባች ።

« አይዞሽ እትፍሪ ፣ ማናጀሩን በደንብ ስላነጋገርኩት ግድ የለም ብሎኛል » ስትል ሕሊናን አደፋፈረቻት ። የሽቀጡን ክፍል አልፈው ወደ ውስጥ ዘለቁ ። ራሄል ሕሊናን ከአንድ ጥግ እቆይታ ፊት ለፊት የነበረውን በር በዝግታ ከፍታ ገባች ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ፈገግታ ተላብሳ ተመለሰች ።

ሕሊና ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካን ምድር ሥራ ዓለም ውስጥ ገባች ። ከራሄል ጋር በአንድ የልብስ መደብር አብረው

መስራት ጀመሩ ። ይህ ሁሉ ሲሆን መስፍን የሚያውቀው ነገር አልነበረም ። በየትኛውም ሁኔታ መስፍን ማወቅ እንዳለበት ብታምንም ማሳወቅ ያለባትን ወቅት መወሰኑ ሳይቻላት ቆየ ። ከዚህ ይልቅ ሥራውን በመለማመድ ላይ ትኩረቷን አደረገች ። ሥራውን በቀላሉ የምትለምደው አልመስልሽ እያላት አለመረጋጋት ፈጥሮባት ነበር ።

« ታዲያስ ቀላል አይደለም ? » ስትል ራሄል ጠየቀቻት በዕረፍት ጊዜአቸው ሠራተኛ ክፍል ውስጥ እንዳሉ ። የሕሊና ለሥራው አዲስ መሆን ይታወቅ ነበር ።

« ስውየው በጣም ስለሚፈጥን አልፎ አልፎ የሚለው አይገባኝም ። በስተቀረ ደህና ይመስላል ። » ቀና ብላ ወደ ራሄል ተመለከተች ።

« ግን ለምንድን ነው ገበያተኛ ሳይኖር መቀመጥ የማይፈቀደው ? እግሬንና ወገቤን በጣም ነው ያመመኝ ። » አለች ሕሊና ወገቧን በእጆቿ በመዳሰስ ህመሟን እየገለፀች ።

« አይዞሽ ፤ የማይለመድ ነገር የለም ። እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ እንደዚሁ ነበርኩ ። » ራሄል ሕሊናን ለማፅናናት ሞከረች ።

« ማርጀቴ ነው እንዴ ? ድሮ ጠንካራ ነበርኩ ። እንኳንና ለሠዓታት ለቀናትም ብቆም እንደዚህ ጉልበቴ በቀላሉ የሚሸነፍ አይመስለኝም ነበር ። » አለች ሕሊና ቀኝ እጇን ከወገቧ ሳታነሳ ።

« ቤት ስትገቢ እንዳትረሺ ። እግርሽን ለብ ባለ ውሃ ጨው ጨምረሽ ዘፍዝፊው ። ለእግርሽ ጥሩ ነው ፤ ይፍታታልሻል » አለቻት ራሄል በምክር መልክ ።

« እባክሽን ብልሃት ብልሃቱን ንገሪኝ ። እንዲህ በቀላሉ የምወጣው አልመሰለኝም »

« አ ! ማይ ጋድ ! በእኔ ይሁንብሽ ። ህመሙ ፣ ቁርጠቱ ሁሉ ለጥቂት ቀናት ነው የሚቆየው ። ሳታውቂው ይጠፋል ። »

ሕሊና እግሮቿን በሙቅ ውሃ ዘፍዝፋ ቴሌቪዥን ከፍታ መመልከት እንደጀመረች መስፍን በሩን ከፍቶ ገባ ።

« መቼም ይሄ የሀገር ቤት ልማድ አይቀርም ። ለምን ሻወር አትወስጂም ? » በማለት ሕሊናን ከእግር እስከራሷ ቃኘ ።

« የዛሬውስ የልምድ ሳይሆን የመከራ ነው ። ይልቅ ተቀመጥና ስለ ቀኑ ውሎዬ ላጫውትህ » አለችው መስፍን አጠገቧ እንዲቀመጥ እየጋበዘችው ።

« ሥራ ገባህ ፤ አያስገርምም ? »

« ምን ያስገርማል ፣ ደስ ይላል እንጂ »

« ስለ ደስታው እንኳ አላውቅም ። ለማንኛውም ከራሄል ጋር ነው የምሰራው ። »

« ከራሄል ጋር ? . . . መልካም ነዋ ፤ ምን አለ ! « አላት በቸልታ ። ፊቱን ከፊቷ እያሸሸ ።

* * *

ሕሊና አሜሪካን አገር የገባችበትን አምስተኛ ዓመት አከበረች:: በዚህ የህይወት ጊዜዋ የምታየውን ፤ የምታደርገውን ፤ የምትቀበለውንና የምትጠላውን ሁሉ በቅርብ የምታማክራት ጓደኛዋ ራሄል ብቻ ነበረች ። የሥራ ቅርበታቸው ፣ የፆታ አመለካከት ባህሪቸውና የቅርብና የሩቅ ትዝታቸው እያደገ ፣ እየጠለቀና እየጠበቀ መጣ ። የግል ህይወታቸው እየከሰመ ፣ ለጋራ ሀሳብና ፍላጎት ቦታ እየለቀቀ ፣ አንድነታቸውን አጠናከረ ። ራሄል መኖሪያዋን ለነመስፍን ቅርብ ወደሆነ ቤት ቀየረች ። ይህም ሁለቱ ጓደኛሞች በጋራ የሚሆኑበትን ስለአረዘመው የቀኑ ፤ የሣምንቱ ብሎም የዓመት ዕቅዳቸውን በማጣመር የትምህርት ፣ የሥራና የትርፍ ጊዜአቸውን በማቀናጀት ራሳቸውን ለማሳደግና ከአካባቢው ጋር ለማመሳሰል ሞከሩ::

ራሄል ለመስፍን ያላት ስሜት የቁጭትም የብቀላም ነበር ። ሆኖም ሁኔታውን በብልሃትና በዘዴ ይዛ ለመስፍን የነበራትን ጥላቻ ከሕሊና ጋር በግልፅ ለማውራት ብትችልም ሙሉ በሙሉ ሕሊና ለምትጠይቃት ጥያቄ በቂ መልስ ለመስጠት አልቻለችም ። የሕሊና ጥያቄዎች ያልመረመረችውንና ያልዳሰሰችውን የግል ስሜቷን ደግማ ደጋግማ እንድታስብበት ገፋፋት ። ሆኖም ከመስፍን ጋር ያሳለፉት ጥሩና መጥፎ ጊዜያት ስሜቷን መሻማቱ አልቀረም ። ይህን ግራ የሚያጋባ ስሜቷን ለማሸነፍና ከእራሷ ላይ ለማስወገድ ሌላ ሰው በመውደድ እራሷን ለማባበል ሞከረች ። በዚህ ሃሳቧ ግን አልገፋችበትም ። የመስፍንና የእርሷ ግንኙነት ትርጉም አልባ መሆኑን ውሎ ሲያድር ተረዳች ። ራሄል ይህን የውስጥ ስሜቷን ለሕሊና ገልፃላት አታውቅም ። ሕሊና ግን ከራሄል ንግግርና ድርጊት

ለመስፍን ያላትን ጥልቅ ስሜት ለመረዳት አላዳገታትም ። እያወቀች ያላወቀች በማስመሰል ትዳሯንና ጓደኛዋን ጎን ለጎን ማስታመሙን ቀጠለችበት ።

ፍጹማዊ የሆነው የአባቷ ምክር ነፃ ፍላጎቷን ለማራመድ የሚያስችላት ብቸኛ መፅናኛዋ ነው ። ያሬድ ፣ ሀሰንና መስፍን መልካምና ውጤታማ ለውጥ እንዲኖራት ቢረዷትም ሁሉም የራሳቸው የሆነ የመጨረሻ ግብ እንዳላቸው አውቃለች ። በእርሷና በራሄል መሀከል ያለው አንድነት ከልዩነታቸው በእጥፍ ድርብ ይበልጣል በማለት አሰበች ።

« ለጋሼ ያሬድ ያለኝ ስሜት ትርጉም በሌለው መጀመሪያና መጨረሻ ተንጠልጥሎ ቀረ ። ስለ እርሱ ባሰብኩ ቁጥር ሀሳቤን አሰባስቤ ደግ ነው ክፉ ፣ እወደዋለሁ እጠላዋለሁ ለማለት እንኳ አልቻልኩም ። ከህይወቴ ፍጹም ስርዝ ላወጣውም አልሞክርም ፤ አልችልም ። ጋሼ ያሬድ ከሌሎች ወንዶች ሁሉ የተለየ ነው » በማለት የተምታታ ሀሳቧን ገመገመች ። የእርሷና የራሄል ጓደኝነት መነሻ መስፍን ቢሆንም እያንዳንዳቸው ያሉበት ባህል የፈጠረባቸው ተፅእኖ ቀላል አልነበረም ። « የሰው ባህሪይ በአካባቢው ይጠነሰሳል ፤ ይታነፃል ፤ አካባቢውንም ይመስላል ። » በማለት ሕሊና ከየት ተነስታ የት እንደደረሰች ማሰቧን ቀጠለች ።

« . . . ራሄልን . . . መጀመሪያ እንደአገኘኋት ዘላባጅ እብድ ናት ብዬ ነበር ያሰብኩት ። ከዛ አልፈን በቁምነገር ተሳሰርን ። እኔ ወይስ እርሷ የተለወጥነው ወይንስ እርስ በእርሳችን ተማማርን »

ሕሊና ፣ የራሄልን ጉዳይ ማሰላሰል እንደጀመረች ወደ ኋላ ተመልሳ የከበቡሽን ጓደኝነት አስታወሰች ። ስለ ከበቡሽ አሁን ያላትን ፍቅርና አክብሮት ከራሄል ጋር አመሳሰለች ። « ከልብ የመነጨ ጓደኝነት ዘለዓለማዊ ነው » በማለት ሁለቱም ለህይወቷ ስለ አደረጉት መልካም አስተዋጽኦ አመሰገነች ።

* * *

ቀኑ አርብ ፣ ወራቱ ፀደይ ነበር ። ፀሐይ በወርቃማ ነፀብራቋ ምድሩን አልብሳ ወደ መጥለቁ ተቃርባለች ። በመንፈስ ላይ ያለው መልካም የፀደይ አየር ለከተማው ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል ። ዛፎቹ ለምልመው ፣ ምድሩ አረንጓዴ ሳር ለብሶ ፣ በየመናፈሻውና በየመኖሪያ ቤቱ አካባቢ የተተከሉ አበባዎች ፈክተው አካባቢውን አሸብርቀውታል ። የወራቱን አመቺነት በመሸማት መንገድ ላይ ውር ውር የሚለው የሰው ብዛትና ዓይነት ለአንዳች ህዝባዊ በዓል ዝግጅት የሚያደርግ ይመስል ነበር ። ሕሊና ከሥራዋ እንደወጣች አውቶቡስ ተሳፍራ ወደ ትምህርት ቤት አመራች ። ለመጀመሪያ ክፍለ ጊዜዋ የጽሁፍ ፈተና ዝግጅት የሚረዳ በመሆኑ ለሕሊና ብዙ ጊዜ አልፈጀባትም ። ሁለተኛና ሦስተኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ደግሞ ለዕለቱ በመሰረዙ ወደ ቤቷ ከመመለስ ሌላ ምርጫ አልነበራትም ። ጊዜዋን እንዴት እንደምታሳልፍ እያሰላች ወደ ቤቷ አዘገመች ።

« የሳምንቱ ድካም . . . በቀላሉ አይለቀኝም ። እንደገባሁ ሻወር ወስጄ አልጋዬ ላይ እሰፍራለሁ ። » ስትል ፍጹም እረፍት ለማድረግ ራሷን አዘጋጅታ ፣ ቤቷ ለመድረስ እርምጃዋን አፋጠነች።

ሕሊና ቤቷ በር ስትደርስ ኃይለኛ ድካም ውስጥ ነበረች ። በትከሻዋ ያንጠለጠለችውን የደብተር ቦርሳ አሳርፋ የቤቱን በር ቁልፍ አወጣች ። በሩ አልከፈት ስለአላት መልሳ መላልሳ ቁልፎቹን በመለዋወጥ ብትሞክርም የሚከፍተው አልነበረም ። በሩን ደግማ ደጋግማ ብታንኳኳም መልስ የሰጠ የለም ። ጮክ ብላ « መስፍን ! መስፍን ! » ስትል ለረዥም ጊዜ ተጣራች ። ከግራና ከቀኝ የነበሩ

ጎረቤቶቿ በድንጋጤ መንፈስ በሮቻቸውን ከፍተው ብቅ ብቅ አሉ ። ሕሊና መሆኗን እንዳወቁ ተመልሰው ወደ ቤታቸው ገብተው በራቸውን ዘጉ ።

ሕሊና በድንጋጤ ተውጣ የምታደርገው ጠፋት ። ጎረቤቶቿን በመረበሿ ተሰምቷት ቆሞ ወደነበረው ሊፍት ገብታ ወደ አሥረኛው ፎቅ ሄደች ። ራሄል ክፍሏ ውስጥ አልነበረችም ።

« ሰዎቹን ምን ዋጣቸው ? . . . እሺ ራሄል የሆነ ነገር አጋጥሟት ሄደች ይባል መስፍን ወዴት ሄደ ? በሩን ደግሞ ምን አደረገው ? የእኔ ቁልፍ ለምን አልከፈተውም ? ቁልፉ ሁለት ጊዜ ዞሯል ። ታዲያ ለምን አልተከፈተም ? » ሕሊና ለጥያቄዋ መልስ ማግኘት አልቻለችም ። ሀሳቧን በማውጣትና በማውረድ ለጥቂት ጊዜያት ራሄል በር ላይ ቆማ ጠበቀች ። ሊፍቱን አልጠበቀችም ። ወደሁለተኛ ፎቅ ቁልቁል ሮጠች ። እንደገና በሩን ለመክፈት ሞከረች። ኃይሏን ሁሉ የተዘጋው በር ላይ በማሳረፍ ስትገፋው በሩ ተበርግዶ ተከፈተ ።

ከግድግዳ ጋር በመጋጨት የፍንዳታ ያህል ድምፅ አሰማ ። በሩን ለመዝጋት ሳትቸኩል ፈጥና ወደ ሳሎን አመራች ።

« መስፍን ! መስፍን ! » ደጋግማ ተጣራች ። ሳሎን ቤቱን አልፋ ወደ ገበታ ቤት ገባች ። ያየችውን አላመነችም ። ሕሊና ሀሳቧን ለማሰባሰብ ሞከረች ። ከወንበሮቹ በአንዱ ጠረጴዛ ላይ አረፍ አለች ። ጠረጴዛው ላይ የተቀመጡትን የምግብ ሳህኖችና ብርጭቆዎች ተመለከተች ። « ማን ነበር ወይስ እነማን ነበሩ ? » በማለት ራሷን ጠየቀች ። መጀመሪያውኑ በሩ ከውስጥ እንደተቀረቀረ ጥርጣሬው ነበራት ። ሆኖም ማን ለምን እንደቀረቀረው መገመት አልቻለችም ። ወደ ምግብ ጠረጴዛው ደግማ ቀረበች ። ጠረጴዛው ላይ የነበሩት ሳህኖችና ብርጭቆዎች ጥንድ ጥንድ ነበሩ ። በምግቡ ሥነ ሥርአት ላይ ሁለት ሰዎች እንደነበሩ አስተዋለች ። ሀሳቧን

ሳትቋጭ ከፍታ የተወችውን በር ለመዝጋት ወደ ዋናው በር አዘገመች:: በሩን ከዘጋች በኋላ ወደመኝታ ቤቷ ገብታ አልጋዋ ላይ ልትቀመጥ ስትል ዓይኖቿ አንድ ቦታ ላይ ተተክለው ቀሩ :: ያየችውን አላመነችም ቀይ የውስጥ ሱሪ ! በጣቶቿ ጫፍ አንጠልጥላ አገላብጣ ተመለከተችው :: ራሷን በማወዛወዝ በመፀየፍ መልሳ አልጋው ላይ ወረወረችው ከመኝታ ቤቷ በዝግታ በሩን ከፍታ ወጣች:: ብዙም ሳትራመድ መስፍን በበሩ ሲገባ በማየቷ ባለችበት ረግታ ቆመች :: መስፍንን በንዴትና በቁጭት ከላይ እስከ ታች ገላመጠችው ::

« ሃይ ሃኒ ! ኖ ስኩል ቱ ዴይ ? » በማለት መስፍን ሕሊናን ለማቀፍ ሲጠጋ ሕሊና እራሷን አንድ እርምጃ ወደ ኋላ አሸሸች ::

« ምን ሆንሽ ደግሞ ? » አለ በእጁ ይዞ ለማቆም እየሞከረ :: የመኝታ ቤቱን በር በቁጣ ዘግታ ከውስጥ ቆለፈች :: መስፍን በሩን እንድትከፍትለት በልመና መልክ ቢያባብላትም ፍቃደኛ ሳትሆን ቀረች:: ድርጊቱ እንቆቅልሽ ሆነባት ::

ሁሉን ነገር ችላ ብላ ሻወር ወሰደች :: ንዴቷን ከድካሟ ጋር በመታጠብ እራሷን ለማረጋጋት ታገለች :: መስፍን ሳሎን ተቀምጦ ቴሌቪዥን ይመለከት ነበር :: ከሻወር መልስ አጠገቡ በነበረው በአንደኛው ሶፋ ለውነቷን አሳርፋ ጥቂት ጊዜ በዝምታ አሳለፈች:: መስፍን በስርቆሽ ሲመለከታት ዓይን ለዓይን ተያዩ ::

« እስቲ የሆነውን አስረዳኝ :: ለእኔ መቼም ትልቅ ዕንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ » ስትል አፈጠጠችበት :: መስፍን ሶፋው ላይ በመገላበጥ ጥቂት ታሸ ::

« ዋት ዱ ዩ ዋንት ሚ ቱ ኤክስፕሌይን » ሕሊና ሊሸሿት ያሉትን የመስፍንን ዓይኖች በዓይኖቿ ተከተለች ::

« ዛሬ የሆነውን ማወቅ እፈልጋለሁ :: »

« ከስራ እንደመጣሁ ምግብ በልቼ ዎክ ለማድረግ ወጣሁ:: አሁን ስመለስ አንቺ እሳት ጎርሰሽ እሳት ለብሰሽ ጠበቅሽኝ :: እኔም የሆነውን አላውቅም »

« እኔ በሩን ሳንኳኳ ቤት ውስጥ አልነበርክም ? »

« ዋት አር ዩ ቶኪንግ አባውት ? »

« እኔ ከትምህርት ቤት ስመጣ በሩን ለመክፈት ብሞክር እምቢ አለኝ :: ያለ ዛሬ ይህ በር እንዲህ ሆኖ አያውቅም :: »

« ድንገት ዩ ማይት ሃቭ ሚስድ ዘ ራይት ኪ »

« ኖ አይ አም ሹር ፤ አልተሳሳትኩም :: በተጨማሪም ምሳህን ብቻህን አልበላህም :: » አለችውና ተንደርድራ ወደ ምግብ ቤት ሮጣ በእጇ ጭላጭ የብርትኳን ጭማቂ ያለባቸው ሁለት ብርጭቆዎች ይዛ ተመለሰች ::

« አንደኛው ብርጭቆ ቆሻሻ ነበር :: አይ ዩዝድ አናዘር ዋን :: ወዴት እያመራሽ እንደሆነ አልገባኝም :: » ይሄስ አለችው አንደኛውን ብርጭቆ ወደፊቱ ደቅና በአመልካች ጣቷ ብርጭቆው ጠርዝ ላይ ያለውን ቀይ የሊፕስቲክ ቀለም እያሳየችው ::

የመስፍን አነጋገር የሕሊናን ትዕግሥት ተፈታተነው :: ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነስታ ወደ መኝታ ቤት ገባች :: በቀኝ እጇ ቀይ የውስጥ ሱሪ አንጠልጥላ ተመለሰች :: የያዘችው የውስጥ ሱሪ መስፍንን አስደነገጠው :: ዓይኖቹን ወደ ምድር ተከለ ::

« እኔ ቀይ የውስጥ ሱሪ በህይወቴ ገዝቼ አላውቅም :: ይሄኛውስ ከየት እንደመጣ ልትነግረኝ ፈቃደኛ ነህ ? » አለችው ንዴት በተሞላበትና በተቆራረጠ አነጋገር ::

መስፍን በጎን አሻቅቦ ወደ ሕሊና ተመለከተ :: ፊት ለፊቱ ወደ አለው ሶፋ እየተመለከተ እንድትቀመጥ ጠየቃት :: በእጇ የያዘችውን የውስጥ ሱሪ ወደ ወንበሩ ወርውራ ሶፋው ጫፍ ላይ

እጆቿን ሰብስባ ተቀመጠች ። በመሀከላቸው ለጥቂት ደቂቃዎች ፀጥታ ሠፈነ ። መስፍን ንግግሩን ከየት እንደሚጀምር አሰበ ።

« ሕሊና ፣ ሌት አስ ሊቭ ኢት አስ ኢት ኢዝ ። እንደዚሁ እንኑር ። »

« ኖ መስፍን እንደዚህ ዓይነት የድብብቆሽ ኑሮ አልፈልግም። ግልፅልጽ አድርገን ካልተወያየን . . . »

« ኦኬ ! ኦኬ ! ጉደዩ እንደዚህ ነው ። እኔና አንቺ እንደ ባልና ሚስት መኖር ካቆምን ቆይተናል ። እኔ እዚህ ቤት የምኖረው እንደ ደባል ነው ። ዩስ ዊ ሼር ኤ ቤድ ኤንድ ኤ ሃውስ በት ኢት ኢዝ ኖት ዛት ማች ኢምፖርታንት ፣ አይ ዱ ኖት ኖው አይ ፊል አይ ሎስት ዩ ሰም ሃው ። »

« ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም ። ባልና ሚስት የሚሰሩትን ሁሉ እንሠራለን የአንተ የጋብቻ ትርጉም ምንን እንደሚጨምር አላውቅም ። »

« ሕሊና የአንቺ ጋብቻ በቤትና በመኝታ ላይ መቆራኘትን ብቻ የሚያጠቃልል ከሆነ ለእኔ እውነተኛ ትዳር አይደለም ። » መስፍን ጥቂት አሰብ አድርጎ « አስታውሺ ፣ መጀመሪያ ሀገር ቤት ገና ስንተዋወቅ ሚስት ሳላገባ የቆየሁበት ምክንያት እውነተኛ የትዳር ጓደኛ እስከማገኝ ድረስ ነው ብዬ ነግሬሽ ነበር ። አንቺን ሳገባሽ ከሚስትነት ባሻገር ጓደኝነትሽን በመፈለግ ጭምር ነበር ። አንቺ ግን በአሜሪካን ህይወትና በትምህርት ዓለም ስለተጠመድሽ ለጓደኝነታችን ምንም ቦታ አልሰጠሽውም ። ተያየን ፣ ተዋደድን ፣ ተፋቀርን ፣ ትዳር ከመሠረትን ይኸው አምስተኛ ዓመታችን አለፈ ። ከዚህ ሁሉ በኋላ አንድ ፍሬ እንኳ ማፍራት አልቻልንም ። » ሕሊና በቀኝ እጇ ጠረጴዛ ላይ ወደ ተቀመጠው የውስጥ ሱሪ አመለከተች ።

« ታዲያ ይሄን ከምትለው ጋር ምን አገናኘው ? »

« የምለውን አዳምጪ ። እኔና አንቺ ስለትዳር ያለን አመለካከት በጣም የተራራቀ ነው ። ለአንቺ ህይወት የመጀመሪያውና ትልቁ ቁም ነገር ትምህርት ነው ። ለሚቀጥለው እየተዘጋጀሽ ነው ። አይ ዱ ኖት ኒይድ ኤ ፓርት ታይም ዋይፍ ። ዋት አይ ኒድ ኢዝ ኤ ፉል ታይም ዲቮትድ ዋይፍ ኖ ሌስ ! »

« በጣም ትገርማለህ ! በአጠቃላይ አንተ የምትፈልገው እውነተኛ የትዳር ጓደኛ ሳይሆን ልጅ አሳዳጊ ገረድ ነው ። ለመሆኑ የእኔ መማር ለምን ይኼን ያህል ያንገበግብሃል ? ሠርቼ ፣ ለፍቼ ትዳራችንን ከአንተ እኩል ለመደገፍ ጥረት አደርጋለሁ ። ይሄ ደስ ሊያሰኝህና ሊያኮራህ ይገባ ነበር ። »

« አሁን ንግግራችን የትም አያደርሰንም ። በአጠቃላይ ለምሰራው ነገር ሁሉ አይ ነው ዩ ኖው ዘ ኤክስፕለኔሽን ዛት ኢንክሉድስ ቱ ዴይስ እንሲደንት » አላትና ባለችበት ትቷት ወደ መኝታ ቤት ገባ ።

ሕሊና በተፈፀመው ድርጊትና በመስፍን አነጋገር ክፉኛ ስሜቷ በመደፍረሱ ባልጠበቀችው መንገድ ህይወቷ ተነካ ። ሀሳቧ ሁሉ ባዶ ሆነባት ።

« ትዳር . . . ድሮም ልጨብጠው እንደማልችል የሚሰማኝ ነገር ነበር . . . ። በአንድ በኩል እም ሀቅ ነው ። ህይወቴ ኢትዮጵያ ከነበርኩበት ጊዜ ተለውጧል ። እኔ እራሴ አንዳንድ ጊዜ ሳስበው ግራ ይገባኛል ። » በማለት ሕሊና ለጥቂት ጊዜ ሀሳቧን ወደ ሀገር ቤት መለስ አደረገች ። አለላ ከተማ የነበረችበትን ቤት አስታወሰች ። ከሀሰን ጋር የነበራትን ጓደኝነትና መጨረሻ ላይ እንዴት እንደተለያዩ አስታወሰች ። ራሷን « የዋሀ » በማለት በዛን ወቅት የነበረችበትን ደረጃ ገመገመች ። ከሀሰን ጋር ለመለያየት ራሷን ምን ያህል እንዳስጨነቀች ትዝ አላት ። ሀሰን እንደ ጓደኛ መስፍንን እንደባል

በመውሰድ በሁለቱ ወንዶች መሀከል የነበራቸውን አንድነትና ልዩነት እያወዳደረች ዝርዝር ሁኔታዎችን ተመለከተች ።

« ወንዶች ፤ የሴቶችን ህይወትና ምንነት ለማንበብ እንደመቸኮላቸው ሁሉ በቅምሻ ብቻ እራሰቸውን ያረካሉ ። ደግሞ ወዲያው ይሰለቻሉ ። ግን እኮ ሁሉም ወንዶች አንድ አይደሉም ። » ሕሊና ሀሳቧን አሰባሰባ ራቅ ወዳለው ትዝታዋ ራሷን አሸጋገረች ።

« ጋሼ ያሬድ ከእነኚህ ሁሉ የተለየ ነው ። በሴትነቴ ለመርካት አልቸኮለም ። በኃይልም ለመጠቀም አልሞከረም ። አስተዋይነቱና ትዕግስቱ ከሁሉም ልዩ ያደርገዋል ። ጋሼ ያሬድ እንደ ህይወቱ ይሳሳልኛል ። እንደሚወደኝም . . . መውደድ . . . ምነው ዘላበድኩ ! » ሕሊና ሀሳቧን ለመግታት ሞከረች ። በዕድሏ በጣም አዘነች ። ሳግ ይዟት ዓይኖቿን ወደ ጣሪያው አቀናች ። ዕንባዋ እንዳይፈስ ታገለች ። ካለችበት ተነሥታ ወደ መኝታ ክፍል ገባች ። ቁምሣጥኗን ከፍታ ዕቃዎቿን አስተካከለች ። ከሀገር ቤት ያመጣችውን ሻንጣ ከፊት አደረገች ። የመጥረቢያዋን ፎቶግራፍ አንሥታ ወደ ደረቷ በማስጠጋት ከአንዳች ሰው ጋር እንደሚነጋገር ወደ ጣሪያው ተመለከተች ።

« አባዬ ይኼ ደግሞ ሌላው ክፉ ቀን ነው ። በል እንግዲህ ከዚህ መዓት ደግሞ እንደለመድከው አውጣኝ ። » አለችና የያዘችውን ፎቶግራፍ ወደ ሻንጣው አስገባች ። አልጋ ላይ ተከናንቦ የተኛው መስፍን ድምጽ ሲሰማ መገላበጥ ጀመረ ።

ሕሊና ከመስፍን ጋር ደግማ ላለመነጋገር ሻንጣዋን ዘግታ ፈጥና ከክፍሉ በመውጣት የምትፈልጋቸውን ዕቃዎች ከወዲያ ወዲህ እያለች በማነሳሳት ላይ ነበረች ። መስፍን የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ወጣ ።

« የት ለመሄድ ነው የምትጣደፊው ? » አላት ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ ፤ « ምን ያስቸኩልሻል ፤ ቢነጋልሽ አይሻልም ? » ሲል ጨመረ ።

« ለምኑ ነው የቀኑን ብርሃን የምጠብቀው ። ከአሁን በኋላ እኔና አንተ በአንድ ጣሪያ ሥር ልናድር አይገባንም ። »

« ኢፍ ኢት ኢዝ ኖት ሴክረት ዌር አር ዩ ጎይንግ ? »

« ዪትም ብሄድ የትም ፣ አይ ሲንክ ኢት ኢዝ ነን ኦፍ ዩር ቢዝነስ » መስፍን አንድ እርምጃ ወደ ሕሊና ተራመደ ።

« እኔ አባባሌ ለክፉ ነገር አይደለም ። ከሀገር ነጥዬ ያመጣሁሽ እኔ ነኝ ። ድንገት እንኳ አንድ ነገር ቢደርስብሽ በማለት ነው ። ነገር ግን አሜሪካ ነፃ ሀገር ነው . . . ካልፈለግሽ . . . እንደፈለግሽ ለማንኛውም ኪፕ ኢን ተች ። »

ሕሊና የምትፈልጋቸውን ነገሮች አሰባስባ ሻንጣዋን እየጎተተች ወጣች ። የራሄልን በር ስታንኳኳ ያልተዘጋጀችበትን የቀኑን ዜና እንዴት አድርጋ እንደምትገልፅላት እያሰበች ነበር ። በሩ ግን አልተከፈተም ። እዚያው ቆማ የት እንደምትሄድ በማሰብ ላይ እያለች ድንገት በሩ ተከፈተ ። ራሄል ነበረች ። ሕሊና የራሄልን ሁኔታ የቀኑ ሌላ አጋጣሚ ሆኖ አገኘችው ። ራሄል በሕሊና መምጣት የተገረመች አልመሰለችም ።

« ወጣሽ » አለች ከፊቷ ላይ ተንጨባሮ የተበተነውን ፀጉሯን በከፊል እያስወገደች ። ራሄል ደስተኛ ለመምሰል ብትሞክርም ፊቷ ላይ የሚታየው ጉስቁልናዋ ለሕሊና በግልፅ ታይቷት ነበር ። ሕሊና ራሄልን ተከትላ ወደ ውስጥ ገባች ። ራሄል ያገኘችው ሶፋ ላይ በቁሟ ወደቀችበት ። ሕሊና ግን ተክዛ መሀል ሳሎን ላይ ፈዛ ቀረች ።

« ተቀመጪ እባክሽ » አለቻት የቆመችውን ሕሊናን በሀዘኔታ እያየቻት ። እንደመባነን ብላ « እ . . . እሺ » አለቻት ። ከሄደችበት

የሀሳብ ጉዞ ተመልሳ ከራሄል ፊት ለፊት ተቀምጣ በእርጋታ የራሄልን ሁኔታ እያጠናች ውስጧ ያቆጠቆጠውን ጥርጣሬ ፈራች ፣ ቀፈፋት:: ከአካባቢው መራቅ ፣ መሰወር ተመኘች :: በልውጣ ልቅር ስታመነታ ድንገት በሩ ተንኳኳ :: ሕሊና በሩን ከፍታ ወደ ሳሎን ስትመለስ ከኋላዋ መስፍን ተከትሏት ነበር ::

« እንደምን ዋለሽ ራሄል » አለና ሁለቱን ሴቶች አልፎ ወንበር ፈልጎ ተቀመጠ :: ሕሊና የራሄልን ምላሽ ለመስማት በጉጉት ጠበቀች :: እየተጫወቱባት እንዳይሆን ፈጠረዋን ለመነች :: ራሄል ለመስፍን የሰጠችው የሠላምታ አፀፋ ከዘወትር አባባሏ የተለየ አልነበረም :: መስፍን ራሄልን ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ « ይኼውልሽ መጨረሻችን እንዲህ ሆነ » በማለት ወደ ሕሊና ተመለከተ ::

« ይህ መቼም የአንተ መጨረሻህ እንጂ የሕሊና እንኳ መጀመሪያዋ ነው :: ለአንተ ሰዎች ሁሉ ለፍላጎትህና ለስሜትህ ማርኪያ ብቻ የተፈጠሩ ናቸው ::መስፍን ! አትሻሻልም ሼም ኦን ዩ:: ስነገሩ ይህ እንደሚሆን እጠብቅ ነበር :: ሆኖም በጣም ፈጠነ :: ነገሩን ቅድም በስልክ ስትነግረኝ አላመንኩም :: ለምን እንደነገርከኝም አላወቅሁም :: በሁኔታው ከአንተ ጋር እንድሆን አስበህ ከሆነ ተሳስተሃል :: » ራሄል ከመቀመጫዋ ተነስታ የሕሊናን ሻንጣ ተቀበለች ::

« በል የምትለውን በልና ውጣልን :: ጊዜው እየመሸ ነው እንተኛበት :: » በማለት ሻንጣውን ጎትታ ወደ ውስጥ ገባች :: ራሄል ሰባልና ሚስቱ የውይይት ቦታ በመልቀቅ ተባበረች ::

« ምን አስቸኮለሽ ? ቤቱ የሁለታችንም ነው :: አሁን ሰው ቤት ከማደር ይልቅ ወደ ቤታችን እንሂድ » አላት መስፍን ::

« የምትናገረውን የምታውቅ አይመስለኝም :: » ሕሊና ከተቀመጠችበት ተነስታ ራሄል ወደ አለችበት አመራች :: መስፍን ብቻውን እንደተቀመጠ ቀረ ::

ራሄል ወደ መኝታ ቤት የገባችውን ሕሊናን አቀፈቻት :: ሕሊና ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች ሳግ በተሞላው አባባል « እኔን ፣ እህቴን ፣ ጎዳሽ ! ይሄ አረመኔ ለማንም አይተኛም :: አይዞሽ ! አይዞሽ ! » አለች :: ሕሊና በውስጧ ያመቀችውን ሀዘን ፣ ሀፍረት ፣ ውርደት አምቃ ማስቀረት አልቻለችም :: ያቀፈቻትን አጥብቃ ያዘች እንገት ለአንገት ተጣምረው የቅርብ ዘመድ እንደሞተባቸው ለጥቂት ጊዜ ተላቀሱ ::

« ምግብ ለማብሰል ስል ቤቱ ሄጄ ነበር :: ወደ ውስጥ ለመግባት ስሞክር መስፍን ከለከለኝ :: መጀመሪያ አልገባኝም :: ገፍቼው ስገባ ግን ያየሁትን አላመንኩም :: ድርጊቱ በጣም ስለአናደደኝ የምይዘውና የምጨብጠውን አሳጣኝ :: ይሉኝታ ቢስ እሱ ምንም አልመሰለውም ፣ « ሂ ቶልድ ሚ ቱ ጎ አውት ዶንት ኢብን ትራይ ቱ ዲስግሬስ ማይ ገስት » አለኝ :: ሕሊና ለአንቺ መቼም ኢት ኢዝ ኤ ብለስንግ » አለች ራሄል ዕንባ የሚተፉትን የሕሊናን ዓይኖች እየተመለከተች :: ሕሊና የተፈፀመባት በደል ከባድ ቢሆንም የፈራችውና የጠረጠረችው ዕውን ባለመሆኑ ደስ አላት :: ለራሄል ያላት ፍቅርና አክብሮት የበለጠ ጎለበተ :: ቀደም ስል የነበራትን ጥርጣሬ ከአሁኑ የራሄል ሁኔታ ጋር አነፃጽራ እራሷን ወቀሰች :: ተስፋ በተሞላው አስተያየት ወደ ራሄል ተመለከተች :: ፍፁም ፍቅር በተሞላበት አባባል « አይዞሽ ምንም አልሆንኩም :: አይ ዊል ቢ ኦኬ » አለቻት ::

« ራሄል ይቅርታ አድርጊልኝና እንዲያው ለነገሩ ማን ነበረች ሴትዮዋ ? » ስትል ሕሊና ጠየቀቻት :: ራሄል ለሕሊና ጥያቄ መልስ ለመስጠት አልቸኮለችም ::

« ምን ታደርግልሻለች :: ይልቁንስ ሳይርብሽ አይቀርም ፣ ነይ ምግብ እንብላ » ብላ ወደ ኩሽና መራመድ ጀመረች ::

« ትናደዳለች ብለሽ አትፍሪ ። በእኔና በመስፍን መሀከል ከአሁን በኋላ ግንኙነት ይኖራል ብለሽ አታስቢ » አለች እጇን ይዛ ።

« ስሟን አላውቀውም ። ማን ብዬ ብነግርሽ ማንን ታውቂያለሽ ? »

« በእናትሽ አሜሪካዊት ናት ? » አለች ለማወቅ መጓጓቷ እያስታወቀባት ።

« አዎ አሜሪካዊት ናት ። በሀገሩ አባባል አፍሪካን አሜሪካን ነች ። ጥቁር ሆነች ነጭ አሜሪካዊት ኢትዮጵያዊት ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ጉዳዩ የእርሱ ነው ። እርሱ ይቸገርበት ። » ተያይዘው ወደ ኩሽና ገቡ ።

* * *

የመስፍንና የሕሊናን መለያየት ዘመድ አዝማዱ እንደሰሙ የቅርቡ በስልክ እና በግንባር የሩቁ ደግሞ ደብዳቤ በመፃፍ ተስማምተው አብረው እንዲኖሩ ተማፀኑ ። መስፍንም በተቻለው መጠን ሕሊናን ለማግባባት ሞከረ ። ሆኖም ሕሊና በመለያየታቸው በመፅናቷ ምክሩና ልመናው ሊበግራት አልቻለም ።

አበራና ከበቡሽ ፣ እንዲሁም ወ/ሮ በላይነሽ « በሰው ሀገር እንዳትንከራተቺ ትዳርሽን አትፍቺ » በማለት የመቆርቆር ስሜታቸውን ቢገልጹላትም ሕሊና ግን ልትለወጥ አልቻለችም ። ሕሊና ከመስፍን ከተለየችበት ዕለት አንስቶ ለሁለት ወራት ያህል ከራሄል ጋር በአንድ ቤት ተዳብለው መኖር ጀመሩ ። ራሄል ለሕሊና ብቸኛና የቅርብ ሰው በመሆኗ ሕሊና ጉዳቷን ፣ ደስታዋን እያዋየቻት ጊዜዋን አሳለፈች ።

ሙሉጌታ የወንድሙን ፀባይ አስቀድሞ ስለሚያውቀው በሁለቱ መለያየት ብዙም አልተገረመም ። ሕሊና በመለያየቱ

መፅናቷን ካረጋገጠ በኋላ በእርሱ በኩል ምንም ዓይነት ቅሬታ እንዳይሰማት ገልጾ በችገራት ጊዜ ሁሉ ከጎኗ እንደሚሆን ነገራት ።

« ሕሊና እኛና አንቺ ቤተሰቦች ነን ። መወለድ ቋንቋ ነው ። የእኛን ቤተሰብ ታሪክ ተካፍለሻል ። በአንቺና በመስፍን መሀከል ስለተፈጠረው ያለመግባባት በጣም አዝናለሁ ። ቢሆንም ለመለያየት ያደረግሽውን ውሳኔ አከብረዋለሁ ። »

አበራና ከበቡሽ የፍቺው ወሬ እንደደረሳቸው የማበረታቻና የማፅናኛ ደብዳቤ ፃፉላት ።

« ታስታውሺ እንደሆነ ገና በፊት ግንኙነታችሁ ሲጠነሰስ አስጠንቅቄሽ ነበር ። ዋናው ነገር ግን ለመማር ያለሽን ጉጉት ስለማውቅ ከአሜሪካን እንድትቀሪ አልገፋፋሁሽም ።

የመስፍን ጋብቻ የአንቺን በአሜሪካ የመማር ዕድል ያጣመረ ስለነበር ነጥሉ ማየትና መቀበል አልተቻለም ። ስለመስፍን ፀባይ በደፈናው ለአንቺ መግምገምና ማስረዳት አልፈለኩም ። አስተዋይ በመሆንሽ በቅርቡ ትደርሺበታለሽ ብዬ ገምቼ ነበር ።

« እህቴ ሕሊና ከመስፍን በመለየትሽ ብዙ እንደማትቆጪ ተስፋ አለኝ ። መስፍን በአስተሳሰቡ አንቺን አይመጥንም ። የሁለታችሁም አስተዳደግ ለየቅል ነው ያም የራሱ የሆነ ተፅእኖ ይኖረዋል ። አንቺን የሚመኙ ብዙ ናቸው ። ቁም ነገሩ በጣም የምትጓጊለትን ትምህርት ዳር አድርሺ . . . » በአጠቃላይ የደረሰብሽን ችግር በቀላሉ እንደምትወጪ አልጠራጠርም ። ያሰፍሽባቸው የህይወት ጉዳናዎች ቀላል አይደሉም ። ባንቺነትሽ በአሸናፊነት

ስለተወጣሽው ለኔ ሕሊና ያለምንም መደለያ ቃል ፣ እንዳንቺ ጠንካራ ፣ አስተዋይ፣ ታታሪና ቆራጥ ሴት በህይወቴ አጋጥሞኝ አያውቅም አንቺ የመጀመሪያዋ ነሽ ።

በዓይነ ህሊናዬ የተነሳሽበትንና የደረስሽበትን ሳሰላስል ፣ ድንቅ ሥራ ፣ በጠበብት የተመራ አንዳች የምርመራ ውጤት ይመስላል ። ይህ ረቂቅ መርህ እንደሚቀጥልና የደረሰብሽ ችግር ትዕግስትሽን እንደማይፈታተነው እርግጠኛ ነኝ ። ለዚህ እምነቴ ሌላ ምንም ምክንያት የለኝም ውስጥሽ ከማየው ጥንካሬሽ በስተቀር ። አንቺ ለኔ የሴቶች ሁሉ ቁንጮ እንደንብ ታታሪ፣ ሥራሽ በምሣሌነት ሊጠቀስ የሚገባ ሰብአዊ ንብ ነሽ ።

የአበራ ደብዳቤ ለሕሊና ምንም አዲስ ነገር ባይጨምርም አባባሉ የእምነቷ መሠረት ከሆነው ከአባቷ ምክር ጋር የተያያዘ በመሆኑ ደጋግማ አነበበችው ። ደብዳቤው ያዘለው መልዕክት አፅናኝና ጥንካሬ እንዲኖራት የሚያበረታታ መሆኑን አሰበች ።

« እስቲ እነማን ናቸው ከእኔ ጋር ለመሆን ምኞት ያላቸው?» በማለት ያለፈ ህይወቷን ለማስታወስ ስትሞክር በደግና በደስታ ትዝታ ሀሳቧን የተሻማው አንድ ሰው ብቻ ነበር ። « አይ ጋሼ ያሬድ ለምን መልኬ መላልኬ በሀሳቤ ውስጥ እንደምሰነቅረው አይገባኝም » በማለት ሀሳቧን ለማሰባሰብ ሞከረች ። ሆኖም የሀገር ቤት ወሬ በተነሳና ደብዳቤ በደረሳት ቁጥር የያሬድ ትዝታ ሀሳቧን መሻማቱ አልቀረም ። ከራሄል ጋር አብራ በመኖር ላይ እያለች ነበር በቅርቡ የዓፈላት ደብዳቤ የደረሳት ።

« እማሆይ ደብረ ሊባኖስ ከገቡ ቆዩ ። ከተማ ለመኖር ፈቃደኛ አልሆኑም ። « ከምትኩም ዘመድ

እንዳይቀብረኝ ለቅሶም እንዳይለቀስልኝ » በማለት ያላቸውን ንብረት በእኔ አደራነት ለአንቺ አውርሰው ሄደዋል ። ደብረ ሊባኖስ ያደረስኳቸው እኔ ነኝ ። አሁን ከአንዲት መነኩሲት ጋር ተዳብለው ነው የሚኖሩት ። ከእርጅናቸው በስተቀር ለጤናቸው ደህና ናቸው ። እማማ በላይነሽም ብቻቸውን መኖር ባለመቻላቸው ከእኔ ጋር መኖር ጀምረዋል ። አልፎ አልፎ ከበቡሽ እየመጣች ትጠይቀናለች ። »

በማለት ስለ ቤተሰቡ ገለጸ ስለ ራሱ ብዙም አላወራም ። « በጣም ደህና ነኝ » የሚል ቃል ከመጨመር በስተቀር ። ከቤተሰቡ ዜና ቀጥሎ ፣

« ሕሊና የደረሰብሽን ችግር ባለፈው ጊዜ ከበቡሽ ነገረችኝ ። በአንቺና በባለቤትሽ መሀከል የተፈጠረውን መለያየት ለምቼ በጣም ነው ያዘንኩት። ልዩነታችሁን አስወግዳችሁ በሠላም አብራችሁ ለመኖር እንደምትበቁ ተስፋ አደርጋለሁ ። ለማንኛውም በዚህ ቀውጢ ቀን አጠገብሽ ሆኜ በሃሳብ ልረዳሽ ባለመቻሌ በጣም አዝናለሁ ። ሆኖም በደብዳቤና በስልክ የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ ። » በማለት የተሰማውን ገለፀ ።

የያሬድ አባባል አዲስ አልሆነባትም ። ሆኖም የማይለወጠው ፀባዩና ደግነቱ በመሀከላቸው ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት አልፎ ለእርሷ እርዳታና ድጋፍ ለመስጠት በመፈለጉ የበለጠ እንድትወደውና እንድታከብረው ጋበዛት ። በፊትም እንደዚሁ ያደርግ ነበር። ህይወቱን ሰውቶ ለእርሷ ደስታና ደህንነት ብዙ ለፍቷል ። ሳላችለት። እርሱን በአካል እንድታይ የሆነ ነገር ጎተጎታት ።

« የሰዎች ሁሉ ፍፁም ነው » ብላ አመነች ። ከአባቷ ቀጥሎ ያላትን አክብሮትና መውደድ ለያሬድ ሠጠች ። ናፍቆቷ ስላየለባት በፀጥታ እንባዋን አነባች ።

« ራሄል ከመታጠቢያ ክፍል ስትወጣ በምታየው ነገር ተደናግጣ ምን ሆነሻል ? ማን ሞተ ? » ስትል ጠየቀች ። ሔሊና በእጇ ይዛ የነበረውን ደብዳቤ ሰጠቻት ። ራሄል የደበዳቤውን መልዕክት ደጋግማ ብታነበውም የሔሊና የለቅሶ ምንጭ ግን ሊታያት አልቻለም ።

« ታዲያ ምን ተፈጠረ ? » አለችና መልሱን ከሔሊና ጠበቀች።

« ምን ብዬ ልግለፅልሽ ? እንዴት አድርጌ . . . » ሔሊና ሀሳቧን ለመግለፅ ከራሷ ጋር ታገለች ።

« ጋሼ ያሬድን ታውቂዋለሽ ? ማለቴ ከዚህ በፊት ነግሬሻለሁ ? . . . » ራሄል አለማወቋን አንገቷን በማወዛወዝ ገለፀችላት ። የሚቀጥለውን አረፍተነገር ለመናገር ጥቂት ካመነታች በኋላ ይኼውልሽ ጋሽ ያሬድን ከማንም በላይ የምወደው ወንድሜ ነው። ብላ ከመነሻው እስከመጨረሻው የነበረውን ታሪክ ነገረቻት ። ታዲያ ይኼውልሽ ፤ « ክብሩን እንደዚያ ዝቅ ከአደረኩ በኋላ አሁንም አልተለወጠም ። ከእኔ አልፎ ተርፎ የምወዳቸውንና የምሳሳላቸውን ሰዎች ህይወት እየተንከባከበ ነው ። ውለታው በጣም ከበደኝ ። አሁን ያለሁበትን ህይወት ሳየው በእርሱ ላይ ያደረኩት ሁሉ ፀፀተኝ ። በእሁኗ ሠዓት አጠገቤ እንዲሆን ተመኘሁ ። ግን ምኞቴ እውን ቢሆን ምን እንደማደርግ አላውቅም » አለች ሔሊና ደብዳቤውን እንደገና ለማንበብ እየሞከረች ።

« እንዲያው በደፈናው ናፈቅሁኝ አትይም » አለች ራሄል ሁኔታውን በማቃለል ።

« መናፈቅ ! . . . መናፈቅ . . . እኔ እንጃ የተሰማኝ ግን ከመናፈቅ በላይ ነው ። ምን ብዬ ልንገርሽ ? » ሔሊና ስሜቷን ለመግለጽ አልቻለችም ቃላት አጠራት በረጅሙ ተንፍሳ ወደ ራሄል ተመለከተች ። ዓይኖቿ ከራሄል እርዳታ ሻቱ ።

* * *

የራሄልና የሔሊና የድበላ ኑሮ ፍጹም ደስታና ፍቅር የተሞላው ቢመስልም አልፎ አልፎ ጥርጣሬ የሚነፍስበት በመሆኑ ሁለቱም የየግል ምስጢራቸውን በማፈን የሀሊና ድንበራቸውን አጠበቡ ። በጓደኝነት የሚካፈሉአቸው ቁምነገሮች በብዛት በጠቅላላ ሁኔታዎች ላይ የሚያተኩሩ ሆኑ ። አብረው ከሚያሳልፉት ጊዜያት ይልቅ በግልና በተናጠል የሚያሳልፉት እያመዘነ መጣ ። ይህ ሁኔታ ሔሊናን እንደ ማዕበል ሳታውቀውና ሳትወድ በግድ ወደማትፈልገው አቅጣጫ እንድታተኩር ገፋፋት ።

ራሄል ውጭ ማደር ከጀመረች ሠነበተች ። ይህ የራሄል ፀባይ አዲስ ባይሆንም በአዳር ማግስት የሚኖራት ፀባይ ፊፅሞ ሊገባት አልቻለም ። ውጪ አድራ በተገናኙ ቁጥር ራሄል ከሔሊና ጋር ከማውራት ትቆጠባለች ። ካወራችም ንግግሯን በአጭር በአጭሩ በማድረግ ራሷን ታገላለች ። ብዙ አብረው በኖሩ ቁጥር ራሄል ድብቅ ተፈጥሮ እንዳላት መረዳት ቻለች ።

በሔሊና ግምገማ ራሄል ድብቅ ብቻ አልነበረችም ። ስልት አዋቂና ውስጣዊ ስሜትዋን በቀላሉ በውጪ ገፅታዋ የምትሸፍን ብልህና ብልጥ ሰው እንደሆነች ተገነዘበች ። ጊዜው እያለፈና እየጨመረ በሄደ ቁጥር ይህ የሔሊና ጥርጣሬ እየጎለበተና ፊር እየያዘ

መጣ ። ስለአዳሯ እና ስለምታወጣቸው ወንዶች ጠረጠረች። ራሄልን ልታውቃት አልቻለችም ። ስለምታወጣቸው ወንዶች አልፎ አልፎ ቆንጠር አድርጋ የምትነግራትን ገጣጥማ ራሄልን ለመተርጎም በፈለገች ቁጥር ፣ . . . ባወቀቻት ቁጥር . . . ውስጧ ይረበሻል ።

ቀኑ ቅዳሜ አመሻሹ ላይ ነበር ። ራሄል ያለወትሮዋ ቤት ውስጥ ዋለች ። ሕሊና በቅዳሜ ምድር ቀኑን አብሯት የሚያሳልፍ ሰው ከብዙ ቅዳሜዎች በኋላ በማግኘቷ ደስታ ተሰምቷት ነበር ። በዚሁ ስሜት ውስጥ ሆና እራት ለማዘጋጀት ምግብ ቤት ጉድ ጉድ በማለት ላይ እንዳለች በመካከል የሆነ የጭንቀት ጥሪ ከመኝታ ክፍል ተሰማት ። ደንግጣ መኝታ ቤት ስትገባ ያየችውን ለማመን ተቸገረች። ራሄል ወለሉ ላይ ተንበርክካ ሽቅብ ከሚላት ሁኔታ ጋር ትንቅንቅ ገጥማለች ።

« ምነው እኔን ! እኔን ! አመመሽ ? » ሕሊና አጠገቧ ተንበርክካ ራሄልን ለማገዝ ሞከረች ።

« አይዞሽ በይው ይውጣልሽ » ያስጨነቃትን እንድታስወግድ ገፋፋቻት ። ከግማሽ ሰዓት የግቢ ነፍስ ውጪ ነፍስ ትግል በኋላ የራሄል ነፍስ ተመለሰ ። በሕሊና እገዛ ከተንበረከከችበት ወለል ተነስታ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባች ። ሕሊና ወለሉ ላይ የተዝረከረከውን ቆሻሻ ጠራርጋ መስኮቱን ከፍታ ቤቱን አናፈሰች። ሕሊና የቅያሪ ልብስ ለማዘጋጀት ወደ ራሄል ክፍል ገብታ የራሄልን ቁምሳጥን ከፈተች መሳቢያ ውስጥ ያየችው ነገር ትኩረቷን ሳበው ።

ምንም እንኳ አንድ ቤት በደባልነት ቢኖሩም ሕሊና የራሄልን የግል ዕቃዎች ነክታ አታውቅም ነበር ። ለመጀመሪያ ጊዜ የራሄልን ሳጥን ከፍታ ስትመለከት መሳቢያው ውስጥ ማስታወሻ ደብተር ፣ ጌጣጌጦች ፣ የውስጥ ልብስና ቀበቶዎች እንዲሁም መስፍንና ራሄል በግልና በጋራ የተነሷቸው ፎቶግራፎች ነበሩ ። ከቀበቶዎቹ አንደኛ ውን አንስታ አገላብጣ ተመለከተች ። የመጀመሪያ ደመወዝዋን

እንደተቀበለች ለመስፍን ማስታወሻ የገዛችው ስጦታ ነበር። ከረባቶቹንም ለመለየት ጊዜ አልፈጀባትም ። የቀድሞ ባሏ የመስፍን የግል ዕቃዎች በራሄል ምስጢራዊ ሳጥን ውስጥ እንዴት ሊገቡ እንደቻሉ ማወቅ አልቻለችም ። ሁለተኛውን መሳቢያ ከፈተች። የውስጥ ሱሪ ! አገላብጣ ተመለከተችው ። ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ ። ስሜቷ ተረበሸ ። ያየችውን ላለመቀበል ፣ ከሀሳቧ ጋር ለመቃረን ሞከረች ። በእጇ የያዘችውን ቀይ የውስጥ ሱሪ በጥላቻ ወደአልጋው በኃይል ወርውራ ከመኝታ ቤቱ ተንደርድራ ወጣች ።

ሕሊና በውስጧ የነደደውን ስሜቷን ሳታረጋጋ የራሄልን የስቃይ ድምጽ ስትሰማ ክፍሉን ለቃ ወጣች ። ብቻዋን ሆና ራሷን ለማረጋጋት ቀጥታ ወደ ኩሽና ገባች ። ሕሊና ዓይኗን ሞልታ ራሄልን ለማየት አልፈለገችም ። ለመስራት ያሰበችውን መቀጠል አልቻለችም ። ክስተቱ የምታደርገውን ሁሉ አጨልሞ አመሰካከቷን አዛባው ። ህይወቷን አማረረች ። የቀረበቻቸውን ሰዎች ሁሉ ልታምናቸውና ልትወዳቸው መቻሏን ጠረጠረች ። ግን አልገፋችበትም ።

« ለጨለማ ብርሃን ፣ ለክፉም ደግ አለ ። » ሀሳቧን አሻግራ ወደ አገር ቤት ወረወረች ። ያሬድን አስታወሰች ። አንድም ቀን መጥፎ ሰው ሆኖባት አያውቅም ። እራስዋን አፅናናች ። በያሬድ ውስጥ ደግ ሰዎችን ፈለገች ። እማማ በላይነሽን ፣ ከበቡሽን . . . በሀገር ቤት ለደስታዋና ለተስፋዋ ምክንያት የሆኑ ሰዎችን አስታወሰች። እንደገና ብሩህ ተስፋ ፤ እንደገና አዲስ ህይወት . . . በህይወት ከኖሩ መልካም ነገር አለ . . . ።

ሕሊና እራሷን ገዝታ ምንም እንዳልተፈጠረ እንደቀድሞዋ ወደ ራሄል ተመለሰች ። ራሄልን አረጋግታ ደግፋ መኝታ ቤቷ አስገብታ አስተኛቻት ።

ራሄል ጀርባዋን ለሕሊና ሰጥታ እንቅልፍ እንዲወስዳት በማሰብ ዓይኖቿን ከደነቻቸው ። ሕሊና ለአፍታ በትዝብት ተመልከታት አንገቷን ሰብራ ክፍሉን ለቃ ወጣች ።

*   *   *

ራሄል የምግብ ፍላጎቷ ቀንሷል ። ሕሊና ያቀረበችላትን ምግብ አፏ ላይ እየተንቀዋለለ መዋጥ ስለአቃታት እንደነገሩ ቀማምሳ ምንም ሳይነካ መልሳዋለች ። ከታመመች አንስቶ የምትበላው ምግብ አይስማማትም በተደጋጋሚ ያስመልሳታል ።

« አንቺ ልጅ ምን ሆነሻል ? ድካም ፣ ማስመለስና የምግብ ሽታ ማስጠላት ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ ? » አለች ሕሊና መብላቱን አቁማ ወደ ራሄል ሙሉ በሙሉ እየተመለከተች ።

« እንደገባኝ የፀነስሽ ይመስለኛል » ስትል አከለች ሕሊና ። ራሄል የሕሊና አመለካከት እንደ ጦር ሲወጋት አንገቷን ሰብራ ራሷን በአዎንታ አነቃነቀች ።

« ለመሆኑ ስንት ወሩ ነው ? » ሕሊና ጠየቀች ። ራሄል አራቱን የቀኝ ጣቶችዋን በማውጣት አራት ወር እንደሆነው አስረዳች። ሕሊና ጥቂት አሰበች ። ከመስፍን ቤት ከወጣች አራት ወራት አለፉ ። ፈራች ።

« ይቅርታ አድርጊልኝና . . . ግን ራሄል . . . ከማን እንዳረገዝሽ . . . » አቋረጠች ።

ራሄል ሀሳቧ ቢገባትም ለማደናገር ሞከረች ። ከተቀመጠችበት ተነስታ መኝታ ክፍሏ ገብታ በሩን ጠረቀመች ። ሕሊና ፈራች ። ፍራቻዋ ለራሷ ብቻ አልነበረም ።

ራሄል በፈፀመችው ድርጊት ተፀፅታ በራሷ ላይ ወይም በፅንሱ ላይ ጉዳት እንዳታደርስ ነበር ። ያለወትሮዋ ተከተለቻት ።

የመኝታ በሩን አንኳኳች ። መልስ አልነበረም ። ቢለለቻት ራሷ በሩን ከፍታ ወደ ውስጥ ዘለቀች ። ራሄል አልጋዋ ላይ በደረቷ ተደፍታ ታለቅስ ነበር ። ሕሊና አልጋው ጠርዝ ላይ አረፍ ብላ ራሄልን ከአንገቷ ቀና አድርጋ ፣ ጭኗ ላይ አሳርፋ ፣ ፀጉሯን እያሻሸች ልታረጋጋት ሞከረች ። ለቅሶውና ማባበሉ ለጥቂት ጊዜ ቀጠለ ።

ከቆይታ በኋላ ራሄል በኃይል ተንፍሳ « በመሀከላችን ሌላ ሽማግሌ ሳያስፈልግ የዘላለም ጭንቀቴን ልነግርሽ ብዙ ጊዜ ሞከሬ አቃተኝ » አለቻት ፣ ፀጉሯን እያሻሸች እንደእናት ወደምታባብላት ሕሊና እየተመለከተች ።

« ሽማግሌ ሀገራችን ቀረ . . . » አለች ሕሊና የሆነ ነገር እየተናነቃት ።

ራሄል ራሷን እያጠናከረች ፣ እንባዋን በእጆችዋ እያደራረቀች ከሕሊና ጭን ተነስታ ፊቷን ከሕሊና አዙራ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች ።

« . . . የምነግርሽን ሳልጨርስ እንዳታቋርጪኝ ። መቼም የምነግርሽ እንደሚያስገርምሽና እንደሚያስቆጣሽ አውቃለሁ ። ብትቆጪም አልፈርድብሽም ። ሕሊና በጣም የምወድሽና የማከብርሽ ጓደኛዬ ነሽ ። ስለዚህም ነው ዛሬ ይህን ታላቅ ምስጢር የምገልፅልሽ . . . » ሁለቱም ባሉበት በዝምታ ለጥቂት ጊዜያት ቆዩ ።

« ለምን እንዲህ ሆነ ? ለምን ዛሬ ገለፅሽው ብለሽ ብትጠይቂኝ መልሱን አላውቅም ። ሕሊና ! እኔና አንቺ በህይወታችን አንድ ሰው ተካፍለናል . . . » ራሄል መናገሩን አልቀጠለችም ። ካለችበት ተነስታ ወደ መስኮቱ ተጠጋች ። የተዘጋውን መስኮት ከፍታ ወደ ውጪ ተመለከተች ። በመስኮቱ በኩል የሚገባውን አየር በኃይል እየተነፈሰች ካለችበት የምድሩን ርቀት ገመተች ።

« ያደረግኩት ትክክል እንዳልሆነ አውቃለሁ ። ነገር ግን ከቁጥጥሬ በላይ ነው ። ስለበደልኩሽ ትልቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ከዚህ በኋላ የእኔ መኖር ትርጉም የለውም ። አንቺ የዋህና ደግ ሰው በመሆንሽ እግዜር ከክፉ ነገር ይጠብቅሻል ። » ራሄል ንግግሯን በሳል ጨረሰች ። ሒሊና የሆነ ነገር ጠረጠረች ።

« ምን ነካሽ ? » በማለት ካለችበት ዘላ የራሄልን ቀሚስና እጅ ይዛ ታገለች ።

« ሒሊና እባክሽን ተይኝ ። አይ ዱ ኖት ዲዘርቭ ቱ ሊቭ » በማለት ግማሽ ሰውነቷን በመስኮቱ በኩል አውጥታ ስትታገል ሒሊና ሃይሏን ጨምራ ስትጎትታት ተያይዘው ወለሉ ላይ ወደቁ ።

« ለማን ብለሽ ነው ህይወትሽን የምታጠፊው ? ለእኔ እህቴ ነሽ ። በርግጥ ስለተፈጸመው ሁኔታ ባዝንም ጉዳትሽን አልሻም ። » ራሄል ባለችበት እንደ ህፃን ልጅ እየተወራጨች ፣ ፀጉሯን እየነጨች « እኔ ወራዳ ነኝ ፤ እኔ ልክስክስ ነኝ ፤ መኖር አይገባኝም ! » አለች።

ሒሊና የራሄልን ትከሻ በሁለት እጆቿ ግጥም አድርጋ ይዛ እየወዘወዘቻት « ራሄል ከጥፋትሽ ለማምለጥ ሞትን ምርጫሽ ማድረግ የዋህነት ወይም አላዋቂነት ነው ። ከበደልሽ ለመንፃት የግድ ወደ ሞት ጎዳና ሽሽት ገብተሽ መሆን አለበት ? ሞት ምንድን ነው ? ተስፋ ሲቆርጡ ፣ እንዲህ እንደ አንቺ በጸጸት አለንጋ ሲገረፉ እንዲሁም የተለያዩ ፈተናዎችን መጋፈጥ ሲያቅት የሞት ጨዋታ መጫወት ። ይሄ ማለት ምንድን ነው ? በሞት ድል ላይገኝ ከሞት ጋር ግብግብ በመግጠም ማሸነፍ አይገኝ ። አሊያም አንቺ ህይወትሽን ስለሰዋሽ ከበደል አይነፃም . . . ይልቅስ በህይወት ኖረሽ ካለፈው ስህተትሽ ተምረሽ ሰው ለመሆን መጣር ይሻላል ። መኖር በራሱ ብዙ ያስተምራል በሞትሽ በሽንፈት ላይ ሽንፈትን ደርበሽ ቁልቁል ወደ መቃብርሽ ተምዘግዝገሽ ስትወርጂ ዝም ብዬ አላይሽም » አለቻት ትንፋሿን በረጅሙ ለቃ ።

« ያልሽውን ብትይ እኔ እወድሻለሁ ። በአንቺና በመስፍን መካከል የነበረውን ግንኙነት ማለቴ ጓደኛሞች እንደነበራችሁ እስከነገርሽኝ ሠዓት በሁለታችሁ መካከል የማያቸውና የምሰማቸው ነገሮች እንዲሁም መስፍን ላንቺ ያለው አመለካከት ጥሩ ይሁን መጥፎ . . . ብቻ. . ብቻ ሁሉም ነገር ግራ ያጋባኝ ነበር አለቻት እጆቿን እያወናጨፈች ።

እየሽ ራሄል ባለማወቅ በሁለታችሁ መሀል ተሰንቅሬ በመግባቴና ህይወትሽን በመበጥበጤ በጣም አዝናለሁ ። በርግጥ ያደረግሽው ባህላችን የማይቀበለውና የሚያወግዘው ድርጊት ቢሆንም በእኔ በኩል እውነተኛና ፍላጎትሽን የሚገልፅ ነው ። » ለማረጋጋት እና ለማፅናናት ለፈለፈች ። ሁኔታው መቀዝቀዝ እንደጀመረ ሒሊና ራሄልን ከመሬት አስነስታ አልጋ ላይ እንድትቀመጥ አደረገች ።

« ራሄል ቀደምሽኝ እንጂ እኔ ነበርኩ ይቅርታ መጠየቅ የነበረብኝ ። ባለማወቅ ህይወትሽን መጥፎ ሁኔታ ላይ ጥየብሻለሁ ። እየሽ የእኔና የመስፍን ትውውቅ እንዴት እንደተጀመረ ፣ በምን እንዳለቀ ለአንቺ እንግዳ አይደለም ። ከመጀሪያውም መስፍንና እኔ ስለ ህይወት ያለን አመለካከት የተለያየ ነው ። ሁኔታዎች ገፋፍተው ለጋብቻ አበቁኝ እንጂ ትዳራችን በፍቅርና በሙሉ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አልነበረም ። . . . ከመስፍን ጋር ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ አንቆቅልሽ ለነበረው ግንኙነቴ ተጨባጭ ፍች በማግኘቴ በጣም ደስታ ይሰማኛል . . . »

ሒሊና ፊቷን ከራሄል አዙራ ወደ መስኮቱ ተመለከተች ። አንዳች ቅዝቃዜ እንደገባው ሰውነቷን እንቀጠቀጣት ።

« ዛሬ የሞከርሽውን ብትፈፅሚ ኖሮ እስከ ህይወቴ መጨረሻ ፀፀት ላይ ጥለሽኝ ነበር » አለች እየዘገነናት ።

« እ . . እኔ በዚህ መልኩ አገኝሻለሁ ብዬ አልጠበኩም ነበር . . . » አለች ራሄል ዓይኖቿ ዳግም በፀፀት ዕንባ እየተሞሉ . . . . ::

*　　*　　*

ሕሊና ሆድ ብሷት ነበር :: ተነስታ አልጋዋ ላይ ጋደም አለች:: እንደድንገት እጇን ስትዘረጋ ኮሜዲኖዋ ላይ አረፈ :: የሆነ ፖስታ ይዞ ተመለሰ :: በቅርቡ ከአገር ቤት የደረሳት ነበር :: ሕሊና ማንበብ ጀመረች ::

« . . .የአባትሽ መጥረቢያ አንድ ነገር ቢሆን በማለት እማማ በላይነሽ አደራ ብለው አስረከበውኛል ::መጥረቢያውን ባየሁ ቁጥር ትዝታሽ ይቀሰቀስብኛል :: ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝና ያልኩትን ከመናገር ለመቆጠብ አልቻልኩም :: ያለ አንቺ የእኔ ህይወት ሙሉ ሊሆን አልቻለም :: በቅን መንፈስና በጥሩ ስሜት ለአንቺ ያለኝን ስሜት ፣ ለአንቺ ያለኝን ፍቅር ለማደብዘዝና ለመርሳት በፅኑ ሞክርኩ :: ሆኖም ሙከራዬ ውጤት አልባ ሆነ :: . . . ሕሊና መጥረቢያሽን በማግኘቴ ባለሁበት በትዝታሽ ለመፅናናት ረድቶኛል:: . . . አንቺም ባለሽበት ፣ እኔም ባለሁበት ሀሳባችንን ለማረጋጋት እግዚአብሄር ይርዳን :: . . . »

« ያሬድ ከዚህ ሁሉ በኋላ እንኳ ሊረሳኝ አልቻለም » አለች እንባዋን እየጠራረገች :: ደብዳቤውን አንብባ የጨረሰችው በለቅሶ ነበር፣ የደስታና የሀዘን ድብልቅ የሆነ ለቅሶ :: ያሬድ ለእርሷ መቼም ቀን ክፋዋ ሆኖ አያውቅም :: በእርግጥም ገንዘቡን ፣ ጊዜውን ብቻ ሳይሆን ህይወቱንም ሰውቶላት ኖሯል :: ባንነች :: እንደበደለችው ፣ ግፍ እንደዋለችበት . . . ዘልቆ ተሰማት እና በሀሳብ አገር ቤት ዘለቀች:: አድባሯ ተቀበለቻት :: . . . ያሬድ የፅጌረዳ አበባ ይሟል ::

- ተፈፀመ -